Volume IV (2020 – 2022)

# Blog Posts

*To all adarashians*

Akiye's Weblog
adarash.net

# የ ዓርዕስት ሰንጠረዥ

ኢ-ፍትሕዓዊዕነት እና ሚዛንዓዊዕነት ........ 1
ማሊንገሪንግ – ማሊንገረር ........ 4
ሃገርን እና ሕዝብን የማዳን ጥሪ! ........ 7
ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ ........ 10
የ "ኮቭ" ጦርዕነት ........ 19
የህይወት ነፀብራቅ ........ 29
ብሶበታል ........ 34
መስኮተ ሰቆቃ ........ 38
ቢለዋወጥ፤ ጉልቻ! ........ 45
በ-እሳት ጨዋታ! ........ 51
ፍትህ–አጐናጻፊ ሃይል ........ 59
ጦርዕነት ........ 66
የ ፍትህ ያለህ! ........ 73
ከድጡ ወደ ማጡ! ........ 77
ምርጫ....... ለምኔ?! ........ 81
መሬት ላይ ቆመን — እንነሳ! ........ 85
የትዉልድ አደራ አለብን! ........ 90
የ ናርሲሲዝም ዩኒቨርስ ........ 94
በ ዕንቅርት ላይ ጆሮ-ደግፍ ........ 102
አጣብቂኝ ውስጥ የገባች ሃገር ........ 104
ዕንቁ....ጣጣሽ! ........ 108
ጦርዕነት እና ሞራልቲ ........ 112
ኢትዮጵያን አደራ! ........ 117
የ ብዕር-ስም፣ አርማ እና አከአሄድአችን ........ 121
እንድይከስሙ ይገደዱ ........ 126
እንድይበቃው ሊገደድ የግድ ነው! ........ 131
የ ትዉልድዐችን ፍፁምዓዊ አደራ ........ 136
የ ቃልዐት አበሣ ........ 141
አመርቃዥ አሸባሪ ኀሠኛዕነት ........ 147
የ ግፍ ሰንሰለትዑ ይበጣጠስ ........ 152
የ ዐማራ ጀኖሳይድ – ይቁም! ........ 157

የ ጋራ ሃገር – የ ጋራ ትግል ........................................................................................................................ 162
ርዕሰ ዐዉደ-ዓመት.......................................................................................................................................... 167
ጥንድዕነት ................................................................................................................................................... 172
የ ጥፋት ፍኖተ-ካርታ ..................................................................................................................................... 177
ዕምዐይዐብዐራ ሰቆቃ ....................................................................................................................................... 182

# ኢ-ፍትሕዓዊዕነት እና ሚዛንዓዊዕነት

ጥር ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ‖ ጄንዌሪ 2020

*ኢ-ፍትሕዓዊዕነት በአጭሩ፤ [ስህተተኛዕነት] ወይም [ትክክል-የአለመሆን] እንደ ማለት ነው። ሚዛንዓዊዕነት ደሞ – የ[ፍትሕዓዊዕነት] መገለጫ ዕምቅ እስትንፋስ ነው። በማህበረሰብዓዊ ህይወትአችን ውስጥ የእሚከሰቱ ማንአቸውም ዓይነት ዕንከኖችን፤ [ጎሠኛዕነትን ጨምሮ ማለቴ ነው] እንዳይከሰቱ የእሚከላከል፤ አልያም ከተከሰቱ በኋላም ቢሆን በፍጥነት እንዲወገዱ ለማድረግ የእሚአግዝ ፍቱን መድሃኒት ነው — ሚዛንዓዊዕነት! ኢትዮጵያ ውስጥ፤ [ኢ-ፍትሕዓዊውዕነት] የተጠናወተው እና [ሚዛንዓዊዕነት የጎደለው] የገዥው-ግንባር፤ ውሁድ ፓርቲ ሆኜአለሁ ብሏል። [ተደማሪ] የገዥው-ግንባር እህት እና አጋር የ[ጎሣ ድርጅቶችን] አክስሟል የሚባለው — ትልቅ ስህተት ነው። የ“ከሰመ” እህት/አጋር ድርጅት ከአለም፤ አኩራፊውን እንዲሁም የ* <u>ሰሞነኛውን</u> *ጎሣ ድርጅት አይመለከትም ባይ ነኝ። ያ-ም የፖለቲካውን ምህዳር አንገጫግጮታል ብዬ አስብ አለሁ። ይህ በእንዲህ እንደ አለ እና በመላ ሃገሪቱ ውስጥ ሰላም እና መረጋጋት በጠፋበት ሞመንት፤ ሃገርዓዊ ምርጫ ለማድረግ የእሚያስችል ቁመና ላይ ነን ማለት፤ ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ኢ-ፍትሕዓዊዕንት የተጠናወተው እና ሚዛንዓዊዕነት የጎደለው — የተንሸዋረረ አመለካከት ነው። ሃገርን እና ሕዝብን አጥፊ የሆነ ዕኩይ አቋም!*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፤ እንዴት ናችሁ?!

እግረ-መንገዴን፤ ዘመን በፈረንጅኛ ጭምር ለ የ እምትቆጥሩ ወገኖቼ፤ መልካም አዲስ ዓመት እላለሁ — ከልቤ! ያ-ም እንግዲህ፤ የ እምታነቧትን ብሎግ፡ ለ 2020 የመጀመሪያዬ ያደርጋታል። አዲሱን ዓመት ስለ [ኢ-ፍትሕዓዊዕነት] እና ስለ [ሚዛንዓዊዕነት] በመደስኮር መጀመሬን፤ እንደ እምትወዱልኝም ዕምነቴ ፅኑ ነው።

እናም፤ አብረን እንድንቆይ — የምንግዜም ግብዣዬ ነው!

*አዎ፤ ሚዛንዓዊዕነት – ዕውነታን፣ ግብረ-ገብዕነትን፣ ሰውዓዊዕነትን፣ ሃቀኛዕነትን፣ ተአማኝዕነትን፣ ቀናዕነትን፣ በጎ-አሳቢዕነትን፣ ዕኩልዕነትን፣ ቻይዕነትን፣ ግልፅዕነትን፣ ቀጥተኛዕነትን፣ የኅሊና ጤነኛዕነትን እና የመሳሰሉትን በጎ መለኮትዓዊ ባህሪያት የተጎናፀፈ፤ የ ማህበረሰብዓዊ እንከኖቻችን ሁሉ ፈውስ የሆነ — የ[ፍትሕዓዊዕነት] መገለጫ ዕምቅ እስትንፋስ ነው። በ ማህበረሰብዓዊ ህይወትአችን ውስጥ የ እሚከሰቱ ማንአቸውም ዓይነት ዕንከኖችን፤ እንዳይከሰቱ የ እሚከላከል፤ አልያም ከተከሰቱ በኋላም ቢሆን በፍጥነት እንዲወገዱ ለ ማድረግ የ እሚአግዝ ፍቱን መድሃኒት ነው — ሚዛንዓዊዕነት! ሃገርን እና ህዝብን የሚጎዳ — ማህበረሰብአዊ ትርምስምስ ሲያጋጥምም፤ በዋናዕነት እና በቅድሚያ ልናነግበው የሚገባን መሣሪያአችንም፤ [ሚዛንዓዊዕነት]ን ነው። ሚዛንዓዊዕነት፤ ኢ-ፍትሕዓዊዕነትን እናሸንፍ ዘንድ ይረዳናል። ሚዛንዓዊዕነት፤ ኢ-ፍትሕዓዊዕነትን አሸንፈን፡ ቫሊድ የሆነ መረጃን ሰንቀን፡ ዕውነታን ጨብጠን፤ ማህበረሰብአዊ ህይወታችን አድልዖ የሌለበት እና ፍትሕዓዊ የሆነ ማህበረሰብዓዊ ህይወትን እንድናጣጥም ይረዳናል።*

አዎ፤ ኢ-ፍትሕዓዊዕነት [ስህተተኛዕነት] ወይም [ትክክል-የአለመሆን] እንደ ማለት ነው። የኢ-ፍትሕዓዊዕነት መገለጫም፤ አድልዖዓዊዕነት ነው። ዕድሜ፣ ፆታ፣ የቆዳ ቀለም፣ ጎሣ፣ ጎጥ፣ ቋንቋ፣ የአቋም ልዩዕነቶች እና የእሚመሳሰሉትን ሁሉ ሰበብ በማድረግ። ኢ-ፍትሕዓዊዕነት በግለሰብእም ሆነ ሰፋ በአለ የማህበረሰብዓዊ ህይወት ውስጥ ይንፀባረቃል። በማህበረሰብዓዊ ህይወትአችን ውስጥ የእሚከሰቱ ማንአቸውም ዓይነት ዕንከኖች፤ የ ኢ-ፍትሕዓዊዕነት፣ የ ስህተተኛዕነት እና የ ትክክል-የአለመሆን ውጤቶች ናቸው። በማህበረሰብዓዊ ህይወት ውስጥ፤ ህይወት ለ አላቸውም ሆነ ህይወት ለ የሌላቸው ፍጥረታት፤ እንዲሁም በ-እየ አንድ-አንዷ ቅጽበት ውስጥ ከየእሚከሰቱ ሁነቶች ጋር፤ አንፃርዓዊም ሆነ ቀጥተኛ በሆነ መልኩ የሚዛመድ [ዕውነታ] አለ። የ-እኛ ሃላፊዕነት እና ግዴታም፤ [ዕውነታን] ፈልጎ ማግኘት ነው። የ-እኛ ሃላፊዕነት እና ግዴታም፤ የግለሰብ ህይወትንም ሆነ፤ ማህበረሰብዓዊ ህይወትን፤ በ[ዕውነት] መምራታችንን እርግጠኞች መሆን ነው። ኢ-ፍትሕዓዊዕነትን ለማረቅ።

ጎበዝ፤ አንድ ማንአችንም ልንክደው የማንችል ዕውነታ አለ። ሰው፤ የትየለሌዕነትን በተጎናፀፈው ዩኒቨርስ ውስጥ፤ በፕላኔት ምድር ላይ ሰፍረው ከ የእሚገኙት፤ ህይወት ከ አላቸው ፍጡራን መካከል አንዱ ነው። ያ-ም ማለት፤ ዩኒቨርስም ሆነ ፕላኔት ምድር፤ የ[ሰው] የግል ንብረት አይደሉም ማለት ነው። የሃገር [ሃገራት] ሸንሸና እና ይገባኛል ባይዕነትም፤ የ አለማወቅ እና የ[ሰው] ልጅ [ድክመት] ብሎም፤ የ[ኢ-ፍትሕዓዊዕነት] የ[ስህተተኛዕነት] እና የ[ትክክል-የአለመሆን] ውጤት ነው።

ዛሬ-ዛሬ [ሰው] ድክመቱን፣ ኢ-ፍትሕዓዊዕነቱን፣ ስህተተኛዕነቱን፣ ትክክል-የአለመሆኑን፤ ለማረቅ እየሞከረ ነው — ኢንቴንሽናል ሆነም አልሆነ። ለምሳሌ፤ የዘመንአችንን የምጣኔሃብት ቁመና ብታዩ፤ [“ሃገር”] ለ የ እሚለው ፅንሰሃሳብ ተገዥ እንደ አይደለ እንደ እምትገነዘቡ ዕገምት አለሁ። አዎ፤ የዘመንአችን የምጣኔሃብት ቁመና፤ ዓለምአቀፍዓዊ ነው። ድንበር-የለሽ ነው። ከጥቂት አስርተ ዓመታት በኋላም የሚኖረው የ ምጣኔሃብት ቁመና [“ሃገር”] የ እሚለውን ፅንሰሃሳብ፤ [ታሪክ] እንደ የ እሚያደርገው ዕምን አለሁ። የ ዘመንአችን ማህበረሰብዓዊ ህይወት አስተዳደር [ፖለቲካ] ቁመና፤ መቸ ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንደ እሚደርስ መገመቱ ከባድ ቢሆንም ቅሉ፤ [“ሃገር”] ወይም የ [“ሃገር ድንበር”] ብሎም፤ [“መንግሥት”] የ እሚሉት ፅንሰሃሳቦችም፤ አንድ-ቀን [ታሪክ] ሆነው እንደ የእሚቀሩ ዕገምት አለሁ። ፍትሕዓዊዕነት [ዩኒቨርሳሊ] ዕውን የሚሆነውም ያ-ኔ ነው ብዬ ዕምን አለሁ።

የሆነ ሆኖ፤

ይህ የእኛው የፈረደበት ትውልድ፤ [ሃገር፣ የሃገር ድንበር፣ መንግሥት] የሚሉት ፅንሰሃሳቦች [ታሪክ] ሆነው ለማየት ተፈጥሮው ስለሚገድበው [ላይፍ ኤክስፔክታንሲን በተመለከተ ማለቴ ነው]፤ በማህበረሰብዓዊ ህይወትአችን ውስጥ ለየእሚከሰቱ ማንአቸውም ዓይነት ዕንከኖች ተገቢውን ፈውስ አግኝተን፤ ምሉዕ ሰውዓዊ ህይወትን የመምራት አቅም ለመፍጠር እንችል ዘንድ፤ [ኢ-ፍትሕዓዊዕነት]ን ፕሮአክቲቭሊ በመታገል ፍትሕዓዊ ማህበረሰባአዊ ህይወት መምራት መቻላችንን እርግጠኞች መሆን ይጠበቅብን አለ። ያ-ንን ማድረግ የእምንችለውም፤ [ሚዛንዓዊዕነትን] መሣሪያአችን አድረገን ለመጠቀም ቆርጠን የተነሳን ቀን እና [ሚዛንዓዊዕነትን] መሣሪያአችን አድረገን ቆርጠን የተነሳን ቀን ብቻ ነው።

ከፍ ብዬ እንደ አነሳሁት፤ የ[ሰው] ልጅ በፕላኔት ምድር ላይ መኖር በጀመረባት ሞመንት፤ "ሃገር" የሚባል ነገር አልነበረም። ማሕበረሰብዓዊ ህይወት እየ አደገ እና ውስብስብ እየሆነ ሲመጣ፤ ከተፈጠሩት የማህበረሰብዓዊ ህይወት መገለጫዎች መካከል — "ሃገር" አንዱ እና የመጀመሪያው በመሆን ተከስቷል ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያ የሚለው ስም፤ ከ አንደኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ጀምሮ፤ "ሃገር" እና "መንግሥት" ከሚሉ ፅንሰሃሳቦች ጋር ተያይዞ በታሪክ ማህደራት ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። እናም፤ ኢትዮጵያዊያን ወይም ኢትዮጵያዊ ዜጋዎች ናቸው ሲባል፤ [እንደ እየ ጊዜው እና ነባርዓዊ ሁኔታዎች፤ ይስፋም ይጥበብም] ኢትዮጵያ በየእምትባል "ሃገር" እና ኢትዮጵያዊ ነኝ በየእሚል "መንግሥት" ዕቅፍ ውስጥ የአሉ፤ በተፈጥሮ የጎሣ አትሪቢውትስ ሕብር የተሳሰሩ ሰዎች ናቸው ማለት ነው። የኢትዮጵያዊያን ወይም የኢትዮጵያ ዜጋዎች፤ ውስብስብ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት የወል መገለጫ ማንዕነትም — ኢትዮጵያዊዕነት ነው። ያ-ም [ዕውነት] ነው! ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊዕነት ሊካድ የማይቻል — በተጨባጭ ሆኖ እየታየ የአለ፤ አንድም-ሁለትም የሆነ መለኮትዓዊ ዕውነታ ነው። ይህንን ዕውነታ በመካድ፤ ኢትዮጵያን በመካድ — ኢትዮጵያዊ አይደለንም በሚል የሚበጠብጡ [ጥቂት አወቅን ባዮች]፤ ሚዛንዓዊዕነት፣ [ዕውነታ፣ ግብረ-ገብዕነት፣ ሰውዓዊዕነት፣ ሃቀኛዕነት፣ ተአማኝዕነት፣ ወናዕነት፣ በጎ-አሳቢዕነት፣ ዕኩልዕነት፣ ቻይዕነት፣ ግልፅዕነት፣ ቀጥተኛዕነት፣ የኀሊና ጤነኛዕነት] እና የመሳሰሉት በጎ መለኮትዓዊ ባህሪያት የጎደላቸው ዕኩይ ፍጡራን ናቸው።

አናም፤

ዛሬ-ዛሬ፤ በጎሠኛዕነት ሳቢያ የተከሰቱ ችግሮችአችንን ለማቃለል፤ ብዙም መዳከር እንደ አይኖርብንም ለማድረግ ይቻለን ዘንድ — መሠረታዊ ምክንያቱ፤ መሠረታዊ ምንጩ ኢ-ፍትሕዓዊዕነት መሆኑን ዐምነን በመቀበል፤ [ሚዛንዓዊዕነት]ን "ጦር እና ጋሻ"አችን አድርገን በቆራጥዕነት ልንታገለው ልናስወግደው መነሳት ይኖርብናል። በሁሉም የማህበረሰብዓዊ ህይወታችን ዕርከኖች – ማለቴ፤ በ-እየ ቤተ-መንግስቱ፣ በ-እየ መሥሪያ ቤቱ፣ በ-እየ ትምህርት ቤቱ፣ በ-እየ ቤተ-ዕምነቱ በ-እየ ቤተሰቡ እና ግለሰቡ ቤት ሁሉ፤ [ሚዛንዓዊዕነት] ተገቢውን ትኩረት እና ክብር እንዲሠጠው አበክረን እና ጠንክረን መስራት ይኖርብናል። አዎ፤ የ ኢትዮጵያዊዕነትን መርሕ አንድ-ሁለት የሞራል ልዕልዕና አቅጥ ከፍ ማድረግ የሚጀምረው — በዋናዕነት [ሚዛንዓዊዕነት]ን መሣሪያአችን በማድረግ ነው ብዬ ዐምን አለሁ።

ጎበዝ፤ ሃሣቤን ከመቋጨቴ በፊት፡ አንድ ጉዳይ እንድጨምር ፍቀዱልኝ።

አዎ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬም ሃገርን እና ሕዝብን ጎጂ የሆነ፤ [ኢ-ፍትሕዓዊእነት] የተጠናወተው እና [ሚዛንዓዊዕነት] የጎደለው መሠሪ ስራ እየተሰራ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕትዕነት ከፍሎ ያመጣውን የድል-ጎሕ አጨልሞ፤ የእራሱን ዕድሜ ለማርዘም ሲል ብቻ፤ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን አጥፊ የሆነ ዕኩይ ስራ እየሰራ ነው — ውሁድ ሆኜአለሁ ባዩ፤ ገዥው-ግንባር። በፍፁም ሊዘነጋ የማይገባ ጉዳይ እኮ ነው። ገዥው-ግንባር፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባርዓዊ እየሆነ የአለውን [ኤትኒክ ክሊንዚንግ] የፈጠረ፤ አክራሪ የ[ጎሣ ፖለቲካ]ን እና [ጎሠኛዕነት]ን የአራገበ — ተግባሪም፣ አጎልባችም፣ አቀንቃኝም የሆነ፤ በየጎሣ ፖለቲካ የተበከለ የመሠሪ ፖለቲከኞች ስብስብ ነው። ውሁድ ሆነ አልሆነ ያንን የ[ጎሠኛዕነት] አቋሙን የሚለውጠው አንድአችም ተዐምር የለም።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ የገዥው-ግንባር ውሁድዕነት — ሰሞነኛውን የ[ጎሣ ድርጅት] በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በፋሽስትዓዊዕነት ለመጫን እንዲረዳአቸው በሚል የታለመ የዕኩይ ፖለቲከኞች ውጤት ነው። አዎ፤ ሚዛንዓዊዕነት የራቃቸው ሰዎች፤ ሰሞነኛውን ጎሣ – በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፤ በአፍሪቃም ትልቁ ጎሣ እንደሆነ ተደርጎ እንዲቆጠር ለማድረግ በተደጋጋሚ [ሲዳከሩ] ሰምታችኋል። የሚገርመው ነገር — ትልቁ ጎሣ ነው በማለትም አያቆሙም። ያለ-ሃፍረት፤ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን፤ የምሥራቅ አፍሪቃ ቀጠና የሚሉትን እና አፍሪቃን በአጠቃላይ መግዛት የሚችል ጎሣ ነው እየሉ ሲንበዛበዙም ሰምታችኋል። እንዲህ ዓይነት ዕብደት፤ በሃያ-አንደኛው መቶ ክፍለዘመን መስማት እጅጉን - አዎ፤ እጅጉን ያሳፍራል። እግረ-መንገዴን አንድ ነገር ልበል። እኔ የፓን-አፍሪቃን እንቅስቃሴን እደግፍ አለሁ። ሆኖም ግን፤ ይሄ ለምሥራቅ አፍርቃም ሆነ ለመላው አፍሪቃ አሳቢ በመምሰል፤ አልፎ አልፎ የእሚራገበው የጥምረት የምናምን ዝባዝንኬ፤ የጤና ሳይሆን — የኢትዮጵያን ስም እና የኢትዮጵያዊዕነትን ደብዛ ለማጥፋት የታለመ ዕኩይ ፖለቲካ መሆኑን፤ ልብ እንድትሉ አሳስብ አለሁ። ለምሥራቅ አፍሪቃም ሆነ ለመላው አፍሪቃ አሳቢ የሆነ ፖለቲከኛ፤ በቅድሚያ የገዛ ሃገሩን [ኢትዮጵያን እና ኢዮጵያዊዕነትን] መውደድ ማጠንከር ማሳደግ፤ ታሪክዓዊ እሴቶቿን መንከባከብ፣ ዳር ድንበሯን ማስከበር እና ሰንደቅ-ዓላማዋን ማንገብ ይጠበቅበታል። የራሱን ማንዕነት የሚያጣጥል፣ የማያከብር አና የማያዝን ፖለቲከኛ — ለኢትዮጵያ በተዘጋጀ ዓለም-አቀፍ ዝግጅት ላይ፤ የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዓላማ ሊሆን ሲገባው፤ የእራሱን ጎሣ የተገንጣይ ድርጅት አርማ ወደ መድረድ አሾልኮ ይዞ የሚወጣ ፖለቲከኛ፤ የሃገር ክህደት እንደፈፀመ ነው መቆጠር የአለበት። እንዲህ የአለን ፖለቲከኛ፤ እንዲህ የአለን ሃገሩን የካደ ፖለቲከኛ፤ ለምሥራቅ አፍሪቃም ሆነ ለመላው አፍሪቃ፤ ቀና ሃሳብ ሊኖረው የሚያስችል የሞራል ልዕልና ይኖረዋል ብሎ ማመን፤ አልያም ግድ ይኖረዋል ብሎ መገመት፤ ዘበት ነው።

እንደገና ልብ እንበል ጎበዝ፤ የገዢው-ግንባር ውሁድ ፓርቲ ሆኜአለሁ ባይዕነቱ፤ በተናጠል የነበሩትን የጎሣ ድርጅቶችን "አክስሚል" እየተባለለት እንደሆነም ሰምቼ አለሁ። ይህንንም "ክስመት" ተብዬ፤ በሁሉም [በገዥው-ግንባር ውስጥ እና ዙሪያ] የነበሩ የጎሣ ድርጅቶች ሁሉ ተግባራዊ የሆነ ለማስመሰል እየተሞከረ ነው። ዕውነታው ግን፤ በገዥው-ግንባር የውሁድዕነት ሂደት፤ የከሰመ የጎሣ ድርጅት አለ ከተባለ፤ የ ገዥው-ግንባር አባል የሆኑትን/የነበሩትን፤ የሰሞነኛው ጎሣ ድርጅትን እና አኩራፊውን የነፃ አውጪ ድርጅት አይመለከትም። አኩራፊው [አምቢ፤ አልደመርም] ብሎ ድርጅታዊ አቋሙን የአስታወቀ ይመስለኛል። ነገ የሚለውን መገመት ባይቻልም። የሰሞነኛው የጎሣ ድርጅት ደሞ — መሪው ተደምሬ አለሁ ቢልም፤ አንድ ኢንፍሉዌንሺያል እንደሆነ የሚውራለት ባለስልጣን፤ አንጃ መሰል ኢንተርቪው ሰጥቶም ሰምተናል።

የገዥው-ግንባር አባል የሆነው፤ የሰሞነኛው ጎሣ ድርጅት ኢንፍሉዌንሺያል ነው የተባለለት ባለስልጣን፤ እራሱን ከውህደቱ ማግለሉ፤ የድርጅቱን አባላት ወደ ሌላ [ተፎካካሪ ተብዬ] የእራስአቸው ጎሣ የሆነ ድርጅት ፈልገው፤ [የድርጅት ፍልሰት] በሆነ መልኩ እንደሚቀላቀሉ መገመቱ፤ ከዕውነታው ብዙም የራቀ አይሆንም ብዬም ዐምን አለሁ። ይህ ሁሉ እንግዲህ፤ የሰሞነኛውን ጎሣ ድርጅቶች፤ በአንድ በኩል — ማዕከላዊ መንግሥቱን በውሁድዕነት ስም በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ፤ ኢትዮጵያን የአለምንም ሃፍረት እየዘረፉ፤ ኢትዮጵያዊዕነትን አያደበዘዙ፤ በሌላ በኩል ደሞ — የሚቀጥለውን ምርጫ ተብዬ አብላጫ ወንበር ለመያዝ የሚያስችላቸውን፤ የሌላውን ጎሣ ድርጅቶች በማታለልም፣ በማነሁለልም፣ በመግዛትም፣ በማስፈራራትም፣ በጉልበትም በማዳከም፤ የተጠናከረ የተደራጀ ስራ ተግተው እየሰሩ መሆኑን — አመልካች እንደሆነ ልብ ማለት ተገቢም ወሳኝም ነው፤ ማለት እወድ አለሁ።

በመጨረሻም፤

ገዥው-ግንባር፤ የሕዝብ ጥያቄዎችን ወደ ጎን በመተው — ምርጫውን አራዝሞ የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ፈንታ፤ በማን አለብኝዕነት ወደ ምርጫ ከገባ፤ በምርጫው ዙሪያ የሚከሰተው ችግር፤ ፖቴንሺያሊ — ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን ሊያጠፋ እንደሚችል መገመቱ፤ ሌላ ሳይሆን ብልህዕነት ነው። እናም፤ በተለይ — ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን ለመታደግ በሚል፤ የማሕበረሰብዓዊ እንቅስቃሴም ሆነ የማሕበረሰብዓዊ እንቅስቃሴ ድርጅት/ፓርቲ ውስጥ ጉልህ ሚና የእምትጫወቱ ወገኖች፤ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን ለማዳን፤ የሞራል ልዕልና የተጎናፀፋችሁ መሪዎች ለ መሆን ከፈለጋችሁ — [ሚዛንዓዊዕነትን] መሣሪያአችሁ ታደርጉት ዘንድ የግድ ነው! እንደ እኔ እንደ እኔ ደሞ፤ በእዚህ ዓይነቱ ክፉኛ አስጊ ወቅት፤ [ሚዛንዓዊዕነትን] መሣሪያው የአደረገ ፍቱን አቋም ይሆናል ብዬ የማምነው፤ ኢትዮጵያን የሚል ፖለቲከኛ እና የፖለቲካ ድርጅት [ሁሉ]፤ መለስተኛ ልዩዕነቶችን ወደ ጎን በመተው፤ ወደ የበለጠ አንድዕነት ሰብሰብ ማለትን እንደሆነ ትገነዝቡልኝ ዘንድ አደራ እላለሁ። በሉ፤ የኢትዮጵያ ዓምላክ፤ ሚዛንዓዊዕነትን ያጎናፅፈን — ያጎናፅፋችሁ። አሜን!

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር።

አኪዬ

— እንደገና እሰከምንገናኝ —

# ማሊንገሪንግ – ማሊንገረር

የካቲት ፪ሺህ፲፪ ዓ.ም ‖ ፌብርዌሪ 2020

አንድ ሰው፤ አሞኛል ሲል – ማንም ሌላ ሰው፤ የለም አልታመምህም ሊለው አይችልም። ያ-ንን ለማለት የሚችለው፤ የህክምና ባለሙያ የሆነ ሌላ ሰው ብቻ ነው። ያውም ስንት እልህ አስጨራሽ ምርመራ ከተደረገ በኋላ። በተዛማጅ፤ አንድ ግለሰብ/ቡድን፤ በደል፣ ጭቆና ደርሶብኛል ከአለ – ማንም ሌላ ግለሰብ/ቡድን፤ የለም አልተበደልህም፣ አልተጨቆንህም ሊለው አይችልም። ያ-ንን ማለት የሚችለው፤ በማህበረሰብአዊ ህይወት፣ በፖለቲካ፣ በህግ እና በታሪክ መስኮች ባለሙያ የሆነ ሌላ ግለሰብ/ቡድን ብቻ ነው። ያውም ስንት እልህ አስጨራሽ ጥናት እና ምርመራ ከተደረገ በኋላ። ያ እንደተጠበቀ ሆኖ — ለ የተለያዩ ምክንያቶች/ጥቅማ-ጥቅሞች በሚል ሆነ-ተብሎ ታስቦ እና ታቅዶ፤ በሃሰት የታመመ ለማስመሰል፤ ሊያጭበረብር/ሊዋሽ/ሊያጋንን/ሊያሳብብ የሚሞክር ሰው እንደአለ ልብ ማለት ጠቃሚ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ገጠመኝ፤ በህክምናው መስክ፤ ተሌሎች በሽታዎች ጎን [ስም] ተሰጥቶት፤ ገጠመኙ ወይም ክስተቱ፤ [ማሊንገሪንግ] ሲባል፤ ግለሰቡ [ማሊንገረር] ተብሎ ይጠራል። በጨዋ ደንብ፤ ውሸት/ዋሾ/ውሸታም እንደ ማለት ነው። በተመሳሳይ — ለ የተለያዩ ምክንያቶች/ጥቅማ-ጥቅሞች በሚል ሆነ-ተብሎ ታስቦ እና ታቅዶ፤ በሃሳዊ ትርክት የተበደለ የተጨቆነ ለማስመሰል፤ ሊያጭበረብር/ሊዋሽ/ሊያጋንን/ሊያሳብብ የሚሞክር ሰው/ቡድን እንደአለም ልብ ማለት እጅጉን ጠቃሚ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ገጠመኝ፤ በማህበረሰብአዊ ህይወት መስክም ማሊንገሪንግ እና ማሊንገረር የሚሉትን ቃላት፤ ውሸት/ዋሾ/ውሸታም ለማለት ሲጠቅምባቸው ይታያል። ለዚህ ለኋለኛው ክስተት — ኢትዮጵያን በተመለከተ፤ [አክራሪዎቹ] የጎሣ-ፖለቲከኞች፣ የጎሣ-ፖለቲካ አራማጅ ድርጅቶች እና ጎሠኞች፤ ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው።

ውድ የኢትዮጵያ  ልጆች፤ ለመሆኑ – እንዴት እንዴት ናችሁ?!

ጎሠኛዕነት፤ በሃሳዊ ትርክት ላይ ተመርኩዞ፤ እያስከተለ የአለው [ኤትኒክ ክሊንዚንግ] እና የ ሃገር የመፈራረስ አደጋ፤ እየ ገደደ መምጣቱን በ አሰብኩ ቁጥር፤ ከ ምን ጊዜውም በበለጠ [ለዚያች ደግ ሃገር እና ለዚያ ደግ ህዝብ] በፅኑ ማዘን ጀምሬአለሁ። ሰሞኑን የተከሰተውን፤ የልጆቻችንን ደብዛ መጥፋት ስሰማ የተሰማኝ ስሜትም ይሄው ነው። አዎ፤ ኢትዮጵያ ተወራለች። ኢትዮጵያ ውስጥ ኢ-ሰብዓዊዕነት ነግሷል። ኢ-ፍትህዓዊዕነት ተንሰራፍቷል። ምንም እንኳን ወርሃዊ ጦማር፤ የ ["ጉሮሮ ለ ጉሮሮ"] ትንቅንቅን ይተካል የሚል ብዥታ ባይኖረኝም፤ እንደ አንድ ያገባኛል ባይ፤ የ እሚሰማኝን አካፍላችሁ ዘንድ — በ አክብሮት ከ ፊትአችሁ ቀርቤ አለሁ።

እናም – አብረን እንድንቆይ፤ የ ምንግዜም ግብዣዬ ነው!

ጎበዝ፤ በርዕሴ ላይ የጠቀስኳቸው ቃላት፤ [ማሊንገሪንግ እና ማሊንገረር] – ከጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች፤ አባባሎችን እና ዘይቤዎችን በመዋስ የተጠነሰሱ የተፈጠሩ፤ በተለይ በህክምናው የሙያ መስክ፤ በህግ እና በውትድርና ሙያ መስኮችም ጭምር ጠቀሜታ ላይ እየዋሉ የአሉ ቃላት ናቸው። [አይሲዲ-10-ሲኤም ዳይግኖስስ ኮድ ዜድ76.5]

[ማሊንገሪንግ] በአጭሩ፤ የሆነ ጥቅም/ጥቅማ-ጥቅሞችን ለማግኘት ሲባል፤ እንደእየ-ሁኔታው ሆነ -ተብሎ፣ ታስቦ እና ታቅዶ፤ በሃሰት የታመመ ለማስመሰል፤ የተፈጠረ፣ የተፈበረከ፣ የተራገበ፣ የተመሳጠረ፣ የተዛባ፣ የተጭበረበረ፣ የተጋነነ፣ የተላከከ፤ የተመሃኘ፣ የተሳበበ — የህመም/የሰውነት ዕክል ምልክቶችን፤ የመደርደር ትያትር ነው። በህክምናው መስክ፤ እንዲያ ዓይነቱ ክስተት በአጋጠመ ቁጥር፤ ማሊንገሪንግ የሚል ብይን ለመስጠት የሚጣደፍ ባለሙያ የለም – በፍፁም! ሆኖም ግን፤ ብዙ ብዙ ጥያቄ እና መልሶች፣ የአካል፣ የላቦራቶሪ እና የሌሎች ቴክኖሎጂው የሚፈቅዳቸው ምርመራዎች ሁሉ ከተደረጉ በኋላ፤ በጥንቃቄ የሚሰጥ ብይን ነው። ምርመራው፤ [ኤክስተርናል ኢንቫይሮንመንት]ን በሰፊው የሚያካትት ከሆነ፤ በሃሰት ላይ ለተመሰረተው ትያትር ምክንያት የሆኑትን ጥቅማ-ጥቅሞችን ለይቶ የማወቅን አቅም እጅጉን ከፍ ያደርገዋል። ማሊንገሪንግ፤ ሆነ ተብሎ የተቀመረ የማታለል ተውኔት፣ ትያትር፣ ድራማ ነው። ማሊንገረሮች፤ ተአማኝ ይሆናል፣ ተቀባይዕነት ያገኝልናል የሚሉትን ምልክቶች መደርደር ላይ ስለሚያተኩሩ፤ የማይሆን ነገር እየዘበራረቁ እራሳችውን ያጋልጣሉ። ማሊንገረሮች ተጨባጭ ማስረጃ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ የሚታዘዙ ምርመራዎችን አሻፈርኝ ይላሉ፤ ወሳኝ የጥያቄ እና መልስ ፕሮግራሞችን ይሸሻሉ። ማሊንገረርስ እየሰሩ ያለው ተውኔት፣ ትያትር፣ ድራማ እንደሆነ እና በሃሰት ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጋችሁ፤ መጣጥፎችን ፈለግ ፈለግ አድርጉ እና አንብቡ፤ አልያም ወደ አንዱ የህክምና ፋከልቲ ጎራ ብላችሁ ጠያይቁ።

[ማሊንገሪንግ] በ ማህበረሰብአዊ ህይወት ደረጃም ይከሰታል የሚለውን  ሃሳብ ሳስብ ሳሰላስል፤ [አክራሪ] የጎሣ-ፖለቲከኞች፣ የጎሣ-ፖለቲካ አራማጅ ድርጅቶች እና ጎሠኞች ከዛሬ አምስት አስርት-ዓመታት ገደማ ጀምሮ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እየሰሩ ያሉትን ስራ ነው — ጥሩ ምሳሌ ሁኖ ያገኘሁት፤

[ጎሣ] እንደ ኤትንሲቲ። ተወላጅእነት፣ ጋብቻ፣ ቋንቋ፣ ወግ፣ ባህል፣ ጎጥ፣ የሃይማኖት ዕምነቶች፣ እና ምንአልባትም ስነልቦና – በቀረቤታ የሚያስተሳስረው ማህበረሰብ። አንድ ሰው፡ የአንድ ጎሣ ወይም ከአንድ በላይ ጎሣዎች ውስጥ የሚካተት፡ በተለያዩ ጎጦች የሚኖር ማህበረሰብም አባል መሆን የመቻሉ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ። [ጎሠኛዕነት] እንደ ኤትንሲዝም። በጎሣ ማንዕነት ላይ ጤናማ ያልሆነ ትኩረት ከማድረግ እና ኦብሰስድ ከመሆን የሚመነጭ፤ የእራስ ያልሆነ ነው በሚል የሚፈረጅ ጎሣ ላይ፡ ጭፍን ጥላቻን ማሳደር። በ ሃሳዊ ትርክት ላይ በመርኮዝ፤ የእራስ ያልሆነ ነው በሚል የሚፈረጅ ጎሣ ላይ በዕኩይዕነት የሚያነጣጥር፡ በጥቂት አወቅን ባይ እና ጤና በጎደላቸው ጠባቦች የሚዘወር – የልዩዕነት፣ የጥላቻ፣ የቅሚያ፣ የጠብ

አጫሪነት እና የመጠፋፋት ስነልቦና መሺነሪ። [የጎሣ-ፖለቲካ] እንደ በ ጎሣ ማንዕነት እና በ ጎሠኛዕነት የተመረዘ፡ ኋላቀር እና ጠባብ ማህበረሰብአዊ እንቅስቃሴ።

ማህበረስብዓዊ ህይወት እየአደገ እና እየተመሰቃቀለ፤ ጊዜም እየገፋ ሲሄድ፤ የሕዝብ ብዛት በፍጥነት እያደገ በመምጣቱ፣ አስተዳደር ውጥንቅጥ እየሆነ መሄዱ እሙን ነው። የሃብት እና የንብረት አለመመጣጠን መፈጠሩ ዕሙን ነው። ከእየማህበረሰቡ መካከል ብቅ የሚሉ አንድ አንድ ነቃ ያሉ ዕኩይ ግለሰቦች፡ “አዋቂዕነታቸው” ባጎናፀፋቸው የታማኝዕነት እና የተቀባይዕነት ሃይላቸውን በመጠቀም፤ በማህበረስብዓዊ ህይወት ዕድገት ሳቢያ የሚከሰቱ የጋራ ለውጦችን እና በጎሣዎች መካከል ያሉ ተፈጥሮአዊ ልዮነቶችን በማራገብ፣ በማጋነን፤ ባማዛባት፤ ባመላከክ ሃገርን ሲያፈርሱ እና ዕልቂት ሲያደርሱ እያን ነው። አሁን አሁን እማ፤ ለጥቂት ግለስቦች ሲባል ሃገር ሲፈርስ እና ህዝብ ሲያልቅ ማየቴ፤ ፅኑ ሃዘን ውስጥ ከትቶኝ አለ። እነኝህ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦችን አደብ ማስገዛት አቅቶን፣ እነሱ የሃሰት ትርክት በመፍጠር ላይ በመሰማራት — ታስቦ እና ታቅዶ፤ የተፈጠረ፣ የተፈበረከ፣ የተራገበ፣ የተመሳጠረ፣ የተዛባ፣ የተጭበረበረ፣ የተጋነነ፣ የተላከከ፤ የተመሃኘ፣ የተሳበበ ውዥንብር ላይ በመመርኮዝ፤ ወደ እርስ በእርስ ግጭት እና ዕልቂት ዘፍቀውን፤ ሃገርን እስከ መሰነጣጠቅ፤ ሃገርን እስከማፈራረስ የሚያደርስ ችግር፤ ቀን ተቀን ልናስተናግድላቸው ምምረጣችን — እጅጉን እጅጉን እጅጉን ያሳፍራል።

ጎሠኛዕነት፤ የሰብአዊ እና የዜጋ መብቶችን የሚፃረር፡ የአረመኔዕነት እና የአውሬዕነት ፖለቲካ ውጤት ነው። የጎሠኛዕነት እና የጎሣ-ፖለቲካ ኢንኽረንት ፍላጎቱ እና ተልዕኮው፤ ዲሚክረሲን ማስፈን በፍፁም አይደለም። ይልቁንስ፤ ሪሶርስ ሽሚያ እንጂ! ከባዕዳን ጋር ተመሳጥሮ ሃገርን ማፈራረስ እንጂ! ለዚህ ነው፤ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የአሉትን [አክራሪ] የጎሣ-ፖለቲከኞች፣ የጎሣ-ፖለቲካ አራማጅ ድርጅቶች እና ጎሠኞች፤ ክስተት ተውኔት/ትያትር/ድራማ [ማሊንገሪንግ] ተዋንያኖቹን ደሞ [ማሊንገረርስ] ውሸት/ዋሾ/ውሸታም መባል ያለባቸው።

ከዛሬ ሃምሳ-ሰላሳ ዓመታት ወዲህ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ የአለውም ይሄው ተላይ የጠቀስኩት ዕኩይ ትያትር/ተውኔት/ድራማ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን አክራሪ ጎሠኞችን፣ እድሜ ልክአቸውን ታዝቤአቸዋለሁ፣ የሚደረድሩትን የሃሰት ትርክቶችን አዳምጬአለሁ፣ የሚያደርጓቸውን ኢ-ሰብዓዊ አውሬዓዊ ትግል-ተብዬ አስተውዬአለሁ፣ ወዳጆቻቸው እነማን ጠላቶቻቸው እነማን እንደሆኑ አውቃለሁ፣ ከባዕዳን ጋር ያላቸውን ቁርኝት ተገንዝቤአለሁ፣ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያን ያላቸውን ጥላቻ ተረድቻለሁ፣ ለክርስትና ሃይማኖት ያላቸውን ጥላቻ አስተውየአለሁ፣ ሃገር ለማፍረስ እና ዕልቂት ለፍጠር መዘጋጀታቸውን እመሰክርአለሁ። ብሶታቸው ማለቂያ የሌለው መሆኑንም አውቃለሁ።

አዎ — ጎሠኛዕነት፤ የሃሰት ትርክት ላይ የተመሰረተ፤ ሆነ ተብሎ የተቀመረ የማታለል የማስመሰል የማጭበርበር ዕኩይ ተውኔት፣ መሰሪ ትያትር፣ አውሬዓዊ ድራማ ነው። ጎሠኞች – ተአማኝ ይሆናል፣ ተቀባይዕነት ያገኝልናል፤ ህዝብን በቀላሉ ያሳምንልናል የሚሉትን የፈጠራ በደሎች እና ጭቆናዎች መደርደር ላይ ያተኩራሉ። ጎሠኞች – እየሰሩ ያለው በሃሰት ላይ የተመረኮዘ ተውኔት/ትያትር/ድራማ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ጎሠኞች – የሚደረድሯቸው በደሎችን እና ጭቆናዎችን፤ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ፤ ዕውነት ወይም ውሸት መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና ለመተማምን ይረዳ ዘንድ የሚዘጋጁ የውይይት እና የሙግት መድርኮችን ይሸሻሉ። ከወደ የአሁኑ ሰሜን አካባቢ የተነሱ ጎሠኞች፤ ለአለፉፋት ሃይ-ስምንት ዓመታት ገደማ – ከወደ ደቡብ ምዕራብ አካባቢ የተነሱ ጎሠኞች ደሞ፤ ለአለፉት ሃይ-ወራት ገደማ፤ ጊዜ አንስቷቸው የስልጣን በርጩማው ላይ የተኮፈሱ ቢሆንም ቅሉ — የሃሰት ትርክታቸውን ነጋ ጠባ ማላዘናቸውን ግን አላቆሙም።

በመጨረሻም፤

ጎበዝ፤ በህክምናው መስክ እና መማህበረሰብዓዊ ህይወት ውስጥ፤ የሚከሰት ማሊንገሪንግ፤ ሁለቱም በ ውሸታምዕነት በአስመሳይዕነት በአጭበርባሪዕነት ላይ የተመሰረቱ መሆኑ ላይ ይመሳሰሉ እንጂ፤ መዘዛቸው እና የመጨረሻ ውጤታቸው ሲታይ — በፍፁም በአንድ አረፍተ-ነገር ጎን ለጎን ሊጠቀሱ ያማይገባቸው ክስተቶች ናቸው።

ጎሠኞች ውሸታሞች ዋሾዎች ናቸው። ጎሠኞች ወኔም አቅምም የላቸውም። ጎሠኞች ኢትዮጵያ ውስጥ እያስከተሉ ያሉት የሃገር መፈራረስ እና የህዝብ ዕልቂት አደጋ፤ በሃሰት ላይ የተመሰርቱ ሆነው ሳለ፤ እየባሱ እንጂ እየቀለሉ ሲሄዱ አለማየታችን፤ የእኛን ቆርጦ አለመነሳት ያሚያሳይ ሃቅ ነው።

በሃገር ውስጥ ትግል ማድረግ አስቸጋሪ እንደሆነ አምናለሁ። በአካል እራቅ ብለን ከአለነው ጋር የኮምፎርት ዞን ልዩነት መኖሩ ግልፅ ነው። የእኛ አቋም ፈርጠም ያለ ሲሆን፤ የእናንተው ለዘብ ያለ የሚሆንበት ምክንያቱ ይገባኛል። ከዚያ በተረፈ፤ መሠረታዊ ልዩነት የሌለባቸው አቋሞች ላይ በመነታረክ ጊዜ የምታባክኑ የአንድዕነት ሃይሎች፤ ትግሉን እየጎዳችሁ እንደሆነ ልትረዱት ይገባል። በአጠቃላይ፤ ኢትዮጵያን እታደጋለሁ የሚለው ኢትዮጵያዊ በአሁኑ ሰዓት በፍርሃት ተውጧል። ፍርሃታችሁ በምትጠቀሟቸው ቃላቶች ያስታውቃል። ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ብሎ ነገር የለም። ያለው ኢትዮጵያዊነት ነው። የብሄር ድርጅት ብሎ ነገር የለም። ያለው የጎሣ-ድርጅት አልያም ኢትዮጵያዊ-ድርጅት ነው። በነገራችን ላይ፤ የጎሣ-ድርጅት ወይም የጎሣ-ፖለቲካ በህግ ይገደብ የምለው፤ [አክራሪ] የጎሣ-ድርጅቶችን ነው — በዋናዕነት። ኢትዮጵያ ውስጥ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች፤ ከሦስት-አራት አይበልጡም። ሌሎቻችሁ የጎሣ-ድርጅቶች ኢትዮጵያዊዕነታችሁን አልጠራጠርም። እናንተ፤ በህግ ይገደቡ እያሉን ነው እያላችሁ መነፋረቁን ትታችሁ፤ ሃይላችሁን አሰባስባችሁ አምርራችሁ ታገሉ። ሲስተማቲካሊ አያጠፏችሁ ነው።

እናም፤ የ ከፉ ነገር ከ መድረሱ በፊት፤ ደጋግሜ እለዋለሁ — [ምርጫው ይራዘም። ገዥው-ግንባር/ፓርቲ በ ከፍተኛ ሃላፊዕነት እና ጥንቃቄ፤ ከስልጣን ይውረድ። የሕዝብን እና የኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጥምረት በማቀናጀት፤

የሽግግር መንግስት ይዋቀር። ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ ያሳተፈ ህገመንግስት ይቀረፅ። አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ እና የጎሣ-ድርጅቶች በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ ይፍረስ። በምትኩም፤ ሕዝብ የሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት ይዘርጋ። ሰው በሰውእነቱ ብቻ የሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን የሚከተል – በፍትሃዊ እና ነፃ ምርጫ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን የሚያገኝ – ሕዝባዊ መንግስት ይመስረት።]

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር።

አኪዩ

— እንደገና እስክምንገናኝ —

# ሃገርን እና ሕዝብን የማዳን ጥሪ!

መጋቢት ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ‖ ማርች 2020

*የዛሬው መልዕክቴ በጣም ግልፅ ነው። መሪር መስዋዕትዕነት የተከፈለበት የሕዝብዓዊው አመፅ መቋጫ – የዘፈቀደ ምርጫ ማድረግ አይደለም። በፍጥፁም! ይልቁንእስ፤ ምርጫው ሊደረግ የታሰበበትን ጊዜ ማራዘም፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣ አዲስ ኢትዮጵያዊ ሕገመንግሥት መቅረፅ፣ ፍትሕዓዊ እና ነፃ ምርጫ ለማካሄድ ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን እና ኢትዮጵያዊ ተቋማትን በአዲስ መልክ ማደራጀት፤ ከእዚያም በመቀጠል — ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት እንጂ! ይህ ሃሣብ የእሚተናነቃቸው ጥቂት ግለሰቦች እንደ አሉ የታወቀ ነው።* እነርሱም፤ በዋናዕነት አንድ አንድ የገዥው-ፓርቲ ሰዎች እና ሸሪኮቻቸው ሲሆኑ፤ ሌሎች – ፖለቲካውን በአግባቡ መረዳት የእማይችሉ፣ የእሚይዙት የእሚጨብጡት ጠፍቷቸው ዓይናቸውን ጨፍነው የእሚነዱ፤ በዕውነተኛ-ለውጥ ፍርሃት የተሽመደመዱ ደካሞች መኖራቸውም ግልፅ ነው። መሠረታዊ ችግሮቻችን ምርጫ በማድረግ አይፈቱም። *በምርጫው መሳተፍ – ለሃገር መጥፋት እና ለሕዝብ ዕልቂት ተባባሪ መሆን ነው። በምርጫው አንሳተፍም እንበል። የሽግግር መንግሥት ጠቀሜታን፤ ለሕዝብ እና ለዓለም-አቀፉ ማሕበረሰብ እናስተምር፣ እንቀስቅስ። ጥያቄዎቻችን ተጠናክረው ይቅረቡ። ገዥው-ፓርቲ፤ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም እንዲያዞር ይጠየቅ፣ ይገደድ።*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፤ እንዴት ናችሁ ?!

ዛሬ፤ ምርጫው ይራዘም – ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የእሚል መልዕክት አንግቤ፤ እንደ አንድ ያገባኛል ባይ – ትንሽ የእምለውን ለማለት ከፊትአችሁ ቀርቤ አለሁ።

እናም፤ አብረን እንድንቆይ የምንጊዜም ግብዣዬ ነው!

ጎበዝ፤

የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ አለን እያልን የመኩራራታችንን ያህል፤ [የወል ስልጡን ዕድገትን በተመለከተ] – ለምን የሃገራት ሁሉ ጭራ ሆነን ቀረን ብለን እራስአችን'ን መጠየቁ ላይ ግን እምብዛም ነን። አዎ፤ ለእማይካደው የወል ኋላቀርዕነታችን፤ ረዥም አመክንዮት መደርደር ይቻላል። እንደ እኔ እንደ እኔ፤ መሠረታዊ እና ጎላ ብሎ ሊታይ ይገባል የምለው አመክንዮ ግን፤ [ዕውነተኛ ለውጥ'ን መፍራት] ነው ብዬ አስብ አለሁ። ብዙውን ጊዜ፤ የሰው ልጆች ዕውነተኛ ለውጥ'ን የእምንፈራው፤ ለውጡ የእሚያመጣው ውጤት ምን እንደሆነ ጤና'ማ ግምት ሊኖረን የአልቻለ እንደሆነ ነው። የሰው ልጅ፤ ዕውነተኛ ለውጥ'ን በማሰብ እና በመፍጠር – እራሱንም አካባቢውንም የበለጠ ማሰልጠን፣ የበለጠ ማሳደግ፤ የበለጠ ማራቀቅ የመቻል ግዙፍ አቅም የአለው መለኮትዓዊ ፍጡር ነው። ያ-ንን ከማድረግ የእሚያግደው – በአመዛኙ፤ በዕውነተኛ ለውጥ ፍርሃት ለመቀፍደድ ፈቃደኛ የሆነ እንደሆነ ነው። የሰው ልጅ ሲፈራ፤ የተጎናፀፈውን ዕምቅ ሃይል እና ዕምቅ ክህሎት ማየት ይሳነዋል። የሰው ልጅ ሲፈራ፤ ምን እንደ እሚከተል ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ የአልሆነውን እርምጃ በመውሰድ፤ ለመለወጥ ከመሞከር ይልቅ፤ ከዕውነተኛ ለውጥ ለመሸሽ የሌለ [ትርክት] ወደ መፍጠር ያዘነብላል። ዕውነተኛ ለውጥ'ን የእሚፈራ ግለሰብ ወይም ዕውነተኛ ለውጥ'ን የእሚፈራ ማሕበረሰብ — ምሉዕ ሰውዓዊ ህይወትን ሳያጣጥም ዕድሜውን ይገፋል። የ-እኛ የወል እጣ-ፈንታችንም ይህ ሆኖ፤ ዛሬ እንደ አለን-አለን።

ልብ እንበል ጎበዝ። በህይወት ወስጥ ሁሉም ነገር ተለዋዋጭ ነው። አዎ፤ በህይወታችን ውስጥ የማይለወጥ ነገር አለ ከተባለ፤ [ለውጥ] እራሱ ብቻ ነው፤ የሚለው አባባል ዕውነት ነው። እናም፤ ዕውነተኛ-ለውጥ'ን መፍራት – የኋላቀርዕነት መሠረታዊ ምክንያት ነው። ደፈር ብለን መሠረትዓዊ ተቋምዓዊ ለውጥ ለማምጣት የእሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ከአልጀመርን፤ ለእሚቀጥሉት ብዙ ሺህ ዓመታት ዛሬ ከአለንእበት ኋላቀርዕነት ቅንጣት ታህል ፈቀቅ ማለት እንደማንችል ሳስብ – እጅጉን አዝን አለሁ። ከአንድ መንግሥት ጋር ሃያ-አርባ ዓመታት ማንጎላጀት ይብቃን። በእዚህ መልኩ ህይወትን መምራት — ማደግን፣ መሻሻልን፣ መራቀቅን፣ መሰልጠንን አያስገኝልንም።

አንዴ ልድገመው። [ዕውነተኛ ለውጥ'ን መፍራት] የእሚመነጨው፣ የእሚጎለብተው በአመዛኙ፤ ለእራስአችን በምንነግረው [ትርክት] ነው። ህይወታችን ከቁጥጥርአችን ውጪ እንደሆነ በማመን እና ሌላው በሚነዳን መነዳቱን መምረጥ ላይ በማዘንበላችን ነው። ምንም እንኳን የህይወት ከቁጥጥርአችን ውጪ የመሆን ፕሮባቢሊቲ ዜሮ ባይሆንም ቅሉ፤ ዕውነተኛ ለውጥ'ን የእምንፈራው፤ የህይወታችንን መዘዉር እራሳችን ጨብጠን ፈር የማስያዝ ሃላፊነቱም ግዴታውም የእራሳአችን መሆኑን አምነን በአለመቀበላችን ነው። ያ-ንን የማድረግ ሙሉ ችሎታው እየ አለን! ምርጫው ይራዘም፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም፣ ለፍትሕዓዊ እና ነፃ ምርጫ ሲኬታማዕነት ወሳኝ የሆኑ ሕገመንግሥትዓዊ እና መዋቅርዓዊ ዝግጅቶችን እናስቀድም ስንል፤ የሕዝብዓዊ'ው ትግል መቋጫ፤ የዘፈቀደ ምርጫ ማድረግ አንዳልሆነ በፅኑ የ ዕምናምን በመሆኑ ነው። ኢትዮጵያን በታማኝዕነት እና በቆራጥዕነት የእሚጠብቅ እና ኢትዮጵያዊያንን በቀናዕነት የእሚያገለግል ኢትዮጵያዊ [ሞልቷል] ብለን በ ፅኑ የዕምናምን በመሆኑ ነው።

ጎበዝ፤

የወቅቱ ወሳኝ ጥያቄ፤ ምርጫው ገዥው-ፓርቲ በተለመው መርሃ-ግብር መሠረት ተግባርዓዊ ይሁን ወይስ ምርጫው ይራዘም የእሚለው ነው። ይህ ወሳኝ ሃገርዓዊ እና ሕዝብዓዊ ጥያቄ ነው። ቀልድ አይደለም። ምርጫው ይራዘም ስንል፤ ከ ነሃሴ አስር ወደ ነሃሴ 23 ይራዘም ማለት አይደለም። ምርጫው

ይራዘም ስንል፤ ለ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት ዓመታት ይተላለፍ ማለታችን ነው። ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት አቋቁመን፣ ለፍትሕዓዊ እና ነፃ ምርጫ ወሳኝ የሆኑ ሕገመንሥትዓዊ እና መዋቅርዓዊ ዝግጅቶችን አሳክተን — ሕዝብዓዊ መንግሥት መመስረት እንችል ዘንድ!

አዎ፤

ለ የምርጫው መራዘም አግባብዕነት – ብዙ ምክንያቶችን መዘርዘር ይቻላል። ለምሳሌ፤

ሀ) አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ መጎልበት ብሎም የሃገር መጥፋት እና የሕዝብ ዕልቂት፤ መሠረታዊ ችግሮቻችን እንደሆኑ ዕሙን ነው። እነዚህ መሠረታዊ ችግሮቻችን – ምርጫ በማድረግ የሚፈቱ አይደሉም። ምርጫው ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ገዥው-ፓርቲ'ን አያስወግድም። ምርጫው ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑትን የግንጠላ ድርጅቶችን አያጠፋም። ምርጫው አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካን በሕግ አይገድብም፣ የጎሣ-ፌደራሊዝሙን አያፈርስም። እንዲያውም ያጎለብታቸዋል እንጂ!

ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ከ ሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከ ምዕራብ እስከ ምሥራቅ፤ በሁሉም ቦታ ሰላም እና መረጋጋት የሚባል ነገር የለም። የ ዕለት ተ ዕለት ህይወት ክፉኛ ተረብሾ አለ። ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል ተበጥብጠዋል። ንፁህ ልጆቻችን ከታፈኑ እና ደብዛቸው ከጠፋ ይሄው እና 88 ቀናት ተቆጠሩ። ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚሉ የባዕዳን ቅጥረኞች፤ በ እየ መንደሩ ይፏልላሉ፣ በመንግሥት ተብዬው መዋቅር ውስጥ ተሰግስገው ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ሌት ተቀን ይዶልታሉ። በ እንደ እዚህ ዓይነት ሁኔታ፤ ምርጫ ይደረግ እያሉ ግግም ማለት፤ ድንቁርና ነው።

ሐ) ምርጫውን ተከትለው ሊከሰቱ የሚችሉ ሃገርን እና ሕዝብን አጥፊ የሆኑ አጅጉን የከፉ አደጋዎች – ዕውነታ ናቸው። አሁን በአለው ሁኔታ፤ ምርጫው ከተደረገ፣ የሰው ህይወት ይጠፋል፣ መፈናቀል እና ስደት ይከተላል፣ የፈረሰችው ሃገር – ጭራሽእኑ ትጠፋለች።

የመረረ መስዋዕትዕነት የተከፈለበት የሕዝብዓዊው ትግል መቋጫ፤ በዘፈቀደ የሚደረግ ምርጫ ላይ መካፈል አይደለም። በፍፁም! የመረረ መስዋዕትዕነት የተከፈለበት የሕዝብዓዊው ትግል መቋጫ፤ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት አቋቁመን፣ ለ ፍትሕዓዊ እና ነፃ ምርጫ ወሳኝ የሆኑ ሕገመንግሥትዓዊ እና መዋቅርዓዊ ዝግጅቶችን ጨርሰን — ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት እንጂ! ይህንን ዕውነታ የሚክዱ፤ በ [ፍርሃት] የተዋጡ ደካሞች፤ ዓይንአቸውን በጨው አጥበው በ ሕዝብ ፊት ሲንበዛበዙ መስማት – እጅጉን – አዎ፤ እጅጉን እጅጉን ያሳፍራል።

ሲያሻቸው — ለውጡ የመጣው በገዥው-ፓርቲ ውስጥ በ የ አሉት ግለሰቦች ስለሆነ፤ ምርጫው ይራዘም ብንላቸው ይከፋሉ፣ እሺ አይሉንም። የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ብንላቸው እማ ይቆጡናል ሲሉ ይደመጣሉ። ኢትዮጵያዊ ነን የእምንል ሁሉ አንድ ነገር ያለማወላዳት ሊገባን ያስፈልጋል። ለውጡ የመጣው በዋናዕነት በመረረ እና እልህ አስጨራሽ የሆነ መስዋዕትዕነት በተከፈለበት ሕዝብዓዊ አመፅ ነው። ይህንን ዕውነታ መካድ ትልቅ ነውር ነው። እናም፤ ገዥው-ፓርቲ'ን ምርጫው እንዲራዘምም ሆነ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ስንጠይቅ፤ [ልምምጥ ወይም ልመና] አይደለም — ግዳጅ መሆኑን አስረግጦ ማሳወቅ እንጅ! ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የማይቻልበት ምክንያት ምንም የለም። ምክንያት ደርዳሪዎች ሁሉ፤ ልታፍሩ ይገባል።

ግራ ሲገባቸው — ምርጫው ይራዘም እንዳንል ሕጉ አይፈቅድም ሲሉ ይደመጣሉ። ስለ ሕግዓዊዕነት ሊያወሩ ሲቃጣቸው ነው እኮ የእሚያስቀው። ለመሆኑ ስለ የትኛው ሕግ ነው የሚያወሩት። ሶስት ለኢትዮጵያ መጥፋት ጫካ ገብተው ሲዳክሩ በነበሩ ከሃዲ ድርጅቶች የተፃፈውን ሕገመንግሥት ተብዬ'ን እኮ ነው፤ እንድንመራበት የሚነግሩን። የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል፤ ያ-ንን ሕገመንግሥት የሚሉትን ቀዳዶ ጥሎ፤ ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ አሳተፊ የሆነ አዲስ ሕገመንግሥት መቅረፅ እንደሆነ፤ እንዴት ሳይረዳቸው ቀረ!

መውጫው ሲጠፋቸው — ማን አለ እና ነው፤ ሰው'ም ድርጅት'ም የለም እኮ፤ ይላሉ። እነ እኚህ [ሰው] የለም [ድርጅት] የለም ባዮች፤ ከ ገዥው-ፓርቲ ሌላ አማራጭ የለም ወደ የ እሚል ድምዳሜ እንዲደረስ [ተቀጥረው እንደ ሆነ እገምታለሁ] እየቀሰቀሱ እንደሆነ ሁላችንም ልብ ልንል ይገባል። የኢትዮጵያ አምላክ ያሳያችሁ፤ ከ 113,000,000 ሕዝብ መካከል፤ የሕዝብ ተወካይ ይጠፋል እያሉ ከሚያላዝኑ ደናቁርት ጋር ነው እየኖርን ያለነው። ኢትዮጵያን በቁርጠኛዕነት እና በታማኝዕነት የእሚጠብቅ እና ኢትዮጵያዊያንን በቀናዕነት የሚያገለግል ሰው'ም ድርጅት'ም የለም እያሉ መድረኩን ከእሚያጣብቡ ድኩማን ጋር ነው እየኖርን ያለነው።

ዕውነት ነው፤ ምርጫውን ላለመሳተፍ መወሰኑ ብቻውን፤ የምንፈልገውን ለውጥ ሊያመጣልን አይችልም። ምርጫውን ባንሳተፍም ገዥው-ፓርቲ በሆነ ቁጥር አሸነፍኩ ብሎ ስልጣኑን መያዙ አይቀርም። ሖኖም ግን፤ ምርጫውን በ አለመሳተፍ አሸናፊ የሆነውን ድርጅት ሌጂቲመሲ ገደል መክተት ይቻላል። ያ-ም፤ ለ የ ገዥው-ፓርቲ ትልቅ ክስረት ነው የእሚሆነው። ያ-ም ብቻም ሳይሆን ምርጫው ቦይካት የተደረገበትን ምክንያት ለሕዝብ በማስረዳት በማሳመን፤ ለ ዓለም-አቀፉ ማሕበረሰብ በማስረዳት፣ በማሳመን ሕዝብዓዊ እንቅስቃሴው ጎልብቶ እንዲቀጥል ማድረግ እና የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ማስገደድ ይቻላል። ያ-እና-ያ ሲሆን ብቻ ነው፤ ወደ የበለጠ ስልጣኔ አንድ እርምጃ ወደ ፊት መራመድ የ እምንችለው።

በመጨረሻም፤

ኢትዮጵያን የአፈረሰ፣ የባሕር-በሮቿን አሳልፎ የሰጠ፣ አንጡራ ሃብቷን የዘረፈ፣ ኢ-ሰብዓዊዕነትን የአንሰራፋ፣ አሸባሪዕነቱን የአመነ፣ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካን፣ ጎሠኛዕነትን እና ተገንጣይዕነትን የአጎለበተውን፤ ማንም ይቅር ሳይለው–እራሱን ይቅር ብየ አለሁ ብሎ፤ ዛሬ በመንግሥትዕነት በርጩማ ላይ የተኮፈሰ'ውን ገዥው-ፓርቲ፤ [ኢትዮጵያን የበለጠ እንዲያጠፋት] ዕድሉ ሊሰጠው አይገባም። በፍፁም! እንደለመደው የእራሱን እና ከሰሞነኛው ጎሣ የተውጣጡ ሸሪኮቹን ኪስ ለማደለብ፤ [ብልፅግና] የሚል የማታለያ ቃል ይዞ

ብቅ በማለቱ፤ በፍፁም መጃጃል በፍፁም መነኋለል አይገባም። በ አለፉት 30 ዓመታት ገደማ ማን እንደበለፀገ አይተናል። አሁንም ቢሆን ከ እዚያ የተለየ ነገር አይመጣም። እንዲያውም እጅጉን የባሰ እንደሚሆን ከ በቂ በላይ ምልክቶችን እያየን ነው። እናም፤ ፍርሃትን ለመሸፋፈን የሚደረደሩትን የፈጠራ ትርክቶች በማቆም — በምርጫው አንሳተፍም በሉ። በምርጫው መሳተፍ – ለሃገር መጥፋት እና ለሕዝብ ዕልቂት ተባባሪ መሆን ነው። በሕዝብ፣ በታሪክ፣ በህግ፣ እና በኢትዮጵያ ዓምላክ ፊት የእሚያስጠይቅ — ትልቅ ነውር እና ከሃዲዕነት! አዎ፤ በምርጫው አንሳተፍም እንበል። የሽግግር መንግሥት ጠቀሜታን ለሕዝብ እና ለዓለም-አቀፉ ማሕበረሰብ እናስተምር፣ እንቀስቅስ። ጥያቄዎቻችን ተጠናክረው ይቅረቡ። ገዥው-ፓርቲ፤ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም እንዲያዞር ይጠየቅ፣ ይገደድ።

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር።

አኪዬ

— እንደገና እስክምንገናኝ —

# ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ

ሚያዝያ ፪ሺህ፲፪ ዓ.ም ‖ ኤፕሪል 2020

በ ድሴምበር መገባደጃ አካባቢ፤ ከወደ እሩቅ–ምሥራቅ የጀመረ፤ የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ወረርሽኝ፤ ከሦስት–ወራት በአልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤ መረር ያለ ጉዳት እየአስከተለ፤ ሁሉንም አህጉራት በማዳረስ፤ ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ደረጃ ላይ ደርሷል። የመከላከያ ክትባት፣ አንቲቦዲስ'ም ሆነ የመፈወሻ መድሃኒት እስከ ዛሬ ድረስ የሌለው ይህ ኮቪድ–19 በእሚል የእሚጠራው በሽታ፤ ከሰው-ወደ-ሰው በቀላሉ የእሚተላለፍ በመሆኑ፤ በቫይረሱ መያዝአቸው የታወቁት ሰዎች ቁጥር'ም ሆነ በሽታው ፀንቶባቸው ህየወታቸው የአለፈ ሰዎች ቁጥር፤ አስፈሪ ደርጃ ላይ ከደረሰ ሰነባብቷል። የመቀነስ ምልከት ለማሳየት'ም፤ ጊዜ ሊወስድ የእሚችል እንደሆነ እግምት ውስጥ የሚገባ ቢሆንም ቅሉ፤ ወረርሽኙን የመከላከል ቆፍጠን የአለ የመቆጣጠር እርምጃዎች የተተገበረበት አካባቢ፤ የቫይረሱ ስርጭት እየቀነሰ እንደመጣ ፍንጭ መታየቱ፤ ተስፋ ሰጪ ነው። ወረርሽኙ ዘግየት ብሎ የተቀጣጠለባቸው ሃገራት እና ዛሬ በወረርሽኙ ብዙም የተጠቁ እማይመስሉ ሃገራት፤ ትልቅ ትምህርት አድርገው ሊወስዱት ይገባል። ወረርሽኙን ለመግታት [ከህሙማን ጋር አለመነካካት፣ በአልታጠበ እጅ አይናችን'ን፣ አፍንጫችን'ን እና አፍአችን'ን  አለመንካት፤ እጅን ሙያተኞች በእሚመክሩት መንገድ መታጠብ፤ አይበለው እና በሽታው ከያዘም – እራስን እቤት ማቆየት፣ ሳል'ን እና ማስነጠስ'ን በተገቢው መንገድ መሸፈን እና ማናቸውን'ም በእጅ ሊነካኩ የእሚችሉ ነገሮችን ማፀዳዳት] — ቫይረሱ በቀላሉ እንዳይተላለፍ እንዳይዛመት ያደርገዋል። ይህ ወረርሽኝ፤ ከፍተኛ ገቢ'ም ሆነ ዝቅተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት'ን ሳያማርጥ እየአጠቃቸው እንደሆነ ግልፅ ነው። ከፍተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት፤ ወረርሽኙን መቋቋም የእሚያስችል ቁመና ለዘመናት የገነቡ በመሆኑ፤ መደናገጡም ሆነ መረበሹ የእማይቀር ቢሆንም፤ በመጨረሻ – ጉዳቱ ብዙም ሳያንሳቁላቸው ቶሎ ማገገም እንደእሚችሉ ዕሙን ነው። እየተባባሰ በመጣው የመንፈስ እረብሻ ሳቢያ ሊከሰት ከእሚችለው፤ የአዕምሮ መታወክ ችግር'ም ጭምር። የአንድ'ን ሃገር ሁለዕንተንዓዊ ቁመና ቀደም ብሎ የመገንባት ጠቀሜታው እዚህ ላይ ነው። ዝቅተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት፤ እንዲህ ዓይነቱ ቻሌንጅ በዕንቅርት ላይ – ጆሮ ደግፍ ስለ እሚሆንባቸው፤ በከፋ መልኩ የእዚህ ወረርሽኝ ሰለባ እንደእሚሆኑ ማስገንዘብ፤ ሌላ ሳይሆን – ሰውዓዊዕነት ነው። ያ–ም በመሆኑ፤ ሁሉም ሃገራት — በተለይም ዝቅተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት፣ ይህ–ን'ን ወረርስኝ ለማሸነፍ፤ በከፍተኛ [ሴንስ ኦፍ ኧርጀንሲ] ጦራቸውን ሰብቀው፤ ዛሬውኑ ወደ ፍልሚያው መግባት ይጠበቅባቸዋል። ወረርሽኝ'ን ለመዋጋት በእሚል የተዘጋጀ መርሃ–ግብር'ን እንዴት ተግባርዓዊ ማድረግ እንደእሚቻል ከወዲሁ ከበቂ በላይ ዝግጅት ማድረግ የግድ ነው። አንድ ነገር በተከሰተ ቁጥር [ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ] ባዮች ከመሆን እንድን ዘንድ። የክረምት ወራት እየተቃረቡ መሆኑን ለእናንተ ማስታወስ ድፍረት እንዳይሆንብኝ፤ ትቸው አለሁ። ተዘጋጅቶ መገኘት፤ እንደ ኮቪድ–19 የአለ ፈተና ሲያጋጥም – ከ ማለቅ'ም ሆነ የሰው እጅ ከ ማየት ያድናል እና በርቱ። አይዞን!

ውድ የኢትዮጵያ  ልጆች፤ ለመሆኑ – እንዴት እንዴት ይዟችኋል?!

የዛሬዋ መጣጥፌ – እረዘም የአለች በመሆኗ፤ ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቅ አለሁ። እየተፋለምን የ አለዉን ወረርሽኝ ምክንያት በማድረግ፤ የይድረስ የይድረስ እና ላይ–ላዩን ቢሆን'ም ቅሉ፤ ከአነበብኳቸው፣ ከሰማኋቸው፤ ከሰራኋቸው፣ ከአሰብኳቸው እና ከአሠላሰልኳቸው ቁም–ነገሮች በመነሳት፤ ትንሽ የእምለውን ለማለት፤ ከፊትአችሁ ቀርቤ አለሁ።

እናም – አብረን እንድንቆይ፤ የምንግዜም ግብዣዬ ነው!

አለፍ ብላችሁ እንደእምታዩት (ቀመር ፩)፤ ከወደ ድሴምበር መገባደጃ አካባቢ የተቀሰቀሰ የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ወረርሽኝ፤ ከሦስት–ወራት በአልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤ የህመም ምልክት ታይቶባቸው፤ የቫይረሱ ምርመራ ከተደረገላቸው መካከል፤ [ግሎባሊ] በመቶ–ሺህዎች የእሚቆጠሩ በቫይረሱ እንደተያዙ ተረጋግጧል። የሙታን'ን ቀመር እዚህ አላሳየሁትም እንጂ፤ በ አሥር–ሺህዎች የእሚቆጠሩ፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ'ም የታወቀ ነው።


የላቦራቶሪ ምርመራው፤ ኅብረተሰቡ ውስጥ [በሰፊው] ምንአልባትም ቀደም ብሎ፤ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፤ በቫይረሱ የተያዘ ሰው ቁጥር፤ ወደ ጃኒዌሪ መጀመሪያ አካባቢ — ማለትም አሁን በግልፅ ከታየበት፤ በ ሰባት ወይም በ 14 ቀናት፤ ቀደም ብሎ የጀመረ መሆኑን፤ ማየት እንችል ነበር።

በቫይረሱ የተያዙ፤ ነገር ግን ምልክት ሳያሳዩ ቀርተው ወይም ቶሎ የላቦራቶሪ ምርመራ ሳይደርግዕላቸው በመቅረታቸው፤ ከኅብረተሰቡ ጋር እንደፈለጉ የተገናኙ፤ ቫይረሱን ለብዙ ሰዎች አስተላልፈው ሊሆን እንደእሚችል መገመት ብልህዕነት ነው። ሪፖርት የእሚደረጉት የ ኮቪድ–19 ህሙማን ቁጥር በእየዕለቱ እየጨመረ መቀጠሉ፤ ጥሩ ዜና አይደለም።

እንደ አንድ የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ፤ ይህእን'ን ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እየአደረግን የአለነው ሁሉ፤ እሚፈለገውን ውጤት፤ በፍጥነት ማምጣት እንደ አላስቻለን እየ አየን ነው። የሰው ልጅ ለ [ጤና] ሊሰጠው የ እሚገባ ትኩረት፤ እንደዋዛ እየታለፈ — ይኼው እና ዛሬ የ እምንይዘው የ እምንጨብጠው ጠፍቶን፤ እነተረማመሳለን።

እንዲህ በአለ ሁኔታ፤ እንደ ሶሻል [ፊዚካል ማለቱ ይሻል ነበር] ዲስታንሲንግ፣ አይዞሌሽን እና የመሳሰሉትን ዓይነት እርምጃዎች'ን፤ አንድአንዶች እንደ እሚፈልጉት፤ ከዛሬ በአንድ ወይም በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ፤ ልንገላገለው የእሚያስችል አስተማማኝ ደረጃ ላይ የእምንደርስ አይመስለኝም። የእሚቀጥለው ወር ፒክቸር፤ ወዴት እየተጓዝን እንደሆነ፤ የተሻለ ምልከታ እንዲኖረን ይረዳን ይሆናል።

ቀመር ፩. ሪፖርት የተደረጉ የ ኮቪድ–19 ህሙማን (የዞረ ድምር): በ ፕላኔት ምድር
12/31/2019 – 03/31/2020




<u>ማስታወሻ</u>፡ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

የሆነው ሆኖ፤

የህክምና ሳይንስ፣ የኅብረተሰብ ጤና ሳይንስ እንዲሁም ተዛማጅ የተፈጥሮ ሳይንስ መስኮችን በተመለከተ፤ የበሽታ'ን ወይም በሽታ'ን የእሚያስከትል ረቂቅ ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል፤ በተወሰነ [ኅብረተሰብ - ጂኦግራፊ - ወቅት] የተሰራጨበት'ን ወይም ሊሰራጭ የእሚችልበት'ን [አቅም - መጠን - ደረጃ] የማስላቱ ስራ፤ እጅጉን ውስብስብ ነው። የውስብስብ ነገሮች ሁሉ፤ አንዱ የጋራ ባህሪያቸው ደሞ — እራሳቸውን ለመግለፅ እና ከተጠቃሚዎቻቸው ጋር በቀላሉ ለመግባባት ይረዳቸው ዘንድ፤ ዳጎስ-ዳጎስ የአሉ እና ብዙ ቁም-ነገሮችን የአዘሉ፣ ሙያ ዘመም እና መሪ ቃላት'ን የእሚጠቀሙ መሆናቸው ነው።

የ ወረርሽኝ ጉዳይ ሲነሳ'ም፤ ሌሎች – አንስቻቸው ቢሆን ኖሮ፤ ተጨማሪ ገላጭዕነት'ን የእሚቸሩ ቃላት መኖራቸው የተጠበቀ ሆኖ፤ በሙያው ቋንቋ [ኢንደሚክ፣ ኤፒደሚክ እና ፓንደሚክ] የእሚሉ ሦስት ቃላት ግን፤ አፍ-ሙሉ እና ብዙ-ብዙ የእሚያነጋሩ፤ አንድ'ን የጤና ችግር፤ እንደ እየአቅሙ፣ እንደ እየመጠኑ፣ እንደ እየደረጃው — ከ አልረፈደ፤ ፊት-ለመንሳት ለመከላከል፤ አልያም – እጅጉን ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ብዙ ጉዳት ከማድረሱ እና ብዙ ህይወት ከመጨርሱ በፊት፤ ለመገደብ፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት እንዲያስችል፤ ሊወሰዱ የእሚገባቸውን፤ ወሳኝ የእሚባሉ እርምጃዎች፤ በአግባቡ እና በጊዜው እንዲወሰዱ እንዲተገበሩ — የሃሳቦች ሁሉ ፊትአውራሪ በመሆን፤ ሙያተኞች'ን የእሚመሩ ቃላት በመሆናቸው፤ የዛሬዋ መጣጥፌ ትኩረት፤ በእነርሱ ዙሪያ እሚያጠነጥን ይሆናል።

ትርጓሜን እና አጠቃቀምን በተመለከተ፤

ኢንደሚክ፣ ኤፒደሚክ እና ፓንደሚክ የእሚሉት ቃላት፤ እንደ [ስም] ሲያገለግሉ — እንደ ተጋላጩ/ተጠቂው ሰው/ኅብረተሰብ ሁለፅንተናዊ ቁመና፣ እንደ በጥቃቱ ሳቢያ የእሚከሰተው በሽታ ስር ሊሰድ የእሚችልባቸው ውስብስብ መንገዶች፣ እንደ ጥቃቱን አድራሽ የሆነው ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል ሁለፅንተናዊ ቁመና፣ እንደ ጂኦግራፊው፣ እንደ ወቅቱ፤ ብሎም እንደ ተጓዳኝ እና ተዛማጅ ከባቢ ሁኔታዎች ምቹዕነት [ድምር ወይም ብዜት] ባህሪያት፤ አተረጓጎማቸው አጠቃቀማቸው ሊለያይ ይችላል። ኢጋዥ፤ ክሊኒካል፣ ጀነቲክ፣ ሞለኪውላር፣ ኤፒዲሚዮሎጂካል ወይም ስታቲስቲካል ሞዴልስ መኖራቸው'ም እንኳን የተጠበቀ ሆኖ። ኬዝ ፋይንዲንግ እና ኮንታክት ትሬሲንግ፤ እንደድሮው በአካል ወይም በመገናኛ መንገዶች ብቻ ሳይሆን፤ በ ጅን ሲኳንሲንግ ጭምርም የእሚታገዝበት ጊዜ ላይ መድረሳችን በጣም ድንቅ ነገር ነው።

ነገሮች'ን የበለጠ ውስብስብ ለማድረግ ደሞ፤ ከፍ ብዬ የአነሳኋቸው ሦስት ቃላት፤ በቀዳሚዕነት፤ የተላላፊ በሽታዎች ስርጭት አቅም - መጠን - ደረጃ'ን ጠቅሶ ለማመልከት የእሚውሉ ቢሆኑም ቅሉ — ተላላፊ ለአልሆኑ የጤና ችግሮች'ም ጭምር ያገለግላሉ። የ ኦቤሲቲ ኤፒደሚክ፣ የ ኦፒኦይድ ኤፒደሚክ፣ የ ክሮኒክ ድዚዝስ ፓንደሚክ፤ የእሚባል ነገር አለ።

ኢንደሚክ የእሚለው ቃል፤ አንድ የጤና ችግር – በተወሰነ [ጂኦግራፊ እና ኅብረተሰብ] ውስጥ፤ የእማያቋርጥ በሆነ መልኩ፣ በቋሚዕነት፣ አዘውትሮ የእሚከሰት መሆኑን የእሚጠቁም፤ መሪ ቃል ነው። በእንዲህ ዓይነቱ፤ "የተለመደ ነው" በእሚባልለት የጤና ችግር – የተጠቂ ሰዎች ቁጥር ብዛት፤ ሁለዕንተንዓዊ አግባበ-ነግሮችን ከእሚያገናዝብ ሙያዊ ግምት፤ "ብዙም" አይርቅም።

በአመዛኙ፤ ኢንደሚክ የጤና ችግሮች፤ ለእያንዳንዳቸው በተለይ [በዘመቻ መልክ ማለቴ ነው] የተዘጋጀ [የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት] መርሃ-ግብር እየተተገበረ በአልሆነበት ሁኔታ፤ የአካባቢው ንዋሪ በነፍስ-ወከፍም ሆነ እንደ ኅብረተሰብ፤ በተፈጥሮም ሆነ በሳይንስ ችሮታ፤ የአዳበረው የአጎለበተው [ኢንዲቪጅዋል አልያም ኸርድ ኢምዩኒቲ]፤ የተጋረጠበትን የጤና ችግር — ፊት-የመንሳት፣ የመገደብ፣ የመቋቋም ቁመና፤ የእሚፈለገው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሆኖ ከአልተገኘ፤ ማንአቸው'ም ኢንደሚክ የጤና ችግሮች፤ በእዚያ [ጂኦግራፊ እና ኅብረተሰብ] ውስጥ፤ ለዘመናት መልካቸውን ሳይቀይሩ እየተከሰቱ ይቀጥላሉ። አንድ በተላላፊ የጤና ችግር የተጠቃ ሰው፤ ህመሙን ወይም ህመሙ እንዲከሰት የእሚያደርገውን ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል፤ የእሚያስተላልፈው፣ የእሚያዘለው፣ የእሚያስፈነጥረው፣ የእሚያራባው፣ የእሚያሰራጨው፣ የእሚያዛምተው፣ የእሚያቀጣጥለው — <u>ለአንድ ሰው ብቻ</u> እስከሆነ ድረስ!

በ ሌላ በኩል፤

<u>ኤፒደሚክ የእሚለው ቃል</u>፤ አንድ [የታወቀ ወይም አዲስ የሆነ] የጤና ችግር፤ በተወሰነ [ጂኦግራፊ እና ኅብረተሰብ] ውስጥ — በድንገት እና በፍጥነት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ፤ ሁለዕንተንዓዊ አግባበ-ነግሮችን ከእሚያገናዝብ ሙያዊ ግምት በላይ የሆኑ ሰዎች'ን ሲያጠቃ — አንድ በተላላፊው የጤና ችግር የተጠቃ ሰው፤ ህመሙን ወይም ህመሙ እንዲከሰት የእሚያደርገውን ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል፤ የእሚያስተላልፈው፣ የእሚያዘለው፣ የእሚያስፈነጥረው፣ የእሚያራባው፣ የእሚያሰራጨው፣ የእሚያዛምተው፣ የእሚያቀጣጥለው፤ <u>ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች</u> መሆኑን እና ወደ ሌሎች አካባቢዎች'ም በፍጥነት የመተላለፍ ቁመና'ም እንደአለው እሚጠቁም መሪ ቃል ነው። ኤፒደሚክ የእሚለው'ን ቃል — [ወረርሽኝ] በእሚለው ኢትዮጵያዊ ቃል፤ ተክተን ስንጠቀም'ም፤ ዘመናት ተቆጥረዋል።

ለ ረዥም ጊዜ ሳይከሰት የቆየ፤ አልያም አዲስ እንግዳ የሆነ ተላላፊ የጤና ችግር ተከስቶ ሲገኝ፤ ተጠቂው [አንድ] ሰውም እንኳን ቢሆን፤ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እና ተገቢውን አፋጣኝ ሙያዓዊ እርምጃ ሊወሰድ የግድ ነው። ሌላ ተጨማሪ ሰው፤ በተመሳሳይ የጤና ችግር ተጠቅቶ ከተገኘ ደሞ፤ ኤፒደሚክ እንደሆነ ተቆጥሮ፤ ተገቢውን የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት እርምጃዎች ተግባርዓዊ መደረግ ይገባቸው አለ። ቁጥርን በተመለከተ፤ እንድን ኤፒደሚክ — ኤፒደሚክ እንዲባል የእሚያበቃው የተጠቂ ሰዎች ቁጥር፤ እንደ ሁለዕንተንዓዊ ተጨባጭ ሁኔታው ይለያያል። እንደ ጥቃቱን የአደረሰው ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል ምንዕነት፣ እንደ ተጠቂ የሆነው ሰው/ኅብረተሰብ ብዛት እና የጤና ችግሩን ፊት-የመንሳት፣ የመከላከል፣ የመገደብ፣ የመቋቋም ቁመና፣ እንደ ኅብረተሰቡ ከእዚህ ቀደም በእዚህ ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል ተጠቅቶ የእሚያውቅ ወይም የእማያውቅ መሆኑ፤ ብሎም — እንደ የጤና ችግሩ የተከሰተበት ጂኦግራፊ እና ወቅት ጭምር'ም ማለቴ ነው።

አዎ፤ አንድ ከሰው–ወደ–ሰው ወይም ከእንስሳ–ወደ–ሰው የእሚተላለፍ የጤና ችግር፤ ኤፒደሚክ ደረጃ የእሚደርሰው፤ የጤና ችግር የእሚያስከትል ህዋስ ወይም የህዋሱ ተሸካሚ እንስሳ [እና] ፊት-የመንሳት፣ የመከላከል፣ የመገደብ፣ የመቋቋም ቁመና የሌለው ሰው/ኅብረተሰብ፤ በቂ በሆነ ቁጥር፣ በአመቺ ኢንቫይሮንመንት፣ ጂኦግራፊ እና ወቅት፤ አብረው የተገኙ ሲሆን ነው። እንዲህ ዓይነት ህመም ወይም ህዋስ በቅድሚያ ከተጠቃው ሰው ወደ ሌላ ሰው የእሚተላፍባቸው፣ የእሚዘልእባቸው፣ የእሚስፈነጥርባቸው፣ የእሚራባባቸው፣ የእሚሰራጭባቸው፣ የእሚዛመትባቸው ወይም የእሚቀጣጠልባቸው መንገዶች — አመቺ፣ ብዙ እና ውስብስብ ሆነው ሲገኙ፤ [መረር እና ሰፋ] የአለ "ወረርሽኝ" የ መከሰቱ'ን ፕሮባቢሊቲ ከፍ ያደርገዋል።

ያ–ም፤ በ የአለፉት ሦስት–አራት ወራት ገደማ፤ እየተቀጣጠለ የአለው፤ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 በእሚል የተጠራው ቫይረስ እሚያስከትለው ኮቪድ–19 — በአንድ አካባቢ ብቻ ተወስኖ የነበረው ወረርሽኝ፤ <u>መረር እና ሰፋ</u> ብሎ [አንታርክቲካን ሳይጨምር] የቀሩትን አህጉራት በሙሉ ማዳረሱን ሰበብ አድርጌ፤ ሰሞኑን በተደጋጋሚ ወደ እሚጠቀሰው፤ መሪ ቃል እሸጋገር አለሁ። ትክክል – "ፓንደሚክ" ወደ እሚለው መሪ ቃል!

<u>ፓንደሚክ ማለት፤</u> በተወሰነ አካባቢ ከመከሰት አልፎ፤ [<u>ሰፊ</u>] ጂኦግራፊ እና ኅብረተስብ [በአንድ ሃገር ውስጥ ብቻም ቢሆን] ወይም ብዙ ሀገራትን ወይም ብዙ አህጉራትን የሸፈነ፣ በፍጥነት የመተላለፍ፣ የመዝለል፣ የመስፈንጠር፣ የመራባት፣ የመሰራጨት፣ የመዛመት ወይም የመቀጣጠል [አቅም ብቃት] የአለው፤ ተየህ በፊት የታወቀ ወይም አዲስ የሆነ — ኤፒደሚክ ማለት ነው። ኤፒደሚክ'ን፤ ውብ በሆነ ቋንቋ [ወረርሽኝ] ብለን ከጠራ'ን — ፓንደሚክ የእሚለው'ን መሪ ቃል ደሞ፤ አንድ ሃገር ውስጥ ብቻ በሰፊው ሲቀጣጠል [ሃገር–አቀፍ ወረርሽኝ] በአንድ ኮንቲነንት ውስጥ ወደ ብዙ ሃገራት ከተቀጣጠለ ደሞ [አህጉር–አቀፍ ወረርሽኝ] ወይም ወደ ብዙ/ሁሉም አህጉራት የተቀጣጠለ መሆኑ ሲረጋገጥ [ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ] በእሚል ኢትዮጵያዊ ሃረግ መጥራት እንችላለን።

እንደ እየአግባበ–ነገሩ፤ አሻሚ የሆነ አተገባበር ሊኖረው የመቻሉ ዕውነታ የተጠበቀ ሆኖ፤ ሰሞኑን እየበጠበጠን የአለው ኮቪድ–19 በመባል የተጠራው በሽታ፤ እንደአጀማመሩ – በአንድ በተወሰነ ጂኦግራፊ እና ኅብረተሰብ ውስጥ፤ ሁለዕንተንዓዊ አግባበ-ነግሮችን ከእሚያገናዝብ ሙያዊ ግምት በላይ የሆኑ ሰዎች'ን በፍጥነት በማጥቃት፤ እንደ [ኤፒደሚክ]፤ ይቅርታ – እንደ [ወረርሽኝ] ተከስቶ ሲያበቃ፤

ሀ) በሰፊው እና በፍጥነት፤ ከሰው–ወደ–ሰው በመተላለፍ፣ በመዝለል፣ በመስፈንጠር፣ በመራባት፣

በመሰራጨት፣ በመዛመት፣ ወይም በመቀጣጠል፤ በሁሉም አህጉራት ሪፖርት መደረግ በመጀመሩ፤

ለ) በአጭር ጊዜ ውስጥ፤ እጅግ ብዙ ሰዎች፤ በቫይረሱ መያዛቸው ብሎም አንዳንዶቹ፤ ህመሙን መቋቋም ተስኗቸው እየአለፉ በመሆኑ እና

ሐ) የጤና ተቋሞቻችን'ም ሆነ የወል ኅብረተሰባዊ የህይወት ቁመናችን፤ ቻሌንጁን መመከት ተስኖት ኮላፕስ ሊያደርግ የእሚችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ፤

ኮቪድ–19 እየአስከተለ የአለው ሁለዕንተንዓዊ <u>ሰውዓዊ</u> (ኅብረተሰብዓዊ፣ ምጣኔሃብትዓዊ፣ ፖለቲከዓዊ) ቀውስ [ፓንደሚክ] ደረጃ ላይ፤ ይቅርታ – [ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ] ደረጃ ላይ መድረሱን ተገንዝበናል። በ ማርች 11 ይኼንኑ ዜና፤ ከ ዓለም ጤና ድርጅት'ም ጭምር ሰምተናል ።

አንዴ ልድገመው። ኢንደሚክ፣ ኤፒደሚክ እና ፓንደሚክ — መሪ ቃላት ናቸው የአልኩት፤ የአንድን የጤና ችግር አስከፊዕነት ደረጃ ስለእሚጠቁሙ ብቻ አይደለም።

ከእዚያም አልፈው፤ ሊወሰዱ የእሚገባቸውን፤ የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት እርምጃዎችን ተግባርዓዊዕነት ለማጎልበት እና ለማሳለጥ — ሊንቀሳቀስ፣ ሊተም የእሚገባውን የ[ሰው፣ የኢኮኖሚ እና የቁሳቁስ] እሴቶችን አቅርቦት፤ የ ዓለም-አቀፍ ተቋማት'ን፣ መንግስታት'ን፣ ፖለቲከኞች'ን፤ ብሎም የሙያተኞች'ን ቀና ስብዕና፣ የማኅበረሰቡ'ን እና ሌሎች በሃላፊዕነት ቦታ ላይ የተቀመጡ ሰዎችን ሁሉ፤ [ልዩ፣ የአልተቆጠበ እና ፈጣን] ትኩረት'ን ለማግኘት እንዲቻል — ምን አለፋችሁ፤ ሊፈጠር የእሚገባው'ን ፍፁምዓዊ [ሴንስ ኦፍ ኧርጀንሲ] በሁሉም ዘንድ እንዲሰርፅ ለማስገደድ የእሚያስችል፤ ዕምቅ ኢነርጂ ስለ አላቸውም ጭምር እንጂ!

ለመሆኑ፤ ኮሮናቫይረስ ድዚዝ 2019 (ኮቪድ–19) ምንድር ነው?

ኮሮናቫይረስ ድዚዝ 2019 (ኮቪድ–19)፤ ከሰው-ወደ-ሰው የእሚተላለፍ – የመተንፈሻ አካላት በሽታ ነው። ኮቪድ–19'ን የእሚያስከትለው ህዋስ ወይም ቫይራል ፓርቲክል ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 በመባል ይታወቃል። የ ኮቪድ–19 ምልክቶች'ን አንድ ሁለት ሶስት በእሚል ማስፈሩ፤ አስቸጋሪ ነው። በአጠቃላይ ግን፤ ከ ቀላል እስከ ከባድ እሚባል ደረጃ ሊደርስ የ እሚችል፤ እንደ የተለመደው ዓይነት “ጉንፋን” መሰል ምልክቶች'ን፤ ሊያካትት ይችላል። ትኩሳት፣ ሳል፣ የትንፋሽ እጥረት'ን እና የመሳሰሉትን ጨምሮ ማለቴ ነው። በሽታው እየተባባሰ ከሄደ፤ ኒሞንያ፣ የተለያዩ የአካልዓችን ክፍሎች በተገቢው መልኩ ስራ መስራት አለመቻል'ን እና መረር ሲል'ም፤ እስከ ህይወት ማለፍ ድረስ የሚያደርስ ችግር ሊፈጥር ይችላል።

እናስ፤ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ምንድር ነው?

ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ከ ሰዓታት እስከ ቀናት፤ በአየር ላይ እና በ እየአረፈበት ቦታ ሁሉ የመቆየት ችሎታ የአለው፣ የውጭ ዙሪያ–ሽፋን ከአላቸው [አርኤንኤ] ኮሮናቫይረሶች ውስጥ አንዱ ነው። ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ከውጭ ዙሪያ–ሽፋኑ አካል፤ ከ ሦስት የተለያዩ ፕሮቲኖች የእሚሰሩ፤ [ስፓይክ] የእሚባሉ አጫጭር [ችፍርግ ወይም ዛላ] መሰል ነገሮች አሉት። ከእነእዚህ ችፍርግ ወይም ዛላ መሰል ፕሮቲኖች አንዱ ናት እንግዲህ፤ [እንደ ዕድሜ ጠገቡ የኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ] ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2'ም በእየሰውዕነታችን ሴሎች ላይ እንዲጣበቅ እና ሰርስሮ በመግባት፤ የኢንፌክሽን ሂደቱን እንዲጀምር የምታደርገው። የ ቫክሲን ፈጠራው ትኩረት'ም፤ በዋናዕነት ታርጌት የሚያደርገው የቫይረሱ ክፍል፤ አሁን የአልኳቸውን አጫጭር ችፍርግ ወይም ዛላ መሰል ፕሮቲኖችን፤ ነው የእሚሆነው።

ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 የሰው አካላት ሴሎች ላይ ለመጣበቅ ብሎም ሰርስሮ ለመግባት [እራሱን የእሚያራባው እዚያ ውስጥ ስለሆነ] እንደ አጋር የእሚጠቀመው፤ አንጂዮቴንሲን ኮንቨርቴንግ ኢንዛይም–2 (ኤሲኢ–2) የእሚባል ሪሰፕተር ሞለኪውልን ነው። እነእኝህ፤ ኤሲኢ–2 የእሚባሉ ሪሰፕተር ሞለኪውሎች፤ ከእሚገኙባቸው ሴሎቻችን መካከል'ም በዋናዕነት – ሬስፓይሬቶሪ ሴልስ የእሚባሉት ናቸው። ሳይንሱ እንደ እሚለው፤ ኤሲኢ–2 ሪሴፕተር ሞለኪውሎች የእሚገኙት፤ በ የሰው ሬስፓይሬቶሪ ሴልስ ላይ ብቻ ሳይሆን፤ በ ሆድ–ዕቃ፣ ትንሹ አንጀት፣ ትልቁ አንጀት እና በሌላም ብዙ የካላችን ክፍሎች ሴሎች ላይ'ም ጭምር ነው።

ተየህ ቀደም፤ የሰው ልጆችን እንደ እሚያጠቁ የታወቀላቸው፤ ስድስት የኮሮናቫይረስ ዝርያዎች አሉ። አዲሱ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 እንግዲህ ሰባተኛው መሆኑ ነው። ሳርስ-ኮሮናቫይረስ፣ መርስ-ኮሮናቫይረስ እና ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ለህይወት አስጊ የሆነ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የእሚደርስ በሽታን ያስከትላሉ። ሌሎቹ — ኤችኪዩ1፣ ኤንኤል63፣ ኦሲ43 እና 229ኢ የእሚባሉት፤ በአመዛኙ ቀለል ከአሉ የህመም ምልክቶች ጋር ነው የ እሚጎዳኙት።

የተወሰኑ ነጥቦች ላይ ትንሽ እንድጨምር ፍቀድሉኝ፤

ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ከ መሰል ኮሮናቫይረስ፤ በላቦራቶሪ ውስጥ [ሆን ተብሎም ሆነ አልሆነ] ማኒፒውሌት ተደርጎ የተፈጠረ “ነው” የእሚል ሃሣብ እንደ አለ አይቼ አለሁ። ይህ ጉዳይ፤ ምንም እንኳን ገና የአልየለት እና ጥናትን የእሚጠይቅ ቢሆንም ቅሉ፤ ሳይንስ–ዓምላኩ የሆኑ፤ ለሙያው ቀረቤታ የአላቸው ሞለኪውላር ባዮሎጂስቶች፤ እርግጠኛ ሊያደርጋቸው የእሚችል ተጨባጭ ሳይንስዓዊ መረጃ የሌለ እንደሆነ፤ እየተናገሩ እየፃፉ ናቸው። የ እየ እራሳቸው የሆኑ ግምቶች አንደ አሏቸው'ም ሳይሸሽጉ።

<u>አንድ</u> — የሆነ የ ኮሮናቫይረስ ዝርያ፤ በእንስሳት ውስጥ እንደአለ፤ በህይወት ለመቆየት በእሚያደርገው ጥረት፤ የዘረመል ለውጥ በማድረግ፤ ወደ ሰው ከመተላለፉ በፊት፤ ወደ አዲሱ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ሊለወጥ ችሎ ይሆናል የእሚል [ግምት] አለ። ኮቪድ–19 ከአንድ የእንስሳት ገበያ ጋር በመገናኘቱ እና፣ የእዚህ ቫይረስ መሰል ዝርያዎች፤ የሌሊት ወፍ ወይም ሌላ እንስሳት'ን እንደ ሪዘርቧየር ስለእሚጠቀሙ፤ ከእንስሳት–ወደ–ሰው የተላለፈ በሽታ ሊሆን ይችላል፤ የ እሚል ሃሣብ ይንሸራሸራል። ነገር ግን፤ ከ የሌሊት ወፍ እና አንድ ሌላ እንስሳ የተገኘው የ ኮሮናቫይረስ ዝርያ ከ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ጋር የተቀራረበ ቢሆንም ቅሉ፤ አንድ–አንድ ተፃራሪ የሆነ

ገፀባህሪው፤ ከእንስሳ–ወደ–ሰው ሊተላለፍ ይችላል የእሚለውን ግምት፤ ፉርሽ ያደርገዋል – ይላሉ፤ ተመራማሪዎቹ።

ሁለት — የሆነ የ ኮሮናቫይረስ ዝርያ፤ ቀደም ሲል ከእንስሳ–ወደ–ሰው ከተላለፈ በኋላ፤ በህይወት ለመቆየት በእሚያደርገው ጥረት፤ [በ ሰው ውስጥ እየአለ እና ከሰው–ወደ–ሰው ሳይነቃበት እየተላለፈ የቆየ ሆኖ] ከረዥም ጊዜ በኋላ በ ሰው ውስጥ፤ የዘረመል ለውጥ በማድረግ፤ አዲሱ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ሊፈጠር ችሎ ይሆናል፤ የ እሚል'ም ሃሳብ አለ። ይህም የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ሪዘርቧየር [ሰው] ሊሆን ይችላል ወደ የእሚል ሃሳብ ያዘማል።

አንድ ተላላላፊ የጤና ችግር፤ ከእንስሳት–ወደ–ሰው ወይም ከሰው–ወደ–ሰው የእሚተላለፍ መሆኑን በእርግጠኛዕነት የማወቁ ጠቀሜታ፤ አሉባልታን ለማጥራት ሳይሆን — ለ ሳይንሳዊ ጥናት እና ምርምር፤ ብሎም የበሽታ አምጪ ህዋሳትን ወይም ቫይራል ፓርቲክሎችን ስርጭትን'ም ሆነ በሽታ'ን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት፤ የእሚቻልባቸውን መንገዶች ለይቶ ለማወቅ ወሳኝ በመሆኑ ነው – ወደፊት ኢ-መርጅ ሊያደርግ መቻሉ አለመቻሉንም ጭምር ለመረዳት።

የሆነስ ሆነ እና፤ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 እነማን'ን ነው የእሚያጠቃው?

ልብ እንበል ጎበዝ፤ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 [የሰው ልጅ] የሆነን ሁሉ ሊያጠቃ ይችላል — የእድሜ፣ የፆታ፣ የጎሣ፣ የጎጥ፣ የሃይማኖት፣ ወይም የአቋም/የሃሳብ ልዩዕነት የአላቸው ሰዎች በእሚል፤ አያዳላም። ከሰው–ወደ–ሰው ስለእሚተላለፍም፤ የአገኘውን ሁሉ በቀላሉ ይበክላል።

የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 መተላለፊያ መንገዶች፤ በዋናዕነት ሀ) በ እምንስልበት ወይም በ እምናስነጥስበት ጊዜ፤ ከ ምራቅ ወይም ከ አፍንጫችን ውስጥ በእሚረጩ በእሚስፈነጠሩ ጥቃቃን እርጥብ–ብናኞች፤ በቀጥታ ወደ ሌላ ሰው መተንፈሻ አካላት የደርሱ ሲሆን፤ ለ) ከ ሳል ወይም ከ ማስነጠስ ጋር የ እሚረጩት የእሚስፈነጠሩት ጥቃቃን እርጥብ–ብናኞች፤ በቀጥታ'ም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ በእሚያርፉባቸው የሰውዕነት አካል'ም ሆነ ማናቸውም በእጅ ሊነኩ የእሚችሉ ነገሮችን ከነኩ በኋላ፤ እጅን በእሚገባ ሳይታጠቡ ሳያፀዱ፤ ፊትን አፍንጫን እና ዓይንን የነካካን እደሆን እና ሐ) ከዓይነ–ምድር ጋር በቀጣትም ሆነ በተዘዋዋሪ በመነካካት፤ የ ቫይረስ ፓርቲክሉ ከእጅ ወደ አፍ ሊተላለፍ ሲችልም ነው። ለ እንደ እኛ የአለ ኅብረተሰብ ይህ በ ዝርዝር "ሐ" ላይ የጠቀስኩት ሦስተኛው የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 የመተላለፊያ መንገድ ገና ብዙ ጥናትን የ እሚጠይቅ ቢሆንም፤ እጅጉን አሳሳቢ ሆኖ መታየት ይኖርበታል። ቀደም ብዬ፤ ስለ ኤሲኢ–2 ሪሴፕተር ሞለኪውሎች፤ በሰው አካል ሴሎች ላይ የት–የት እንደእሚገኙ ጠቆም አድርጌ አለሁ።

አንድ በ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 የተያዘ ሰው፤ እስከ አስራ–አራት ቀናት [በአማካይ ወደ አምስት ቀናት] በሆነ ጊዜ ውስጥ፤ ምልክቶችን ማሳየት ይጀምራል። ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ፤ የግድ የህመም ምልክቶች ሊታዩበት ይገባል የእሚባል ነገር የለም። ሆኖም፤ ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፍ ፕሮባቢሊቲ እጅጉን ከፍ የእሚለው፤ ምልክት ማሳየት በጀመሩ ሰዎች ላይ ነው።

ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 አዲስ ቫይረስ በመሆኑ፤ ማንኣችንም ቫይረሱን [ፊት–ለመንሳት፣ ለመከላከል፣ ለመገደብ ወይም በቀላሉ ለመቋቋም] የእሚያስችል ኢምዩኒቲ የለንም። [አለን ተብሎ አይገመትም — ማለት ሳይሻል አይቀርም]። ሰሞኑን፤ የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 አንቲቦዲ የአላቸው ሰዎችን ፍለጋ ተጀምሯል እና የእሚሆነውን ማየት ነው። መጥፎው ነገር፤ አንቲቦዲ ቢገኝም እንኳን፤ በጣም ኮምፕሌክስ ፕሮሰሶችን ማለፍ ስለእሚኖርበት እና ውድ ስለእሚሆን፤ የቫክሲንን ያህል – ብዙም ለ ኅብረተሰቡ የእሚጠቅም ኢኖቬሽን ነው ማለት አያስደፍርም። እናም፤ ለ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 የተጋለጠ ማናቸውም ሰው፤ ኮቪድ–19 እንደሚይዘው ለአፍታም እንኳን መጠራጠር አይጠቅምም። በተለይ፤ በእድሜ የገፉ እናም የተለያዩ ክሮኒክ በችታዎች የአሉባቸው ሰዎች፣ በብዙ መልኩ በሽታው ስለእሚጠናባቸው እና ምናልባትም፤ ህይወታቸው'ን ሊያጡ ስለእሚችሉ፤ ለየት የአለ ትኩረት እና እንክብካቤ ሊደረግላቸው የግድ ይላል።

የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ስርጭትን ለመከላከል፣ ለመግታት፣ ለመቆጣጠርም ሆነ ለማጥፋት፤ ምን እየተደረገ ነው?

አስከ ዛሬ ድረስ፤ የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ስርጭት'ን የእሚገድብ፤ ከትባትም ሆነ [አንዳንድ ምልክቶችን ለማስታገስ ሊወሰዱ ከእሚችሉት በስተቀር] ቫይረሱን በመግደል ፈውስን የእሚያስገኝ መድሃኒት የለም። በሙከራ ላይ የአሉ ግን ብዙ አሉ — ተስፋ እንዳትቆርጡ!

አናም፤ ሁልአችንም የአለን ብቸኛ አማራጭ፤ እራስን መከላከል እና እራስን መከላከል ብቻ ነው።

ከታመሙ ሰዎች ጋር በአካል ንክኪ አታድርጉ። እጅአችሁን የጤና ባለሙያዎች በእሚመክሯችሁ አግባብ ሳትታጠቡ ሳታፀዱ – ዓይንአችሁን፣ አፍንጫችሁን ወይም አፋችሁን በፍፁም አትንኩ። እጃችሁን በተደጋጋሚ በሳሙና እና በውሃ ለ 20 ሰኮንዶች ያህል በደንብ እያሻችሁ ታጠቡ። ከ60% የአላነሰ አልኮሆል የተደባለቀበት የእጅ ማፅጃ [ሳኒታይዘር] የ እምታገኙ ከሆነ'ም፤ እሱን መጠቀሙ ይበጃል። የደረቀ እና የፈሳሸ ቆሻሻዎችን በጥንቃቄ አስወግዱ። የግል ንፅህናችሁ ላይ ትኩረት አድርጉ። እነኚህን እራስን የመከላከያ መንገዶች'ን የሰማችሁ ከልብአችሁ እንድትተገብሩት፤ ለአልሰሙት'ም ሁሉ እንድታዳርሱ አደራዬ ከምን ጊዜዉም በላይ የጠበቀ ነው! አደራ! አደራ! አደራ!

አንድ ነገር ልጨምር፤ በችግርም ላይ ሆነን ጥናት እና ምርምር ከማድርግ መቆጠብ የለብንም — ፕራዮሪታይዜሽን'ን ፈር በእማያስለቅቅ መልኩ። የባህልም ሆነ የዘመናዊ መድሃኒቶች ላይ የእሚደረግ ጥናት እና ምርምር፤ ምን ጊዜም ቢሆን መቋረጥ የለበትም። ዋናው ነገር፤ ጥናት እና ምርምሮች ሳይንሳዊ ፕሮቶኮል እና ኤቲክስ'ን የጠበቁ መሆናቸውን እርግጥኞች መሆኑ ላይ ነው።

አይበለው እና፤ በቫይረሱ የመጠቃት ነገር ሲመጣ'ስ ምን ማድረግ ይቻላል?

ማናቸውም በቫይረሱ የተጠቃ መሆኑ የተረጋገጠ ሰው ወይም ምርመራ ማድረግ ሳይቻል ቀርቶ አንድ አንድ ምልክቶችን ማሳየት የጀመረ ሰው፤ ከ ማንአቸውም ሰው እርቆ – እቤቱ ውስጥ መቆየት ይጠበቅበታል። ሲያስልም ሆነ ሲያስነጥስ፣ በ ተገኘው ነገር አፍ እና አፍንጫን መሸፈን የግድ ነው። እራስንም ሆነ ማንአቸውንም በእጅ ሊነኩ የእሚችሉ ነገሮች'ን ሁሉ፤ በተገቢው ሁኔታ ማፅዳት፤ እጅጉን ወሳኝ ነው።

አዎ፤ ከ ወደ እሩቅ–ምሥራቅ የጀመረ፤ የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ወረርሽኝ፤ ከሦስት ወራት በአልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤ ሁሉንም አህጉራት የአዳረሰ መሆኑ'ን አይተናል ሰምተናል። እስከ ፌብሪዌሪ መጨረሻ ድረስ፤ የህመም ምልክት ታይቶባቸው – የቫይረሱ ምርመራ ከተደረገላቸው መካከል፤ በቫይረሱ የተያዙ መሆኑ ተረጋግጦ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን፤ ሙሉ በሙሉ ከ ኤዥያ ነው (ቀመር ፪) — የ ወረርሽኙ [ፔሽንት ዚሮ] ተከስቶባታል በእሚል የተጠረጠረችዋን፤ ቻይናን ጨምሮ።


አውሮጳ ማርች ሲገባ የጀመረች፤ እስከ ዛሬ ድረስ ከሌሎች አህጉራት በጣም በበለጠ መጠን፤ በቫይረሱ እንደተያዙ የተረጋገጠባቸው ህሙማን'ን በእየዕለቱ ሪፖርት እየአደረገች ትገኛለች። በአለፉት ሁለት–ሦስት–ቀናት ትንሽ'ም ቢሆን የመቀነስ ምልክት ማሳየት መጀመሯን ማየት ይቻላል። እንዲህ ዓይነት ክስተቶች ራንደም ቫሪዬሽን ከመሆን አልፈው፤ እየተወሰደ የአለው የ መከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃ የአመጣው ውጤት ነው ለማለት እቸገራለሁ።

አሜሪካ'ም፤ [በነገራችን ላይ ሰሜን አሜሪካ'ን፣ ደቡብ አሜሪካ'ን፣ ካናዳ'ን እናም ሊሎች ቴሪቶሪዎች'ንም ያካትታል] አውሮጳ'ን ተከትላ፤ ሌላዋ በ ከፍተኛ ቁጥር በቫይረሱ እንደተያዙ የተረጋገጡ ህሙማን'ን ሪፖርት እየአደረገች የአለች አህጉር ናት።

የቀሩት አህጉራት፤ በአንፃራዊ መልኩ፤ ሪፖርት የእሚያደረጉት፤ በቫይረሱ እንደተያዙ የተረጋገጠባቸው ህሙማን ቁጥር፤ በጣም አነስተኛ ነው። ለእዚያም፤ ሊጠቀሱ የ እሚችሉ አያሌ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም ቅሉ፤ በዋናዕነት – የላቦራቶሪ ምርመራው በኅብረተሰቡ ውስጥ በሰፊው ሳይደረግ በመቅረቱ ሊሆን ይችላል የሚለው አመክንዮ፤ የበለጠ አሳማኝ ይመስላል። እንደ የ እሚታወቀው አንድ–አንድ ሃገራት፤ ስክሪኒንግ እንኳን የ እሚያደርጉት ከውጭ በእሚገቡ ሰዎች ላይ ብቻ እንደሆነ የታወቀ ነው።

በነገርአችን ላይ፤ ሰው ሁሉ መንቀሳቀስ በማቆሙ እና የ ላቦራቶሪ ምርመራ ለማድረግ የእሚያስፈልገው ስፔስመን የእሚወሰደው በ ጤና ባለሙያ በመሆኑ፤ የ ሳርስ–ኮሮናቫይረስ–2 ቴስት'ን በኅብረተሰቡ ውስጥ በሰፊው ለማዳረስ ትልቅ ችግር ሆኗል። ገና በ እሚመለከተው አውቶሪቲ ፈቃድ አላገኙም እንጂ፤ [አት–ሆም ቴስት ኪትስ] ገበያውን ለማጣበብ አኮብኩበው እየተጠባበቁ ናቸው። ጥቅም ላይ ሲውሉ፤ ማንአቸውም ሰው ስፔስመኑን እራሱ ወስዶ ወደላቦራቶሪ በመላክ፤ በቫይረሱ መያዝ አለመያዙን ማወቅ ይችላል። ይህ ተስፋ የእሚሰጥ ኢኖቬሽን ሆኖ ሳለ ተገቢው'ን ፈቃድ አስኪያገኝ ድረስ ግን፤ ጊዜ ሊወስድ ይችላል እና — አሁን እየአደረግነው ለ አለነው ግብግብ፤ ሊያግዘን የ እሚደርስልን አልመስልህ እያለኝ ነው።

ቀመር ፪. ሪፖርት የተደረጉ የ ኮቪድ–19 ህሙማን (የ እየ ዕለቱ): በ አህጉር
12/31/2019 – 03/31/2020





ማስታወሻ: በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶች በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ከፌብሪዌሪ የመጀመሪያው ሳምንት በኋላ፤ ከ ኤዥያ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ቁጠር የቀነሰ የመሰለበት ምክንያት፤ ቻይና ወረርሽኙ የተቀሰቀሰባትን ከተማ በ ጃኒዌሪ 23 ጀምራ ሲሪየስ የሆነ ሽትዳውን ተግባራዊ በማድረጓ ነው ተብሎ ይገመታል — የቫይረሱን ስርጭት በቅጡ ሊቀንሰው በመቻሉ።

ይህም፤ ወረርሽኙ ዘግየት ብሎ የተቀጣጠለባቸው ሃገራት፤ ተመሳሳይ እርምጃ መውሰድ እንደ አለባቸው፤ ትምህርት የሆናቸው ይመስላል። ዛሬ ብዙ ኬዞችን ሪፖርት ማድረግ የአልጀመሩ ሃገራትም ቢሆን፤ ለእኔ ብለው በመስማት አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ቀመር ፫. ሪፖርት የተደረጉ የ ኮቪድ–19 ህሙማን (የ እየ ዕለቱ): በ አፍሪቃ
12/31/2019 – 03/31/2020




ማስታወሻ፡ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ጥሬ ዳታውን የወሰደኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በ አፍሪቃ፤ በ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 እንደተያዙ ተረጋግጦ — በእየዕለቱ ሪፖርት እየተደረጉ የአሉት የህሙማን ቁጥሮች፤ ከሌሎች አህጉራት ጋር ሲነፃፀር፤ አነስተኛ ነው። (ቀመር ፫) ያ–ም ሆኖ ግን፤ ወደ ማርች አጋማሽ ጀምሮ፤ በፍጥነት እየጨመረ እንደሄደ ማየት ይቻላል። ቀደም ብዬ እንደአልኩት፤ ቁጥሮቹ አነስተኛ መሆናቸው፤ የላቦራቶሪ ምርመራው በ ኅብረተሰቡ ውስጥ በሰፊው ሳይደረግ በመቅረቱ ሊሆን መቻሉ የተጠበቀ ሆኖ — በፍጥነት እየአሻቀበ የሄደበት ምክንያት፤ ቫይረሱን [አይደንቲፋይ] ለማድረግ የእሚችሉ ላቦራቶሪዎች በርካታ እየሆኑ ስለመጡ'ም ይመስለኛል። የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ወረርሽኝ የጀመረ ሰሞን፤ በአፍሪቃ — ቫይረሱን በላቦራቶሪ ማረጋገጥ የእሚችሉ ሃገራት ቁጥር፤ ሁለት ብቻ ነበሩ። ዛሬ ቢያንስ አርባ–ሰባት ሃገራት ያ–ን የማድረግ አቅም አላቸው። እየአንድ አንዱ ሃገር አለው የተባለው አቅም ምን ያህል በቂ የሚባል መሆኑ የ እሚያሰጋኝ ቢሆንም፤ ጥሩ ዜና ነው!

አንድ ሰው በቫይረሱ ከተያዘ በኋላ ምልክት ማሳየት እስከእሚጀምርበት ጊዜ ድረስ፤ ወደ 14 ቀናት ገደማ ሊወስድ ይችላል፡ በ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 እንደተያዙ ተረጋግጦ ሪፖርት የተደረጉ ሰዎች፤ በ ቫይረሱ የተያዙበት ቀን'ም ሆነ ምልክት ማሳየት የጀመሩበት ቀን፤ በ ቀመሩ ላይ እንደምታዩት ሳይሆን፤ ቢያንስ ከ 7 ቀናት እስከ አስራ–አራት ቀናት፤ ቀደም ብሎ ነው የእሚሆነው። አስፈሪው ነገር፤ ምልክት ከማሳየታቸው በፊት እና አይዞሌት ከመደረጋቸው በፊት፤ ቫይረሱን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ስለ እሚችሉ፤ የመመርመር ዕድሉን ብዙ ሰዎች አግኝተው ቢሆን ኖሮ፤ አሁን ሪፖርት እየተደረገ ከአለው ቁጥር እጅጉን የበለጠ ሰው በቫይረሱ እንደተያዘ እና ምናልባትም፤ በአፍሪቃ ከ ፌብሪዌሪ አጋማሽ ጀምሮ እንደተከሰተ ማየት ይቻል ነበር ብዬ እገምት አለሁ።

ኅበዝ፤

የህዝብ ብዛት ፈጣን ዕድገት፣ በአስፈሪ ሁኔታ እየበዛ የመጣው የሰዎች [ከቦታ-ቦታ ከሃገር-ሃገር ከአህጉር-አህጉር] መዘዋወር፣ የደኖች ምንጠራ፣ የሰዎች ከአልተለመዱ እንስሳት ጋር ንክኪ መፍጠር፣ ክላይሜት ቼንጅ፣ የሶሽያል-የኢኮኖሚ-የፖለቲካ አለመረጋት፣ ፖቨርቲ አናም በ [ተደራሽዕነት-አቅርቦት-ከአቅም በላይ በአለመሆን-በጥራት እና በብቃት] የኀለበቱ የጤና ተቋማት በአለመኖር ሳቢያ — አፍሪቃ ውስጥ የአለው ኅብረተሰብ፣ መጀመሪያውንም ቢሆን፤ በብዙ የጤና ችግሮች የተጠቃ፤ የተጎሳቀለ፣ የተዳከመ እንደሆነ መካድ አይቻልም።

እንደ ኮቪድ–19 የአሉ አዳዲስ የጤና ችግሮች'ን የእሚያስተናግድበት ቁመና የሌለው መሆኑ'ም፤ ሳይታለም የተፈታ ነው። በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ – የእሚለው የሃገሬ ሰው፤ እንዲህ የአለ የቸገረ ነገር ሲገጥመው ነው። እናም፤ ደግሜ ደግሜ ደጋግሜ አደራ የእምለው – እስከ ዛሬ ሪፖርት የተደረጉትን ቁጥሮች፤ ለመዘናጊያ ሰበብ ወይም ምክንያት አድርገን ልንጠቀምባቸው እንዳንሞክር ነው። በፍፁም!

ምን እንዳይቀርብን ነው። በእዚህ ገጠመኝ፤ የሃገራችን'ን የጤና ተቋማት ሁለዕንተንዓዊ ቁመና፣ ከፍተኛ ገቢ መፍጠር ከቻሉት ሃገራት ተርታ እንዲደርሱ የቻልነውን ያህል ብንሞክር፤ ኮቪድ–19 ዛሬ ከአለበት ደረጃ ከፍ ሳይል ቢጠፋም እንኳን፤ የአጎለበትነውን አቅም ሌሎች [ተላላፊ ሆኑም አልሆኑም] ለዘመናት ተሸክመናቸው የአሉትን የጤና ችግሮቻችን'ን

ለማቃለል እና የ ኢመርጀንሲ ፕሪፔርድነስ ቁመናችንን ልናጎለብት እንችል ዘንድ— ኦፖርቹኒቲውን ያመቻችልናል።

ዛሬ የሰው ልጅ የገጠመው ፈተና፤ ከቅርብ ገጠመኞቻችን የከፋ ነው። ሳርስ፣ ስዋይን ፍሉ፣ ኢቦላ፣ ዚካ፣ እናም የአሁኑ ኮቪድ–19 በአለፉት [ሃያ] አመታት ውስጥ መከሰታቸውን ሳስብ፤ እንደምንም ብለን ይህንን ጊዜ ብናልፍም እንኳን፤ ሌላ ከእዚህ ተመሳሳይ፤ ምንአልባትም የባሰ ተላላፊ በሽታ፤ ብዙም ሳይቆይ ሊከሰት ይችል ይሆናል ብዬ፤ አስብ አለሁ።

ይህ ወረርሽኝ፤ ከፍተኛ ገቢ’ም ሆነ ዝቅተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት’ን ሳያማርጥ እየአጠቃቸው እንደሆነ ግልፅ ነው። ከፍተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት፤ ወረርሽኙን መቋቋም የእሚያስችል ቁመና ለዘመናት የገነቡ በመሆኑ፤ መደናገጡም ሆነ መረበሹ የእማይቀር ቢሆንም፤ በመጨረሻ – ጉዳቱ ብዙም ሳያንሳቁላቸው ቶሎ ማገገም እንደእሚችሉ ዕሙን ነው። እየተባባሰ በመጣው የመንፈስ እረብሻ ሳቢያ ሊከሰት ከእሚችለው፤ የአዕምሮ መታወክ ችግር’ም ጭምር። እኔን ዕንቅልፍ የ እሚነሳኝ – የ ዝቅተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራት ጉዳይ ነው።

እናም፤ ሙሉ ትኩረታችንን — የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ስርጭት’ን ለመከላከል፣ ለመገደብ፣ ለመቆጣጠር ብሎም ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን፤ ሃገራችን’ን በሁሉም መልኩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ መሆን ይኖርበታል።

ሁሌም እንደእምለው — ይህን’ን አስከፊ ጊዜ ልንወጣው የእምንችለው፤ በጋራ በአንድዕነት ለመቆም የወሰን’ን እንደሆነ ብቻ ነው። ምን እንደምፈልግ በእሚገባ ታውቃላችሁ እና፤ ዛሬ አሱን ብዙም አላነሳም። ዕውነት ለመናገር ከሆነ ግን፤ ደስታ’ም ሆነ ሃዘን የ እሚያምርብን፤ በአንድዕነት ስንቆም ነው። መለያየት ትላንትም አልበጀን፣ ዛሬም ሆነ ወደፊትም አይበጀንም። አንድዕነትዓችን ለ ኮቪድ–19 ብቻ ሳይሆን፤ ለሁለእንተናዊ ችግሮቻችን መቅረፊያ ልንጠቀምበት ይገባል።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፤

ወረርሽኝ’ን – ፊት–ለመንሳት፣ ለመከላከል፣ ለመግታት፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት በእሚል፤ በ ዓለም ጤና ድርጅትም ሆነ በ ሲዲሲ የተዘጋጁ ጋይድላየንስ አሉ። በእጃችሁ እንደእሚገኙ’ም አልጠራጠርም። እነሱን ለሃገርአችን በ እሚያመች መልኩ እያስተካከላችሁ መተግበሩ እጅጉን ጠቃሚ ነው። በ [ኢቦላ] ወረርሽኝ ጊዜ የተካበተ ተመክሮ ከአለ፤ ወደ ተግባር የእሚመነዘርበት ጊዜው አሁን ነው።

የመንግሥት፣ የሙያተኞች እና የኅብረተሰቡ፤ በቅንዕነት እና ኦርኬስትሬትድ በሆነ መልኩ፤ ሌት ተቀን አብሮ መስራት የግድ ነው። የጤና ባለሙያዎች፣ ተጋላጭ መሆን ሊያደርስ የ እሚችለው ጉዳት እጥፍ ድርብ ነው። መንግስት የተለየ ትኩረት ሊያደርግበት የእሚገባ ኤሪያ ነው። ሰዎች [አረጋዊያን’ን ወይም ህሙማን’ን ጨምሮ] ሰብሰብ በአለ መልኩ የእሚኖሩበት ቦታ ሁሉ፤ እንደ ነርሲንግ ሆም፣ ቦርዲንግ ስኩል፣ ሆስፒታሎች እና የመሳሰሉ ተቋማት ላይ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረድ ይገባል።

የገጠሩንም የከተማውንም ንዋሪ በአገናዘበ መልኩ፤ በጤና ባለሙያዎች የእሚመራ፤ በ ኮቪድ–19 ላይ የአተኮረ ለ 24/7 የእሚተላለፍ የማንቃት የማስተማር ስራ ቢኖር ጥሩ ነው። እንደ እኛ በአለ ሃገር፤ የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ስርጭት ስር ሰዶ በኅብረተሰቡ ውስጥ መሰራጨት ከጀመረ፤ ማጠፊያው ሊያጥረን እንደእሚችል አልጠራጠርም።

የላቦራቶሪ ምርመራ የማድረግ አቅምን ማጎልበት፣ ተጠርጣሪዎችን’ም ሆነ በቫይረሱ መያዛቸውን የተረጋገጠባቸውን ሰዎች አይዞሌት ለማድረግ የእሚአስችል ቦታ ማዘጋጀት፣ የህመም ምልክቶችን ለማስታገስ’ም ሆነ ኮምፕሊኬሽኖችን ለማከም፤ የእሚያስፈልጉ ማንአቸውም ነገሮች’ን ከ በቂ በላይ ዝግጅት ማድረጋችን’ን እርግጠኞች መሆን ይጠበቅብናል።

ከ ዛሬ ሳይሆን – ከትናንት ወዲያ ጀምሮ፤ ወረርሽኝ’ን ለመዋጋት በእሚል የተዘጋጀ’ን መርሃ-ግብር፤ [የአለአንዳች] ግድፈት እንዴት ተግባርዓዊ ማድረግ እንደእሚቻል፤ ተወዲሁ ከበቂ በላይ ዝግጅት አድርጎ መጠበቁ የግድ ነው። አንድ ነገር በተከሰተ ቁጥር [ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ] ባዮች ከመሆን፤ እንድን ዘንድ። በአንድአንድ አካባቢዎች፤ የ ክረምት ወራት እየተቃረቡ መሆኑን፤ ለእናንተ ማስታወስ — ድፍረት እንዳይሆንብኝ ብዬ ትቸው አለሁ። በሉ እንግዲህ በርቱ። አይዞን!

በመጨረሻም፤

ኅብረተሰብዓዊ ምጣኔሃብትዓዊ ፖለቲክዓዊ አለመረጋጋትን ሙሉ–በ–ሙሉ ማስወገድ፣ የ ንፁህ ውሃ እና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦትን ለዜጎች ሁሉ ማዳረስ። የ ደረቅ እና የ ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገዳችን’ን ማዘመን። የቫክሲን፣ የመድሃኒቶች፣ ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች ተደራሽዕነት’ን አቅርቦት’ን ከአቅም በላይ አለመሆን’ን እርግጠኞች መሆን። በሽታ’ን የመከላከል የመቆጣጠር እና የማጥፋት ፕሮግራሞች’ን ማዘመን ማሳደግ ማጎልበት። የ ፖለቲካ ካድሬዎች’ን ከማሠልጠን ይልቅ፤ የጤና ባለሙያዎችን ቁጥር በ [አንድ–ሽህ] ፐርሰንት ከፍ ማድረግ እና ለዜጎች ሁሉ ተደራሽ ዘመናዊ ስልጡን ጠንካራ የጤና ተቋማት’ን በአፋጣኝ መገንባት። እንኝህ ሁሉ — እንደ ኮቪድ–19 መሰል ተላላፊ በሽታዎችን ብቻ ሳይሆን፤ እንዳንቆም እንዳንተቀመጥ እንዳንተነፍስ – ሰንቀው የያዙንን ሁለዕንተንዓዊ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ የእሚያስችሉን አማራጭ የለሽ፣ ለ ነገ በእሚል ሊተላለፉ የ እማይገባቸው መሳሪያዎቻችን ናቸው። በተለይም – ከ ኅብረተሳብአችን ጫንቃ ላይ ለዘመናት አልወርድ የአለው፤ የ ተላላፊ በችታዎች ሸክም [ለነገሩ፤ የ ሁሉም ዓይነት በሽታዎች ሸክም] — የ ሰብዓዊ መብቶች መረገጥ፣ የ [ሰው ልጆች] በነፃነት የመኖር ተፈጥሮአዊ መለኮትዓዊ ማንዕነታቸው’ን የመዝረፍ ጉዳይ’ም ጭምር በመሆኑ፤ የ “ጤና ችግሮች” እየተባለ እየተፌዘ የ እሚታለፍ ጉዳይ መሆኑ — ዛሬውኑ መቆም ይኖርበታል።


የመንግስታት ደካማዕነት፣ ጎሠኛዕነት፣ ኢ-ፍትህዓዊዕነት እና አግላይዕነት፤ የእሚያስከትለው ዳፋ፤ ኅብረተሰቡን እየአንገላቱት እያማረሩት እየአጎሳቆሉት የአሉትን ሁለዕንተንዓዊ ችግሮችአችንን – የበለጠ ማባባስ ብቻ ነው።

ጤናማ እና አስተማማኝ ህይወት ለመገንባት እና በፈጣሪ ዘንድ የእሚያስጠይቅ ነውር የሆኑትን ሁለፅንተንዓዊ ችግሮቻችንን ለማረቅ ለመቅረፍ ለማስወገድ ለመቆጣጠር ለማጥፋት — የሰለጠኑ ኅብረተሰብዓዊ እንቅስቃሴዎች፣ በተለይም ሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚያተኩሩ እንቃቃሴዎች፤ በሰፊው ተጠናክረው [የሰው ልጆች ሁሉ] ምሉዕ ሰውዓዊ ህይወትን ሊያጣጥሙ ይችሉ ዘንድ — አምርረን መታገል ይጠበቅብን አለ። ዕድሜ ለ ኢኖቬሽን፤ ግዙፍ ትመስለን የነበረችው ፕላኔት ምድር፤ [ጎጆ] አክላልን አለች እና!

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር።

አኪዩ

— እንደገና እስከ እምንገናኝ —



# የ “ኮቭ” ጦርዕነት

ግንቦት ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ‖ ሜይ 2020

ሰሞነኛውን፤ የ “ኮቭ” ጦርዕነት ለመቋቋም እና ፍልሚያውን በድል ለመወጣት — ፕላኔት ምድር፤ አበክራ ደፋ-ቀና ማለት ከጀመረች አምስት ወራትን ማስቆጠር ጀምራ አለች። በ ድሴምበር 2019 መጨረሻ ላይ በቻይና የጀመረ ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ፤ ገና ባይለይለትም — ጓዙን አራግፎ፤ ነጋሪቱን ሲጎስም የሰነባበተባቸው ሃገራት በወሰዱአቸው የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች፤ “መተንፈሻ” የአገኙበት ጊዜ ላይ መድረሳቸውን እየ-አየን ነው። አንዳንዶቹም ወደ ቅድመ ሳርስ-ኮቭ-2 ህይወት ለመመለስ ጉግታቸውን ሲገልፁ እየተሰማ እየታየም ነው። የ ፕሮፓጌትድ ወረርሽኝ ባህሪን ሳስብ እና የ ዕለት-ተዕለት ቁጥሮችን ሳገናዝብ፤ ወደ ቅድመ ሳርስ-ኮቭ-2 ህይወት ለመመለስ መቻኮሉ፤ ሊያሳስበን እንደእሚገባ ነው እሚሰማኝ። በአንፃሩ — ሌሎች ሃገራትን ለጊዜውም ቢሆን፤ ወረርሽኙ የጎሪጥ እየ-አያቸው የ አለፈ ቢመስልም፤ ክረምት እየተቃረበ በመሆኑ — ስጋት፣ ቁርጠኛዕነት እና ተስፋ የተቀላቀሉበት መንፈስ እንደተንሰራፋባቸው መገመት አያዳግትም። በአጠቃላይ፤ ከ የተወሰኑ መዘናጋቶች ውጪ፤ እንደ አንድ የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ — ዕምነት፣ ዕውቀት እና አቅም የፈቀዱትን ዕርምጃዎች በመውሰዳችን፤ ወረርሽኙ እጅጉን የከፋ ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ ከማድረሱ በፊት ልንገድበው ተቃርበናል ብዬ ዕገምት አለሁ። ያ ባይሆን ኖሮ — ማለቴ፤ እጅ እና እግርአችንን አጣጥፈን ተመልክተን ቢሆን ኖሮ፤ ሊደርስ ይችል የነበረውን እጅጉን የከፋ አደጋ፤ በቃላት መግለፅ አዳጋች ይሆን ነበር። ዛሬም ቢሆን — ስለ መተላለፊያ መንገዶች፣ አንቲቦዲዎች የመፍጠር ቁመናችን እና ሪኢንፌክሽን ሊከሰት መቻል ወይም አለመቻል፤ የተወሰኑ ፍንጮች ቢኖሩም ገና ብዙ ጥናቶችን ማድረግ እሚጠይቅበት ደረጃ ላይ ነው የ አለነው። ክትባት፣ አንቲቦዲዎችም ሆኑ መድሃኒቶች አሁንም ቢሆን ለ ይፋ ጠቀሜታ አልደረሱም። ለ ጤና ባለሙያዎች፣ ለ ዘረፈ-ብዙ አገልግሎት ሰጪ የ ኅብረተሰቡ አባላትም ሆነ ለሰፊው ኅብረተሰብ ጠቀሜታ እሚያስፈልጉ፤ እራስን የመጠበቂያ ቁሳቁሶች እጥረትም በጣም አሳሳቢ ሆኖ ሰነባብቷል። በእዚህ ሁሉ መሃል፤ ወደ 3.2 ሚልየን እሚቆጠሩ ሰዎች በቫይረሱ የተያዙ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን – ከእነሱም ውስጥ ወደ ሰባት ከመቶ እሚቆጠሩ ሰዎች ህይወታቸው አልፏል። ከ በሽታዎች ጋር እምናደርገው ጦርዕነት፤ በእዚህ እሚያበቃ አይደለም። ዛሬ ላይ ሆነን፤ ወደ ቅድመ ሳርስ-ኮቭ-2 አንፃርዓዊ የተረጋጋ ህይወት መቼ ልንመለስ እንደእምንችል መናገርም ቀላል አይደለም። ቢሆንም ቅሉ — ሰው በመሆንአችን፤ ሰሞነኛውን የ “ኮቭ” ጦርዕነት ለመቋቋም እና ፍልሚያውን በ ድል ለመወጣት ብቻም ሳይሆን፤ ለ ዘርፈ-ብዙ ክሮኒክ ችግሮቻችን፤ ተቋምዓዊ በሆነ መልኩ እና በዘላቂዕነት መፍትሄ እምንሰጥባቸውን ዜዴዎች መፍጠር እሚያስችለን፤ ዕምቅ አቅም እንደ አለን፤ በፍፁም አልጠራጠርም። እናም፤ ምሉዕ [ጤናማ ሰውዓዊ መለኮትዓዊ] ህይወትን ማጣጣም እንችል ዘንድ፤ እንደ አንድ ስልጡን የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ፤ በመሠረትዓዊ ጉዳዮች ላይ — ከምን ጊዜውም በተለየ መልኩ፤ በቀናዕነት እና በጥሞና መነጋገር መቻል፤ ይጠበቅብን አለ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፤ እንዴት እንዴት ናችሁ?!

የወቅቱ መነጋገሪያ ርዕስ በሆነው በ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ዙሪያ በማጠንጠን፤ መሠረትዓዊ ጉዳዮችን ለማነሳሳት ነው እንግዲህ፤ የዛሬው አመጣጤ። ትክክል። ዛሬም – አዎ ዛሬም፤ የ ጤና ባለሙያዎች እና የ መንግስት አካላት እሚሰጡትን ምክር እና መመሪያ ተቀብለን በአግባቡ በመተግበር፤ ሰሞነኛውን የ “ኮቭ” ጦርዕነት [“ኮቭ” – እንደ ሲዖቪ፣ እንደ ኮሮናቫይረስ] ለመቋቋም እና ፍልሚያውን በ ድል ለመወጣት እንችል ዘንድ፤ ሁልአችንም እንደ አንድ ስልጡን የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ፤ ሃላፊዕነትአችንን እና ግዴታችንን፤ ቆፍጠን ብለን እንወጣ — ለማለት!


እናም፤ አብረን እንቆይ — የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።

አለፍ ብላችሁ እንደእምታዩት፤ ከወደ ድሴምበር መገባደጃ አካባቢ እንደተቀሰቀሰ እሚገመተው የ ሳርስ-ኮቭ-2 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ፤ ከአምስት ወራት በአልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤ የህመም ምልክት ታይቶባቸው፤ የቫይረሱ ምርመራ ከተደረገላቸው መካከል፤ ይህችን ብሎግ እየጨራረስሁ እስከአለሁባት ቀን ድረስ፤ በድምሩ [ግሎባሊ] — ወደ 3.2 ሚልየን እሚቆጠሩ ሰዎች በቫይረሱ እንደተያዙ፤ ከእነዚህም ውስጥ ሰባት ከ መቶ እሚሆኑት ሰዎች፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለም ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ተደርጓል። ወረርሽኙ በሁሉም የ ዕድሜ ክልል ውስጥ የአሉትን — ፆታ፣ ጎሣ እና ሃገር ሳይለይ እሚያጠቃ መሆኑን አይተናል።

በአንዳንድ አካባቢዎች፤ ኢንስቲቲውሽናላይዝድ የሆኑ ሰዎች እና የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ ሙያዎች ውስጥ የተሰማሩ ሰዎች፤ ለቫይረሱ የበለጠ ተጋላጭ ሲሆኑ ታይቷል። ህመሙ ጠንከር የአለባቸውም ሆነ ህይወታቸው የአለፈ ሰዎችም፤ በአመዛኙ ዕድሜአቸው ከ 60ዎቹ በላይ የሆኑ፣ በተጨማሪም ሌሎች ህመሞች የአሉባቸው እና በህዝብ ብዛት የተጨናነቁ ከተማዎች ውስጥ ንዋሪ የሆኑ ሰዎች ናቸው።

በቫይረሱ የተያዙ — ግን፤ ምልክት ሳያሳዩ ቀርተው ወይም የላቦራቶሪ ምርመራ ሳይደርግዕላቸው በመቅረታቸው፤ ትክክለኛውን አሀዝ ማወቅ አስቸጋሪ መሆኑ አሁንም የተጠበቀ ሆኖ፤ በ አብዛኛዎቹ አህጉራት ሪፖርት የእሚደረጉትን የ ኮቪድ–19 ህሙማን ቁጥሮችን ስመለከት፤ በአውሮጳ ከ ማርች 27፣ በአሜሪካ እና በ ኤዥያ ከ ኤፕሪል አምስት ጀምሮ፤ ሁለት ተስፋ ሰጪ ባህሪያት መከሰትአቸውን ተገንዝቤ አለሁ።

ፐላኔት ምድር





<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ኪውምሌቲቭ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

የመጀመሪያው፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የእሚደረጉት አዲስ ህሙማን ቁጥር፤ ኤክስፖነንሻሊ መምዘግዘጉን ማቆሙ ሲሆን — ሁለተኛው ደሞ፤ ምንም እንኳን የ "ፕሮፓጌትድ ኤፒደሚክ" ባህሪው ተጠናውቶት ከፍ-ዝቅ ማለቱን ባይተውም፤ ፈራ-ተባ እየአለ <u>በአማካይ</u> "ፍላተንኢንግ ዘ ከርቭ" ወይም "ፕላትዖ" እሚባለው ደረጃ ላይ የደረሰ የ መሆኑ ነገር ነው። አንዴ እዚህ ደረጃ እስከደረስን እና የመከላከል የመቆጣጠር ጥረትአችንን በአግባቡ እስከቀጠልንበት ጊዜ ድረስ፤ የ አዲስ ህሙማን ቁጥር በፍጥነት እየአሽቆለቆለ ይሄድ እና፤ ወረርሽኙ ብዙም መቆየት ሳያስፈልገው እጅጉን ወደ መቀነስ – ብሎም፤ ጭራሽእኑ ወደ ማክተም ደረጃ ሊደርስ ይችላል በዬ እገምት አለሁ።


እንደእምታዩትም፤ አውሮጳ ከ ኤፕሪል 13 ጀምሮ፤ የወረርሽኙ መጠን እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የቁልቁለቱን መንገድ የተያያዘችው ይመስላል።

አህጉራት





<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሲሆን፤ ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶች በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን፣ ደቡብ፣ ካናዳን እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።

የቀሩት አህጉራት — አፍሪቃን ጨምሮ፤ በ ሳርስ-ኮቭ-2 እንደተያዙ ተረጋግጦ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እሚያደረጉት ህሙማን ቁጥር፤ አሁንም አነስተኛ ነው። ለ እዚህ ክስተት የተለያዩ መላምቶች ቢኖሩም – በእርግጥኛዕነት፤ እንዲህ ወይም እንዲያ ስለሆነ ነው ለማለት፤ ጥናት እና ምርምሮችን ይጠይቃል። አፍሪቃ — በእየዕለቱ ሪፖርት እምታደርጋቸው ህሙማን ቁጥር፤ ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ሆኖ ሳለም ፤ እየአሻቀበ መምጣቱ ግን አሳሳቢ ነው።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሲሆን፤ ጥሬ ዳታውን የወሰደኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ፤ ኮቪድ–19’ን በተመለከተ ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ማድረግ የጀመረችው፤ ማርች 14 ላይ ነው። ለ የመጀመሪያዎቹ 20 ቀናት ገደማ እየአሰለሰች ሪፖርት ታደርግ የነበረቻቸው የሰዎች ብዛትም፤ በጣም ትንሽ እሚባል ነበር። ከ ኤፕሪል አራት ጀምሮ ሪፖርት እየአደረገች የአለችው፤ በ እየዕለቱ ወደመሆን ቢቀየርም፤ መጠኑ ግን እስከዛሬ [የ እየ ዕለቱን ማለቴ ነው] ከ ሲንግል ዲጂት አልፎ አያውቅም።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሲሆን፤ ጥሬ ዳታውን የወሰደኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

የቁጥሮቹ በጣም አነስተኛ መሆን፤ ከዕለት-ወደ-ዕለት ከፍ-ዝቅ ስለማለታቸው ብዙም ማለት ባያስችልም፤ ከ ኤፐሪል 19 ጀምሮ፤ እየጨመረ ከመሄድ ይልቅ ወደ መቀነሱ ለማዘመም እየአቅማማ መሆኑ፤ ተስፋ ሰጪ ነው። ወደፊት፤ በእየ ክፍለሃገሩ ቴስት እሚደረጉ ሰዎች ብዛት እየጨመረ ሲሄድ፤ ነገሮች ሁሉ በፍጥነት ሊለዋወጡ እንደ እሚችሉ መገመት ብልህዕነት ነው። መዘናጋት እሚባል ነገር መኖር የለበትም።

በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር አነስተኛዕነት፤ ምርመራውን ከማድረግ አቅም ጋር የተያያዘ ሊሆን ቢችልም እና ትክክለኛውን የቫይረሱ ተጠቂዎች ቁጥርን ማወቁ አሁንም አስቸጋሪ ሆኖ ቢገኝም፤ በኅብረተሰቡ ውስጥ ጉንፋን መሰል ህመምም ሆነ በ ጉንፋን መሰል ህመም ሊሆን ይችላል የተባለ፤ የህይወት ማለፍ እየተከሰተ ለመሆኑ [ቢያንስ] በ አለመስማቴ፤ በኢትዮጵያ ሪፖርት እየተደረጉ የአሉት ቁጥሮች ከዕውነታው ብዙም የአልራቁ ሳይሆኑ አይቀርም፤ ከእሚሉ የሙያው ሰዎች ጋር እስማማለሁ።

በአመዛኙም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በቫይረሱ ተይዘው የተገኙ ሰዎች — ከውጪ ሃገራት የመጡ በመሆናቸው እና ወደ ኅብረተሰቡ ከመቀላቀላቸው በፊት ጥንቃቄ ማድረግ በመቻሉ፤ ሊከሰት ይችል የነበረውን ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ ለመከላከል አስችሎልን አለ ማለትም ይቻላል። ሆኖም ግን፤ አልፎ አልፎ የውጭ ሃገር ጉዞ ታሪክ የሌላቸው እና ከውጭ ከመጣ ሰው ጋር ግንኙነት እንደ የሌላቸው እሚገመቱ፤ በቫይርሱ ተይዘው መገኘታቸው፤ አሁንም ቢሆን በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ሊታይ ይገባል።

እየተቃረበ የመጣው የክረምት ወቅትም፤ የቫይረሱን ስርጭት ከቁጥጥር ውጪ ሊያደርሰው ይችል ይሆናል የእሚል የቀደመ ስጋቴን እየጨመረው ሲሄድ እያስተዋልሁ ነው። እናም፤ እስከ አሁን እየተደረጉ የ አሉትን ጥረቶች ሁሉ፤ ከ ስፖርትኛ ቋንቋ አንድ ቃል ልዋስ እና – እንደ "ማሚሚቅ" ነው ልንቆጥረው እሚገባን ማለት እወድ አለሁ። ጊዜው ደርሶ፤ ይህ–እንን በማለቴ ስህተተኛ እንደሆንኩ የአወቅሁኝ ቀን – ሻምፔይን ከፍቼ፤ ድምፄን ከፍ አድርጌ በቅድሚያ "ሆሬይ" እምለው እኔው እራሴ ነኝ።

በሌላ በኩል — የአንድም ሰው ህይወት ማጣት የእሚያስቆጭ ቢሆንም ቅሉ፤ የፈተናው አጣዳፊዕነት እና ውስብስብዕነት ዕግምት ውስጥ ሲገቡ፤ ለ ፈጣሪ ክብር ምስጋና ይግባው እና እስከዛሬ በ እዚህ ወረርሽኝ ሳቢያ በ ኢትዮጵያ፤ ህይወታቸው የአለፈ ሰዎች ቁጥር ኢምንት ሊባል የእሚችል ነው።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ኢትዮጵያ በቅንዕነት እየአደረገቻቸው የአሉት፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር ትኩረቶች እና ጥረቶች ሁሉ፤ አበረታታች ብቻ ሳይሆኑ፤ ሊመሰገኑ የእሚገባውቸውም ጭምር ናቸው ብዬ፤ አምን አለሁ — ከልቤ!

ሌሎች መሠረትዓዊ ጉዳዮችን ልጨምር።

ኅበዝ፤ እንደ እምታዩት — የዛሬዋ መጣጥፌ ትንሽ ዕረዘም ስለ እምትል፤ የሆን በርጬማ ቢጤ ፈልጋችሁ አረፍ ብትሉ ይሻላል።

በ ኢትዮጵያ፤ በቫይረሱ ሊያዙ እሚችሉ ሰዎች ብዛትን በተመለከተ፤ በአለፈው ወር በተለያዩ ምንጮች የተጠቀሱ ቁጥሮች አነጋጋሪ ሆነው መሰንበታቸውን አስተውያለሁ።

ወረርሽኝ በተከሰተ ቁጥር፤ [ከመከላከል፣ ከመቆጣጠር እና ከማጥፋት] ጥረቶች በአልተናነሰ መልኩ፤ ጎን-ለጎን ሊከናወኑ እሚገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ፤ በጥንቃቄ እሚዘጋጅ የ "ፐብሊክ ሪሌሽንስ" ስራ አንዱ ነው። ለ ጤና ሙያተኞች፤ ለተመራማሪዎች፣ ለመንግስት ባለስልጣናት እና ለ ሰፊው ኅብረተሰብ እሚነገረውን፤ እንደ እየ ፈርጅ-ፈርጅአቸው በተገቢው መልኩ በተቀመረ ቋንቋ፤ ለየት–ለየት በእሚሉ አገላለፆች ኮምዩኒኬት ማድረግ መቻል፤ እጅጉን ወሳኝ ነው። ስለ ቁጥሮች ብቻ ሳይሆን፤ ስለ ማናቸውም ተጓዳኝ መረጃዎችም ጭምር። አብዛኛው ሰው፤ መረጃ እንደልብ ማግኘት እሚችልበት ጊዜ ላይ በመሆንአችን፤ ከ እሚመለከተው አካል ሰርክል ውጭ ሲሰማ – ግርታን ጥርጣሬን፣ መረበሽን፤ ምንአልባትም የአልታሰበ ጉዳትን ሊያስከትሉ እሚችሉትን — ለ ሰፊው ኅብረተሰብ እንዲደርሱ ከመደረጋቸው በፊት፤ በከፍተኛ ሙያዓዊ ጥንቃቄ መዘጋጀትአቸውን እርግጠኞች መሆን፤ ጠቀሜታው፤ ጎተራ ሞልቶ ይተርፋል።

የሆነው ሆኖ፤

በ ሳርስ-ኮቭ-2 ሊያዙ እሚችሉ ሰዎችን መጠን ለማስላት ጠቀሜታ ላይ እሚውሉት በዛ ያሉ ሚድልዖች እሚጠይቋቸው ፐራምትርስ እና ምንም የመከላከል እና የመቆጠጠር እርምጃ አለመውሰድን ጨምሮ፤ በሌሎች አሰምሽንዖችም ሳቢያ፤ አነጋጋሪ ሆነው የሰነበቱት ቁጥሮች፤ ኢንኸረንትሊ "ግምትዓዊ" ናቸው። እናም፤ ቁጥሮቹን ለማስላት እሚጠይቀውን ውስብስብ ስራ በመጠኑም ቢሆን መገንዘብ — አመለካከትአችን፣ አተረጓጎምአችን እና አረዳድአችን፤ ሰከን እንዲል ይረዳናል።

አዎ፤ የ ሳርስ-ኮቭ-2 አዲስ መሆን፣ ቀጥተኛ ተሞክሮም ሆነ ሂስቶሪካል ዳታ አለመኖር እና የወረርሽኙ የመቀጣጠል ሂደት የመጀመሪያው ደረጃ ላይ መሆናችን፤ ፐራምትርዖቹ እና አሰምሽንዖቹ በተዘዋዋሪ ወይም በተውሶ እሚገኙ አህዞች እና ኮንሴፐቶች ላይ ዕምነት እንዲጥሉ የግድ ይላቸው አለ። አብሮአቸው እሚጓዘውም አንሰርትንቲ የእዚያኑ ያህል ሰፋ ያለ ነው። እናም፤ አነጋጋሪ ሆነው የሰነባበቱት ቁጥሮች፤ ከፍተኛ መሆንአቸው እና ከ አንዱ የመረጃ ምንጭ – ወደ ሌላው የመረጃ ምንጭ፤ የተለያዩ ሊሆኑ መቻላቸው — የአመለካከት፣ የአተረጓጎም እና የአረዳድ ልዩዕነቶችን ማስከተላቸው እሚጠበቅ ነው።

እንዲያው........

ለየት የአለ ኢንተረስት አለኝ የእሚል የኅብረተሰብአችን አካል ከአልሆነ በስተቀር — ለ ሳይንስዓዊ ጥናት እና ምርምር ቀረቤታ ከአላቸው የሙያው ሰዎች ውጪ ለአለው ሰፊው ኅብረተሰብ፤ በ ወረርሽኝ ዙሪያ እሚያጠነጥኑ፤ ከጤና ጋር እሚዛመዱ ውስብስብ ጉዳይዖችንም ሆነ የካልኩለስ ዕውቀትን እሚጠይቁ ሚድልዖችን ማወቅ፤ ግድ አይልም። ቢሆንም — አነጋጋሪ ሆነው በሰነባበቱት ቁጥሮች ዙሪያ፤ የተወሰኑ መሠሰረትዓዊ

ጉዳይዎችን [አንዱ አንብባችሁ] እንድታልፉአቸው ያህል እና ፖቴንሻሊ፤ ቁጥሮች ከፍተኛ ሊሆኑም እንደእሚችሉ ዕግምት ውስጥ እንድታስገቡ ያህል ብቻ፤ ላ–ላ በአለ አገላለፅ፤ እምለውን እንድል ፈቃዳችሁ ይሁን።

ሦስት ጥያቄዎችን ሰንቄ ልንደርደር፤

ጥያቄ አንድ — ሳርስ-ኮቭ-2 በ ከፍተኛ ወረርሽኝ ደረጃ ሊሰራጭ ይችል ይሆን፣

ጥያቄ ሁለት — በ ሳርስ-ኮቭ-2 ተይዘው፤ ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ "ኢንፌክቲቭ" ሰዎች፤ ብዛት መጠን፤ ምን ያህል ከፍ ሊል ይችል ይሆን እና

ጥያቄ ሦስት — በ ወረርሽኙ መገባደጃ፤ ምን ያህል ሰዎች ኮቪድ–19 ተከሰቶባቸው ይሆን፤ የ እሚሉትን።

ለእነዚህ ሦስት ጥየቄዎች መልስ ለማፈላለግ፤ ጠቀሜታ ላይ እሚውሉ፤ የተለያዩ ሚድልዖች የአሉ ቢሆንም፤ ሁሉም፤ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በእሚገለገሉባቸው ፐራምትርዖች እና አሰምሽንዖች ሳቢያ፤ እሚመሳሰሉባቸው በዛ-ያሉ ስፔሲፊኬሽንስ አሉ።

እነርሱም.........

ሀ) ሳርስ-ኮቭ-2 ሊይዛቸው እሚችሉ ሰሴፐትብል ሰዎች ብዛት፣ ለ) በ ሳርስ-ኮቭ-2 ተይዘው በፍጥነት የመከላከል አቅም "ስለአላቸው" — ማለትም፤ ኤክስፖዝድ ሆነው ኢንፌክትድ ሳይሆኑ እሚቀሩ ሰዎች ብዛት፣ ሐ) በ ሳርስ-ኮቭ-2 ተይዘው እና ቫይረሱን ለሌሎች ሰዎችም ማስተላለፍ እሚችሉ ኢንፌክቲቭ ሰዎች ብዛት፣ መ) በ ሳርስ-ኮቭ-2 ኢንፌክትድ ሆነው ነገር-ግን በሆነ መልኩ፤ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ሪከቨር እሚያደረጉ አልያም ህመሙን መቋቋም አቅቷቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እሚችል ሪሙቭድ ከእሚል ጎራ እሚመደቡ ሰዎች ብዛት፣ ሠ) ወረርሽኙ በእሚቆይባቸው ቀናት፣ ሳምንታት ወይም ወራት ውስጥ የተወለደ ሰው ብዛት፤ ብሎም በሌላ ምክንያት ህይወታቸው የአለፈ ሰዎች ብዛት እና ረ) የ እነዚህን ሁሉ ስፔሻል [እንደ ስፔስ፣ እንደ ጂኦግራፊ] ዲስትሪቢውሽንስ — በተጨማሪም፤ በአንዱም ሆነ በሌላ መልኩ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል በእሚል፤ እግምት ውስጥ እሚገቡ የዕለት-ተዕለት ውስብስብ የህይወት አትሪቢውትስ'ን ቀለል ለማድርግ እሚያግዙ፤ ቁጥርአቸው ወደ ስድስት እሚደርሱ አሰምሽንዖች፤ ናቸው።

ማብራሪያ አንድ — ጥያቄ አንድን በተመለከተ፤

ሳርስ-ኮቭ-2 በ ከፍተኛ ወረርሽኝ ደረጃ ሊሰራጭ ይችል ይሆን፤ የእሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፤ ብዙውን ጊዜ "ኤስ-አይ-አር" በእሚል ምህፃረ-ቃል እሚታወቅ ቤዚክ ሚድል ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ሚድል የተመሠረተባቸውን [ዲፍረንሻል ኢኳዥንስ] ለዛሬ አልፈአቸው — ሁለት፤ ሁሉም በቀላሉ ሊገንዘብአቸው እሚችሉ ኮንሴፕቶችን በማንሳት ልቀጥል።

ኮንታክት ሬሽዖ እና ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖ በመባል እሚጠሩትን፤ ማለቴ ነው።

ኮንታክት ሬሽዖ – በአንድ መንደር፣ ክፍለሃገር፣ ሃገር፣ አህጉር ወይም ፕላኔት፤ ከ እሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ ውስጥ፤ በ የአልተገደበ የዕለት–ተዕለት የህይወት ስብጥር እንቅስቃሴ ምክንያት፤ ሳርስ-ኮቭ-2 ኖሮባቸው ለሌሎች ማስተላለፍ ከእሚችሉ –– ማለትም፤ "ኢንፌክቲቭ" ከሆኑ ሰዎች ጋር በቀረቤታ ኮንታክት ሊኖራቸው እሚችሉ "ሰሴፐትብል" ሰዎች ብዛትን ይነግረናል። ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖ በበኩሉ፤ ኮንታክት ሬሽዖን ለየት ከአለ ዳይሜንሽን እየአማተረ፤ አንድ በ ሳርስ-ኮቭ-2 የተያዘ ሰው ቫይረሱን፤ በአማካይ ለ ስንት ሰዎች ሊያስተላልፍ እንደእሚችል፤ ነው እሚነግረን።

በአጠቃላይ፤ አንድ ተላላፊ በሽታ ወደ ከፍተኛ ወረርሽኝ ደረጃ ሊደርስ እሚችለው — ኮንታክት ሬሽዖ እጅጉን ከፍ የአለ ሲሆን እና በተጓዳኝም ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖ ከ አንድ በላይ ሲሆን ነው።

ለምሳሌ........

ወቅት እየጠበቀ እሚከሰተው ኢንፍሉዌንዛ፤ እኛ "ጉንፋን" እምንለው፤ በእየወቅቱ እሚሰጡ ክትባቶችን እግምት ውስጥ በማስገባት፤ ኮንታክት ሬሽዖው፤ ሊሆን ይችል የነበረውን ያህል እጅጉን ከፍ የአለ ባይሆንም፤ ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖው ግን ሁለት ገደማ እንደሆነ ነው እሚገመተው። ይህ ግምት፤ ዝም ብሎ የተፈበረከ ሳይሆን – የብዙ ዓመታት ልምዶች ላይ በመመርኮዝ የተገኘ ነው።

በአንፃሩ፤ ሳርስ-ኮቭ-2 አዲስ በመሆኑ እና የተዘጋጀ ክትባት ስለሌለን፤ ኮንታክት ሬሽዖው እጅጉን ከፍ የአለ ሊሆን በመቻሉ — የብዙ ዓመታት ልምዶች ላይ የተመመርኮዘ ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖ እስከ አሁን ባይሰላም፤ ከ ጥቂት-ጊዜ ተሞክሮ ከሰው-ወደ-ሰው በቀላሉ እንደ እሚሰራጭ ግልፅ እየሆነ መምጣቱን እና ሁላችንም ኢምዩኒቲ የሌለን መሆኑን እግምት ውስጥ በማስገባት፤ ለ ዕውነት ቀረብ እሚል የ ሳርስ-ኮቭ-2 ስርጭት ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖው፤ በአማካይ አራት እንደሆነ ነው በአንዳንዶች እየተገመተ የአለው። ማለትም፤ አንድ በ ሳርስ-ኮቭ-2 የተያዘ ሰው፤ በአማካይ – ለ አራት ሰዎች ቫይረሱን ሊያስተላልፍ ይችላል ማለት ነው።

መልስ አንድ — ጥያቄ አንድን በተመለከተ፤

አዎ፤ ሳርስ-ኮቭ-2 በ ከፍተኛ ወረርሽኝ ደረጃ ሊሰራጭ ይችላል። ተገቢውን የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃ ፈጥነን እስከአልወሰድን ድረስ! ለምን ቢሉ፤ ኮንታክት ሬሽዖው [ሁሉንም ማህበረሰብ ሊያካትት ይችላል በ እሚባል መጠን] ከፍተኛ በመሆኑ እና በተጓዳኝም፤ ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖው ከ አንድ በላይ፤ እንዲያውም በአማካይ አራት እንደሆነ ስለ እሚታመን።

ይ-ህ ፌኖምና፤ ቀደም ብዬ የጠቀስኩላችሁን ኤስ-አይ-አር ሚድል በመጠቀም እሚዘጋጅ ላየን-ግራፍ ላይ፤ ኢንፌክቲቭ የሆኑ ሰዎችን መጠን እሚጠቁመው ከርቭ፤ ኤክስፖነንሻሊ ሲያሻቅብ በእሚታየው በመጀመሪያው ግማሽ ሴግመንት ይንፀባረቃል።

ለነገሩ፤ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፤ ዛሬ ላይ ምንም የቁጥር ማስረጃ መጥቀስ አያስፈልግም ነበር። የ ሳርስ-ኮቭ-2 ወረርሽኝ፤ ከ አንዲት ከተማ የጀመረ፣ ወደ ሃገር–አቀፍ ወረርሽኝ ከፍ ብሎ፣ ወደ አህጉር–አቀፍ ወረርሽኝዕነት በመሸጋገር እና በሰፊው ከአህጉር ወደ አህጉር እየተቀጣጠለ በመሄድ፤ ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ደረጃ መድረሱን፤ እኔም እናንተም አስተውለናል እና!

*<u>ማብራሪያ ሁለት — ጥያቄ ሁለትን በተመለከተ፤</u>*

በ ሳርስ-ኮቭ-2 ተይዘው፤ ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ ሰዎች — ማለትም፤ “ኢንፌክቲቭ” የሆኑ ሰዎች፤ ብዛት መጠን ምን ያህል ከፍተኛ ሊሆን ይችል ይሆን እሚለውን ጥያቄ ማለቴ ነው።

ድንገት አልጠረጠራችሁ ከሆነ፤ ለእዚህ ጥይቄ መልስ ለመስጠት በእሚል እሚሰላ ቁጥር ነው እንግዲህ፤ እንደ ሳርስ-ኮቭ-2 ለአለ ተላላፊ በሽታ፤ የ ቁጥሩ ከፍተኛ ሊሆን መቻል — አነጋጋሪ ሆኖ የሰነባበተው።

ያ–ው፤ ሳርስ-ኮቭ-2 አዲስ ከመሆኑ የተነሳ እና የሰው ልጆች ሁሉ፤ ምንም ዓይነት ኢምዩኒቲ ይኖረናል ተብሎ ስለ እማይገመት፤ ቫይረሱ ሊይዛቸው እሚችሉ እና ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ “ኢንፌክቲቭ” ሰዎች ብዛት፤ ፖቴንሻሊ – <u>ሁሉንም</u>..... [ከፈለጋችሁ በመንደር፤ ከፈለጋችሁ በክፍለሃገር፣ ከፈለጋችሁ ደሞ በ ሃገር ደረጃ ውሰዱት] – አዎ፤ ሁሉም ሰው ቫይረሱ ሊይዘው እሚችል መሆኑ ብቻም ሳይሆን፤ ከዚያም በኋላ ወደ ሌላ ሰውም ሊያስተላልፍ ይችላል በእሚል ነው፤ መታየት ያለበት።

በእዚህ መልኩ በእሚገመተው ኮንታክት ሬሽዮ እና ተጓዳኝ በሆነው ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዮ ሳቢያ እንግዲህ፤ ከ አንድ ወደ አራት፣ ከአራት ወደ 16፣ ከ 16 ወደ 64፣ ከ 64 ወደ 256 — ምን አለፋችሁ እንዲህ እየአለ፤ ከአንድ ሳምንት በአነሱ ቀናት ውስጥ፤ በ ቫይረሱ ተይዘው ወደ ሌላ ሰውም ሊያስተላልፉ የእሚችሉ ሰዎች ከፍተኛው የቁጥር መጠን “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” እሚባለው — ፖቴንሻሊ፤ ከሰባ ፐርሰንት በላይ የእሚሆነውን ህዝብ ሊያካትት እሚችልበት ከፍታ ላይ በቀላሉ ሊደርስ ይችላል።

ይ-ህ ፌኖምና፤ ቀደም ብዬ የጠቀስኩላችሁን ኤስ-አይ-አር ሚድል በመጠቀም እሚዘጋጅ ላየን-ግራፍ ላይ፤ ኢንፌክቲቭ የሆኑ ሰዎችን መጠን እሚጠቁመው ከርቭ፤ ኤክስፖነንሻሊ ሲያሸቅብ ቆይቶ ሲያበቃ እና አደብ መግዛት ሲጀምር በእሚከሰተው፤ ከፍተኛውን የ ኢንፌክቲቭ ሰዎች መጠን “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” በ እሚጠቁመው “ፍላት ሴግመንት” ይንፀባረቃል።

በነገራችን ላይ.........

ተገቢው የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች በፍጥነት ከ አልተወሰዱ፤ እንደ ሳርስ-ኮቭ-2 የአሉ ተላላፊ በሽታዎች፤ “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” ደረጃ ላይ ለመድረስ ጊዜ አይወስድባቸውም። እንዲያውም፤ በሦስት አራት ቀናትም ውስጥ ሊሆን ይችላል። በአንፃሩ — ኮንታክት ሬሽዮአቸው፤ በተጓዳኝም ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዮአቸው እምብዛም የሆኑ ተላላፊ በሽታዎች፤ ሲጀመር – ኢንፌክቲቭ ማክሲመምአቸው እራሱ ብዙም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ላይደርሱ ይችላሉ፤ ሲቀጥል – ሊደርሱበት የቻሉባቸው ደረጃዎች ላይ ለመድረስም ቢሆን፤ ሪሌቲቭሊ ዕረዘም የአለ ጊዜ ይፈልግአሉ።

ፒክቸር ማድረግ ለእሚቀናችሁ አንባቢዎቼ፤

“ኤስ-አይ-አር” በሚል እሚጠራውን ቤዚክ ሚድል እሳቤ በማድረግ — ሦስት ስቴት–ቫርየብልስ፤ 1) <u>ሰሴፐትብል</u> የሆኑ ሰዎች ብዛት፣ 2) <u>ኢንፌክቲቭ</u> የሆኑ ሰዋች ብዛት እና 3) [ቁጥራቸው እየበዛ በእሚሄደው ሪከቨር እሚያደርጉ ህሙማንን እና በአንፃሩ ደሞ ቁጥራቸው እየቀነሰ በእሚሄደው ህይወታቸው የአለፈ ህሙማንን የደመረ] <u>ሪሙቭድ</u> የተደረጉ ሰዎች ብዛትን ሪፕረዘንት እሚያደርግ ላየን–ግራፍ፤

በኅሊናችሁ ውስጥ ፍጠሩ እና — ተከተሉኝ።

<u>ቨርቲካል አክሲስ፤</u> ከዜሮ ተነስቶ — ዜሮ ነጥብ አንድ፣ ዜሮ ነጥብ ሁለት፣ ዜሮ ነጥብ ሦስት እየአለ እስከ አንድ እሚዘልቅ። <u>ሆሪዞንታል አክሲስ፤</u> ከዜሮ ተነስቶ — አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት እየአለ እስከ 63 እሚደርስ። ቨርቲካል አክሲሱ፤ ሪፕረዘንት እሚያደርገው፤ ሰሴፕትብል፣ ኢንፌክቲቭ እና ሪሙቭድ እሚሆኑ ሰዎች ብዛት <u>መጠንን</u> ነው። ሆሪዞንታል አክሲሱ ደሞ፤ ሪፕረዘንት እሚያደርገው፤ ወረርሽኙ በአንድ ኅብረተብ ውስጥ እና በአንድ የተወሰነ ጂኦግራፊ፤ የቆየባቸው <u>ጊዜያት</u> በ እየ ዕለቱ ሲደረደሩ ነው። ስድሳ–ሦስት ቀናት ያ–ው ሁለት ወር ገደማን እሚያካትት ነው እሚሆነው። ቨርቲካል አክሲሱ እና ሆሪዞንታል አክሲሱ ኢንተርሴክት የእሚያደርጉት ደሞ፤ ሁለቱም [መጠን እና ጊዜ] ዜሮ የሆኑበት ቦታ ላይ ነው።

ትንሽ ቀደም ብዬ በተራቁጥር 3 ላይ የጠቀስኩት ስቴት ቫርየብል፤ “ሪሙቭድ” የተባለውን ማለቴ ነው፤ ዋናው ኮንሴፕቱ — በቫይረሱ ተይዘው ሪከቨር እሚያደርጉ ሰዎች፤ የሆነ [የአጭር ጊዜ ወይም የእረዥም ጊዜ] አንቲቦዲስ/ኢምዩኒቲ ይኖራቸዋል በእሚል እና ህመሙን መቋቋም ተስኗቸው ህይወታቸው እሚያልፍ ሰዎችን ጨምሮ፤ “ሪኢንፈክትድ” ሊሆኑ ስለእማይችሉ፤ ሰሴፐትብል ከነበሩት ሰዎች ጋር ተመልሰው ሊቀላቀሉ የእማይችሉ መሆንአቸውን እሳቤ በማድረግ፤ ኮንሴፕችዋሊ እንደ አንድ ዩኒት መቆጠራቸው፤ ስለ ወረርሽኝ እስከአወራን ድረስ — ሴንስ እሚሰጥ በመሆኑ የተፈጠረ ኮምፓርትመንት ነው።

የአንድ ወረርሽኝ ሁለዕንተንዓዊ ሂደት እሚወስነው፤ ሦስቱ ስቴት ቫርየብልስ፤ ወረርሽኙ በእሚቆይባቸው ቀናት ውስጥ — በጋራ በእሚያሳድሩት/በእሚያስተናግዱት ተፅዕኖ ሳቢያ፤ በእየግልአቸው በእሚወክሉት የ ህዝብ ብዛት፤ የመቀነስ/የመጨመር ባህሪያቸው ነው።

ቀደም ብዬ ጠቆም አድርጌ የአለፍኩት፤ “ዲፍረንሻል ኢኳዝንስ” ዋናው ተግባርአቸው፤ በአንድ ጂኦግራፊ ውስጥ ንዋሪ የሆነን <u>ሰሴፐትብል</u> ህዝብ ቁጥር ብዛት እግምት ውስጥ በማስገባት፤ ትራንስሚሽን ሬት [የህዋሱ/ፓርቲክሉ ስርጭት ፍጥነት] እና ሪከቨሪ ሬት [ህዋሱ/ፓርቲክሉ የያዛቸው ሰዎች እሚያገግሙበት ፍጥነት] እሚባሉትን ፐራምትርስ “የተማረ–ግምት” በመስጠት

— ብሎም፤ ኮንታክት ሬሽዖን እና ቤዚክ ሪፐሮዳክቲቭ ሬሽዖን በማስላት፤ የ ሳርስ-ኮቭ-2 ወረርሽኝ “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” ከፍተኛው መጠን ምን ያህል እንደእሚሆን እና መቼ እዚያ ደረጃስ እንደ እሚደርስ፤ ቁልጭ አድርጎ ማሳየት ነው።

ለ ጥያቄ ሁለት መልሱም — ይሄው “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” የእሚነግረን ቁጥር ነው እሚሆነው።

በጎሊናችሁ ውስጥ እየአያችሁት ወደአለው፤ ሦስቱ ስቴት ቫርየብልስን ወደ የአካተተው ላየን–ግራፍ ስመለስ...........

(ሀ) — ፖቴንሻሊ፤ ኅብረተሰቡን በሙሉ ሊያካትት ይችላል ተብሎ እሚገመተው ሰሴፐትብል የሆነው ህዝብ ብዛት [መጠን] በፍጥነት እየአሽቆለቆለ ኢምንት ወደመሆን ሲጓዝ፣ (ለ) — ሪከቨር እሚያደርጉት ሰዎች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ሲሄድ እና ህይወታቸው እሚያልፈው ሰዎች ኢምንት እየሆነ ሲመጣ፤ እናም ሪሙቭድ እሚደረጉት ሰዎች ብዛት ከ ዜሮ ተነስቶ በፍጥነት እየአደገ በእሚጓዝበት [ጊዜ]፤ ሁለቱ [ ሀ እና ለ] እኩል አንድ [መጠን እና ጊዜ] ነጥብ ላይ ሲገጥሙ ነው፤ የ ሳርስ-ኮቭ-2 ወረርሽኝ፤ እንደ አዲስ በቫይረሱ እሚያዙ ሰዎች ቁጥር በፍጥነት ከማደግ በመቆጠብ፤ አደብ ገዝቶ “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” ደረጃ ላይ እሚደርሰው።

ማለትም፤ “ፍላተንኢንግ ዘ ከርቭ” ወይም “ፕላትዖ” እሚባለው ክስተት ላይ፤ ለሆኑ ቀናት እረፍት እሚወስደው።

ከእዚያ በኋላ ነው እንግዲህ፤ የከፋ ነገር እስከአልገጠመ ድረስ፤ ቤዚክ ሪፐሮዳክቲቭ ሬሽዖው ከ አንድ በታች ዝቅ እየአለ እንዲሄድም እሚገደደው።

ይ-ህ ፌኖምና፤ ቀደም ብዬ የጠቀስኩላችሁን ኤስ-አይ-አር ሟድል በመጠቀም እሚዘጋጅ ላየን-ግራፍ ላይ፤ ኢንፌክቲቭ የሆኑ ሰዎችን መጠን እሚጠቁመው ከርቭ፤ “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” ከደረሰ በኋላ፤ በፍጥነት እያችቆለቆለ በእሚሄደው የ ሁለተኛው አጋማሽን በ እሚጠቁመው ሴግመንት ይንፀባረቃል።


ማለትም፤ ቤዚክ ሪፐሮዳክቲቭ ሬሽዖ ከ አንድ በታች ዝቅ እየአለ ስለእሚሄድ እና የ ሳርስ-ኮቭ-2 ስርጭት፤ ወረርሽኝ ሆኖ የመቀጠል ጉልበቱ ስለእሚዝል፤ ኢንፌክቲቭ የሆነው ሰው ቁጥር መጠን፤ በፍጥነት እያሽቆለቆለ፤ ኢምንት ወደ መሆን ብሎም ዜሮ ወደ መሆን ደረጃ ይገፈተራል።

ያ–ኔ ነው እንግዲህ፤ ወረርሽኙ ሊያደርስ የቻለውን ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ ሁሉ አድርሶ — እሚያልፈው ወይም እሚያከትመው። ምንአልባትም፤ እንደገና እስከ እሚከሰት ድረስ!

<u>መልስ ሁለት — ጥያቄ ሁለትን በተመለከተ፤</u>

አዎ፤ በ ሳርስ-ኮቭ-2 ተይዘው፤ ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ ሰዎች ከፍተኛ ብዛትአቸው “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” እንዲያው [ከፍ የአለ] ነው ብቻ ተብሎ የ እሚታለፍ ሳይሆን፤ ፖቴንሻሊ — ከ ሰባ ፐርሰንት በላይ የእሚሆነውን ህዝብ እሚያካትትም ሆኖ፣ በጣም በጥቂት ቀናት ውስጥም ሊከሰት ይችላል በእሚል ነው መታየት የአለበት። <u>ተገቢውን የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃ ፈጥነን እስከአልወሰድን ድረስ!</u>

ይ–ህንን የመሰለ ቁጥር — ማለትም፤ “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” ነው እንግዲህ — ምናልባትም፤ ለ ሄልዝ ፐላነርስ ጠቀሜታ እንዲሆን በእሚል ተዘጋጅቶ፤ ሁልአችንም ጆሮ የደረሰው እና በእዚህ በአሳለፍነው ወር ውስጥ — አነጋጋሪ ሆኖ የሰነባበተው።




<u>ማስታወሻ፤</u> ይ–ህ ቀመር ሃይፖተቲካሊ በአሰፈርኳቸው ፐራምትርስ ላይ በመመርኮዝ፤ ቤዚክ የሆነ ኤስ-አይ-አር ሟድልን ተጠቅሜ የአገኘሁትን ሲምዩሌትድ ዳታ እሚያንፀባርቅ ነው። ማለትም፤ የትእኛዉንም ህዋስ/ፓርቲክል፣ የትእኛውንም ወረርሽኝ ሆነ የትኛውንም ሃገር እሚመለከት ሳይሆን — የተላላፊ በሽታ ወረርሽኝ ቲዮረቲካል ሂደቶች ውስጥ የአንዱን ገፅታ ለማንፀባረቅ ያህል ብቻ የአዘጋጀሁት ነው። በእዚህ ሲምዩሌሽን መሠረት — ኢንፌክቲቭ ማክሲመሙ 0.72 ነው (72 ፐርሰንት ማለት ነው)። በ መንደር “ምሳሌ” 10 ሚልየን ንዋሪዎች አሉ እንበል — [10,000,000 x 0.72 = 7,200,000]። ይህንን ያህል እጅጉን ከፍ የአለ ሰው ነው እንግዲህ፤ በአንዲት መንደር ብቻ እና ከወር በአነሰ ጊዜ ውስጥ በቫይረሱ ሊያዝ እሚችለው! <u>ተገቢውን የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃ ፈጥነን እስከአልወሰድን ድረስ።</u>

ኀበዝ፤

እዚህ ላይ፤ ሁለት የወረርሽኝ ዓይነቶች እንደአሉም ማስታወሱ ጥሩ ነው። ፖይንት ሶርስ ኤፒደሚክ እና ፕሮፓጌትድ ኤፒደሚክ እሚባሉ።

ለዛሬ፤ ፖይንት ሶርስ ኤፒደሚክን የጎሪጥ አይቸው እንዳልፍ ፍቀዱልኝ እና፤ እንደ ሰሞነኛው የአለ ከሰው-ወደ-ሰው እሚተላለፍ፤ ፕሮፓጌትድ ኤፒደሚክ አንዱ መገለጫው፤ በ ቫይረሱ ተይዘው፤ ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ ሰዎች ከፍተኛው ብዛትአቸው መጠን “ኢንፌክቲቭ ማክሲመም” ደረጃ ላይ እሚደርሰው፤ ያ–ም ማለት፤ “ፍላተንኢንግ ዘ ከርቭ” ወይም “ፕላትዖ” ላይ እሚደርሰው፤ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁለት ሦስት አራት አምስት ጊዜ – ምናልባትም፤ ከእዚያም በላይ ሊሆን የመቻሉ ነገር ነው።

እናም፤ ገና-ለ-ገና “ፍላተንኢንግ ዘ ከርቭ” ወይም “ፕላትዖ” ላይ ደርሷል፣ ኢንፌክቲቭ የሆኑ ሰዎች ቁጥር የዕድገት ፍጥነት ትራጀክተሪ ዚሮ ስሎፕ ላይ ደርሷል ተብሎ፤ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እየተወሰዱ የአሉትን ወሳኝ እርምጃዎች በጥድፊያ ማላላላት፣ ማንሳት ወይም መሰረዝ፤ አደጋው የከፋ ነው እሚሆነው። እየቀነሰ የእሚሄድ መስሎ፤ በቀናት ውስጥ እንደገና ሊያገረሽ እና ሌላ ከፍ የ አለ፤ ብሎም ተደጋጋሚ የሆነ ኢንፌክቲቭ ማክሲመም ደረጃ ላይ መድረሱ — እማይቀር ሊሆን ይችላል እና!

ይህ–እንን በተመለከተ፤ ሃላፊዕነት የአለበት አካል ቢያደርግ ይበጃል ተብሎ እሚመከረው፤ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እየተወሰዱ የአሉትን ወሳኝ እርምጃዎች፤ ተሽቀዳድሞ ከማላላት ከማንሳት ከመሰረዝ በፊት —ኢንፌክቲቭ ማክሲመም ደረጃ ላይ ከተደረሰ በኋላ፤ ቢያንስ፤ ሁለት ኢንኪዩቤሽን ፒርየድስ ለ እሚሸፍን ጊዜ፤ እረጋ ብሎ በጥንቃቄ ማየትን ነው።

ተላላፊ በሽታዎችን በተመለከተ እንግዲህ፤ ከፍ ብዬ ላይ–ላዩንም ቢሆን የጠቃቀስኳቸውን ዘረፈ–ብዙ ባህሪያት በእሚገባ እና በጥሞና መረዳት፤ ለ ጤና ፖሊሲ ፕላኒንግ እና ሪሶርስ ዲስትሪቢውሽን ጠቀሜታው፤ እጅጉን – አዎ፤ እጅጉን ወሳኝ ነው።

ማብራሪያ ሦስት — ጥያቄ ሦስትን በተመለከተ፤

በወረርሽኙ መገባደጃ ላይ፤ በድምሩ ምን ያህል ሰዎች ኮቪድ–19 ሊከሰትባቸው ይችል ይሆን ወይም ሊከሰትባቸው ችሎ ነበር የእሚለውን ጥያቄ ማለቴ ነው። በተደጋጋሚ እንደአነሳሁት፤ እንደ ሰሞነኛው ዓይነት — ከአጀማመራቸው፤ ኮንታክት ሬሽዖአቸው እና በተጓዳኝም ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖአቸው ከፍተኛ የሆኑ ተላላፊ በሽታዎች፤ በ ቫይረሱ ተይዘው፤ ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ ሰዎች — ማለትም፤ በሽታው የያዛቸው ሰዎች ብዛትአቸው፤ [የበሽታዎችን ፎርማል ክላሲፊከሽን ኮድ ለጊዜው ወደ ጎን ትተን ማለቴ ነው] ሁሉንም ኅብረተሰብ ሊያካትት ይችላል በእሚል መጠን፤ እጅጉን ከፍተኛ ነው እሚሆነው — ፖቴንሻሊ!

ደግዕነቱ፤ ሳርስ–ኮቭ–2’ን በተመለከተ በ ቫይረሱ ተይዘው፤ ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እሚችሉ ሰዎች እጅጉን ብዙ መሆናቸው አስፈሪ የመሆኑን ያህል – ከእነሱ ውስጥ፤ በቀላሉ እሚያልፍላቸውም ሆነ ጠንከር ብሎባቸውም ቢሆን [በህክምና ዕርዳታ ጭምር] ሪከቨር እሚያደርጉ ሰዎች ብዛትም እንዲሁ እጅጉን — አዎ፤ እጅጉን ብዙ ነው እሚሆነው።

አንዳንዶች ግምታቸውን ወደ 80 ፐርሰንት ያደርሱታል።

ገና እየተጠና ስለሆነ፤ በ ሳርስ-ኮቭ-2 መያዝ በ ሰውነታችን ውስጥ ሊፈጥር “ስለእሚችለው” አንቲቦዲስ ዛሬም ብዙ ማለት አይቻልም። ኤክስፖዝድ ወይም ኢንፌክትድ የሆነ ሰው፤ ሾርት–ተርም በተለይም ሎንግ–ተርም አንቲቦዲስ መፍጠር እሚችል ከሆነ፤ ወደፊት እንደገና ሊከሰት እሚችለውን የ ሳርስ-ኮቭ-2 ወረርሽኝ፤ ብዙም አስፈሪ እንዳይሆን ያደርገው ይሆናል የእሚል ተስፋን የሰነቀ ሃሳብ ነው፤ ለጊዜውም ቢሆን እየተንሸራሸረ የአለው።

መልስ ሦስት — ጥያቄ ሦስትን በተመለከተ፤

በወረርሽኙ መገባደጃ ላይ፤ ምን ያህል ሰዎች ኮቪድ–19 ሊከሰትባቸው ችሎ ነበር ለእሚለው ጥያቄ መልሱ፤ ፖቴንሻሊ – ከጥቂት ተዐምረኛ ሰዎች በስተቀር፤ ሁሉም የኅብረተሰብ አባል ነው የእሚል ነው። ተገቢውን የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃ ፈጥነን እስከአልወሰድን ድረስ!

ምን አለፋችሁ፤ ለ ቫይረሱ ኤክስፖዝድ እናም ኢንፌክትድ ሆነው፤ ነገር ግን በተወሰኑ ቀናት ውስጥ [በህክምና ዕርዳትም ጭምር] ሪከቨር የአደረጉ ሰዎችን እና ህመሙን መቋቋም አቅቷቸው ህይወታቸው የአለፈ ሰዎችን ቁጥር መደመር ብቻ ነው።

ኀበዝ፤

በቫይረሱ ሊያዙ እሚችሉ ሰዎች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ሊሆን እንደእሚችል በተደጋጋሚ መጥቀሴ — ወረርሽኙን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ምንም ሳንሰራ፤ እጃችንን አጣጥፈን የተመለከትን ሲሆን ብቻ ነው በእሚል እሳቤ እንደሆነ ልብ እንድትሉልኝ አበክሬ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። ለእዚያም ነው፤ ያ–ንን ተገቢ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ፤ በተደጋጋሚ መጥቀሴን እርግጠኛ እንድሆን፤ በድርብ ሰረዝ አፅንዖት ሰጥቼባቸው የአለፍኩት።

ደግዕነቱ፤ እንኳን ዛሬ እና — የጥንታዊው ጥንት የሰው ልጅም ቢሆን፤ ወረርሽኝም ሆነ ሌላ ችግር ሲገጥመው፤ እጁን አጣጥፎ የተመለከተበት ጊዜ አልነበረም። አዎ፤ ዕምነት፣ ዕውቀት እና አቅም በፈቀደ መጠን፤ የእሚቻለውን ሁሉ ስለ አደረገ ነው፤ የሰው ልጅ ህይወት ሊቀጥል የቻለው።

ያ–ም በመሆኑ፤

የ ሳርስ-ኮቭ-2 ወረርሽኝን በተመለከተ፡ በሙያተኛ ተሰልተው እሚወጡ ከፍተኛ ቁጥሮች እሚያንፀባረቁትን — ማለትም፤ ፖቴንሻሊ [የተደቀነብንን ሁለእንተንዓዊ ቀውስ] ለመቀነስ እንድንችል እና እኛም በተራአችን የሰው ልጅ ህይወት

እንዲቀጥል ለማድረግ እንችል ዘንድ፤ ["እምልህን ከአልተገበርክ አስርህ አለሁ እንዲህ አደርግሃለሁ"] የእሚልውን ኋላቀር፤ ብሎም ኢ–ሰውዓዊ ቋንቋ ወዲያ ትተን፤ ቀና በሆነ መንፈስ ኅብረተሰብአችንን ለማገልገል በእሚጠቅም መልኩ፤ ልንተገብራቸው እሚገባቸውን፤ ወረሽኝን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በእሚል እሚጠቆሙ መፍትሄዎችን፤ ሳናመነታ ተግባርዓዊ እናደርግ ዘንድ — አደራ እላለሁ።

ከ የመፍትሄ ሃሳቦች ውስጥም፤ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል በእሚል በ ዓለም ዙሪያ የእሚገኙ ሙያተኞች በአፀንዖት እሚጠቁሙአቸው እና እኔም በ እሚገባ እምጋራቸው፤ የ እሚከተሉት ናቸው።

<u>የ መፍትሄ ሃሳብ (ሀ) — ሳርስ-ኮቭ-2 ሊይዛቸው እሚችሉ [ሰሴፕትብል የሆኑ] ሰዎችን ብዛት መቀነስ።</u>

ከላይ እንደ ጠቀስኩት፤ ቫይረሱ አዲስ በመሆኑ እና ማንአችንም ኢምዩኒቲ አለን ተብሎ ስለእማይገመት፤ ሰሴፕትብል የሆኑ ሰዎች ቁጥር እጅጉን ከፍተኛ ነው እሚሆነው።

ያ–እንን ተሽቀዳድሞ መቀነስ መቻል፤ ከ የ መፍትሄ ሃሳቦች ሁሉ በቀዳሚዕነት እሚጠቀስ ነው።

ሰሴፕትብል የሆኑ ሰዎችን ብዛት ለመቀነስ፤ ከመጀመሪያውእኑ ልንወስድ እንችል የነበረው እርምጃ ደሞ፤ ቀደም ብለን ተገቢውን <u>ክትባት</u> ለ ኅብረተሰብአችን በሰፊው ማዳረስን ነበር — ኸርድ ኢምዩኒቲ እሚባለውን ለመገንባት።

በነገራችን ላይ፤ ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖው አራት ለሆነ ተላላፊ በሽታ፤ በቂ የሆነ ኸርድ ኢምዩኒቲ ለመገንባት፤ ሰሴፕትብል ከሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ፤ ቢያንስ 75 ፐርሰንት የሆነው ሰው ክትባቱን ማግኘት ይጠበቅበታል። ችግሩ፤ ያ–ንን በአሁኑ ጊዜ ተግባርዓዊ ለማድረግ፤ ዝግጁ አይደለንም። የ ሳርስ–ኮሮናቫይረስ–2'ን ስርጭት ለመከላከል እሚረዳ ክትባትም ሆነ አንቲቦዲዎችን በተመለከተ፤ ተስፋ እሚጣልባቸው ስራዎች እየጨመሩ ከመምጣታቸው በአሻገር – ዛሬ ጥቅም ላይ የሚውል ክትባትም ሆነ አንቲቦዲ ፈልጋችሁ አታገኙም።

ህምምም................ እንድ ነገር ትዝ አለኝ!

ብዙ ሰዎች በነፍስ–ወከፍ ኤክስፖዝድ ወይም ኢንፌክትድ ሲሆኑ፤ ምንአልባትም ናቹራሊ ሊፈጥሯቸው በ እሚችሏቸው አንቲቦዲዎች ሳቢያ፤ ገና–ለገና ኸርድ ኢምዩኒቲን ለመገንባት እንችላለን በእሚል — ሰዎች ኢንፌክትድ እንዲሆኑ እጅ እና እግራችንን አጣጥፈን እንመልከታቸው ማለት፤ ሃላፊዕነት የጎደለው የተንሸዋረረ ሃሳብ ተደርጎ ነው ሊወሰድ እሚገባው። የስዊድንን እና የኖርዌይን ኮምፓሪዝን ፈልጋችሁ አንብቡ።

<u>የ መፍትሄ ሃሳብ (ለ) — ኮንታክት ሬሽዖን እና ተጓዳኝ የሆነውን ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖን መቀነስ።</u>

ይህ–እንን ማድረግ አሳምረን እንችላለን። እንዲያውም፤ አሁን በዋናዕነት ማድረግ እምንችለው ቁምነገር ቢኖር፤ ይህ–እንን እና ይህ–እንን ማድረግ ብቻ ነው።

እጆቻችንን መታጠብ፣ ጠቅላላ የአካልአችንንም ሆነ የ አካባቢያችንን ንፅህና መጠበቅ፣ ከማንም ሆነ ማንም ጋር በአካል ሁለት የአዋቂ እርምጃዎችን ያህል መራቅ፣ ሳልን እና ማስነጠስን በእሚገባ መሸፈን፣ ትፍፍግን ማስወገድ፣ አፍ እና አፍንጫችንን በማስክ ወይም በሆነ ሻርፕ መሰል ጨርቅ መሸፈን፣ ፊዚካል ዲስታንሲንግ'ን በአግባቡ ተግባርዓዊ ለማድረግ እንዲያግዙ እንቅስቃሴዎችን ሃላፊዕነት በተሞላው መልኩ መግታት — ስክሪኒንግ፣ ቴስቲንግ፣ ኳራንቲን ማድረግን፣ ኬዝ ፋይንዲንግ እና ኮንታክት ትሬሲንግ'ን አጠናክሮ መቀጠል ሁሉ፣ የግድ ነው። አደጋው እስከእሚያልፍ — ምንአልባትም፤ የ ኢንፌክቲቭ ከርቭ በፍጥነት ከ ማሻቀብ አደብ ገዝቶ፣ [ፍላተንኢንግ ዘ ከርቭ] የ እሚባለው ደረጃ ደርሶ ሲያበቃ፤ በአስተማማኝ መልኩ በፍጥነት ቁልቁል ወርዶ፤ ኢምንት ወይም ዜሮ ወደ እሚሆንበት ደረጃ ላይ፤ እስከ እሚደርስ ድረስ!

የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን ሁሉ፤ ቆፍጠን ብለን ተግባርዓዊ በማድረግ — ማለትም፤ በ ሰሴፕትብል የሆኑ ሰዎች እና ኢንፌክቲቭ በሆኑ ሰዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን፤ በአልተገደበ የዕለት–ተዕለት የህይወት ስብጥር እንቅስቃሴ ምክንያት፤ ሳርስ-ኮቭ-2 ኖሮባቸው ለሌሎች ማስተላለፍ ከእሚችሉ ኢንፌክቲቭ ከሆኑ ሰዎች ጋር በቀረቤታ ኮንታክት ሊያደርጉ እሚችሉ ሰሴፕትብል ሰዎች ብዛትን በመቀነስ፤ በተደጋጋሚ የጠቀስኳቸውን ኮንታክት ሬሽዖ እጅጉን መቀነስ እና ተጓዳኝ የሆነውን ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖ ከ አንድ በታች ወርዶ፤ ኢምንት እና ዜሮ መጠን ላይ ማድረስ ይቻላል።

<u>የ መፍትሄ ሃሳብ (ሐ) — ለ ሳርስ-ኮቭ-2 ኤክስፖዝድ ብሎም ኢንፌክትድ መሆንን የአላመለጡ፤ ነገር ግን በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ሪከቨር እሚያደርጉ ሰዎችን ብዛት ከፍ ማድረግ — እንዲሁም፤ ኢንፌክሽኑን መቋቋም አቅቷቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እሚችል ሰዎችን ብዛት መቀነስ።</u>

ይህ–እንን ማድረግ መቻል፤ የግድ ነው።

እዚህም ላይ ነው እንግዲህ፤ እንደ አንድ የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ በወል የደርስንበት የስልጣኔ ደረጃ — ብሎም፤ የአንድ ሃገር ሁለዕንተንዓዊ ዕድገት እና የጤና ተቋምአት ቁመና – ጉድ እሚፈላው።

የ መድሃኒቶች [ምናልባትም አንቲቦዲስን ጨምሮ]፣ የ ዘመናዊ ህክምና መሳሪያዎች ተደራሽዕነትን እና አቅርቦትን ከፍ ማድረግአችንን፤ ብሎም — ከአቅም በላይ አለመሆንአቸውን እርግጠኞች መሆን። በሽታን የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት ፕሮግራሞችን ማዘመን፣ ማሳደግ እና ማጎልበት። የጤና ባለሙያዎችን ቁጥር በ በእጅጉ ከፍ ማድረግ እና ለዜጎቻችን [በገጠር አካባቢዎች እሚኖሩትን እማይዘነጋ] ተደራሽ፣ ዘመንዓዊ፣ ስልጡን እና ጠንካራ የጤና ተቋምአትን መገንባት — በቃላት መግለፅ ከ እሚቻለው በላይ ለዘርፈ-ብዙ ችግሮችአችን ወሳኝ ፈውሶች ናቸው — ኢንፌክትድ ከመሆን ማምለጥ የአልቻሉትን በመርዳት፤ ሪከቨር ሊያደርጉ እሚችሉ ሰዎችን ቁጥር ከፍ ለማድረግ እና ኢንፌክሽኑን መቋቋም አቅቷቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እሚችል ሰዎችን ቁጥር ደሞ፤ በእጅጉ ለመቀነስ።

እነእኝህን ሁሉ በማድረግም — የቫይረሱን ስርጭት አቁመን፤ የታማሚንም ሆነ ህይወታቸው እሚያልፍ ሰዎችን ቁጥር ወደ ዚሮ ደረጃ በማውረድ፤ የ "ኮቭ" ጦርዕነትን መቋቋም እና ፍልሚያውን በ ድል መወጣት እንችላለን።

በመጨረሻም፤

ዛሬ፤ የጠቃቀስኳቸው ኮንሰፕቶች፣ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች ሁሉ፤ የጋራ እና ወሳኝ ዕውቀቶቻችን ናቸው። በ ጤና ባለሙያዎች እና በ መንግስት አካላት እየተጠቀሱም፣ እየተመከሩም ሆነ እንደ መመሪያም ጭምር እየተላለፉ የአለውም፤ ያ–ን ያህል የሞት የሽረት ጉዳዮች ሰለሆኑ እንደሆነ እና ሁልአችንም ሃላፊዕነታችንንም ሆነ ግዴታችንንም መወጣት እንደአለብን፤ ለማስገንዘብ ነው። እኔም፤ የአለመሰልቸት ደግሜ ደጋግሜ ሃሳቤን ማካፈሌ'ን፤ እንደ አንድ ያገባኛል ባይ — ሰውዓዊ ሃላፊዕነቴ እድርጌ ነው እምቆጥረው። ያ–ንን በ አደረግሁ ጊዜም ሁሉ፤ መታደሌን ስለእሚያስታውሰኝ፤ ፈጣሪ ዓምላኬን ዝቅ ብዬ አመሰግን አለሁ።

ከምንም በላይ ቅድሚያ በመስጠት፤ ሁለዕንተንዓዊ በሆነ መልኩ ተዘጋጅተን — የሰው ልጅን ህይወት የአለጊዜው ሊነጥቅ እሚችል፤ እንደ የ[የጎሣ ፖለቲካ] ሰው–ሰራሽ የሆነ እና እንደ [ሳርስ–ኮቭ–2] የተፈጥሮ አደጋዎች — ከመከሰታቸው በፊት፤ አልያም – የከፋ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት፤ ተቋምዓዊ በሆነ መልኩ፣ በዘላቂዕነት ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት ሌት–ተቀን ዘብ ቆመን መገኘትን — ስልጡን ኢትዮጵያዊ ባህል አድርገን ከተቀበልነው እና ከአዳበርነው፤ ሌላ–ሌላ ነገሮቻችን ሁሉ [ሲምለሥሊ] ተመቻችተውእልን እናገኛቸውአለን ብዬ በፅኑ አምን አለሁ።

በሉ እንግዲህ፤ በፍፁም መዘናጋት አይገባም — በርቱ። የጫጫርኳትን፤ ጊዜ ወስዳችሁ ስለአነበባችሁአትም፤ አመሰግን አለሁ!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዬ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# የህይወት ነፀብራቅ

ትናንትን በቀናዕነት ለመዘከር – ዛሬን በዕውነተኛዕነት ለመታደግ – የተሻለ ነገን ለመገንባት

ሰኔ ፪ሺህ፲፪ ዓ.ም ‖ ጁን 2020

<u>ልዩ ዕትም</u>

**አዳራሽ** — በይነመረብ ላይ አሻራዬን ለማኖር በእሚል፤ አዳራሽ'ን ከገነባሁ፤ ይኸውዕና በዛሬዋ የሰኔ ወር፤ አስር ዓመታት'ን አስቆጠርሁ። እናም፤ የ ሰኔ ወር በመጣ ቁጥር፤ ወርሃዓዊ መጣጥፌን "ልዩ ዕትም" እሚል ነገር-ማሳመሪያ ቢጤ ሃረግ በመዶል፤ ቀልብአችሁን የበለጠ ለመሳብ እየሞከርሁ የ ለሁት፤ የ አዳራሽ ዓመትዓዊ በዓል'ን እንደ-ማክበር እየቃጣኝ እንደሆነ፤ ፍንጭ ለመስጠት ያህል ብቻ ነው — ለጤናችን! አንባቢዎቼ፤ አዳራሽ ሁለዕንተንዓዊ ጉዳዮችን እንደእምታስተናግድ ታውቃላችሁ። ዛሬ'ም ቢሆን፤ ከ ዋሾው፣ ከ አፍራሹ፣ ከ አጥፊው የጎሣ-ፓለቲካ፤ እንዲሁም ከ ኮሮናቫይረስ ጋር የገጠምነውን "ጦርዕነት" መቋቋም፤ ብሎም ፍልሚያውን በድል መወጣት ዋና–ዋናዎቹ ጉዳዮቻችን ቢሆኑ'ም፤ በ ጥቁር ዓባይ ዙሪያ አልረግብ የአለው ውዝግብም ሃገርዓዊ ትኩረትን እሚሻ ጉዳይ መሆኑ'ም አልቀረ — የኋለእኛው ከልኩ ያልፋል እሚል ስጋት ባይኖረኝም። ብዙ ነገር ብለናል፣ ተብሏል፣ እየተባለም ነው — ስለ እኛ። እንደ ስልጡን ኅብረተሰብ በጋራ ማሰብ ስለአቃተን፤ የረባ ነገር ስንሰራ አንታይም እንጂ! መቼም፤ በሃገር እና በህዝብ ተቆርጦ አይቆረጥም ሆኖብኝ እንጂ፤ የእኛ ነገር ጊዜ አባካኝ'ም ተስፋ አስቆራጭ'ም ነው። እንደ-እኔ እንደ-እኔ፤ ዛሬም ቢሆን፤ ሁልአችንም በጋራ እናሸንፍ ዘንድ፤ የ ስልጡን ህይወት ነፀብራቅ ፍንትው አድርጎ እሚያሳየን'ን <u>ቀና መንገድ</u> መከተል የቅንጦት አማራጭ ሳይሆን፤ የግድ መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል፤ ባይ ነኝ። ያ–ም መንገድ፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ ከ እሚያቅፍ ስልጡን ምክክር ተነስቶ፤ በ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግስት የተሟላ ድልድይዕነት፤ አዲስ ህገመንግስት ቀርፆ፣ ተየህ-ማዶ ወዲያ-ማዶ በቁርጠኛዕነት ዘልቆ ተሻግሮ፤ ወደ ኢትዮጵያዊ ህዝባዊ መንግስት ምስረታ እሚወስደን፣ እሚያደርሰን ቀና'ው አዳራሽ'አችን ነው። ዕመኑኝ፤ አሁን የተያያዝነው መንገድ፤ የትም እሚያደርሰን አለመሆኑ ብቻም ሳይሆን፤ አጥፊያችንም ነው። በግልፅ እየታየ ዕኮ ነው። አካሄዳችን ሁሉ፤ አብሮ የመኖር ሃሳብ እንደአለው ዜጋ ሳይሆን፤ የቀማኛ-የወራሪ-የባዕድ አካሄድ ነው — አካሄዳችን ሁሉ፤ ኢትዮጵያዊዕነትን የማጥፋት የተቀነባበረ ዘመቻ ነው። የአንድዕነት ኃይሉ'ም ቢሆን፤ በሚረባው በእማይረባው እርስ በእርሱ እየተናቆረ፤ አሸናፊ በሆነ መልኩ መደራጀት'ን አሻፈረኝ በማለቱ፤ እየነደደ በአለው እሳት ላይ ቤንዚን እያርከፈከፈ — አፈራረሳችን'ን አጠፋፋችን'ን እየአባባሰው እየአፋጠነው መሆኑ፤ እንጅጉን — አዎ፤ እጅጉን ያሳዝናል።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች — እንዴት ናችሁ?!

የዛሬው አመጣጤ ሁለት ጉዳዮች'ን አነሳስቼ ለማለፍ ነው። ላይ-ላዩንም ቢሆን። <u>ጉዳይ አንድ፤</u> ስለ ኢትዮጵያ በአለኝ ስጋት ላይ የአመዘነ አተያዬን በማካፈል፤ የኢትዮጵያ'ን ልጆች፤ ዛሬም – አዎ ዛሬም፤ ሰበብ መደርደሩን ትታችሁ አንድ አሸናፊ ህብረት ፍጠሩ ለማለት ሲሆን፤ <u>ጉዳይ ሁለት</u> ደሞ፤ የወቅቱ መነጋገሪያ ርዕስ በሆነው በ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ዙሪያ በማውጠንጠን፤ የኢትዮጵያ'ን ልጆች፤ ዛሬም – አዎ ዛሬም፤ የ ጤና ባለሙያዎች እና የመንግስት አካላት እሚሰጡትን ምክር እና መመሪያ ተቀብላችሁ በአግባቡ በመተግበር፤ ሁልአችሁም እንደ አንድ ስልጡን የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ አባል፤ ሃላፊዕነትአችሁን እና ግዴታችሁን፤ ቆፍጠን ብላችሁ ተወጡ — ለማለት ነው።

እናም፤ አብረን እንቆይ — የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።


**<u>ጉዳይ አንድ፤</u>** ሁለዕንተንዓዊ ፈተናዎቻችን

ዕውነት ነው፤ ፈተናዎቻችን ዘርፈ-ብዙ ናቸው። የእኛ ችግር ግና፤ ያ–አይደለም ባይ ነኝ። ለምን ቢሉ — ፈተና፤ [የህይወት ነፀብራቅ] ከ እሚያካትታቸው ህብረ–ቀለማት ውስጥ አንዱ በመሆኑ እና ቢያንስ–ቢበዛ እንጂ፤ ከ ፈተና ነፃ የሆነ ህይወት ስለ የሌለ።

ይልቁን እስ፤ የእኛን ችግር ለየት እሚያደርገው፤ ፈተናችን'ን እሚያጠነክር፣ ስቃይአችን'ን እሚያባብስ፣ እሚያራዝም እና መጥፊያችን'ን እሚያቃርብ መንገድ በመከተልአችን፤ እምንኩራራ፣ እምንዘባነን እና እምንደሰት የመሆናችን ዕውነታ ነው። የእኛን ችግር ለየት እሚያደርገው፤ ወንዝ መሃል ተንጠልጥሎ የቀረ የተጨናገፈ ማሻገሪያ ፕሮጀክት ላይ ቆመን እያንጎላጀን፤ የሰማዕታት አደራ በአባነነን ቁጥር ስንደነባበር፤ አንድ በ አንድ እየተንጠባጠብን ማለቃችን'ን አለማወቃችን፣ አለመረዳታችን እና አለመገንዘባችን ነው። የእኛን ችግር ለየት እሚያደርገው፤ የሺህ'ዎች ዘመናት ታሪክ የአለን ነን እየ አልን የመኩራራታችንን ያህል፤ አንድም ቀን ለምን ኋላ ቀር ምፅዋተኛ ሆነን ቀረን ብለን ስንጠይቅ እና በጋራ የመሻሻል በጋራ የመሰልጠን እልህ ሲይዘን አለመታየታችን ነው። እንዲያው ዝም ብለን በባዶ መዘባነን። አዎ፤ የእኛን ችግር ለየት እሚያደርገው፤ የጋራ ህይወታችንን ስልጡን እና ሰውዓዊ በሆነ መንገድ መምራት አለመቻላችን'ን — አለማወቃችን፣ አለመረዳታችን እና አለመገንዘባችን'ም ጭምር ነው።

ዛሬ'ም ቢሆን፤ ከ ዋሾው፣ ከ አፍራሹ፣ ከ አጥፊው፣ ከ ወራሪው የጎሣ-ፓለቲካ እና ከ ኮሮናቫይረስ ጋር የገጠምነውን "ጦርዕነት" መቋቋም፤ ብሎም ፍልሚያውን በድል መወጣት ዋና–ዋናዎቹ ፈተናዎቻችን ቢሆኑ'ም፤ በ ጥቁር ዓባይ ዙሪያ አልረግብ የአለው ውዝግብም ሃገርዓዊ ትኩረትን፣ ህዝብዓዊ ቁርጠኛዕነትን እና ብልጥዕነትን የእሚሻ ጉዳይ መሆኑ'ም አልቀረ — የኋለኛው ከልኩ ያልፋል እሚል ስጋት ባይኖረኝም። ከ ሉዓላዊ ግዛትህ እሚመነጭ'ን ወንዝ ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም የእሚል ህግ የለም። ኖሮም ከሆነ፤ ለዓለም ህዝብ ትምህርት ሊሆን በ እሚችል፤ ሰልጠን ፈርጠም የአለ [ሰላምዓዊ የሃሳብ ፍልሚያ] ለ አንዴ እና ለመጨረሻ፤ ኢሬስ መደረጉን እርግጠኞች እምንሆንበት ጊዜው አሁን ነው። ይህ አጋጣሚ ሊያመልጠን አይገባም። በፍፁም! አያያዙን አይተው፤ ጭብጦውን ቀሙት ይላል የሃገሬ ሰው። አዎ፤ ዛሬም ቢሆን ፖለቲካችን፣ ምጣኔ ሃብታችን፣ ኅብረተሰብዓዊ ህይወታችን፣ ጥናት እና ምርምርአችን፣ እንዲያው ምን አለፋችሁ፤ ሁለዕንተንዓዊ ስልጣኔአችን፣ እንዲያ እየሆነ፤ እንዲያው በደመነፍስ መንቀሳቀሱ እጅጉን እየጎዳን ነው።

ፐላኔት ምድር
12/31/2019 — 05/31/2020




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ዳታው [አፕዴት] የተደረገው ሜይ 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት ቆጣጠር ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

**<u>ጉዳይ ሁለት</u>**፤ ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ

የወቅቱ ወረርሽኝ የተለየ ትኩረት ማግኘቱ አግባብነት የአለው ጉዳይ ነው። ያ-ን ማለት ግን፤ ሌሎች የጤና ችግሮቻችን ይዘንጉ ማለት አይደለም። ይልቁን እስ፤ አዳዲስ ተጨማሪ ችግሮች ሲያጋጥሙን ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንችል ዘንድ፤ ዝግጅት አድማስአችንን ማስፋት እና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ቁመናችንን ማጎልበት ማዘመን ላይ ትኩረት ማድረግ የግድ መሆኑን እንደገና የአስታወሰን  የከፋ አጋጣሚ እንደሆነ ነው ሊቆጠር እሚገባው።

የ ሳርስ-ኮቭ-2 ቫይራል ፓርቲክል አዲስ መሆን፣ ኅብረተሰቡ ምንም ዓይነት ኢምዮኒቲ አለው ተብሎ ስለእማይገመት፣ ከሰው-ወደ-ሰው እጅጉን በቀላሉ የእሚተላፍ መሆኑ፣ ክትባትም ሆነ መድሃኒት የሌለው መሆኑ፤ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እሚወሰዱት እርምጃዎች የዕለት ተዕለት የአኗኗር ዘይቤአችንን መለወጥ የግድ ስለእሚያደርጉት እና የመግደል ጉልበቱ በተለምዶ ከእሚታየው ኢንፍሉዌንዛ ከፍ ያለ እንደሆነ ስለእሚታመን፤ እየተሰጠው የአለው ትኩረት፤ እንዲያውም ሊሆን ከእሚገባው ዝቅ የአለ ነው ማለት ይቻላል።

ያ-ም ሆነ ይ-ህ፤ የወቅቱ ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ፤ ዛሬ ሰባት ወራት'ን ሊያካልል በመጣደፍ  ላይ ነው። ይህችን ብሎግ እየጨራረስሁ እስከአለሁባት ቀን ድረስ'ም፤ በ ጥቅል ድምሩ በዓለም ዙሪያ — ወደ 6.03 ሚልየን እሚቆጠሩ ሰዎች በቫይረሱ እንደተያዙ፤ ከእነዚህም ውስጥ 6.1 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ'ም ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ተደርጓል።  ከፍ ብላችሁ እንደ የአያችሁትም፤ ከ 12/31/2019 እስከ 05/31/2020 በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ብዛት፤ <u>አራት</u> ጉልህ ባህሪያት'ን አንፀባርቋል። ለአራቱም ባህሪያት የ እየግላቸውንም ሆነ የ እየ ጋራ ክስተቶችን እንደ ምክንያት በመዘርዘር፤ ብዙ ብዙ ማለት ቢቻልም ቅሉ፤ ለዛሬ የህሙማንን ስርጭት በተመለከተ ብቻ የተወሰኑትን ጠቃቅሼ ልለፍ።

<u>ባህሪይ አንድ፤ (12/31/2019– 03/10/2020)</u>

[ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት፤ ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝ ደረጃ እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ | ስርጭቱ በቻይና እና በአካቢው ሃገራት የተወሰነ ይመስል ነበር | ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ብዛት በጥርጣሬ ታይቷል | አዲስ ቫይረስ እንደሆነ፣ ከሰው-ወደ-ሰው በቀላሉ እንደሚተላለፍ፣ ክትባትም ሆነ መድሃኒት እንደሌለው ታውቋል | ስርጭቱን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ወሳኝ እርምጃዎች ተወስደዋል | እጅን ማፅዳት፣ በአካል መራራቅ፣ በእየመኖሪያ ቤትአችን መመሸግ እና አፍ እና አፍንጫን መሸፈን ግዴታ ሆኑ | አንዳንድ ከተሞች ሙሉ በሙሉ ተዘጉ | ወደ ሌሎች አህጉራት መሰራጨቱ ግን አልቀረም | አየሩ በ ቫይረስ፣ በ ጥርጣሬ፣ በ ስጋት፣ እና በ ጭንቀት የተሞላ ይመስላል።]

ባህሪይ ሁለት፤ (03/11/2020–04/05/2020)

[ወረርሽኙ ከቻይና እና ኤዥያ አልፎ ወደ አውሮጳ፣ አሜሪካ፤ አፍሪቃ እና ወደ ሌሎችም አካባቢዎች በፍጥነት ተሰራጨ | ወደ ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝነት ከፍ ማለቱም ይፋ ሆነ | ኮቪድ-19 ተብሎም ተጠራ | በእየሃገራቱ ቴስት እሚደረጉት ሰዎች ቁጥር ጨመረ | በአውሮጳ እና በ አሜሪካ የህሙማን ቁጥር ኤክስፖነንሻሊ አደገ | ትንሽ ዘግየት ብሎም ቢሆን፤ እጅን ማፅዳት፣ በአካል መራራቅ፣ በእየመኖሪያ ቤትአችን መመሸግ እና እየአቅማማንም ቢሆን አፍ እና አፍንጫን መሸፈን ግዴታ ሆነ | ትልቅ ስጋት፣ መደናበር እና መረበሽ ሰፈነ።]

ባህሪይ ሦስት፤ (04/06/2020–05/12/2020)

[በሁሉም አህጉራት፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች በሰፊው ተግባራዊ ሆኑ | እጅን ማፅዳት፣ በአካል መራራቅ እና በእየመኖሪያችን መመሸግ፤ በተጨማሪም አፍ እና አፍንጫን መሸፈን በሰፊው ቀጠለ | እናም፤ ወረርሽኙ በፍጥነት መቀጣጠሉን ትቶ፤ ፈራ-ተባ እየአለ'ም ቢሆን፤ አደብ ገዛ | በአማካይ የተራዘመ "ፕላትዖ" ላይ ሰነባበተ፤ ኢንደሚክ ሆኖ የመቀጠል ፍላጎት እንደ አለው ፍንጭ ሰጠ | የምጣኔ ሃብቱ ስጋት የወረርሽኙን ስጋት የጋረደው ይመስላል | እገዳዎች እንዲቃለሉ ግፊቱ እየአየለ ነው | በዛ በአሉ ሃገራት በእየዕለቱ ሪፖርት እሚደርጉ ህሙማን ብዛት የመቀነስ አዝማሚያን ማሳየት ጀመረ።]

ባህሪይ አራት፤ (05/13/2020–05/31/2020)

[የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች ቀስ በቀስ እየላሉ መጡ | ወደ ቅድመ ወረርሽኝ ህይወት ለመመለስ እርምጃዎች መወሰድ ጀመሩ | በኅብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት ስሜት እየአደገ የመጣ ይመስላል | እንደ አህጉር፤ ከአውሮጳ በስተቀር በሌሎች አህጉራት ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ቁጥር እንደገና እየአገረሸበት እንደመጣ እየታየ ነው።]

ዝቅ ብላችሁ እንደእምታዩት ደሞ፤ አውሮጳ ከ ኤፕሪል 13 ጀምራ፤ ወረርሽኙ እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የቁልቁለቱን መንገድ አጥብቃ የተያያዘችው ይመስላል። በአንፃሩ'ም፤ በ አሜሪካ፣ ኤዥያ እና አፍሪቃ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እሚያደረጉት ህሙማን ቁጥር፤ እየጨመረ ከመሄድ ሊቆጠብ አለመቻሉ ነው ጎልቶ የታየው። አፍሪቃ በቀመሩ ላይ እስከ ኤፕሪል አጋማሽ ድረስ ድምጿን አጥፍታ ከቆየች በኋላ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲድ፤ ይኼው እኔስ ለምን ይቅርብኝ እየአለች ይመስላል።

አፍሪቃ — በእየዕለቱ ሪፖርት እምታደርጋቸው ህሙማን ቁጥር፤ ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ሆኖ ሳለም፤ እየአሻቀበ መምጣቱ ግን፤ አሁንም ቢሆን አሳሳቢ ነው።


ወደታች ወረድ ብላችሁ እንደ እምታዩት — ኢትዮጵያ፤ ኮቪድ–19'ን በተመለከተ በ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት መዝገብ ላይ የሰፈረችው፤ ማርች 14 ላይ ነው። ለ 20 ቀናት ገደማ እየአሰለሰች ሪፖርት ታደርግ የነበረቻቸው የሰዎች ብዛትም፤ በጣም ትንሽ እሚባል ነበር። ከ ኤፕሪል አራት ጀምሮ ኢትዮጵያ ሪፖርት እየአደረገች የአለቻቸው ህሙማን፤ በ እየዕለቱ ወደመሆን ቢቀየርም፤ መጠኑ ግን እስከ ሜይ የመጀመሪያው ሳምንት ድረስ [የ እየ ዕለቱን ማለቴ ነው] ከ ሲንግል ዲጂት አልፎ አያውቅም ነበር። ከእዚያ በኋላ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ቁጥር እየጨመረ እንደመጣ ማየት አያዳግትም።

አፍሪቃን እና ኢትዮጵያን በተመለከተ፤ የቁጥሮቹ አነስተኛ መሆን፤ ከዕለት-ወደ-ዕለት ከፍ-ዝቅ ስለማለታቸው ብዙም ማለት ባያስችልም፤ ቴስት እሚደረጉ ሰዎች ብዛት እየጨመረ መሄድን ከመጠቆም አልፎ፤ በኅብረተሰቡ ውስጥ መተላለፍ መጀመሩንም ፍንጭ ሰጪ ሊሆን እንደእሚችል ልብ ማለቱ ግን፤ ብልህዕነት ነው። ነገሮች ሁሉ በፍጥነት ሊለዋወጡ ስለእሚችሉ፤ መዘናጋት እሚባል ነገር መኖር የለበትም።

**እጆችአችንን በአግባቡ እናፅዳ | የአካል እርቀትአችንን እንጠብቅ | አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን | አዲስ የአኗኗር ዘይቤን እንላመድ**

## አህጉራት


12/31/2019 — 05/31/2020





ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሲሆን፤ ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ዳታው [አፕዴት] የተደረገው ሜይ 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት ቆጣጠር ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶች በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን፣ ደቡብ፣ ካናዳን እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።

## አፍሪቃ

12/31/2019 — 05/31/2020




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሲሆን፤ ጥሬ ዳታውን የወሰደኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ዳታው [አፕዴት] የተደረገው ሜይ 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት ቆጣጠር ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው ሪፖርት የተደረጉት ለ ዓለም ጤና ድርጅት ሲሆን፤ ጥሬ ዳታውን የወሰደኩት ግን ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ነው። ዳታው [አፕዴት] የተደረገው ሜይ 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት ቆጣጠር ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመጨረሻም፤

የኢትዮጵያ ነገር እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል። አሁን አሁን እማ፤ አዛኝ የአላት አልመስልህ እየአለኝ ነው። አለን የእሚል ከአለ፤ ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው መኖሩን በተግባር ማሳየት የአለበት። ነገ የኢትዮጵያ ላይሆን ይችላል እና! ዕመኑኝ፤ ከ ቅድሚያዎቻችን ሁሉ ቅድሚያ ልንሰጠው እሚገባው መሰረትዓዊ ጉዳይአችን፤ ለ አፍራሹ እና ለ አጥፊው የጎሣ-ፓለቲካ በሽታ ፍቱን መድሃኒት መፈለግ ነው። ለ የአለፉት 30 ዓመታት እየሄድንበት የአለው የፖለቲካ መንገድ፤ አፍራሽ እና አጥፊ እንደሆነ <u>በተግባር</u> አይተናል። ዛሬ'ም የተለወጠ ነገር የለም። የጎሣ-ፓለቲካ'ን ጥግ ከአስያዝነው፤ አይደለም — ወረርሽኝን እና የውጭ ጣልቃ ገብዕነትን አደብ ማስዝት፤ የሃገራት ሁሉ ጭራ ሆነን እንድንቀር የአደረጉንን ሌሎች ሌሎች ፈተናዎቻችን'ንም በቁርጠኛዕነት ለመጋፈጥ ጊዜውም፣ ድፍረቱም፣ ብልጥዕነቱም ሆነ አቅሙም ይኖረናል።

ሁልአችንም በጋራ እናሸንፍ ዘንድ፤ የ ስልጡን ህይወት ነፀብራቅ ፍንትው አድርጎ እሚያሳየን'ን ቀና መንገድ መከተል፤ የቅንጦት አማራጭ ሳይሆን — የግድ ነው። ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ ከ እሚያቅፍ <u>ስልጡን ምክክር</u> ተነስተን፤ <u>በ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግስት</u> የተሟላ ድልድይዕነት፤ አዲስ ህገመንግስት ቀርፀን፣ ተየህ-ማዶ ወዲያ-ማዶ በቁርጠኛዕነት ዘልቀን ተሻግረን፤ ወደ <u>ኢትዮጵያዊ ህዝባዊ መንግስት</u> ምስረታ እሚያደርሰን'ን መንገድ መከተል'ም — እንዲሁ!

ወረርሽኙን በተመለከተ፤ ኢትዮጵያ አንድ የ ጂ-አይ-ኤስ ፕሮጀክት ሰርታ፤ ኮቪድ-19'ን እና ሌሎች ሁለት ሦስት በሽታዎችን፣ ሶሽዮ-ዲሞግራፊክ ፕሮፋይልአችን'ን እንዲሁም የተመረጡ ጤና እና ጤና ነክ ካፓሲቲአችንን — ኢንተርአክቲቭ በሆኑ [ሌየርስ] እስከ ወረዳ ድረስ፤ በተቻለ መጠን በ [ሪል ታይም] ማየት ብንችል፤ ግንዛቤአችንን እና ውሳኔ የመስጠት ቁመናችንን የእሚያጎለብት ሪሶርስ ይሆናል የሚል ዕምነት አለኝ። ሁሉም የሚንስትር መስሪያቤቶች ተካፋይ ሊሆኑ ይችላሉ። ዳታውም ሆነ ቴክኖሎጂው እሚል ነገር መማት አልፈልግም። በሉ እንግዲህ፤ በርቱ!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዬ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# ብሶበታል

ሃምሌ ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ‖ ጁላይ 2020

**አዳራሽ** — ከ ሜይ አጋማሽ ጀምሮ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረጉት የ ኮቪድ-19 ህሙማን ቁጥር እየባሰበት መጥቷል። ህይወታቸውን እሚያጡት ህሙማን መጠን ግን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ በትንሹም ቢሆን መቀነስ የጀመረ ይመስላል። የ እየ 7–ቀናት አማካይ የ ህሙማን ቁጥር ብዛት'ን በተመለከተ፤ አውሮጳ ወረርሽኙ እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የ ቁልቁለቱን መንገድ እንደገፋችበት እየታየ ነው። በአንፃሩ'ም በ አሜሪካ፣ ኤዥያ እና አፍሪቃ የ እየ 7–ቀናት ሪፖርት እሚያደረጉት ህሙማን አማካይ ቁጥር እየጨመረ ከመሄድ ሊቆጠብ አለመቻሉ ነው፤ አሁን'ም ጎልቶ እየታየ የአለው። ኢትዮጵያ ሪፖርት እየ አደረገች የ አለቻቸው የ ህሙማን ቁጥር'ም [ለፈጣሪ ክብር ምስጋና ይግባው እና] "ትንሽ" ሊባል የእሚችል ነው። በ ዓለምአችን፤ ዛሬ'ም ቢሆን የ ተላላፊ በሽታዎች ሸክም፤ እጅጉን ከባድ እንደሆነ አለ። ወደፊትም ቢሆን፤ በ ቁጥር'ም ሆነ በ አደገኛዕነት እየጨመረ እየከፋ እንደእሚሄድ'ም ዕሙን ነው። የ ግል-የጋራ-የአካባቢ ንፅህና'ን መጠበቅ እና የ ክትባት እና መድሃኒቶች መፈጠር፤ የተላላፊ በሽታዎች ሸክም ጊዜ እየወሰደ'ም ቢሆን ለ መቀነስአቸው'ም ሆነ በቁጥጥር ስር ለመዋላቸው ድንቅ እሚባል አስተዋፅዖ አበርክተዋል። የ በሽታዎች'ን የመከላከል-የመቆጣጠር መመሪያዎች መሳለጥ፣ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ውልጠት — ተላላፊ በሽታዎችን ሳይዘገይ አይደንቲፋይ ለማድረግ፣ ብሎም ለመከታተል-ለመከላከል-ለመቆጣጠር ዓይነተኛ ሚና እየተጫወቱ አሉ። በአጠቃላይ፤ ተላላፊ በሽታዎች'ን በተመለከተ የመሻሻል ምልክቶች መኖራቸው እንደ የተጠበቀ ሆኖ — መድሃኒት እማይበግራቸው፣ አዳዲስ እና ጠፉ ከተባለ በኋላ እንደገና ብቅ እሚሉ ተላላፊ በሽታን እሚያስከትሉ ህዋሳትም ሆነ ፓርቲክሎች መከሰት ማብቂያ የሌለው መሆኑ፣ የ ዓለም ህዝብ ቁጥር እጅጉን መናር፣ የ ሶሻል-ኢኮኖሚክ-ፖለቲካል አለመረጋጋቶች፣ የ ሰዎች በብዛት ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር፤ እንዲሁም የአየር ሁኔታ ለውጥ እና መዛባት — ተላላፊ በሽታ'ን ከ እሚያስከትሉ ህዋሳትም ሆነ ፓርቲክሎች ጋር እየአደረግነው የአለውን "ጦርዕነት" መራር እና አስከፊ እንደሆነ እንዲቀጥል አስገድደውታል። እንደ ማናቸውም በህይወታችን ውስጥ የአሉ ፈታኝ ጉዳዮች ሁሉ፤ ተላላፊ በሽታዎች [የጤና ችግር] ብቻ አይደሉም። ይልቁን እስ፤ የሰውዐዊ መብት እና የ ሞራል ጉዮችም ጭምር እንጂ! ማናቸውም መንግስት፤ በ ጤና ችግሮች ጉዳይ ዋናእኛው ተጠያቂ አካል ነው። አይመለከተኝም ማለት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። በፍፁም!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች — ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

እየተባባሰ በመጣው ሰሞነኛው ወረርሽኝ ዙሪያ በማውጠንጠን፤ ሁልአችን'ንም — በ ጤና ባለሙያዎች እሚሰጠውን ምክረ-መመሪያ ተቀብለን በአግባቡ በመተግበር፤ ሃላፊዕነትአችንን እና ግዴታችንን ቆፍጠን ብለን እንወጣ፤ ለማለት ነው ያዛሬው አመጣጤ።

እናም፤ አብረን እንቆይ — የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።


ወረድ ብላችሁ እንደ እምታዩት፤ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረገው ጥቅል የ ህሙማን ቁጥር፤ ከ ሜይ አጋማሽ የጀመረ፤ ይህችን የ ሃምሌ ወር ብሎግ እየጨራረስሁ እስከ አለሁእባት ቀን ድረስ፤ እየባሰበት እና እየአሻቀበ በመሄድ ላይ እንደ አለ፤ ጎልቶ እየታየ ነው። ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት ቀን ከ 12/31/2019 እስከ 06/30/2020 ድረስ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ብዛት፤ በ ጥቅል ድምሩ — ወደ 10.3 ሚልየን ሲደርስ፤ ከእነዚህም ውስጥ 4.9 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ'ም ሪፖርት ተደርጓል።

በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ቁጥር ብዛት፤ በ ማርች ወር መጨረሻ [777,798] የነበረ ሲሆን፣ በ ኤፕሪል ወር መጨረሻ 2,353,002 አዲስ ህሙማን'ን በመጨመር ወደ [3,130,800]፣ በ ሜይ ወር መጨረሻ 2,897,335 አዲስ ህሙማን'ን በመጨመር ወደ [6,028,135] እና በ ጁን መጨረሻ 4,244,866 አዲስ ህሙማን'ን በመጨመር ወደ [10,273,001] ሊያሻቅብ ችሏል።

የመከላከል–የመቆጣጠር እርምጃዎች እየላሉ ስለሄዱ እና በኅብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት– የመሰላቸት ማይንድሴት እየጎለበተ በመምጣቱ ሳቢያ፤ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ብዛት ከ ሜይ አጋማሽ ጀምሮ ሲብሰበት–ሲያሻቅብ ቢታይም ቅሉ፤ ምን አልባት'ም አንድ ሁለት ሊረዱ የቻሉ መድሃኒቶች'ን መጠቀም'ን ጨምሮ፤ የተሻለ ፔሽንት ማኔጅመንት እየጎለበተ ስለመጣ፤ ህይወታቸውን የእሚያጡ ህሙማን መጠን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ በትንሹም ቢሆን እየተሻለ–እየቀነሰ እንደመጣ አስተውዬ አለሁ።

ጎበዝ፤ ለ ኮቪድ–19 ብቻ ሳይሆን፤ ለየትእኛውም ዓይነት — ማለቴ፤ [ተላላፊም ሆኑ ተላላፊ የ አልሆኑ በሽታዎች] ትክክለኛውን/አይዲኧል የህሙማን ቁጥር ብዛት ማወቅ፤ እጅጉን ቻሌንጂንግ ነው። ከፈለጋችሁ'ም፤ በፍፁም አይቻልም ማለት'ም ይቻላል። ለምን ብትሉ፤ እየ አንድ–አንዱን የሰው ልጅ በነፍስ-ወከፍ ቴስት ማድረግ እንቻል ቢባልም እንኳን፤ የ ቴስት ቫሊዲቲ [ፎልስ-ፖዝቲቭ እና ፎልስ-ኔጌቲቭ] ኢሹ ስለ አለ እና ቴስት ሪዘልቱ እንከን አልባ ሊሆን እሚችልበት ደረጃ/ጊዜ ላይ በ አለመሆናችን መሆኑን ማንሳቱ ተገቢ ነው። እንግዲህ የእሚቀረን አማራጭ፤ በሁሉም መስክ የተቻለውን ያህል ጥሩ ስራ ለመስራት እየጣርን፤ እምናገኛቸውን ቁጥሮች፤ ወረርሽኙን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በእሚያስችለን መልኩ በጥንቃቄ መጠቀም መሆኑ፤ የግድ ይሆናል።

ፐላኔት ምድር
12/31/2019 — 06/30/2020
የ እየ ዕለቱ




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁን 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

እናም፤ ሪፖርት እየተደረገ የአለው የ አዲስ ህሙማን'ን ቁጥር፤ ከወር–ወር እየጨመረ መሄድ እጅጉን ሊያሳስበን ይገባል ባይ ነኝ። እንዲያውም፤ ቴስት ከተደረጉት ሰዎች ብዛት መጨመር ጋር ሊገናኝ እንደ እሚችል መገመት ባይከብድም — የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች ስኬታማዕነትን ለመፈተሽ፤ ጠቃሚ ፍንጭ ሰጪ በመሆን ሲያገለግልም አስተውላችሁ አለ ብዬ አስብ አለሁ። ማለቴ፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች'ን በማላላት ወደ ቅድመ ወረሽኝ ህይወት ለመለስ የጀመሩ አንድ አንድ ሃገራት/ክፍለሃገራት፤ በ እየ አስተዳደራቸው የአዲስ ህሙማን ቁጥር ማሻቀቡን ማየት ከጀመሩ በኋላ፤ የመደንገጥ ስሜት ሲያድርባቸው – ብሎም፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች'ን እንደገና ለማጠንከር እና ለማጥበቅ፤ የእርምት ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ መገደዳቸው'ን ማስተዋላችሁ አይቀርም እና!


ይ–ህ እንግዲህ፤ ወደ ቅድመ ወረሽኝ ህይወት ለመመለስ በመቸኮል እና የመከላከል የመቆጣጠር እርምጃዎች'ን ተጣድፎ ማላላት'ን ተከትሎ የተከሰተ ሊሆን ቢችልም — አዲስ የአኗኗር ዘይቤን በመማር በመለመድ እና በመተግበር በኩል፤ ተገቢውን እና ተመጣጣኝ ዝግጅት በ አለመደረጉ'ም ጭምር ሊሆን እንደ እሚችል ልብ ማለቱ ብልህዕነት ነው ብዬ አምን አለሁ። ኀበዝ፤ ይ–ህ ወረርሽኝ በጊዜ ብዛት የ ኤፒደሚክዕነቱን ቁመና ሊያጣ እንደእሚችል መገመቱ ከ ዕውነታው የራቀ ባይሆንም፤ የተወሰኑ ስፖራዲክ ኢቬንትስ እዚህም እዚያም መታየት እንደእሚችሉ፤ የተማረ-ግምት መቸር'ን ጨምሮ፤ ኢንደሚክ በሆነ ቁመና ለ የአልተወሰነ ጊዜ አብሮን ለመቆየት እንደ እሚችልም መተንበዩ ብልህዕነት ነው።

ዝቅ ብላችሁ እንደእምታዩት ደሞ፤ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን፤ የ እየ 7–ቀናት አማካይ ቁጥር ብዛት፤ አውሮጳ ከ ኤፐሪል 13 ጀምሮ፤ ወረርሽኙ እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የ ቁልቁለቱን መንገድ አጥብቃ እንደ ተያያዘችው ይጠቁማል። በአንፃሩ'ም፤ በ አሜሪካ፣ ኤዥያ እና አፍሪቃ የ እየ 7–ቀናት ሪፖርት እሚያደረጉት ህሙማን አማካይ ቁጥር፤ እየጨመረ ከመሄድ ሊቆጠብ አለመቻሉ ነው፤ አሁን'ም ጎልቶ የታየው።

አፍሪቃ በቀመሩ ላይ እስከ ኤፐሪል አጋማሽ ድረስ ድምጿን አጥፍታ ከቆየች በኋላ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፤ ይኼው ኤኔስ ለምን ይቅርብኝ በማለት — በ ጁን መጨረሻ ላይ፤ የ እየ 7–ቀናት የአማካይ ቁጥር፤ ከ አውሮጳ ጋር የሚስተካከል ደረጃ ላይ እንደደረሰ ታይቷል።


**እጆችአችንን በአግባቡ እናፅዳ | የአካል እርቀትአችንን እንጠብቅ | አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን | አዲስ የአኗኗር ዘይቤን እንላመድ**

አህጉራት
12/31/2019 — 06/30/2020
የ እየ 7–ቀናት አማካይ




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ 7–ቀናት አማካይ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከአሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁን 30/2020 ከ 6:00 እስከ 10:00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶች በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን፣ ደቡብ፣ ካናዳን እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።


አፍሪቃ
12/31/2019 — 06/30/2020
የ እየ ዕለቱ




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከአሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁን 30/2020 ከ 6:00 እስከ 10:00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ ሪፖርት እምታደርጋቸው ህሙማን ቁጥር ፤ ለ ፈጣሪ ክብር ምስጋና ይግባው እና — በቁጥር ትንሽ ሊባል እሚችል ነው። እናም፤ ከዕለት-ወደ-ዕለት ከፍ-ዝቅ ስለማለታቸው'ም ብዙም ማለት አይቻልም። ሆኖም ግን፤ የቁጥሮቹ አነስተኛ መሆን፤ በአጠቃላይ ቴስት እሚደረጉት ዜጎች ቁጥር አነስተኛ ከመሆን ጋር እሚያያዝ መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ቁጥር በመጠኑም ቢሆን ከፍ እየአለ መምጣቱ — ቴስት እሚደረጉ ሰዎች ብዛት ሪሌቲቭሊ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድን ከመጠቆም አልፎ፤ በኅብረተሰቡ ውስጥ መሰራጨት መጀመሩንም ፍንጭ ሰጪ ሊሆን እንደእሚችል ልብ ማለቱ፤ ብልህዕነት ነው። ነገሮች ሁሉ በፍጥነት ሊለዋወጡ ስለእሚችሉ፤ መዘናጋት እሚባል ነገር መኖር የለበትም።

ኢትዮጵያ
12/31/2019 — 06/30/2020
የ እየ ዕለቱ




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁን 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመጨረሻም፤

ለ የ ሰው ልጅ — ተላላፊ በሽታዎች፤ ዛሬ'ም ቢሆን ግዙፍ ሸክም መሆናቸው ዕሙን ነው። በ ቁጥር'ም ሆነ በ አደገኛዕነት'ም እየጨመሩ እሚሄዱ መሆኑ'ም እንዲሁ! የ ግል-የጋራ-የአካባቢ ንፅህና'ን መጠበቅ፣ እንዲሁም የ ክትባት እና መድሃኒቶች መፈጠር እስከዛሬ የአስተዋልንአቸውን የተላላፊ በሽታዎች ሸክም ጊዜ እየወሰደ'ም ቢሆን ለ መቀነስአቸው'ም ሆነ በቁጥጥር ስር ለመዋላቸው ድንቅ እሚባል አስተዋፅዖ አበርክተዋል። የበሽታዎች የመከላከል እና የመቆጣጠር መመሪያዎች መሳለጥ እና የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ውልጠት — ተላላፊ በሽታዎችን ሳይዘገይ አይደንቲፋይ ለማድረግ፤ ብሎም ለመከታተል-ለመከላከል-ለመቆጣጠር ወሳኝ ሚና አላቸው።

ዕውነት ነው። እስከዛሬ፤ ተላላፊ በሽታዎች'ን በተመለከተ በ ዓለም ዙሪያ የታዩት መሻሻሎች እሚያስደንቁ ናቸው። በተለይም ከፍተኛ ገቢ በአላቸው ሃገራት። ዝቅተኛ ገቢ በአላቸው ሃገራት ግን፤ የመሻሻል ምልክቶች አልታዩም ባይባልም፤ ገና ብዙ-ብዙ መሰራትን እሚጠይቅ ኅስቋላ ደረጃ ላይ ነው የ አሉት። በአጠቃላይ፤ የመሻሻል ምልክቶች መኖራቸው እንደ የተጠበቀ ሆኖ፤ መድሃኒት በቀላሉ እማይበግራቸው፣ አዳዲስ እና ጠፉ ከተባለ በኋላ ብቅ እሚሉ ተላላፊ በሽታን እሚያስከትሉ ህዋሳትም ሆኑ ፓርቲክሎች መከሰት ማብቂያ የሌለው መሆኑ፣ የ ዓለም ህዝብ ቁጥር እጅጉን መናር፤ ሶሻል-ኢኮኖሚክ-ፖለቲካል አለመረጋጋቶች፣ ሰዎች በብዛት ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር፤ እንዲሁም የአየር ሁኔታ ለውጥ እና መዛባት — ተላላፊ በሽታ'ን ከ እሚያስከትሉ ህዋሳትም ሆነ ፓርቲክሎች ጋር እየአደርግነው የአለነው'ን "ጦርዕነት" መራር እና አስከፊ እንደሆነ እንዲቀጥል አስገድደውታል።

እንደማንአቸውም በህይወታችን ውስጥ የአሉ ፈታኝ ጉዳዮች ሁሉ፤ ተላላፊ በሽታዎች [የጤና ችግር] ብቻ አይደሉም። ይልቁንእስ፤ የሰውዐዊ መብት እና የ ሞራል ጓዮችም ጭምር እንጂ! ማናቸውም መንግስት፤ በ ጤና ችግሮች ጉዳይ ዋናእኛው ተጠያቂ አካል ነው። አይመለከተኝም ማለት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። በፍፁም!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዬ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# መስኮተ ሰቆቃ

ነሃሴ ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ‖ ኦገስት 2020

***አዳራሽ*** *— የግንጠላ አባዜ የተጠናወታቸው በሽተኛ ፖለቲከኞች በፈጠሯቸው ሦስት [አክራሪ እና ሽብርተኛ] የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች በፃፉት ፀረ–ኢትዮጵያ "ህገመንግሥት" ተብዬ ድልዳልዕነት የተዘረጋው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፈዴራሊዝም'ን በመጠቀም፤ ለ 30 ዓመታት ያህል የተዘራው መርዝ እየአስከተለ በ አለው ተደጋጋሚ [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፤] ክቡር ህይወታቸው በአጭር ለተቀጨ፤ የአካል እና የስነልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው፤ ሃብት ንብረታቸው ለወደሙባችው ንፁሃን ወገኖቼ ሁሉ — የኢትዮጵያ ዓምላክ በ እየ አላችሁበት ይታደጋችሁ ዘንድ የዘወትር ፀሎቴ ነው! አንድ ነገር ግልፅ ማደረግ እፈልጋለሁ። እንዲህ ዓይነቱ ሰቆቃ ዳግም እንዳይከሰት ለማድረ ከፈለግን፤ መፍትሄው፤ መደራጀት መደራጀት እና መደራጀት ብቻ መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል። አደጋ በተከሰተ ቁጥር ማለቃቀሱ አይጠቅመንም። በ እሚረባ በእማይረባ ነገር ሰበብ እየፈጠርን አንከፋፈል። የሃሳብ ልዩዕነቶች ሲፈጠሩ፤ አብሮ የመኖር ሃሳብ እንደ አለው ስልጡን ኅብረተሰብ ጊዜ ወስደን እንነጋገር እንወያይ። ወደ ማምረር አንጣደፍ! ፖለቲካዉን ወደ የግለሰብ ፍቅር አንቀይረው። ፖለቲካው ግለሰብን የመውደድ የመጥላት ጉዳይ ሳይሆን፤ የ ሃገር እና የህዝብ ጉዳይ ነው። እዚያ ላይ እናተኩር። ልዩዕነትን አስወግደን ጠንካራ የተደራጀ ሃይል እንፍጠር። የኢትዮጵያ ጠላቶች እየበጠበጡን የአሉት እኮ ከ እኛ በላይ መደራጀት በመቻላቸው ነው። አይደለም እንዴ?! ስለ ፖለቲካችን የእምለውን እዚህ ላይ ልቋጭ እና ወደ ኮቪድ-19 ስሻገር፤ ወረድ ብልችሁ እንደ እምታዩት፤ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረገው የ እየ ዕለቱ አዲስ ህሙማን ቁጥር፤ ከ ሜይ አጋማሽ የጀመረ፤ ይህችን የ ነሃሴ ወር ብሎግ እየጨራረስሁ እስከ አለሁእባት ቀን ድረስ፤ እየባሰበት እና እየአሻቀበ በመሄድ ላይ እንደ አለ፤ ጎልቶ እየታየ ነው። መድሃኒትም ሆነ ክትባትን የማፈላለግ የማግኘት ጥረቶች፤ ተስፋ አስቆራጭ ባይሆኑም ሊደርሱልን በነበረበት ጊዜ አለመድረሳቸው፤ ብዙ ጥፋትን እንድናስተናገድ አስገድደውን አሉ። ለማንኛውም፤ ጥሩ መድሃኒትም ሆነ ክትባት በ ተገኘ ጊዜ፤ ለዜጎቻችን ሁሉ በፍጥነት ለማዳረስ እንዲቻል — ቅድመ ዝግጅቱ ከወዲሁ መጠናቀቅ አለበት።*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች — ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

ዛሬ እማተኩረው፤ ላይ-ላዩን'ም ቢሆን፤ በ ሁለት መሠረትዓዊ ጉዳዮች ዙሪያ ነው።

<u>በቅድሚያ</u> — የግንጠላ አባዜ የተጠናወታቸው በሽተኛ ፖለቲከኞች በፈጠሯቸው ሦስት [አክራሪ እና ሽብርተኛ] የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች በፃፉት ፀረ–ኢትዮጵያ "ህገመንግሥት" ተብዬ ድልዳልዕነት የተዘረጋው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፈዴራሊዝም'ን በመጠቀም፤ ለ 30 ዓመታት ያህል የተዘራው መርዝ፤ በተደጋጋሚ እየአስከተለ በ አለው [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፤] ዙሪያ ትንሽ እምለውን ለማለት፤

<u>በመቀጠል'ም</u> — በ አደብ አልገዛም ባዩ፤ የጊዜአችን ዓለም-አቀፍ የ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዙሪያ በማውጠንጠን፤ ሁልአችን'ንም፤ በ ጤና ባለሙያዎች እሚሰጠን'ን ምክረ-መመሪያ ተቀብለን በአግባቡ በመተግበር፤ ሃላፊዕነትአችን'ን እና ግዴታችን'ን፤ እንደ አንድ ስልጡን የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ አባል፤ ቆፍጠን ብለን እንወጣ ለማለት ነው።

እናም፤ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።

<u>ቀዳሚው ጉዳይ</u> — የ ዛሬ ወር ገደማ፤ የግንጠላ አባዜ የተጠናወታቸው በሽተኛ ፖለቲከኞች በፈጠሯቸው ሦስት [አክራሪ እና ሽብርተኛ] የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች በፃፉት ፀረ–ኢትዮጵያ "ህገመንግሥት" ተብዬ ድልዳልዕነት የተዘረጋው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፈዴራሊዝም'ን

በመጠቀም፤ ለ 30 ዓመታት ያህል የተዘራው መርዝ በተደጋጋሚ እየአስከተለ በ አለው [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፤] ክቡር ህይወታቸው በአጭር ለተቀጨ፤ የአካል እና የስነልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው፤ ሃብት ንብረታቸው ለወደሙባችው ንፁሃን ወገኖቼ ሁሉ — የኢትዮጵያ ዓምላክ በ እየ አላችሁበት ይታደጋችሁ ዘንድ የዘወትር ፀሎቴ ነው!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ምነዋ፤ እንድ ወር ያህል እንዴት አስቻለህ እና ዝም አልክ እንደእምትሉኝ እገምታለሁ።

ዕመኑኝ — ሳላዝን፣ ሳያንገበግበኝ፣ ውስጤ ሳይነድ እና ኢሞሽናል ሳልሆን ቀርቼ እንዳይመስላችሁ።

አዎ፤ አስቤ'ም ጀማምሬ'ም ነበር። ግና – መልሼ በአነበብኩት ቁጥር፤ እጅግ መረር የአለ ስለመሰለኝ እና ምን አልባትም እኔ ወዳጆቼ የእምላቸውንም ጭምር ያስከፋብኝ ይሆናል ብዬ ስለፈራሁ ትቸዋለሁ።

ምን ላድርግ ብላችሁ ነው፤

[የራቀውን ልቤን እንዳቀርብ ሲቃጣኝ — ሰው ሆኖ እማውቀው አውሬ ወልዶ ቆየኝ።]

ደግሞስ፤ በእዚያች ደግ ሃገር እና በዚያ ንፁህ ህዝብ ላይ — አደጋ፣ ስቃይ፣ ዕንባ፣ መከራ እና ሰቆቃ እንዳይደርስ፤ ቀድሞ መከላከል ነበር እንጂ፤ አደጋው ከደረሰ በኋላ እ-የ-ዬ ማለቱ ምን ይፈይዳል ብላችሁ ነው!

ለነገሩ — እኔ የ አላልኩት የ አለ አይመስለኝም። ምን አልባት ጊዜ ወስጄ ስርዐት በአለው መልኩ አላቀረብኩት ይሆናል እንጂ። በተለይም፤ ይህ አሁን የስልጣን በርጩማው ላይ የተኮፈወሰው መንግሥት፤ ቃል-ኪዳን ከመፈፀሙ አንድ ቀን በፊት ጀምሬ፣ [ሳላሰልስ] ዛሬ እየአየናቸው የአሉት፤ [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ]

ሊከሰቱ እንደ እሚችሉ እና በቅድሚያ ሊደረጉ ስለ እሚገባቸው እና ሊወሰዱ ስለ እሚገባቸው እርምጃዎች አበክሬ ከመወትወት የተቆጠብኩበት ጊዜ አልነበረም።

ሰሚ ጠፋ እንጂ!

እየደረሰ ለአለው ሰቆቃ እና የ ሃገር መጥፋት አደጋ፤ ቀዳሚ ተጠያቂው አሁን የስልጣን በርጩማው ላይ የተኮፈሰው መንግሥት እና አሁን የስልጣን በርጩማው ላይ የተኮፈሰው መንግሥት ብቻ ነው።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ በ ስልጣን ላይ የአለው መንግሥት፤ በሃሰት ትርክት የተሰራ የ እራሱ [በብል] ውስጥ የታገተ ዲስፈንክሽናል አካል ሆኖ ነው እሚታየኝ — የዕውቀት እና የሞራል አድማሱን ማደስም ሆነ ማስፋት አሻፈረኝ የአለ፣ ያለማቋረጥ እየተለወጠ ለአለው ዩኒቨርስ እና አብሮ መለወጥ ስለአለበት የሰውዕነት ሚኒንግፉል ኤግዚስተንስ፤ ፕሮፐርሊ ሪስፖንሲቭ የአልሆነ፤ እጣ ፈንታው ውድቀት ብቻ ሆኖ የቀረ፤ በአካባቢው የአለውን ሁሉ እና በስተመጨረሻም እራሱንም ጭምር የ እሚያስከፋ፣ የእሚያበሳጭ፣ የእሚያስቆጣ እና ምን አልባትም የእሚያጠፋ አካል።

ለእዚያም ነው ፤

ህዝቡ ሲፈናቀል፤ ሲራብ ሲጠማ፣ ህግ እና ፍትህ ሲጓደል፣ በ ዕብድ መንጋ አረመኔዓዊ አዉሬዓዊ በሆነ መልኩ፤ ሲታረድ ሲሰቀል፣ መሬት ለመሬት ሲጎተት፤ የተረፈው ለዘመናት ድባቅ የእሚከተው ሰቆቃ ሲደርስበት፤ እናም ኢትዮጵያ ልትጠፋ ስትቃረብ፤ በ ስልጣን ላይ የአለው አካል ምንም ደንታ የሌለው ለመሆኑ <u>በተደጋጋሚ</u> የ አየነው። በተደጋጋሚ!

ምክንያት — ይህ ሁሉ ዓለም የ አወቀው ፀሃይ የሞቀው ሰቆቃ፤ እየተከናወነ የአለው፤ ሰሞነኛው መንግሥት ተብዬ እራሱን ከአገተበት [በብል] ውጪ ስለሆነ።

አዎ፤

ሰሞነኛው መንግሥት ተብዬ ደንታ የ እሚሰጠው፤ የ እሚጎረብጠው ከ እራሱ [በብል] ውጪ እየተከሰተ የአለው መከራ እና ሰቆቃ እየጋለ ሄዶ፤ ከታገተበት [በብል] ውስጥ የአለዉን አየር ማጋል ሲጀምር እና በርጩማውን ማንገጫገጭ የጀመረ ቀን ብቻ ነው።

ምስክር — የሰሞኑ መንፈራገጥ።

ጉድ እኮ ነው!

ይ-ኼ ዲስፈንክሽናል “መንግሥት” ተብዬ፤ የሃሳብ ልዩዕነቶችን በማስተናገድ በኩል ቸር እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲደሰኩር እንሰማለን። በ የአለፉት ሁለት ዓመታት ከምናምን፤ የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር ግን፤ ለ ሰሞነኛው መንግሥት፤ “የሃሳብ ልዩዕነቶችን የማስተናገድ” ቸርዕነቱ፤ ያ-ው [ሃሳብ] የእርሱ [በብል] ውስጥ የአለውን አየር እስከ አላጋለ እና በርጩማውን እስከ አላንገጫገጨ ድረስ ብቻ መሆኑን ነው።

ጎበዝ፤

እኔ ኢትዮጵያ ስል — ዛሬ ህዝቧ ወደ 120 ሚልየን አካባቢ የደረሰ፣ ወደ ሰማንያ አካባቢ የ እሚጠጉ ቋንቋዎች የ እሚነገሩባት፣ በ ዉብ ባህል ወግ ልማዶች የበለፀገ፤ በጋብቻ በመዋለድ እና በተለያዩ ገጠመኞች የታዛመደ፤ ደስታን ሃዘንን፣ ፈተናን በጋራ ያሳለፈ፤ አብሮዕነት ዉበት ጥንካሬው የሆነ፤ በ ሺ-ህ ዓመታት የእሚቆጠር ዕንቁ ታሪክ የአለው ህብር ህዝብ የእሚኖርባት፤ የሰው ዘር መጀመሪያ ከርሰ-ምድር የሆነችዋን፤ በጊዜ ስትሰፋ በጊዜ ስትጠብ የኖረችዋን፤ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መለያ ኩራትዋ የሆነችዋን፤ በአስራ አራት ክፍለሃገራት የተዋቀረች፣ አሁንም የአለችዋን እና ወደፊትም የእምትኖረዋን ውብ ሃገርአችንን ማለቴ ነው።

እኔ ኢትዮጵያዊ ስል — በዋናዕነት፤ ኢትዮጵያ በእምትባለዋ ሃገር ውስጥ የተፈጠረ ማናቸውም የሰው ልጅ’ን ጠቅሼ ለማመልከት ነው።

እኔ ኢትዮጵያዊዕነት ስል — በዋናዕነት፤ ኢትዮጵያ በ እምትባለዋ ሃገር ውስጥ፤ እያ አንድ አንዱ ዜጋ፤ በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበት – በፈለገበት የኢትዮጵያ ምድር ውስጥ በነፃዕነት የመኖር፤ የመስራት፣ ሃብት ንብረት የማፍራት፣ የመምረጥ እና የመመረጥ ሙሉ መብት የአለው – ቋንቋው ወግ ባህል ልማዶቹ፣ ሰውዓዊ መብቶቹ ተከብረው፤ በ ሁለዕንተንዓዊ ኢትዮጵያዊ እሴቶች የታነፀ ምሉዕ መለኮትዓዊ ኢትዮጵያዊ ህይወት ማለቴ ነው።

እንዲያው በፈጠራችሁ፤

ለመሆኑ አሁን በስልጣን ላይ የአለው መንግሥት፤ በ እርሱ [በብል] ውስጥ ተቀምጦ፤ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊ፣ ኢትዮጵያዊዕነት ሲል፣ ምን እየአለ ይሆን?!

መቼም፤ ልዩዕነት የለንም እንዳይል ብቻ!

ያ ቢሆን ኖሮ እማ፤ ልዩዕነት ከሌለን እማ፤ በ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊ እና ኢትዮጵያዊዕነት ዙሪያ አንድ ከሆንን እማ፤ ኩቶ ለምን ይሆን፤ የ ኢትዮጵያ’ን፤ የ ኢትዮጵያዊ’ን እና የ ኢትዮጵያዊዕነት’ን ህብር እና አንድዕነትን የእሚሰብኩ፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ አላማዋን በኩራት የእሚያውለበልቡ፣ በድሎቻችን የእሚኮሩ፣ በችግሮቻችን የእሚያዝኑ ፖለቲከኞቻችንን ሲያይ/ሲሰማ ዛሩ እሚነሳበት?!

እኮ ለምንድን ነው — ኢትዮጵያን ከሚል ኢትዮጵያዊ ጋር እንዲህ የ እሚያባላው?! ኩቶ ለምንድን ነው ኢትዮጵያን በቀናዕነት የእሚያነሳ ሰው ሲገጥመው ደሙ የ እሚፈላው?!

ኩቶ ለምን ይሆን፤

አሁን በስልጣን ላይ የአለው መንግሥት፤ ንፁህ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ የአላቸውን ፖለቲከኞችንም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች’ን፤ ወደ ሃገራቸው እንዳይገቡ ማገዱ?! ሃገር ቤት የአሉትን ንፁህ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ የአላቸውን ፖለቲከኞችንም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች’ን ቢሆንስ፤ መውጫ መግቢያ ማሳጣት እና መሪዎቻቸውን ወደ እስር ቤት መወርወሩስ — ምን ይባላል?!

አሁን በስልጣን ላይ የአለው መንግሥት፤ የሃሳብ ልዩዕነቶችን በማስተናገድ በኩል ቸር ነን ሲል፤ እየዋሸ ነው እንዴ?

ነው ወይስ፤ ገና ዲቤቱ ሳይጀመር መዘረራችሁን አመናችሁ?! በሃሳብ የአሚበልጧችሁን እየመረጣችሁ ማሰራችሁ፤ እስከአነ አካቴው የረባ ሃሳብ የሌላችሁ ድኩማን ፖለቲከኞች መሆናችሁን ለአገር ምድሩ እየአበሰራችሁ መሆኑ አይታያችሁም?! እኛንስ ተውን፤ አንዴ ለይቶልናል – ወዳጅ ዘመዶቻችሁ ይታዘቡናል ብላችሁ እንኳን አታስቡም?!

የ እምትፈሩት ፈጣሪ አላችሁ ብዬ ስለ እማላምን፣ ፈጣሪን አትፈሩም ወይ ልላችሁ አሰብኩ እና — ተውኩት!

አንድ ሌላ ነጥብ ልጨምር እና በእዚህ ጉዳይ ላይ የአለኝን ሃሳብ ልቋጭ።

አሁን በስልጣን ላይ የአለው መንግሥት ሌላው ችግር፤ ከ[በብል]'ም፤ ሰነፍ የሰራው [በብል] ውስጥ እየሚኖር የ መሆኑ ዕውነታ ነው። እናንተን እየመሰሉ፣ የእናንተ [በብል] ውስጥ አብረዋችሁ እየኖሩ፣ እየሸወዷችሁ ከ በብሉ ውስጥ ተደብቀው እየወጡ፤ እኛን ብቻ ሳይሆን እናንተን'ም ጭምር ለማጥፋት ሌት ተቀን የእሚዶልቱ መሰሪዎች የመኖራቸው ጉዳይ። ይህንንም በተደጋጋሚ ነገረናችኋል፤ አሻፈረኝ አላችሁ እንጂ።

አሁንም ነካካችኋቸው እንጂ፣ ገና የምሳቸውን አልሰጣችኋቸውም። በእናንተ አያያዝ አይደለም፤ እነሱ ልክ የእሚገቡት። አሁን እየወሰዳችሁት በአለው ተልካሻ እርምጃ ረከታችሁ ወደ መለሳለስ ወደ መዘናጋት ከሄዳችሁ፣ የሚቀጥለው የአክራሪዎቹ እርምጃ — መጥፊያችሁ እንደእሚሆን አትጠራጠሩ።

ነግሬ አለሁ!

እራሳችሁንም ኢትዮጵያንም ማትረፍ ከፈለጋችሁ፤ የ እምላችሁን ስሙ!

ችግሩም መፍትሄውም ግልፅ ነው።


<u>ችግሩ፤</u> — በጥቅሉ [የጎሣ ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች፤ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ህገመንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌዴራሊዝም እና አነእኝህን ተከትሎ በተደጋጋሚ እየተከሰተ የ አለው ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና ኢትዮጵያን የ ማጥፋት የተቀናጀ ዘመቻ ነው።]

<u>መፍትሄው፤</u> ገዥው-ፓርቲ [በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ] የ ሕዝብን ስልጣን ለ ሕዝብ ያስረክብ። ለ 30 ዓመታት ያህል ቁጥር ስፍር የሌለው ወንጀሎች ፈፅማችሁ አለ — እስቲ ይብቃን በሉ! የ ሕዝብን፣ የ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጥምረት በማቀናጀት፤ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ይመስረት። በቴክኖክራቶች የእሚሞላ ፈርጀ-ብዙ [ታስክ ፎርስ] ተዋቅሮ፤ ለ የሽግግር መንግስቱ እሚያስፈልገውን ሙያዊ ድጋፍ ይስጥ።

የሽግግር መንግስቱ፤ በዋናዕነት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ያስከብር፣ የህዝቧን ሰላም እና መረጋጋት ያስፍን፣ የ ሁሉንም ተቋምአት ተግባር በሃላፊዕነት ይምራ፣ እሚቀጥለውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበት'ን ምርጫ – ፍትህዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ እሚያስፈልጉትን ተቋምዓዊ ለውጦች ተግባርዓዊ ያድርግ። ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት ይቅረፅ።

እንደ አዲስ በእሚቀረፀው ህገመንግሥት ውስጥ — አለመረሳቱን ብቻ ሳይሆን፤ ጎልቶ መታየቱንም ጭምር እርግጠኛ ልንሆን ከእሚገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳይዖች መሃከል፤ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ይደረግ። በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ይካተት። ሰው በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ይመስረት። አላስ — ሌላ አማራጭ የለም!

<u>ቀጣዩ ጉዳይ</u> — እንደ እምታዩት፤ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረገው የ ኮቪድ-19 ህሙማን ቁጥር፤ ከ ሜይ አጋማሽ የጀመረ፤ ይህችን የ ነሃሴ ወር ብሎግ እየጨራረስሁ እስከ አለሁእባት ቀን ድረስ፤ እየባሰበት እና እየአሻቀበ በመሄድ ላይ እንደ አለ፤ ጎልቶ እየታየ ነው።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ [https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases](https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases) ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁላይ 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት ቀን ከ 12/31/2019 እስከ 07/31/2020 ድረስ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ብዛት፤ በ ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ድምሩ — ወደ 17.3 ሚልየን ሲደርስ፤ ከእነዚህም ውስጥ 3.9 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሲያልፍ እንደቻለ'ም ሪፖርት ተደርጓል።

የ እምታዩት ሰንጠረዥ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት አዲስ ህሙማን ቁጥር ብዛት እስከ ማርች 2020 ድረስ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ በ እየ ወሩ ሪፖርት የተደረጉትን አዲስ ህሙማን፣ የ አዲስ ህሙማን ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ድምር፣ የ ሙታን ቁጥርን እና ሙታን በፐርሰንት ሲሰሉ የተገኙትን ቁጥሮች ነው የያዘው።

| በ 2020 | አዲስ ህሙማን | አዲስ ህሙማን ጥቅል ድምር | የሙታን ቁጥር | ሙታን በ ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| ማርች | 777,798 | 777,798 | 37,272 | 4.8 |
| ኤፐሪል | 2,353,002 | 3,130,800 | 227,051 | 7.3 |
| ሜይ | 2,897,335 | 6,028,135 | 368,944 | 6.1 |
| ጁን | 4,244,866 | 10,273,001 | 505,295 | 4.9 |
| ጁላይ | 7,023,302 | 17,296,303 | 673,290 | 3.9 |

ከ ሜይ አጋማሽ ጀምሮ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ብዛት ሲብስበት–ሲያሻቅብ እየታዩ የአለው፤ ቴስት የእሚደረጉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄድ'ን ጨምሮ የመከላከል–የመቆጣጠር እርምጃዎች እየላሉ ስለሄዱ እና በኅብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት– የመሰላቸት ማይንድሴት እየጎለበተ በመምጣቱ ሳቢያ እንደሆነ መገመት አይከብድም።


ወደ ቅድመ ወረሽኝ ህይወት ለመመለስ ማሰቡ የእማይቀር ነገር ቢሆንም ቅሉ፤ የ አዲስ ህሙማን ቁጥር ከወር–ወር እየጨመረ የ መሄዱ ዕውነታ፤ ዛሬም ቢሆን እጅጉን ሊያሳስበን ይገባል ባይ ነኝ።

ወደ ቅድመ ወረሽኝ ህይወት መመለስ የጀመሩ አንድ አንድ ሃገራት/ክፍለሃገራት፤ በ እየ አስተዳደራቸው የአዲስ ህሙማን ቁጥር የበለጠ ለማሻቀቡ ምክንያት መሆኑን ከአዩ በኋላ፤ የመደናገጥ ስሜት ሲያድርባቸው – ብሎም፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን'ን እንደገና ለማጠንከር እና ለማጥበቅ፤ የእርምት ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ ሲገደዱ ማየታችን፤ ለሌሎቻችን ትምህርት ሊሆን ይገባል።

እጆችአችንን በአግባቡ ማፅዳት፣ የአካል እርቀትአችንን መጠበቅ፣ አፍ እና አፍንጫችንን መሸፈን እና አልፎ ተርፎም፤ በእየመስኩ አዳዲስ ተጓዳኝ የአኗኗር ዘይቤዎችን መላመድ ጊዜው የእሚጠይቀው ግዴታ መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል።

እጆችአችንን በአግባቡ እናፅዳ | የአካል እርቀትአችንን እንጠብቅ | አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን | አዲስ የአኗኗር ዘይቤን እንላመድ


ኅበዝ፤ ህይወታቸውን የእሚያጡ ህሙማን መጠን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ በትንሹም ቢሆን እየተሻለ–እየቀነሰ እንደመጣ ስለ መታየቱ ብዙ ምክንያቶች መጠቃቀስ ይቻላል። ለምሳሌም ያህል — ሀ) ቴስት የእሚደረጉት ሰዎች ቁጥር እጅጉን መጨመር ለ) አንድ ሁለት ሊረዱ የቻሉ መድሃኒቶች'ን መጠቀም'ን ጨምሮ፤ የተሻለ ፔሽንት ማኔጅመንት እየጎለበተ ስለመጣ እና ሐ) የ ኮሮናቫይረስ-2 በፍጥነት ሚውቴት የማድረግ ባህሪው፤ በአንድ በኩል ክትባት ለመስራት የእሚደረገውን ጥረት እንደተፈታተነው ዕሙን ቢሆንም፣ ምን አልባትም የከፋ ጉዳት የማያደርሱ ሙቴችንስ ተፈጥረው ሊሆን በመቻሉም ጭመር ሊሆን እንደ የእሚችል መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ 7–ቀናት አማካይ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁላይ 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶች በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን (ዩኤስኤ እና ካናዳ)፣ ደቡብ እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።

ቀደም ብላችሁ እንደአያችሁት ደሞ፤ እንደ አዲስ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን፤ የ እየ 7–ቀናት አማካይ ቁጥር ብዛትን በተመለከተ፤ አውሮጳ ከ ኤፕሪል አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ፤ ወረርሽኙ እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የ ቁልቁለቱን መንገድ አጥብቃ ተያይዛው፤ ይኼው እና ዛሬ በቁጥሩ ትንሽ ከ እሚባልለት የ አፍሪቃ ረፖርት ከእምታደርጋቸው የአዲስ ህሙማን ቁጥር ጋር መሣ ለመሣ መሆኗ በግልፅ ታይቷል።

በአንፃሩ'ም፤ በተለይ በተለይ በ አሜሪካ እና ኤዥያ፤ በአፍሪቃ'ም ቢሆን የ እየ 7–ቀናት ወራጅ አማካይ ቁጥር፤ እየጨመረ ከመሄድ ሊቆጠብ አለመቻሉ ነው፤ አሁን'ም ጎልቶ የታየው። አፍሪቃ በቀመሩ ላይ እስከ ኤፕሪል አጋማሽ ድረስ ድምጿን አጥፍታ ከቆየች በኋላ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፤ ይኼው እኔስ ለምን ይቅርብኝ በማለት — በ ጁላይ መጨረሻ ላይ፤ የ እየ 7–ቀናት የአማካይ ቁጥር፤ ከ አውሮጳ ጋር ትከሻ መለካካት እንደጀመሩ በግልፅ ታይቷል።





<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት’ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁላይ 31/2020 ከ 6:00 እስከ 10:00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ ሪፖርት እምታደርጋቸው ህሙማን ቁጥር ፤ ለ ፈጣሪ ክብር ምስጋና ይግባው እና — ዛሬም ቢሆን፤በቁጥር ”ትንሽ” ሊባል እሚችል ነው። እናም፤ ከዕለት-ወደ-ዕለት ከፍ-ዝቅ ስለማለታቸው’ም ብዙም ማለት አይቻልም። የቁጥሮቹ አነስተኛ መሆን፤ በአጠቃላይ ቴስት እሚደረጉት ዜጎች ቁጥር አነስተኛ ከመሆን ጋር እሚያያዝ መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ቁጥር በመጠኑም ቢሆን እየአሻቀበ መምጣቱ  ግን ሊያሳስበን ይገባል። ነገሮች ሁሉ በፍጥነት ሊለዋወጡ ስለእሚችሉ፤ መዘናጋት እሚባል ነገር መኖር የለበትም። በፍፁም!

ኢትዮጵያን በተመለከት፤ ሪፖርት የተደረጉትን አዲስ ህሙማን ቁጥር የእሚያሳየውን ቀመር ስታዩ፤ አንድ ለየት የአለ ነገር እንደአስተዋላችሁ አምን አለሁ። አዎ፤ በ ጁላይ መጀመሪያ ላይ ለስድስት ቀናት ገደማ ሪፖርት የተደርጉ ኮቪድ-19 ህሙማን አለመኖራቸውን የ እሚጠቁም ክፍተት። ለምን ይሆን?

የእናንተን አላውቅም እንጂ፤ እኔ ያንን ክፍተት በአየሁ ቁጥር፤ በኅሊናየ ውስጥ የእሚቀረፀው ልብ ሰባሪ ኢሜጅ ነው — የግንጠላ አባዜ የተጠናወታቸው በሽተኛ ፖለቲከኞች በፈጠሯቸው ሦስት [አክራሪ እና ሽብርተኛ] የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች በፃፉት ፀረ–ኢትዮጵያ “ህገመንግሥት” ተብዬ ድልዳልዕነት የተዘረጋው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌዴራሊዝም’ን በመጠቀም፤ ለ 30 ዓመታት ያህል የተዘራው መርዝ፤ በተደጋጋሚ እየአስከተለ የ አለው፤ አላባራ የአለው [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ!] <u>መስኮተ ሰቆቃ!</u>




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት’ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ጁላይ 31/2020 ከ 6:00 እስከ 10:00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመጨረሻም፤

የኢትዮጵያ ነገር አሁንም እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል። ከ ቅድሚያዎቻችን ሁሉ ቅድሚያ ልንሰጠው እሚገባው መሰረትዓዊ ጉዳይአችን፤ ለ አፍራሹ እና ለ አጥፊው የጎሣ-ፖለቲካ በሽታ ፍቱን መድሃኒት መፈለግ ነው። ሁልአችንም በጋራ እናሸንፍ ዘንድ፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ ከ እሚያቅፍ ስልጡን ምክክር ተነስተን፤ በ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት የተሟላ ድልድይዕነት፤ አዲስ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት ቀርፀን፣ ተየሀ-ማዶ ወዲያ-ማዶ በቁርጠኛዕነት ዘልቀን ተሻግረን፤ ወደ ኢትዮጵያዊ ህዝባዊ መንግሥት ምስረታ እሚያደርሰን'ን መንገድ መከተል፤ የቅንጦት አማራጭ ሳይሆን — ግዴታ ነው!

ለእዚያም ወሳኙ መሳሪያችን፤ መደራጀት መደራጀት እና መደራጀት መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል። አደጋ በተከሰተ ቁጥር ማለቃቀሱ አይጠቅመንም። መፍትሄው መደራጀት ነው። በ እሚረባ በእማይረባ ነገር ሰበብ እያደረግን አንከፋፈል። የሃሳብ ልዩእነቶች ሲፈጠሩ፤ ጊዜ ወስደን እንነጋገር እንወያይ። ፖለቲካዉን ወደ የግለሰብ ፍቅር አንቀይረው። ፖለቲካው ግለሰብን የመውደድ የመጥላት ጉዳይ ሳይሆን፤ የ ሃገር እና የህዝብ ጉዳይ ነው። መፍትሄው፤ ልዩዕነትን አስወግዶ ጠንካራ የተደራጀ ሃይል መፍጠር ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ጠላቶች እየበጠበጡን የአሉት እኮ ከ እኛ በላይ መደራጀት በመቻላቸው ነው። አይደለም እንዴ?!

ኮቪድ-19'ን በተመለከተ — አሁን አሁን እየአመረረ እንደመጣ ገሃድ ቢሆንም፤ የ ኤፒደሚክዕነቱን ቁመና ሊያጣ እንደእሚችል መገመቱ ከ ዕውነታው ብዙም አይርቅም። በጣም ወደፊት፤ የተወሰኑ ስፖራዲክ ኬዝስ እዚህም እዚያም መታየት እንደእሚችሉ፤ መገመት ይቻላል። ኢንደሚክ በሆነ ቁመና ለ የአልተወሰነ ጊዜ አብሮን ለመቆየት እንደ እሚችልም መተንበዩ ብልህዕነት ነው። ለማንኛውም፤ እጆችአችንን በአግባቡ ማፅዳት፣ የአካል እርቀትአችንን መጠበቅ፣ አፍ እና አፍንጫችንን መሸፈን እና አልፎ ተርፎም፤ ተጓዳኝ የአኗኗር ዘይቤዎችን መላመድ ጊዜው የእሚጠይቀው ግዴታ መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል። ለእራሳችንም ሆነ ለሰው ልጅ ሁሉ፤ ደግመን ደጋግመን ልንነገር የእሚገባን ቁም ነገር ነው!

መድሃኒትም ሆነ ክትባትን የማፈላለግ የማግኘት ጥረቶች፤ ተስፋ አስቆራጭ ባይሆኑም ሊደርሱልን በነበረበት ጊዜ አለመድረሳቸው፤ ብዙ ጥፋትን እንድናስተናገድ አስገድደውናል። ለማንኛውም፤ ድንገት ቢሳካ እና ጥሩ መድሃኒትም ሆነ ክትባት ከተገኘ — መድሃኒቱንም ሆነ ክትባቱን ለዜጎቻችን በፍጥነት ለማዳረስ እንዲቻል ከአሁኑ ዝግጅት መደረግ አለበት።

ኢትዮጵያዊ የህሊና/የሃሳብ እስረኞች የአለምንም ቅድመ ሁኔታ ዛሬውኑ ይፈቱ!

ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ዛሬውኑ ይመስረት!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዩ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# ቢለዋወጥ፤ ጉልቻ!

መስከረም ፪ሺህ፲፫ ዓ.ም ‖ ሴፕቴምበር 2020

**አዳራሽ** – እኛ ኢትዮጵያዊያን፤ ሃገርዓዊ ፈታና በተገደጋጋሚ በገጠመን ቁጥር ተፈጥሮዓዊ ህብር የአጎናፀፈን'ን አይበገሬ አንድዕነት፣ ዕምቅ ሃይል፣ አልገዛም ባይዕነት፣ ፅናት እና ጀግናዕነት በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል፤ ሁሌም በአሸናፊዕነት የተወጣን የ [ነፃዕነት] ህያው ትርጓሜ የሆን'ን ኩሩ ህዝብ ነን። ይህ እም፤ ከ አባት/እናት አያት ቅድመ-አያቶቻችን የወረስነው ክቡር መስዋዕተዕነት የተከፈለበት መለያ ማንዕነታችን እና ኩራታችን ነው። ይህ-እን'ን ረቂቅ ውርስ፤ ሃላፊዕነት በተሞላው መልኩ ጠብቀን ለ እሚቀጥለው ትውልድ ማሸጋገር፤ የ ዛሬው ትውልድ ሰው'እኛ ሃላፊዕነት'ም ግዴታ'ም ነው። "መንግስት" በጠራን ቁጥር ዘራፍ ማለቱን ከ አወቅንበት – ኢትዮጵያ ስትጠራን፤ <u>አምርረ'ን</u> ዘራፍ ማለቱን አስአምረን ልንአውቅበት የግድ ነው!

ድሮ-ድሮ፤ የተከሰቱት ፈተናዎቻችን የውጭ <u>ቀጥተኛ</u> ወረራን'ም ጭምር የአካተቱ ነበሩ። በ የ አለፉት 30 ዓመታት ገደማ የገጠሙን ሃገርዓዊ ፈተናዎች ግና፤ በአመዛኙ የውጭዎቹ ተቀጣሪ የሆኑ በጣት እሚቆጠሩ ነፃ-አውጪ ተብዬ ባንዳዎች በ እሚቀፈቅፉት መንጋ በመታጀብ፤ የኢትዮጵያ ፀር በሆነ መንግስት እና ህገመንግስት ተብዬ በመታገዝ እና በመመራት፤ ወገን'ን ከወገኑ ለማጣላት፣ እርስ በእርስ ለማፋጀት እና ሃገርን ለማፈራረስ ሌት-ተ-ቀን በመስራታቸው ምክንያት እየተከሰቱ የአሉ መጠነ-ሰፊ እና የ እማያባሩ ጦርዕነትዎች ናቸው። ታዲያ እማ፤ መከራ እና ስቃይ የ አንገፈገፈው ኢትዮጵያዊ በ አደረገው የሞት የሽረት ትግል እና በከፈለው ክቡር መስዋዕትዕነት፤ አራት-ኪሎ መሻገው'ን ገኸው-ግንባር ለመበስበስ እና ለመፍረስ አብቅቶት የአለ ቢሆንም ቅሉ፤ እንደ አለመታደል ሆኖ የ ኢትዮጵያ ወገን የሆነ የተደራጀ የተዘጋጀ ሃይል ስለ አልነበረ፤ ከግንባሩ ውስጥ ጊዜ የአነሳቸው ግለሰብዎች ወደ ስልጣነ መንበሩ እራስአቸውን ሾመው በ"መንግስትዕነት" መቀጠልአቸው ግልፅ ነው። ለተወሰኑ ወራት'ም፤ አብዛኛዎቻችን [በማመን፣ በመታለል፣ በመጠራጠር እና በመደናገር] ምህዋር ዙሪያ ስንዋዥቅ፤ ምን እየሆነ እንደአለ በግልፅ እንድንገነዘብ መቻል አቅቶን፤ ትግሉን እንደተፋፋመ እንዲቀጥል በማድረግ ፈንታ፤ እጅ እና እግራችንን አጣጥፈን በመመልከታችን፤ ሰቆቃው ያለማቋረጥ እንዲቀጥል እና ሃገርአችን'ንም እንድትጠፋ ለማድረግ እሚያስችል እጅጉን አስጊ – እጅጉን ፈታኝ አኳኋን ላይ አድርሰናት አለን።

ጎበዝ፤ ሰሞነኛው መንግስት ተብዬ ኢትዮጵያን ከመፍረስ አትርፈናታል የ እሚል ቀብድ እንደ አስያዘ በተደጋጋሚ ሲደሰኩር እንሰማለን። ይ-ህ ድብን የአለ ቅጥፈት ብቻ'ም ሳይሆን፤ ቀብድ በማስያዙ ይሉኝታ ይዞን ኢትዮጵያን ሲአጠፋ ዝም ብለን እንድናየው እያስገደደን እንደአለ'ም ዕሙን ነው። ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ሰሞነኛው መንግስት ተብዬ በ 1993 ነው ኢትዮጵያን አፍርሷት የ አለ። ዛሬ እማ፤ ማፍረስ ብቻ ሳይሆን ይበልጡኑ እየአጠፋትም ነው። ይ-ሄ ኢትዮጵያን የአፈረሰ፣ የባሕር-በሮቿን አሳልፎ የሰጠ፣ አንጡራ ሃብቷን የዘረፈ፣ ኢ-ሰብዓዊዕነትን የአንሰራፋ፣ አሸባሪዕነቱን የአመነ፣ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካን፣ ጎሠኛዕነትን እና ተገንጣይዕነትን የአጎለበተ፤ ማንም ይቅር ሳይለው እራሱን ይቅር ብዬ አለሁ ብሎ በመንግሥትዕነት በርጩማ ላይ ግግም ብሎ የተኮፈሰ'ው ገኸው የግንባር-ፓርቲ፤ ትጥቅ እና ስንቅ፣ የሰለጠነ የጦር ሃይል እና የመንግስት መዋቅሩን በመጠቀም፤ ለ አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች ለ ወራሪዎች ከለላ፣ ሽፋን እና ደጀን በመሆን፤ እየተከሰተ የአለውን ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ ሊ አስቀጥል እና ኢትዮጵያን ጭራሹኑ ሊ አጠፋት ሳያሰልስ በመዳከር ላይ ይገኛል። ጎበዝ፤ ሆነ ተብለው በተዘጋጁ አማላይ አዘናጊ ቃላት፤ ወራሪዎቹ እንደ እሚሉት "ኮንቪንስ" እና "ኮንፍዩዝ" እየአደረጉን፤ ሰሞነኛው መንግስት ተብዬ ኢትዮጵያን እንዲያጠፋት ዕድሉ'ን ልንሰጠው – አይገባም። በፍፁም!

ወራሪዎቹ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች እና በ እየ መንግስት ተብዬው መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉት ከሃዲዎች፤ ኢትዮጵያዊ ነን ብለው አያምኑም። ለአንድዕነት፣ ለዕኩልዕነት፣ ለሰላም እና ለሰውዓዊ መብቶች እሚታገሉ'ም አይደሉም። ይልቁን እስ፤ እነ እርሱ "ጠላት" እሚሉትን ኅብረተሰብ አጥፍተው፣ ኢትዮጵያዊ እሴትዖችአችን'ን አውድመው፣ ብርቅዬ ኢትዮጵያዊ ቋንቋችን'ን ሆሄያቶቻችን'ን አጥፍተው፣ ኢትዮጵያን እንደገና ወርረው በ እነ እርሱ ከልት'ዓዊ ማንዕነት ስር በማስገደድ ጠምጥመውን፤ በባዕድ ፊደላት እየአፃፉ ማንዕነታችን'ን ኢትዮጵያዊዕነታችን'ን አጥፍተው ረግጠው መግዛት'ን – አልሆን ከአላቸው ደሞ ኢትዮጵያችን'ን ማጥፋት'ን ዕቅድ ነድፈው ነው እየተንቀሳቀሱ የ አሉት። ይህ-እን'ን ዕውነታ ለ ዓመታት ስንነግራችሁ አንዓምን'ም የአላችሁ ወገኖች፤ በተለያዩ ጊዜያት – ወራሪዎቹ፤ እማይሰማ እየመሰላቸው "በድብቅ" መድርኮች ላይ ድርጅትዓዊ ተልዕኮ'አቸውን ለአባሎቻቸው ለመንጋቸው በ ትዕቢት ሲ አብራሩ ከሰማችሁ እና በተግባር እየሰሩ ከአሉት ጋር ከአመሳከራችሁ በኋላ፤ ኢትዮጵያን ለማዳን በፅናት ከእሚታገለው ወገን እንደአትቀላቀሉ ቀፍድዶ የያዛችሁ አጋንንት እንደለቀቃችሁ እንገምት አለን። ኢትዮጵያዊ ሰላምዓዊ ዜጎች'ን ከወንጀለኞችጋር ደባልቆ ወደ እስር ቤት ሲ አጉር፤ "መቃወም አያስፈልግም፤ የፍትህ ስርዐቱን ተከትሎ እሚሆነው ይሆናል" እምትሉ'ም ወገኖችአችን፤ ምን ያህል ስሁት እንደሆናችሁ ቢገባችሁ መልካም ነው። ለመሆኑ፤ ኢትዮጵያዊ ሰላምዓዊ ዜጎችን እና ሰንደቅ-ዓላማችን'ን፤ ፍትህዓዊ እና ህግዓዊ በሆነ መልኩ እማይጠብቅ'ን ወራሪ መንግስት ተብዬ – በ እንዴት የአለ ተዐምር ነው፤ ጠላት ብሎ በአደባባይ ጦርዕነት የ አወጀባቸውን ንፁሃን ሃሳብ–ታጣቂ ብዕር–ታጣቂ ዜጎች፤ ፍትህዓዊ እና ህግዓዊ ብይን ይሰጣቸዋል ብላችሁ እምታስቡት?! ስልጡን መሆናችሁን ብቻ ሳይሆን፤ ሰው መሆናችሁን'ም እንድንጠራጠር እየ አስገደዳችሁን እኮ ነው – ጎበዝ!

አሁንም፤ ጊዜ አላችሁ። የአልቆረጣችሁ ቁረጡ! ኢትዮጵያዊ አይደለሁም የ እሚልን ጠላት፤ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ በማካሄድ ላይ የአለን ዕብድ የአውሬ መንጋ የግድ ኢትዮጵያዊ ነህ/ነሽ ብለን መለማመጡ እና መአባበሉ ሊቆም ይገባል። በመንግስትዕነት'ም ሆነ በሃገሪቱ የፖለቲካ ዲስኮርስ ውስጥ ተካፋይ የመሆን መብት ሊኖራቸው'ም አይገባም። <u>ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለዋል እና!</u> ይሄ'ም – የ ዕብድ መንጋው የእንጀራ አባት እና የእንጀራ እናት የሆኑትን ከሃዲ ባለስልጣናት ከመቅጣት መጀመር አለበት። በሃገሩ ህዝብ ላይ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ ሲፈፀም – አይደለም፤ ማጋለጥ፣ መከላከል፣ መመከት፣ መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን – አንዲትም ሰው'እኛ ቃል ሲተነፍስ የአልተሰማው፤ ለ [<u>ሰው</u>] ክብር የሌለው ወራሪው መንግስት ተብዬ እሚአራምደው፤ የሌለ "የሁለት ፅንፍ" ዝባዝንኬ'ም፤ የሃገር ክህደት ተብሎ ሊመዘገብ ይገባል። ኢትዮጵያዊዕነት ፅንፈኚዕነት አይደለም፤ ዕውነተኛ ማንዕነታችን እንጂ! አክራሪ ጎሠኛዕነት ግን፤ ድብን የአለ በቀጣፊዎች የታመቀ ድርብ ፅንፈኚዕነት ነው። እናም፤ በፖለቲካው ዲስኮርስ ውስጥ "ወደ መሃል መምጣት" የ እሚባል የፈሪ፣ የተሸናፊ፣ የአፍራሽ እና የወራሪ አቋም ሊያዝ ቀርቶ፤ መታሰቡ'ም ከሃዲዕነት ነው። የአለው አማራጭ፤ ወራሪዎቹ ለ <u>ዕውነት</u> እጅ መስጠት ብቻ ነው። <u>ዕውነት'ም</u> ኢትዮጵያዊዕነት ነው!

የቅርቡ የ ባለ-ስልጣንአት መዘዋወር'ም፤ ፊውታል ኤክሰርሳይስ ነው። ቢለዋወጥ፤ ጉልቻ! “ብሄርዓዊ መግባባት” በ እሚል ሽፋን – ከ ኢንስቲቲውሽናል ኤክስክሉዥን የተረፉ ተፎካካሪ ተብዬዎች መገናኘትአቸው'ም፤ በ ኮቪድ-19 ሰበብ የተራዘመውን የምርጫ ዝግጅት እንደገና ነፍስ ሊዘሩበት እየአቅማሙ ለመሆኑ ፍንጭ ሰጪ ነው። ሰላም እና መረጋጋት ሳይሰፍን፣ የኅሊና እስረኞች ሳይፈቱ እና ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግስት ተመስርቶ አዲስ ኢትዮጵያዊ ህገመንግስት ሳይቀረፅ፤ ምርጫ የ እሚባል ነገር መኖር የለበትም። በምርጫው መሳተፍ'ም – ለሃገር መጥፋት እና ለሕዝብ ዕልቂት ተባባሪ መሆን ነው። በ ሕዝብ፣ በ ታሪክ፣ በ ህግ እና በ ኢትዮጵያ ዓምላክ ፊት የ እሚያስጠይቅ – ግዙፍ ነውር! ይልቁን እስ እንደራጅ።አዎ የበለጠ እንደራጅ። የ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ አደጋን እና ለኢትዮጵያ የ እሚመጥን የሽግግር መንግሥት ጠቀሜታን ለሕዝብ እና ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ እናስተምር እንቀስቅስ። ኀዥው የግንባር-ፓርቲ፤ ወደ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ፊቱን እንዲያዞር'ም ይጠየቅ ይገደድ። ይ-ህ'ም ተግባርዓዊ እንዲሆን፤ አመራር በ እየ አንድ-አንዱ ሀገር ወዳድ ዜጋ ውስጥ የአለ እሴት መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ – በዋናዕነት ግን፤ በፅናት የተፈተን'ን፣ በ ኢትዮጵያ እና በ ኢትዮጵያዊዕነት ድርድር እማይቃጣን ንፁህ የኢትዮጵያ ልጆች፤ እንደ አመቺዕነቱ በ ግለሰብ ደረጃም ሆነ በ ድርጅት፤ እጅጉን በተጠናከረ በተቀናጀ ስልት – መኖርአችን'ን በተግባር እንአስመስክር። ትርጉም ለ አለው ትግል እናብር። በሉ እንግዲህ፤ በርቱ – እንበርታ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!




እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገራችሁ – አሸጋገረን!

አዎ፤ ሃዘን ላይ ነን። ግና፤ ዝም አንልም። ለማን ደስ ይበለው ብለን?!

እንዘክር አለን እንአከብር አለን። የ ኢትዮጵያዊዕነትአችን የ ማንዕነትአችን አካል ነው እና! አንድ ህይወት ነው የአለን። ተመልሰን አንመጣም። ኢትዮጵያዊዕነታችን'ን ከትልድ ወደ ትውልድ ማስተላላፍ'ም፤ ግዴታችን ነው።

አዎ፤ እየታገልን እንኑር – እየኖርን እንታገል!

ኅበዝ፤

ተየህ በመቀጠል እንግዲህ እማተኩረው፤ በ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዙሪያ በማውጠንጠን፤ ሁልአችን'ንም በ ጤና ባለሙያዎች እሚሰጠን'ን ምክረ-መመሪያ ተቀብለን በአግባቡ በመተግበር ሃላፊዕነትአችን'ን እና ግዴታችን'ን እንደ አንድ ስልጡን የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ አባል፤ ቆፍጠን ብለን እንወጣ በ ማለት ላይ ነው።

እናም፤ “አብረን እንቆይ” – የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።

ቁጣ'ም ቢሆን፤ ከ የ እራስ ሰው ሲሰሙት ቀለል ይላል እና፤ አንዴ ስሙኝ እማ።

የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ፓርቲክል ወረርሽኝ፤ በ አንድ-አንድ ሃገራት፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ እየባሰበት ሲሄድ እንጂ ሲቀንስ እየታየ አይደለም። ይህ እም፤ በከፊል – ቴስት እሚደረጉ ሰዎች ቁጥር ከሙብዛት ጋር የተገናኘ ሊሆን ቢችልም፤ በማኅበረሰቡ ውስጥ ወደ ቅድመ ወረርሽኝ የ ዕለት-ተ-ዕለት ህይወት ለመመለስ እየተቻኮልን መሆኑ እና ተመጣጣኝ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን ለመውሰድ አለመዘጋጀታችን፤ ብሎም በሃላፊዕነት ቦታ ላይ በአለን ሰዎችም ሆነ በ እየ አንድ-አንዱ የ ማኅበረሰብ አባል፤ የለየለት መዘናጋት'ም ጭምር መሆኑን እንደገና ልብ ማለት ተገቢ ነው።

ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን፤ የህሙማን ቁጥር እየበዛ ሲሄድ ማየቱ ብቻ፤ እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል። ወረርሽኝ የ እሚጠይቅአቸውን ዘርፈ-ብዙ አገልግሎትዖች'ን የማዳረስ እና ለ ህሙማን ተገቢውን ህክምና የመስጠት አቅምአችን በቀናት ውስጥ ተሟጥጦ ሊያልቅ ይችላል፤ ወረርሽኙ በኅብረተሰቡ ውስጥ የበለጠ እየተቀጣጠለ'ም ሊሄድ ይችላል። ያ-ኔ መያዥያ መጨበጫው እንዳይጠፋን፤ አሁን እኑ ከ እንቅልፍአችን ልንነቃ ይገባል!

የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ፓርቲክል፤ የ መተላለፊያ መንገዶች አሁንም ቢሆን፤ በአመዛኙ ሀ) በትንፋሽ፣ በ እምንስልበት ወይም በ እምናስነጥስበት ጊዜ'ም፤ ከ ምራቅ ወይም ከ አፍንጫችን ውስጥ በእሚረጩ በእሚስፈነጠሩ ጥቃቃን እርጥብ–ብናኞች፤ በቀጥታ በቀረቤታ ወደ አለ ሌላ ሰው መተንፈሻ አካላት የደርሱ ሲሆን እና ለ) ከ ሳል ወይም ከ ማስነጠስ ጋር የ እሚረጩት የእሚስፈነጠሩት ጥቃቃን እርጥብ–ብናኞች፤ በቀጥታ'ም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ በ እሚያርፉባቸው የሰውዕነት አካል'ም ሆነ ማናቸውም በእጅ ሊነኩ የእሚችሉ ነገሮችን ከነኩ በኋላ፤ እጅን በእሚገባ ሳይታጠቡ ሳያፀዱ፤ ፊትን አፍንጫን እና ዓይንን የነካካን እደሆን ነው።

እናም፤ እጆችአችንን በአግባቡ ማፅዳት፣ የአካል እርቀትአችንን መጠበቅ፣ አፍ እና አፍንጫችንን መሸፈን እና በዛ ብሎ አለመሰብሰብን ጨምሮ አዲስ የአኗኗር ዘይቤን መላመድ፤ የግድ እንደሆነ ደግሜ ደጋግሜ መናገር እወዳለሁ! ኢንስቲቲውሽናላይዘድ የሆኑ የማኅበረሰቡ አባላትን፣ የጤና ሙያተኞችን፤ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ የስራ መስኮች ላይ የአሉ ሠራተኞችን የተለየ እንክብካቤ ሊደረግላቸው የ እሚገባ መሆኑን'ም እንዲሁ!

ኅበዝ፤

በተገቢው መጠን ክትባት የወሰዱ የማኅበረሰቡ አባላትን እስከእምንፈጥር እና የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ፓርቲክል'ን ስርጭት ከወረሽኝዕነት ደረጃው ዝቅ ማድረግ እስከእምንችል ድረስ፤ [መዘናጋት] የ እሚባል ነገር፤ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት ከማጣት ጀምሮ ሁለዕንተንዓዊ በሆነ መልኩ፤ ዋጋ


እንደእሚያስከፍለን፤ ደጋግመን ልብ ልንል ይገባል። ጦርዕነቱ አደብ አልገዘቶም!

ከዚያም በላይ፤

ወደድንም ጠላን'ም እየኖርን የአለነው ማህበረሰብዓዊ ህይወት ነው። የ ጋራ ህይወት ነው። የ አብሮዕነት ህይወት ነው። አብሮዕነት ደሞ ስልጡንዕነት'ን ይጠይቃል። ስልጡን ሰው ደሞ፤ ለእራሱ ብቻ ሳይሆን – ለቤተሰቡ፣ ለጎረቤቱ፣ ለሰፈሩ፣ ለከተማው፣ ለሃገሩ፣ ለአህጉሩ፣ በ ዓለም ዙሪያ ተሰራጭቶ ለ እሚኖረው የሰው ልጅ ሁሉ እና ለ እሚቀጠለው ትውልድም ጭምር ያስብ አለ፤ ይጨነቅ አለ። ትክክል! ከ ቤትአችን ጀምሮ፤ የ እምንኖርበትን ዩኒቨርስ ሁለዕንተንዓዊ በሆነ መልኩ የ መንከባከብን'ም ወሳኝዕነት እግንዛቤአችን ውስጥ በአካተተ መልኩ።

የ ሳርስ-ኮሮናቫይረስ-2 ፓርቲክል'ን ስርጭት ከ ወረሽኝዕነት ደረጃው ዝቅ ለ ማድረግ እንችል ዘንድ፤ እናም ወደ ቅድመ ወረርሽኝ የ ዕለት-ተ-ዕለት ህይወትአችን አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንድንመለስ ይረዳን ዘንድ፤ እንድንወስድአቸው የእምንመከራቸው ጥርት በአለ ሳይንስ ላይ የተመሰረቱ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎች ሁሉ፤ ስልጡን የ ፕላኔት ምድር ማኅበረሰብ አባል መሆንአችንን እምናስመሰክርበት አንዱ ትንሹ እና "ቀላሉ" ቴስት ነው። ሁልአችንም ያ-ን'ን ሃላፊነትአችን'ን እና ግዴታችን'ን በአግባቡ መወጣት እንደ እምንችል አልጠራጠርም። በሉ በርቱ!

ቀጥሎ እንደ እምታዩት፤ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረገው የ ኮቪድ-19 ህሙማን ቁጥር፤ ከነበረበት ብዙም በአይቀንስም፤ በ ኦገስት አደብ ገዝቶ መታየቱ ግን፤ ተመስገን ነው።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኦገስት 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020፤ በኪርጊዝስታን ደሞ በ ጁላይ 2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት ከ 12/31/2019 እስከ 08/31/2020 ድረስ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ብዛት፤ በ ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ድምሩ – ወደ 25.3 ሚልየን ሲደርስ፤ ከእነዚህም ውስጥ 3.4 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ'ም ሪፖርት ተደርጓል።

ወረድ ብላችሁ የ እምታዩት ሰንጠረዥ ደሞ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት አዲስ ህሙማን ቁጥር ብዛት ከ ዲሴምበር 2019 እስከ ማርች 2020 ድረስ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ በ እየ ወሩ ሪፖርት የተደረጉትን አዲስ ህሙማን፣ የ አዲስ ህሙማን ጥቅል ድምር፣ የ ሙታን ጥቅል ድምር ቁጥር'ን እና ሙታን በፐርሰንት ሲሰሉ የተገኙትን ቁጥሮች የያዘው ነው።

ከ ሜይ አጋማሽ ጀምሮ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ብዛት ሲያሻቅብ ከቆዩ በኋላ፤ በነሃሴ ወር ብዙም ሳይቀንስ አደብ ለመግዛት እየአቅማማ ግን መሆኑ፤ አሁን'ም ቴስት የተደረጉ

ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄድ'ን፣ የመከላከል–የመቆጣጠር እርምጃዎች እየላሉ መሄድአቸውን እና በኅብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት– የመሰላቸት ማይንድሴት እየጎለበተ መምጣቱን ጠቋሚ ሊሆኑ እንደ እሚችሉ ማነሳሳቱ ክፋት የለውም።


ህይወታቸውን የእሚያጡ ህሙማን መጠን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ በትንሹም ቢሆን እየተሻለ–እየቀነሰ እንደመጣ ስለ መታየቱ ብዙ ምክንያቶች መጠቃቀስ ይቻላል። ለምሳሌ'ም ያህል — ሀ) ቴስት የእሚደረጉት ሰዎች ቁጥር [ዲኖሚኔተር] እጅጉን መጨመር ለ) አንድ ሁለት ሊረዱ የቻሉ መድሃኒቶች'ን መጠቀም'ን ጨምሮ፤ የተሻለ ፔሸንት ማኔጅመንት እየጎለበተ ስለመጣ እና ሐ) የ ኮሮናቫይረስ-2 በፍጥነት ሚውቴት የማድረግ ባህሪው፤ በአንድ በኩል ክትባት ለመስራት የእሚደረገውን ጥረት እንደተፈታተነው ዕሙን ቢሆንም፣ ምን አልባትም የከፋ ጉዳት የእማያደርሱ ሚውቴሽንስ ተፈጥረው ሊሆን በመቻሉም ጭመር ሊሆን እንደ እሚችል መጥቀሱ፤ ለአነበባችሁ ሰዎች እንደ የውውይት መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ፤ በቂ ይመስለኛል።

ኮቪድ-19 | ፕላኔት ምድር | 12/31/2019 – 08/31/2020


| ወራት | የ አዲስ ህሙማን ቁጥር | የ አዲስ ህሙማን ጥቅል ድምር | የሙታን ጥቅል ድምር | ሙታን በ ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| ከ ዲሴምበር 2019 እስከ ማርች 2020 | 777,798 | 777,798 | 37,272 | 4.8 |
| ኤፕሪል 2020 | 2,353,002 | 3,130,800 | 227,051 | 7.3 |
| ሜይ 2020 | 2,897,335 | 6,028,135 | 368,944 | 6.1 |
| ጁን 2020 | 4,244,866 | 10,273,001 | 505,295 | 4.9 |
| ጁላይ 2020 | 7,023,302 | 17,296,303 | 673,290 | 3.9 |
| ኦገስት 2020 | 7,955,031 | 25,251,334 | 846,841 | 3.4 |

ቀጥሎ የአለው ዝግብ ደሞ፤ እንደ አዲስ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን፤ የ እየ 7–ቀናት አማካይ ቁጥር ብዛትን በተመለከተ፤ በነሃሴ ወር አሜሪካ ከ ብዙ አስፈሪ የማሻቀብ ወራት በኋላ፤ የመቀነስ ምልክት አሳይታለች። አፍሪቃ ሪፖርት የ እምታደርጋቸው የ ኮቪድ-19 ህሙማን ቁጥር ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ፤ በእዚህ በነሃሴ ወር እንደ አህጉር፤ ይበልጡኑ የመቀነስ አዝማሚያ'ን ማሳየቱ ይበል እሚያሰኝ ነው።

በሌላው ጎን ደሞ፤ ከ ኤዥያ ሪፖርት የ እሚደረጉት የ ኮቪድ-19 ቁጥር ሳያሰልስ ማሻቀብ፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት ዝም ብሎ ባይመለከተው ጥሩ ይመስለኛል — ክትባት ከ ሶስት አራት ወራት በኋላ ለጥቅም እንደእሚዉል ተስፋ ማድረጋችን የተጠበቀ ሆኖ። አውሮጳ'ም ለብዙ ወራት ወረርሽኙ እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የ ቁልቁለቱን መንገድ አጥብቃ እንደተያያዘችው አይተን ደስ ሲለን፤ በነሃሴ እንደገና እንደአሻቀበ ማየት'ም ይቻላል።





ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ 7–ቀናት አማካይ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኦገስት 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለሚፈጅ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020 በኪርጊዝስታን በ ጁላይ 2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶች በመጠቀማቸው ሳቢያ፤ እየእያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን (ዩኤስኤ እና ካናዳ)፣ ደቡብ እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኦገስት 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

የ ኢትዮጵያ ነገር የበለጠ እየአሳሰበኝ ስለመጣ፤ አንድ-አንድ ነገሮችን ከፍ ብዬ አነሳስቼአለሁ። አዎ፤ ኢትዮጵያ ሪፖርት እምታደርጋቸው ህሙማን ቁጥር፤ ከ ዕለት-ወደ-ዕለት እየአሻቀበ መምጣቱ [እንደገና እደግመውአለሁ] እንቅልፍ ሊነሳን ይገባል። እየከፋ የመጣው የሰላም እና መረጋጋት አለመኖር፤ አሉትአዊ ኮንትሪቢውሽን ኖሮት ይሆናል ብዬ ብገምት'ም — አትፍረዱብኝ። ለማንኛውም ጎበዝ፤ ነገሮች ሁሉ በፍጥነት ሊለዋወጡ ስለእሚችሉ፤ መዘናጋት እሚባል ነገር መኖር የለበትም። በፍፁም!




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኦገስት 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቁጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ'ም ጭምር፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመጨረሻም፤

የኢትዮጵያ ጥቅል መሠረትዓዊ ችግር፤ [የባዕድ ተስፈኞች፣ አሳፋሪ ሃገር-ወዳድ ተብዬዎች፣ የጎሣ ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች፤ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ህገመንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌዴራሊዝም እና አነእኘህን ተከትሎ በተደጋጋሚ እየተከሰተ የ አለው ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ እና ኢትዮጵያን የ ማጥፋት የተቀናጀ ዘመቻ] ነው።

ችግርአችን፤ ግለሰብ'ን የመውደድ እና የመጥላት ጉዳይ ሆኖ አያውቅም። እንዲያውም፤ ገዥው የግንባር-ፓርቲ ውስጥ የ አላችሁ ቀና ኢትዮጵያዊያን፤ ሰሞኑን እየሆነ የአለውን ጉድ ሁሉ ከአያችሁ በኋላ፤ ለምን በሙሉ ልብአችሁ፤ ዛሬውኑ ከ ህዝብ ጎን እንደእማትቆሙ ማወቅ በእጅጉ ተቸግረን አለን! ይ-ህን'ን እምንለው የእሚያዋጣችሁ ያ-ነው ብለን ብቻ ሳይሆን፤ ጤናማ ኅሊና የአለው ሰው ሊወስድ የእሚችለው አቋም ያ-እና ያ-ብቻ እንደሆነ ታጡትአላችሁ ብለን ስለእማናምን መሆኑን ልንነግራችሁ ስለእምንፈልግ ጭምር'ም ነው። ዕመኑን፤ ቁጥር አንድ ችግርአችን ኢትዮጵያዊ ከአልሆነ መንግስት እና ኢትዮጵያዊ ከአልሆኑ ተቋምአት ጋር ነው።

እናም፤ የጉልቻ መለዋወጥ – እርባና ቢስ ነው። እምንፈልገው እና እምንታገልለት "ስርነቀል" የ ስርዐት ለውጥ ነው።

አዎ፤ ገዥው የግንባር-ፓርቲ [በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ] የ ሕዝብን ስልጣን ለ ሕዝብ ያስረክብ። ለ 30 ዓመታት ያህል ቁጥር ስፍር የሌለው ወንጀሎች ፈፅማችሁ አለ — በቃችሁ! የ ሕዝብን፣ የ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጥምረት በማቀናጀት፤ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ይመስረት። በቴክኖክራቶች የእሚሞላ ፈርጀ-ብዙ [ታስክ ፎርስ] ተዋቅሮ፤ ለ የሽግግር መንግስቱ እሚያስፈልገውን ሙያዊ ድጋፍ ይስጥ።

የሽግግር መንግስቱ፤ በዋናዕነት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ያስከብር፣ የህዝቧን ሰላም እና መረጋጋት ያስፍን፣ የ ሁሉንም ተቋምአት ተግባር በሃላፊዕነት ይምራ፣ እሚቀጥለውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበት'ን ምርጫ – ፍትህዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ እሚያስፈልጉትን ተቋምዓዊ ለውጦች ተግባርዓዊ ያድርግ። ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት ይቅረፅ። እንደ አዲስ በእሚቀረፀው ህገመንግሥት ውስጥ — አለመረሳቱን ብቻ ሳይሆን፤ ጎልቶ መታየቱንም ጭምር እርግጠኛ ልንሆን ከእሚገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳይዖች መሃከል፤ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ይደረግ። በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ይካተት። ሰው በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ይመስረት።

ጎበዝ፤ ደጋግመን ገልፀናል — ይ-ሄ ከላይ የጠቀስኩት ሁሉ የአዳራሽ ሃሳብ ነው። በአካሄድ ለየት-የአሉ የተሻሉ፤ በግብ ግን [አይደንቲካል] የሆኑ ሃሳቦችን ለማስተናገድ ዝግጁ ነን። ዋናው ነጥብ ማሸነፍ ነው። ዋናው ጉዳይ ህዝብን እና ሃገርን ከጥፋት ማዳን ነው። እናሸንፍ ዘንድ'ም፤ በግልአችን ስልጣን ለመያዝ እየዓለምን መታገል ማቆም አለብን። መታገል የአለብን ለማሸነፍ እና ድል ለማድረግ ነው መሆን የአለበት። መታገል የአለብን ህዝብን እና ሃገርን ከጥፋት ለማዳን ነው መሆን የአለበት።

ከ አሸነፍን እና ድል ማድረጋችንን እርግጠኞች ከሆንን በኋላ፤ ህዝብን እና ሃገርን ከጥፋት ከአዳንን በኋላ፤ ህዝቡ፤ በማሸነፉ ትግል ውስጥ እና ለድል በእሚደረገው ፍልሚያ ውስጥ — ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትአቸውን እና ሃላፊዕነአቸውን መሸከም እንደ እሚችሉ የአስመሰከሩ ብቁ ስልጡን ዜጎችን፤ በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ እንዲወስን ይደረጋል። አበቃ!

ኮቪድ-19'ን በተመለከተ፤ ደጋግሜ መናገር እመፈልገው፤ ጦርዕነቱ ገና የ አላበቃ መሆኑን ነው። እናም፤ መዘናጋት የ እሚባል ነገር መታሰብ የለበትም። አደራ!

ሆኖም፤ እንደ አጀማመሩ ፍፁም አስፈሪ ሁኔታ ላይ አይደለም የአለነው። እንዴት ቢሉ – አሁን አሁን እዚህም እዚያም እየተሰማ የአለው፤ ክትባት ተገኝቷል'ም ሆነ ሊገኝ እየተቃረበ ነው እሚለው ዜና፤ ተስፋ ፈንጣቂ ነው እና። ልብአችን አረፍ የእሚለው ግን፤ ክትባቱን በተገቢው ብዛት ማኅበረሰብአችን ማግኘቱን እርግጠኞች ከሆንን በኋላ እና — ኮንታክት ሬሽዖ እምንለውን በእጅጉ መቀነስአችንን እርግጠኞች ስንሆን እንዲሁም ቤዚክ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዖ እምንለውን ደሞ አንድ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በአስተማማኝ መጠን ከአንድ በታች መውረዱን የመዘገብን እንደሆነ ብቻ ነው። በሉ እንግዲህ፤ በርቱ – እንበርታ።

ኢትዮጵያዊ የህሊና/የሃሳብ እስረኞች የአለምንም ቅድመ ሁኔታ ዛሬውኑ ይፈቱ!

ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ዛሬውኑ ይመስረት!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዬ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# በ-እሳት ጨዋታ!

ጥቅምት ፪ሺህ፲፫ ዓ.ም ‖ ኦክቶበር 2020

**አዳራሽ:** ለ ዓመታት እየተጠቀምንባቸው የአሉት የትግል ስልቶቻችን፤ ስኬታማ እንደአልሆኑ መገንዘብ አለመቻልአችን ግልፅ ነው። የለም፤ ተገንዝበን አለ ከአልንም – ሌላ የተሻለ መፍትሄ ፈልገን ትግሉን በአሸናፊዕነት መወጣት የ አልቻልንበት ምክንያቱን ምን ብለን ልንጠራው እንደእሚገባ ማወቅ እፈልግ አለሁ። እርባና–ቢስ ጉዳዮች ላይ ጊዜ እያጠፋን፤ ሰቆቃችን አላባራ እየአለ ዜጎቻችን አረመኔዓዊ ጭፍጨፋ እየደረሰባቸው እና ሃገርአችንም እየተሰቃየች መሆንዋ የወቅቱ ዕውነታ እንደሆነ አለ። የ[ሰው] ልጅ ሰቆቃ ያከትም ዘንድ እና ሃገርን ከስቃይ ለማዳን፤ [ገዥው አካል እና የተወሰኑ ሸሪኮቻቸው ብቻ ሳይሆን፤ በእራስአችን ላይ የጣልነውን መአቀብ አንስተን፤ ውጪ ሃገር እሚገኙ በኢትዮጵያ ሉዐላዊዕነት ፅኑ ዕምነት የአላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም የሠራተኞች እና የሕዝብ ተወካዮችን ጭምር በቅንነት የአካተተ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ውይይት ማድረግ የግድ ነው። ገንጣይ ተገንጣይ መሃል ሃገር እየጨፈረ፤ የ ኢትዮጵያ ልጆች ባይተዋር እሚሆኑበትን ጊዜ፤ ቁጭ ብሎ መመልከት — ያማል!

ተደጋግሞ እንዲነገረን የግድ ነው። ለምን ቢሉ፤ ሰቆቃችን ተደጋጋሚ መሆኑን ስለአላቆመ! በ ጥቅምት 2012፣ በ ሰኔ/ሃምሌ 2012 እና በመስከረም 2013 የተፈፀሙት እና እየተፈፀሙ የአሉት አረመኔዓዊ ጭፍጨፋዎች [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ–ሪሊጀስ ክሊንዚንግ] የመሳሰሉት ክስተቶች፤ እየተደጋገሙ ከመፈፀም ልናስቆምአቸው የአልቻልንበት ምክንያቱ፤ ከእዚህ በታች የእምለውን በማድረግ ፈንታ፤ ሌሎች [ኦብቪየስሊ፤ ስኬትአማ የአልሆኑ] ጉዳዮች ላይ ጊዜ በማጥፋት ስለተጠመድን ነው እና! ጎበዝ፤ ይ–ሄ ለእናንተ ይጠፋችኋል ብዬ አይደለም — በፍፁም። ግና፤ ከጓዶቻችሁ፣ ከ ጓደኞቻችሁ፣ ከ ወዳጅ ዘመድ ጋር ሁሉ ትወያዩበት ዘንድ ምክንያት ይሁንአችሁ ብዬ እንጂ። መሠረትዓዊ ችግርአችን በእራሱ በተዐምር አይጠፋም፤ ተገቢውን መፍትሄ በተገቢው ጊዜ መተግበር እስክአልቻልን ድረስ። መሠረትዓዊ ችግርአችን ደሞ በጥቅሉ — [የጎሣ ፖለቲካ እና የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች፤ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ– ኢትዮጵያ ህገመንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌደራሊዝም፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግስት የ አለመኖር፣ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋምአት የ አለመኖራቸው እና እነእርሱንም ተከትሎ፤ ለ 30 ዓመታት ያህል <u>በተደጋጋሚ</u> እየተከሰተ የ አለው ሰቆቃ፣ ብሎም ኢትዮጵያን የ ማሰቃየት የተቀናጀ ዘመቻ] ነው። እናም፤ <u>ትኩረትአችን እነእርሱ እና እነእርሱ ላይ ብቻ ይሁን እያልኩኝ ነው።</u>

መፍትሄው ግልፅ ነው። [ገዥው የግንባር–ፓርቲ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ የ ሕዝብን ስልጣን ለ ሕዝብ ማስረከብ – የ ሕዝብን፣ የ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጥምረት ማቀናጀት፤ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት መመስረት – በቴክኖክራቶች የእሚሞላ ፈርጀ-ብዙ [ታስክ ፎርስ] ማዋቀር፤ ለ የሽግግር መንግስቱ እሚያስፈልገውን ሙያዊ ድጋፍ መስጠት። ብሎም፤ የሽግግር መንግስቱ፤ በዋናዕነት የኢትዮጵያን ዳር–ድንበር ማስከበር፣ የህዝቧን ሰላም እና መረጋጋት ማስፈን፣ የ ሁሉንም ተቋምአት ተግባር በሃላፊዕነት መምራት – እሚቀጥለውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበትን ምርጫ – ፍትህዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ እሚያስፈልጉትን ተቋምዓዊ ለውጦች ተግባርዓዊ ማድረግ እና ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት መቅረፅ] ነው። ግብአችንም፤ እንደ አዲስ በእሚቀረፀው ህገመንግሥት ውስጥ አለመረሳቱን ብቻ ሳይሆን፤ ጎልቶ መታየቱንም ጭምር እርግጠኛ ልንሆን ከእሚገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳይዖች መሃከል፤ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ማድረግ – በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ማካተት፣ ሰው በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመስረት – ብቻ ነው። ሌላ አማራጭ የለም።

ይህ–እን'ን ማድረግ ይቻላል። ሪሜምበር?..... አራት–ኪሎ መሻጊው ገዥው–ግንባር፤ የ ሺህ–ዓመታ ፅኑ መሠረት የነበረውን በ ዜጋዕነት ላይ የአተኮረ መርህን እሚከተል መንግስትዓዊ የአተዳደር ስርዐትን ነው፤ በ "አንድ ጨረቃ" — ወደ ጎሣ–ተኮር ሃገር አፍራሽ ወገን አስጨራሽ ስርዐት የለወጠው። ያደረገው ነገር ቢኖር፤ ህገመንስቱን በእሚፈልገው መልኩ ቀረፀ፤ ለተግባርዓዊዕነቱም በሙሉ ልብ ሌት–ተ–ቀን ሰራ። የሺህ ዓመታት ፅኑ መሠረት የአለው፤ ዜጋዕነት ላይ የአተኮረ ስርዐትን ብቻ እሚያውቀው፤ በብዙ ሚልየን እሚቆጠር ትውልድ እና መንግስትዓዊ መዋቅር ስለአለ፤ ህዝቡ እሺ አይለንም በእሚል ሽብረክ አላለም። ዩ – ሲ?! ለውጥ እሚመጣው እንደእዚያ ነው! አንድ–አንድ ወገኖች ግና፤ የ ጎሣ–ፖለቲካ እና ዕኩዩ ፌደራሊዝም ለሰላሳ ዓመታት ተግባርዓዊ ስለተደረገ እና ከሰላሳ ዓመት ዕድሜ በታች የአለው ትውልድ፤ ዜጋ ላይ የአተኮረ የ ፖለቲካ ስርዐትን ስለእማያውቅ፤ ወደ ዜጋ ተኮር ፖለቲካ "በአንድ ጨረቃ" እንለውጥ ብንል እሺ ብሎ አይቀበለንም በእሚል፤ ህዝብ እንዳይታገል የከላከላሉ። ዕመኑኝ፤ በእሚገባ መለወጥ ይቻላል — "በአንድ ጨረቃ!" ማድረግ የአለብን ነገር ቢኖር፤ ለዜጋ በእሚጠቅም መልኩ – ማለትም፤ የኢትዮጵያን ሉዐላዊዕነት በጠበቀ መልኩ [ቋንቋው – ወግ ባህሉ – ሰውዓዊ መብቶቹ ተከብረው – በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ተዘዋውሮ የመኖር – የፈለገውን የማግባት፣ የመውለድ የመክበድ – ሃብት ንብረት የማፍራት፤ <u>የመምረጥ የመመረጥ</u>] መብቶቹ ሁሉ ሳይሸራረፉ እሚከበሩበት እንዲሆኑ ለ ማድረግ፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ በቅንነት በማሳተፍ ህገመንግስቱን በጋራ ቀርፀን ለተግባርዓዊዕነቱም በሙሉ ልብ ሌት–ተ–ቀን መስራት ብቻ ነው። ያ–እንን በማድረጋችን እምንአገኘው ትርፍ ደሞ፤ እጅጉን ግዙፍ ነው። እንዴት ቢሉ — በተደጋጋሚ እየተከሰተ የ አለውን ሰቆቃ፤ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ግዜ <u>መወገዱን</u> ያስገኝልናል እና!

ፍትህ – በ ማንዕነትአቸው ምክንያት በእየ–ዕለቱ ለእሚጨፈጨፉ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን! | ፍትህ – ለ ኢትዮጵያዊ የኅሊና/የሃሣብ እስረኞች! | ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግስት ዛሬውኑ ይመስረት!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

የ — ተየህ በታች ትኩረቴ፤ በ ሁለት ተጓዳኝ ጉዳዮች ዙሪያ ያውጠነጥናል። የ የሰሞነኛው መንግስት ተብዬ ብሔርዓዊ ምርጫ፤ እንዲሁም የ ጤና ተቋማቱ ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣብ አንደኛው ሲሆን፤ የ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ወርሃዊ ወፍ–በረር ዳሰሳ ደሞ ሁለተኛው ይሆናል።

እናም፤ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።

**<u>ጉዳይ አንድ፦</u>** <u>የሰሞነኛው መንግስት ተብዬ ብሔርዓዊ ምርጫ፤ እንዲሁም የጤና ተቋማቱ ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣብ።</u>

በ ወርሃ ነሃሴ 2012 ዓ.ም. ሊደረግ ታቅዶ የነበረው ስድስተኛው ብሔርዓዊ ምርጫ፤ በተለየ መልኩ አወዛጋቢ ሆኖ እንደቆየ አይዘነጋም። ምርጫው በታቀደው መሠረት መደረግ አለበት እሚሉ በአንድ በኩል — የለም፤ ምርጫው በታቀደው መሠረት አይደረግ፣ ይተላለፍ እሚሉ [አክባሪዎን ጨምሮ] ደሞ — በሌላ በኩል ተሰልፈን እንደመገዳደር ሲቃጣን!

ጉዳዩ፤ ከ መጠነኛ ሰልፍ አቀያየር በስተቀር፤ አሁንም ድረስ የቀድሞውን ገፅታ እንደጠበቀ ነው።

እስከ ሚያዝያ 2012 ዓ.ም. ድረስ፤ ምርጫው በእቅዱ መሠረት መደረግ አለበት ይሉ የነበሩትን፤ በሦስት ጎራ ማስቀመጥ ይቻላል።

1. ሰሞነኛው፤ የጎሣ–ፖለቲካ አራማጁ መንግስት ተብዬ — የሃገሪቷን የመንግስት መዋቅርአትን እና ሪሶርስ እየተቆጣጠረ መሆኑን፣
2. ተደጋፊ፤ አስመሳይ ተፎካካሪ ድርጅት ተብዬዎች — ከ መንግስት ተብዬው ጋር ሽሪክነታቸው ትርፍራፊ ስልጣን እንደእሚያስገኝላቸው ማመንን እና
3. ህዝብ-አስጨራሽ ሃገር-አፍራሽ የጎሣ–ፖለቲካ ድርጅቶች ደሞ — በቂ ዝግጅት አድርገው በቂ ደጋፊም እንደአላቸው በ እብሪት እሚያምኑ የነበር መሆናቸውን መጥቀስ፤ በቂ ነው።

በሌላ በኩል፤

የለም፤ እንዴት ተደርጎ — ምርጫው በታቀደው መሠረት መደረግ የለበትም፣ መተላለፍ ነው የአለበት እምንለውን ደሞ በአንድ ጎራ ማስቀመጥ ይቻላል።

ከምንም በላይ፤ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን መሠረትዓዊ ማንዕነትአችን የአደረግን ህብር ኢትዮጵያዊያን፤ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ድርጅት —

ሰላም እና መረጋጋት የእሚባል ነገር በአለመኖሩ፣ <u>መሠረትዓዊ ችግሮቻችን</u> ምርጫ በማድረግ የ እሚፈቱ በ አለመሆናቸው እና ዘርፈ–ብዙ አመቺ ሁኔታዎች — ያገባኛል በእሚል ኢትዮጵያዊ ተቋምአዊ ተሳትፎ፤ ተሟልተው እና ተተግብረው እስኪገኙ ድረስ፤ ምርጫው ሊሰረዝ፣ ሊተላለፍ ይገባል ብለን እምንዐምን ስለነበር እና ዛሬም ስለእምንዐምን መሆኑን መጥቀስ በቂ ነው።

ጎበዝ፤

እስከ ሚያዝያ 2012 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ድረስ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተባባሰ የመጣው ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ፤ ምርጫው በእቅዱ መሠረት መደረግ አለበት ይሉ የነበሩት አካላትን እንኳ፤ እሚይዙት እሚጨብጡትን አሳጥቷቸው፤ ምርጫውን እናራዝመው ወይስ አናራዝመው እሚል፤ ነፍስ–ውጪ ነፍስ–ግቢ ጭንቅ ላይ እንደነበሩ እናስታውሳለን።

ምርጫ ቦርድም፤ ሁሉ ነገርአችን ምርጫ ማድረግ እሚያስችል አለመሆኑን በቅንዕነት እግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ የሆነ አልተርኔቲቭ ሃሣብ እያንሸራሸረ እንደነበር መገመትም ይቻል ነበር — በግልፅም ባይሆን!

ይህ በእንዲህ እንደ አለ፤

በ ታህሳስ 2012 ዓ.ም. መገባደጃ ላይ፤ ከ ወደ ሩቅ ምሥራቅ እንደተከሰተ የተነገረለት የ ሳርስ–ኮቭ–2 ወረርሽኝ፤ እስከ መጋቢት 2012 ዓ.ም. የመጀመሪያው ሳምንት ድረስ፤ በፕላኔት ምድር ላይ የአሉ ሃገራትን ሙሉ በሙሉ በማዳረስ — የ አዲስ ህሙማን እና ህመሙን መቋቋም ሳይችሉ ቀርተው ህይወትአቸው በአጭር እሚቀጨው ሰዎች ቁጥር በፍጥነት እየአሻቀበ መምጣቱ የፈጠረውን ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ ተከትሎ፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት የተደቀነብንን አደጋ ወደ ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝዕነት እንደአሳደገው እና ኮቪድ–19 ብሎም እንደሰየመው፤ የቅርብ ግዜ ተመክሯችን ነው።

እንቅልፍ–አልባ እንደሆነች እምናውቃት፤ በ ኮቪድ–19 ምክንያት — ኢንተርናሽናል ትራቭል በመታገዱ፣ ቢዝነሶች በመዘጋትአቸው፣ ስብሰባዎች በመገደብአቸው፣ የአለ በቂ ምክንያት ከቦታ ቦታ መዘዋወር በመታገዱ፣ አዳሜ [አጁን እንዲያፀዳ – አፍ እና አፍንጫውን እንዲሸፍን – የአካል እርቀቱን እንዲጠብቅ እና በእየቤቱ እንዲመሽግ በመገደዱ] ምክንያት በተፈጠረው ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ ሳቢያ — ፕላኔት ምድር ፀጥ እረጭ በማለቷ፤ ሁልአችንም ከፍተኛ ጥርጣሬ፣ ስጋት እና ጭንቀት ውስጥ ገብተን እንደነበርም አይዘነጋም።

ኢትዮጵያም፤ የ ሳርስ-ኮቭ-2 ቫይራል ፓርቲክል ኢንፌክሽን መጋቢት 2012 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ እንደተከሰተ ለመጀመሪያ ጊዜ ሪፖርት ማድረግ ከጀመረች በኋላ — ሚያዝያ 2012 ዓ.ም. መገባደጃ ላይ፤ ምንም እንኳን አጠቃላይ ፕሮፋይሏ [በእየ ዕለቱ ሪፖርት ይደረጉ የነበሩት ህሙማን ቁጥር ስቴል ሲንግል–ዲጅት ውስጥ ስለነበር] ሪሌቲቭሊ የከፋ ደረጃ ላይ ደረሰ እሚባል ባይሆንም ቅሉ፤ ስርጭቱ በ አንሰርቴንቲ የታጀበ፤ እየጨመረ ለመሄድ ፈራ–ተባ እየአለ ይከሰት የነበረበት ጊዜ ላይ የደረሰች ይመስል ስለ ነበር እና በተፈጠረው ከፍተኛ ግሎባል ተፅዕኖ ሳቢያ — ቀስ እያለችም ቢሆን፤ ጥርጣሬውን ስጋቱን እና ጭንቀቱን ከቀሪው የ ዓለም ኅብረተሰብ ጋር ከመጋራት ማምለጥ እንደአልቻለች አይተናል።

እናም፤ ለ ግሎባል ስቴት ኦፍ ኢመርጀንሲ'ው፤ አቅም በፈቀደ መጠን ጠንካራ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን ተግባርዓዊ በማድረግ፤ የ ፕላኔት ምድር ኅብረተሰብ ስልጡን አባል ከሆኑት ውስጥ አንዷ መሆኗን አሳይታለች።

ያ–ኔ ነበር፤

ማሸነፍ የመቻልአቸው ነገር፤ ከቀን ወደ ቀን የበለጠ አጠራጣሪ የሆነባቸው፤ ምርጫው ይደረግ ባይ ፖለቲከኞች [ከ ጎሣ–ፖለቲከኞቹ በስተቀር] የ ኮቪድ–19 ግሎባል ስቴት ኦፍ ኢመርጀንሲ የፈጠረውን ቀውስ፤ "ጥሩ" እና የአልታሰበ አጋጣሚ እንደሆነ፤ ከላይ ከፈጣሪያቸው በ ራዕይ ስለተነገራቸው፤ አራት–ኪሎን ዕኩለ ሌሊት ላይ ከእንቅልፏ ቀስቅሰው፤ በ ጂም ጃም'አቸው እንዳሉ ነበር ጉዳዩን ቶሎ አፈፍ አድርገው፤ ምርጫውን ለማራዘም እንደምክንያት ሊጠቀሙበት የወሰኑት።

ወዲያውኑም፤ ገዥው የግንባር–ፓርቲ የ ብሔርዓዊ ጤና ተቋሙን ምስክርዕነት ኋላ ኪሱ ውስጥ ከትቶ፤ ወደ ሞት እየተጓዘ የበነረውን ፖለቲካውን ሪሰሲቴት በ እሚያደርግለት መልኩ በቀመረው ናሬቲቭ፤ ኮቪድ–19'ን መቼ በቁጥጥር ስር ማዋል እንደእሚቻል መገመት ስለእማይቻል በእሚል እና እደሆነው ሆኖ በቁጥጥር ስር ማድረግ ከተቻለ፤ አልያም በቁጥጥር ስር ማድረጉ አዳጋች ሆኖ 'ኒው ኖርማል" መጀመር እምንገደድ ከሆነ — ከ ዓመት በአልበለጠ ግዜ ውስጥ ምርጫውን ወደ ማድረግ ሊጓዝ እንደእሚችል በይፋ አስታወቀ።

ገዥው የግንባር–ፓርቲ፤ ይ–ህ እንን ሁሉ ያደርግ የነበረው — ምርጫውን ለማራዘም ብቸኛው እና ዕውነተኛው ምክንያት ኮቪድ–19 እንደሆነ፤ ፀረ–ኢትዮጵያ የሆነውን ህገመንግስት ተብዬ ዓምላኪ የ ፍትህ ተቋም የሙጥኝ ብሎ፤ የ አንድ አንድ ግለሰቦችን እና የ ብሔርዓዊ ጤና ተቁዋሙን ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣቦች ተላብሶ፤ አዳሜን "ሊያሳምን" የሰራው [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ] ቲያትር እንደነበር መገንዘብ፤ በወቅቱ ከባድ አልነበረም።

እኛም ታዲያ፤

ኮቪድ–19፤ ሰበብ "ጥሩ" አጋጣሚ መሆኑን ብናውቅም እና ዘላቂ–መፍትሄ ሊሆን እንደእማይችል ብናምንም፤ ምርጫው መራዘሙን ግን፤ ሁልአችንም [መቼስ ማል ጎደኒ] በእሚል፤ በበጎ መልኩ አይተነው አልፈናል።

ጎበዝ፤

ሲቆላ ሲታመስ የነበረውን የ ገዥው የግንባር–ፓርቲ አሻሮ ፖለቲካ፤ የምርጫው መራዘም ጭራሽእኑ እየአሳረረው መጥቶ፤ እሳት የላሱ ፖለቲከኞች ተአማኝዕነት የአለው "ህገመንግስትዓዊ" ነጥብ በመጥቀስ፤ የ መንግስት ተብዬውን ሌጂትመሲ አደጋ ላይ ስለጣሉት — የሆነ መውጫ ቀዳዳ መፈለግ ግዴታ ሆኖበት ነበር።

ገዥው አካል እና ገዥው አካል ብቻ ሊያውቀው በእሚችል ዕኩይ ስራ በተፈጠረው ክስተት ዙሪያ እና በተከታታይም ለቀናት በሰፊው የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ ሲተገበር የቆየው [ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ – ብሎም፤ ኢትዮጵያን የማጥቃት የተቀናጀ ዘመቻ] የፈጠረው ቀውስ በርጩማውን ስለ አንገጫገጨበት፤ አውሬ ወንጀለኞችን እና ንፁህ ኢትዮጵያዊያንን [ተገዳዳሪ ፖለቲከኞችን ጨምሮ] በገፍ ወደ እስርቤት በመወርወር — በማረር ላይ የነበረውን ፖለቲካውን ማብረጃ መተንፈሻ ቦታ በመፍጠር፤ በምርጫ የማሸነፍ ዕድሉን እንደገና ነፍስ የዘራበት ኢንቫይሮንመንት የተፈጠረለት ለማስመሰል፤ እራሱን እየአታለለ ይገኛል።

ጊዜው እየገፋ ሄዶ፤ መስከረም 2013 ዓ.ም. አጥቢያ ላይ ስንደርስም፤

ብቸኛው እና ዕውነተኛው ምክንያት የ ፖለቲካ ጫና እንደሆነ በ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ ተንታኞች እየተነገረ በአለበት ወቅት፤ ተራዝሞ የነበረውን ብሔርዓዊ ምርጫ ሪሰሲቴት ለማድረግ እንዲያስችለው በእሚል፤ መንግስት ተብዬው ኮቪድ–19'ን በዋስ ጠበቃዕነት እንደገና ተጠቅሞበታል።


የ ሚያዝያው 2012 ዓ.ም. [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ] ቲያትር ስኼሌ [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ 2] መሆኑ ነው እንግዲህ — የ መስከረም 2013 ዓ.ም. አጥቢያው ሪሊዝ!

በ [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ 2] ላይ የቀረበው አመክንዮም፤ ኮቪድ–19 አሁንም የጤና ስጋት መሆኑን ጠቁሞ፤ አብሮን ሊቆይ ስለሚችል — እንዲሁም፤ የተሻለ ሰርቬይላንስ እና መረጃ፣ የመከላከል ቁመና እና የኀብረተሰብ ግንዛቤ በመፈጠሩ — ብሎም፤ የማስክ እና የሳኒታይዘር ምርት በሃገር ውስጥ በስፋት በመኖሩ፣ የ ጤና ተቋማት ዝግጁዕነት እና ግብዐት አቅርቦት በመሻሻሉ፣ የምርመራ ኪት ማምረትን ጨምሮ የላቦራቶሪ አቅም ማደጉን እና የዘርፈ ብዙ ምላሽ በተሻለ ቁመና ላይ እሚገኝ በመሆኑ — በተጓዳኝም፤ የሃገራት የምርጫ ተመክሮን በማየት፤ አንድ አንድ [ጀስት–ኢን–ኬዝ] እሚል ፕሬሚስ ላይ የአጠነጠኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በመጠቃቀስ፤ የ ጤና ተቋማቱን ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣብ በምስክርዕነት ጨብጦ፤ ብሔርዓዊ ምርጫው በ 2013 ዓ.ም. ይደረግ ዘንድ እንደወሰነ ሰምተናል።

<u>**ጉዳይ ሁለት፡-** የ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ወርሃዊ ዳሰሳ።</u>

ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት ከ 12/31/2019 እስከ 09/30/2020 ድረስ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት ህሙማን ብዛት፤ በ ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ድምር – ወደ 33.7 ሚልየን ደርሷል። ከእነዚያም ውስጥ 2.9 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለም ሪፖርት ተደርጓል።

ከ ሜይ አጋማሽ ጀምሮ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ብዛት ሲያሻቅብ ከቆዬ በኋላ፤ በኦገስት መጀመሪያ ላይ ከነበረበት ብዙም ሳይጨምር እስከ ሴፕቴምበር መጨረሻ ድረስ አደብ ሊገዛ እየአቅማመ የአለ መስሎ ቆይቷል። በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን ቁጥር — አሁን በአለበት ከፍተኛ ደረጃ አየ አደገ መሄድ መቀጠሉ፤ ቴስት የተደረጉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄድን፣ የመከላከል–የመቆጣጠር እርምጃዎች እየላሉ መሄድአቸውን እና በኀብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት እና የመሰላቸት ማይንድሴት እየጎለበተ መምጣቱን ጠቋሚ ሊሆኑ እንደ እሚችሉ ልብ ማለቱ፤ ተገቢ ነው።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው የተሰበሰቡት፣ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ሴፕቴምበር 30/2020 ከ 6:00 እስከ 10:00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020፤ በኪርጊዝስታን ደሞ በ ጁላይ 2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። በ ሴፕቴምበር 10 2020 ጀርሲ ዘጥኝ ህሙማንን አዲስ እንደአልሆኑ ሪፖርት ስላደረገች የ ሴፕቴምበር 11 2020 ሪፖርት ላይ ቅናሽ አስመዝግባለች። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ከ መስከረም 7 2020 ጀምሮ፤ የ ኢኳዶር ሪፖርት ከ ራፒድ ቴስት የተገኙ ህሙማንን በማንሳት፤ በጥቅል ድምሩ ላይ ቅናሽ አስመዝግቧል። በተጨማሪም፤ ከ ኦገስት 2020 መጨረሻ ጀምሮ፤ የስዊዲሽ ባላስልጣናት በ እየ ዕለቱ ዳታ ኮንሶሊዴት ማድረግ በመጀመራቸው፤ ወደ ኋላ በመመለስ ማስተካከያ እሚፈልጉትን ማስተካከል አይቀሬ ሆኗል።


ወረድ ብላችሁ እምታዩት ሰንጠረዥ ደሞ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት አዲስ ህሙማንን ቁጥር ብዛት — ከ ዲሴምበር 2019 እስከ ማርች 2020 ድረስ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ በ እየ ወሩ ሪፖርት የተደረጉትን አዲስ ህሙማን፣ የ አዲስ ህሙማን ጥቅል ድምር፣ የ ሙታን ጥቅል ድምር ቁጥርን እና ወረርሽኙ ከተከሰተ ጀምሮ እምስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ፤ ሙታን በፐርሰንት ሲሰሉ የተገኘውን ቁጥር የያዘው ነው።

ኮቪድ-19 | ፕላኔት ምድር | 12/31/2019 – 09/31/2020

| ግዜያት (በወራት) | የ አዲስ ህሙማን ቁጥር | ጥቅል የ አዲስ ህሙማን ቁጥር ድምር | ጥቅል የሙታን ቁጥር | ጥቅል የ ሙታን መጠን በ ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| ከ ድሴምበር 2019 እስከ - ማርች 2020 | 777798 | 777798 | 37272 | |
| በ ኤፕሪል 2020 | 2353002 | 3130800 | 227051 | |
| በ ሜይ 2020 | 2897335 | 6028135 | 368944 | |
| በ ጁን 2020 | 4244866 | 10273001 | 505295 | |
| በ ጁላይ 2020 | 7023302 | 17296303 | 673290 | |
| በ ኦገስት 2020 | 7955031 | 25251334 | 846841 | |
| በ ሴፕቴምበር 2020 | 8463261 | 33714595 | 1008932 | 2.99 |

ህይወታቸውን የእሚያጡ ህሙማን መጠን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ በትንሹም ቢሆን ኤፕሪል 2020 ላይ ወደ ሰባት ፐርሰንት የነበረው፤ ዛሬ 3 ፐርሰንት አካባቢ ስለ መሆኑ፤ ብዙ ምክንያቶች መጠቃቀስ ይቻላል። ለምሳሌም ያህል ሀ) ቴስት የእሚደረጉት ሰዎች ቁጥር እጅጉን መጨመር ለ) አንድ ሁለት ሊረዱ የቻሉ መድሃኒቶችን መጠቀምን ጨምሮ፤ የተሻለ ፔሸንት ማኔጅመንት እየጎለበተ ስለመጣ እና ሐ) የ ኮሮናቫይረስ-2 በፍጥነት ሚውቴት የማድረግ ባህሪው፤ በአንድ በኩል ክትባት ለመስራት የእሚደረገውን ጥረት እንደተፈታተነው ዕሙን ቢሆንም፣ ምን አልባትም የከፋ ጉዳት እማያደርሱ ሚውቴሽንስ ተፈጥረው ሊሆን በመቻሉም ጭምር ሊሆን እንደ እሚችል መጥቀሱ፤ ለአነበባችሁ ሰዎች እንደ የውውይት መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ፤ በቂ ይመስለኛል።

**እጆችአችንን በአግባቡ እናፅዳ | የአካል እርቀትአችንን እንጠብቅ | አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን | አዲስ የአኗኗር ዘይቤን እንላመድ**





<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ 7–ቀናት አማካይ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ሴፕቴምበር 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። በ ቻይና ሁቤ ክፍለ–ሃገር፤ በፌብሪዌሪ 13 እና 20 እንዲሁም በፈረንሳይ በ ሜይ 29/2020፤ በኪርጊዝስታን ደሞ በ ጁላይ 2020 የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ አሳይቷል። በ ሴፕቴምበር 10 2020 ጀርሲ ዘጥኝ ህሙማንን አዲስ እንደአልሆኑ ሪፖርት ስላደረገች የ ሴፕቴምበር 11 2020 ሪፖርት ላይ ቅናሽ አስመዝግባለች። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ከ መስከረም 7 2020 ጀምሮ፤ የ ኢኳዶር ሪፖርት ከ ራፒድ ቴስት የተገኙ ህሙማንን በማንሳት፤ በጥቅል ድምሩ ላይ ቅናሽ አስመዝግቧል። በተጨማሪም፤ ከ ኦገስት 2020 መጨረሻ ጀምሮ፤ የስዊዲሽ ባላስልጣናት በ እየ ዕለቱ ዳታ ኮንሶሊዴት ማድረግ በመጀመራቸው፤ ወደ ኋላ በመመለስ ማስተካከያ እሚፈልጉትን ማስተካከል አይቀሬ ሆኗል። አሜሪካ [ሰሜን (ዩኤስኤ እና ካናዳ)፣ ደቡብ እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።

ከፍ ብላችሁ የአያችሁት ዝግብ ደሞ፤ እንደ አዲስ ሪፖርት እሚደረጉት ህሙማን፤ የ እየ 7–ቀናት ወራጅ አማካይ ቁጥር ብዛትን በተመለከተ ነው። ከ ጁላይ 2020 ጀምሮ፤ አሜሪካ ከ ብዙ አስፈሪ የማሻቀብ ወራት በኋላ፤ የመቀነስ ምልክት በማሳየት ላይ መሆንዋ፤ አበረታታች ነው።


በሌላው ጎን ደሞ፤ ኤዥያ ሪፖርት እየአደረገች የአለችው የ ኮቪድ-19 ህሙማን ቁጥር፤ ሳታሰልስ ማሻቀቡን ገፍታበት፤ ከ ወደ አምስት ወራት በኋላ፤ ዛሬ አሜሪካ ሪፖርት እየአደረገች ከነበረችው በበለጠ መጠን ሪፖርት ማድረግ መጀመሯ፤ ጉልህ ሆኖ እየታየ ነው።

አውሮጳ'ም ለብዙ ወራት ወረርሽኙ እየቀለለ እንደመጣ እሚጠቁመውን የ ቁልቁለቱን መንገድ አጥብቃ እንደተያያዘችው አይተን ደስ ሲለን፤ በኦገስት አገረሸበት መሰለኝ፤ ይሄው እና አስከዛሬ ድረስ እየአሻቀበ መሆኑን ማየት ይቻላል።

አፍሪቃ ሪፖርት እምታደርጋቸው የ ኮቪድ-19 ህሙማን ቁጥር ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ፤ ከ ጁላይ 2020 መገባደጃ ጀምሮ፤ አሁን እስከ አለንበት ግዜ ድረስ እየቀነሰ በመሄድ ላይ መሆኑም፤ ይበል እሚያሰኝ ነው።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ሲፕቴምበር 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፣ የ ዓለም ጤና ድርጅትን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ሲፕቴምበር 30/2020 ከ 6:00 እስከ 10:00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቁጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ'ም ጭምር፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ከፍ ብለን የአየነው ዝግብ ደም፤ ዕውነታን አንፀባራቂ ነው ብለን እምናምን ከሆነ፤ ኢትዮጵያ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እምታደርጋቸው የ አዲስ ህሙማን ቁጥር፤ ሲጀምረም ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ — እስከ ኦገስት 2020 ኢጋማሽ ድረስ እየጨመረ የነበረው በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረገው አዲስ ህሙማን ቁጥር፤ መስከረም 2020 እስከተገባደደበት ግዜ ድረስ፤ እየቀነሰ እንደ አለ ማየት ይቻላል። ያ–ም አበረታታች ነው።

በመጨረሻም፤

የኢትዮጵያ ጥቅል መሠረትዓዊ ችግር፤ [የባዕድ ተስፈኞች፣ አሳፋሪ ሃገር-ወዳድ ተብዬዎች፣ የጎሣ–ፖለቲካ፣ የጎሣ–ፖለቲካ ድርጅቶች፣ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ህገመንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌዴራሊዝም እና አነእኝህን ተከትሎ በተደጋጋሚ እየተከሰተ የ አለው ጀኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና ኢትዮጵያን የ ማጥፋት የተቀናጀ ዘመቻ] ነው። የ ቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ የ መፍትሄ ትኩረትአችንም፤ <u>መሠረትዓዊ ጥቅል ችግርአችንን፤ በህብረት ቆርጦ በመነሳት ማረቅ እና በህብረት ቆርጦ በመነሳት ማረቅ ላይ ብቻ ሊሆን እንደ እሚገባ</u> በድርብ ሰረዝ እንደገና አፅንዖት በመስጠት ማለፍ ወድጄ አለሁ።

ያ–ከአልሆነ ግን፤

በ ጥቅምት 2012፣ በ ሰኔ/ሃምሌ 2012 እና በመስከረም 2013 ዓ.ም. የተፈፀሙት እና ዛሬም ጭምር እየተፈፀሙ የአሉት ጀኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ–ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፤ እየአሰለሱ እየተደጋገሙ መታየታቸው አይቀሬ ነው እሚሆነው!

የሰሞነኛው መንግስት ተብዬ ብሔርዓዊ ምርጫ፤ እንዲሁም የጤና ተቋማቱን ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣብ በተመለከተ፤ የ እኔ አቋም፤ ግልፅ ነው። ያ–ኔ፤ ከሚያዝያ 2012 ዓ.ም. መገባደጃ በፊትም ሆነ አሁን መስከረም 2013 ዓ.ም. ላይ እየአለንም ቢሆን፤ ስድስተኛው ብሔርዓዊ ምርጫ መደረግ አለበት ብዬ አላምንም — አራት ነጥብ

ለእዚያም፤ የ ፖለቲካ እና የኅብርተሰብ ጤና ምክንያቶች እምልአቸውን እንደ እሚከተለው አቀርብ አለሁ።

<u>የ ፖለቲካ ምክንያቶች፤</u>

ሀ) መሠረትዓዊ ችግሮቻችን ዛሬም ቢሆን ምርጫ በማድረግ የ እሚፈቱ በ አለመሆናቸው፣ ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ መሃል ሃገርን ጨምሮ ሰላም እና መረጋጋት የእሚባል ነገር ጭራሽእኑ በአለመኖሩ እና እንዲያውም እየባሰበት በመሄድ ላይ የአለ በመሆኑ፣ ሐ) ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያን ዋስ ጠበቃ መሆናቸውን የአስመሰከሩ፤ ንፁህ ኢትዮጵያዊያን [ተገዳዳሪ ፖለቲከኞችን ጨምሮ] የአለምንም ጥፋት፤ በግፍ እና <u>በቁም በቀል</u> እስር ቤት ስለተወረወሩ እና መ) በማን አለብኝዕነት፤ ምርጫው ከተካሄደ — ሊፈጠር እሚችለው ሁለዕንተንዓዊ ቀውስ እጅጉን የከፋ ሊሆን ስለእሚችል፤ እሚሉትን ያካትት አለ።

<u>የኅብረተሰብ ጤና ምክንያቶች፤</u>

ብሔርዓዊ የ ጤና ተቋማት፤ ኮቪድ–19'ንም ሆነ ማንኛውንም ጤና እና ጤና ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ፤ የ ኅብረተሰቡን [ጤና እና ደህናዕነት] ለመጠበቅ እሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን እና ምን ማድረግ እንደሚበጅ ሙያዓዊ ሪፖርት ማቅረብም ሆነ ሙያዓዊ ምክረ–ሃሣብ መስጠት — ስራቸውም፣ ሃላፊዕነትአቸውም እና ግዴታቸውም ነው።

ሆኖም ግን፤ ምርጫ በምርጫዕነቱ — ማለትም፤ ምርጫ ከ የፖለቲካ መሣሪያዕነቱ አግባበ–ነገር አኳያ በማማተር፤ ምርጫ ይደረግ አይደረግ እሚል ውሳኔ መስጠት፤ የ ጤና ተቋማት ስራ፣

ሃላፊዕነትም ሆነ ግዴታ እንደአልሆነ እነእርሱም ይጠፉቸዋል ብዬ በፍፁም አላስብም። ምርጫ ከ የፖለቲካ መሣሪያዕነቱ አኳያ — ፒውርሊ የፖለቲካ/የፍትህ/የህግ/የሰውዓዊ መብት ጉዳይ መሆኑን ብዙዎች ስለ እሚስማሙ!

እንዲያውም፤

ለህዝብ እንዲሰማ የተደረገውን ናሬቲቭ፤ ፖለቲከኞቹ አልያም አፈቀላጤዎቻቸው ዳክተርድ አድርገውት ይሆናል የእሚል ጥርጣሬ እንደ አለኝ ሳልጠቅስ ማለፍ አልፍልግም። የ ጤና ተቋማቱ፤ አሰቡትም አላሰቡት፤ ትኩረት ሰጡትም ትኩረት አልሰጡት — "ምርጫ ይደረግ አይደረግ" የማለት ማንዴቱን ለጤና ተቋማቱ ማን ሰጣቸው በእሚል፤ በአድማጭ በአንባቢ ዘንድ ግርታን መፍጠሩ አልቀረም እና!

የ ጤና ተቋማቱ ሰጡ የተባለው ሙያዓዊ ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣብ [በነገራችን ላይ፤ ሙሉውን ማድመጥም ሆነ ማንበብ ዕድሉን አላገኘሁም] ትክክለኛ እና ኮምፕሊት የሆኑ ቁጥሮች [ስንት ሰው ኢንፌክትድ እንደሆነ፣ ስንት ሰው ኢንፌክትድ ሆኖ ሪከቨር እንደአደረገ እና ኢምዩኒቲ ዴቬሎፕ እንደአደረገ፣ ስንት ሰው አሁንም ሰሴፐትብል እንደሆነ እና ስንት ሰው ህመሙን መቋቋም አቅቶት ህይወቱ እንደአለፈ፤ የመሳሰሉትን ማለቴ ነው] የተካተቱበት አለመሆኑ፤ የ ሪፖርት እና ምክረ–ሃሣቡ ኢንቴንት — ተዐማኝዕነቱን፤ ከ ሳይንስ ይልቅ ለ ፖለቲካ የአስረከበ መሆኑን ሹክ የእሚል አቀማመር አለው።

እነእኛን ትክክለኛ እና ኮምፕሊት ቁጥሮች ለማግኘት ደግሞ፤ እጅጉን ሰፊ የሆነ የ ቴስቲንግ እና የ ሰርቬይላንስ ትግበራን ይጠይቃል። ያ–ው የእኛን ሃገር የቴስቲንግ'ም ሆነ የ ሰርቬይላንስ ሽፋን፤ ኢምንት የመሆን ዕውነታ — ሆድ ይፍጀው ብሎ ማለፉ ነው እሚሻለው! ትክክል፤ በ ሪፖርቱ እና ምክረ–ሃሣቡ ላይ፤ አንድ አንድ ቁጥሮች ተጠቅሰዋል። ቢሆንም፤ በብሔርዓዊ ደረጃ የወረርሽኙን ዕውነተኛ ባህሪይ ማንፀባረቅ ስለመቻላቸው፤ መተማመኛ አልቀረበም።

ዝኾነ–ኾይኑ፤

እኔ ምርጫው መደረግ የለበትም እምልባቸው የኅብረተሰብ ጤና ምክንያቶች፤ የ እሚከተሉት ናቸው።

ሀ) ኮቪድ–19 አሁንም ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ በሆነ መጠን የጤና ስጋት በመሆኑ።

ኢትዮጵያም ውስጥ፤ [ትክክለኛውን ቁጥር ማወቅ ባይቻልም ቅሉ] ኢንፌክትድ እደሆኑ ሪፖርት የተደረጉት ሰዎች ብዛት [ወደ 70 ሺህ ገደማ እንደደረሰ አይቻለሁ] ቀላል እሚባል አይደለም።

እስከዛሬ በእየ ዕለቱ ሪፖርት እየተደረጉ የአሉትን የአዲስ ህሙማን ቁጥሮች ስናመዛዝን — መስከረም 2013 ዓ.ም. ላይ ሪፖርት እየተደረጉ ያአሉት፤ ሚያዝያ/ግንቦት 2012 ዓ.ም. መገባደጃ ድረስ ይደረጉ ከነበሩት እጅጉን ከፍ ያሉ መሆንአቸውም ዕሙን ነው። [ምክንያቱ ይህ እና ያ ስለሆነ እሚለውን ለጊዜው ወደ ጎን ትተነው ማለቴ ነው።]

በተጨማሪም፤ እስከ ሚያዝያ 2012 ዓ.ም. መገባደጃ ድረስ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኙት እና ሪፖርት የተደረጉት አዲስ የ ኮቪድ–19 ህሙማን፤ ሁሉም በእሚያሰኝ መጠን ከ ውጭ ሃገራት የገቡ መንገደኞች የነበሩ እና ዛሬ መስከረም 2013 ዓ.ም. ላይ ሆነን ግን፤ ሁሉም በእሚያሰኝ መጠን፤ የ ውጭ ሃገር ጉዞ ታሪክ የሌላቸው እንደሆኑም ሰምተን አለ። ይህም እሚነግረን፤ የ ወረርሽኙ ስርጭት ፕራይሜርሊ፤ በኅብረተሰቡ ውስጥ እየተዛመተ መሆኑን ነው። ያ–ም–እንቅልፍ ሊነሳን እሚገባ ሪያልቲ ነው!

ሌላው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰሴፐቲብል የሆኑ ሰዎች ብዛት፤ [ስለ ኢምዩኒቲ ስናወራ] ኢንፌክተድ የሆነው ሰው ቁጥር እዚህ ግባ እሚባል በአለመሆኑ እና ክትባት ገና በአለመገኘቱም ጭምር፤ ናቹራል'ም ሆነ አርቲፊሻል በሆነ መንገድ ኢምዩኒቲ ዴቬሎፕ የአላደረጉ ሰዎች — ማለትም፤ ሰሴፐትብል የሆኑ ሰዎች ብዛት፤ ዛሬም ከ ወደ መቶ–አስር ሚልየን ከፍ እሚለውን ዜጋ ሁሉ ሊያካትት ይችላል ማለት እንደሆነ ልብ ማለቱ፤ ይጠቅማል።

በድምሩ — የ ኸርድ ኢምዩኒቲ ሽፋን ዜሮ ሌቨል ላይ መሆኑን፣ ሰሴፐትብል የሆኑ ሰዎች ብዛት አሁንም ሁሉንም ዜጋ እሚያካትት መሆኑን፣ ኢንፌክትድ የሆኑ ሰዎች ብዛት ፖቴንሽያሊ እየአሻቀበ መምጣቱን፣ ኮንታክት ሬሽዮ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ አይቀሬ መሆኑን እና ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዮ ከአንድ በላይ ለመሆን ምቹ ሁኔታዎች ሁሉ መኖርአቸውን፤ በማናቸውም ዲሲሽን ሜኪንግ ፕሮሴስስ ውስጥ፤ እግንዛቤ ውስጥ ማካተቱ፤ ሊዘነጋ አይገባም።

ያ–ም እንግዲህ፤ ኢትዮጵያን በተመለከተ የ ሳርስ–ኮቭ–2 ቫይራል ፓርቲክል፤ በከፍተኛ መጠን [በ ኤፒደሚክ ደረጃ ማለት ነው] ከሰው–ወደ–ሰው የመተላለፍ አደጋው፤ ሚያዝያ 2012 ዓ.ም. መገባደጃ አካባቢ [ምርጫ መደረግ አይገባም የእሚል ምክረ–ሃሣብ በተሰጠበት ጊዜ] ከነበረችበት፤ ዛሬ መስከረም 2013 ዓ.ም. ላይ — እጅጉን የባሰ አደጋ ላይ የደረሰች መሆንዋን ነው እሚነግረን።

እናም፤ ህዝብ በተፋፈገ ሁኔታ ሊንቀሳቀስባቸው አጋጣሚውን እሚፈጥሩለት የዕለት–ተ–ዕለት ህይወት እንዲጀምር፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን ማላላት እንዲቻል፤ ለ የ[ሰው] ልጆች ህይወት ደንታ እንደሌላቸው ደጋግመው ለአስመሰከሩ አረመኔ ፖለቲከኞች፤ የልብ ልብ እሚሰጥ ምክረ–ሃሣብ መለገስ፤ የሆነ "ናቹራል ኤክስፐሪመንት" ውስጥ መግባት ይሆን እና ምንአልባትም በ እሣት መጫወት እንዳይሆንብን — ከፍተኛ ስጋት አለኝ።

ከ ቦታ ቦታ የተለያየ ተመክሮ እንደ አለ መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ፤ እኔ አከባሪያችሁ አሁን በእምኖርበት ሃገር፤ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን በማላላት ወደ ቅድመ ኮቪድ–19 የ ዕለት–ተ–ዕለት ህይወት ለመመለስ የሞከሩ ክፍለሃገራት — ሳይውል ሳያድር፤ የአዲስ ህሙማን እና የሙታን ቁጥር እጅጉን ሲያሻቅብ በማየታቸው፤ በድንጋጤ ውሳኔአቸውን ለማጠፍ ተገደው እንደነበር ጠቅሼ ማለፍ መልካም ይሆናል ብዬም አስብ አለሁ።

ለ) ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ "ሰርጅ ካፓሲቲ'ዋ" በተሻለ ቁመና ላይ እሚገኝ መሆኑን መስማት ይበል እሚያሰኝ ነው። ቢሆንም፤ የ ሳርስ–ኮቭ–2 ስርጭት አንዴ ማምረር የጀመረ ቀን፤ ከፍተኛ ገቢ የአላቸው ሃገራትን እንኳ እንዴት እንዳንገጫገጨ የአየን በመሆኑ — የእኔዋ [በእራሷ ልጆች፤ ደካማ እንድትሆን የተፈረደባት] ኢትዮጵያ፤ ምን ያህል የተሻለ ቁመና ላይ ደርሳ አለች ቢባልም፤ አይበለው እና የመረረ ቀን የመጣ ግዜ፤ ተፈጥሯል የተባለለት "ሰርጅ ካፓሲቲ" በቂ ሆኖ ለመገኘቱ እርግጠኛ መሆን ይቸግረኛል።

በተጨማሪም፤ ሐ) የኅብረተሰቡ ግንዛቤ የተሻለ ደርጃ ላይ መድረሱን መስማት እጅጉን ጥሩ ሆኖ ሳለ፤ 1. የማስክ እና የሳኒታይዘር ምርት በሃገር ውስጥ በስፋት መኖሩ ብቻውን፣ ኅብረተሰቡ [ከከተማ እስከ ገጠር] በተገቢው መጠን ኮምፕላያንት ሆኖ አለ ማለት ስለአይደለ እና 2. የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን ማላላት ከተጀመረ በኋላ ሊከሰት እሚችለው የ ሳርስ–ኮቭ–2 "ፖቴንሺያል ግሬዲየንት ኦፍ ትራንስሚሽን" ምን ሊመስል እንደእሚችል፤ አስከአሁን ከአለን የአገርቤት ተመክሮ መተንበይ ስለሚቸግር፤ የ መሃል ሃገርን ፕሮፋይል ብቻ [የ አንድ ክለስተር] ፕሮፋይል ብቻ ጥሩ ደረጃ ላይ የአለ ሆኖ መታየትን፤ ከ እሚገባው በላይ ተርጉመን፤ ለ ሃገር–አቀፍ ውሳኔ አጓጉል መተማመኛ አድረገን እንዳንወስደው፤ እሰጋለሁ።

እናም፤ ዛሬ መስከረም 21 2013 ዓ.ም. ላይ ቆሜ፤ የ ኢትዮጵያን ወደ ቅድመ ኮቪድ–19 የ ዕለት–ተ–ዕለት "ህይወት"ዋ ለመመለስ ትችል ዘንድ፤ አቅም በፈቀደ መጠን ሲደረጉ የነበሩትን እና ምን አልባትም እየተደረጉ የአሉትን የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን ለማላላት፤ የተደረሰውን መንግስትዓዊ ውሳኔ፤ ፕሩደንት የሆነ እርምጃ እንደሆነ አድረጌ መውሰድ አይደለም — ይልቁንስ፤ መድገም ይሁንብኝ እና የሆነ "ናቹራል ኤክስፐሪመንት" ውስጥ መግባት ይሆን እና ምንአልባትም <u>በ እሣት መጫወት</u> እንዳይሆንብን — ከፍተኛ ስጋት አለኝ።

ይልቁን እስ — እኔ የተለየ አቋም እይዝ የነበረው፤

ሀ) የቴስቲንግ የሰርቬይላንስ ሽፋንአችን እጅጉን ተስፋፍቶ የአየሁ ቀን፣ ለ) የ ሳርስ–ኮቭ–2'ን ስርጭት በአወጣ ያውጣው ተብሎ፤ ኢንፌክትድ የሆነው ኢንፌክትድ ሆኖ፣ የሞተው ሞቶ፣ የተረፈው [ከ ናቹራል ኢምዩኒቲ ጋር] ተርፎ — ሰሴፕትብል የሆነው የኅብረተሰብ ቁጥር መጠን ከ 100 ፐርሰንት ወደ ሰላሣ ፐርሰንት እና ከእዚያም በታች ዝቅ ብሎ የአየሁ ቀን፣ [ጀስት ፎር ዘ ሬከርድ፤ እኔ ይሄ እንዲሆን በፍፁም አልመኝም!] ሐ) ክትባት ተገኝቶ/ተሰጥቶ፤ የ ኸርድ ኢምዩኒቲ ሽፋንአችን [አርቲፊሺያሊ] ወደ ስድሣ ሰባ ፐርሰንት ገደማ አድጎ የአየሁ ቀን፣ [ይህ ነው የእኔ ምርጫ] እናም፤ መ) ኮንታክት ሬሽዮ እጅጉን ቀንሶ፣ ኢንፌክቲቭ የሆኑ ሰዎች ቁጥር ማሻቀቡን አብቅቶ፣ ሪፕሮዳክቲቭ ሬሽዮ ከአንድ በታች አስተማማኝ በሆነ መጠን ለአራት አምስት ሳምንትአት፤ ሳያመነታ ቁልቁል መውረዱን የአየሁ ቀን ነበር፤

እንደተባለው — ሰርጅ ካፓሲቲ'አችንን ይበልጥ እየአሳደግን እና እየአጎለበትን ወደ ቅድመ ኮቪድ–19 የ ዕለት–ተ–ዕለት "ህይወት"አችን መመለስ መጀመሩን ልንሞክረው እንንችል ዘንድ፤ ይሁንታዬን — ለጎሊናዬ እምፈቅደው።

ያ የደረሰ ቀን — የኢትዮጵያ ልጆች፤

ቢፈልጉ፤ የጎሣ–ፖለቲካን እየአጎለበተ የአለውን ሰሞነኛውን መንግስት ተብዬ ከስልጣን እንዲወርድ ድምፃቸውን ለማሰማት [ሎካል ሃገር–አቀፍም ሆነ ዓለም–አቀፍ] ህዝብዓዊ ሰላምዓዊ ሰልፍ ለመውጣት፣

ቢፈልጉ፤ ስለ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ–ሪሊጀስ ክሊንዚንግ አደጋ ለመወያየት [ሎካል ሃገር–አቀፍም ሆነ ዓለም–አቀፍ] ህዝብዓዊ ስብሰባ ለመካፈል፣

ቢፈልጉ፤ ስለ የሽግግር መንግስት ጠቃሚዕነት ለመመካከር [ሎካል ሃገር–አቀፍም ሆነ ዓለም–አቀፍ] ህዝብዓዊ ስብሰባዎችን ለመጥራት፣

ቢፈልጉ፤ እንዴት አድርገን ሰቆቃችን በተባባሰ ቁጥር፤ "ሃገር ልትፈርስ" ነው ከእሚል ናሬቲቭ ተላቀን — ወደ "መንግስት ሊፈርስ" ነው ወደ እሚል ናሬቲቭ መለወጥ እንደእሚቻል ለመመካከር፣

ቢፈልጉ፤ ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ ሲኒማ ቤት ለመሄድ፣ ስቴድየም ለመግባት፣ ትምህርት ቤት ለመሄድል፣ ይችሉ ዘንድ፤

እኔም አክባሪያችሁ ሙሉ ፈቃዴን ለመስጠት ዝግጁ እንደእምሆን አረጋግጥላችሁ አለሁ። የእዚያ ቀን፣ የእዚያ ሰው ይበለን — አሜን!

ፍትህ፤ በማንነታቸው እየተለዩ የ አለማሰለስ ለ እሚጨፈጨፉ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን! ‖ ፍትህ – ለ ኢትዮጵያዊ የኅሊና/የሃሣብ እስረኞች! ‖ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ዛሬውኑ ይመስረት! ‖ የሕዝብን ስልጣን ለሕዝብ አስረክቡ!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዩ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ --

**የ ሕዝብን ስልጣን ለ ሕዝብ አስረክቡ!**

# ፍትህ–አጐናጻፊ ሃይል

ህዳር ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ኖቬምበር 2020

**አዳራሽ:** አንድ አባባል አለ — የፈረደበት አይንስታይን ተናግሮት አለ እሚባልለት። እጠቅስ አለሁ...... “ፕላኔት ምድርን ከጥፋት ለማዳን የ አንዷት ሰዓት ቅጽበት ብቻ ቢሰጠኝ፤ ሃምሳ–ዘጠኝ ደቂቃዎቹን መሠረትዓዊ ችግሯ ምን እንደሆነ ለማወቅ፡ የቀረችዋን አንዷት ደቂቃ ደሞ ለማስወገድ፡ እጠቀምባቸው ነበር” ብሎ አለ ነው እሚባለው። ትርጉም የ እራሴ።

እናም... የ አዳራሽ አብላጫ ትኩረት ኢትዮጵያ ስለሆነች፤ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን — እንደ አንድ ያገባኛል ባይ፤ 59–ደቂቃዎችን በ እኔ ሂሣብ አወራርጀ፤ ጥቅል መሠረትዓዊ ችግሯ የ አልኩትን ትኩረት ይስጥበት ዘንድ፡ በተደጋጋሚ ማጋራትን መርጨ አለሁ። አዎ፤ ኢትዮጵያ — መሠረትዓዊ ችግሯ በጥቅሉ [ጎሲና ቢሶች የቀፈቀፉት፡ ጭልጥ የአለ ቅጥፈት ላይ የተመሠረተ የጎሣ–ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት፣ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩይ ፈደራሊዝም፣ ተቋማት ሁሉ በገዥው ፓርቲ እና በግለሰቦች ስለ የ እሚነዱ እና አነእኝህን ሁሉ ተከትሎ ለ 30–ዓመታት ያህል የ አለማቋረጥ እየተከሠተ የ አለው፤ ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ ጀኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፣ “መጤ” በመባል ለ መፈናቀል፣ ለበሽታ፣ ለረሃብ፣ ለአሰቃቂ የስነልቦና ጫና መጋለጥ፣ ኢትዮጵያን በሁለዕንተንዓዊ መልኩ የማሠቃየት የተቀናጀ ዘመቻ እና አምባገነኑ መንግሥት ተብዬ የችግሯ ሁሉ ፈጣሪ ቀቃፊ እና አድራጊ የመሆኑ ዕውነታ] ነው። ሌላው ሁሉ ዕዳው ገብስ ነው!

ማድረግ ይገባን አለ [ይገባን ነበር ማለቱ ሳይሻል አይቀርም] ብዬ የ እማምነውም፤ አሸናፊ የመሆን አቅም የአለው ፍትህ–አጐናጻፊ ኢትዮጵያዊ ሃይል ለመገንባት፤ ሳይውል ሳያድር በጋራ በወል በአንድዕነት በህብረት በቅንጅት በአብሮዕነት በቀናዕነት በተግባር እና በሥልጡን አግባብ ተሰባስበን፤ [አንዷን ሰዓት] ሙሉ የኢትዮጵያን መሠረትዓዊ ችግር ለማስወገድ ልንጠቀምባት የ እሚገባን መሆኑን አምነን መቀበልን ነው።

መሠረትዓዊ ችግሯ — ጥልቅ፣ ሰፊ፣ ውስብስብ ስለ ሆነ እና ለማስወገድ በእሚደረገው ፈታኝ የሐሣብ ግንባታ ጉዞ አዳራሽ መካፈልን ስለመረጠችም፤ እንደ አብዛኛዎቹ፤ የአሁኑ ትውልድ የኢትዮጵያን ፖለቲካ እሚያስተናግድባቸው ፍትህ–አጐናጻፊ ፅንሰ–ሐሣቦች ሁሉ፤ በተለይም ዋና ዋናዎቹ — ሌላ ማንም ሳይሆን፤ ተኪ የለሽ ኮከቦቹ የ ያ–ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ሰማዕታት፤ ክቡር ህይወትአቸውን የከፈሉባቸው እና —እጅጉን በተሻለ አገላለፅ፤ በአንጋፋው ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ፡ ከ 1960’ዎቹ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ፤ በ አስተማሪዕነት እና በ የትግል መሪዕነት፤ በኢትዮጵያዊ ፅናት እሚያስተጋባቸው ቁልፍ ሐሣቦችን — አዳራሽ፤ ዛሬም ቢሆን ለኢትዮጵያ የ ፖለቲካ ቀውስ ማስወገጃዕነት አማራጭ የሌላቸው ፍቱን መድሃኒቶች መሆናቸውን ሙሉ በሙሉ እንደ እምታምንባቸው እና ንፁህ ወገንዓዊዕነት እንደ እሚሰማትም ጭምር ለመግለፅ፤ እንደ የ እሚከተለው ማስፈርን መርጣ አለች።

ቁልፍ ሐሣቦች፤

ሀ) ለ የ አለፉት 30–ዓመታት በሥልጣን ላይ የ አለው መንግሥት ተብዬ፤ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ የ ሕዝብን ሥልጣን ለ ሕዝብ ማስረከብ የ አለበት መሆኑን እና ከፖለቲካው መድረክ እራሱን ማግለል አልያም በሕግ መገደብ የአለበት መሆኑን አምኖ መቀበል። ለ) ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት መመሥረት እንደ አለበት እና በቴክኖክራቶች የእሚሞላ ፈርጀ-ብዙ ታስክ ፎርስ ተዋቅሮ፡ ለ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥቱ እሚያስፈልገውን ሙያዊ ድጋፍ ሊሰጥ እንደ እሚገባ መቀበል። ሐ) ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ሥልጡን ኢትዮጵያዊ ሕገ-መንግሥት መቀረፅ እንደ አለበት ማማን። መ) እንደ አዲስ በእሚቀረፀው ኢትዮጵያዊ ሕገ-መንግሥት ውስጥ አለመረሳቱን ብቻ ሳይሆን፤ ጐልቶ መታየቱንም ጭምር እርግጠኛ ልንሆን ከእሚገባቸው ጉዳይዎች መሃከል፤ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-አደረጃጀት በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩዩ ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ማድረግን – በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ሥርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ማካተትን፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ቋንቋዎቹ ወግ ባህሎቹ ሰውዓዊ መብቶቹ ተከብረው፡ በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት በ አሻው ቦታ ተዘዋውሮ — የመኖር፣ የፈለገውን የማግባት የመውለድ የመክበድ፣ ሃብት ንብረት የማፍራት እና የመምረጥ የመመረጥ መብቶቹ ሁሉ ሳይሸራረፉ ተከብረው፤ ምሉዕ መለኮትዓዊ ሥልጡን ህይወት እሚጐናፀፍባት ኢትዮጵያ እንድትኖረን እርግጠኞች መሆን። ብሎም ሠ) ሰው በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ኢትዮጵያን የመጠበቅ እና ኢትዮጵያዊያንን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት እንደ የ እሚገባን — ለ አመኔታችን በኢትዮጵያዊ ጨዋዕነት — ከልብአችን ቃል–ኪዳን መግባት።

ከ የጋራ የወል የሐሣቦች ፍጭት በኋላ፤ ነጥረው እሚወጡ ቁልፍ ሐሣቦቻችን ዕውን ሆነው ለማየት እንችል ዘንድ እም፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘርፈ–ብዙ ተወካዮችን፣ በ አገር ቤት እና ከ አገር ቤት ውጭ የ አሉ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን፣ ኢትዮጵያዊ የሙያ ማሕበራት ተወካዮችን እና ኢትዮጵያዊ የሃይማኖት መሪዎችን ሁሉ፤ አንድአችንም ሳንገለል [አልፋ’ዕነትአችንን፣ ሰው’ዕነትአችንን፣ ረቂቅ’ዕነትአችንን፣ ህብር’ዕነትአችንን፣ አንድ’ዕነትአችንን፣ ጠንካራ’ዕነትአችንን፣ ዐዋቂ’ዕነትአችንን እና ውብ’ዕነትአችንን] ከጐንአችን በማሰለፍ፤ በ ፍትህ–አጐናጻፊ ኢትዮጵያዊ ጉባኤ ፈታኙን ጉዞአችንን ዛሬውኑ መጀመር፤ የግድ ነው። ሌላ አማራጭ የለም!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

ጐበዝ....... አዘውትሬ፤ ለመሆኑ እንዴት ናችሁ እምለው፡ እንዲያው ሰላምታ ለማቅረብ ያህል ብቻ አይደለም። በልቤ ውስጥ የአለውን ሁሉ እምታዩልኝ እምትረዱልኝ እየመሰለኝ እና እኔንም፤ ውስጥአችሁ የአለሁ ያህል እንዲሰማኝ ስለእሚያግዘኝ ጭምርም እንጅ።

አሁን አሁን እማ፤ ሁሌም ከኀሊናዬ ውስጥ ከእማትጠፋዋ በ መንግሥት ተብዬው አፈና እየተጐሳቆለች የአለችዋ ኢትዮጵያ — የሃዘን፣ የመከዳት፣ የመጠቃት፣ አለሁ ባይ ፍትህ–አጐናጻፊ ወገን የማጣት፣ የፅናት፣ የቆራጥዕነት እና የተስፋ ገፅታ ህብር ፊታችሁ ላይ ተጋርዶ እየአለም፤ እናንተ ግን እንደተለመደው ሰብሰብ ብላችሁ፤ "አ–ለ–ን!" የ እሚለው የጀግናዕነት የተስፋሙሉዕነት ምላሽአችሁ — የአምባገነኖቹ አፈና እና አረመኔዕነት ሳይገድበው፤ በ ሺህ–ማይልስ እሚቆጠረውን ርቀት ሳይታክት በመጓዝ እየተንጐደጐደ፤ እዚህ የተቀመጥኩባት የንባብ ክፍሌ ድረስ ዘልቆ፤ ጥርት ብሎ ስለ እሚሰማኝ — [ለመሆኑ እንዴት ናችሁ በአልኩ ቁጥር] ከ የወገንዓዊዕነት ሲቃ ጋር ትንቅንቅ እገጥም እና፤ አይበገሬ ሪዞልቭ'አችሁን እየአሰብኩ እፅናና አለሁ።

ይህ–እን ክፉ ፈተና በህብረት፣ በአንድዕነት እና በፅናት እንድንወጣው፤ የልብአችንን መጨዋወት መድሃኒትዕነት አለው ብዬ በማመን፤ የእኔን ድርሻ በእየ ወሩ በእምትወጣው ብሎግ ስለ እማጋራ፤ እንደ እምትከታተሏት ከ ጓዶቻችሁ፣ ከ ጓደኞቻችሁ፣ ከ ወዳጆቻችሁ እና ከ ዘመዶቻችሁ ጋርም፤ በአመዛኙ የ ኮፊ–ቴብል ኮንቨርሴሽን ስታርተር በማድረግ እንደ እምትጠቀሙባት ዕምነቴ ነው።

የ ዛሬው መልዕክቴንም ታዲያ፤ ከ እዚህ በታች በ ሦስት ክፍሎች አቀናጅቼ በ ቅደም ተከተል እንደ እሚከተለው አቀርብ አለሁ። በ መጀመሪያ፤ የወቅቱን የኢትዮጵያን ነገር በጨረፍታ ነካ አድርጌ አልፍ እና በ መቀጠል፤ የ ኮቪድ-19'ን ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ወርሃዊ ወፍ–በረር ዳሰሳ'ዬን አጋርቼ ሳበቃ — እንደ ማጠቃለያ፤ መዘንጋት የለባቸውም እምላቸውን ነጥቦች አፅንኦት በመስጠት፤ አበቃ አለሁ።

እናም፤ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።

ክፍል አንድ — የ ኢትዮጵያ ነገር።

በስልጡኑ ዓለም፤ የአንድ ሃገር አስተዳደርዓዊ መዋቅር ጉልላት ወይም የአንድ ሃገር ባለቤት ወይም የአንድ ሃገር ቀዳማይ መሪ — ሕዝብ ነው። ሕዝብ፤ እንደ የዜጐች ህብር፣ የዜጐች

አንድዕነት፣ የዜጐች ሉዓላዊዕነት መገላጫ፤ ዕምቅ እስትንፋስ። በ አመዛኙ!

በሌላ በኩል፤ መንግሥት [ጤናማ መንግሥት ተብሎ ይነበብልኝ] — በ ሕግ እና በፍትህዓዊዕነት ጥላ ግዳጅ ስር፤ ከሕዝብ በታች ሆኖ ማኅበረሰብዓዊ ህይወትን ለመምራት፡ በሕዝብ እሚወከል/እሚቀጠር አገልጋይ መዋቅር፣ አገልጋይ ጣራ ወይም አገልጋይ አካል ነው።

ይ–ኼ የ ሕዝብ እና የ መንግሥት ትስስር በጥቂትም እንኳን ከተዛነፈ፤ አምባገነንዕነት ይሰፍናል። አምባገነንዕነት እሚለው ቃል ወይም ሃረግ፤ መንግሥትን በተመለከተ ጥቅም ላይ ሲውል — መንግሥት፤ የሕዝብ ተወካይዕነቱን፣ ተቀጣሪዕነቱን እና አገልጋይዕነቱን ረስቶ፤ ለ ሕግ እና ለ ፍትህዓዊዕነት ተገዥ መሆኑን አቁሞ፤ ሕዝብን እና ሃገርን አጥፊ በሆነ መልኩ በማን አለብኝዕነት፤ እንደ ወራሪ ጠላት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ነው [በትክክል] እሚገልፀው።

የ አንድ ሥልጡን ሃገር መንግሥት [የህልውናው መሠረትዓዊ ተልዕኮ] የሃገርን ሉዐላዊዕነት መጠበቅ፣ የዜጐችን ጤና ሠላም እና መረጋጋት ማስፈን፣ የዜጐችን መለኮትዓዊ ሰውዓዊ መብቶችን ማክበር መጠበቅ፣ ሁለዕንተንዓዊ ዕድገትን መምራት እንዲሁም ከማናቸውም ሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ መታደግ ነው። በዋናዕነት!

ተላይ የጠቀስኳቸው የ መንግሥት የህልውናው መሠረትዓዊ ተልዕኮ ዋና ዋና አትሪቢውትስ፤ በአንዱም ሆነ በሌላው መልኩ የተያያዙ የተዛመዱ ናቸው። ለዛሬ ግን፤ "ሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ" በ እሚሉት ላይ በተለየ መልኩ በማተኮር፤ ትንሽ እምለውን ልበል።

የሰው ሰራሽ ጥፋትንም ሆነ የተፈጥሮ አደጋን በተመለከተም — በ የዛሬው የተለየ ትኩረቴ፤

ጀኖሳይድን፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግን፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግን እና መፈናቀልን፤ ከ ሰው ሰራሽ ጥፋት አኳያ — በተጨማሪም፤ ጐጂ ህዋስዐትን ወይም ጐጂ ፓርቲክልስ'ን እየአሰብኩ፤ የ አንበጣ መንጋን እና ሳርስ–ኮቭ–2'ን፤ ከ የተፈጥሮ አደጋ አኳያ በማካተት — በህይወት፣ በንብረት እና በተፈጥሮ በእራሷ ላይ እሚደርስ ዕልቂት ጥፋት አዳጋ ከ ኅሊናዬ አድማስ ሳይውጡ፤ ከ የ መንግሥት የ ህልውናው መሠረትዓዊ ተልዕኮ አግባበ–ነገር አንጻር እየአማተርኩ ለመዳሰስ እሞክር አለሁ። ላይ ላዩን፤ ቢሆንም ቅሉ።

ያ–ው፤ ማኅበረሰብዓዊ ህይወት እየአደገ እና ውስብስብ እየሆነ በመጣ ቁጥር፤ የአንድ ሥልጡን ሃገር መንግሥት፤ የህልውናው መሠረትዓዊ ተልዕኮ እየአደገ እና ውስብስብ እየሆነ መምጣቱም አይቀሬ ነው። እናም፤ ዛሬ የ እየ ሃገራቱ መንግሥታት ዜጐቻቸውን ከማናቸዉም የሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ ከ የተፈጥሮ አደጋ መጠበቅን፤ በ ሪል ታይም በ ኤሌክትሮን ማይክሮስኮፕ እሚፈተሽ ቀዳሚ ስራቸው፣ ሃላፊዕነትአቸው እና ግዴታቸው መሆኑን በግልፅ ይገነዛባሉ፣ ሬቨረንትሊ "ይተገብራሉም" — አምባገነንዕነትን ከ እሚመረጡት በስተቀር!

መንግሥት — የ ህልውናው መሠረትዓዊ ተልዕኮን በአግባቡ ለመወጣት፤ የሰው ሰራሽ ጥፋትንም ሆነ የተፈጥሮ አደጋን በተመለከተ ሊያደርግ ከእሚገባቸው ዝግጅቶች አኳያ፤ እንደ ስታንደርድ እሚቆጠሩ ክንዋኔዎች አሉ። በከፊል ልጥቀስ.... ሀ) ስለ ሃገሩ የሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ ተፈጥሮ አደጋ ፕሮፋይል በቂ እና ቀጣይዕነት የአለው ዕውቀት ማዳበር፣ ለ) የሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ ላይ እሚሰሩ ብቁ እና ዘመንዓዊ ተቋምአትን መገንባት፣ ሐ) በ ሪል–ታይም፤ የሰው ሰራሽ ጥፋትንም ሆነ የተፈጥሮ አደጋን ክትትል ትንበያ እና ማስጠንቀቂያ ተግባራትን ማከናወን፣ መ) በአጭር እና በረዥም ጊዜ ዕቅድ ስር በቂ የመከላከል እና የመልሶ ማቋቋሚያ ዝግጅት መኖሩን እና ችግሮቹ ዳግም እንደማይከሰቱ ተደርገው መወገዳቸውን እርግጠኛ መሆን እሚያስችል ዝግጅት ማድረግ፣ ሠ) የ ሃገር እና የ ሌሎች ሃገራት የ የሰው ሰራሽ ጥፋትንም ሆነ የ ተፈጥሮ አደጋን የመከላከል ትብብር እና ቅንጅት መፍጠር እና ማጐልበት፤ እንዲሁም ረ) እነኝህን ሁሉ ለማሳለጥ ይቻል

ዘንድ አስተማማኝ የሆነ በጀት ማዘጋጀት ሌት–ተ–ቀን ተግቶ መስራት ።

አንድ መንግሥት ለ መሠረትዓዊ ተልዕኮው ሁለዕንተንዓዊ ስኬታማዕነት፤ ሌት–ተ–ቀን ተግቶ መስራት የ አለበት፤ እንዲያው ቸር ስለሆነ ሳይሆን፤ የ ሕዝብ የዕምነት ውክልና "ስለተሰጠው" — ብሎም የተቀጠረበት ስራው ሃልፊዕነቱ እና ግዴታው በመሆኑ ነው። አምባገነንዕነትን የመረጡ መንግሥታት ግና፤ ይ–ህ አይገባቸውም፣ ሊገባቸውም አይፈልጉም። በፍፁም!

ለ እዚያም ነው፤ በ አምባገነኖች የ እሚመሩ ሃገራት — ዘግናኝ ሰው ሰራሽ ጥፋቶችም ሆኑ አስከፊ የ ተፈጥሮ አደጋዎች በተደጋጋሚ እየተከሰቱ መሆናቸው እየታወቀ፤ ዘላቂ መፍትሄ የ እማያገኙበት ምክንያት።

በዓለምአችን፤ ሕዝብን ከ የ ሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ ከ የ ተፈጥሮ አደጋ መጠበቅን አካትቶ፤ ሃገርን እንደ ሃገር ለማንቀሳቀስ እሚያስፈልገውን በጀት፤ ከ እየሃገራቱ አንጡራ ሃብት፣ በ ብድር፣ በ ድጋፍ፣ በ ችሮታ ወይም በ ልመና መልክ በእሚገኝ ንዋይ ሲሸፈን ማየት አዲስ ነገር አይደለም።

መንግሥታት በእየ ሃገርአቸው ለ እሚያከናውኑአቸው ማናቸውም ፕሮጀክቶች፤ ከእየ ሃገራቱ ከ እሚገኘው አንጡራ ሃብት ከ[የተፈጥሮ ሃብት፣ ጥሪት ቅርስ፣ ግብር፣ የንግድ ገቢ] በስተቀር — በብድር፣ በድጋፍ፣ በችሮታም ሆነ በልመና እሚገኝ ማናቸውም በጀት፤ በአንዱም ሆነ በሌላው መልኩ [በአመዛኙ በወለድ] — በህይወት፣ በጥሬ ገንዘብ፣ በጉልበት፣ በተዘዋዋሪ ቅኝ አገዛዝ መልክ፤ አልያም በ አሉታዊ የስነልቦና ጫና፤ ሕዝብ እሚከፍለው ከትውልድ ትውልድ እሚተላለፍ የሃገር [ዕዳ] ነው።

ሜክ ኖ ምስቴክ — ዜር ኢዝ ኖ ሰች ቲንግ አዝ ኤ ፍሪ ላንች፤ ይላሉ እኔ አካባቢ የአሉ ሰዎች።

ሰው ሰራሽ ጥፋት — የጎሣ–ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት እና በ ቋንቋ በ ጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩዮ ፌደራሊዝም እየአስከተለ የአለውን አራዊትዓዊ ፍጅት እና አረመኔዓዊ ጭፍጨፋን ለመከላከል፣ መልሶ ለማቋቋም እና መሠረትዓዊ ችግሩን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ — አሁን በሥልጣን ላይ የአለው ገዥው አካል፤ የህልውናው መሠረትዓዊ ተልዕኮ መሆኑን ተገንዝቦ፤ ግዴታውን በአግባቡ አለመወጣቱ እና ሃገርን ለ ፍርሰት፣ ሕዝብን ለ ዕልቂት አጋልጦ መስጠቱን ብቻ ሳይሆን፤ የችግሮቹ ሁሉ ፈጣሪ ቀፍቃፊ አድራጊም መሆኑን — ዓለም የአወቀው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው።

የ ተፈጥሮ አደጋ — ገዥው አካል፤ የ ሳርስ–ኮቭ–2'ንም ሆነ የ አንበጣ መንጋ የመከሰትን ስጋት፤ በ ያገባኛል ባይ ዜጐች ሲነገረው እና ግዴታውን በአለመወጣቱም በአግባቡ ሲገሠጽ፤ ከማመስገን እና ፈጥኖ ስራውን በመስራት፣ ግዴታውን በአግባቡ ከመወጣት ይልቅ — "መንግሥት ኮሮናን አልፈጠረም፣ መንግሥት አንበጣን አልፈጠረም" የእሚል ዲፌንሲቭ ማይንድሴት ውስጥ በመዘፈቅ፤ ከዜጐች ጋር እርባና ቢስ አተካራ ሲገጥምም ታይቷል። ግዴታውን በአለመወጣቱም፤ ዜጐች ለበሽታ፣ ለሞት፣ ለረሃብ፣ ለስደት እና ለ የ ስነልቦና ጥቃት እንዲጋለጡ ምክንያት ሆኗል።

በ የጎሣ–ፖለቲካ፣ የአክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት እና ዕኩዮ ፌደራሊዝም እንዲሁም በ ሳርስ–ኮቭ–2'ም ሆነ በ አንበጣ መንጋ ሳቢያ [በየትኛውም ዓይነት ሰው ሰራሽ ጥፋትም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ፤ ፎር ዛት ማተር] በንፁሃን ኢትዮጵያዊያን ላይ — ፐቲኩለርሊ በ አማራ እና በ የ ኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶስ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ላይ አለማቋረጥ እየደረሰ የአለውን ዕልቂት ሰቆቃ፤ መፈናቀል፣ ለ በሽታ እና ለ ረሃብ መጋለጥን — መከላከል፣ መልሶ ማቋቋም ብሎም የኢትዮጵያን መሠረትዓዊ ችግር ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ አለመፈለጉ አለመቻሉ ብቻ፤ [ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን] ዛሬ በስልጣን ላይ የአለው መንግሥት ተብዬን፤ በ ኢ–ሰውዓዊዕነት እና በ ከፍተኛ ሃገርዓዊ ወንጀሎች ቀዳሚ ተጠያቂ ያደርገዋል።

ለምን ቢሉ፤ [መንግሥት] የሕዝብ አመኔታ ውክልናን ፈቅዶ የ እሚቀበልበት አልያም የሕዝብ ተቀጣሪዕነቱን ፈቅዶ የ እሚቀበልበት ፕራይመሪ ፐርፐዝ፤ ሃገርን እና ሕዝብን [የአለምንም ሰበባ ሰበብ] ከ እንደ እነዚያ የ አሉ ጥቃቶች ዕልቂቶች ጥፋቶች እና አደጋዎች ለመጠበቅ፣ ለመከላከል፣ መልሶ ለማቋቋም እና መሠረትዓዊ ችግሮቿን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ ነው እና!

ይ–ህ እንን ተልዕኮ በአግባቡ መወጣት የአልቻለ ማንአቸውም "መንግሥት" ተብዬ፤ ሌላው ቢቀር ሥልጡን መሆኑን ለማስመከር ሲል ብቻ፤ ሌላ ኬፐብል የሆነ መንግሥት እሚተካበትን መንገድ አመቻችቶ፤ ሳይውል ሳያድር የመንግሥትዕነቱን ቦታ መልቀቅ ይኖርበታል። የትውልድን ጊዜ ማባከን፤ ኋላቀርዕነት ነው እና! ሃገርን እንደ የግል ንብረት በመቆጣር ሥልጣን አልለቅም በእሚል፤ የባሰ ዕልቂት ጥፋት እና አደጋ እየተከሰተ እንዲቀጥል ማድረግም፤ የለየለት ድንቁርና ነው እና!


ገዥው አካል፤ ከ አፍ የወደቀች ጥሬ እምታክል [ሰው]ዓዊዕነት ውስጡ ቢኖረው ኖሮ፤

ኤርትራን ማስገንጠሉን፣ የባሕር በሮቻችንን አሳልፎ መስጠቱን፤ ፀረ–ኢትዮጵያ ሕገ–መንግሥት ተግባርዓዊ ማድረጉን፣ አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀቶች እና ዕኩዮ ፌደራሊዝም እየአስከተሉ የአለውን ዕልቂት እና ሰቆቃ፣ በ ሳርስ–ኮቭ–2'ም ሆነ በ አንበጣው መንጋ ሳቢያ ጭምር የደረሰውን እና እየደረሰ የአለውን ለበሽታ እና ለረሃብ የመጋለጥን ጥፋት እና አደጋ — ኢሊትሬትሊ ዲፌንሲቭ በመሆን፤ በ እየ ናኖ ሰከንዱ ከድጡ ወደ ማጡ ከመዘፈቅ ይልቅ — መፍትሄው፤ አዲስ ሥልጡን ሕገ–መንግሥት ቀርፆ ተገቢውን የዕርምት ዕርምጃዎች በመውሰድ፤ በ ዕኩልዕነት በአብሮዕነት መኖሩ አማራጭ የሌለው ፍቱን መድሃኒት መሆኑን፤ በቀጣፊ ትርክቶቹ የተደናቆረውን መንጋ ለማስተማር፤ እንደ ሊያመልጠው እማይገባ [ቲችኤብል ሞመንት] ወስዶ፤ ሊጠቀምበት በተገባ ነበር።

ክፍል ሁለት — የ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ወርሃዊ ወፍ–በረር ዳሰሳ።

ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት ከ 12/31/2019 እስከ 10/31/2020 ድረስ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት አዲስ የ ሳርስ–ኮቭ–2 ፓርቲክል [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ብዛት፤ በ ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ድምሩ – ወደ 45.7 ሚልየን ደርሷል። ከእነዚያም ውስጥ 2.6 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለም ሪፖርት ተደርጓል።

በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረጉት [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር — አሁን በአለበት ከፍተኛ ደረጃ አየ አደገ መሄድ መቀጠሉ፤ ቴስት የተደረጉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄድን እንደምክንያት መጥቀስ ከእሚቻልበት ኮምፈርት ዞን የአለፈ በሆነ መልኩ፣ የመከላከል–የመቆጣጠር እርምጃዎች እየላሉ መሄድአቸውን እና በኅብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት እና የመሰላቸት ማይንድሴት እየጐለበተ መምጣቱን ጠቋሚ ሊሆኑ እንደ እሚችሉ ልብ ማለቱ፤ ተገቢ ነው። እንደ አዲስ ሪፖርት እሚደረጉ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር ብዛት በ ኤፕሪል 2020 ሪፖርት ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር፤ በ ኦክቶበር 2020 ሪፖርት የተደረገው በ [408] ፐርሰንት አብላጫዕነት እንደነበረውም ታይቷል።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኦክቶበር 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጐም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።


እጆችአችንን በአግባቡ እናፅዳ | የአካል እርቀትአችንን እንጠብቅ | አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን | አዲስ የአኗኗር ዘይቤን እንላመድ

ወረድ ብላችሁ እምታዩት ሰንጠረዥ ደሞ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ፤ ከ ዲሴምበር 2019 እስከ ማርች 2020 ድረስ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ በ እየ ወሩ ሪፖርት የተደረጉትን፣ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ብዛት — የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ቁጥር፣ የ ሙታን ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ቁጥርን እና ወረርሽኙ ከተከሰተ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ፤ ሙታን የ እየ ወሩ በጥቅል በፐርሰንት ሲሰሉ የተገኙን ቁጥሮች የያዘው ነው።

ኮቪድ-19 | ፐላኔት ምድር | 12/31/2019 – 10/31/2020

| ግዜያት (በወራት) | የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር | የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ቁጥር | ጥቅል/ኪሙሌቲቭ የሙታን ቁጥር | ጥቅል /ኪሙሌቲቭ የ ሙታን ብዛት በ ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| ከ ድሴምበር 2019 እስከ - ማርች 2020 | 777,798 | 777,798 | 37,272 | 4.79 |
| በ ኤፕሪል 2020 | 2,353,002 | 3,130,800 | 227,051 | 7.25 |
| በ ሜይ 2020 | 2,897,335 | 6,028,135 | 368,944 | 6.12 |
| በ ጁን 2020 | 4,244,866 | 10,273,001 | 505,295 | 4.92 |
| በ ጁላይ 2020 | 7,023,302 | 17,296,303 | 673,290 | 3.89 |
| በ ኦገስት 2020 | 7,955,031 | 25,251,334 | 846,841 | 3.35 |
| በ ሴፕቴምበር 2020 | 8,463,261 | 33,714,595 | 1,008,932 | 2.99 |
| በ ኦክቶበር 2020 | 11,953,185 | 45,667,780 | 1,189,499 | 2.60 |

ህይወታቸውን የእሚያጡ ህሙማን መጠን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ ኤፕሪል 30/2020 ላይ ወደ ሰባት ፐርሰንት የነበረው፤ ዛሬ ኦክቶበር 31/2020 ላይ 2.60 ፐርሰንት ስለ መሆኑ፤ ብዙ ምክንያቶች መጠቃቀስ ይቻላል። ለምሳሌም ያህል ሀ) ቴስት የእሚደረጉት ሰዎች ቁጥር እጅጉን መጨመር ለ) አንድ ሁለት ሊረዱ የቻሉ መድሃኒቶችን መጠቀምን ጨምሮ፤ የተሻለ ፔሽንት ማኔጅመንት እየጐለበተ ስለመጣ እና ሐ) የ ሳርስ-ኮቭ-2 ፓርቲክል በፍጥነት ሚውቴት የማድረግ ባህሪው፤ በአንድ በኩል ክትባት ለመስራት የእሚደረገውን ጥረት እንደተፈታተነው ዕሙን ቢሆንም ቅሉ፤ ምን አልባትም የከፋ ጉዳት እማያደርሱ ሚውቴሽንስ ተፈጥረው ሊሆን በመቻሉም ጭምር ሊሆን እንደ የ እሚችል መጥቀሱ፤ ለአነበባችሁ ሰዎች እንደ የውውይት መንደርደሪያ ይሆን ዘንድ፤ በቂ ይመስለኛል።





ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ 7–ቀናት አማካይ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኦክቶበር 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጐም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን (ዩኤስኤ እና ካናዳ)፣ ደቡብ እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።

ከፍ ብላችሁ የአያችሁት ዝግብ ደሞ፤ እንደ አዲስ ሪፖርት እሚደረጉት የ አዲስ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች፤ የእየ አህጉራቱ የ እየ 7–ቀናት ወራጅ አማካይ ቁጥርን በተመለከተ ነው። አሜሪካ፤ በጁላይ መጨረሻ አካባቢ ጀምራ እስከ ሴፕቴምበር የመጀመሪያው ሳምንት አካባቢ ድረስ፤ የመቀነስ አዝማሚያዎችን አሳይታ ስታበቃ፤ አክቶበር ሙሉውን ግን ሲአገረሸበት ሰነባብቷል።

በሌላው ጐን ደሞ፤ ኤዥያ ሪፖርት እየአደረገች የአለችው የ አዲስ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር፤ ለብዙ ወራት እየአሻቀበ ከከረመ በኋላ፤ ከ ሴፕቴምበር አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ የመቀነስ አዝሚያ እየሳየ መሆኑ፤ አበረታች ነው።


ጎበዝ፤ የ አውሮጳ ነገር አሳሳቢ ሆኗል። አገስት ላይ የአገረሸበት፤ ይሄው እና አስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ አስፈሪ በሆነ መጠን እየአሻቀበ መሆኑን ማየት ይቻላል። ፈረንሳይ፣ ጀርመኒ ምንአልባትም ብሪታንያ ወደ ሌላ ሎክዳውን ለመመለስ እንደተገደዱ — እየተነገረ ነው።

አፍሪቃ ሪፖርት እምታደርጋቸው የ አዲስ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር፤ ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ቢሆንም፤ ከ ጁላይ መገባደጃ ጀምሮ እስከ ሴፕቴምበር መጨረሻ ድረስ እየቀነሰ ከመጣ በኋላ፤ አክቶበር ላይ በመጠኑም ቢሆን የመጨመር አዝማሚያ ታይቶበታል።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት አክቶበር 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጐም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እምታደርጋቸው የ አዲስ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር፤ ሪሌቲቭሊ አነስተኛ ነው። ቢሆንም፤ ከ መስከረም መጨረሻ ጀምሮ እስከ አክቶበር የመጀመሪያው ሳምንት አካባቢ ድረስ በጥቂቱም ቢሆን ከፍ እየአለ ከመጣ በኋላ፤ በመቀጠል ግን እስከ አክቶበር መጨረሻ ድረስ፤ እየቀነሰ እንደ አለ ማየት ይቻላል። ያ–ም አበረታታች ነው። በ አጠቃላይ፤ እንደ ሳርስ–ኮቭ–2 የአለ [ፕሮፓጌተድ] ኤፒደሚክ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ ዝቅ የማለት ባሕሪይ ማንፀባርቁ የ እሚጠበቅ ነው።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት አክቶበር 31/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የ መሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ'ም ጭምር፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅም ይችል ይሆናል እና – አተረጓጐም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ክፍል ሦስት — እንደ ማጠቃለያ፤

ኢትዮጵያ፤ በደርሰባት የፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ — ዘግናኝ ችግር ላይ ነች። አዎ፤ እጅጉን የዘግናኝም ዘግናኝ ችግር ላይ ነች!

የ ችግሯ [ዘግናኝዕነት]፤ የጎሣ ማንዕነት እና ሃይማኖት ላይ መሠረት የአደረገ የለየለት ሀ) ጄኖሳይድ ለ) ኮኧርሲቭ ወይም ፎርስድ ኮሌክቲቭ ኢቪክሽን [ከተወለዱበት ቀዬ መንደር እና ከ የ ኖሩበት ሃገርአቸው፤ በ ማንዕነትአቸው ምክንያት "መጤ" እየተባሉ እንዲሸሹ እንዲባረሩ መገደድ] ሐ) ወረራ ዘረፋ እና ጭልጥ የአለ አፓርታይድዕነት እና መ) የ ምሥራቅ አፍሪቃ ቀጠናን መገንባት በእሚል የማነሁለያ ናሬቲቭ፤ ኢትዮጵያን እና ኢዮጵያዊዕነትን የማደብዘዝ እና የማጥፋት የተቀነባበረ ዘመቻ እየተተገበረ በ መሆኑ፣

የ ችግሯ [እጅግ ዘግናኝዕነት] ደሞ፤ የ ችግሯ ቀፍቃፊ ፈጣሪ አድራጊ ተዋንያኑ የሕዝብ የ ውክልና "አመኔታ"'ውን መዋቅር፣ የመንግሥትዕነቱን ቦታ በጉልበት ግግም ብለው የያዘው እራሱ የ ገዥው አካል በ መሆኑ እና

ችግሯን [እጅጉን የዘግናኝም ዘግናኝዕነት] ደረጃ ላይ የአደረሰው ደሞ፤ አለሁ ባይ ዋስ ጠበቃ እና ፍትህ–አጐናጻፊ ወገን የማጣትዋ ዕውነታ ነው።

በእዚህ በአለፈው ሳምንት ውስጥ ታዲያ፤ ተላይ የጠቀስኩትን ስነሪዮ ሊቀይር የከጀለ በእሚመስል መልኩ፤[ገዥው አካል ሕገ–መንግሥት ተብዬው ይፈቅዳል እየአለ እሚኩራራበትን] ሰብዓዊ መብቶች በመጠቀም — አላባራ የአለውን የጎሣ ማንዕነት እና ሃይማኖት ላይ መሠረት የአደረገውን የንፁሃን ኢትዮጵያዊያን ዕልቂት፣ መፈናቀል እና የሃገር መፍረስ አደጋ፤ ተገቢው ትኩረት ይሰጠው ዘንድ ለማሳሰብ፤ ሁለት ሕዝብዓዊ ሰላምዓዊ ሰልፍዖችን የመጥራት አዝማሚያ ተከስቶ እንደነበር ሰምተናል።

ገዥው አካልም፤ [እስከ ዛሬ ማመን ለ አቃታቸው እና ማመን ለ እማይፈልጉም ጭምር] አምባገነንዕነቱን አጉልቶ ለማስመስከር በእሚረዳው መልኩ፤ መሣሪያ የታጠቀ ሠራዊቱን በመጠቀም ሕዝብዓዊ ሰላምዓዊ ሰልፍዖቹ እንዳይደረጉ ከልክሏል።

ወጉ አይቀርም እና፤ ምክንያትዓዊ ለመምሰል በእሚል፤ የጠቃቀሳቸው የተወሰኑ ነጥቦች ቢኖሩም፤ ሁሉም ሲሊ ሰበባ ሰበቦች ነበሩ፤ ናቸውም። በ ሜንጫ እየተጨፈጨፉ፣ በጥይት እየተደበደቡ፤ በቆርቆሮ እየታረዱ የ አለማባራት ዕልቂት እየተፈፀመባቸው ለአሉ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን ምንም ደንታ ዬሌለው መንግሥት ተብዬ፤ ሕዝብ በ ኮቪድ–19 እንዳይሞት በማሰብ ነው ሰልፍዖቹን የከለከልኩት በማለት፤ እሚአምነው ጤናማ ኅሊና የአለው ሰው አገኝአለሁ ብሎ ማሰቡ፤ የ ክፍለ ዘመኑ — ጭልጥ የአለ ቧልት በእሚል ሊመዘገብለት ይገባል!

የሆነው ሆኖ፤

ሕዝብዓዊ ሰላምዓዊ ሰልፍዖቹ የተከለከሉ ሆኖም ሳለ፤ የመጀመሪያው ይሆናል በተባለበት ዕለት የተወሰኑ ዜጐች ወጥተው እንደነበር እና በገዥው አካል አግባብ የአልሆነ ጥቃት እንደደረሰባቸውም ሰምተናል።

ሕዝብ፤ ታግሶ ታግሶ፤ አንድ ቀን ብሶትኡን መግለፅ ከጀመረ፤ ግፍ አንገሽግሾት በቃኝ ማለት ጀምሯል ማለት ነው። ከእዚያ በኋላ፤ ምንም ዓይነት አምባገነንዓዊ አፈና አያቆመውም። አዎ፤ ለሰልፉ የወጣው ሰው ጥቂት ነበር ተብሏል። ዋናው ነገር፤ አንድ ሰው እንኳን የሕዝብን ድምፅ፣ የሕዝብን ብሶት ለማስተጋባት ወደ አደባባይ ከወጣ — ፈረንጆቹ ሜታፎሪክሊ [ቲፕ ኦፍ ዘ አይስበርግ] እንዲሉ፤ በሚሊየን እሚቆጠሩ ግፍ የአንገፈገፋቸው ሰዎች በ እየ ቤትአቸው መሽገው አሉ ማለት ነው። ለእዚያም ነው፤ ግፍ የአንገሸገሸው ሕዝብ እና አምባገነንዕነት ትግል በገጠሙ ቁጥር፣ ግፍ የአንገሸገሸው ሕዝብ ሁል ጊዜም ከአላይ የ እሚሆነው። ታይታኒክን የአየ በ ሕዝብዓዊ እምቢትኛዕነት አይቀልድም!

በነገራችን ላይ፤ ይደረጋል የተባለለት ምርጫ፤ ነፃ እና ፍትህዓዊ ይሆናል እያላችሁ እምትምሉ እምትገዘቱ እምትቃዡ ተላሎች፤ እንደእዚህ የአለው የገዥው አካል ኢንኸረንት ሕላዌ — እርምአችሁን እድታወጡ ድፍረቱን ቢሰጥአችሁ፤ ይመረጥ አለ!

በሉ እንግዲህ — ለዛሬ በእዚሁ ላብቃ።

ፍትህ – በ ማንዕነትአቸው ምክንያት በእየ–ዕለቱ ለእሚጨፈጨፉ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን!

ፍትህ – በ ማንዕነትአቸው ምክንያት [መጤ] እየተባሉ በመንግሥት አካላት ጠንሳሽዕነት ተባባሪዕነት አቀነባባሪዕነት ተግባሪዕንት፤ በገዛ ቀዬአቸው፣ በ ሠላም መኖር እንዳይችሉ፤ አዳጋች ለሆኑ ችግሮች እንዲጋለጡ በመደረግአቸው፤ መቆሚያ መቀመጫ ለአጡ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን!

ፍትህ – ለ ኢትዮጵያዊ የኅሊና፣ የሐሣብ፣ እና የፖለቲካ እስረኞች!

ምርጫው ይሠረዝ — ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ዛሬውኑ ይመሥረት!

የሕዝብን ስልጣን ለሕዝብ አስረክቡ!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዬ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# ጦርዕነት

ታህሳስ ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ዲሴምበር 2020

**አዳራሽ:** ጦርዕነት — የሰው ልጅ፤ በ እራሱ፣ በ ሌሎች ፍጡራን እና በ ኢንቫይሮንመንት ላይ ከእሚፈፅማቸው ዘግናኝ ውድመቶች መሃከል አንዱ ነው። አዎ፤ ጦርዕነት እንደ [ዋር] በ ሃገራት መሃከል ወይም በ አንድ ሃገር ውስጥ በ የተለያዩ ቡድኖች መሃከል፤ መደኛም ሆነ መደበኛ የአልሆነ፣ የተደራጀ፣ ዘመኑ የፈቀደውን መሣሪያ የታጠቀ ቡድንን ወይም ሠራዊትን በመጠቀም፤ እሚደረግ ግጭት።

[ሥርወ ጦርዕነት] ከ የሰው ልጅ ኢንኸረንት እራስ ወዳድ ባህሪዕነት - እስከ - የሰው ልጅ ማኅበረሰብዓዊ ግንኙነቶች እሚፈጥሯቸው አለመጣጣሞችን ለመቋጨት በእሚል እሚወሰድ ሃይል የተጨመረበት እርምጃዕነት - እስከ - ሁለቱንም በእሚያካትት መልኩ እሚቀመር፤ የመላ ምት ምህዳር ውስጥ እሚስተናገድ ሁነት ነው። በ ዓለምአችን የአሉ የዘመኑ ጦርዕነቶች፤ በአመዛኙ — የ[ሰለጠንን] ነን እየ አሉ እሚምሉ እሚገዘቱ ፖለቲከኞች፤ የሃሳብም ሆነ የአቋም ልዩዕነቶችን ስልጡን በሆነ መንገድ መፍታት እማይሆንላቸው መሆኑን፤ በ ስሁት ውሳኔዎቻቸው እና ሃይል በተሞላባቸው አሰቃቂ እርምጃዎቻቸው እሚገልፁባቸው፤ በ የለየለት ዕብደት እሚለኩሷቸው የመጥፋት እና የመጠፋፋት [“ድግሶች”] ናቸው።

ለ የአለፉት 50-ዓመታት ገደማ፤ ኢትዮጵያዊያን [ከ ሶማሊያ ጋር ከተደረገው ጦርዕነት በስተቀር] ቀጥተኛ በሆነ መልኩ የውጭ ጠላት መጥቶብን ሳይሆን፤ እርስ በ እርስአችን በፈጠርናቸው ችግሮች ሳቢያ፤ ማብቂያ በሌላቸው ጦርዕነት’ዖች ውስጥ ተዘፍቀን — ለ የ[ሰው] ልጅ ህይወት ደንታ የሌለን፣ ለሃገር ሉዐላዊዕነት ክብር የሌለን፤ የበሽታ ቋት የሆንን፣ ሰላም የአጣን፣ እራስአችንን መመገብ እማንችል፣ በሁሉም መመዘኛዎች የ ዓለም ሃገራት ጭራ የሆንን፣ ከረባት አጥላቂ ማፈሪያዎች ሆነን ቀርተናል። ዛሬ ዛሬም፤ በ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ እጅጉን በባሰበት መልኩ እየተደረጉ የ አሉት ጦርዕነት’ዖች — [ቢብሊካል ፕሮፖርሽን] ሊባል በ እሚችል መጠን፤ የሃገር ክህደት እና ሃገር አፍራሽዕነት፣ ሽብርተኛዕነት፣ ጀኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ’ን እና የጦር ወንጀለኛዕነትን ጨምሮ፤ ዘግናኝ ሰቅጣጭ አረመኔዓዊ ዕልቂት እና ሰቆቃ በማስከተል፤ ኢትዮጵያን ወደ የ ምድር ገሃነምዕነት ቀይረዋት አሉ።

ጉበዝ፤ ለ የአለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት እየተደረጉ የአሉት ጦርዕነት’ዖች፤ መሠረትዓዊ ምክንያትዖቹ — ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው ሕገ መንግሥት፣ የጎሣ ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ አደረጃጀት እና በ ቋንቋ እና በ ጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩዩ ፌደራሊዝም ሲሆኑ፤ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ ተጠያቂው አካል ደሞ — ከተፀነሰባት ዕለት ጀምሮ፤ ዐማራ’ን በጠላትዕነት በመፈረጅ [ለመፍጀት] ብሎም የ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን’ን [ለማጥፋት] እናም ኢትዮጵያ’ን ለማፈራረስ በ የተማማሉ፤ ኢትዮጵያዊ አይደለንም በ እሚሉ የ እናት ጡት ነካሽ  አረመኔ ከሃዲዎች የተመሠረተው፤ ህወሓት በ እሚል ምህፃረ-ቃል ይጠራ የነበረው ነውረኛ ድርጅት ነው።

ህወሓት፤ ጊዜ አንስቶት ስልጣን ላይ ፊጢጥ ከማለቱ በፊት የፈፀመው ዕልቂት፣ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች፣ የ ዐማራ [ወልቃይት ጠገዴ ራያ]ን ለም መሬቶች እና ሰውዓዊ ማንዕነትን ቅሚያ እና ግዙፍ ሃገር የማፍረስ ተግባሮቹ ተዘርዝረው አያልቁም። ስልጣን ላይ የመውጣት ዕድሉን ሊያገኝ አቅራቢያም፤ ኢህአዴግ እሚባል ጭምብል ግንባር ፈጥሮ — ኤርትራን የገነጠለ፣ የባሕር በሮቻችንን አሳልፎ የሰጠ፤ ፀረ ኢትዮጵያ ሕገ–መንግሥት ተግባርዓዊ የ አደረገ፣ አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀቶችን እና በ ቋንቋ እና በ ጐጥ ላይ የተመሠረተ ዕኩይ ፌደራሊዝም ዘርግቶ፤ ጎሣ እና ሃይማኖት ላይ የአተኮረ፣ በቅጥፈት ትርክት ላይ የተመሠረተ ጥላቻን የቀፈቀፈ፤ በተለይ በ ዐማራ’ው እና በ የ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያን ላይ  ቁጥር ስፍር የሌለው ዕልቂት እና ሰቆቃ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ እየአካሄደ የአለ፣ ሰብዓዊ መብቶችን የገፈፈ፣ በ ትሪሊየን እሚቆጠር ዶላር፣ ንብረት እና የጦር መሣሪያዎችን የዘረፈ — የ ኢትዮጵያዊዕነት ሁለዕንተንዓዊ ፋብሪክ ብል የሆነ፤ ጨካኝ አረመኔ ወንጀለኛ ነውረኛ ድርጅት ነው።

ትክክል፤ ህወሓት ካንሰር ነው። ታዲያ — አጥብቀን አደራ እምንለው፤ ህወሓት ሜታስታሳይዝ የአደረገ ካንሰር ስለሆነ፤ ሎካላይዝድ በሆነ አንድ ሰርጂካል ፕሮሲጀር ብቻ ይጠፋል ብለን እንዳንዘናጋ ነው። እናም፤ ሎካላይዝድ የሆነው ሰርጂካል ፕሮሲጀር እየተደረገም ሆነ ከተጠናቀቀም በኋላ፤ መሠሪዎቹ አንድ በአንድ እየተጠረነፉ በ አስቸኳይ ለፍርድ ቀርበው — በሕግ ተወግዘው እና ተገቢውን ከፍተኛ ቅጣት ተቀብለው፤ ርኩስ ከም አሪዎስ ተብለው ከ ኢትዮጵያ የ ፖለቲካ መድረክ እስከ መጨረሻው ሊወገዱ ይገባል። ያ-ም ብቻም ሳይሆን፤ ፍትህ የተነፈገችው ኢትዮጵያ ውስጥ — ሜታስታሳይዝ የአደረገውን ካንሰር ለማጥራት፤ ዘርፈ-ብዙ [አድቫንስድ ካንሰር ትሪትመንት ሞዳሊቲ’ስ] ኮንከረንትሊ ሊጀመሩዕላት ይገባል እንል አለን።

ዘርፈ-ብዙ [አድቫንስድ ካንሰር ትሪትመንት ሞዳሊቲ’ስ] ኮንከረንትሊ ሊጀመሩዕላት ይገባል ስንል እም — ህወሓት፣ ያነግ እንዲሁም መሰል ነፃ አውጪ ተብዬ ርዝራዥ ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ፤ [አደረጃጀትዖቻቸውም ሆነ መሠሪ አመለካከትዖቻቸው] ከምድረ ገፅ ይጥፉ ማለትአችን ነው — በ ሕዝብ እና በ ሃገር ክህደት፣ በ አሸባሪዕነት በ ጀኖሳይድ በ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ በ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና በ የጦር ወንጀለኛዕነት ለፍርድ ቀርበው፤ ተገቢው ከፍተኛ ቅጣት ይፈፀምባቸው ማለትአችን ነው። “ነፃ አውጪ” ተብዬ ከሃዲዎችን እማያካትት፤ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ምሥረታ ሂደት ዛሬውኑ ይጀመር ማለትአችን ነው። አዲስ ኢትዮጵያዊ ሕገ-መንግሥት ይቀረፅ ማለትአችን ነው። አቅለሸላሹ ኮከብ ከ ሰንደቅ-ዓላማችን ላይ ይነሳ ማለትአችን ነው። የ ጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የ ጎሣ-አደረጃጀት በሕግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩዩ ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ ዛሬውኑ ይፍረስ ማለትአችን ነው። ወልቃይት ጠገዴ ራያ ለባለቤቱ ለ ዐማራ ይመለሱ ማለትአችን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ቋንቋዎቹ ወግ ባህሎቹ ሰውዓዊ መብቶቹ ተከብረው፡ በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት በ አሻው ቦታ ተዘዋውሮ — በ ዕኩልዕነት የመኖር፣ የፈለገውን የማግባት የመውለድ የመክበድ፣ ሃብት  ንብረት የማፍራት እና የመምረጥ የመመረጥ መብቶቹ ሁሉ ሳይሸራረፉ ተከብረው፤ ምሉዕ መለኮትዓዊ ሥልጡን ህይወት እሚጐናፀፍባት ኢትዮጵያ እንድትኖረን እርግጠኞች እንሁን ማለትአችን ነው። “መንግሥት” ሕዝብን እና ሃገርን እንደ የግል ንብረቱ መቁጠሩን እንዲያቆም በጥብቅ እና በግልፅ ይነገረው ማለትአችን ነው። ሰው በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ኢትዮጵያን የመጠበቅ እና ኢትዮጵያዊያንን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ይመሥረት ማለትአችን ነው።  እናም፤ ኢትዮጵያ ፍትህ ተጐናጽፋ እና ሰላም አግኝታ እፎይ ትበልልን ማለትአችን ነው!

ያ-ም ወደ ተግባር ተለውጦ ማየት እንችል ዘንድ፤ ገዥው አካል "እየአደረግሁ የ አለሁት — ሪፎርም ነው" እሚለውን የ ሦስት ዓመታት ገደማ ቧልት አሽቀንጥሮ ሊወረውረው የግድ ነው። የአለውን ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ለማስቀጠል፤ ክፍለጦሮችን እሚያንቀሳቅስ፣ መድፍ ታንክ ሮኬቶችን እና የአየር ድብደባን የአካተተ የለየለት ጦርዕነት እሚካሄድበት አንዳችም ስልጡን ምክንያት ሊኖር አይችልም። ይህ ሁሉ ሃገርዓዊ ሕዝብዓዊ መስዋዕተዕነት ከተከፈለ በኋላ ደሞ፤ ዝብአዝንኬ የጎሣ ፖለቲካችሁን ተሸክማችሁ የ እምታንጎላጁብን ከሆነ፤ እነእርሱን ሆናችሁ የመገኘት እጣ ፈንታችሁ የጊዜ ጉዳይ ብቻ መሆኑን በ እሚገባ ልትገነዘቡት ይገባችሁ አለ። እናም፤ ገዥው አካል ሊያደርግ ይገባል ብለን እምናምነው፤ ተላይ ከፍ ብለን በዝርዝር ያቀረብናቸውን ስርነቀል እርምጃዎች ተግባርዓዊ በማድረግ፤ የተጐሳቆለችዋን ኢትዮጵያ በቀናዕነት መታደግ እና የተጐሳቆለችዋን ኢትዮጵያ በቀናዕነት መታደግ ብቻ ነው።

በመጨረሻም፤ የ አዳራሽ ሃላፊዕነት — ድምፅአቸው ለታፈነ ድምፅ መሆን እና ፍትህ ለተነፈገች ሃገር የጤናማ ኅሊና ዕምቅ እስትንፋስ ሆኖ መገኘት በመሆኑ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ሊደረግለት እሚገባው ድፍን የአለ "ሕግ ማስከበር" ብቻ ሳይሆን፤ ተገቢውን ስርነቀል ለውጥ ተግባርዓዊ በማድረግ፤ በተለያዩ የ ኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ እየተደረጉ የ አሉት ጦርዕነትዖች፤ ፍትህ አጐናጻፊ ሆነው [ጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ] በ አፋጣኝ ለአንዴ እና ለመጨረሻ፤ ሊጠናቀቁ እንደ እሚገባ — በተገጋጋሚ አምርረን ማስገንዘብ እንድወድ አለን!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

በ እዚህች የ ታህሳስ ወር ብሎግ፤ የቅርብ ቀናት ጉዳይዖችን በተመለከተ የ እምለውን ብዬ ሳበቃ፤ እንደ ልማድ እየሆነ የመጣውን የ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ወርሃዊ ወፍ በረር ዳሰሳ'ዬን አጋርቼ — በመጨረሻም፤ አፅንዖት ሊደረግባቸው እሚገቡ ነጥቦችን ጠቃቅሼ፤ አበቃ አለሁ።

እናም፤ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣዬ ነው።

<u>የቅርብ ቀናት ጉዳይዖችን በተመለከተ።</u>

ጐበዝ፤

ህወሓት፣ ዖነግ እና ከ ኢህአዴግ ጭምብል በስተጀርባ የተካተቱት ድርጅቶች ሁሉ [አደረጃጀትዖቻቸውም ሆነ መሠሪ የፖለቲካ አመለካከትዖቻቸው] ሙሉ በ ሙሉ እንዲጠፉ እስከ አልተደረገ ድረስ፤ ኢትዮጵያ — ፍትህ የተነፈገች ሃገር ከመሆን አትድንም።

ሆኖም ግን፤ የ ህወሓት እና የ ዖነግ አጠፋፍ — አሁን እየሆነ በ አለው መልኩ መሆኑ፤ ጤናማ ኅሊና የአለው ኢትዮጵያዊን ያስፈነድቀው አለ ብለን አናምንም። ምክንያቱም፤ እስከ አፍንጫቸው በታጠቁ ፖለቲከኞች መሃከል በ እሚደረግ የትእኛውም ዓይነት [ጦርዕነት] እሚማገደው፤ የመከላከያ ሠራዊቱን እና የ ሲቪል ማኅበረሰቡን ጨምሮ፤ በ አጠቃላይ የ[ሰው] ልጅን፤ በቀረቤታም የፈረደበት የዋሁን ምስኪኑን የ ኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ — ዕሙን ስለሆነ!

በ የ አለፈው ወር ብቻ ሳይሆን፤ ቢያንስ በ አለፉት 30-ዓመታት ዉስጥ እየተደረጉ በ አሉት ጦርዕነትዖች ሳቢያ፤የአለጊዜው እሚቀጨውን እሚቀጠፈውን ህይወት፣ እሚያስተናግደውን ሰቆቃ እና ሊወድም እሚችለውን ንብረት በውል ማወቅ የ ጥናት እና ምርምር ስራ እሚጠይቅ ቢሆንም ቅሉ፤ ከ እሚታየው ከ እሚሰማው እና ሊገመት ከ እሚችለው በመነሳት ዘግናኝዕነቱን ማሰቡ ብቻ መፈጠርን እስከ እሚያስጠላ ድረስ፤ ልብ ሰባሪ፣ አንጀት አሳራሪ፣ ከ አሳዛኝም አሳዛኝ ህይወት "እየኖርን" መሆኑን መገንዘቡ ግን — ከባድ ሊሆን አይችልም። በፍፁም!

በነገርአችን ላይ፤

ሰሞኑን የተባባሰው ጦርዕነት እንዲጀመር እንደ ምክንያት የተጠቀሰው፤ በ ኖቬምበር ሦስት/አራት አኩራፊው ነፃ አውጪ ተብዬ፤ ፀባይ መግዛት ተስኖት በ የሃገር መከላከያ ሠራዊቱ ላይ የፈፀመውን ጄኖሳይድ፣ የጦር ወንጀል እና የሃገር ክህደት፤ ["በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ ተሰምቶ የ እማይታወቅ፤ በ ዓለም በየትኛውም ሃገር ታይቶ ተሰምቶ ተደርጎ የ እማይታወቅ"] ወንጀል ነው እየ አሉ፤ የ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች እና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣንአት፤ <u>በመገረም</u> መንፈስ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ግን — ግን፤

ከፍተኛ የጦር መኮንኖቹ እና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣንአቱ "በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ ተሰምቶ እማይታወቅ" ሲሉ፤ ምን እየ አሉን ነው?!!!

[ሰው] ማለት ወይም [ኢትዮጵያዊ] ማለት፤ የታጠቀ የተደራጀ የጦር ሠራዊት ብቻ ነው ከ አላሉን በስተቀር፤ መሠሪው አረመኔው ስግብግቡ ህወሓት ከ መሠሪው አረመኔው ስግብግቡ ዖነግ ጋር በመቀናጀት፤ በብዙ የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ — አብሮ በልቶ ጠጥቶ፣ ተጋብቶ ወልዶ ከብዶ፣ አምኖ ወገኔ ሃገሬ ብሎ፤ ሲወለድ ዕልል ብሎ፣ ልጆቹን ስሞ'ለት እደጉ ተመንደጉ ብሎ መርቆ፣ ሲሞሽር ዘፍኖ፣ ሲሞት አልቅሶ ቀብሮ፣ ችግርን ደስታን ሙሉ ህይወቱን አብሮ የተካፈለን ንፁህ የዋህ ደግ ምስኪን ኢትዮጵያዊ — በተለይ በተለይ ዐማራ እና የ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማንያን ላይ፤ ህወሓት እና ዖነግ የ አለማቋረጥ እየፈፀሙ የአለውን የ[ሰው]ን ልጅ ከእነ ህይወቱ ወደ ገደል መወርወርን እና በቤት ውስጥ ቆልፎ ማቃጠልን መረሸንን የጨመረ – ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ እየአካሄዱ፤ ኢትዮጵያን ቢያንስ ለ 30-ዓመታት ያህል አኬልዳማ፣ የምድር ገሃነም አድርገውአት እንደ አሉ፤ የጦር መኮንኖቹ እና የመንግሥት ባለሥልጣንአቱ፤ እንዴት ላይታይአቸው ቻለ?!

ግን — ግን፤

የጦር መኮንኖቹ እና የመንግሥት ባለሥልጣንአቱ "በ ዓለም በየትኛውም ሃገር ታይቶ ተሰምቶ ተደርጎ የ እማይታወቅ" ሲሉስ፤ ምን እየ አሉን ይሆን?!!!

ህወሓት እና ፆነግ በመቀናጀት፤ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ሕገ-መንግሥት ተግብረው፣ የጎሣ-ፖለቲካን እና አክራሪ የጎሣ-አደረጃጀቶችን እየቀለቡ አጎልብተው፣ ዘጠኝ ገደማ እሚሆኑ የጎሣ ግርግሞች ፈጥረው፣ አርማ እሚሆንአቸው ጨርቅ እንዲያሰፉ ገፋፍተው፣ እስከመገንጠል ድረስ መብት ሰጥተው፣ የቅጥፈት ትርክት በመፍጠር አንድ የሆነውን ህብር ሕዝብ ከፋፍለው ለያይተው፣ የሃገር መከላከያ አቋም የአለው የጎሣ የጦር ሠራዊት እንዲኖራቸው ፈቅደው፣ በ ዓለም ላይ ተፈልጐ እማይገኝ ሞሮኒክ የፌደራል አስተዳደር ስርዓት ዘርግተው፣ "ፕሬዝደንት" እሚል ማዕረግ አሸክመው፣ ሉዓላዊ ሃገር እንደሆኑ እንዲሰማቸው አድርገው የልብ ልብ ሰጥተው በዕብሪት አደልበው፤ እራሳቸው አብደው ተከታዮቻቸውንም ከ አሳበዱ በኋላ — ደረሰ የተባለው ዕልቂት መፈፀሙ፤ የጦር መኮንኖቹን እና የመንግሥት ባለሥልጣንአቱን፤ እንዴት ሊያስገርምአቸው ቻለ?!

ጐበዝ፤

እነ እዚያ ሁለት የ ቅርብ ቀናት ትውስታዎቻችን ላይ ትንሽ ለማለት የመረጥነው፤ የ ኢትዮጵያ መሠርትዓዊ ችግርዖች ደም-ቅዳ እና ደም-መልስ [አርተሪ'ስ አና ቬይን'ስ] ሆነው እሚአገለግሉ — እንዲሁም፤ የ ገዥው አካልአት የ ኩርማን አረዳድአቸው እና የ ዕኩይ አመለካከትአቸውም ጭምር መጋቢ ቱቦዎች ናቸው ብለን የ እምናምን በመሆኑ እና — ቢነገርአቸው፤ ምንአልባት ምንአልባት ስለ የ ኢትዮጵያ ችግሮች ምንዕነእት ምሉዕ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ፤ ያግዛቸው አለ ብለን በማመንአችን ነው።

ልብ እንበል፤

ዛሬ፤ ከፊትአችን ተደቅኖ የ አለው ከፍተኛ ስጋት፤ መንግሥት ተብዬው፤ ኢትዮጵያ ስለ የተዘፈቅችበት ችግር የአለው ኩርማን አረዳድ በመሆኑ እና የ ጦርዕነቱ ውጤት የእራሱንም ህልውና አደጋ ላይ እሚጥል እንዳይሆን ስለ እሚፈራም ጭምር፤ ህወሓትን ፆነግን ምንአልባትም ህወሓት እና ፆነግ ውስጥ የ አሉ አልገብር የአሉ ሰዎችን ከፖለቲካው ምህዳር ማስወገድ ብቻውን ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሄ እንደ እሚሆን አድርጐ ሊወስድ የ እሚችል የመሆኑ ዕውነታ ነው። ገና ከአሁኑ፤ አንድ አንድ ምልክቶች በመታየትም ላይ ናቸው። ውጤቱ እንደ የ እሚጠበቀው ከሆነ ደሞ — ለ ኢትዮጵያ፣ ለ ኢትዮጵያዊዕነት እና ለ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ተደጋጋሚ ክህደት እና ቀጣዩ ዘግናኝ ፈተና እንደ እሚሆንም መገመቱ ብልህዕነት ነው።

ድንገት እንዲያው ለምን አልባቱ፤ በ ገዥው አካል ውስጥ የ እሚሰማ ቀና ኢትዮጵያዊ ከ አለ [አለ ብለን እናምን አለን] — ኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጠረ የ አለው ዕልቂት እና ሰቆቃ ግለቱ እየፋመ ሄዶ በርጩማችሁን እስኪአንገጫግጨው ድረስ እየጠበቃችሁ፤ በ እሚፈጠሩ ክስተቶች መገረም ሳይሆን ከ እናንተ እሚጠበቀው፤ ይልቁን እስ ከእናንተ የ እሚጠበቀው — ስለ የ ኢትዮጵያ መሠርትዓዊ ችግሮች የአላችሁን ጠማማ አመለካከትአችሁን አቅንታችሁ እና ኩርማን አረዳዳችሁን አስፍታችሁ፤ የመሠረትዓዊ ችግሮቿ [ሩት ኮዝስ] ምን እንደሆኑ እና ፍቱን መድሃኒትአቸው ምን ሊሆኑ እንደ እሚገባ የጠራ ግንዛቤ እንዲኖርአችሁ ማድረግ መሆኑን አምናችሁ መቀበል የግድ ነው።

ያ-እንን ለማድረግ እንዲአግዝአችሁ በ እሚል እም፤ እጅጉን ብዙ ቀና አሳቢ ኢትዮጵያዊያን፤ የ መሠረትዓዊ ችግሮቿ [ተጨባጭ የሆኑ፣ እርምጃ ሊወስድባቸው እሚቻል፣ እንዲጠፉ ማድረግ እሚገባ እና እንዲጠፉ ማድረግ እሚቻሉትን መሠረትዓዊ ችግሮች ማለትአችን ነው] "ሩት ኮዝስ" ምን እንደሆኑ እና ፍቱን መድሃኒትዖቻቸው ምን ምን እንደሆኑም፤ ሳንታክት በተደጋጋሚ በግልፅ አስረድተንአችሁ አለ።

ሆኖም፤ የ እናንተ አለመስማት አለመቀበል እና በ አግባብ በ አግባቡ የ አለመተግበር ጦስ፤ ኢትዮጵያ አሁን ወደ አለችበት ዘግናኝ ዕውነታ ላይ የ አደረሷት መሆኑን፤ እንድትረዱትም እንፈልግ አለን።

አዎ፤


በተደጋጋሚ የጠቀስናቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች ለመተግበር፤ ፈቃደኛ ለመሆን የ እምታመንቱ ከሆነ፤ አሁንም ዕመኑን — ዛሬ እየአየነው ከአለው ዕልቂት እና ሰቆቃ የባሰ ተደጋጋሚ ዕልቂት እና ሰቆቃ እየተከሰተ እንዲቀጥል፤ ምክንያቶቹ እናንተው በመሆን ለመቀጠል መምረጣችሁ እንደሆነ እና የ ጊዜ ጉዳይ ከ አልሆነ በስተቀር፤ ተጠያቂ ከመሆንም እንደ እማታመልጡ በድርብ ድርብርብ የ ጎሊና ሰረዝ አፅንዖት በመስጠት፤ በጥብቅ እና በግልፅ ማስንዘብ እንወድ አለን።

<u>የ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ ወርሃዊ ወፍ–በረር ዳሰሳ።</u>

ወረርሽኙ ጀመረ ከተባለበት ከ 12/31/2019 እስከ 11/30/2020 ድረስ፤ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት የተደረጉት አዲስ የ ሳርስ–ኮቭ–2 ፓርቲክል [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ብዛት፤ በ ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ድምሩ – ወደ 62.8 ሚልየን ደርሷል። ከእነዚያም ውስጥ 2.3 ፐርሰንት እሚሆኑት፤ ህመሙ ፀንቶባቸው ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለም አይተናል።

በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እሚደረጉት [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር አሁን በአለበት ከፍተኛ ደረጃ አየ አደገ መሄድ መቀጠሉ — አሁንም፤ ቴስት የተደረጉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄድን እንደምክንያት መጥቀስ ከእሚቻልበት ኮምፈርት ዞን የአለፈ በሆነ መልኩ፣ የመከላከል–የመቆጣጠር እርምጃዎች እየላሉ መሄድአቸውን እና በኅብረተሰቡ ውስጥ የመዘናጋት እና የመሰላቸት ማይንድሴት እየጐለበተ መምጣቱን ጠቋሚ ሊሆኑ እንደ እሚችሉ ልብ ማለቱ፤ ተገቢ ነው።

እንደ አዲስ ሪፖርት እሚደረጉ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር ብዛት በ ኤፕሪል 2020 ሪፖርት ከተደረገው ጋር ሲነፃፀር፤ በ ኖቬምበር 2020 ሪፖርት የተደረገው ቁጥር በ [626] ፐርሰንት አብላጫዕነት እንደአለውም አይተናል።





ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፤ ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኖቬምበር 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጐም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ወረድ ብላችሁ እምታዩት ሰንጠረዥ ደሞ፤ በ ዓለም–አቀፍ ደረጃ ከ ዲሴምበር 2019 እስከ ማርች 2020 ድረስ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ በ እየ ወሩ ሪፖርት የተደረጉትን አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ብዛት — የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ቁጥር፣ የ ሙታን ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ቁጥርን እና ወረርሽኙ ከተከሰተ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ፤ ህይወትአችውን የአጡ ሰዎች የ እየ ወሩ በጥቅል በፐርሰንት ሲሰሉ የተገኙን ቁጥሮች የያዘው ነው።

ኮቪድ-19 | ፕላኔት ምድር | 12/31/2019 – 11/30/2020

| ግዜያት (በወራት) | የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር | የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ጥቅል/ኪሙሌቲቭ ቁጥር | ጥቅል/ኪሙሌቲቭ የሙታን ቁጥር | ጥቅል /ኪሙሌቲቭ የ ሙታን ብዛት በ ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| ከ ድሴምበር 2019 እስከ - ማርች 2020 | 777,798 | 777,798 | 37,272 | 4.79 |
| በ ኤፕሪል 2020 | 2,353,002 | 3,130,800 | 227,051 | 7.25 |
| በ ሜይ 2020 | 2,897,335 | 6,028,135 | 368,944 | 6.12 |
| በ ጁን 2020 | 4,244,866 | 10,273,001 | 505,295 | 4.92 |
| በ ጁላይ 2020 | 7,023,302 | 17,296,303 | 673,290 | 3.89 |
| በ ኦገስት 2020 | 7,955,031 | 25,251,334 | 846,841 | 3.35 |
| በ ሴፕቴምበር 2020 | 8,463,261 | 33,714,595 | 1,008,932 | 2.99 |
| በ ኦክቶበር 2020 | 11,953,185 | 45,667,780 | 1,189,499 | 2.60 |
| በ ኖቬምበር 2020 | 17,089,760 | 62,757,540 | 1,460,477 | 2.33 |

ህይወታቸውን የእሚያጡ ህሙማን መጠን፤ ከአጠቃላይ በፐርሰንት ሲተመን፤ ኤፕሪል 30/2020 ላይ ወደ ሰባት ፐርሰንት የነበረው፤ ዛሬ ኖቬምበር 30/2020 ላይ 2.33 ፐርሰንት ስለ መሆኑ፤ ብዙ ምክንያቶች መጠቃቀስ ይቻላል። ለምሳሌም ያህል ሀ) ቴስት የእሚደረጉት ሰዎች ቁጥር እጅጉን መጨመር ለ) አንድ ሁለት ሊረዱ የቻሉ መድሃኒቶችን መጠቀምን ጨምሮ፤ የተሻለ ፔሽንት ማኔጅመንት እየጐለበተ ስለመጣ እና ሐ) የ ሳርስ-ኮቭ-2 ፓርቲክል በወር ሁለት ሦስት ጊዘ ገደማ ሚውቴት የማድረግ ባህሪው [ምንም እንኳን ያን ያህልም ፈጣን እማይባል ሚውቴሽን ቢሆንም] ምን አልባት የከፋ ጉዳት እማያደርሱ የቫይረስዩ ዝርያዎች ተፈጥረው ሊሆን በመቻሉም ጭምር ሊሆንም እንደ እሚችል መጥቀሱ፤ እንደ አንድ የውውይት መንደርደሪያ ሃሣብ ይሆን ዘንድ፤ አካትተንው አለ — እንደ አዲስ እሚፈጠሩት የቫይረሱ ዝርያዎች፤ የረባ የ ፕሮቲን ሪአሬንጅመንት የ አላቸው አይደሉም [እንደ ማይነር ድሪፍት ሊወሰዱ እሚችሉ ናቸው] እና እየታየ በአለው የ ፓንደሚክ ትሬንድ ላይ እሚኖራቸው አንደምታ ሚዛን ደፊ አይደለም በእሚል የ እሚሞግቱ የአሉ መሆኑም ሳይዘነጋ።




ማስታወሻ፤ በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ እየ 7–ቀናት አማካይ ብዛት እና ስርጭት በ እየ አህጉራት – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኖቬምበር 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አሜሪካ [ሰሜን (ዩኤስኤ እና ካናዳ)፣ ደቡብ አሜሪካን እና ሊሎች ቴሪቴሪዎችንም ያካትታል]።

ከፍ ብላችሁ እምታዩት ዝግብ፤ እንደ አዲስ ሪፖርት የተደረጉ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች፤ የእየ አህጉራቱን የ እየ 7–ቀናት ወራጅ አማካይ ቁጥርን በተመለከተ ነው።

በ አውሮጳ፤ ወረርሽኙ አክቶበር መጀመሪያ አካባቢ አገርሽቶበት ከቆየ በኋላ፤ ኖቬምበር ሲገባ እንደምንም እየቀነሰ እንደመጣ ማየት ይቻላል። ለ እዚያም ምክንያቱ፤ አንዳንድ የህብረቱ ሃገራት በቅርቡ ጠንከር ወደ አለ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃ መውሰድ እንዲመለሱ ተገደው የነበረ እንደሆነ መገመት ከ ዕውነታው ብዙም እሚርቅ አይሆንም።

አሜሪካም፤ አክቶበር መጀመሪያ አካባቢ አገርሽቶበት የነበረው ወረሰኝ፤ እስከ ዛሬም አደብ ሳይገዛ እንደቀጠለበት የአለ መሆኑን ማየት ይቻላል።


በሌላው ጐን ደሞ፤

ኤዥያ ሪፖርት እየአደረገች የአለችው የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር፤ ለብዙ ወራት እየአሻቀበ ከከረመ በኋላ፤ ከ ሴፕቴምበር አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ የመቀነስ አዝሚያ ማሳየቱን ተገንዝበን አለ። በ ኖቬምበር ግን፤ የማንገራገር ስሜት የ አለው መስሎ ሰነባብቷል።

አፍሪቃ ሪፖርት እምታደርጋቸው የ አዲስ [ቴስት ፒዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር፤ ለ ረዥም ጊዜ አነስተኛ መባል እሚችል ሆኖ ቆይቷል። ስለ እዚህ ሪሌቲቭ ፓተርን፤ በ አህጉሩ የአሉ ተመራማሪዎች፤ ከ ጥናት እና ምርምርአቸው ውጤት በመነሳት የ እሚሰጧቸውን ሳይንስዓዊ ማብራሪያዎች ለማንበብ በጉጉት ላይ ነን።


እጆችአችንን በአግባቡ እናፅዳ | የአካል እርቀትአችንን እንጠብቅ | አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን | አዲስ የአኗኗር ዘይቤን እንላመድ

አፍሪቃ
12/31/2019 — 11/30/2020
የ እየ ዕለቱ




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ አፍሪቃ – ሪፖርት አድራጊ በሆኑት ሃገራት የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኖቬምበር 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ሃገራት የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን በመጠቀማቸው ሳቢያ'ም፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅ ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ
12/31/2019 — 11/30/2020
የ እየ ዕለቱ




<u>ማስታወሻ፤</u> በ ኮቪድ–19 የተያዙ ሰዎች የ-እየ ዕለቱ ብዛት እና ስርጭት በ ኢትዮጵያ – ሪፖርት በአድራጊዋ ሃገር የምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌት ላይ የተመረኮዘ። ዳታው የተሰበሰቡት፤ የ ዓለም ጤና ድርጅት'ን ጨምሮ ወደ 500 ከእሚጠጉ ምንጮች ነው። ጥሬ ዳታውን የወሰድኩት ከ https://www.ecdc.europa.eu/en/geographical-distribution-2019-ncov-cases ሲሆን፤ [አፕዴት] የተደረጉት ኖቬምበር 30/2020 ከ 6፡00 እስከ 10፡00 እንደ የመሃከለኛው አውሮጳ ሰዓት አቆጣጠር ነው። የ እየ ሃገራቱ ዳታ በ የተለያዩ የ ሰዓት አቆጣጠር ቀጠናዎች ስለ እሚለያይ እና ዳታውን ለማዘጋጀት ጊዜ ስለእሚወስድ፤ እየ እያችሁት የአለው ዳታ እና ሃገራቱ በግል ሊኖራቸው የ እሚችለው ዳታ ልዩዕነት ሊያሳዩ ይችላል። ሃገራት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ማረጋገጫ ስሌት ለውጥ ሊያሳዩ ስለ እሚችሉ፤ ሪፖርት እሚደረጉ ቁጥሮች ፓተርን ላይ ለውጥ ሊታይ ይችላል። ህመሙ የተከሰተበት ቀን አለመታወቁ እና ምናልባትም፤ የተለያዩ የ ምርመራ እና የማረጋገጫ ስሌቶችን የመጠቀም ገጠመኞች ይኖሩ ከሆነ'ም ጭምር፤ እየአያችሁት የአለው ቀመር፤ የወረርሽኙን ሂደት ላያንፀባርቅም ይችል ይሆናል እና – አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

እንደ የ ተለመደው፤ ኢትዮጵያ በ እየ ዕለቱ ሪፖርት እምታደርጋቸው የ አዲስ [ቴስት ፓዚትቭ] የሆኑ ሰዎች ቁጥር ዛሬም ድረስ አነስተኛ ሊባል እሚችል ነው — ሪሌቲቭሊ። እናም፤ እንደ ሳርስ–ኮቭ–2 የአለ [ፕሮፓጌትድ] ኤፒደሚክ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ ዝቅ የማለት ባሕሪይ ማንፀባርቁ ከመሆኑ በአሻገር — እየተሰራ የአለው ምንም ሆነ ምን፤ ቀጥሉበት በርቱ እሚያሰኝ ነው ከማለት ውጪ፤ ትሬንድ'ኡን በማስመልከት ብዙም ማለት አይቻልም።

ተ ወደ ላይ እንደጠቀስነው፤ እየታየ ስለ አለው ሪሌቲቭ ትሬንድ፤ በ ኢትዮጵያ የአሉ ተመራማሪዎች፤ ከ ጥናት እና ምርምርአቸው ውጤት በመነሳት የ እሚሰጧቸውን ማብራሪያዎች ለማንበብ በጉጉት ላይ ነን።

<u>ክፍል ሦስት — እንደ ማጠቃለያ፤</u>

ኢትዮጵያ፤ በደርሰባት ዘግናኝ የፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ የ ምድር ሲዖል ሆና አለች። ግልፅ ነው — ይህ ግዙፍ የፖለቲካ ቀውስ፤ የተወሰኑ መሠሪዎችን ከፖለቲካው መድረክ በማጥፋት ብቻ ለ ኢትዮጵያ፤ ለ ኢትዮጵያዊዕነት እና ለ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትህ ማጐናጸፍ በ እሚችል መልኩ ሊወገድ አይችልም። ያ-ም፤ ለ እየአንድአንዱ ኢትዮጵያዊ ግልፅ ይሆንለት ዘንድ፤ ያገባናል እምትሉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ፤ ማስተማሩ እና ማስገንዘቡ ላይ ሳይውል ሳያድር መረባረብ ይጠበቅብን አለ። ብረትን ማቃናት እንደጋለ ነው እንዲሉ!

ያ-ን እንም ስንል፤ ሊደረግ እሚገባው — የ ህወሓት የ ያነግ እና የ ሌሎች ርዝራዥ ነፃ አውጪ ተብዬ መሠሪዎች አደረጃጀት እና ዕኩይ የፖለቲካ አመለካከትአቸው ላይ ስርነቀል ለውጥ በማድረግ፤ ከምድረ ገፅ እንዲጠፉ ማድረግ ይገባል ማለትአችን ነው።

ዕመኑን፤ ያ ከ አልሆነ [ተገቢውን ኢትዮጵያዊ ስርነቀል ለውጥ ማድረግን አሻፈረኝ ከ አልን] ዛሬ እየኖርንአቸው የ አሉትን ዕልቂት እና ሰቆቃ — በባሰ መልኩ ነገ ከነገ ወዲያ ከዚያም በኋላ በተደጋጋሚ እንዲደርሱብን ወደን ፈቅደን ተቀቅብለን አለን ማለት ነው።

የለም፤ ወደን ፈቅደን አንቀበልም የ እምንል፤ ያገባናል እምንል ኢትዮጵያዊያን ሁሉ፤ በ እሚጠይቀው መራራ ትግል ውስጥ በሙሉ ልቡ የ እየ ድርሻችንን ማበርከት ይጠብቅብን አለ።

ኢትዮጵያን የ እምንል [በሃገር ቤትም ሆነ ከ ሃገር ቤት ውጪ የአለን] አንድ አልላቀቀን የአለ ችግር እንዳለ መጥቀስም ተግቢ ነው።

ችግርአችን ህወሓት እና ህወሓት ብቻ የሆነ ይመስል፤ ሰሞኑን በተፈጠረው ክስተት፤ ያ-ውም እየተከፈለ የ አለው ክቡር መስዋዕትዕነት ወዴት እንደ እሚያደርሰን ገና ምኑም ሳይለይለት — ሰርግ እና ምላሽ የሆነላችሁ እና ፈንጥዝያ የጀመራችሁ ወገኖች፤ የዛሬ ሁለት ዓመት ተኩል ገደማ ወደ የገባንበት ከፍተኛ ስህተት፤ ዓይንአችንን ጨፍነን በድጋሜ እንዳንዘፈቅ፤ ኧረ እየተስተዋለ ማለት እንወድ አለን።

ዛሬ — ስሜትአችንን ተቆጣጥረን፤ ምን እየሆነ ነው፣ ወዴት እየሄድን ነው እየአልን መጠየቅ ነው እሚገባን። ከ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊዕነት እና ከ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ውጪ የሆነ፤ የባሰ ችግር ውስጥ እንዳንገባ ሰከን ብለን ማሰብ እሚገባን ጊዜ ላይ መሆናችንን በ እሚገባ መረዳት ነው እሚገባን — መልሰን መላልሰን እራስአችንን እሚያጠፋንን ሃይል እንድንደግፍ ለ እሚያደርግ ንሁለላ ከመሸነፍ እንድን ዘንድ!

የ ሳርስ–ኮቭ–2 ፓርቲክል ዓለም-አቀፍ ወረርሽኝን በተመለከት፤

አስፈሪዕነቱ እስከ ዛሬም ቢሆን እንደ አለ ቢሆንም ቅሉ፤ በ እሚቀጥሉት ስድስት ወራት ውስጥ፤ ክትባት ጥቅም ላይ እሚውልበት ጊዜ ላይ በ መድረሳችን ሳቢያ፤ የ ተስፋሙሉዕነት ገፅታ በ እያንዳንዳንዳችን ፊት ላይ እየተንፀባረቀ እንደመጣ ማየት የጀመርን ይመስላል።

እናም፤ የ መከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃዎችን አጠንክረን መቀጠሉን ሳንዘነጋ — ጎን ለጎን፤ ለ 120 ሚልየን እሚጠጋ ኢትዮጵያዊ በቂ እሚሆን ክትባት ማግኘት እና በፍጥነት ማዳረስ እሚቻልባቸውን ዝግጅቶች ከወዲሁ መጠናቀቅአቸውን እርግጠኞች መሆን እንደ እሚገባን — አላሰባችሁበትም ብለን ሳይሆን — የ ሰላም እና መረጋጋት እጦት፤ እንቅፋት መሆኑ ስለ እማይቀር ከሌሎች ሃገራት በተለየ መልኩ፤ ማሰብ መጨነቅ እንደ እሚገባን ማስታወስ እንወድ አለን ለማለት ነው።

በሉ እንግዲህ፤ ለዛሬ በ እዚሁ ላብቃ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አኪዮ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

ፍትህ – ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ!

ፍትህ – ለ ኢትዮጵያዊዕነት!

ፍትህ – ለ ኢትዮጵያ!

# የ ፍትህ ያለህ!

ጥር ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ጃኒወሪ 2021

**አዳራሽ:** ከእዚህ በፊትም ደጋግመን ተናግረን አለን። ኢትዮጵያ፤ ፖለቲካዋን ፈር ማስያዝ ከቻለች፤ በሽታንም ሆነ የውጭ ሃገርዐት ጣልቃ-ገብዕነትን አደብ ማስገዛት አያቅታትም ብለን — ዛሬም እንዲሁ! ኮቪድ-19'ም ሆነ ሌሎች በሽታዎች፤ ከአቅም በላይ እየሆኑ እንደመጡ ሰምተን አለን። በ ጎሣ-ፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ በደም እየጨቀየች እንደሆነም እናውቅ አለን። ጐረቤትአችን እንደወረረን እንዲሁም፤ የ ሃገርዐቱ ህብረት፣ ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች እና የተወሰኑ ሃገርዐትም፤ እራስአቸውን ጠላት አድርገው ማሰለፍ መምረጥአቸውን በማስተዋልአችንም ጭምር — እንደ ወገን፤ ከልብ አዝነን አለን።

ያ እንደ የተጠበቀ ሆኖ፤ ለ እዚያ ሁሉ ምስቅልቅል እና ስቃይ የተሞላበት ህይወት ቀዳሚ ተጠያቂው፤ የ ኢትዮጵያን የ ጎሣ-ፖለቲካ ፈር ማስያዝ የተሳነው፣ በቅጥፈት ትርክት ላይ የተመሠረተ የስግብግብዕነት እና የ ወረራ ፖለቲካውን የመተግበር ቅዠት ውስጥ የተዘፈቀው፣ ዜጋዎቻችንን የ አለምንም እርህራሄ እሚጨፈጨፈው እና እሚያስጨፈጨፈው፣ ከ ሸገር ፓርክ ውጭ ሃገርን ማረጋጋት እና ሕዝብን በሰላም ማስተዳደር የ አቃተው — ገዥው ቡድን መሆኑ፤ በፍፁም አያጠራጥርም። ጉበዝ፤ ገዥው-ቡድን እየሆነ የ አለውን ሁሉ አይቶ-እንደ-አላየ እሚያልፈው፤ የ ኢትዮጵያን መሠረትዓዊ ችግር ምን እንደሆነ ሳያውቅ ቀርቶ ወይም መፍትሄው ጠፍቶት እንዳይመስላችሁ። በ የዋህዕነት፣ ተታልሎም ሆነ ሰዎች እንዳይሰራ ስለ ገቱትም አይደለም። ይልቁን እስ፤ ፖለቲካዊ ተፈጥሮው እና ዕምነቱ — ጭልጥ በአለ ቅጥፈት ላይ የተመሠረተው እና ቅዠት የሆነበትን የጎሣ–ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት እና የ ሰሞነኛውን ጎሣ የበላይዕነት ዕውን ማድረግን ግቡ የአደረገው — መሠሪ ማንዕነቱ አልፈቅድለት ስለአለው አንጅ! ፈልጎ መርጦ የተማማለበት ተልዕኮው በመሆኑ እንጅ!

እናም፤ እኛ — የኢትዮጵያን መሠረትዓዊ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሣብዖችን ደጋግመን በመጥቀስ ለ መሞገት እምንመርጠው፤ ገዥው-ቡድን [ኮንቪንስድ ወይም ኮንፊውዝድ] ሆኖ ወደ እኛ ዕምነት ይመጣል የ እሚል ብዥታ ውስጥ ስለሆንን አይደለም — ከ አልተገደደ በስተቀር። ይልቁን እስ — ትኩረት ሊሰጥባቸው እሚገቡ መሠረትዓዊ ኢትዮጵያዊ ጉዳይዖች መሆናቸውን ለ ኢትዮጵያዊ ወገንአችን ሳንታክት በማስገንዘብ በማስታወስ ለውጥ አምጪ ሕዝብዓዊ ሃይል ለመፍጠር እንዲቻል ለማገዝ እና ያ-እንን ከማድረግ ማፈግፈግም ሆነ መለሳለስ፤ የለየለት ባሪያዕነትን አምኖ ፈቅዶ መቀበል፣ የሕዝብን ሰቆቃ እና ዕልቂት ማራዘም እና በቁም ለመሞት በእራስአችን ላይ መፍረድ እንደሆነ በፅኑ ስለ እምንዐምን በመሆኑ ነው። ደግዕነቱ፤ [ግዜ] – በ ዕረፍት የለሽ ለውጥ እየጐለበተ እሚቀጥል ክስተት በመሆኑ እና ዛሬ በ ኢንፎርሜሽን እጅጉን እየበለፀገ እሚሄድ ማኅበረሰብ ስለ አለን፤ ገዥው-ቡድን የ ስግብግብዕነት፣ የ ወረራ እና የ ጭፍጨፋ ፖለቲካው – ቅዠት እንደሆነበት ይቀራል እንጅ፤ በምንም ተዐምር ዕውን ሆኖ ተደላድሎ ተመቻችቶ ሊያየው እንደ እማይበቃም ዕሙን ነው። ለእዚያም ሦስት ምክንያቶችን እንጥቀስ።

<u>ምክንያት አንድ</u>፡- አምባገነንዕነት እና ጎሠኛዕነት፤ ለጊዜው [ኢንቪንስብል] የሆነ ክስተት ሊመስል ይችል ይሆናል። በ ሕዝብዓዊ ነበልባል፤ ውስጥ ውስጡን እየተቦረቦረ ነዶ ወደ ዐመድዕነት መለወጡ ግን አይቀሬ ነው። የ ኢሠፓን እና የ ህወሓትን መጨረሻ ማየት ከበቂ በላይ ነው። <u>ምክንያት ሁለት</u>፡- የ ዩኒቨርስአችን [ሰከንድ ኔቸር] የመሆን አመኔታን በዘለቄታዊዕነት የተጐናፀፈው፤ ሳይንስ'ዓዊ ውልጠት እና ተጓዳኝ የ ማኅበረሰብዓዊ ህይወት ስልጣኔ እሚመራበት ኮድ ኦፍ ኮንዳክት፤ የ ጎሣ-ፖለቲካ እንዲጐለብት እሚያስችል አልጎሪዝም እንዳይፈጠር [ፕሮአክቲቭሊ] ይገድበው አለ። የ[ሰው] ዘር ዕድገት እና ቀጣይዕነት ከ ዕይታው ውጭ እንዲሆኑ አይፈቅድም እና! አዎ፤ የ ጎሣ-ፖለቲካ ሁለመናው [አን-ኤቲካል] ነው። የ ጎሣ-ፖለትካን እየአራመዱ፤ ስለ ሰውዓዊዕነት፣ ስለ ብልፅግናም ሆነ ስለ ስልጣኔ ማውራት — የለየለት ዲስኢንጂኒወስ'ዕነት ነው። ዕሙኑን — በ ስልጡን እና በ ፊውቸርስቲክ ዩኒቨርስ ውስጥ፤ የ ጎሣ-ፖለቲካ ቦታ የለውም፣ ሊኖረውም አይገባም። <u>ምክንያት ሦስት</u>፡- ዕውነትእኛው የ ምድር እና የ ሰማይ ጌታ [የ ኢትዮጵያ ዓምላክ] – የ ንፁሃን በእራስአቸው ሃገር እና በእራስአቸው "መንግስት" መካድ፣ ልብ መሰበር፣ መፈናቀል፣ ሰቆቃ፣ ዕልቂት እና የደም ጐርፍ — መና ሆኖ እንዲቀር አያደርግም። የ ሃይል አሰላላፉ ለጊዜው ኢ-ፍትህዓዊ በመሆኑ፤ ወገን ግፉአንን መታደግ አቅም አንሶት ቢታይም ቅሉ፤ የ ኢትዮጵያ ዓምላክ አንድ ቀን ተገቢውን ፍርድ እንደእሚሰጥ አንጠራጠርም። ዕውነት፤ በ ደካማ በ መሠሪ ሰዎች ዘንድ ትጎሳቆል እንደሁ እንጅ፤ በ ጌታ ፊት ግና ምንጊዜም አሸናፊ ናት — ኢትዮጵያም ዕውነት ናት!

ትክክል፤ እኛም እንደ ወገንዖቻችን ደግመን ደጋግመን እንጮሃለን። የ ኢትዮጵያ – ወቅትዓዊው መሠረትዓዊ ችግር በጥቅልሉ [ጭልጥ የአለ ቅጥፈት ላይ የተመሠረተ የጎሣ–ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት፣ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩይሉ ፌደራሊዝም፣ ተቋዋምአት ሁሉ በገዥው ቡድን እና በግለሰቦች ስለእሚነዱ እና አነእኝህን ሁሉ ተከትሎ ለ 30–ዓመታት ያህል የ አለማቋረጥ እየተከሠተ የ አለው፤ ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፣ "መጤ" በመባል ለ መፈናቀል፣ ለበሽታ፣ ለረሃብ፣ ለአሉታዊ የስነልቦና ጫና መጋለጥ፣ ኢትዮጵያን በሁለዕንተንዓዊ መልኩ የማሦቃየት የተቀናጀ ዘመቻ እና አምባገነኑ ገዥው-ቡድን በቀዳሚዕነት መጠቀስ የ አለበት የችግሯ ሁሉ ፈጣሪ ቀፍቃፊ አድራጊ የመሆኑ ዕውነታ] ነው። ከ እንግዲህ ወዲያ በ ህወሓት ማመካኘት — ኢንጅሩ!

እኛ፤ ከህወሓት ጋር የተደረገው ጦርዕነት ሕግ አስከብሮ እና ፍትህ አጐናጽፎ ተጠናቅቆ አለ ብለን አናምንም። በ ጦርዕነትኡ ሳቢያ አዲስ የተፈጠረ ነገር ቢኖር፤ ለ ገዥው-ቡድን አልገብር የአሉትን የተወሰኑ በርጨማ ተቀናቃኞች ገሸሽ አድርጐላቸው ሊሆን መቻሉ ብቻ ነው። ያ-ብቻውን ግና — ለ ኢትዮጵያ፣ ለ ኢትዮጵያዊዕነት እና ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እሚፈይደው ነገር የለም። ጦርዕነትኡ በድል ተጠናቅቆ፤ እፎይታን የፈጠረላቸው ከመሰላቸው — ድሉም ሆነ እፎይታው ለ የ ገዥው-ቡድን እና ለ የ ገዥው-ቡድን ብቻ መሆኑን እንዲረዱት እንፈልግ አለን። እናም፤ ሕግ የ ማስከበር እርምጃዎች፤ ፍትህ አጐናጻፊ ሆነው በመጠናቀቅ፤ ለ ኢትዮጵያ፣ ለ ኢትዮጵያዊዕነት እና ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውነተኛ እፎይታን ለማጐናፀፍ ይቻል ዘንድ፤ ደግመን ደጋግመን የ እምንጠቅስአቸው ዘረፈ-ብዙ የመፍትሄ እርምጃዎች የአለምንም መዘግየት ወደ ተግባር ተለውጠው መታየት ይኖርብአቸው አሉ — የተቀናጀ የተናበበ ስልጡን እና ሰላምዓዊ ትግል በማካሄድ።

*አዎ፤ ምርጫው ይሰረዝ – ሊስተካከሉ እሚገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳይዖች ሁሉ እስከ እሚስተካከሉ ድረስ። የ ገዥው-ቡድን [በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ] የ ሕዝብን ሥልጣን ለ ሕዝብ ያስረክብ። የ ሕዝብን፣ የ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጥምረት በማቀናጀት፤ "ነፃ-አውጪ" ተብዬዎችን እማያካትት ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ይዋቀር። የሽግግር መንግሥቱ፤ በዋናዕነት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ያስከብር፣ የሕዝብዋን ሰላም እና መረጋጋት ያስፍን፣ የ ሁሉንም ተቋዋምአት ተግባር በሃላፊዕነት ይምራ፣ እሚቀጥለውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበትን ምርጫ – ፍትህዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ እሚያስፈልጉትን ተቋዋምዓዊ ለውጦች ተግባርዓዊ ያድርግ። ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ኢትዮጵያዊ ሕገ-መንግሥት ይቅረፅ። እንደ አዲስ በ እሚቀረፀው ሕገ-መንግሥት ውስጥ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-አደረጃጀትዖች በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ይፍረስ። <u>በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ይካተት</u>። ሰው በሰውዕነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ይመስርት። ሌላ አማራጭ የለም!*

እንደገና ለመጥቀስ እንገደድ አለን። እነ-እኛን ዘረፈ-ብዙ መፍትሄዎች ተግባርዓዊ ሆነው እናይ ዘንድ፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ [<u>እስከ እሚደመጥ ድረስ</u>] ሳይታክት ድምፁን ከፍ አድርጎ ለመጮህ ማመንታት የለበትም — ማንም ሊሠጠውም ሆነ ማንም ሊነፍገው እማይችል፤ ሰውዓዊ መለኮትዓዊ ተፈጥሮዓዊ መብቱ ነው እና።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

በቅርብኡ በ ዩ-ኤስ-ኤ የተደረገውን ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ ሰበብ አድርገን አንድ/ሁለት ነጥቦችን በመነካካት እና አፅንኦትን የግድ እሚሉ ጉዳይዖችን እንደማጠቃለያ በማስፈር ላይ-ላይኡን ቢሆንም፤ በቅደም ተከተልአቸው እንአጋራ ዘንድ ከፊትአችሁ ቀርበን አለን።

ስለ ኮቪድ-19 ዓለም–አቀፍ ወረርሽኝ እናደርገው የነበረው የ ወፍ-በረር ዳሰሳ፤ ከ እዚህች የ ጥር 2013 ዓ.ም. ብሎግ ጀምሮ አይኖረንም። ወደፊት በ [Healthy Précis Quarterly] ዕትምዓችን ላይ ደጐስ አድርገን ልናካትተው ወስነን አለን እና — ጠብቁን!

እናም፤ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

<u>ስለ የቅርብኡ ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ — ነጥብ አንድ።</u>

ከ 1789 የ አውሮጳዊያን የዘመን አቆጣጠር ጀምሮ፤ ዩ-ኤስ-ኤ ፕሬዝደንትዋን በ እየ አራት ዓመትኡ በአመዛኙ ፍትህዓዊ እና ነፃ በሆነ የዜጋዎች የ ድምፅ አሰጣጥ ስርዐት ትመርጥ አለች። የ ድምፅ አሰጣጥ ስርዐትኡ ሁለት ገፅታዎች አሉት – ፖፒላር ቮት እና ኤሌክቶራል ኮሌጅ ቮት እሚባሉ።

በ የቅርብኡ ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ የ ዴሞክራትኡ ተወካይ በልጣን ላይ የነበሩትን የ ሪፐብሊካንኡ ተወካይን በማሸነፍ – 46ኛው ፕሬዝደንት በመሆን ተመርጠው አሉ። ይ-ህ በ እየ አራት ዓመትኡ እሚደረገው ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ ዋናው ትኩረትኡ በ ፕሬዝደንትዕነቱ ላይ ቢሆንም ቅሉ፤ የ ሴኔት እና የ ሃውስ ኦፍ ሬፐረዘንተቲቭ ተወካዮችን እንዲሁም በ እየ ስቴትዖቹ ገቨርነርዖችን እና በተዋረድ ሌሎች የተለያዩ የሕዝብ ተወካይዖችንም ያካትት አለ።

ምርጫን፣ መራጭን እና ተመራጭን በተመለከተ [እንከን ዐልባ እሚባል ባይሆንም፤] የ እየ አንድ-አንዱን ዜጋ ዕኩልዕነትን እና አንድዕነትን እሚደነግግ እና ሃገርዓዊ ሉዐላዊዕነትን እሚያጐላ ሕግ ዛሬ በ ዩ-ኤስ-ኤ በስራ ላይ በአለው ሕገ-መንግሥት ውስጥ በእማያወላዳ መልኩ በግልፅ ሰፍሮ አለ።

በ ዩ-ኤስ-ኤ፤ ፕሬዝደንት ሆኖ ለመመረጥ፤ ዩ-ኤስ-ኤ ውስጥ መወለድን [እናም የ ዩ-ኤስ-ኤ ዜጋዕነት ስታተስ የአለ ሰው መሆንን]፣ ቢያንስ የ 35 ዓመት ዕድሜ ላይ መድረስን እና ቢያንስ ለ 14 ዓመታት ያህል የ ዩ-ኤስ-ኤ ንዋሪዕነትን ማረጋገጥ የግድ ይላል።

የ ዜጋዕነትን ስታተስ የአለው እና የ ዕድሜ መመዘኛውን የ እሚያሟላ ማንአቸውም ሰው፤ ከ እየ ስቴትኡ ገቨርነርዖች እስከ የ ጥቃቅን ከተማዎች የአስተዳደር ዕርከኖች ድረስ የሕዝብ ተወካይ ሆኖ ለማገልገል እሚችል ተወዳዳሪን ለመወሰን በእሚል በ እሚካሄድ የምርጫ ሂደት ውስጥ፤ የ መምረጥም ሆነ ለፈለገው የሕዝብ ተወካይዕነት ወንበር የ መወዳደር እና የ መመረጥ ሙሉ ሕገ-መንግሥትዓዊ መብት አለው።

በሆነ ምክንያት የ ዩ-ኤስ-ኤ'ን መሬት የረገጠ ማንአቸውም ሰው፤ ለምሳሌም – በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው፤ ሌሎች መመዘኛዎችን አሙዋልቶ ሲገኝ እና የ ዜጋዕነት ስታተስ እስከተሰጠው ድረስ፤ ነዋሪ በሆነበት ማንአቸውም ስቴት የመምረጥም ሆነ የመመረጥ ሙሉ ሕገ-መንግሥትዓዊ መብት አለው። ሆኖም ግን፤ ከ ዩ-ኤስ-ኤ ውጪ እንደ የተወለደ ሰው፤ የ ዩ-ኤስ-ኤ ዜጋዕነት ስታተስ ቢኖረውም፤ የሀገሪትዋ ፕሬዝደንት ለመሆን መወዳደር አይፈቀድለትም። ለፕሬዝደንትዕነት የመወዳደር መብት የ አላቸውን ተወዳዳሪዎች ግን፤ የ መምረጥ ዕኩል ሕገ-መንግሥትዓዊ መብት አለው።

ነገሮች ሁሉ ተገጣጥመው፤ እናት እና አባት በትውልድም ሆነ በዜጋዕነትም ጭምር ኢትዮጵያዊ ሆነውም እንኳ፤ ልጅአቸው ዩ-ኤስ-ኤ ውስጥ እስከተወለደ(ች) ድረስ እና ሌሎችንም መመዘኛዎች አሙዋልቶ(ታ) እስከ ከተገኘ(ች) ድረስ፤ የሃገሪትዋ [የ ዩ-ኤስ-ኤ] ፕሬዝደንት ለመሆን የ መወዳደርም የመመረጥም ሙሉ [ዕኩል] ሕገ-መንግሥትዓዊ መብት አለው፤ አላት።

የ እየ ስቴትዖቹ ገቨርነርዖችን ለመምረጥ የተደነገጉት ሕግጋት፤ ከ ስቴት ወደ ስቴት የተለያዩ ቢሆኑም ቅሉ፤ መሠረትዓዊ በሆኑ መመዘኛዎች ሁሉም አንድ ዓይነት ናቸው። ማለትም፤ የ ዩ-ኤስ-ኤ የ ዜጋዕነት ስታተስን፣ በ እሚወዳደሩበት ስቴት ለተወሰኑ ዓመታት [በ እየ ስቴትኡ ይለያያል] ንዋሪ መሆንን እና ሕግዓዊ ተመራጭ መሆንን፤ እንዲሁም የተወሰነ ዕድሜ ላይ [በ እየ ስቴትኡ ይለያያል] መድረስ እሚሉትን መመዛኛዎች ማሙዋላት የአለባቸው መሆኑን በተመለከተ – ሁሉም አንድ ዓይነት ናቸው።

ዋናው ነጥብ፤ ለ ፕሬዝደንትዕነትም፣ ለ ገቨርነርዕነትም ሆነ እንደ እየ ዕርከንኡ ለሌሎች የሕዝብ ተወካይዕነት መራጭም ሆነ ተመራጭ ለመሆን — የ እዚህ ወይም የ እዚያ [ጎሣ] አባል መሆን አለብህ ወይም አለብሽ የ እሚል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተቀመጠ መመዘኛ የለም። በፍፁም!

በ ዩ-ኤስ-ኤ እጅግኡን ብዙ ቋዋንቋዋዎች እሚነገሩ ቢሆንም፤ በሁሉም ሰው በአብዛኛው እሚነገረው ቋዋንቋዋ እንግሊዝኛ ስለሆነ — እንደ [ዲ ፋክቶ] የሃገሪትዋ ብሔርዓዊ ቋዋንቋዋ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠር አለ። ለ ፕሬዝደንትዕነትም፣ ለ ገቨርነርዕነትም ሆነ እንደ እየ ዕርከንኡ ለሌሎች የሕዝብ ተወካይ ሆኖ መመረጥ ለ እሚፈልግ ሰው፤ የ እንግሊዝኛን ቋዋንቋዋ መጠቀም መቻል — የግድ ነው።

<u>ስለ የ ቅርብኡ ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ — ነጥብ ሁለት።</u>

ሌላው የ ቅርብኡን ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ ሰበብ በማድረግ ማንሳት የፈለግነው ነጥብ፤ የ ዜጋዎችን ተሳትፎ እና የ ሰንደቅ–ዓላማ አጠቃቀምን የ እሚመለከት ነው።

ዩ-ኤስ-ኤ 50 ስቴትዖች፣ አንድ የፌደራል ዲስትሪክት፣ አምስት ዋና ዋና ቴሪቴሪዎች እና የተወሰኑ ደሴትዖች አሉአት።

ዩ-ኤስ-ኤ በ [ቀይ ነጭ ሰማያዊ] ቀለማት ላይ የተመሰረተ፤ ሃምሳ ነጫጭ ክዋክብት በ ሰማይዓዊ መደብ ላይ፣ በቀረው ቦታ ደሞ ስድስት ነጭ እና ሰባት ቀይ መስመሮች የሰፈሩበት የሃገሪትዋ ሰንደቅ-ዓላማ አላት። በተጨማሪም፤ ሃምሳዎቹም ስቴትዖች [ለጊዜው እነሱ ላይ ብቻ እናተኩር እና] የ እየ እራስአቸው — አርማ መለያ ምልክት "ሰንደቅ-ዓላማ" አሉአቸው።

በ እየ ስቴት'ኡ እሚገኙት አርማዎች መለያ ምልክትዖች ሰንደቅ-ዓላማዎች አመጣጥ ሁለት ሁነትዖች ላይ ደገፍ የአለ ነው። <u>ሁነት አንድ</u> — እየ አንድአንዱ ስቴት እራስአቸውን የቻሉ የተሙአሉ የ አስተዳደር ቁመና የአላቸው አካልአት የነበሩ መሆንአቸው። ማለትም፤ የ እየ እራስአቸው የሆነ የ አስተዳደር ወሰን፣ የእየ እራስአቸው አገረ-ገዢ፣ ሕገ-መግሥት እና ሕግ የ አላቸው አካልአት የነበሩ መሆንአቸው። <u>ሁነት ሁለት</u> — ዩ-ኤስ-ኤ እንደ እራስዋን የቻለች [አንድ ሃገር] ፈንክሽን ማድረግ ከመጀመርዋ በፊት፤ ዛሬ ስቴት የሆኑት፤ ያ-ኔ በጊዜው እንደ ሃገር፣ ስቴት፣ ሪጅን ወይም ሲቲ እራስአቸውን ችለው ፈንክሽን ያደርጉ ስለነበር፤ ሰንደቅ-ዓላማዎችን ጨምሮ አንድአንድ መለያ ምልክትዖች ከ የነበራቸው ታሪክ ወግ ባህል ጋር እሚያስተሳስርአቸው ማስታወሻ ይሆኑላቸው ዘንድ ያስፈልጉናል በእሚል መወሰንአቸው።

አሁን አሁን ግና፤ እነእኛ የ እየ ስቴት'ኡ መለያ ምልክቶች ሰንደቅ-ዓላማዎች ጠቀሜታ ላይ እሚዉሉት፤ በ አመዛኙ ለ ማስተዋወቂያዕነት ነው — ልክ እንደ አንድ ዩኒቨርስቲ፣ የ ስፖርት ክለብ፣ የነዳጅ ማጣሪያ እና ማከፋፈያ ካምፓኒ፣ እንደ የመኪና ሰሪ አስመጪ እና አከፋፋይ ድርጅቶች አርማ ወይም መለያ ምልክት ማለት ነው።

በነገርአችን ላይ፤

ማንአቸውም ምርጫ፤ በ ሃገርዓዊ ደረጃም ሆነ በ እየ ስቴት'ኡ [ክፍለ-ሃገር ማለት ነው] በ እሚደረግበት ወቅት፤ [ፕሬዝደንትዓዊ ምርጫ ከሆነ እስከ ስድስት-መቶ ገደማ እሚሆኑ ተከታታይ ቀናት ሊወስድ ይችላል፤] ነዋሪው ዜጋ በ አካል እና በ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የ <u>አለመታከት</u> ንቁ ተሳታፊ ነው። ተሳትፎውንም ለማጉላት እና እሚደግፈውን ፓርቲ ወይም ግለሰብ እንዲያሸንፍ ለማገዝ እልህ አስጨራሽ ጥረትም ያደርጋል። የተለያዩ ዥግጅቶቹም ድምቀት ይኖርአቸው ዘንድ፤ በ ሁሉም ምርጫ በ እሚደረግባቸው የ ሃገሪትዋ ስቴትዖች [ክፍለ-ሃገርአት] ውስጥ፤ ልብ እንበል ጎበዝ — በ ክፍለ-ሃገርኡ ሰንደቅ-ዓላማ ሳይሆን፤ <u>በ ሃገርዓዊው የ[ዩ-ኤስ-ኤ] ሰንደቅ-ዓላማ</u> ብቻ መሸብረቅ እና መንቆጥቆጥ የ ትዕይንቶቹ ቀዳሚው እና ዋነኛው አካል ነው — የ አለምንም ማጋነን።

የ እየ ስቴትኡ አርማ ወይም መለያ ምልክት ወይም የ እየ ስቴትኡ ሰንደቅ-ዓላማዎች፤ በ እየ ስቴትኡ ከፍተኛ የ መንግሥት ተወካዮች ቢሮዎች እና በ መንግሥት መስሪያ ቤቶች ግቢዎቻቸው ብቻ፤ ከ ቀይ ነጭ ሰማይዓዊው ሃገርዓዊ ሰንደቅ-ዓላማ ጎን ለጎን ይውለበለቡ ወይም ይቀመጡ እንደሆነ እንጅ — ለ ፖለቲካ ነክ ጉዳይዖች ጥቅም ላይ ሲውሉ አይተን አናውቅም። በምንም ዓይነት፤ የ እየ ስቴትኡ መለያ አርማ "ሰንደቅ-ዓላማ" ለብቻው ጠቀሜታ ላይ እሚውልበት ገጠመኝ የአለም አይመስለንም።

ባይገርምአችሁ — ከ ነዋሪው ሰው ውስጥ፤ እየ አንድ-አንዱ ስቴት የ እየ እራሱ አርማ መለያ ምልክት "ሰንደቅ-ዓላማ" የአለው መሆኑን እሚያውቅ ብዙ ሊሆን እንደ እሚችል ቢገመትም፤ የ እየ እራስአቸውን ስቴት አርማ መለያ ምልክት "ሰንደቅ-ዓላማ" ድንገት ቢጠየቁ፤ ትክክለኛውን መልስ መስጠት እሚችሉት፤ እጅግን [አዎ በጣም እጅግን] በጣት እሚቆጠሩ ሰውዖች ብቻ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለነገሩ፤ አብዛኛዎቹ የ ስቴት ሰንደቅ-ዓላማዎች የ ስቴቱን ስም በ ላይአቸው ላይ ስለ እሚያሰፍሩ፤ በ ማየት በማንበብ አይደንቲፋይ ማድረጉ ከባድ አይሆንም።

ሃምሳዎቹንም ስቴትዖች በእግር እየዞራችሁ ብትጠይቁ፤ የ ስቴትኡን ሰንደቅ-ዓላማ በእጁ ይገኑ አውቃለሁ እሚል አንድም ነዋሪ ሰው አይገጥማችሁም። እነዚህ፤ በሆኑ ዝግጅቶች ላይ ብዙውን ጊዜ ሕዝብ ይዞአቸው እሚታዩት [ትናንሽ] ሰንደቅ-ዓላማዎች አሉ አይደል — አንድ እንኳን የ ስቴት ሰንደቅ-ዓላማ በ እዚያ መልክ [በትንንሹ] ተዘጋጅቶ አይተን አናውቅም።

ከ እዚያም በላይ፤ በ ሃገር አቀፍ ደርጃም ሆነ በ እየ ስቴትዖች ትኩረት የ እሚስቡ ዝግጅትዖች በ እሚኖሩባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ — በ እየ ዓመቱ የሚከበሩ የተለያዩ ክብረ-በዓላት፣ የሙዚቃ ትርዒትዖች፣ የ ስፖርት ዝግጅትዖች፤ የፖለቲካ፣ የምርጫ ቅስቀሳ [የተቃውሞም ሆነ የድጋፍ ሰልፍዖችን ጨምሮ] እና የመሳሰሉት ትዕይንትዖች ሲኖሩ፤ <u>ዝግጅቱ የትም ስቴት ይሁን የትም፤</u> በ <u>የትኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ይዘጋጅ፤</u> በ እዚያ መንደር ውስጥ የ አሉ ህንፃዎች፣ መንገዶች፣ የመዝናኛ ቦታዎች፣ የስፖርት ስቴድየምዖች፣ አዳራሽዖች፣ የተለያዩ

አልባሳት እና ጌጣጌጥዖች ሁሉ፤ በ ሃገርዓዊው የ ዩ-ኤስ-ኤ [ቀይ ነጭ ሰማይዓዊ]ው ሰንደቅ-ዓላማ ብቻ ነው እሚያሸበርቁት።

ምን አለለፋችሁ፤ በ ዩ-ኤስ-ኤ ነዋሪ የሆነ ሕዝብ፤ በማንአቸውም ዝግጅቶችም ሆነ በ የ ዕለት-ተ-ዕለት ህይወትኡ፤ ህፃናት፣ ሴት ወንዱ፣ ወጣት አዋቂ አዛውንቱ፤ ከአፍ የወደቀ ጥሬ እሚያካክሉ ወደዚህ ዓለም በቅርቡ የመጡ ህፃናት እንኳን ሳይቀሩ እና ሳር ቅጠሉም ሳይቀር፤ ዓይን እና ቀልብ በሚስብ መልኩ በ ሃገርዓዊው የ ዩ-ኤስ-ኤ [ቀይ ነጭ ሰማይዓዊው] ሰንደቅ-ዓላማ ብቻ በማሸብረቅ፤ የ አንድ ሃገር ሉዐላዊዕነት ክብር ፍቅር፣ የሕዝብ ዕኩልዕነት እና አንድዕነት — በከፍተኛ የኩራት መንፈስ የ እሚንፀባረቅባት ሃያል ሃገር ናት።

እንደ ማጠቃለያ፤

ኢትዮጵያ፤ በደርሰባት የ ጎሣ-ፖለቲካ ቀውስ ሳቢያ — ዛሬም የ ምድር ሲዖል እንደሆነች አለች። እንደ አለመታደል ሆኖ የረባ ትግል ማድረግ እና ሰውዓዊ መለኮትዓዊ ተፈጥሮዓዊ መብቶቻችንን ማስከበር ስለ አቃተን፤ ፈተናዎቻችን እየጠነከሩ፣ እየበዙ እና ማቆሚያ የሌላቸው እየሆኑ መምጣትአቸው አልቀረም።

አዎ፤ ወዲያ ወዲህ ማለት አያስፈፍልግም። በአሁኗ ሰዓት – ቁጥር አንድ የኢትዮጵያ የ ውስጥ-እግር እሳት፤ የ አዴፓ-አነግ መራሹ ገዥው-አካል ነው። ሃገር መጠበቅን እና ሕዝብን ማገልገል በፍፁም አልቻለበትም — እራሱን ለማረቅም ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም። ሪፎርም ተብዬው ከተጀመረ ሁለት-ዓመት ከ መንፈቅ ቢያስቆጥርም፤ ሰላም እና መረጋጋት የሰፈነባት አንዲት ቀን በውስጡ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም።

ዛሬም፤ የ ኢትዮጵያ ቁጥር አንድ መሠረትዓዊ ችግሯ፤ የጎሣ–ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት እና በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ነው። እነእኚህን ችግርዖች ስር-ነቀል ለውጥ በማምጣት፤ ሃገርን እና ሕዝብን በቀናዕነት ከመታደግ በስተቀር፤ ሌላ አማራጭ የለም — ሊኖርም አይችልም። በፍፁም!

አንድ ጊዜው ግልፅ የአደረገው ዕውነታ አለ። ብቸኛው ፍቱን መድሃኒት [ስር-ነቀል ለውጥ] በፈቃደኛዕነት ሊተገበር ሲቻል፤ ግና ሳይፈለግ የቀረ መሆኑ! እናም፤ ለ ኢትዮጵያ ለ ኢትዮጵያዊዕነት እና ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውነተኛ ፍትህ እና እፎይታን ለማጐናፀፍ ይቻል ዘንድ — የተቀናጀ የተናበበ ስልጡን እና ሰላምዓዊ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ፤ የግድ ነው።

ያ-ም ማለት፤ ሕዝብ [እስኪደመጥ ድረስ] ሳይታክት ድምፁን ከፍ አድርጐ ለመጮህ ይችል ዘንድ፤ ያገባኛል ባይ ኢትዮጵያዊ ሁሉ — ከ ልብአችን በ ንፁህዕነት እና በ ቀናዕነት፤ ሌት-ተ-ቀን ከ ሕዝብ ጐን ለመቆም ቃል ኪዳንአችንን ማስታወስ እና ማደስ ይገባን አለ።

ምርጫን በተመለከተ፤

ኢትዮጵያ የ አለችባቸውን ተጨባጭ ሁኔታዎች ዕግምት ውስጥ አስገብቶ፤ ሃገርዓዊ ምርጫ ማድረግን እንደ ፕራዮሪቲ እሚወስድ ግለሰብ፣ ፓርቲም ሆነ የመንግሥት አካል — ሳይውል ሳያድር ወደ ጠበል ሊወሰድ ይገባዋል!

ምርጫ ለ ኢትዮጵያ አዲስ ነገር አይደለም። በ እኛ እድሜ እንኳን፤ በ ንጉሡም በ ወታደሩም ሆነ በ “ነፃ-አውጪ” ተብዬው መንግሥትዓዊ ስርዐት፤ ምርጫዎች ተደርገው አይተን አለ። አንድአቸውም እሚጓጓለት ለውጥ ሲያመጡ ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም እንጅ! እናንት ሰሞነኛዎቹም ብትሆኑ አዲስ ሰዎች አይደላችሁም፤ ያ-ው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ እሚያውቃችሁ ለ 30 ዓመታት ገደማ ከ ህወሓት ጋር ሆናችሁም ሆነ በ የ አለፉት ሁለት-ዓመት ከ መንፈቅ ገደማም፤ ኢትዮጵያን ስታሰቃዩ ስትወሩ ስታስወርሩ ስታፈናቅሉ ስትዘርፉ ስትጨፈጭፉ እና ስታስጨፈጭፉ የኖራችሁ ክፉ ሰዎች ናችሁ።

ታዲያ፤ ዛሬም ድረስ ማደሪያችሁን አራት-ኪሎ ማድረጋችሁ፤ የ ጡርም ጡር ሆኖ ሊሰማችሁ ሲገባ፤ እናንተ...... እናንተ የባሰውኑ ሌላ አምስት ወይም አስር ዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆየት እያሰባችሁ መሆኑ፤ ምን ያህል የጉዶች ሃገር ሆነን መቅረትአችንን ነው ፍንትው አድርጐ የ እሚያሳየን።

እርግጥ ነው። ሰሞነኞቹ እናንተ ስለሆናችሁ፤ ለ ምርጫ መዘጋጀቱንም ሆነ ምርጫ ማድረጉን ልንከለክልአችሁ አንችልም።

ሆኖም፤ ሀ) ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መግሥት አርቃቂ እና አምላኪ የፍትህ ተቋዋም ተሸክማችሁ በተዐምር ፍትህዓዊ ምርጫን ተግባርዓዊ ልታደርጉ እንደ እማይቻላችሁ ለ) ከ ሸገር-ፓርክ ውጭ በሰላም እምትቆጣጠሩት የኢትዮጵያ ግዛት ስለ የሌለ፤ እራስአችሁም ሆነአችሁ ተፎካካሪ ተብዬ ፓርቲዎች የረባ የምርጫ እንቅስቃሴ አድርጋችሁ ነፃ ምርጫ ማካሄድ መቻል ዘበት ስለ ሆነ እና ሐ) በ ሰበብ-አስባቡ ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኞችን አስራችሁ፣ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን ከምርጫ ቦርድ አባርራችሁ፣ “ነፃ አውጪ” ተብዬዎችን እና ጠባብ የጎሣ ብሄርተኞችን ሰብስባችሁ እምታካሄዱት ምርጫ፤ የፈለጋችሁትን ያህል ብትደሰኩሩ፤ ከ[ሰው] ተርታ ሊያሰልፋችሁ እንደ እማይችል ግና፤ በ ግልፅ እንዲገባችሁ እንፈልግ አለን።

የወቅቱ የኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ችግርዖች፤ ሊደረግ በታሰበው ምርጫ አንድአቸውም እሚፈቱ አይደሉም። የ ኢትዮጵያ ሕዝብም — እስከ ዛሬ ድረስ ከ ኢትዮጵያ፤ ከ ኢትዮጵያዊዕነት እና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን ከንጥፁሃን ጐን ሲቆም ለ የአላየው ግለሰብ፤ ፓርቲም ሆነ የመንግሥት አካል፤ ሸራፋ የአመኔታ ድምፅ ካርዱን መስጠት የለበትም!

በሉ ጐበዝ፤ ለዛሬ በእዚሁ እናብቃ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# ከድጡ ወደ ማጡ!

የካቲት ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ፌብሪወሪ 2021

**አዳራሽ** – ለ የ[ሰው] ልጆች ዕድገት እና ቀጣይዕነት መተማመኛ ይሆነን ዘንድ እሚረዱ ፈርጀ-ብዙ [ኢንተሌክችዋል ትራንዛክሽን'ስ] ሞልተው አሉ። ከ እነእዚያም መሃከል፤ በዋናዕነት የ [ኢሊት'ኡን] ማኅበረሰብዓዊ ህይወት እሚዘውረው [ፖለቲካ] አንዱ ነው። እኛ፤ ለ ፖለቲካችን – ምንአልባትም ትንሽ ከ እሚገባው በላይ ትኩረት መስጠትአችን የግድ ቢሆንም – ፖለቲካውን፤ ተገቢውን መፍትሄ አምጪ እና ፍትህ-አኅናፂፊ በሆነ መልኩ የማኀልበት ተልዕኰአችን የበለጠ ተሳክቶልን በሆነ፤ ምንኛ በተደሰትን! ሆኖም ግና፤ መልሰን መላልሰን ስለ የኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ችግርያች እምንሞግተው፤ በቀዳሚዕነት [ሰው]ዕነትአችን የግድ ስለ እሚለን እና የሕዝብ እና የሃገር ህልውና ጉዳዮች መሆናቸውን'ም ስለ ዕምንዐምን፣ ችግርያችዋ እንደገና ላይመለሱ ሆነው ከመቀረፍ ይልቅ እየባሱ እየጠነከሩ እየከረሩ እና እየመረሩ ከመሄድ በ አለመቆጠብአቸው፣ ለ ወገንአችን ለውጥ አምጪ እና ፍትህ-አኅናፂፊ ሕዝብዓዊ ሃይል መፍጠር ዛሬም የግድ መሆኑን አበክረን ለማስገንዘብ ለማስታወስ ለማገዝ፣ አመኔታችንም በሕዝብ ላይ በመሆኑ እና ያ-እንን ከማድረግ ማፈግፈግም ሆነ መለሳለስ የለየለት ባሪያዕነትን አምኖ ፈቅዶ መቀበል፣ የሕዝብን ሰቆቃ እና ዕልቂት ማራዘም እና በቁም ለመሞት በእራስአችን ላይ መፍረድ እንደሆነ በፅኑ ዕምንዐምን በመሆናችንም ጭምር ነው።

እርግጥ ነው፤ የ ኢትዮጵያ ፈተናዎች እጅጉን አፀያፊ እና ኢንኮምፐረብል ናቸው። እኛ ደሞ፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባን አለ ብለን በፅኑ እንዐምን አለን። እናም፤ ሰሞነኛውን መንግሥት ተብዬ አጥብቀን እምንአወግዘው – ለምን ተዐምር አልሰራም በእሚል ሳይሆን – በዋናዕነት፤ ኢትዮጵያ ለ ዓይን-የአወጣ ቅጥፈት ላይ የተመሠረተ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ አደረጃጀት፣ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ሕገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተ ዕኩይ ፌደራሊዝም፣ የ አለማቋረጥ እየተከሠተ የአለው ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እንዲሁም ለ በሽታ፣ ለ ረሃብ፣ ለ አሉታዊ የስነልቦና ጫና መጋለጥዋን እና የእራስዋን ሕዝብ የ እራስዋን ሃገር በሁለዕንተንዓዊ መልኩ የማሠቃየት የተቀናጀ ዘመቻ እየ አካሄደ የአለ "መንግሥት" እሚገዛት ሃገር ለምን ሆነች በ እሚል ነው። እናም – ወቅትዓዊ መርህአችን ሊሆን ይገባል እምንእለው፤ [ብልፅግና] ሳይሆን – ይልቁን እስ [<u>ሰላም መረጋጋት እና ዕኩልዕነት</u>] የ እሚል መሆን እንደ እሚገባው፤ አበክረን ማስገንዘብ እንፈልግ አለን!

ትክክል፤ በደለኛዎችአችን ድብቅ አይደሉም። ይታወቁ አሉ! ዋናዎቹም፤ ስለ ፈተናችን ስንአነሳባቸው — ሰውዓዊ መብትአችሁን ስንገፍአችሁ፣ ተፈጥሮዓዊ ማንዕነትአችሁን ስንነጥቅአችሁ፣ ዳር-ድንበራችሁን ስንአስደፍርባችሁ፣ ከቀዬአችሁ ስንአፈናቅልአችሁ፣ ስንወርአችሁ፣ ስንዘርፍአችሁ፣ ስንጨፈጭፍአችሁ እና በግፍ ከገደልንአችሁ በኋላ እንደቆሻሻ በ [ሮድ-ግሬደር] በጅምላ ወደ ጉድጓድ ስንዘረግፍአችሁ – ዝም ብልአችሁ ብትፈቅዱልን፣ ከስልጣን እንድንወርድ በአትጠይቁን እና ፀጥ ለጥ ብልአችሁ ብትገዙልን፤ በሁለት/ሦስት አስር ዓመታት ከዓለም የመጀመሪያዋ የበለፀገች ኢትዮጵያን እንፈጥርእላችሁ አለን የእሚል፤ ሰውዓዊዕነት የጎደለው አረመኔአዊ የድፍረት ዝብአዝብኬአቸውን እሚደሰኩሩብን፤ በ አምባገነኑ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ የገዥው-ቡድን ጥላ ስር የተሰባሰቡት፤ የጎሣ-ፖለቲካ አምላኪ ጠባብ ድንዙዝ ፖለቲከኞች ናቸው።

ሌሎች በደለኛዎችአችንም አሉ። አላባራ ለአለው ጄኖሳይድ ቀዳሚ ተጠያቂ የሆኑ የሰሞነኛው ጎሣ ድርጅት መሪ/ነፃ-አውጪ ነን ባይ'ዖች፤ ዓይንአቸውን በ አሸቦ አጥበው፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካ እኛ እንምራ የ እሚሉንን ይጨምር አለ። እጅግኡን እምያሳፍረው ደሞ፤ እነ እገሌ እኮ ኢትዮጵያን ይወዳሉ፣ አላሰራ ስለአሉዋቸው ነው፣ ጊዜው አጭር ስለሆነ ነው፣ ቀስ እየአሉ ሕገ-መንግሥቱንም ሆነ የ ጎሣ አደረጃጀቱን ይለውጡታል፣ ጊዜ እንስጣቸው፣ በምርጫ ስለአልተመረጡ ነው፣ ዝም በሉ፣ ሲያምአችሁ አትጨሁ፣ ንፁሃን ሲጨፈጨፉ አትናገሩ አትዘኑ አታልቅሱ – የ እሚሉን፤ በእዚህ በአለፈው ሁለት-ዓመት ተ-መንፈቅ ገደማ፤ ለ የገዥው-ቡድን ሽፋን ሰጪ በመሆን በማገልገላቸው ሳቢያ፤ ሕዝብዓዊ ትግሉ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንደቸለሱበት እና እየተቀጣጠለ ለአለው ጄኖሳይድ ብሎም አይቀሬ እየሆነ ለመጣው የ ሃገር መፍረስ አደጋ ከ አምባገነኑ የ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ገዥው-ቡድን የ አልአነሰ ተጠያቂ ለመሆን – ወደው ፈቅደው ተቃቅፈው ተሰልፈው የ እሚገኙትን እንድ-አንድ የዜጋዕነት ፖለቲካ አራማጅ ነን ባይ ፖለቲከኞችን ይጨምር አለ። በ የአለፉት ሁለት ዓመት ተ-መንፈቅ ገደማ እየደረሰ የ አለው ጄኖሳይድ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ ብሎም አይቀሬ እየሆነ የመጣው የ ሃገር መፍረስ አደጋ፤ በ ህወሓት ዘመን ከነበረው እጅጉን – አዎ፤ እጅጉን የባሰ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ እየ አለ — የ ያ-ኔ የ ህወሓት መራሹን ኢህአዴግ ተቃዋሚ ተፋላሚ ነበርን ባይ'ዖች፤ ዛሬ ከ አምባገነኑ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ ጋር አንሶላ እሚጋፈፉበት ምክንያት፤ ለሃገር እና ለሕዝብ ብለው ሳይሆን፤ በተግባርም ሆነ በተልዕኮ አይደንቲካል በመሆናቸው እና የበርጩማ ፍቅር አነሁልሎአቸው መሆኑ አያጠራጥርም።

ፈተናችንን መቅረፍ አስቸጋሪ ሊሆን አይገባም! አምባገነኑ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ የገዥው-ቡድን እየሰራ የአለው ሁሉ፤ የስልጣን ጊዜውን ለማራዘም፣ የ ሰሞነኛውን ጎሣ የበላይዕነት ለማረጋገጥ፣ የ ጎሣ-ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ አደረጃጀትንም ሆነ በስራ ላይ የአለውን ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ለማኀልበት ለማስቀጠል፣ ዐማራን ለማጥፋት እና ኢትዮጵያን ለማፍረስ እንደሆነ፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ ተገንዝቦ አለ። ይ–ህ ትልቅ ድል ነው! የኢትዮጵያ ሕዝብ ለ ዓመታት እየታገለ የአለው ለ ስር-ነቀል ለውጥ ስለሆነ – የለየለትን እብሪት ትዕቢት እና መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ መንግሥትዓዊ ዕብደት፤ በዝምታ ሊያልፈው አይገባም! ውጪም ሆነ አገር-ቤት ለ አሉ፤ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ-ዓላማዋን ለእሚያከብሩ የፖለቲካ ድርጅትያች የአለውን አመኔታ እና ድጋፍ በተግባር የበለጠ ቢያጎለብተው፤ የትግሉን ስኬትአማዕነት እንደእሚያፋጥነውም በፍፁም አንጠራጠርም። እናም — ምርጫው ይሰረዝ፣ በ ዐማራ ላይ እየተፈፀመ የአለው መዋቅርዓዊ መንግሥትዓዊ ጄኖሳይድ ዛሬውኑ ይቁም! ኢትዮጵያዊ የጋራ ፍትሕ-አኅናፂፊ የምክክር ሂደት ይጀመር፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት። በተጨማሪም፤ ዐማራው እነ ማን እነ ማን እንደጠላት እንደእሚቆጥሩት እና ሊያጠፉት ቆርጠው መነሳታቸውንም በግልፅ ይነገረው። ተጠንቅቆ ነቅቶ እንዲጠብቅም፤ እንደአመቺነቱ ይደራጅ ይታገዝ። ዝም ብሎ መጨፍጨፉ ያብቃ! አዎ፤ እንደ-እኛ እንደ-እኛ፤ ምርጫው ቢሰረዝ አልያም ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ቦይካት ቢያደርጉ እንመርጥ አለን። ያ-ም ከአልተሳካ፤ ለከፉም ለደጉም – ይደረጋል ለተባለው ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ ይዘጋጅ — ማንን መምረጥ እና ማንን አለመምረጥ እንደአለበት ጠንቅቆ እንዲአውቅ የአላሰለሰ ቆራጥ ዘመቻ ይደረግ።

መሠረትዓዊ ጉዳይያችአችንን ሰብሰብ አድርገን ስንአገናዝብ — የገዥው-ቡድን አባልዐት የረባ ነገር እንደ እማይሰሩ እና አያያዛቸውም አደገኛ እንደሆነ፤ ገና ዓመት ሳይሞላቸው ጀምረን ስንነግርአቸው ቆይተን አለ። ዛሬ [ጊዜ] እየመሰከረልን የአለው፤ ትክክል መሆንአችንን ነው። ተቋምዓዊ መዋቅርዓዊ በሆነ መልኩ የተተገበረ፤ ያ-እንኳን ባይሆንእልአቸው አዝማሚያቸውን የ አሳየን፤ ለ [<u>ሁልአችንም</u>] እሚበጅ፤ አንድአችም ቁም ነገር ሳይሰሩ – ይሄውእና ሦስት ዓመት እየሞላቸው ነው። ዝ-ገደደ፤ በትጋት ሌት-ተ-ቀን እየሰሩ የአለው ሁሉ – ኢትዮጵያን እሚጎዱ መሠሪ ስራዎችን ብቻ በመሆኑ — ተጨማሪ

ጊዜ ከተሰጣቸው፤ ከእዚህ የባሰ ሰቆቃ ዕልቂተና የሃገር መፍረስ አደጋ እንደእሚአስከትሉብን ምንም ጥርጥር የለውም። ይ-ህ እንን አምኖ ለመቀበል የ እሚቸገር ወይም ከ ሕዝብ ጎን በመቆም ስር-ነቀል ለውጥ ለማምጣት ቆርጦ ለመታገል እሚያቅማማ ኢትዮጵያዊ፤ ነገ ኢትዮጵያዊ እሚለው ሕዝብ እና ኢትዮጵያ የ እሚላት ሃገር እንደእማይኖረው እና የመፀፀቻ ጊዜ እንኳን እንደእማያገኝ ከአሁኑ እንዲአውቀውም እንፈልግ አለን።

*ዕመኑን – መርዘኛው በደለኛ፤ ለ የጎሣ-ፖለቲካ፣ ለ አክራሪ የጎሣ-አደረጃጀት እና በቋንቋ በጎጥ ላይ ለተመሰረተው ዕኩዩ ፌደራሊዝም መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ መደላድል የሆነው፤ ገኘው-ቡድን አራት-ኪሎ [ሰርጥ] ውስጥ ደብቆ እየተንከባከበው እየአጎለበተው የአለው፤ በ ህወሓት-ኦነግ የተቀረፀው ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ነው! አምባገነኑ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ገኘው-ቡድን፤ ለ እራሱ ህልውና ሲል ስር-ነቀል ለውጥ ለማምጣት ፈቃደኛ ሆኜአለሁ ማለት ከፈለገ፤ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት ከ ምድረ-ገፅ መደምሰሱን <u>በተግባር</u> በማሳየት ሊያረጋግጥእልን የግድ ነው – ከምርጫው በፊት! አለበለእዚያ – ምርጫው፤ [የ ህወሓትን ፀረ-ኢትዮጵያ አገዛዝ] ለ [ኦዴፓ-ኦነግ ፀረ-ኢትዮጵያ አገዛዝ] አስረክቦ አጠናክሮ ለማስቀጠል የ እሚደረግ መንግሥትዓዊ ወንጀል ከመሆን አይአልፍም — የ እኛ ሰው፤ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲል።*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

የወገንአችን ጉዳት እየከፋ እየመረረ እንደሄደ እናውቅ አለን። እየደረሰ የአለውን ሰቆቃ እና ዕልቂት በሰማን ቁጥር፤ ልክ እዚያው አብረንአችሁ የአለን ያህል ነው እሚሰማን። ሁሌም ቢሆን እንአስብአችሁ አለን። ፈጣሪ ፈተናችንን በቃ እንዲለን እና ሁልአችንም አፎይ እንል ዘንድ የ ዕለት-ተ-ዕለት ፀሎትአችንም ነው። የምን ጊዜም ወገንአችሁ ነን እና በፅናትአችሁ እንኮራ አለን፣ ልክ እንደ ጥንት'ኡ እንወድአችሁ አለን — አይዞን!

ከ እዚህ በመቀጠልእም፤ በቅርቡ የተከሰቱ ጉዳይዎችን ምክንያት በማድረግ እምንለውን ብለን፣ በደለኞችአችን እየተናበቡ እሚያነሱአቸው አንድ-አንድ ነጥብዎች ላይ ምልከታችንን አስፍረን፣ በመጨረሻም፤ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባ አለ እምንልአቸውን ነጥብዎች እናጋራችሁ ዘንድ፤ በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበን አለን።

እናም፤ “አብረን እንቆይ” – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

1. <u>በቅርቡ የተከሰቱ ጉዳዮች፤</u>

አዳራሽ፤ የሃሣብ ማንሸራሸርያ መድረክአችን – ወርሃዊ በመሆንዋ፤ በ ሃገርአችን ስለእሚፈጠሩ ክስተትዎች፤ የ እሚሰማንን ስሜት እና የአለንን ምልከታ በ ሪል-ታይም እንአካፍል ዘንድ አትመችም። በአመዛኙ፤ ስሜትአችንን እምንገልፀው እና ሃሳብአችንን እምንገአጋራው፤ ረፈድ አድርገን መሆኑም፤ አልተመቸንም። የ አንድ ቀን ርዝመት፤ [ሃያ-አራት ሰዓት] ሳይሆን [ሃያ-አራት ሰከንድ] እየሆነብን መቸገር የጀመርነው፤ ገና በወጣትዕነት ዕድሜአችን ነበር እና፤ ዛሬ-ዛሬ ቢብስእብን አትፍረዱእብን።

ያ-ም ሆኖም ታዲያ፤ በ እየ ዕለት'ኡ በ እምንአነብበው፣ በ እምንሠማው፣ በ እምንአየው ሰቆቃ እና ዕልቂት ልብአችን ክፉኛ የተሰበረ መሆኑን እና ያ-እንን ማስቆም እሚአስችል አቅም ተፈጥሮ በ አለማየትአችን – ሁሌም እንአዝን አለን!

አዎ፤ በ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ገዥው-ቡድን ቀጥተኛ ተሳትፎ የተደረገ እና እየተደረገም ያለው መንግሥትዓዊ መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ ጄኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ በብዙ የኢትዮጵያ ግዛትዎች ውስጥ በተለይም በ ወለጋ፣ በ መተከል እና በ ማይካድራ፤ በንፁሃን ምስኪን ዐማራ ወገንዎችአችን ላይ የደረሰውን እና የአለማብአራት እየደረሰም የአለውን ሰቆቃ እና ዕልቂት – እንዲሁም በቅርብኡ በ ህወሓት በተጫረው የለየለት ጦርዕነት ሳቢያ፤ በሁለቱም ጎራ የአሉት ተዋጊዎችን ጨምሮ – በትግራይ፤ በንፁሃን ወገንዎችአችን ላይ እንደደረሰ የ እማንጠራጠረውን ሁለዕንተንዓዊ ሰውዓዊ ቀውስ ማሰብ፤ ሃዘንአችንን እጅጉን አግዝፎት አለ!

እኛ፤ ከአገርቤት ከመልቀቅአችን በፊት፤ በልጅዕነትአችንም ሆነ በ እየሙያ መስክአችን ከተሰማራንም በኋላ — መሃል ሃገርን ጨምሮ፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከ ምዕራብ እስከ ምሥራቅ፤ በዛ የአሉ ከተማዎችን ኖረንእባቸው እንናውቅ አለን። ጊዜው እየረዘመ ቢመጣም ቅሉ፤ ስለ እየአንድ-አንዱ ከተማ እና ነዋሪው ሕዝብ የነበሩንን በፍቅር የተሞሉ ትዝታዎችአችንን፤ ዛሬም ቢሆን ማውራት ከጀመርን፤ ማቆሚያ የለንም። አለመታደል ሆኖ፤ አሁን አሁን ጨዋታዎችአችን ሁሉ፤ ከ ዕንባ ጋር እየተቀላቀሉ፤ አብዛኛውን ጊዜ – በአግባቡ ሳንእሰነባበት እንለያይ አለን።

አዎ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰውዓዊ መብቱን ከአልተገፈፈ፣ ሰላም ከአልአጣ፣ ማንዕነትኡን ከአልተነጠቀ፣ ሃይማኖትኡን ሰንደቅ-ዓላማውን ከአልተዳፈሩበት፣ የሃገርኡን ዳር-ድንበር ከአልአስደፈሩበት – ከመንግሥት ተብዬዎች ብዙም ሳይፈልግ፤ ጥሮ-ግሮ መሬት ጭሮ የ እሚኖር፣ ለመደሰትም ሆነ ለመርካት ብዙም እማይፈልግ፣ የአለው-የሌለውን ለማካፈል እማያቅማማ፤ ንፁህ ነፍስ የተጐናፀፈ ቀና ርሁሩሁ ሰላምዓዊ እና ጀግና ሕዝብ ነው። ትክክል፤ ይህእንን ሕዝብ፤ አይደለም መጉዳት – አለመውደድ፣ ሲሰቃይ አለማዘን አለማገዝ እና [አይዞን] አለማለት፤ የ-ለ-የ-ለ-ት ድንዙዝዕነት ነው!

አዎ፤ በተለያየ አጋጣሚ በመንግሥትዕነት ቦታ ላይ ለመወዘፍ አጋጣሚው ለተመቻቸላችሁ ፍጡራን፤ [ሰው] ብትሆኑ፤ ከአቅም በላይ የሆነ ብዙም ሳይጠበቅእባችሁ፤ የ ሕዝብን ህይወት ለማሻሻል እሚአግዙ የተወሰኑ ነገሮች ላይ አተኩርአችሁ ብትሰሩ ኖሮ፤ አልያም እንድንአተኩር ሰላም አግኝተን ቢሆን ኖሮ፤ የት-እና-የት በደረስን ነበር።

የ ማኅበረሰብዓዊ ህይወት እየሰፋ እየአደገ በመጣ ቁጥር፤ ደግም ክፉም አብሮ እየሰፋ እየአደገ መሄዱ አይቀሬ ቢሆንም – በ ኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያዊያን ላይ እየደረሰ የአለው ሰቆቃ እና ዕልቂት፤ በየትእኛውም ጤናማ መመዘኛ ተቀባይዕነት ሊኖረው እማይገባ፣ ቀስ እየአለ ይወገድአል እየተባለ ውሎ እንዲያድር ሊፈቀድ እማይገባ — የ ሕዝብ እና የ ሃገር ህልውና የ [ሰው]ዓዊዕነት ጉዳይ ነው።

እንደ አለመታደል ሆኖ – በተለይ በ የአለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት ገደማ፤ ኢትዮጵያ ላይ የተጫናችሁባት መንግሥት ተብዬዎች፤ ተሸቀዳድምአችሁ የሰራችሁት እና ዛሬም ቢሆን እየሰራችሁ የአላችሁት ነገር ቢኖር፤ ሰውዓዊ መብቱን መንፈግ፣ ሰላምኡን ማስአጣት፣ ማንዕነትኡን መንጠቅ፣ ሃይማኖትኡን ሰንደቅ-ዓላማውን መዳፈር፣ ከ የሌለችው አቅም ሃብት ንብረቱን መዝረፍ፤ ወገንን ከወገን ማጣላት እና የሃገርኡን ዳር-ድንበር ማስደፈር ላይ ነው።

እናም፤ መንግሥትዓዊ ወንጀልዖች በ ገለልተኛ አካልዐት ይጣሩ እሚለውን የ ወገንዖቻችንን ጥሪ እንደ ፕሪንስፕል እምንደግፈው ቢሆንም ቅሉ፤ ሊሆን ይገባል ብለን በፅኑ ዕምንዐምነው ግና፤ ጨፍጫፊው የ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ የ ገዥው-ቡድን ዛሬውእኑ ከስልጣን መልቀቅን እና ለፍርድ መቅረብ የአለበት መሆኑን ነው – አራት ነጥብ

2. <u>በደለኞችአችን እየተናበቡ እሚያነሱአቸው ነጥብዖች፤</u>

በመቀጠልም፤ ጊዜ የአነሳቸው በደለኞችአችን እየተናበቡ ከ እሚያነሱአቸው ነጥብዖች መሃከል ለዛሬ በሃሳብአችን ነቅሰን ከአወጣንአቸው ውስጥ ሁለት’ኡን እንዳስስ አለን — ላይ ላዩንእም ቢሆን።

*ሀ) የጎሣ-ፖለቲካ እና ሕገ-መንግሥት*

የጎሣ-ፖለቲካን እና ሕገ-መንግሥትኡን በተመለከተ፤ በአጠቃላይ ስለ ኢ-[ሰው]ዓዊዕነትአቸው፤ በቀረቤታም ፀረ-ኢትዮጵያ፣ ፀረ-ኢትዮጵያዊዕነት እና ፀረ-የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ መሆንአቸው፣ ተየህ ቀደም ብዙ ብለን አለን እና ዛሬ አንደግመውም። የ ኢትዮጵያ ሕዝብ የታገለውም ሆነ እየታገለ የአለው፤ ሙሉ በሙሉ እንዲወገዱ እና በአዲስ የአስተዳደር ስርዐት እና በአዲስ ኢትዮጵያዊ ሕገ-መንግሥት እንዲተኩ ለማድረግ መሆኑንም – እንዲሁ!

የጎሣ-ፖለቲካን እና በስራ ላይ የአለውን ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት በተመለከተ እየተናበቡ የ እሚያንቆለጳጵሱ ጊዜ የአነሳቸው በደለኞችአችን፤ ከ ሁለት ምንጭ ይቀዱ አሉ። ፊት ለፊት ቀማሪ፣ ዕድሜ-ልክአችወን ተግባርኢ፣ አራማጅ፣ ድጋፍ ሰጪ፣ ዋስ ጠበቃ ለመሆን መሃላ የፈፀሙት እና ለውጥ ፈላጊ ተብዬ ምክንያት ደርዳሪዎች።

*ቀማሪ፣ ዕድሜ-ልክአችወን ተግባርኢ፣ አራማጅ፣ ድጋፍ ሰጪ እና ዋስ ጠበቃ ለመሆን መሃላ የፈፀሙ፤*

በግልፅ ፀረ-ኢትዮጵያ ተልዕኮ የአላቸው መሆኑን እሚነግሩን፤ የጎሣ-ፖለቲካው እና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው ሕገ-መንግሥት የአመቻቸላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም፤ እነእርሱ እንደፈለጉት እሚያሽከረክሯት ኢትዮጵያን ለመፍጠር፤ ያ ከአልተሳካላቸውም አንድ ቀን ተገንጥለው የእየእራስአቸውን ሃገር እንፈጥርአለን እሚል ቅዠት ውስጥ የተዘፈቁት፤ ህወሓት፣ ኦነግ፣ ሌሎች ርዝራዥ ነፃ-አውጪ ተብዬ ድርጅቶች እና ጠባብ የጎሣ-ፖለቲካ አራማጅዖች ናቸው። ጎበዝ፤ እነእዚህ በምንም መልኩ እሚታረሙ እሚማሩ አይደሉም። በእሚገባ ተደራጅቶ ተዘጋጅቶ ከመታገል ሌላም አማራጭ የለም። የፖለቲካ ተፈጥሮአቸው፤ ዋሾ አጭበርባሪ አስመሳይ ስግብግብ ከሃዲ መሠሪ አረመኔ አድርጎ ስለፈጠረአቸው፤ ኢትዮጵያችንን እንደአሻአቸው እንዲአሽከረክሩአትም ሆነ እንዲያፈርሷት ልንፈቅድእላቸው አይገባም — በፍፁም!

*ለውጥ ፈላጊ ተብዬ ምክንያት ደርዳሪዎች፤*

በ እዚህ ጐራ፤ የቅርብኡ የጎሣ-ድርጅቶች ስብስብ የሆነው ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ገዥው-ቡድን እና የተወሰኑ የዜጋ-ፖለቲካን እንአራምድአለን ባይ ደጋፊዎችአቸው [ባለሟልዖችአቸው ለ አለማለት ብለን ነው] ተቃቅፈው እንአገኝአቸው አለን። ተግባርዕን በተመለከተ፤ እነእዚህ ሁለት’ኡ የ አንድ [ኢ-ቨል] ሁለት ገፅታዎች ናቸው!

ምክንያትዖቻቸውም፤ [የ ጎሣ-ፖለቲካውን እሚመርጡ እሚፈልጉ አሉ፣ ለ 30-ዓመትዐት ያህል ተግባርዓዊ መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ ስለሆነ አሁንእኑ ማስወገድ አስቸጋሪ ነው፣ ሕገ-መንግሥቱን በአዲስ ከእምንለውጠው የአለውን እንአሻሽለው፣ ቀስ እየአልን እንለውጠው፣ ማንዴት’ኡ የለንም፣ ከምርጫ በኋላ እንለውጠውአለን] እሚሉትን ሁሉ ያካትቱ አሉ – በዋናዕነት።

እኛ ታዲያ – ትክክል፤ የጎሣ-ፖለቲካውንም ሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት እሚመርጡ እሚፈልጉ ሊኖሩ እንደእሚችሉ እና እንደአሉ የአደባባይ ምስጢር ነው። ግና፤ ከ ብዙ መቶ-ፐርሰንት በላይ በሆነ መጠን የ እምንበልጥአቸው፤ የጎሣ-ፖለቲካውንም ሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት እምንፀየፍ ኢትዮጵያዊያን አለን፤ ነው እየአልንአቸው የ አለነው። እነኝህ ፍጡራን [ለመታረቅ] ከፈቀዱ፤ እስቲ <u>አፈናውን</u> ያቁሙ እና – ኢትዮጵያን እምትሉ፣ የጎሣ-ፖለቲካውንም ሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት ከ ምድረ-ገፅ እንዲጠፉ እምትመርጡ ሰልፍ ውጡ ተብሎ፤ የእሚወጣውን ሕዝብዓዊ ማዕበል ይመልከቱ!

ጐበዝ፤ ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ እነእርሱ የጎሣ-ፖለቲካውንም ሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት እሚመርጡ እሚፈልጉ አሉ ሲሉን፤ በትክክል እየአሉን የአሉት – ዛሬ ጉልበት [ታንክ’ኡም ባንክ’ኡም] የአላቸው [ሰሞነኞች] የ የጎሣ-ፖለቲካውንም ሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ የ ሆነውን ሕገ-መንግሥት ፈጣሪ ተግባሪ ጠባቂ ባለቤቶች እንደሆኑ እና – በቀናዕነት ኢትዮጵያን እሚለው ወገን፤ በ የሃሳብ “ቡጢ” እንደ እሚዘርርአቸው በእሚገባ ቢያውቁትም ቅሉ፤ በጉልበት ግና ስለእማታሸንፉአቸው ዝም ብላችሁ ተገዙ እየ አሉን ነው የአሉት። ወይ ነዶ!

እኛ ታዲያ – ትክክል፤ ዛሬ ጉልበት የአላቸው ይመስል አለ። ግና፤ ሕዝብ እስከጠላቸው፣ አንቅሮ እስከተፋቸው ድረስ፣ ግፈኛዎች እስከ ሆኑ ድረስ፤ የፈለገውን ያህል ጉልበት ቢኖርአቸውም – ከ ሕዝብ ሃይል እና ከፈጣሪ መለኮትዓዊ ፍርድ በላይ ሊሆኑ አይቻልአቸውም፤ ነው እየአልንአቸው የአለነው። በ የአሳለፍንአቸው ሁለት ወርዐት፤ የሃገርዐቱ ህብረት፣ አንድ-አንድ ዓለማቀፍ ተቋምዐት እና አንድ-አንድ ሃገርዐት – ህወሓት እሚሸነፍ ስለአልመሰላቸው ነበር፤ ድርድር ምናምን እየአሉ ኊሴንሻሊ ከህወሓት ጐን የቆሙት። አሁን-አሁን ግና ከሕዝብ ሃይል እና ከፈጣሪ መለኮትዓዊ ፍርድ በላይ

መሆን በፍፁም እንደእማይቻል በተግባር በማየትአቸው፤ ስህተተኞች እንደሆኑ በደንብ ሳይገባቸው አልቀርቶም።

ጨፍጫፊውን የኸሮው-ቡድን እና የ ጎሣ-ፖለቲከኛውን አጓጉል አግዝፋችሁ እምትአዩት የገኸሮው ቡድን አባልዐትም ሆነ ደጋፊዎችአቸው፤ ግምኛ ስሁት እንደሆናችሁ እምትገነዘቡበት ጊዜው ዕሩቅ እንደእማይሆን ልንነራችሁ እንወድ አለን።

ጐበዝ – የቅጥፈት ተረከአቸውን፣ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩዩ ፌደራልዝምን፣ የአኖሌን ሃውልት እና የመሳሰሉትን ስንአስብ – ትክክል፤ ለ 30-ዓመትዐት ያህል ተግባርዓዊ መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ ስለተደረገ አሁንእኑ ማስወገድ አስቸጋሪ ደረጃ ላይ የአደረሱት ሊመስልአቸው ይችላል።

እነእዚህ ፍጡራን ሊያስታውሱ የ እማይፈልጉት ግና፤ የ ብዙ ሺህ ዓመትዐት ፅኑ መሠረት የአለአትን፣ ዜጋዕነት ላይ የአተኮረ ስርዐትን ብቻ እሚያውቀው ዕልፍ-አዕላፍ ቀና [ንፁህ ነፍስ] የአለው ትውልድን፣ ኢትዮጵያዊ መንግሥትዓዊ መዋቅርዐት እና ተቋምዐት የነበርአትን የተከበረችዋ ኢትዮጵያ’ን፤ ህወሓት እና ኦነግ ዛሬ ወደ የአለችበት አፀያፊ ዘግናኝ ደካማ ቁመና [“በአንድ ጨረቃ”] የቀየርዋት የመሆኑን ዕውነታ ነው — ዕኩይ ተልዕኰአቸውን፤ ሕገ-መንግሥትዓዊ በማድረግ!

እኛ – [ሕገ-መንግሥቱ ይለወጥ፤ የለም ይሻሻል] እሚለው አተካራ አይጥመንም። ተለወጠም ተሻሻለ፤ ፀረ-ኢትዮጵያ፣ ፀረ-ኢትዮጵያዊዕነት እና ፀረ-የኢትዮጵያ ሕዝብ [የሆኑ፣ ሊሆኑ የአሰቡ፣ ሊሆኑ የማሰብ ፍላጎቱ የአላቸው] ምዕራፍዖች አንቀፅዖች ንዑስ-አንቀፅዖች አረፍተ-ነገርዖች እና ቃላት፤ ሙሉ በሙሉ ተንነው እንዲጠፉ ነው እምንእታገልኸው። አዎ፤ የጎሣ-ፖለቲካ በሕግ እንዲገደብ ነው እምንእታገልኸው — ለ ኢትዮጵያችን ሴፍ-ጋርድ በመሆን እንዲጠቅምአት!

እኛ – ስር-ነቀል ለውጥ [አሁን!] ስእንል፤ የእምንፈልገው ለውጥ የቅንጦት ሳይሆን የህልውና ጉዳይ እንደሆነ በድርብ ድርብርብ የጎሊና ሰረዝ አፅንዖት ሰጥተንበት ለማለፍ እና ውጤቱን ሳይሆን፤ ቁርጠኛዕነትአችንን እይሚያሳዩ ለመተማመኛ ያህል እሚተገበሩ አዝማሚያቸውን ፍላጎትአቸውን መደላድልአቸውን ሊጠቁሙ እሚችሉ ጅማሮዎችን በተጨባጭ እሚአሳዩን፤ ከጎሣ-ፖለቲካ እና መዘዙ እምንእላቀቅበት መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ እንቅስቃሴዎች መታየት ይ-ጀ-መ-ሩ እየ አልን ነው።

ከ የቅጥፈት የማታለያ ናሬቲቭ’ስ ውጪ፤ በገኸሮው-ቡድን ሌት-ተ-ቀን በትጋት በተግባር እየተሰሩ የአሉት ሁሉ ግና – በተቃራኒው፤ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያዊዕነትን እና የ ኢትዮጵያን ሕዝብ እሚጎዱ – ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገመንግሥት እና በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተውን ዕኩዩን ፌደራልዝም እሚያጎለብቱ እሚያስቀጥሉ፣ መሠሪ ስራዎችን ብቻ የመሆኑ ዕውነታ፤ እጅጉን አሳፋሪ ነው!

*ለ) በቅርቡ ይደረግ አለ እየተባለ ስለ እሚወራለት ምርጫ*

ከ ሁለዕንተንዓዊ ግንዛቤ ተነስተን፤ ከሂደቱ ጀምሮ የተአሰበውን ምርጫ መተግበርን፤ እንደ ስሁት አደገኛ እርምጃ እንደ እምንቆጥረው ተየህ በፊት በግልፅ የተናግረን ቢሆንም፤ ስለ አንድ ጉዳይ ትንሽ እንድንእል ፍቀዱልን።

የጎሣ-ድርጅትዖች ስብስብ የሆነውን ገኸሮው-ቡድንን እና የዜጋ ፖለቲካን እናራምድ አለን ባይ የተወሰኑ ደጋፊዎችአቸውን – ለምን ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት አንድ-ነገር አንአደርግም? ለምን በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረትውን ፌደራሊዝም አንድ-ነገር አንአደርግም ስንልአቸው፤ ማጭበርበሪያ እና ጊዜ-መግዣ ይሆንአቸው ዘንድ፤ “በ ምርጫ የተሰየመ መንግሥት ስለአልሆነ እና ማንዴቱ ስለየሌለው፤ ምርጫው ተደርጐ ሕግዓዊ ማንዴት እና አስተማማኝ ሌጂትመሲ እሚላበስኸው መንግሥት፤ ተገቢውን ስር-ነቀል ለውጥ እሚያመጡ እርምጃዎችን ይወስዳል” ይሉን አሉ።

ጎበዝ፤ የጎሣ ፖለቲካቸው ስር-እንዲሰድ የእሚረዱአቸው ጉዳይዖችን ሁሉ፤ በሕዝብ አልተመረጥንም፣ ማንዴቱ የለንም ሳይሉ፤ እየተጣደፉ ሌት-ተ-ቀን እየተገበሩ ለመሆንአቸው ምስክርዕነቱን እና ፍርዱን ለሕዝብ እና ለፈጣሪ ሰጥተን፤ [አይበለው እና] ምርጫው ተደረገ ብንል እንኳ፤ ተየህ-ቀደም በጠቀስንአቸው ምክንያትዖች ሳቢያ – በተዐምር ፍትህዓዊም ሆነ ነፃ ሊሆን ይቅር እና አጠገቡም ሊደርስ ስለእማይችል – እናገኙአለን እየአሉ የ እሚቋምጡለት ሌጂትመሲ፤ [ፎ-ሌጅትመሲ] ሲውዶ-ሌጅትመሲ፣ ኢሚቴትድ-ሌጅትመሲ ወይም የአራዳ ልጆች የቁጩ-ሌጅትመሲ ሊሉት እሚችሉት ዓይነት ከመሆን እንደ እማያልፍ ልንነግርአቸው እንወድ አለን — ከወዲሁ ቁርጥአቸውን ያውቁት ዘንድ!

3. <u>ትኩረት ይደረግባቸው የ እምንልአቸው ነጥብዖች፤</u>

የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ የኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ችግሮች፤ የጎሣ–ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ–ፖለቲካ አደረጃጀት እና ፀረ–ኢትዮጵያ የሆነው ሕገ-መንግሥት ናቸው። ሌላው ሁሉ ዕዳው ገብስ ነው።

የ ጥቁር ሕዝብ ኩራት፤ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዓላማ፤ ወደ የክብር ቦታው ይመለስ ዘንድ መታገል፤ የግድ ነው። ሕዝብዓዊ ሰላምዓዊ ትግል የበለጠ ተጠናክሮ ይቀጥል። ጀኖሳይድ’ኡን አሁን’እኑ እንዲቆም ማድረግ እና ግፉአንን መታደግ ላይ እንረባረብ።

ጨፍጫፊው ብልፅግና ፓርቲ የሕዝብን ስልጣን ለሕዝብ መልሶ እንዲአስረክብ በግልፅ ይነገረው። ሃገርዓዊ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ጉባኤ ይደረግ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት። ሕዝብ — የአሰቃዩትን የጨፈጨፉትን፤ ሲሰቃይ ሲጨፈጨፍ ዝም ብለው የተመለከቱትን የገፋፉትን የተሣተፉትን በደለኛዎቹን ጠንቅቆ በመለየት፤ ሽራፊ የአመኔታ የድምፅ ካርዱን እንድአይሰጣቸው፤ በእሚገባ ይምከር ይዘጋጅ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

--- እንደገና እስከ እምንገናኝ ---

# ምርጫ....... ለምኔ?!

መጋቢት ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ማርች 2021

**አዳራሽ** – ኢትዮጵያዊያን፤ እንደ የሉዐላዊት ሃገር ሕዝብ – በዘመናት የአረፈደ ቢሆንም፤  ውስጥአችንን በእሚገባ መመርመር፣ ማጥራት እና ማቃናት ከምን ጊዜውም በላይ የግድ የ እሚለን ጊዜ ላይ እንዳለን በፅኑ ዕንዐምን አለን – በተለይም [ኢሊት'ኡ]። የ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት ፈር ቀያሽዕነት፣ አልሚዕነት፣ አጥፊዕነት እና ተጠያቂዕነት የተጫነው በ ኢሊት'ኡ ትከሻ ላይ ከመሆን አያልፍም እና! ሊሆን እሚገባው ተልዕኰዉም፤ በ አመዛኙ በ 1960'ዎቹ የተጀመረውን የ[ዕውነትኛ ፍትህ] የ[ዕውነትኛ ነፃዕነት] የ[ዕውነትኛ ዕኩልዕነት] ጥያቄዎች፤ እንዲያብቡ እና እንዲያፈሩ፣ እየ አንድ-አንዱ ዜጋ እንደ [ሰው] እንዲቆጠር፣ መለኮትዓዊ [ረቂቅ] ፍጡርዕነቱን ምሉዕ በሆነ አግባብ ማጣጣም እንዲቻለው፣ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ ለማሳደግ እና [ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ ስር ያደርግ ዘንድ፤ የ እየድርሻውን አበርክቶ ማለፍን ነው።

የ [ሰው] ዘር – እራሱን፣ ሌሎች ፍጡራንን እና አካባቢውን ለማወቅ ለመቆጣጠር ለመቀየር፤ በፈነቀላቸው ቁጥር-ስፍር የሌላቸው ድንጋዮች አማካኝዕነት ከአመጣቸው የ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት ስኬቶች ውስጥ፤ ዲሚክረሲ አንዱ ነው። ዲሚክረሲ ብቻውን፤ ለሁሉም የ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት ፈር የአለመያዝ ችግሮች፤ መፍትሄ እንደሆነ አድርጐ መቁጠር፤ ትክክል ባይሆንም ቅሉ – በቀናዕነት ከተቀመረ ከተተገበረ ግና፤ እየ አንድ-አንዱ ዜጋ እንዴት መተዳደር እንደእሚፈልግ ለመምረጥ፤ [ፍትህዓዊ እና ነፃ] በሆነ መልኩ በዕኩልዕነት የመሳተፍ መብቱ እንዲጠበቅለት እና በዛ የአሉ የ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት ችግሮች ይፈቱ ዘንድ– ዕውነተኛ ዲሚክረሲ በትክክል ይመራናል።  "የ ሕዝብ መንግሥት፣ በ ሕዝብ እና ለ ሕዝብ" በ እሚለው መርህ፤ [ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ ከ አረመኔዎች፣ የማፍያ ቡድኖች፣ በሽተኛ ፖለቲከኞች እና አምባገነኖች መዳፍ እንዲነጥቅ፤ ዕውነተኛ ዲሚክረሲ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደእሚያደርግም ዕሙን ነው። ምርጫ – የ ዲሚክረሲ ዕምቅ እስትንፋስ  ነው። አዎ፤ ጊዜ ፈጥረን – የ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት አስተዳደር ስርዐትን ወደ የዓይን ብሌንአችን ቀረብ ጐላ አድርገን ብንመረምር፤ በ ዲሚክራሲ ኒዉክልየስ ውስጥ እንደ (ዲ-ኤን-ኤ) ምርጫን እናያለን። በ ሰውዓዊ መብቶች ዲክለሬሽንስ ውስጥ "የ መንግሥት ስልጣን እሚመሠረተው በእየወቅቱ በእሚደረጉ ዕውነተኛ ምርጫዎች በኩል በእሚገለፅ – ሕዝብዓዊ ፍላጎት እና ሕዝብዓዊ ፈቃድ ነው" እሚል ሃሣብም ሰፍሯል። በደንብ ወደ ውስጥ ቀረብ ጐላ አድርገን ብንመለከት ደሞ፤ በምርጫ ቁመና ላይ እንደ (ኒውክሊዮታይድስ) – ሕዝብዓዊ ተልዕኮን የአዘሉ መመሪያዎች በአግባቡ እንዲተላለፉ እሚያደርጉ ንጥረ-ነገሮችን – ማለትም፤ መንቃት፣ መደራጀት፣ መተባበር እና ድምፅ-መስጠት ተካተው እናያለን። ድምፅ-የመስጠት መብት፤ ለሃገርዐት ዲሚክረሲዓዊ ስርዐት ፅኑ መሠረት እንደሆነም፤ ዕውነትኛ ዲሚክረሲ አለማወላዳት ያስገነዝበናል። በፈቃደኛዕነት ድምፅ-መስጠት – መንግሥትን የመቅረፅ፣ የመገሰፅ፣ የመቀየር እና የማባረር ዓይነተኛ ሕዝብዓዊ መሣሪያ ነው።

ትክክል። በማህበረሰብዓዊ ህይወት ውስጥ – ዲሚክረሲዓዊ መንግሥት ምስረታም፣ የ ምርጫም ሆነ በፈቃደኛዕነት ድምፅ-የመስጠት መብትን ዕውን ማድረግ፤ ቀላል እንዳልነበረ እና እንዳልሆነ፣ መስዋዕትዕነት ያስከፈለ እና እየአስከፈለም እንደአለ ዕሙን ነው — ለ የ[ሰው] ዘር ዕድገት እና ቀጣይዕነት ዋስ-ጠበቃ መሆኑም ጭምር። ዕብሪተኞች እና አምባገነኖች፤ የምርጫን እና የድምፅ-መስጠት መብትን አንደ አልባሌ መቁጠራቸው እና [ዳሜጅ] ሊያደርጉት ወደኋላ እማይሉ መሆናቸውም፤ የ ፖለቲካዊ ተፈጥሯቸው ምንዕነት ነው። በተጨማሪም፤ በ ፖለቲካ ዙሪያ የአሉ ባህሪያት (ኢንቫይሮንመንታል ቬሪየብልስ)፣ እንደ [የዜጎች ንቃት፣ የፖሊሲ ቀመሮች፣ የብዙሃን መገናኛዎች፣ የደጋፊዎች/የተቃዋሚዎች የምርጫ ዘመቻ፣ የሃሣብ አራማጆች፣ ማስፈራሪያዎች፣ ማጭበርበሮች] እና ሌሎችም፤ የ እያንድአንዱ ዜጋ የአመኔታ-ድምፅ አሰጣጥ ዳይናሚክስ እና ውጤታቸው ላይ አዎንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ ያሳድራሉ። የ መራጭዎችን ውሳኔ ወደ አንድ ተወዳዳሪ ግለሰብ/ፓርቲ እንዲያዘም እሚገፋፋው ምክንያት የቱም-ሆነ-የቱ፤ ሁሉም መራጭ እሚጋራው አንድ [ፈተና] መኖሩም አይካድም። ያ-ም ፈተና፤ እርግጠኛ መሆንን አዳጋች እሚያደርጉ በዛ የአሉ ሁነትዖች የመኖርአቸው ዕውነታ ነው – [አንሰርተንቲስ]። እኮ እንዴት የአሉ እንደሆን፤ የተወዳዳሪዎችን ተጨባጭ ማንዕነት/ምንዕነት፣ ለአቋምአቸው የአላቸውን ፅናት ተዐማኒዕነት እና ስኬትአማዕነት፤ እንዲሁም ከምርጫው በሁዋላ እሚከሰቱ ሁለዕንተንዓዊ የ ማሕበረሰብዓዊ ህይወት አግባብ-ነገሮችን በእሚገባ ማወቅ መተንበይ፤ እጅጉን አዳጋች መሆኑን መጠቃቀስ ይቻላል።

የምርጫ ሂደት እጅጉን ፈታኝ ቢሆንም — የ [ሰው] ዘር መለኮትዓዊ ተፈጥሮው፤ ፍፁምዓዊ ነፃዕነትን ዕውን ማድረግን ሳያረጋግጥ እንቅልፍ እንዳይወስደው የግድ ይለው አለ።  ይህ-እንን [ለ ዘመንዐት] ተግባርዓዊ ማድረግ የአልተቻለ ከሆነ ነው እንግዲህ፤ ታዲያ....... [የ ምርጫ ጠቀሜታው፣ ፋይዳው ምኑ ላይ ነው] የ እሚል ጥያቄ የመጠየቁ አግባብዕነት። የ መምረጥ የመመረጥ መብትን ማክበር ማስከበር ከምንም በላይ ክቡር ነገር ሆኖ ሳለ – ተወዳዳሪዎችን ማወቅ አስቸጋሪ ከሆነ፣ መራጮች በመረጡት ሰው/ፓርቲ እንደተጠበቀው መገልገል መቻል አለመቻልአቸውን እርግጠኛ መሆን ከአልተቻለ፣ እናም የባሰውኑ – ይጠቅመናል በ እሚል በቂ የአመኔታ የድምፅ ካርድ አግኝቶ የተመረጠ ሰው/ፓርቲ፤ ምርጫው ከተጠናቀቀ በሁዋላ – በተቃራኒው ጎጂ መሠሪ ተግባርዐትን ሲያከናውን ማየት የተለመደ ከሆነ፤ ዲሚክረሲንም ሆነ በተጓዳኝ ምርጫን እና የአመኔታ ድምፅ አሰጣጥ ስርዐትን ኤክሰርሳይስ የማድረጉን ፋይዳ፤ ጥርጣሬ ውስጥ ቢከትቱት አያስገርምም። ግራም ነፈሰ ቀኝ — ምርጫ ከተደረገ አይቀር፤  [ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የ መንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ ስር የማድረግ ተልዕኮው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ፤ የመንከባከቡን ግዴታ በእሚገባ መወጣት ይጠበቅበታል። በዋናዕነት — የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ፤ የ [ግለሰቦች] ጉዳይ ሳይሆን፤ የሃገር እና የ[ሰው] ዘር ዕድገት እና ቀጣይዕነት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ፤ እጅጉን – አዎ፤ እጅጉን ወሳኝ ነው።

እዚህ ላይ፤ መራጩ ትኩረት ቢያደርግ፣ በማሕበረሰብዓዊ ህይወት ጉዳዮች ዙሪያ ንቁ ተሳትፎ ቢያደርግ፣ የምርጫ ክርርክሮችን ቢከታተል፣ በስብሰባዎች ቢሳተፍ፣ ጋዜጣ ቢያነብ፣ ሬዲዮ ቢያዳምጥ፣ ኢንተርኔትን በእሚገባ ቢጠቀም ወዘተርፈ እሚሉ ነጥብዖች መነሳታቸው አይቀርም። እስቲ ፈጣሪ ያሳያችሁ – ስንቶችአችን ነን፤ ከተዘረዘሩት ቢደረጉዎች ውስጥ በቂ የሆኑትን ተከትለን፤ ምርጫ በመጣ ቁጥር እየ አንድ-አንዱን ተመራጭ ግለሰብ/ፓርቲ ማንዕነቱን ምንዕነቱን አንጥረን እምንዐውቀው? ምንያህሉ መራጭስ ነው፤ በምርጫው ወቅት እሚነሱትን መሠረትዓዊ ጉዳዮች ውስብስብዕነት በእሚገባ የመረዳት ፍላጎቱም ሆነ አቅሙ የአለው? ይ-ህ ሁሉ እንግዲህ፤ በምርጫ ወቅት ለእሚያደቡት አንሰርተንቲስ እሚኖረው አስተዋፅዖ እሚናቅ አይሆንም። ደግዕነቱ፤ ዛሬ-ዛሬ [በቂ ባይሆንም] ኢንፎርሜሽን በሡፊው እሚሰራጭበት ዘመን ላይ በመድረስአችን፤ ተወዳዳሪ ግለሰብ/ፓርቲ ከእሚያዘጋጃቸው የመሬት ፖሊሲ፣ የሰማይ ፖሊሲ ዲስኩሮች በበለጠ – መሠረትዓዊ ችግሮቻችን፤ ማለትም [የጎሣ-ፖለቲካ፣ የጎሣ-ፌደራሊዝም እና ፀረ-ዜጋ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው ሕገ-መንግሥት] ከኢትዮጵያ፣ ከኢትዮጵያዊዕነት እና ከ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕለት-ተ-ዕለት ህይወት ጋር በጥብቅ የተቆራኙ የህልውና ጉዳዮች

*መሆንአቸውን — ለፖለቲካ ብዙም ትኩረት አይሰጥ ይሆናል ተብሎ ለእሚገመተው የሕብረተሰብ ክፍል ሳይቀር፤ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያዳብር፤ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብን አለ።*

ለማጠቃለል፤ ሂደቱም ሆነ ውጤቱ እሚጓጓለት ባይሆንም ቅሉ — ኢትዮጵያ፤ ምርጫ ልታካሂድ ነው። ደግዕነቱ፤ ለፖለቲካው ነውጥ፣ ለመንግሥትዓዊው ጄኖሳይድ፣ ለየለየለት ጦርዕነት፣ ለሰላም እና መረጋጋት እጦት፣ ለ ተጨማሪ ግርግሞች ፈጠራም ሆነ ክልከላ፣ ለ የከንቲባዎች አሿሿም የከተማ-ወረራ እና ዘረፋ ሁሉ መሠረትዓዊ ምክንያቶችአቸው – የጎሣ-ፖለቲካው፣ በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩዩ ፌደራሊዝም፣ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው ሕገ-መግሥት መሆናቸውን እና ዛሬውኑ – አዎ፤ ዛሬውኑ ሊቀየሩ እንደእሚገባ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ የተገነዘበበት ደረጃ ላይ መድረሱ፤ ተስፋ ሰጪ ነው። ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን፤ በገዛ ሃገርአቸው በገዛ ቀዬአቸው ሲሰቃዩ፣ ሲፈናቀሉ፣ ሲታረዱ፣ ሲጨፈጨፉ፣ በግፍ ከተገደሉ በሁዋላም በ ሮድ-ግሬደር በጅምላ ወደገደል ሲዘረገፉ፤ ሲራቡ ሲጠሙ ሲታረዙ — ማን ኢትዮጵያን እየበጠበጠ እንዳለ፣ እነማን በማሰቃየቱ በማፈናቀሉ በመጨፍጨፉ እንደተሳተፉ፣ እነማን ሰምተው እንደአልሰሙ ጭጭ ብለው እንደተመለከቱ፤ ቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገንአቸው [መራጩ] በ እሚያደነቁር ዝምታው ተቃውሞውን ከመግለፅ አልተቆጠበም። እናም፤ አደራ — ለመመረጥ በእሚደረደር መሸንገያ፣ ዝብአዝንኬ የፖሊሲ ዲስኩር እና ውሃ የእማይቋጥር "ቃል-ኪዳን" ሳይሸነገል፤ ሽራፊ የአመኔታ የድምፅ ካርዱን ለገዥው-ግንባር ተወዳዳሪዎችም ሆነ ለደጋፊዎቻቸው እንድአይሰጣቸው፤ መራጮች ፈርጠም ብለው ያንቁ ይከላከሉ ይጠብቁ። [ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ ስር የማድረግ እርምጃውን እሚጀምረው – መራጮች፤ ያእንን የ አደረጉ እንደሆነ ብቻ ነው እና!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

እንኳን ለ 125ኛው የ አድዋ-ድል በዓል አደረሰን!

ዛሬ፤ እየቀረበ የመጣውን ሃገርዓዊ ምርጫ ምክንያት በማድረግ ተየህ ቀደም ከአጋራናችሁ ብሎግዖችአችን መሃከል፤ ከሊትሬቸር የተበደርነውን ሟድል ጨምሮ አንድ ሁለቱ ላይ ተመርኩዘን፤ በንፁህ ያገባናል ባይዕነት —እምንለውን ለማለት ከፊትአችሁ ቀርበን አለን።

እናም፤ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

ጎበዝ – የሕዝብ ተወካዮችን መምረጥ፤ ለ ኢትዮጵያ አዲስ ነገር አይደለም። በ ስርዐትዓዊ ምንዕነትአቸው፤ አንዱ ንጉሥዓዊ፣ ሌላው ወታደርዓዊ አምባገነን፣ ይህ-እኛው ደሞ ገንጣይ አስገንጣይ ጠባብ የጎሣ-ፖለቲከኛ በመሆን ካቴጎሪክሊ ይለያዩ እንጅ።

እንዲያው ለምንአልባቱ፤ ሁሉንም እሚያመሳስሉአቸው ባህሪያት ይኖሩ እንደሆነ ለ እሚጠይቅ፤ ተመራጮች በጥቅል – ሀገርን መጠበቅ እና ሕዝብን በቀናዕነት ማገልገል እሚያስችሉ፤ ሰውዓዊዕነትን፣ ዕኩልዕነትን፣ ሰላምን፣ ህብርዕነትን፣ ዘመንዓዊ ስልጣኔን፣ ቀጣይዕነት እና ትርጉም የአለው የጋራ ዕድገትን [በተገቢው ፍጥነት] በተሳካ መልኩ ተግባራዊ እሚያደርጉ ኢትዮጵያዊ ተቋዋምአትን መገንባት መፍጠር የአልቻሉ የ መሆንአቸውን ዕውነታዎች መጠቃቀስ ይቻል አለ። ምስጋና ቢስ ለ አለመሆን፤ የተወሰኑ ፍላጐቶች ሙከራዎች የተስተዋሉባቸው ገጠመኞች ነበሩ ማለት ቢቻልም እንኳ፤ ትራንስፎርሜቲቭ የሆኑ ውጤቶች አልባ ሆነው ለመቅረትአቸው ግና፤ እስከ የ ዛሬዋ ዕለት ድረስ የአለውን ኢትዮጵያዊ ህይወት – ዓይንን፣ ልቦናን እና ኅሊናን ክፍት አድርጐ መመልከት፤ ለ ምስክርዕነት ያህል በቂ ነው ብለን ዕንዐምን አለን።

ታዲያ........... እየተቃረበ የአለው ምርጫስ፤ ኢትዮጵያዊ ፋይዳው ምንድን ይሆን?

አዎ፤ በተደጋጋሚ ለማስገንዘብ ሞክረናል፤

- ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መግሥት አርቃቂ እና አምላኪ የፍትህ ተቋዋም ተሸክሞ እሚደረግ ምርጫ፤ በተዐምር ፍትህዓዊ እና ነፃ ሊሆን እንደ እማይችል፣
- በመላው የኢትዮጵያ ግዛቶች ሰላም እና መረጋጋት እሚባል ነገር በ አለመኖሩ፤ ምርጫ-ቦርድም፣ ገዥው-ግንባርም ሆነ ተፎካካሪ ተብዬ ፓርቲዎች የረባ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደእማይቻላቸው እና
- በ ሰበብ-አስባቡ ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኞች በግፍ በገፍ ታስረው፣ ሲያራምዷቸው ሲፋለሙእላቸው የነበሩትን ኢትዮጵያዊ አጀንዳዎች መሠሪ በሆነ መልኩ ፕሌጀራይዝ ተደርገው፣ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በ ሰበብ-አስባቡ ከምርጫው ተገልለው፣ አጨብጫቢዎችን፣ "ነፃ አውጪ" ተብዬዎችን እና ጠባብ የጎሣ-ፖለቲከኞችን አግበስብሶ እሚካሄድ ምርጫ የመሆኑ ዕውነታዎች ተደማምረው፤ አንድአችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረው የእማይችል መሆኑን፤ ዛሬም – አምርረን ማስገንዘብ እንወዳለን

ሆኖም ግና፤ ከወደ 15-ቀናት ገደማ ጀምሮ የተለያዩ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ አንድ-አንዶቹ በቪዲዮ ክሊፕ፣ ሌሎች በስብሰባ፣ ሌሎችም በደማቅ የጐዳና የአደባባይ ትዕይንት፤ ምርጫው እንደእሚደረግ እና ተሳታፊ መሆንአቸውንም ሲያስተዋውቁ አይተናል ሰምተናል። ሌሎች እስካሁን ዝም እንደአሉ የመሆናቸውን ትርጉም ግና፤ በቅርቡ አብረን እምናየው ይሆናል።

ምርጫው መደረጉ ከአልቀረ ዘንዳ፤ ውጤቱን በተመለከተ ለ ኢትዮጵያ እንደ አንጋፋዋ ሉዐልዓዊት ሃገር እና ለ ኢትዮጵያዊያን እንደ አንድ ጀግና ህብር ሕዝብ በእሚጠቅም መልኩ እንዲጠናቀቅ ቢያግዘው በእሚል፤ በ ሁለት ወቅቶች የአንሸራሸርናቸውን እይታዎችአችንን ሰንቀን፤ ትንሽ እንድእንል ፍቀዱልን።

ወቅት አንድ – [ጥቅምት 2012 ዓ.ም አካባቢ]

የዛሬ ዓመት-ተ-መንፈቅ ገደማ፤ ሪፎርሚስት ነኝ ባዩ ገዥው-ግንባር ልዋሃድ ነው ሲል የነበረበት እና ምርጫም ይደረግ አለ የ እሚባልበት ወቅት ነበር።

እናም እኛ፤ አ...ይ ልዋሃድ ነው ማለት ለ ኢሕአዴግ – አዲስ ነገር አ-ይ-ደ-ለ-ም። በጎሣ አይዲዮሎጂ ተቦክተው ተጠፍጥፈው የተጋገሩ፤ በግንባሩ ውስጥ የታቀፉ የጎሣ-ድርጅቶች [ግንባር

ሆነው ቀኑ፤ ውሁድ] ለሃገር እና ለሕዝብ የእሚፈይዱት የረባ ነገር ሊኖር አይችልም እሚል አቋዋምአችንን ገልፀን ነበር – ግንባሩ ዕድሜውን ለማርዘም ይረዳው መስሎት ግና፤ ዕውነትም እንደእሚያስወራው “ውህደት” እሚለውን ሊተገብር እንደእሚችልም ጭምር።

የ ያ-ኔ ጥቅል ምክንያትአችንም፤

<u>አንደኛ</u>፤ የ አንድዕነቱ ጐራ ጎልብቶ የወጣበት ጊዜ ላይ መሆኑን እና ፕሬዝደንትዓዊ ሲስተም የመመሥረት ፍላጐት በ አንድ-ሁለት ፖለቲከኞች ዘንድ እየተንፀባረቀ መሆኑን፣

<u>ሁለተኛ</u>፤ በዛ የአሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ሃገርቤት መግባታቸውን ተከትሎ በተከሰተው የመራጮች ቅርምት ስጋት ሳቢያ፣ አንድ-አንድ ፓርቲዎች ቀደም ብለው መጣመር/መዋሃድ መጀመራቸውን፣

<u>ሦስተኛ</u>፤ በዛ በአሉ ፓርቲዎች መሃከል የረባ የፖሊሲ ልዩዕነቶች አለመኖሩ እና የእረዥም ጊዜ የመተባበር ተለምዶን እና ተሞክሮን ተመርኩዘው በ ፖለቲከኞቻችን መሃከል፤ በግለሰብ ደረጃም ጭምር ቀላል የእማይባል ቅርርቦች እና መናበቦች — ለ አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች፤ መጣመር/መዋሃድ “ናቹራል” እንደእሚሆን ስለዐመንን፣

<u>አራተኛ</u>፤ የትግሉ መርዘም – ጊዜን፣ ሃብት-ንብረትን፣ አካልን-ህይወትን-ነፍስንም ጭምር ስለእሚያስከፍል፤ ቢያንስ ድል ቀረብ እንዲል የማድረግ ፍላጎቱ፤ ጥቃቅን ልዩዕነቶችን አቻችሎ መጣመሩ/መዋሃዱ፤ ምርቱ ጎተራ ሞልቶ ተራፊ ሊሆን እንደእሚችል ስለዐመንንበት እና

<u>አምስተኛ</u>፤ ትንንሽ ድርጅቶችም ቢሆኑ፤ የረባ ስልጣን ለመያዝ አቅሙ ባይኖራቸውም፤ በመጣመር በመዋሃድ እሚገነቡት የተሻለ ቁመና፤ ዲሚክረሲን ለመለማመድ እንዲሁም ፖሊሲዎችአቸውን ለመፈተሽ እና ለማስፋፋት ሊጠቅማቸው እንደእሚችል እማይጠፋቸው መሆኑንን ሁሉ — ከ ስልጡን የግንዛቤ ፕሮሰሰርአችን ውስጥ አካትተናቸው ስለነበር እንደሆነ ማስታወስ እንወድ አለን።

እናም፤

በ አንዱም ሆነ በሌላው መልኩ የተጣመሩ የተዛመዱ እና የተቆራኙ ወሳኝ መሠረትዓዊ ነጥቦች ተመቻችትው መገኘት – የገዥው-ግንባርም ሆነ ሌሎች ፓርቲዎች ወደ ጥምር/ውሁድ ድርጅትዕነት ይቀየሩ ዘንድ የማማለል ግዙፍ አቅም የአላቸው መሆኑን ጠቁመን ነበር። ያ ሁሉ ከሆነ በኋላ ግና፤ ምርጫ ተብዬው እንደአሰቡት ከተካሄደ፤ ማንአቸውም [ጥምር ሆነ ውሁድ] ድርጅት በሰፊ የድምፅ ብልጫ ለማሸነፍ ስለእማይችል፤ የማታ የማታ ምን አልባትም ከገዥው-ግንባር እና ከሌሎች ድርጅቶች የሚወለድ ገዘፍ የአለ ውሁድ ፓርቲ፤ የጥምር መንግሥት በመመሥረት፤ ለ አምስት ዓመትዐት ያህል ኢትዮጵያን ይገዛሉ – የእሚል ትንበያ ነው የነበረን።

<u>ወቅት ሁለት – [መጋቢት 2013 ዓ.ም አካባቢ]</u>

ዛሬ ላይ ሆነን ስንእመለከተው ግና፤

<u>አንደኛ</u>፤ እንደገመትነው ገዥው-ግንባር “ተዋሃድኩ” ብሎ ስሙንም ቀይሮ እራሱን ብልፅግና ብሎ መጥራት ቢጀምርም፤ <u>በተግባር ሲታይ</u> አጋር የጎሣ-ድርጅቶችን አንድ ዕርከን ከፍ ከማድረጉ በስተቀር፤ ያ-ው ህወሓት መራሽ ከነበረው ኢህአዴግ ወደ ኦዲፓ-ኦነግ መራሽ ኢህአዴግ የተቀየረ፤ [ዕውነትን መካድ ከአልተመረጠ] ዛሬም ቢሆን — ዋሾ የጎሣ-ድርጅቶች ስብስብ መሆኑን ከ ሕዝብ ዕይታ መደበቅ ስለእማይቻለው፣

<u>ሁለተኛ</u>፤ የመራጮች ቅርምት ስጋት የአስከተለው የፓርቲዎች ጥምረት/ውህደት ቀደም ብሎ መፈጠርን ተከትሎ አንድ ብቻ ሳይሆን፤ ተጨማሪ ፈርጠም የአሉ ጥምረቶች እና ውህደቶች በ መከሰታቸው፣

<u>ሦስተኛ</u>፤ በቅርቡም በገዥው-ግንባር እና በምርጫ ቦርድ መሃከል የተፈጠረ በእሚመስል መሠሪ ሽርክና፤ በተለይም በዕውነት ኢትዮጵያን የእሚሉ ድርጅቶችንም ሆነ ግለሰብ ፖለቲከኞችን ከፖለቲካው ምህዳር ለማግለል የተወሰዱት እርምጃዎች፤ ግለሰቦቹ በግፍ በገፍ ወደ እስርቤት ሲወረሩ፤ ድርጅቶቻቸው ደሞ በሰበብ-አስባቡ ከምርጫ ቦርድ እንዲባረሩ፤ አልያም እንዲዳከሙ መደረጋቸውን ተከትሎ — የተወሰኑት፤ እንደ ድርጅትም ሆነ እንደ ግለሰብ ወደ ጥምረት ወደ ውህደት በማምራታቸው፣

<u>አራተኛ</u>፤ የጎሣ-ፖለቲካ፣ በጎጥ በቋንቋ ላይ የተመሰረተው ዕኩዩ ፌደራሊዝም እና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው ሕገ-መንግሥት፤ ለኢትዮጵያም ሆነ ለማንኛውም የ[ሰው] ዘር እምአይመጥኑ – ሁዋላቀር፣ አፍራሽ፣ አጥፊ እና የአውሬ የደናቁርት ተግባራት መሆናቸውን፤ ለ 30-ዓመትዐት ያህል የተከሰቱት የንፁሃን ሃዘን ሰቆቃ፣ ጀኖሳይድ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እንዲሁም የሃገር ወረራ ዘረፋ እና የመፍረስ አደጋን ተከትሎ – የ[<u>ኢትዮጵያዊዕነት</u>] መርህ አማራጭ የለሽ አሳማኝ ፈውስ እንደሆነ እና እየጎለበተም በመምጣቱ እና

<u>አምስተኛ</u>፤ ገዥው-ግንባር አምባገነንዕነቱ እና የለየለት ስግብግብዕነቱ ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ፤ ውስጡ ክፉኛ እየተሰነጣጠቀ መምጣቱ እና “የ-እኔ” ከእሚለው መንጋ ጋር ዕንኳን የልብ መራራቅ በመፍጠሩም ጭምር – በገዥው-ግንባር እና በሌላ ውሁድ ፓርቲ እሚፈጠር ጥምር መንግስት፤ ለእሚቀጥሉት አምስት ዓመትዐት ኢትዮጵያን ይገዛሉ የእሚለው ትንበያችን፤ ዛሬ መስራቱን እንድንጠራጠር አድርገውን አሉ።

እኮ እንዴት.... ቢሉ – – ዛሬ፤

ኢትዮጵያ የፖለቲካ ነውጥ ውስጥ ተዘፍቃ ትገኝ አለች፣ ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ የንፁሃን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት የ ዕለት-ተ-ዕለት ቀለብአችን ሆኗል። ዐማራ እና ተዋህዶ ላይ የአነጣጠረው ጀኖሳይድ በመንግሥት ቀጥተኛ መዋቅርዓዊ ተቋዋምዓዊ ተሳታፊዕነት እና በአንድ-አንድ ተፎካካሪ ተብዬ ፓርቲዎች ደጋፊዕነት ሽፋፋኝዕነት በሰፊው እየተተገበረ በመሆኑም ጭምር – ለፖለቲካ ግድ ሊኖረው እማይችል ምስኪ ዜጋ እንኳን ሳይቀር፤ በገዥው-ግንባር እና በአንድ-አንድ ደጋፊ ፖለቲከኞች ላይ የመረረ ጥላቻን ያሳድር ዘንድ የግድ እንደሆነበት በማየትአችን፣

የ አዲስ-አበባ ከንቲባዎችን አመዳደብ እና ከተመደቡ በኋላ ከ ገዥው-ግንባር ጋር እጅ-ተ-ጓንት ሆነው የፈፀሙት የመሬት/የሕንፃ/የገንዘብ/የማንዕነት ዝርፊያ ወረራ እና ቁጥር-ስፍር የሌላቸው ኢ-ሰብዓዊ ከተማዓዊ እና ሃገርዓዊ ወንጀሎች፤ የ አዲስ-አበባን ኗሪ በገዥው-ግንባር እና በ አንድ-አንድ ደጋፊ ፖለቲከኞች ላይ ጥርስ እንዲነክስባቸው እንደአስገደዱት በማስተዋልአችን፣

ይገብርልናል ብለው ለገሙቱት ጎሣ፤ ተጨማሪ ግርግም ፈጥረው ሲሸልሙ፤ ሌሎች ኢ-ፍትህዓዊ በሆነ ውሳኔ መከልከልአቸውን ተከትሎ ከፍተኛ ሕዝብዓዊ ኩርፊያ እና ተቃውሞ ተቀስቅሶ በ ማየትአችን፣

ብረት አንስተው ንፁሃንን ጨፈጭፉ ግዛቶችን ጨምሮ፤ የማንዕነት ቅምያ ላይ የተመሠረቱ የድንበር ጥያቄዎች እና የለየለት ጦርዕነት እየተካሄደባቸው የአሉ ግዛቶች ውስጥ እሚኖረው ሕዝብ – ስለመረረው፤ ገዥው-ግንባርን እና ደጋፊዎቹን፤ ለ መልስ-ምት እሳት-ጎርሶ እደእሚጠብቃቸው መገመቱ ከባድ ስላልሆነ እና

ገዥው-ግንባር – ከሰሞነኛው ጎሣ መንጋ ጋር የገባውን የቋንቋ የጎጥ ፌደራሊዝሙን እና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ሕገ-መንግሥት የማስቀጠል "ቃል-ኪዳን" – በ የምርጫ ውድድር-መሰል ዲስኩሩ ግልፅ ማድረጉ፤ ቀና ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ በማስቀየሙ፤ ከ ሁለት ዓመት ገደማ በፊት የነበረው ድጋፍ እንደ ጉም ተንኖ – ዕርቃኑን መቅረቱን ዕንዐምን ዘንድ በመገደዳችን ጭምር መሆኑን መጠቃቀስ እንችል አለን።

እናም፤ ተዋሃድኩ ባዩ ብልፅግናም ሆነ የብልፅግና ደጋፊ ፓርቲዎች፤ እንኳንእስ ሕዝብ ሊመርጣቸው ይቅር እና ለምርጫ ቅስቀሳ ብለው አጠገቡ እንዳይደርሱ፤ [ሕዝብ] ከአሁኑ ፊት እንዲነሳቸው እሚያስገድዱት ሁኔታዎች በሙብዛታቸው፤ በአንድዕነቱ ጎራ — ያለመዘናጋት የተቀነባበረ የጋራ ስራ ከተሰራ፤ የአሸናፊዎችን ላንድስኬፕ ለ ኢትዮጵያዊዕነት አዎንታዊ ፋይዳ በአለው መልኩ ሊቀይረው እንደእሚችል ወደ ማመኑ አዘንብለን አለን።

በመጨረሻም፤

ምርጫው፤ ፍትህዓዊ እና ነፃ ሊሆን ስለ እማይችል እና የ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያንን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት እሚያራዝም በመሆኑ፤ አንድአችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረውም አይጠበቅም። ዛሬም፤ ምርጫው እንዲሰረዝ ለማስገደድም ሆነ ተፎካካሪ ተብዬ ፓርቲዎች በሙሉ [ቦይካት] ያደርጉ ዘንድ፤ እንደ የሰላም እና መረጋጋት ዕጦት የአሉ፣ በቂ ኢትዮጵያዊ ምክንያትዖች አሉ።

ምርጫው እንዲሰረዝ እምንፈልገውም፤ ብልፅግና ፓርቲ እንደለመደው የጎሣ-ፖለቲካውን አዝሎ ያንጐላጅብን ዘንድ ሳይሆን፤ በቀጥታ – ወደ ሃገርዓዊ ኢትዮጵያዊ የጋራ የምክክር ሂደት እና ወደ ኢትዮጵያዊያንን ብቻ እሚያካትት ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ምስረታ እንድእንአመራ መሆኑን፤ በድርብ የጎሊና ሰረዝ አፅንዖት ሰጥተን ማለፍ ግዴታችን እንዲሆንም ፈቅደናል።

ሆኖም፤

ምርጫው መደረጉ ከአልቀረ፤ ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረው በእሚችል መልኩ እንዲከናወን፤ የሞት የሽረት ጥረት ማድረግ ይገባል። ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ስንልም፤ አዴፓ-ኦነግ መራሹ የ ብልፅግና ፓርቲን – በተናጠል ሳይሆን፣ በተቀናጀ የጋራ አሰላልፍ በድምፅ ብልጫ ተዘርሮ የኢትዮጵያ [ሕዝብ] — የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ አስተማማኝ በሆነ መልኩ በቁጥጥሩ ስር ሊያደር እሚችልበትን ወሳኝ እርምጃ ይጀምር፤ ማለትአችን ነው።

ትክክል። ብልፅግና ፓርቲ – ኢህአዴግ ነው። ኢህአዴግ ደሞ፤ ኢትዮጵያን የአፈረሰ፣ የባሕር-በሮችአችንን አሳልፎ የሰጠ፣ አንጡራ ሃብትዋን የዘረፈ፣ ኢ-ሰብዓዊዕነትን የአንሰራፋ፣ አሸባሪዕነቱን የአመነ፣ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካን፣ ጎሠኛዕነትን እና ተገንጣይዕነትን የአጎለበተ፤ ማንም ይቅር ሳይለው – እራሱን ይቅር ብየአለሁ ብሎ፤ እስከዛሬ በመንግሥትዕነት በርጩማው ላይ ግግም ብሎ የተኮፈሰ፤ የአገኘውን ቀና አጋጣሚ ተጠቅሞ እራሱን ማሻሻል መቀየር አሻፈረኝ የአለ እና ከ ህወሓት የከፋ ወንጀል እየፈፀመ የአለ የጎሣ-ድርጅቶች ስብስብ ነው።

ብልፅግና ፓርቲ ተጨማሪ ጊዜ ከተሰጠው፤ በ ኢኮኖሚዋ የደቀቀች ሃገር፤ ወገን ከወገን እማይግባባበት፣ ንፁሃን ዜጎች በገዛ ሃገርአቸው በገዛ ቀዬአቸው እሚፈናቀሉበት፣ የጀኖሳይድ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና የሃገር መፍረስ አደጋ የተንሰራፋበትን ማሕበረሰብዓዊ ህይወት በቀጣይዕነት ለመኖር — አውቀን ፈቅደናል ማለት ነው እሚሆነው። ያ-ም የሞት ሞት ነው!

ጎበዝ፤ ህወሓትን አስወገድን ከተባለልን በኋላ – በመላው ዓለም የተወገዘ፤ እንዲሁም ኢትዮጵያም ውስጥ ለ 30-ዓመትዐት ያህል ተተግብረው አይወድቁ አወዳደቅ ወድቀው – ውጤትአቸው፤ የከፋ ሃዘን ሰቆቃ ዕልቂት እና የሃገር መፍረስ አደጋ ማስከተል መሆኑን፤ በ ዓይንአችን በብሌኑ የአየናቸው — ፀረ-ዜጋ ፀረ-ሃገር የሆነ ሕገ-መንግሥትን እና የጎሣ-ፊደራሊዝምን የሙጥኝ ማለት፤ ከሃዲዕነትም በሽተኛነትም ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፤

ቀጣዩ የትግል ምዕራፍ ትኩረት፤ ነፃ-አውጭ እና ፍትህ-አጎናፃፊ ሕዝብዓዊ ሃይል መፍጠር እና ትግሉን የበለጠ ማጎልበት ላይ መሆን የግድ ነው። የእሚመጣው ምርጫም፤ የትግሉ አካል እንደሆነ ነው እሚቆጠረው። እናም፤ ብልፅግና ፓርቲ በሰፊ የድምፅ ብልጫ ተሸንፎ፤ ከፖለቲካው ማማ እንዲወርድ ማድረግ፤ በምርጫው የመሳተፉ ዋና ተልዕኮ ተደርጎ ሊወሰድ እንደእሚገባ፤ ደግመን እንደነገርንአችሁ እርግጠኞች መሆን እንፈልግ አለን። ዕመኑን፤ ትግልአችን ፍትህዓዊ ነው — የሃገር እና የህዝብ፤ የህልውናቸው ጉዳይ ነው እና! የምርጫው ሂደትም ሆነ ውጤቱ የተጭበረበረ የተዛባ መሆኑ ከተረጋገጠ ግና፤ ሕዝብ እስከመጨረሻው በጋራ ይታገለው ዘንድ፤ ዝግጅቱ ከወዲሁ ሊጠናቀቅ ይገባል።

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እስከ እምንገናኝ –

# መሬት ላይ ቆመን — እንነሳ!

ሚያዝያ ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ኤፕሪል 2021

አንድ አባባል አለ። ኔልሰን ማንዴላ ተናግረውት አለ እሚባልለት። *“መቼም ቢሆን የ እማይሳካ ሊመስል ይችላል፤ ተጠናቅቆ እስከ እሚታይ ድረስ”* ......የ እሚል።

ትርጉም፡ የ አዳራሽ።

ይህን አባባል፤ የ ሳይንስዓዊ አስተምህሮ ዐማኒያን በ[አርምሞ] ብንአልፈው አይገርምም — ለፕሬዝደንቱ አክብሮትን ለ አለመንሳት። እርሳቸው በአመዛኙ በፖለቲከኛዕነት ስለእሚታወቁም ፖለቲካን እንደ ፖለቲካ ለማስተናገድም እምንፈቅድ [አከባሪዎቻችሁን ጨምሮ] የአባባሉን ኮንቴክስችዋል ጭብጥ ፈጥነን ማገናዘቡም እምብዛም አይገድኸንም።

ማለትም..........

*[መቼም ቢሆን እማይሳካ ሊመስል ቢችልም ቅሉ፤ የጎሣ-ፖለቲካ መንግሥትዓዊ-ጄኖሳይድ የሃገር-ወረራ እና የሃገር-መፍረስ-አደጋ እንድያከትም መታገል፤ የግድ ነው። ለ እዚያ እንድእንበቃም፤ የተባበረ ሁለገብ ሕዝብዓዊ ፍልሚያ ከማድረግ ጐን-ለ-ጐን የፊትአችንን ምርጫ አስገድደን ማሠረዝ አልያም በይካት ማድረግ — የአባትም-የእናትም ነው። ከአልተቻለም፤ “ህይወት” መቀጠሉ አይቀርምና ኢትዮጵያን የ ዕምንዕል ከድርጅት በላይ የሆነ የጋራ የተቀናጀ ስልጡን ስልት በመጠቀም፤ ምርጫው ተጠናቅቆ ውጤቱ እስከ እሚታይ ድረስ — አረመኔው ገዥው ፓርቲን፤ በሰፊ የድምፅ ብልጫ ሲሸነፍ ከፖለቲካው ማማ ሲወርድ ሲባረር እና ኢትዮጵያዊዕነት ድል ሲያደርግ ማየትን — በምርጫው የመሳተፍአችን፤ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ ተልዕኮአችን አድርገን ልንወስደው ይገባን አለ]*

..........ማለትአችን ነው።

አዎ፤ ምርጫውን በተመለከተ ሰላም እና መረጋጋት አለመስፈንን ጨምሮ፤ ሌሎች ሊስተካከሉ እሚገባቸው መዋቅርዓዊ ተቋምዓዊ የህልውና ቅድመ ሁኔታዎች በ አለመሟላትአቸው፤ አሻፈረን ማለትን መገፋፋት በማስቀደማችን ትክክለኛ ብቻ ነው እምንሆነው። የተሻለ አማራጭ ሕዝብዓዊ እንቅስቃሴ ዝግጁ ሆኖ ከ አለማየታችን የተነሳ ግና በምርጫው የመሳተፍን “በጐ” ጐን፤ ሆነ ብለን ማጉላትአችን አልቀረልንም — በ እዚህ አያያዝአችን፤ ለ ዜጐች እሚመጥንን ድል ዕውን ማድረግ፤ *መቼም ቢሆን እማይሳካ ሊመስለን* ቢችልም ቅሉ። ከ እዚያም በላይ፤ “ህይወት” [የእኛውም ህይወት ከተባለ] መቀጠሉ አይቀርምና — ነፃ ደጋፊዎችን በተመለከተ፤ አረመኔው ከሃዲው ገዥው ፓርቲ ዕርቃኑን መቅረቱን ስለ ዕምንዐምን [ግብረ-ገብዕነት] በተሞላበት መልኩ ትኩረታችንን ከተልዕኳችን ላይ በማነጣጠር [ስኬት]ዓማ ለመሆን በጋራ በ[ፅናት] ኢትዮጵያዊ ቁርጠኛዕነትን ሰንቀን፤ ገዥው ፓርቲ ሽራፊ የ አመኔታ ድምፅ ካርድ እንዳያገኝ ለማድረግ *ምርጫው ተጠናቅቆ ውጤቱ እስከ እሚታይ ድረስ* — የ <u>አለመዘናጋት</u> በትጋት “መፋለምን” የ የቀጣዩ ሁለገብ ሕዝብዓዊ እንቅስቃሴ ጥንስስ አንዱ አካል አድርገን መውሰድአችን፤ አግባብዕነት አለው ብለንም ዕንዐምን አለን።

ትክክል — ሀ) ኢትዮጵያ የፖለቲካ ነውጥ ውስጥ ተዘፍቃ፣ ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ የንፁሃን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት፣ በተለይም የ ዐማራ ተወላጆች ላይ እና የተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያን ላይ የአነጣጠረው ህወሃትዓዊ አነግዓዊ መንግሥትዓዊ ጄኖሳይድ ገንኖ ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን በፍፁም አለመፈለጉ፣ ለ) ስራ አጥዕነት ችጋር እና በሽታ ከአቅም በላይ መሆኑ፡ ሐ) የማንዕነት ቅምያ ላይ የተመሠረቱ የከተማ ባለቤትዕነት፣ የድንበር ጥያቄዎች እና የለየለት ጦርዕነት እየተካሄደባቸው የአሉ ግዛቶች መብዛታቸው፣ መ) የ-እኔ ከእሚላቸው የጎሣ ድርጅቶች [ኦፌኮ እና ግማሽ-ኦነግ] አባላት ጋር ስለተኮራረፈ የ እኔ በእሚለው ግርግም እንኳን ሳይቀር፤ ምርጫው እንዳይሳካለት መደረጉ ስለእማይቀር እና ሠ) በ ዓለም-አቀፍ ደረጃም ብዙ ችግሮችን እየአስተናገደ መሆኑም ጭምር ተደማምረው፤ ነፃ መራጮችን በተመለከተ — ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ገዥው ፓርቲ በመላው ኢትዮጵያ መለመላውን መቅረቱ ምቹ አጋጣሚን በመፍጠሩ፤ ሚስድ-ኦፖርቹኒቲ ለፀፀት እንዳይዳርገን ለእሚቀጥሉት ሁለት-ወራት ገደማ በአለመዘናጋት በትጋት መስራት፤ ተገቢ ነው ባዮች ነን።

ዛሬ-ዛሬ፤ አሸናፊነትን ስናስብ — *መሠረተ ቢስ ዕምነትአችንን የብዙሃን መገናኛ ላይ የጣልን ይመስላል።* እናም፤ ይህን እርምጃችንን ቶሎ ማረቅ የግድ ነው። በ ስልጡን ሃገራት፤ የብዙሃን መገናኛ “አራትኛው የመንግሥት ቅርንጫፍ” ፖለቲካን ሃገራዊ እና ሕዝባዊ ችግሮች ላይ እንዲያተኩር በማስገደድ፤ አሸናፊ እሚሆንን ፓርቲ የማገዝም ሆነ ለፖሊሲ ለውጦች ካታላይዘር የመሆን ግዙፍ ሚና አለው። እኛን በተመለከተ፤ የብዙሃን መገናኛ ቁመና እና ሽፋን እምብዛም ስለሆነ ቀጣይዕነት እሚጐላቸው ወፍ-ዘራሽ እንቅስቃሴዎችን ከመፍጠር በአለፈ፤ አሸናፊ እሚሆንን ፓርቲ ለማወቅም ለማገዝም ሆነ የፖሊሲ ለውጦችን ለማምጣት እሚያስችል ትሬሽሆልድ ላይ የደረሰ አይደለም — አድርባይዕነቱንም ፈሪዕነቱንም ለጊዜው እንተወው እና። ያ-ም፤ ሀ) የብዙሃን መገናኛ ሊታረቅ እንደእሚገባው፣ ለ) የፓርላማ እና የካቢኔ አባላት ሪስፖንሲቭ ሊሆኑ እንደእሚገባቸው እና ሐ) ንቁው ዜጋም፤ ኢንፎርሜሽን ፕሮሰስ አድርጐ መንግሥት መለወጥም ሆነ ፖሊሲ ማስቀየር እሚያስችል እንቅስቃሴ መፍጠርን ሊያውቅበት እንደእሚገባ፤ ጠቋሚ ነው። ወደ-እዚያ ደረጃ ለመድረስ፤ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት እሚመራው ሁለገብ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ እንቅስቃሴ መኖር ወሳኝ ነው — በደለኞቻችንን እና ፈተናዎቻችንን እሚገዳደር አሸናፊ ቁመና ይኖረን ዘንድ። ትክክል፤ ሁልአችንም የትግል ፊደልአችንን መልሰን በማውጠንጠን በፅናት ከተፈተሸ ሕዝብዓዊ የፖለቲካ ድርጅት ዕገዛን በመጠየቅ በመቀላቀል በማጠናከር እና የተናበበ ትግሉን በማጎልበት፤ መሬት ላይ ቆመን — እንነሳ!

*ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!*

በቅድሚያ — ብሏግአችንን በማንበብ የተጨናነቀ ጊዜአችሁን ስለእምታካፍሉን እና ለጓዶችአችሁ ለጓደኞችአችሁ እና ለወዳጅ-ዘመድ እንደ እኛ ሁናችሁ ታጋሩልንአላችሁ የእሚል ዕምነት ስለ አለንም፤ የ ጥፋት አፋፍ ላይ ዘመም ብላ በአለችው ኢትዮጵያ እና የወላጅ መካን በሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም እናመሰግናችኋለን። ዛሬ፤ የ ምርጫው መቃረብን ምክንያት አድርገን ተጓዳኝ ዕውነታዎችን ጭምር ሰንቀን ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ድልን፤ በተናጠል ሳይሆን — በአንድዕነት በጋራ

ቀረብ ለማድረግ እሚያስችል የተሻለ እርምጃችንን እንዴት ፈር ማስያዝ ማጎልበት ማስቀጠል እንደእሚገባን፤ በግብረ-ገብዕነት በፅናት እና በስኬት ዙሪያ በማውጠንጠን፤ ዕምንዕለውን ለማለት ከፊታችሁ ቀርበን አለን።

እናም፡ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

አዎ፤ ግብረ-ገብዕነት እንደ [ቅን ከሆነ ስህተት የተነሳ ሳይሆን] – በአመዛኙ ሆነ ተብሎ ታቅዶ ከእሚፈጠር ዕኩይዕነት የፀዳ ሃሳብን ምልከታን ተግባርን እሚጠቁም ቃል። ፅናት እንደ እምአይነጥፍ – በህይወት ዙሪያ የተቀየሰ የስልት ትግበራ ሂደት ዕምቅ ኃይል። ስኬት ደሞ፤ ትክክል – እንደ ስኬት! በጥንቃቄ የተተለመን ተልዕኮ የተቀመረን ግብ፤ ዕውን ሆኖ ማየት።

ግብረ-ገብዕነት

ግብረ-ገብዕነት፤ ሁለት [አድራጊ እና ተደራጊ] ገፅታዎች የአሉት ጥልቅ የማንዕነት ስነ-ምግባር ልዕልና ነፀብራቅ ነው። [አድራጊ] ስለ ዩኒቨርስ የ አለን ሁለንተናዊ ሃሳብ ምልከታ እና የዕለት-ተ-ዕለት ተግባርአችንን ገላጭ የሆነው ገፅታ ሲሆን [ተደራጊ] ደሞ፤ ስለ ዩኒቨርስ በ አለን ሁለንተናዊ ሃሳብ፣ ምልከታ እና የዕለት-ተ-ዕለት ተግባርአችን ሳቢያ — በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ወይም ተጎጂ [ኢንፍሉዌንስድ፣ አፌክትድ] የእሚሆነው ሌላእኛው ገፅታ ነው።

ጎበዝ፡ አድራጊ እና ተደራጊ ገፅታዎችን በጥንቃቄ ማገናዘብ ሲቻል ብቻ ነው፤ ስለ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ማውራቱ ፋይዳ የእሚኖረው። አዎ፤ የግብረ-ገብዕነት ልዕልና ለ ዩኒቨርስ ሉዐልዓዊዕነት ድንቅዕነት የበላይዕነት "ተገዢ" በመሆን ሁለንተናዊ ሃሳብአችን ምልከታችን እና ተግባራችን – ማንንም ሆነ ምንንም ጎጂ የ አልሆነ፤ ይበልጥኡንም – ሰውዓዊ ገንቢ አልሚ እና ትሁት የሆነ ዕውነታ ላይ የተመሠረተ ሃሳብን እና ምልከታን አጐልባች በሆነ መልኩ እሚተገብር፤ በበጐ በጥሩ ሥነ-ምግባር የታነፀ ህይወት መምራትን የተጎናፀፈ – [የስብዕና ፍፁማዊዕነት] የ [ሰው]ዕነትአችን ረቂቅ መገለጫ ነው።

የ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና በ ማህበረሰብዓዊ ህይወት ውስጥ ሁለንተንዓዊ እና ፈርጀ-ብዙ አግባብዕነት የአለው ወሳኝ ባህሪይ እንደመሆኑ፤ በ አጠቃላይ በ ፖለቲካ – በቀረቤታ ደሞ በምርጫ ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና የአለው መሆኑ ዕሙን ነው። ይህ-እንን ዕውነታ የምርጫን ሁለት ፈርጆች በማጉላት ለማስገንዘብ እንሞክር። የምርጫ ሁለት ፈርጆች ስንልም – አንደኛው የተለያዩ መንገዶችን እሚጠቀሙ የምርጫ ዘመቻ ቅስቀሳዎች እና የተወዳዳሪዎች የመድረክም ሆነ ከ መድረክ በስተጀርባ እሚደረጉ ሙግቶች ሲሆን ሁለተኛው የ ተወዳዳሪዎች በጀት ምንጭ እና የ በጀት አጠቃቀም ሥነ-ምግባርን ማለትአችን ነው። እነ እኚህን ሁለት ፈርጆች በመርመር በመፈተሽ፤ የምርጫ ዘመቻዎች — የምርጫ ተሳታፊዎችን ማንዕነት እና ምንዕነት፤ በዋናዕነትም ብዙውን ጊዜ በቀላሉ እማይገለፁ ግብረ-ገብዕነት የጎደላቸው ባህሪያት፤ ፍንትው ብለው እሚታዩባቸው አጋጣሚዎች ናቸው።

በ ዋናዕነት፤ የ ምርጫ ተወዳዳሪዎች — በቅድመ-ምርጫ በምርጫ እና በድኅረ-ምርጫ ወቅት የአሳዩትንም ሆነ እሚያሳዩትን ተላይ በሁለቱ ፈርጆች ስር የአስቀመጥናቸውን መመዘኛዎች ተከትለን "ለ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ" ከ እሚባል ጎራ እሚመደቡ መሆን አለመሆናቸውን መገንዘብ ማለትአችን ቢሆንም ቅሉ፤ የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪዎችም ሆኑ ግልፅ/ስውር ደጋፊዎችአቸውም ቢሆኑ፤ በ እዚህ የ የሥነ-ምግባር ፍተሻ መአቀፍ ውስጥ መካተትአቸው አይቀሬ ነው።

እስቲ ለግንዛቤ ያክል ሁለቱን ፈርጆች በዝርዝር እንሂድባቸው፤ ላይ-ላይዉንም ቢሆን።

ፈርጅ አንድ – በ ምርጫ ወቅት፤ የ ምርጫ ዘመቻ ቅስቀሳ እና የተወዳዳሪዎች የመድረክም ሆነ ከመድረክ በስተጀርባ እሚደረጉ ሙግቶች በሁሉም መልኩ ትኩረትን ከ እሚስቡ ወሳኝ ፖለቲካዊ ሁነቶች ዝርዝር ውስጥ የመጀመሪያውን ቦታ እሚነጥቃቸው የለም።

ለሙያው ቀረቤታ የአላቸው ሰዎች እንደ እሚነግሩን፤ የምርጫ ዘመቻ ቅስቀሳንም ሆነ የተወዳዳሪዎችን የመድረክ እና ከመድረክ በስተጀርባ እሚደረጉ ሙግቶችን አሸናፊ ሊሆን በ እሚችል መልኩ ለመተግበር ይቻል ዘንድ የ አተገባበር ሥነ-ምግባራቸው "አወንታዊዕነት" – ወሳኝ እንደሆነ ይመክራሉ። ሌሎች ይህ-እንን እሚሞግቱ ደሞ አ---ይ አወንታዊ የሆነ ሁሉ ዕውነተኛ ነው ማለት ስለ እማይቻል፤ ዕውነተኛ የሆነም ሁሉ ደሞ አዎንታዊ ሆኖ ላይገኝ ይችላልና ይልቁን እስ – የ ምርጫ ዘመቻ ቅስቀሳንም ሆነ የተወዳዳሪዎች የመድረክ እና ከመድረክ በስተጀርባ እሚደረጉ ሙግቶችን የመፈተሻ መስፈርቱ ለ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ መሆን አለመሆንአቸው ላይ ቢያተኩር ይመረጣል ይላሉ። የ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና [ኢሴንሻል ኢንግሪዲየንትስ] ዕውነት እና ትህትና ስለሆኑ፤ እኛም ይህ የ ኋለኛው ሃሳብ ተመችቶን አለ።

አዎ፤ አንድን የ ምርጫ ዘመቻ ቅስቀሳም ሆነ የተወዳዳሪዎች የመድረክ እና ከመድረክ በስተጀርባ እሚደረጉ ሙግቶችን የ አተገባበር ሥነ-ምግባር ለ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ መሆን አለመሆንን ለመፈተሽ — ለ አድማጭ ተመልካች እሚቀርቡ መልዕክቶች፤ ሌሎችም መኖራቸው የተጠበቀ ሆኖ በዋናዕነት ግና – ዕውነተኛ መሆን አለመሆንአቸው እና በትህትና መቅረብአቸውን እርግጠኛ መሆን፤ እጅጉን ተገቢ ነው።

እንደ እምታውቁት፤ የምርጫ ነገር ሲነሳ – የተመራጭ ብቁዕነት እና ችሎታ፣ በመሠረትዓዊ ጎዳዮች ላይ የ እሚቀነቀን አቋም እና ከምርጫው ጋር የተያየዙ የ "ጀርባ" ታሪኮች ሁሉ በደምብ መፈተሽ ከአለባቸው ባህሪያት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እናም፤ የአንድን ተመራጭ ብቁዕነት ችሎታ እና አቋም ሃሳብን እና ሃሣብን ብቻ እንደመሣሪያ በመጠቀም ፊት-ለ-ፊት "ማጥቃት" እና "ጉሮሮ ለጎሮሮ መተናነቅ" ለ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ አለመሆን ተደረገው ሊቆጠሩ አይገባም — የ ሙግትኡ ሃሳቦች ዕውነት ላይ የተመረኮዙ እና ትህትና የተሞላቸው አገላለፆችን የ እሚጠቀሙ እስከሆኑ ድረስ!

ለምሳሌ፤ የጎሣ-ፖለቲካን ቋንቋ ጎጥ ላይ የተመሠረተ ዕኩይ ፌደራሊዝምን እና ፀረ-ሰው ፀረ-ዜጋ ፀረ-አንድዕነት ፀረ-ህብርዕነት ፀረ-ሃገር የሆነ ሕገ-መንግሥትን ተሸክሞ ሊሚገት እሚቀርብ ተወዳዳሪ፤ የፖለቲካ ፍጥረቱ ስግብግብዕነትን

የሃሰት-ትርክትን ውሸትን ጄኖሳይድ-ሽፋፋኝነትን አረመኔዕነትን ማስቀጠል የግድ ስለእሚለው — በመሠረትዓዊ ጉዳዮች ላይ የ እሚይዘው አቋም ጥቅል መዘዝ፤ ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ ማባሪያ የሌለው ኢ-ሰውዓዊዕነት ሃዘን-ሰቆቃ-ዕልቂት-መፈናቀል እና የሃገር-መፍረስ-አደጋ መሆኑ አይቀሬ ነው። እንዲሁም፤ ከምርጫው ጋር የተያየዙ የጀርባ ታሪኮች ሁሉ ለ 30-ዓመት የተተገበሩ ስለሆኑ፤ ዕውነተኛ ማስረጃ ፍለጋ ብዙም መዳዝ እምያስፈልጉ አይደሉም። እናም፤ የ ኢትዮጵያዊዕነት የ አንድዕነት ጎራ ዕጩዎች — በ የምርጫ ዘመቻ ቅስቀሳም ሆነ በመድረክ እና ከመድረክ በስተጀርባ በእሚደረጉ ሙግቶች ላይ እንዲያ የአለ ተወዳዳሪ ሲገጥም፤ በዕውነት በትህትና እና በግልፅ መሞገትን፤ ለግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ አለመሆን አድርገው ሊቆጠሩት አይገባም። በፍፁም!

ከ እዚያም በላይ፤ ውሸት ያው ውሸት ከመሆኑም በላይ አንድ-አንድ ውሸቶች ቀላል ወይም እማይጎዱ ሊመስሉ ቢችሉም ቅሉ ብዙውን ጊዜ – እማይጎዱ እሚመስሉ ውሸትዖችን እሚዋሽ ተወዳዳሪ እስከ እሚያዝ ድረስ ነው እንጅ፤ አጥፊ አፍራሽ ለሕዝብም ለሃገርም አደገኛ የሆኑ ውሸትዖችን እየዋሸ እንደአለ፤ በ ድፍረት መናገር ይቻላል።

ለምሳሌ፤ አረመኔው ገዥው ፓርቲ በሃሰት ትርክት ላይ የተመሠረተ የ ጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ መሆኑ እና እንደ ግለሰብም አመራሮቹ አባልዐቱ እና ደጋፊዎቹ – ዕልም የአሉ ውሸታምዕነትአቸውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መዘርዘር ለቀባሪው አረዱት እንዳይሆንብን ላዛሬ ብናልፈውም፤ በ እየ ዕለቱ ከእምንሰማቸው ውሸትዖች በአለፈ፤ ከኤርትራ ከሶማሊያ ከሱዳን ከአረብ-ሃገራት ከቻይና ወዘተ ጋር – ውስጥ ውስጡን ውሸትዖች ላይ የተመርኮዙ ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ የ አልተደረጉ የ ሕዝብ እና የሃገር ህልውናን አደጋ ላይ እሚጥሉ ስምምነቶች ድርድሮች ውልዖች መደርጋቸውን፤ መጠርጠሩ መጠየቁ ብልህዕነት ነው።

እናም፤ የገዥው ፓርቲ አባላትንም ሆነ በገዥው ፓርቲ ስር በግል እሚቀርቡ ዕጩዎች በ ፖለቲካዊ አፈጣጠርአቸው ለ የ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ የአልሆኑ መሠሪ ፍጡራን መሆንአቸውን በተደጋጋሚ የታዘብናቸው በመሆኑ፤ ሃገርን መጠበቅ እና ሕዝብን በቀናዕነት ማገልገልን እሚጠይቁ የሕዝብ ስልጣን በርጩማዎችን በምርጫ እንዲያሸንፉ መፍቀድ፤ ከታሪክዓዊ ስህተትዕነትም በ አሻገር — ሃጢያትም ጭምር ነው እሚሆነው።

ስለሆነም፤ ብቁዕነትን ችሎታን አቋምን – እንዲሁም ከምርጫው ጋር የተያየዙ የጀርባ ታሪኮችን በተመለከተ፤ የሙግት ሃሳብዖችን በተጨባጭ ማስረጃዎች መረጋገጥ እሚችሉ ዕውነታዎች እስከሆኑ ድረስ እና ስም ለማጥፋት ሲባል እሚደረጉ እስከአልሆኑ ድረስ — ኢትዮጵያዊዕነትን ለ እሚል መራጭ ሁሉ በአፅንዖት በትህትና በግልፅ ማሳወቁ ማስተማሩ – ታሪክዓዊ የህልውና ግዴታችን ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።

በተጨማሪም፤ የ ገዥው ፓርቲ ዕጩዎችንም ቢሆን ወደ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ዳግም ብቅ እንዳይሉ ፖለቲካዊ ማንዕነትአቸውን እና ምንዕነትአቸውን በተመለከተ በሕዝብ ፊት በ ጥሩ ቋንቋ ልክ ልክአቸውን በግልፅ መንገሩ ማጋለጡ ተገቢ እንደሆነ አስገንዝበን ማለፍም እንወድ አለን — በ እኛ ወገን ጥቅም ላይ በእሚዉሉ ናሬቲቮች ዙሪያም፤ በቅድሚያ ሰፊ ንባብ እና ምክክር ሊደረግባቸው እንደእሚገባም ጭምር!

ፈርጅ ሁለት – ተላይ እንድአሠፈርነው፤ የ ግለሰብም ሆነ የ ፓርቲ የቅድመ-ምርጫ የምርጫ እና የድኅረ-ምርጫ ዘመቻ የበጀት ምንጭ እና የበጀት አጠቃቀም ሥነ-ምግባር — ለ የግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ መሆን አለመሆን እሚመዘንበት ሌላው መስፈርት በመሆን ያገለግላል። ዋናው ተልዕኮም፤ [የምርጫ ዘመቻዎችን] እና በምርጫ ዘመቻ ወድድር አማካኝዕነት እሚመሠረትን [መንግስት] — የበለጠ አግባብዕነት የ አላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

በ ዲሚክረሲ፤ እየአንድ አንዱ ሰው ዕኩል ተደርጎ ነው እሚወሰደው። ሃብታም የሆኑ ሰዎች፤ ከፍተኛ የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ከፖለቲከኞች ጋር ሽርክና ዝምድና ሊፈጥሩ እሚችሉበት አጋጣሚ እንዲኖር አይፈቀድም። ማናቸውም የምርጫ ድጋፎች ጥቅምን ከ እሚፈልጉ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች እንዳይመጡም በአፅንዖት ይመከራል።

ከምርጫ ጋር የተያያዘ፤ በጀት ንብረት የሰው ሃይልም ሆነ ጊዜ – ለዕጩዎች ለምርጫ-ቅስቀሳ ሰራተኞችም ሆነ ለደጋፊዎች የግል ጥቅም እንዲዉሉ ማድረግ ለግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ አለመሆን ብቻ ሳይሆን፤ እዚህ እኛ በአለንበት ሃገር ለምሳሌ – ወንጀል እንደሆነም ነው እሚቆጠረው። በተመሳሳይ፤ ከምርጫ ጋር የተያያዘ ገቢ እና ወጪ በምንም መልኩ በመንግሥት ሃብት [ተቋማት መዋቅራት ጊዜ ገንዘብ ንብረት እና የሰው-ኃይል] መታገዝም የለበትም። በፍፁም!

በእዚህ ረገድ፤ የገዥው ፓርቲ የዕለት-ተ-ዕለት ተግባሩን እሚያንቀሳቅስበት በጀት ምንጩ የት እንደሆነ፤ በ መቶ-ሺህ ይቆጠራሉ የአላቸውን ካድሬዎቹን እና የፓርቲው አባላትን መሪዎችን ደምወዝ ቀለብ አንፈላሳሽ ወጪዎችን እሚከፍላቸው ማን እንደሆነ፤ የገዥው ፓርቲ እና የምርጫ-ቦርድ ግንኙዕነቶች ምን እንደ እሚመስሉ – ማለትም፤ በቅድመ-ምርጫ በምርጫ በድኅረ-ምርጫ ወቅት ገዥው ፓርቲ ምን ምን ሚና እንደነበረው ሊጠየቅ ሊፈተሽ ሊበረበር ሊመረመር የግድ ነው — ወሳኝ ሕዝብዓዊ እና ሃገርዓዊ ፋይዳ የአላቸው ጉዳዮች ናቸው እና! እናም፤ በ የምርጫ ዘመቻ ቅስቀሣ ላይም ሆነ በ መድረክ እና ከመድረክ በስተጀርባ በ እሚደረጉ ሙግቶች ላይ፤ አጋጣሚው በተገኘ ቁጥር በ እነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በድፍረት በቆራጥዕነት በግልፅ መሞገቱ ለ የግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ አለመሆን እንደአይደለ እና እንዲያውም፤ ለሕዝብ ማሳወቁ ማስተማሩ ማጋለጡ፤ ኢትዮጵያን የእሚሉ ተወዳዳሪዎች ሁሉ ታሪክዓዊ ግዴታቸው መሆኑን ደግመን ማስገንዘብ እንወድ አለን።

ልብ እንበል ጎበዝ፤ በምርጫ ዘመቻ ወቅት ከተቃራኒው ጎራ ግለሰቦች ጋር እሚደረጉ ሙግቶች – በእነእዚያ ወገን የቀረቡ ዕጩዎችን ለማሳመን እሚደረጉ አይደሉም። ይልቁንስ፤ በምርጫ ወቅት ከተቃራኒው ጎራ ግለሰቦች ጋር እሚደረጉ ሙግቶች ላይ፤ የእኛን ሃሳብዖች ዕውነት ላይ የተመረኮዙ እንዲሆኑ እና በትህትና እንዲገለፁ ማድረግ፤ ለ ሕዝብአችን ለ ሃገርአችን የአለንን ከፍተኛ ፍቅር፣ ከፍተኛ ከበሬታ ማሳያ እና መራጮችአችንን በማንቃት በማሳወቅ በማስተማር ሚዛን

እሚደፋ ሙግት በማድረግ የመራጮችአችንን የአመኔታ ድምፅ ለማሸነፍ መሆኑን መገንዘብ — ብልህዕነት ነው።

ፅናት

ጐበዝ፤ ስለ ፅናት ስንአነሳሳ – ቀና መልካም ጥሩ ለ ግብረ-ገብዕነት ልዕልና ተገዢ የሆኑ ጉዳዮችን ኋላ-ኪስአችን ውስጥ አስቀምጠን እንደሆነ፤ ልብ እንደእምትሉልን በመገመት ነው።

ፅናት – እንደ እምአይነጥፍ የዕቅድ ትግበራ ሂደት ዕምቅ ኃይል፤ የብዙ የተለያዩ ባኅሪያት ውጤት ነው። አዎ፤ ፅናት – የጥንካሬ የአይታክቴዕነት የብርታት የቆራጥዕነት የተአማኒዕነት የታታሪዕነት የብልህዕነት የአላሚዕነት የተላሚዕነት የአርቆ-አስተዋይዕነት የጠያቂዕነት የመርማሪዕነት የተስፋ-ሙሉዕነት የ ለመሻሻል-ዝግጁዕነት የ ለመለወጥ-ዝግጁዕነት የጤናማዕነት የጀግናዕነት — ምጥን ምግብ ነው።

ትክክል። ለ ማህበረሰብዓዊ ህይወት ዕድገት እና ቀጣይዕነት ወሳኝ የሆኑ ማናቸውም ጉዳዮችአችን፤ ፅናትን ይጠይቁ አሉ። የ እየግልአቸው ስፋት እና ጥልቀትም ሆኑ እሚጠይቋቸው መስዋዕትዕነት ይለያዩ እንጂ – አዲስ ቋንቋ መማር የሰፈር ልጆችን የእግር-ኳስ ቡድን ማሰልጠንም ሆነ በ ኢትዮጵያ ዕውነትኛ ዲሚክረሲን ማስፈን እሚጠይቋቸው እርምጃዎች ሁሉ፤ ፅናትን እሚጠይቁ ናቸው።

ፅናት፤ የ ቀና ፅናት አርአያ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ እሚቻለው — ዕድገትን ስልጣኔን ቀጣይዕነትን ወደፊት መራመድን ዕውን ማድረግ በ እሚያስችል መልኩ በፅናት ስር እሚካተቱ ፈርጀ-ብዙ ባኅሪያትን እንደ እየ አግባበ-ነገሩ በደንብ መተነተን መፈተሽ ማደስ ማሻሻል መቀየር የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው። አዎ፤ እነ-እኛ ፈርጀ-ብዙ ባኅሪያትን አናብቦ አሳልጦ ማስተናገድ የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው።

አልያ እማ፤ ፅናት ፅናትዕነቱ ይደበዝዝ እና [ጭፍን ግትርተኛዕነት] ለመሆን ይገደዳል። በፅናት እና በጭፍን ግትርተኛዕነት መሃከል የአለውን ልዩዕነት በእሚገባ መገንዘብ ጠቀሜታው ግዙፍ ነው። ጭፍን ግትርተኛዕነት፤ ወቅትዓዊ የሆኑ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመመርኮዝ በማገናዘብ የተለያየ/የተሻለ ስልት/ዘዴ መጠቀምን የእሚገድብ እና በእዚያም ሳቢያ ፅናት፤ ሲጀመርም ተገቢ እንደሆነ የሚታመንበትን ተልዕኮ – ማለትም፤ [ስኬት]ዐማዕነትን ዕውን እንዳይሆን የሚያደርግ እና ፅናትን መና የማስቀረት አቅም ያለው — ተቀባይዕነት ሊኖረው እማይገባ ኮንስትራክት ነው።

ገዥው ፓርቲ ~~ለ ምዕተ-ዓመት~~ ለ 30-ዓመት በ “<u>ፅናት</u>” በስልጣን ላይ የቆየ ቢሆንም፤ የ እርሱ “ፅናት” በቀና ባህሪያት የታነፀ ሳይሆን — መገለጫው ኢ-ሰውዓዊነት አፍራሽዕነት አረመኔዕነት ላይ ሙጭጭ ማለት በመሆኑ፤ የ እርሱ ፅናት – ቀና ፅናት የመሆን ዕድል ሳይገጥመው የቀረ ጭፍን ግትርተኛዕነት እንደሆነ እንገነዘብ አለን። እኛም ብንሆን ዛሬ-ዛሬ እየአደረግን የአለነው ወፍ-ዘራሽ ትግልም፤ እንዲሁ!

ስኬት

ስኬት፤ ትክክል – እንደ ስኬት በጥንቃቄ የተቀመረን ተልዕኮ፣ በፅናት ተግባርዓዊ የሆነን ዕቅድ/ውጥን ዕውን ሆኖ ማየት ማለት ነው። ስኬትዐማ ነን የእምንለው ምን ዕውን ሲሆን እንደሆነ እና መመዘኛ መስፈርቶቹ ምን ምን እንደሆኑ በቅድሚያ የ አልተዘጋጁ በግልፅ የ አልታወቁ እንደሆነ፤ ነገሮች ሁሉ የተበለሻሹ ሆነው መቅረትአቸው አይቀሬ ይሆንና — ስኬትም፤ የአገራችን ሰው — የ ዉሃ ሽታ፤ እንዲል ዓይነት ሆኖ ይቀራል።

ገዥው ፓርቲ፤ “ስኬትኡ” ከድርጅቱ ተልዕኮ አኳያ ለጊዜው ዕውን የሆነለት ቢመስልም ቅሉ፤ እኛን በተመለከተ የ “ስኬት”ዖቹ መገለጫዎች – ሰላም እና መረጋጋት ማጣት፣ ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ በተለይም፤ ዐማራ እና የ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያን ላይ የአተኮረ አላባራ የአለ መንግስትዓዊ [ሃዘን ሰቆቃ ዕልቂት መፈናቀል ችጋር ጄኖሳይድ] እና የሃገር መፍረስ አደጋ በ መሆናቸው — ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ <u>ስኬት</u> ሳይሆን አስፀያፊ አስነዋሪ አረመኔዓዊ ወንጀሎችን ~~ለ ምዕተ-ዓመት~~ ለ 30-ዓመት የአስተናገደ ይቅርታ እማይገባው፤ ማፈሪያ <u>ውድቀት</u> መሆኑን ነው እምንመሰክረው።

በመጨረሻም

እየጠፋ የአለ ሕዝብ፤ እየፈረሠች የአለች ሃገር — እየአጠፋት እየአፈረሣት የአለን የፓርላማ የካቢኔ ደናቁርት የጎሣ-ድርጅቶች ስብስብ፤ ዛሬውኑ ከስልጣን ወርዶ ህግ-ፊት እንዲቀርብ ከማስገደድ ይልቅ — ዓይኑን በአሸቦ አጥቦ ምረጡኝ እየአለ እንዲያላዝን ዕድል እሚሰጥ ሕዝብ፤ ዕድል እምትሰጥ ሃገር በዓለም ዙሪያ ብንፈልግ፤ ዛሬ እጅ-ከፍንጅ እምትያዘዋ የእኛዋ ጉድ ኢትዮጵያ ብቻ እንደእምትሆን በፍፁም አንጠራጠርም።

አረመኔው አዴፓ-ኦነግ መራሹ የጎሣ-ድርጅቶች ስብስብ፤ ኢትዮጵያን አኬልዳማ አድርጎ እየአሰቃያት ነው። የበሽተኛ ፖለቲከኞች ጥርቅም የሆነው ይህ ገዢው ፓርቲ እያሰለጠነ እሚያሰማራው የ ኦነግ መንጋ፤ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያንን — በተለይም፤ ከፖለቲካ ጋር ንክኪ የሌላቸውን መሣሪያ የአልታጠቁ ሰላማዊ የዐማራ ተወላጆችን እና የተዋህዶ አማኒያንን ፈጅቶ ኢትዮጵያን ሊያጠፋት ቆርጦ ተነስቷል። ጨፍጫፊዎችን እየአሰማሩ የኢትዮጵያ ምድር በንፁሃን ደም እንዲጨቀይ እየአደረጉ የአሉ የመንግሥት አካልዐት፤ ዛሬዉኑ ከስልጣን ወርደው ለፍርድ እንዲቀርቡ — እንጮሃለን!

ምርጫው፤ ሃገርዓዊ ፍትህዓዊ እና ነፃ ሊሆን እማይችል፣ የ ንፁሃንን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት እሚያራዝም እና አንድአችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረውም እማይጠበቅ ስለሆነ — ዛሬም፤ እንዲሰረዝ ማስገደድም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በሙሉ ቦይካት ያደርጉ ዘንድም፤ በአፅንዖት እንመክር አለን። ለእዚያም፤ እንደ የሰላም እና መረጋጋት ዕጦት እና የኮቪድ-19 ስርጭት በርደን ኤክስፖኔንሻሊ ማሻቀብን ጨምሮ፤ ከበቂ በላይ ኢትዮጵያዊ ምክንያትዖች አሉ። ምርጫው እንዲሰረዝ እምንፈልገውም፤ ገዥው ፓርቲ የጎሣ-ፖለቲካውን ተሸክሞ ያንጐላጅብን ዘንድ ሳይሆን በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያዊ የጋራ የምክክር ሂደት እና ወደ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ምስረታ እንድእንአመራ መሆኑን፤ ማስገንዘብም እንወድ አለን።

አዎ፤ “ህይወት” መቀጠሉ ስለእማይቀር – [አይበለው እና] በምርጫው መሳተፍ ግድ ከሆነብን ግና የገዥው ፓርቲ ዕጩዎችን ጠንቅቆ በመለየት ሽራፊ የአመኔታ የድምፅ ካርዱን እንድአይሰጣቸው፤ ሕዝብ  በእሚገባ ይምከር ይዘጋጅ። ሂደቱም ሆነ ውጤቱ የተጭበረበረ የተዛባ መሆኑ ከተረጋገጠ፤ ሕዝብ እስከመጨረሻው በጋራ ይታገለው ዘንድም ዝግጅቱ ከወዲሁ ይጠናቀቅ — አንድ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት እሚመራው ሁለገብ ሕዝብዓዊ እንቅስቃሴን በማቀጣጠል!

ጐበዝ፤ ጎስቋላው ሕዝብዓዊ ትግል፤ ተስፋ እንድያስቆርጠን መፍቀድ የለብንም። አዲስ ፓርቲ ድርጅት ማህበር አድ-ሃክ ኮሚቴ በእየቀኑ በማቋቋም ለ የአለፉት 30-ዓመታት ያህል የሞከርነው ወፍ-ዘራሽ ትግል፤ እንዳልበጀን መረዳቱ ተገቢ ነው። ዛሬም፤ ሙሉ ዕምነትዐችንን የብዙሃን መገናኛ ላይ ብቻ ጥለን እምንአደርገው አንጀት ላይ ጠብ እማይል ጥረት አደጋው ከአልታየን — ሲሪየስ የመብሰል ሂደት ውስጥ ማለፍ እንደ እሚጠብቀን ፈጥነን መረዳቱ፤ እጅጉን — አዎ፤ እጅጉን ወሳኝ ነው። እናአም፤ ሁልአችንም የትግል ፊደልአችንን መልሰን ማውጠንጠን እና በ [ሰው]ዓዊዕነት ሥነ-ምግባር በፅናት የተፈተነን አንድ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የፖለቲካ ድርጅት ፈልገን በማጐልበት እሚጨበጥ ተገዳዳሪ አሸናፊ መሆን እሚችል ሁለገብ ሕዝብዓዊ እንቅስቃሴን በማፋፋም፤ ሃገር-አፍራሹ ሕዝብ-ጨፍጫፊው ቅርስ-አውዳሚው ዋሾው የጎሣ-ድርጅቶች ስብስብ ከፖለቲካው ማማ ወርዶ ይባረር ዘንድ በተናጠል-ሳይሆን በኢትዮጵያዊ ቆራጥዕነት በአንድዕነት በጋራ፤ መሬት ላይ ቆመን — እንነሳ!

በሉ እንግዲህ፤ ለዛሬው በእዚሁ ይብቃን።

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንገናኝ –

# የትዉልድ አደራ አለብን!

ግንቦት ፳፻፲፫ ዓ.ም ‖ ሜይ 2021

**አዳራሽ** – ነገሮች ሁሉ የከፉ ደረጃ ላይ ናቸው። የተጠናከረ ሁለገብ ሕዝብዓዊ ንቅናቄን እሚጠይቁ! ዛሬም ቢሆን፤ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ መሠረትዓዊ ችግርያችአችን፤ ህወሓትዓዊ ኦነግዓዊ እና ኦዴፓ-ኦነግ መራሽ ብልፅግናዊ ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ የጎሣ-ፖለቲካ እና እኩዩ ፈደራሊዝም፤ በተጓዳኝም አላባራ የአለው ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ፣ ጄኖሳይድ፣ ሃገርን የመውረር የማስወረር፣ ሃገርን የማፍረስ የማስፈረስ እና ኦሮሙማን የማንሰራፋት ዘመቻ ናቸው። የተጋረጡብን ፈተናዎች፤ ፈርጠም የአለ ሁለገብ ሕዝብዓዊ ንቅናቄን እሚጠይቁ ናቸው። ቆፍጠን ያለ ድርጅትዓዊ ቁመናን የግድ እሚል – ሕዝብዓዊ ንቅናቄ። ሕዝብን ከአደጋ ሃገርን ከፍርሰት እሚጠብቅ ንቅናቄ። ኢትዮጵያ ዛሬ፤ [መንግሥት] አልባ ናት – በፈጣሪዋ እጅ የ አለች። መንግሥት ተብዬው ሃገርን እና ሕዝብን ከድቷል። ገዥው ቡድን፤ የስልጣን ጥማቱን ለማርካት – ብሎም፤ በዙሪያው የአሉትን በተልዕኮ አንድ ዓይነት – የበርጩማ ተቀናቃኞቹን ለማስታገስ ይቻለው ዘንድ፤ የጋራ ጠላትአቸው እንደሆኑ እሚስማሙባቸውን፤ ኢትዮጵያን እንደ ሃገር፣ ዐማራን እና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያንን እንደ ሕዝብ — [ጭዳ] በማድረግ እድሜውን እያራዘመ ነው። የገዥው ቡድን መንጋ እና ደናቁርት አሽቃባጮችአቸው የ ኢትዮጵያ ቀንደኛ በደለኞችዋ ናቸው። አላባራ ለአለው ጄኖሳይድ፣ የሃገር ምዝበራ እና ፍርሰት ቀዳሚ ተጠያቂዎች! መሠረትዓዊ ችግሮችአችን እንዳሉ [ምን አልባትም ተባብሰው] ይቀጥላሉ። ምርጫው ተደረገም አልተደረገም፤ እሚያመጣው አንዳችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ አይኖርም። መፍትሄው ግልፅ ነው – ምርጫው ሙሉ በሙሉ ይሰረዝ፣ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ይዋቀር፣ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት ይቀረፅ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ይመሥረት። አዎ፤ ልክ እንደ የስልሳዎቹ እንደተለሙት። ያኔም ትክክል ነበሩ – ዛሬም ትክክል ናቸው እና! እሚታረም ነገር ከአለ ይታረማል። ከፊትአችን እየተቃረበ የመጣው ምርጫ፤ ሃገርዓዊ ፍትህዓዊ እና ነፃ ሊሆን አይችልም። የ ዜጎችን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት እሚያራዝም፣ አንድአችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረውም እማይጠበቅ እና መሠረትዓዊ ችግርያችአችንን እሚያባብስ፤ አንዳችም መፍትሄ ይሆናል ተብሎ እማጠበቅ — ፊዩታይል ኤክሰርሳይስ ነው። አዎ፤ ምርጫው ገና ከሂደቱ ከሽፏል። የ ኢትዮጵያ በደለኞች ጠብአቸው ከ [ዕውነት] ጋር ነው። እናም፤ ይሸንፋሉ! ሕዝብ – ባለመዘጋጀቱ፤ ገዥው ቡድን ፈርጠም ብሎ የታየበት ጊዜ ላይ ነን። ከፍተኛ ጥፋት እያደረሰ ነው – ገዥው ቡድን። አንዲት ቀን – ሰቆቃ ውስጥ የአለውን እና በ ዕልቂት እየተናጠ የአለውን የ ኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይም – ለ ዐማራ እና ለ ተዋህዶ አማኒያን ለቅሶ ያልደረሱ የ ገዥው ቡድን ፍጡራን እና አሽቃባጮቻቸው፤ አሁን ምርጫ ሲደርስ ምረጠን ሊሉ ደጁን እሚረግጡት ሁሉ፤ ለ ሕዝብ የ አላቸውን ከፍተኛ ንቀት እና የ እራስአቸውንም ኀሊናቢስዕነት መገለጫ ነው እና፤ ጀግናው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ — አደራ፤ እንድአመጣጣቸው አስተናግዳቸው! ኢትዮጵያ – ድንበርዋን፣ ኢትዮጵያዊያን – [ሰውዓዊ] መብታችንን ህብርዕነትአችንን አንድዕነትአችንን እስከእምናስከብር እና [የ ኢትዮጵያ ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ እስኪያደርግ ድረስ፤ የተጀመረው ሕዝብዓዊ ንቅናቄ ተጠናክሮ ይቀጥል። ሌላ አማራጭ የለም!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

ነገሮች እየከረሩ እየመረሩ እየከፉ መምጣትአቸውን ታሳቢ በማድረግ፡ የፈረደባት ኢትዮጵያን በተመለከተ፤ ዕምንዕለውን ለማለት – ከፊትአችሁ ቀርበን አለን።

እናም፤ “አብረን እንቆይ” – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

የ [ሰው] ዘር፤ ፍፁምዓዊ ነፃዕነትን ዕውን ማድረግ ሳያረጋግጥ እንቅልፍ እንዳይወስደው፡ መለኮትዓዊ ተፈጥሮው የግድ ይለው አለ። ይህ እም፤ ዕውነት ነው። አዎ፤ በ ከሃዲ በ ደካማ በ መሠሪ ሰዎች ዘንድ ትጐሳቆል እንደሁ እንጂ፤ በአመንዐት በታመንዐት ጀግና ሕዝብ ፊት እና በ ፈጣሪዋ በ ጌታ ፊት ግና – ዕውነት፤ ምንጊዜም አሸናፊ ናት። ኢትዮጵያም ዕውነት ናት!

ስለ መሠረትዓዊ ችግርያችአችን ስንሞግት፤ ዛሬ የመጀመሪያችን አይደለም፤ የመጨረሻችንም አይሆንም – ኢትዮጵያዊዕነት አሸናፊ እስከእሚሆን ድረስ።

ለ 30-ዓመትዐት ተግባርዓዊ እየተደረገ የአለው፡ ህወሓትዓዊ ኦነግዓዊ እና ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ብልፅግናዊ ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ የጎሣ-ፖለቲካ እና እኩዩ ፈደራሊዝም፤ በተጓዳኝም አላባራ የአለው ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ፣ ጄኖሳይድ፣ ሃገርን የመውረር የማስወረር፣ ሃገርን የማፍረስ የማስፈረስ እና ኦሮሙማን የማንሰራፋት ዘመቻ ሁሉ – ጠብአቸው ከ [ዕውነት] ጋር ነው። መነሻቸውም የሀሠት ትርክት ከሃዲዕነት መሠሪዕነት አጉል አራዳዕነት እንጭጭዕነት እና በሽተኛዕነት ነው። ይህ-እንን የተደራጀ ዕብደት ከ እሚመራው ከ ሰሞነኛው ገዥው ቡድን ጋር፤ እንደ [አደልት] ሃሳብ መለዋወጥ አይቻልም – በፍፁም! እኛ ሃገር የአሉ ላሞች እሚሰጡት ወተት ቀለሙ [አረንጓዴ] ነው ይል እና፤ ነጭ ነው እምትሉ ሁሉ ተሳስታችኋል፤ የስልሳዎቹ ትውልድ ከሸቀጥ ጋር ወደ ሃገር ኢምፖርት ያደረገው ቀለም ነው [ነጩ] ይል አለ። እስቲ ፈጣሪ ያሳያችሁ፤ ዛሬ አንድ ቦታ የአነበብነው “የተወሩት የሃሰት ወሬዎች” የተባሉት የትኞቹ ናችው?

የ ኤርትራ ሠራዊት – ትግራይ መግባት? የደምቢ-ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዋች ደብዛ መጥፋት? ዜጎች በኦነግ መንጋ ከእየቀየአቸው መባረር? ኢትዮጵያዊያን በማንዕነትአቸው እየተለዩ – መባረር፣ መታረድ፣ መጨፍጨፍ፣ እንደ ቆሻሻ በገፍ ወደ ጉድጓድ መዘርገፍ? ፅንስ በሳንጃ ተቀዶ መውጣት፣ ህፃንዐትን አረመኔአዊ አገዳደል መግደል፤ የ[ሰው]ን ልጅ በቤት ወስጥ ዘግቶ ማቃጠል፣ መንደር በከባድ መሣሪያ መደብደብ በእሳት ማጋየት ማውደም፣ በ ዕብድ የ ኦነግ መንጋ መውረር? በ ጎረቤት ሃገር ድንበራችን ማስደፈር? ኦሮሙማን መንሰራፋት?

ከቶ የትኞቹን ይሆን ገዥው ቡድን – “የተወሩት የሃሰት ወሬዎች” የአለን? ከ እንዲህ ዓይነት ፍጡራን ጋር እንዴት መግባባት ይቻላል – ጐበዝ?! እንዴትስ ሃገርን ለእሚያክል

ሃላፊዕነት ይታመናሉ?! እኛን የበለጠ አልገባ የአለን ደሞ፤ በ 21ኛው ክፍለ-ዘመን ባርቤሪክዕነትን መምረጥ – ለምን? ለምን ለምን ለምን???

ሕዝብዓዊ ንቅናቄ

ሰሞነኛው ገኸው ቡድን የ ኢትዮጵያን ሕዝብ፤ በተለይም ዐማራውን እና የ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያንን፡ እንደ ጋሪ ፈረስ [ብላይንደርስ] አልብሶ ሊነዳ እየከጀለው እንደ አለ ግልፅ ነው። እስከ አሁንም እየተሳካለት ይመስላል። ሕዝብ ከ ዕንቅልፉ ነቅቶ አንድ ነገር ከአላደረገ በስተቀር፤ ኢትዮጵያ- ኢትዮጵያ እየ አለ እየአታለለ አልያም የ አለምንም ርህራሄ ሕዝብን እየጨፈጨፈ እና ሃገርን እያስወረረ – የ [ኦሮሙማ] ዕቅድኡን ተግባርዓዊ ማድረጉ አይቀሬ ነው።

ሰሞነኛው ገኸው ቡድን፤ ቤተመንግሥት ቁጭ ብሎ እያሰለለጠነ የአለውን የ ኦነግ ሰራዊት፤ በ ኢትዮጵያ ግዛቶች ሁሉ እየአሰማራ – ሃገሩን ሁሉ ነጥቄ እናንተንም ጨፍጭፌ፡ የተረፈውን አባርሬ ተመቻችቼ ልኑር እየአለን ነው። እስከነ አካቴው፤ በ ሶሪያ ሰዎች ሊተካን ቢቃጣውም አይገርመንም።

የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤ ይህ አፈ-ታሪክ ሳይሆን፤ ዛሬ እየኖርነው የአለነው ሪያሊቲ ነው።

ሰሞነኛውን ገኸው ቡድን ጨምሮ፤ የኦሮሙማ ዲሳይፕልስ ኢትዮጵያን አያውቋትም፤ አልያም ከድተዋታል። ከፊትአችን እየተቃረበ የመጣው ምርጫም፤ ሃገርዓዊ ፍትህዓዊ እና ነፃ ሊሆን እማይችል፣ የ ንፁሃንን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት እሚያራዝም፣ አንድአችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረውም እማይጠበቅ እና መሠረትዓዊ ችግርያችአችንን ማባባስ ከአልሆነ በስተቀር፤ አንዳችም መፍትሄ ይሆናል ተብሎ እማይታሰብ — ፊዩታይል ኤክሰርሳይስ ነው። አዎ፤ ምርጫው ገና ከሂደቱ ከሽፏል። ለ ዲሚክረሲ በር ከፋች ነው እሚባለውም፤ ተራ ቧልት ነው።

በነገርአችን ላይ፤ ዲሚክረሲ "ከ ሸቀጥ ጋር" ወደ ኢትዮጵያ ኢምፖርትድ የተደረገ ቃል አይደለም አንዴ!?

ወድ የኢትዮጵያ ልጆች፤ መንግሥትዓዊ – ክህደት ብልግና ጭቆና ዝርፊያ ወረራ ጭፍጨፋ፤ ሕዝብዓዊ ንቅናቄን መውለዱ አይቀሬ ነው። የጊዜ ጉዳይ ከአልሆነም በስተቀር፤ ድሉ የሕዝብ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

በ የአለፈው ወር ውስጥ ጀምሮ፤ በሃገርቤትም ሆነ በ ዓለም ዙሪያ፤ በተለይ – ዐማራ [ሆ!] ብሎ የተነሣው እና [በቃ!] ያለው – ዕውነትም ቢመርረው ቢያንገሸግሸው ነው። ዳር ድንበሩ ቢደፈር ሃገሩ ብትወረር ወገን ቢሰቃይበት ነው። አዎ፤ ዐማራ ሆ! ብሎ የተነሣው – እናት ማህፀን ውስጥ የአለ ፅንስ በሳንጃ ቢታረድ፣ ስቀው ሮጠው ቦርቀው የ አልጠገቡ ህፃናት ቢጨፈጨፉ፣ ምስኪን ጭሮ ለፍቶ አዳሪ እናቶች አባቶች፤ ወጣት ሽማግሌ አረጋዊያን የ አለምንም ዕዳቸው ቢታረዱ ቢጨፈጨፉ እንደ ቆሻሻ በጅምላ ወደ ገደል ቢወረረሩ ቢሳደዱ በእሳት ቢቃጠሉ — አዎ፤ ተቆራርጠው ስለተበሉም ጭምር ነው።

ሰሞነኛው ገኸው ቡድን ተቀበለውም አልተቀበለው፤የአንድ ሃገር የበላይ ሃላፊ – ሕዝብ ነው። መንግሥት፤ የ ሕዝብ ተቀጣሪ ሰራተኛ በመሆን፤ ሃገርን እና ሕዝብን በአግባቡ ያገለግል ዘንድ እሚመረጥ እሚቀጠር ኤንትቲ ነው። የሃገር ሉዐላዊዕነትን እየአስደፈሩ፣ ሊያገለግሉት እሚገባን ሕዝብ እየጨፈጨፉ መቀጠል አይቻልም። ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ይ-ህ ሁሉ እየሆነ እንደ አለ እሚያውቅ በ መንግሥት የሃላፊዕነት ቦታ ላይ የተቀመጠ ማን አቸውም የ[ሰው] ፍጡር፤ እንዴት ከተጠያቂዕነት ላመልጥ እችላለሁ ብሎ እንደ እሚያስብ መገመቱ ቀላል አይደለም። ወይ ህግ አልያም የኢትዮጵያ ዓምላክ ለ እየ አንድአንዱ ወንጀለኛ፤ ተገቢውን ፍርድ እንደ እሚሠጥ ግና፤ አንጠራጠርም — አዎ፤ የጊዜ ጉዳይ ነው!

በቅርቡ የተቀሰቀሰው ሕዝብዓዊ ንቅናቄም፤ ጫጫታ ሳይሆን <u>ክሪቲካል ሲግናል</u> ነው። [ሰው] ብትሆኑ ኖሮ፤ ተገቢውን ትኩረት እሚሻ እና እርምት እሚጠይቅ ክሪቲካል ሲግናል!

ሕዝብ እየነገራችሁ የአለው እኮ፤ የ ህወሓት ኦነግ ውላጅ ኦዴፓ- ኦነግ መራሹ ብልፅግና ፓርቲ፤ ከ አስመሳይ "መንግሥትዕነት" ወደ የለየለት ባዕድ ወራሪ መንጋዕነት መለውጡን ነው። ሕዝብ [በቃ!] ሲልም — መገደል መጨፍጨፍ፣ መንደራችን መቃጠል መውደም መፈናቀል፣ ኢትዮጵያን መዝረፍ እና ኢትዮጵያን ማፍረስ ይቁም፤ እየ አለ ነው።

አልሰማም አላችሁን እንጂ – እኛ እንዲያውም፤ ሃገር ማስተዳደሩን አልቻላችሁበትም እና [የ ሕዝብን ስልጣን ለሕዝብ አስረክቡ] ነው እያልንአችሁ የአለነው። ይህም ከሰሞነኛው ገኸው ቡድን መሪ ሊጀምር ይገባል — የ መንደር ካድሬዎቻችሁን በማባረር እምትገላገሉት ከመሳላችሁ፤ ክፉኛ ተሳስታችኋል! ለ ኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ እንደ ሃገር ለ ኢትዮጵያ፤ አሳቢ መምሰሉን ተውት። ቅጥፈት እንደሆነ ሁሉም አውቆባችኋል – የውጪዎቹ ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ። የኦሮሙማ ዲሳይፕሎችአችሁን ይዛችሁ ከ ኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ጥርግ በሉ! ከ እናንተ የተረፈውን ሕዝብ እና ከእናንተ የተረፈችውን ሃገር ይዘን እንገነባለን።

ጉበዝ፤ የተጋረጠብን ፈተና የተቀነባበረም የተደራጀም ጭምር ነው። በ ሰሞነኛው ገኸው ቡድን መሪ ስምሪት ሰጪዕነት እና በ ሕገ-መንግሥቱ ሽፋን እየተተገበረ የአለው መንግሥትዓዊ የሃገር ክህደት እና መንግሥትዓዊ ጄኖሳይድ ነው። በደለኞችአችን ሁሉ ጠብአቸው ከ [ዕውነት] ጋር፤ መሠረትአቸው የህሡት ትርክት ከሃዲዕነት እና መሠሪዕነት ስለሆነ፤ የትም እንደ እማይደርሱ ዕሙን ነው። የ ኦሮሙማ ተልዕኮአቸውም ቅዡት እንደሆነባቸው ይቀራል እንጂ፤ አይሳካላቸውም።

ሆኖም ግና፤ ሕዝብ – የ እኛ ናቸው ብሎ ስለአመንአቸው እና ትንሽ በመዘናጋቱም የተነሳ፤ እነእርሱ በ አዘገጃጀት ብዙ ቀድመውን አሉ። በ የተደራጀ ኃይል አሰላለፍ፤ ሕዝብ የበላይዕነቱን እስከእሚይዝ ድረስ – ጥፋት ማድረስአቸውም አይቀሬ ነው። እናም፤ ተገቢውን ጥንቃቄም ዝግጅትም – ምኪታም ፍልሚያም ማድረግ የግድ ነው።

ሕዝብዓዊ ንቅናቄው ወፍ-ዘራሽ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል። ምንጊዜም ቢሆን ፍልሚያው እሚደረገው እዚያው ሃገርቤት መሬት ላይ መሆኑን መዘንጋት አይገባም። ይ-ህ ሕዝብዓዊ ንቅናቄ፤ ፍፁም ዲሲፕሊንድ የሆነ ድርጅትዓዊ መሠረት ሊኖረው የግድ ነው።

በ ሶሻል-ሚድያ ሰልፍ-አፖይንትድ ስምሪት ሰጪዎች ሊኖሩ ይገባል እሚል ዕምነት የለንም። እንዲያውም፤ እጅጉን አደገኛ እና አጥፊ ሊሆን እንደ እሚችል በግልፅ ማስገንዘብ እንወድ አለን። ማይክራፎን ተከፍቶ፤ እንደዋዛ እማይወሩ ጉዳዮችን በዘፈቀደ መዘርገፋችን፤ ያስጠቃናል። ሙያ በልብ ነው ይላል ዕኮ የሃገራችን ሰው። ከ እዚህ የተሻለ መስራት ይጠበቅብን አለ። እርግጥ ነው – የ መከራችን መርዘም፤ የበደልአችን ዘግናኝዕነት፤ መረባረብን የተጠማን እንድእንሆን የአደረገን ቢሆንም፤ ልንጠቅማት እምንፈልጋትን ሃገር እና ልንጠቅመው እምንፈልገውን ሕዝብ ለአደጋ እንድአናጋልጥ፤ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ግና፤ እጅጉን – አዎ፤ እጅጉን ወሳኝ ነው።

*መንግሥት አልባዋ ኢትዮጵያ*

ኢትዮጵያ ዛሬ፤ [መንግሥት] አልባ ናት። የ ከፋው ነገር ግን፤ የ ሕዝብ ሥልጣን መተግበርያ የሆነውን መዋቅር በጉልበት የያዘው፤ የ አዴፓ-ኦነግ-ብልፅግና መንጋ – አሰልጥኖ በአሰማራው ወራሪ፤ ኢትዮጵያዊያንን እየጨፈጨፈ ኢትዮጵያንም እያስወረረ እየወረረ እና እያፈረሰ እያስፈረሰ የመሆኑ ሪያሊቲ ነው። ትክክል። በስልጣን ላይ የአለው ወራሪ መንጋ፡ ኢትዮጵያን እየመራ አይደለም። የ ሕዝብ ስልጣን ሃብት ንብረት መዋቅራትን ተቆጣጥሮ፤ የሰሞነኛውን ጎሣ በፖለቲካ በኢኮኖሚ በደህንነትም ሆነ በመከላከያ የበላይዕነቱን አስጨብጦ፤ የ ኦሮሙማ ቅዠቱን ዕውን ለማድረግ ወደፊት እየገሰገሰ ነው።

ሰሞነኛው ገዥው ቡድን፤ መስጊድ ወይም የሰሞነኛው ጎሣ ሰው ተጐዳ እሚል ነገር ሲሰማ፤ እንዴት እየተንደረደረ ስሜቱን እንደ እሚገልፅ፤ ሳታስተዉሉት የቀራችሁ አይመስለንም። ለምን አደረገ ማለትአችን አይደለም!

በተቃራኒው ግና፤ ዐማራ የአለዕዳው ሲፈናቀል፣ ሲጨፈጨፍ – የ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባቶች ስለ ቤተክርስቲያናት መቃጠል እና ስለ ካህንዐት እና ምዕመናን መጨፍጨፍ፣ ስለ የ ኢትዮጵያ ቅርሶች መውደም ሲነግሩት የመለሰላቸውን መልስ ሰምተናል — አንረሳውም! ዐማራ ላይም ሆነ በ ተዋህዶ አማንያን ላይ እየደረሰ የአለውን [እያደረሰ የአለዉን ማለቱ ትክክል ሳይሆን አይቀርም] ሰቆቃ እና ዕልቂት አንድም ቀን፤ እንደ "መሪ"ዕነት ይቅር – እንደ [ሰው] ስሜቱን ሲገልፅ ታይቶ ተሰምቶ አይታቀቅም። ሰሞኑን በ አጣዬ እና አካባቢዎቿ ስለ ተጨፈጨፉት ሰዎች ስለ ወደሙት ከተማዎች ስለተሰደዱት ዜጎች አንዲትም ቃል ሳይተነፍስ፤ የሆነ ግንብ ምረቃ ላይ ነጭ ልብስ ለብሶ ታይቷል። አዎ፤ ሃዘናችን ላይ አልደረሰም – እኛም ሃዘኑ ላይ አንደርስም!

አልፎ ተርፎም፤ በ ሱዳን ስንወረር – ሰሞነኛው ገዥው ቡድን፡ ጀሮ ዳባ ልበስ ብሎ እየአለፈው እንደሆነ ታሪክ እየመዘገበው ነው። አዎ፤ በ ገዥው ቡድን ፈቃድ ኢትዮጵያን በጎረቤት ሃገር አስወርሮአት አለ።

ይ-ህ ሁሉ ሜይሃም እና ዲስቶፒያ፤ ለ ሰሞነኛው ገዥው ቡድን ጉዳዩም አይደል። እርሱ፤ የአሰበው ሁሉ እንደተሳካለት እየቆጠረው የአለ ይመስላል። ስፕሪንክለር ሲስተም መዘርጋት፣ ፓርክ ምናምን መስራት፣ መንገድ መጥረግ፣ ዛፍ መትከል – እየተጨፈጨፈ ለ አለ ሕዝብ እና ልትፈራርስ እየአጣጣረች ለአለች ሃገር ትልቅ ፕራዮሪቲ አድርጎ ሊቆጥረው እንደ እሚችል መገመት ቀላል አይደለም። የ ክላውድ-ሲድኢንግ እና የ ሳይበር-ሴኪዩሪቲ ቴክኖሎጂን ወደሃገር ማስገባት፤ ትራይ-ሳይክል እንደተገዛለት ቶድለር ሲያስፈነድቀው ማየት ሆኗል የ እኛ እጣ። ቴክኖሎጂውን ዲስከቨር አድርጎት ቢሆን ኖሮ እንኳን፤ አንድ ነገር ነበር እኮ – ጉበዝ!

ልብ እንበል፤ ይህ ሁሉ እንዲሆን የፈቀድነው እራስአችን ነን። ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን ለመታደግ እሚያስችል ዝግጅት እና ቁመና የአለው ተገዳዳሪ ኃይል ፈጥረን ወራሪውን የ ኦሮሙማ ኃይል እንደ አመጣጡ መመለስ ሲገባን፤ ዝም ብለን እየተመለከትን ነው። ዕንቁ ሃገርአችን እና ዕንቁ ሕዝብአችን፤ ልንአፍሰው በ እማንችልበት ደረጃ ከመበተንአቸው በፊት፤ የ አቆማዳችንን አንገት በመዳፍአችን አጥብቀን መያዙን — በፍጥነት ልንአውቅበት ይገባን አለ።

*የደም ገፀ-በረከት*

ዛሬ በመንግሥትዕነት ቦታው ላይ የተቀመጠው፤ የ አዴፓ-ኦነግ መራሹ ብልፅግና ፓርቲ፤ የስልጣን ጥማቱን ለማርካት – ብሎም፤ በዙሪያው የአሉትን በተልዕኮ አንድ ዓይነት፤ በስልጣን በርጩማ እሚቀናቀኑትን ፍጡራን ለማስታገስ እሚያስችለውን አመኔታ ለመግዛት ይቻለው ዘንድ፤ የጋራ ጠላትአቸው እንደሆኑ እሚስማሙባቸውን፤ ኢትዮጵያን እንደ ሃገር፣ ዐማራን እና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያንን እንደ ሕዝብ — [ጭዳ] በማድረግ እድሜውን እያራዘመ ነው።

ሰሞነኛው ገዥው ቡድን፤ በ እየ ዕለቱ ስለ እሚከሰተው የ ሕዝብ ሰቆቃ እና ዕልቂት፣ የድንበር ደፈራ እና የኑሮ ዉድዕነት በፍፁም ደንታ የለውም። ምን ታመጣላችሁ እየአለን ነው። ለስልጣኑ አስጊ የመሰለውን ሁሉ፤ ወይ እርስ በእርስ አጣልቶ እያጋደለ እራሱን ያመቻቻል፣ አልያም ጠንከር የአለበትን – መከላከያ እሚለውን አነጋይዝድ የጦር ኃይል በማሰማራትም ሆነ እግረኛ እና የ አየር ኃይሉን ጭምር በመጠቀም ኢትዮጵያዊያንን ከ ምድርም ከ ሰማይም እየጨፈጨፈ የደም ጥማቱን በማርካት ላይ ይገኛል።

*በደለኞችአችን*

ከእዚህ በፊትም ተናግረን አለን። የገዥው ቡድን መንጋ እና ደናቁርት አሽቃባጮችአቸው የ ኢትዮጵያ ቀንደኛ በደለኞችዋ ናቸው። አላባራ ለአለው ጄኖሳይድ፣ የሃገር ምዝበራ እና ፍርሰት ቀዳሚ ተጠያቂዎች!

በእዚህ በአለፈው ሦስት-ዓመታ፤ ለ የገዥው-ቡድን ሽፋን ሰጪ በመሆን በማገልገላቸው፤ ሕዝብዓዊ ትግሉ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንደቸለሱበት እና እየተቀጣጠለ ለአለው ጄኖሳይድ ብሎም

አይቀሬ እየሆነ ለመጣው የ ሃገር መፍረስ አደጋ ከ አምባገነኑ የ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ብልፅግና ፓርቲ የአልአነሰ ተጠያቂ ለመሆን – ወደው ፈቅደው ተቃቅፈው ተሰልፈው የ እሚገኙትን አንድ-ሁለት የ ዜጋዕነት ፖለቲካ አራማጅ ነን ባይ ፍጡራንን ሁሉ ያካትት አለ።

አዎ፤ በ የአለፉት ሦስት-ዓመታት የደረሰው እና እየደረሰ የ አለው ጀኖሳይድ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ እና ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ ብሎም አይቀሬ እየሆነ የመጣው የ ሃገር መፍረስ አደጋ፤ በ ህወሓት ዘመን ከነበረው እጅጉን የባሰ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ እየ አለ፤ የ ያ-ኔ የ ህወሓት መሪሹን ኢህአዴግ ተቃዋሚ ተፋላሚ ነበርን ባይ'ዎች፤ ዛሬ ከ አምባገነኑ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ብልፅግና ጋር አንሶላ እየተጋፈፉ መሆናቸው፤ በጣም አሳፋሪ ድርጊት ነው።

አንዲት ቀን – ሰቆቃ ውስጥ የአለውን እና በ ዕልቂት እየተናጠ የአለውን የ ኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይም – ዐማራውን እና ተዋህዶ አማኒያንን ለቅሶ ያልደረሱ የ ገዥው ቡድን ፍጡራን እና ሌሎች ፖለቲከኛ ነን ባዮች ሁሉ፤ አሁን ምርጫ ሲደርስ ምረጠን ሊሉ ደጁን መርገጥ ማሰብአቸው፤ ለ ሕዝብ የ አላቸውን ከፍተኛ ንቀት እና የ እራስአቸውንም ኅሊናቢስዕነት መገለጫ ነው እና፤ ጀግናው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ — አደራ፤ እንድአመጣጣቸው አስተናግዳቸው!

እንደ ማጠቃለያ

ኅበዝ፤ የተደቀነብን ፈተና ግዙፍ ቢሆንም፤ ከ እይታችን ውጪ እንዲሆን ግና ልንፈቅድዕለት አይገባም። አይቀሬው ሕዝብዓዊ ንቅናቄ፤ ዘግይቶ መጀመሩም አይገድኧንም — ጭራሽዕኑ በ አለመቅረቱ እጅጉን ደስተኞች ነን እንጂ። ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ጅማሮው አኩሪ ነው። የ ጊዜ ጉዳይ ከአልሆነ በስተቀር፤ ይ-ህ ቀን እንደ እሚመጣም ምንም ጥርጥር አልነበረንም። ከ አገርቤት ውጪ የተጀመሩትም ሆነ አገርቤት ውስጥ እየተደረጉ የአሉት ሁሉ፤ ፈርጠም የአለ ድርጅትዓዊ ቁመና እንዲይዙ እና ቀጣይዕነት ይኖርአቸው ዘንድ ግና ደጋግመን ማስገንዘብ እንወድ አለን።

ያ-ዉ የ እራስአችን ጉዳይ ቢሆንም፤ ሃገርቤትም ሆነ በ ዉጪ ሃገር፤ በማስተባበርም ሆነ በተለያዩ መንገዶች ተሳታፊ ለሆናችሁ ሁሉ — [ኩዶስ] ማለት አግባብ ነው ብለን ዕንወምን አለን። በ እዚህ ወር ሊሰሩ የተቻሉት ሁሉ፤ የአንድ ሰሞን ጉዳዮች ሳይሆኑ፤ ችግሮችአችን ሙሉ በሙሉ እስኪቀረፉ ድረስ፤ የበለጠ ተጠናክረው በቀጣይዕነት ተግባራዊ ሊደረጉ እንደእሚገባቸው፤ ልንዘነጋ አይገባም — ተገዳዳሪ አሸናፊ ቁመና ይኖረን ዘንድ!

እጅጉን ወሳኝ ስለሆነ፤ አንዴ እንድንደግመው ፈቃዳችሁ ይሁን። ዛሬም ቢሆን፤ መሠረትዓዊ ችግሮችአችን — የጎሣ ፖለቲካ፣ የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች፤ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ– ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌደራሊዝም፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግስት የ አለመኖር፣ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋምአት የ አለመኖራቸው እና እነእኛን ሁሉ ተከትሎ፤ ለ 30-ዓመታት ያህል በተደጋጋሚ እየተከሰተ የ አለው፤ በተለይ በ ዐማራ እና በ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኒያን ላይ እየደረደ የአለው መንግስትዓዊ – ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና ጀኖሳይድ፣ ብሎም ኢትዮጵያን የ ማሰቃየት የማፍረስ እና አሮሙማን የማንሰራፋት ዘመቻ ናቸው። እናም፤ ዓይንአችንን ከ እነእርሱ እና ከ እነእርሱ ላይ መንቀል አይኖርብንም።

ምርጫው፤ ሃገርዓዊ ፍትህዓዊ እና ነፃ ሊሆን አይችልም። የኢትዮጵያዊያንን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት ያራዝማል። አንድአችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ ሊኖረውም አይጠበቅም። መሠረትዓዊ ችግሮቻችአችንን ማባባስ ከአልሆነ በስተቀር — መፍትሄ ይሆናል ተብሎም አይታሰብም። ትክክል።ምርጫው፤ ገና ከሂደቱ ከሽፏል። መራጩ ዜጋ፤ እሚፈልገውን አቋም ቢይዝ፤ ከጎኑ እንቆማለን። ምርጫው ተደረገም አልተደረገም፤ እሚያመጣው አንዳችም ኢትዮጵያዊ ፋይዳ አይኖርም። መሠረትዓዊ ችግሮችአችን እንዳሉ [ምን አልባትም ተባብሰው] መቀጠልአቸው አይቀሬ ነው።

አዎ፤ "ህይወት" መቀጠሉ ስለእማይቀር – በምርጫው መሳተፍ ግድ ከሆነ፤ የብልፅግና እና የባለሚሎቻቸውን ዕጩዎች፣ የኢትዮጵያዊዕነት ጠላቶችን፣ አስመሳይ የዜጋ ፖለቲከኞችን ሁሉ ጠንቅቆ በመለየት ሸራፊ የአመኔታ የድምፅ ካርዱን እንድአይሰጣቸው፤ ሕዝብ በእሚገባ ይምከር ይዘጋጅ። ኢትዮጵያ ድንበርዋን፣ ኢትዮጵያዊያን [ሰውዓዊ] መብታችንን ህብርዕነትአችንን አንድዕነትአችንን እስከእምናስከብር እና [የ ኢትዮጵያ ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ እስኪያደርግ ድረስ፤ ሕዝብዓዊ ንቅናቄው ተጠናክሮ ይቀጥል።

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንገናኝ –

# የ ናርሲሲዝም ዩኒቨርስ

የግለሰብ እና የቡድን ዐዕምሮ መታወክ

ትናንትን በቀናዕነት ለመዘከር – ዛሬን በዕውነትኛዕነት ለመታደግ – የተሻለ ነገን ለመገንባት

ከ ሰኔ ፲፱ሺ፻፶፱ ዓ.ም ጀምሮ – እንደ ኢትዮጵያዊያን የ ዘመን አቆጣጠር

የ አዳራሽ ጦማር ‖ ሰኔ ፲፱ሺ፻፲፫ ዓ.ም

<u>ልዩ ዕትም</u>

አዳራሽ – <u>እንደ መንደርደሪያ</u> – በይነመረብ ላይ አሻራችንን ለማንበር በእሚል አዳራሽ'ን ከቀለስን፡ ይኼው እና በዛሬዋ ሰኔ፤ አስራ-አንድ ዓመት ሞላን። ሰኔ በመጣ ቁጥር፡ ወርሃዊ ጦማርአችንን "ልዩ ዕትም" እሚል ነገር-ማሳመሪያ ቢጤ ሃረግ በመዶል፡ ቀልብአችሁን ለመሳብ እየሞከርን የአለነው፡ የ አዳራሽ ዓመትዓዊ በዐልን እንደ-ማሰብ እየቃጣን እንደሆነ፡ ፍንጭ ለመስጠት ያህል ብቻ ነው – ለ'ጤናችን! ኀበዝ፤ የወርዐት መጀመሪያ ሲቃረብ፡ ርዕስ መርጠን እና ዕምንዕለውን ብለን ስንአበቃ፡ ጊዜአችሁን ታካፍሉንአላችሁ ብለን በማመን፡ ስንአጋራችሁ – ሁልጊዜም በታላቅ አክብሮት ነው። ለዛሬም እንግዲህ፤ በዋናዕነት [የ ናርሲሲዝም ዩኒቨርስ] በእሚል ርዕስ ዙሪያ የጫጫርነውን ይዘን ቀርበናል። በ የአለፉት 30-ዓመትዐት፤ በተለይ በ የቅርብዖቹ 3-ዓመትዐት፡ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቡድን፡ ናርሲሲስት ሊያሰኛቸው እሚበቁ ገላጭ ባህሪይዐትን የተላበሱ እና ዕማኘ ተግባራትን እየፈፀሙ የአሉ፤ ፖለቲካውን የማጨናነቅ አጋጣሚው የተፈጠረላቸው ፍጡራን፤ በተደጋጋሚ ትኩረትአችንን ሲስቡ ተገንዝበናል። እናም፤ የይድረስ የይድረስ በመሆኑ ሁሉንም ጉዳይ ማካተት ባይቻልም፤ ይለይለት ብለን – የ'ናርሲሲዝም ዩኒቨርስ በግለሰብ እና በቡድን እሚገለፅባቸው የተወሰኑ ባህሪይዐትን ልንአጋራችሁ ፈቀደን። የ እናንተ ድርሻ፤ ማንበብ እና ኢትዮጵያዊ ገጠመኞችን እየአካተታችሁ መወያት ይሆናል ማለት ነው። <u>እንደ ፕሬሚስ</u> – የመረረ ውሸታምዕነት፣ የግል የሆነ የተዛባ ሪያልቲ'ን መፍጠር እና ለ'እሚፈበረከው የግል የተዛባ "ዕውነታ" ተገዢ መሆን፣ የተጋነነ መደነቅን ትኩረትን የመሻት ጥማት፣ ለሌሎች ደንታ አለመኖር፣ ዕርማትን ግሰፃን በቀላሉ አለመቀበል፣ ጥፋትን ማጣጣል፣ የ ሁሉ ነገር ባለቤቱ እኔ ነኝ ማለት፣ ዕብሪተኛ እራስ ወዳድ እና አልጠግብ ባይ መሆን፣ አድሎአዊዕነት፣ ጥፋትን በሌሎች ላይ ማመሃኘት፣ ከሁሉ በላይ ነኝ ብሎ ማሰብ፣ የሌሎችን አቅም እና ስኬት የማጣጣል አባዜ፣ መፀፀትም ሆነ ተጠያቂ መሆንን እርም አድርጐ መውሰድ፣ ከፉኛ የስልጣን ጥማት፣ እራስን አገዝፎ የተለየ እና ወደር-የለሽ አድርጐ መገመት፣ አስመሳይዕነት፣ ይገባኛ አለ ብሎ እሚያምነውን ንዋይ-ንብረት-ስልጣን-ከበሬታ-ተቀባይዕነት-ትኩረት በአለማግኘት ሳቢያ እሚከሰት ብስጩዕነት እና በቀለኛዕነት። <u>እንደ ዉሳኔ</u> – ተላይ የተዘረዘሩት አትሪቢዩትስ በተደጋጋሚ እሚጠቀሱ — የ'ናርሲሲዝም ገላጭ ባህሪይዐት ናቸው። የ ናርሲሲዝም መገለጫ ባህሪይዐት በአመዛኙ በግለሰብ ላይ እሚንፀባረቁ ሆነው ሳለ፤ ስለ ናርሲሲዝም የአለው ዕዉቀት እየሰፋ እና ጥልቅ እየሆነ ሲሄድ፤ በቡድን ደረጃ እንደሚንፀባረቁም ግልፅ ሆኗል። የግለሰብ ናርሲሲዝም፤ የእኔ ወደ እሚለው ማህበረሰብዓዊ ህይወት ሲዛመት፤ የቡድን ናርሲሲዝም በመሆን ይከሰታል። በ ፍልስፍና፤ ፕሬሚስ'ን የመፍጠር የማዛመድ ሂደት እና ዉሳኔን ድምዳሜን ማሳመኛ ማረጋገጫ እድርጐ የመጠቀም ችሎታ፤ ሎጂክ እና ዲዳክቲቭ ሪዝኒንግ እሚጠይቅ የአዋቂ ሰዉ ስራ እንደሆነ ነው እሚቆጠረው። አመክንዮን እና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ተመርኩዞ፡ ዕውነታን ማረጋገጥን እሚጠይቅ – ብልህዕነት። ተላይ የአቀረብነው [ፕሬሚስ – ዉሳኔ] ስነተግባር በአመዛኙ ዕንከን አይወጣለትም ባይዖች ነን። ኀበዝ፤ ይህ – ግለሰብን ወይም ቡድንን የመፈረጅ ጉዳይ አይደለም። ይልቁን እስ፤ በማህበረሰብዓዊ ህይወት ዉስጥ እሚፈጠርን የሃሣብ መፍለቅለቅ ለማብረድ በእሚል – ዕውነትኛዕነትን እና ትክክልኛዕነትን የመፈለግ እና የማናበብ ሂደት እንጂ! አዎን፤ የቀረበው ፕሬሚስ፤ ዕውነትኛዕነትን ትክክልኛዕነትን ለማረጋገጥ ሲባል የቀረበ የሃሳብ ክምችት ነው። ፕሬሚስ – የዉሳኔን የድምዳሜን የአቋዋምን ትክክልኛነት ለመደገፍ ለማረጋገጥ እሚቀርብ ዕምቅ ሃሳብ ነው። ፕሬሚስ'ኡን የፈጠረው የሃሳብ ክምችት፤ ዕውነት ትክክል ከሆነ፡ ውሳኔውም ድምዳሜውም – ዕውነትም፣ ትክክልም ነው ማለት ነው። የ'ፕሬሚስ ረቂቅዕነትም – አንባቢ ፕሬሚስ'ኡ ዕውነት ትክክል መሆኑን ዐምኖ መቀበሉ ላይ ነው። አንባቢ ፕሬሚስ'ኡን ዐመነ ማለት፤ ዉሳኔውን ድምዳሜውን አቋዋሙን ተቀበለ ማለት ነው። ያ-ም ትልቅ ስኬት ነው። <u>እንደ ሰሞነኛ ጉዳዮች</u> – ምርጫው ፍትህዓዊም ነፃም ህግዓዊም አይደለም። ዲሚክረሲንም ሊያዋልድ አይችልም። መላው የኢትዮጵያ ግዛቶች በሰላም እና መረጋጋት እጦት እየተናጡ ናቸው። <u>እንደ ማጠቃለያ</u> – ልብአችንን ከፍተን ከተመለከትን፤ የ ኢትዮጵያ ነገር ከድጥኡ ወደ ማጥኡ መዘፈቁን፣ ምርጫው – ምርጫ ቢስ መሆኑን፣ ሰላም እና መረጋጋት ሊሰፍን አለመቻሉን፣ የኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አለመደረጉን ሁሉ እንገነዘባለን። ምርጫው እንዲሰረዝ፣ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ እንዲጠራ፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም፣ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት እንዲቀረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት እንዲመሠረት ከአልተደረገም – ነገ የከፋ ችግር ላይ እንደእምንወድቅ ምንም ጥርጥር የለውም። እናም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአግባቡ ነቅቶ ተደራጅቶ እና ተዘጋጅቶ መጠበቅ የግድ ይለው አለ። የተጀመረውን ሕዝብዓዊ ንቅናቄ አጠናክሮ መቀጠልንም — እንዲሁ!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – ለመሆኑ እንዴት ናችሁ?!

ዛሬ፤ ተላይ የአቀረብነው [ፕሬሚስ – ዉሳኔ] ስነተግባር ላይ ተመርኩዘን፡ ሊካሄድ ስለ የታሰበው ምርጫ፣ ወቅታዊ ዕውነታዎች እና እንደ ማጠቃለያም ዕምንእለው ይኖረናል። በቅድሚያ ግና በ የግለሰብ እና በ የቡድን ናርሲሲዝም ዙሪያ በማውጠንጠን ላይላዩንም ቢሆን የተወሰኑ ሃሳብዖችን እንአጋራችኋለን።

እናም፡ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

በ'[የ ናርሲሲዝም ዩኒቨርስ] ዙሪያ የእምናጋራችሁ ሃሳብዖች፤ ሌሎች መፃህፍትን ጨምሮ፤ በዋናዕነት የ Agnieszka Golec de Zavala እና Dorotty Lantos ምርምርዖችን ተጠቅመን የ አቀናበርንአቸው ናቸው። የአንባቢዎችአችን ድርሻ እሚሆነው፤ ማንበብ እና የሆነ ሰዉ በመፈለግ [እንደ ግለሰብ] – እርሱ

እሚከተለውን አይዲዮሎጂ እና በዙሪያው የአሉትን ዲሳይፕል'ስ ደሞ [እንደ ቡድን] በመውሰድ፤ መወያየት ነው።

ለማንእኛውም፤

የ'ናርሲሲዝም ስርወ-ቃል፡ የ'ግሪክ አፈ-ታሪክ ላይ የተመሠረተ፤ የአፈ-ታሪኩ ገፀ-ባህሪይም [ናርኪሶስ] እሚባል ዕብሪተኛ ጐረምሳ እንደነበር እና እርሱም – ከ ወቅትዐት አንድ ፀደይ፤ ከ የእራሱ ቁንጅና ጋር በፍቅር ተሸንፎ ስሜቱ በመጎዳቱ ህይወቱ ከአለፈ በኋላ – [ናርሲሰስ] ተብሎ ወደ እሚጠራ አበባ እንደተቀየረ ይተርካል። ቃሉ ከ'ዳክትሪን፣ ከ'ቲየሪ፣ እና ከክስተት አኳያ ጠቀሜታ ላይ ሲውልም፤ ናርሲሲዝም ናርሲሲስቲክ እና  ናርሲሲስት የ እሚሉትን ስያሜዎች ይዞ እንአገኝ አለን።

ናርሲሲዝም፤ በ ጤና ሳይንስ፡ [ናርሲሲስቲክ ፐርሰናልቲ ዲስኦርደር] በእሚል ስያሜ ተመዝግቦ እሚገኝ፤ ክሊኒካል ኢቫልዌሽን እሚጠይቅ እና ሳይኮቴራፒ'ን እሚሻ የ ዐዕምሮ መታወክ ነው። ናርሲሲዝም፤ የተዛባ የገነነ ተክለ-ስብዕና በመላበስ፣ በ የመደነቅ እና በ የትኩረት ጥማት፣ ለሌሎች ሰዎች ስሜት ግድየለሽዕነት፣ በዕብሪት እና በ የግል-ጥቅምን የማሳደድ አባዜ፣ በአጓጉል ምኞት ሱስ በመጠመድ እና እንደ እየ አግባበ-ነገሩ ሌላ ሰዉን ወይም ሌላ ቡድንን [አብዩዝ] በማድረግ አባዜ፤ ይገለፃል።

*<u>ተጨማሪ የ'ናርሲሲስዝም ገላጭ ባህሪይዐት</u> – የመረረ ውሸታምዕነት፣ የግል የሆነ የተዛባ ሪያልቲ'ን መፍጠር እና ለእሚፈበርከው የግል የተዛባ "ዕውነታ" ተገዢ መሆን፣ የተጋነነ መደነቅን ትኩረትን የመሻት ጥማት፣ ለሌሎች ደንታ የአለመኖር፣ ዕርማትን ግሰፃን በቀላሉ አለመቀበል፣ ጥፋትን ማጣጣል፣ የ ሁሉ ነገር ባለቤቱ እኔ ነኝ ማለት፣ ዕብሪተኛ እራስ ወዳድ እና አልጠግብ ባይ መሆን፣ አድልኦዓዊዕነት፣ጥፋትን በሌሎች ላይ ማመሃኘት፣ ከሁሉ በላይ ነኝ ብሎ ማሰብ፣ የሌሎችን አቅም እና ስኬት የማጣጣል አባዜ፣ መፀፀትም ሆነ ተጠያቂ መሆንን እርም አድርጎ መውሰድ፣ ከፋኛ የ ስልጣን ጥማት፣ እራስን አገዝፎ የተለየ እና ወደር-የለሽ አድርጎ መገመት፣ አስመሳይዕነት፣ ይገባኛ አለ ብሎ  እሚያምነውን  ንዋይ-ንብረት-ስልጣን-ከበሬታ-ተቀባይዕነት-ትኩረት በአለማግኘት ሳቢያ እሚከሰት ብስጩዕነት እና በቀለኛዕነት ወዘተ ወዘተርፈ።*

የተዘረዘሩት የ'ናርሲሲዝም ባህሪይዐት፣ ከ ጥንትዓዊው ጥንት ጀምሮ፤ በግለሰብ ላይ እሚንፀባረቁ አትሪቢዩትስ መሆንአቸው የበለጠ ትኩርት የሳበ ቢሆንም ቅሉ – ዕድሜ እና ጤና ለ የስነ-ልቦና ተመራማሪዎች፤ ከ አንድ ምዕተ-ዓመት ወዲህ፤ ስለ ናርሲሲዝም የአለው ዕዉቀት እየሰፋ እና ጥልቅ እየሆነ፤ የ'ናርሲሲዝም ባህሪይዐት በቡድን ደረጃ እንደእሚንፀባረቁም ግልፅ ሆኖ አለ።

*የ ግለሰብ ናርሲሲዝም፤ ወደ የእኔ እሚለው ማህበረሰብዓዊ ህይወት ሲዛመት – የቡድን ናርሲሲዝም በመሆን ይከሰታል። ማለትም፤ ናርሲሲስቲክ ቡድን እንደ ናርሲሲስት ኤንትቲ ፈንክሽን ያደርጋል፤ ማለት ነው። "ቡድን" ሲባል'ም እንግዲህ – እንደ የአንድ ሃገር ሕዝብ፤ እንደ አንድ ጎሣ አባልዐት፣ እንደ የአንድ ሃይማኖት ተከታይዖች፣ እንደ የአንድ አይዲዮሎጂ ተከታይዖች፣ እንደ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባልዐት፣ እንደ የአንድ የ'ስፖርት ቡድን ደጋፊዎች እና የመሳሰሉትን ማለት ነው።*

የግለሰብ እና የቡድን ነገር ሲነሳ – መቼም ቢሆን፤ ስለ [ስም] ስለ ስያሜ መነሳቱ አይቀሬ ነው።

አንድ ግለሰብ በባህልዓዊ ወይም በህግዓዊ ስርዐት፡ በወጣለት ስም ይጠራል። ጠዋት ስሜ "ጄ"፤ ከሰዐት ደሞ "ኤ" ነው ማለት አይችልም። አንድ-አንዴ በስም ሞክሼዕነት ተጠያቂ እምይሆንበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። አንተ አለመሆንህን ታረጋግጥ እና እራስህን ነፃ ታወጣለህ እንጂ፤ ለምን ተጠየቅሁ በ እሚል አካኪ-ዘራፍ ማለት አይአዋጣም። የቡድን ስምም እንዲሁ!

አንድ ቡድን፤ መጠሪያ ስሜ "ይህ-ኤ" ነው ብሎ መጠሪያው ከአደረገ – የእሚጠራበት የቡድንኡ ስም "ይህ-ኤ" ነው እሚሆነው። የቡድን መጠሪያ ስም አሻሚ የሆነ ትርጉም ሲኖረው እና በአጋጣሚ ሌላ ቡድን ተጠቅሞበት ሲገኝ – በህግ-ፊት ቀርቦ ሪዞልቭ የማድረጉ ሃላፊዕነት፤ የ "ይህ-ኤ" ባለቤትኡ ዕኔ-ነኝ ባይ አካል ብቻ ነው። በአንድ ስም በእሚጠራ ቡድን በእሚቀነቀን አይዲዮሎጂም ሆነ በተግባር እሚፈፀሙ ተግባርዐት ዙሪያ ቅዋሜ እሚአስነሱ ገጠመኞች ሲፈጠሩ፤ [ያ] የቡድን ስም እየተጠቀሰ ቢሞገት ቢብጠለጠል ቢገሰፅ ቢረገም፤ ማንም የመከልከል መብት የለውም። የ እኔም መጠሪያ ስም ስለሆነ፤ የቡድን ስሜ እየተጠቀሰ እማልፈልገው ነገር ከተባለ፤ እኔን እንዳላችሁኝ ነው እምቆጥሮው በእሚል ማላዘን – ነዉር ነው።

ናርሲሲዝም – በ ግለሰብ ደረጃ ሲንፀባረቅ

ትክክል። ናርሲሲዝም የ ዐዕምሮ መታወክ ነው – የጤና አይደለም። ስለ ናርሲሲዝም መንስኤ ዛሬ የአለው ዕዉቀት፤ በተፈጥሮ [ኔቸር] እና በተሞክሮ [ነርቸር] ጥምረት ሊከሰት እንደእሚችል ነው እሚነግረን። የመጀመሪያው፤ ከወላጅዖች በዝርያ [ዲኤንኤ] – ሁለተኛው፤ ከአስተዳደግ [የበዛ መቀማጠል፣ በ አጓጉል ተስፋ መሞላት እና የመሳሰሉትን አካትቶ] በእሚዋሃዱ አጓጉል ባህሪይዐት ሊጐለብት እንደ እሚችል።

የ አንድ ናርሲሲስት ዩኒቨርስ ነፍስ እሚዘራው፡ ለ ግልኡ እሚፈጥረው <u>የተዛባ ሪያልቲ'ን</u> እና እሚፈበርከውን የግልኡን የተዛባ ዕውነታን መተንፈስ የጀመረበት ቅፅበት ላይ ነው። ተ-ያ በኋላ ማቆሚያ የለውም። እንድገመው። ለ አንድ ናርሲሲስት – ["ዕውነት"] ሁልጊዜም፤ እራሱ የ አዛነፈው እራሱ የአደፈረሰዉ የግልኡ "ሪያልቲ" ብቻ ነው።

ሳይኪያትሪስትዖች፤ የከፋ <u>የዕዉቀት ግድፈት</u> እና <u>የገነነ ጭፍን-ግትርዕነት</u>፡ ሪያልቲ'ን ያዛባል ይላሉ። ይ-ህ ሪያልቲ'ን የማዛባት የማደፍረስ ዝንባሌ፤ በ ናርሲሲስቲክ ፐርሰናልቲ ዲስኦርደር የተጠቃ ሰዉ፤ ዓይነተኛ መገለጫ ነው። አንድ ናርሲሲስት፤ የአዛባውን ሪያልቲ በተጠቀመ ቁጥር፡ ስለ እራሱ የ አለዉን የተዛባ ምልከታ ያረካል።

ጥናቶች — የባሰበት አለአዋቂዕነትን፣ ሪያልቲ'ን የማዛባት ሪያልቲ'ን የማደፍረስ አባዜን እና የገነነ ጭፍን-ግትርዕነትን በመጠቀም፤ ዕኩይ ህይወት ከመምራት ይልቅ፤ የችግርዖችን ዕውነትኛ መንስኤ በቀናዕነት ለመገንዘብ ጥረት ማድረግ – የብልህዕነት የአስተዋይዕነት እና የአዋቂዕነት መገለጫ እንደሆነ ይጠቁሙ አለ።

*ዕውነት ነው። ማንአቸውም ሰዉ፡ ለ ሁነትዖች የተለየ ዕይታ ሊኖረው ይችላል። ["ያ"] ምንም ከፋት የለውም – በፍፁም! ከፍተኛ የእራስ-መተማመን መኖርም ችግር የለውም። እንዲያውም ጤናማ ከፍተኛ የእራስ-*

*መተማመንን የተጐናፀፉ ሰዎች፣ ብዙውን ጊዜ ቀና እና ትሁት ሰዎች ናቸው። በአንፃሩ ግና – ናርሲሲስቲክ የሆነ ግለሰብ [ፍራጃይል የሆነ – "ከፍተኛ" የእራስ-መተማመን] ነው ያለው። ይ-ህ እንን ስሜቱን ይ-ህ እንን ዕምነቱን እሚገልፀውም እሚተገብረውም፡ ፍፁም ንቀት እና ለሰዉ ስሜት ደንታ በሌለው፡ ጋጠ ወጥ በሆነ መልኩ ነው።*

እራስን በትክክል ማወቅ እና የእራስ ስህተትን ጥፋትን መፈተሽ እና ማረቅ እሚፈቅድ ሰዉ – ስለ እራሱ፤ የአልተዛባ እና ከ'ሪያልቲ የአልተዛነፈ ግንዛቤ እንዲኖረው ያግዘዋል። ስህተቱን ጥፋቱን በቅንዕነት እንዲያምን፣ ከልብ እንዲፀፀት እና ከስህተቱ ከጥፋቱ እንዲማር እንዲሻሻል እሚያስችለውን ተክለ-ስብዕና ይፈጥርለታል።

አልፎ አልፎ፤ በ ናርሲሲዝም ተጠቂ የሆነ ሰዉ፡ ዕውነትኛ ዕዉቀት በእጅት ስለ እሚያንሰዉ እና ስህተቱን ጥፋቱን በቀናዕነት መቀበል ሞቱ ስለሆነ፤ ምንአልባት፡ ሪያልቲ'ን ማዛባቱን ሪያልቲ'ን ማደፍረሱን ሊያውቀው እማይችልበት የራቀ ፖሲቢሊቲ ሊኖር ይችላል – በእሚል እሚሞግቱ አሉ። እናም፤ ምን እየሰራ እንዳለ እማያውቅ ከሆነ፤ እንዴት ለስህተቱ እና ለጥፋቱ ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል፤ እሚል ጥያቄንም ሲያቀርቡ ይደመጡ አሉ።

በሌላው ጎራ የአሉ የሙያው ሰዎች ደሞ፤ አ.....ይ! አወቀውም አላወቀው – ለስህተቱ ለጥፋቱ ተጠያቂ ከአልሆነ፤ ስህተቱን ጥፋቱን መካድ ይገፋበታል፣ አስከፊ ውሸቱን ይቀጥልበታል፣ ስህተቱንም ሆነ ጥፋቱን ወደ ሌሎች ማላከክም፣ ሌሎችን መወንጀሉንም አጠናክሮ እንዲቀጥልበት የልብ ልብ እንዲያገኝም ያስችለዋል – ዕውነታው፤ ቀንደኛ ወንጀለኛው እርሱ ናርሲሲስት'ኡ እራስኡ ሆኖ እየ አለ፤ በማለት ግብረመልስ ይሰጣሉ።

ዋናው ነገር፤ አንድ ናርሲሲስት፤ የእራሱን አላዋቂዕነት፣ ሪያልቲ'ን የማዛባት እና ሪያልቲ'ን የማደፍረስ አባዜውን ላያውቅ ይችል ይሆናል ቢባልም – ስለ ተግባሩ ግና በደንብ ያውቃል። ምን እየሰራ እንዳለም በእሚገባ ይገነዘባል። ችግርኡ፤ የአዛባቸው የአዛነፋቸው የአደፈረሳቸው ሪያልቲ'ዎች፤ ስሁት መሠሪ ጠባይኡን ["ትክክልኛ"] እንደሆነ አድርጐ ይቀበለው ዘንድ፡ ተክለ-ስብዕናውን እንደገና ፈጭተው አቡክተው ጠፍጥፈው ጋግረው ነፍስ ይዘሩበታል።

የባሰዉ ነገር ደሞ፤ ናርሲሲስት፡ የአለእኔ አዋቂ የለም ባይዕነት እና ሌሎችን አሳንሶ ማየት፤ ከ እዚያም በአሻገር፤ ሌሎችን የማስተማር የማሳወቅ የማሳመን ሃላፊዕነት እና ግዴታ እንደአለበት ጭምር ይሰማዋል። ብዙዉን ጊዜ ይ-ህ እንን ስሜትኡን ይ-ህ እንን ዕምነትኡን እሚገልፀውም እሚተገብረውም፡ ፍፁም ንቀት እና ለሰዉ ስሜት ደንታ በሌለው፡ ጋጠ ወጥ በሆነ መልኩ ነው።

ይህ ሁሉ ነው እንግዲህ፡ በ ናርሲሲዝም ተጠቂ ከሆነ ሰዉ ጋር እንደ [አደልት]፣ ፊደል እንደቆጠረ ሰዉ ተነጋግሮ አንድን ችግር ማቃለል በፍፁም አዳጋች እሚያደርገው። ናርሲሲስት የሆነ ሰዉ፤ ከ ሁሉ በላይ ነኝ ብሎ ስለእሚያምን – በ የ አዛነፈው በ የ አደፈረሰዉ ሪያልቲ "ዕውነትዕነት" በፅኑ ያምናል። እናም፤ ሌላ ጤናማ ሰዉ ዕውነትዐን ይዞ ሲቀርበው እና ሊያሳምነው ሲሞክር፤ ናርሲሲስት'ኡ በእርሱ ብሶ ያ-እንን ቀና ሰዉ እንደ ውሸታም በመቁጠር ማብጠልጠል እና መበቀል ይቀናው አለ።

የ'ናርሲሲስት ሌላእኛው ባህሪይ – አስመሳይዕነት ነው። ተጠያቂ ሆኖ መቅረብ እና በሃሣብ የመስማማት ፍላጐት የአለው መስሎ መቅረብ ለእርሱ ቀላል ነው። ዕውነታው እና እየአደረገ የአለው ግና፤ ማታለል መሸወድ ማምታታት አጉል-አራዳ ሆኖ መቅረብ ሆኖ እየ አለ። ሲያመቸው፤ እራሱ በድሎ እራሱ ተበዳይ ሆኖ ሊቀርብ ይከጅለዋል። የ አላመቸው ጊዜ ደሞ፤ በ ስህተቱ ወይም በጥፋቱ የአዘነ ወይም የተፀፀተ መስሎ ለመቅረብ ሲሞክር ይታያል።

የእዚህ ቲያትር፤ [አስመሳይዕነት] እንደሆነ እሚረጋገጠው፡ ናርሲሲስት'ኡ – ሳይውል ሳያድር፤ አሁን የተናገረውን፣ አሁን ቃል-የገባውን ከመቅፅበት በመለወጥ፤ ያደርግ የነበረውን ስሁት መሠሪ ስራዎች፤ ምን አልባትም አባባብሶ ሲደግምአቸው እና ሲቀጥልባቸው እጅ-ከፍንጅ ስለእሚያዝ ነው። በ ናርሲሲዝም ተጠቂ የሆነ ሰዉ፤ ከልብ ማዘን ከልብ መፀፀት ከልብ መታረም እና ከልብ መሻሻል እሚባል ነገር – አልተፈጠረበትም።

በ ናርሲሲዝም ተጠቂ የሆነ ሰዉ፡ ዕዉነትኛ ዕዉቀትን ሪያልቲ'ን እንዲያዛባ እሚያደርገውን፣ ጥፋቱን እንዳያምን እሚያደርገውን፤ የዕውነት የዕዉቀት ግድፈቱን እና ጭፍን-ግትርዕነቱን — እንዲገነዘብ እንዲያርም እንዲቀየር እና እንዲሻሻል፤ መመከር መገሠፅ መገደድ አለበት። ፈቃደኛ ከአልሆነ፣ እሚሠራቸው ስህተትዖች ጥፋትዖች ወንጀልዖች እምይአደርስአቸው ጉዳትዖች፤ ማቆምያ አይኖርአቸውም።

በ ናርሲሲዝም ተጠቂ የሆነ ሰዉ ሲያጋጥም፡ በዕልህ በንዴት ወይም በግልፍትኛዕነት መቅረብ አይጠቅምም። ናርሲሲስት ባህሪይዉን ጠባይዉን ድርጊትኡን ሁሉ ስለእሚያዉቅ እና በእዚያም የተነሳ፤ ከሰዎች በምላሹ ንዴትን ብስጭትን ስለእሚጠብቅ፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ፤ ነገርዖችን ሊያገንባችሁ ወይም ወደ እናንተው ሊያዞርባችሁ ይሞክራል። የተሻለው መንገድ፤ ዕውነትኛ መረጃን ሰንቆ፤ ፈርጠም ብሎ እና በግልፅ – ስሜትኡን በእማይጎዳ መልኩ መንገር ነው። ዕውነታው ምን እንደሆነ እንደእምታውቁ በግልፅ ልታሳዉቁት ይገባል። ዳግም እንዳይዋሽ፣ መሠሪ ስራውንም እንዲአቆም በግልፅ ሊነገረውም የግድ ነው። ዝም ብሎ መመልከት – ትልቅ ስህተት ነው! አዎን፤ ለ ናርሲሲስት ዕጅ መስጠት ያስፈልግም፤ በፍፁም! ከሆነ ከሆነ፡ ቶሎ የ ህክምና ዕርዳታ እንዲአገኝ ማድረግ ወይም ፀበል ማስረጨት። እማይሆን ከሆነም – እንዲህ ዓይነቱን ግንኙዕነት ማፍረስ፤ አለያም ከእንዲህ ዓይነት ግለሰብ፤ እራስን በ ትሪሊየን ማይል'ስ ማራቅ ተገቢ ነው።

ናርሲሲዝም – በ ቡድን ደረጃ ሲንፀባረቅ

የ ቡድን ናርሲሲዝም ከ 1920ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ እየጎለበተ የመጣ ፅንሰ-ሃሣብ ነው። ቀደም ብለን ጠቆም እንዳደረግነው፤ የ ግለሰብ ናርሲሲዝም፤ የ እኔ ወደ እሚለው ማህበረሰብዓዊ ህይወት ሲጋባ ሲተላለፍ ሲዛመት – የ ቡድን ናርሲሲዝም በመሆን ይከሰታል።

የ ቡድን ናርሲሲዝም፤ አንድ ሰዉ የ እራስኤ ለእሚለው ቡድን የገነነ ፍቅርን በመስጠት፤ የመረረ ውሸትን ሴራን እና ጥርጣሬን መሠረት በማድረግ፡ እንደ ጠላት በቆጠረው ሌላ ቡድን ላይ በእሚፈበርከው የተዛባ የደፈረሰ ሪያልቲ ላይ ተመርኩዞ፤ የበለጠ ተቀባይዕነት የበለጠ ድርሻ እንዲያገኝ እና ልዩ-ጥቅም ይሰጠው ዘንድ እሚያምን፤ ጥላቻን፣ ፀብ-አጫሪዕነትን እና ብቀላን እሚያቀነቅን እሚተገብር ስርዐት ነው። እራሱን ፍፁም "ወደር-የለሽ" እንደሆነ ይቆጥር እና፤ ["ያ"] ፍፁም ወደር-የሽዕነቱ በሌሎች ዘንድ የአልታወቀለት ወይም የእሚጠብቀውን ያህል ተቀባይዕነት የአላገኘለት እንደሆነ [አሰርት] የአደረገ የታወከ የ ቡድን ዕምነት ነው።

አዎን፤ የ ቡድን ናርሲሲዝም – ስለ የ እራስ ቡድን ወደር-የለሽዕነትን በማቀንቀን በ የእራስ ቡድን መተማመንን ከመፍጠር ከማጎልበት አልፎ ተርፎ፤ የ "ሌላ" በ እሚለው ቡድን ላይ ንቀትን ስጋትን ጥላቻን በማዳበር፤ በቀል-ተኮር ጥቃትን መቆስቆስ እና የሌላ ቡድን እሚለው ላይ መከራ፣ ስቃይ እንዲደርስበት መቀስቀስ፣ ጭራሽእኑ እንዲደመሰስ ማድረግንም ያቀነቅናል፤ በተግባርም ያሳያል።

ጎበዝ፤

ሰዎች "ሌሎች" ላይ ጥላቻን ሳያሳድሩ፤ ለእራስአቸው ቡድን የ ወደር-የለሽዕነት ዕምነቶችን ቢያጎለብቱ ምንም ክፋት የለውም። ያ-እንንም ማድረግ ይቻል አለ። ነገር-ግን፤ ስለ እራስ ቡድን ምንዕነት ወይም ማንዕነት የእሚሰጥ የገነነ ግምትን እና የእራስን ቡድን ከሌሎች የበለጠ የተሻለ እንደሆነ መቁጠርን — ሌሎች የእርሱን ቡድን "ወደር-የለሽዕነትን" ዐምነው እንዲቀበሉላቸው መጠበቅን፣ ማስገደድን፣ ብሎም የተለየ አድናቆትን ከመሻት እና ልዩ-ጥቅምን ከመጠበቅ ጋር ማዛነቅ ግና ለእየቅል ናቸው። ይህ-እኛው የቡድን ናርሲሲዝም መገለጫ ነው።

*አዎን፤ በአመዛኙ – ቡድን-ኤክስ ከ ቡድን-ዋይ ጋር እሚኖረው አላስፈላጊ ነገሮች ሁሉ እሚፈጠሩት፤ ቡድን-ኤክስ ጠንካራ በእራስ-ቡድን መተማመን ስላለው አይደለም። ይልቁን እስ፤ ከጠንካራ በእራስ-ቡድን መተማመን እና ከሌሎች የበለጠ የተሻለ ቡድን እንደሆነ ማመንን ተከትሎ፤ የተለየ አድናቆትን ተገዢዕነትን መሻት እና ልዩ-ጥቅም መጠየቅን ከማቀንቀን ጋር የተዛነቀ ዕምነት ሲኖር — እንዲሁም፤ ተጓዳኝ ጥላቻ ጠብ አጫሪዕነት እና ብቀላ የምላበት እርምጃዎችን መውሰድ ጋር የተጎዳኘ እንደሆነ ብቻ ነው፤ የቡድን ናርሲሲዝም መገለጫ እንደሆነ እሚቆጠረው።*

የ ቡድን ናርሲሲዝም፤ "ሌላ" በእሚለው ቡድን ላይ እሚፈጥረው ጤናማ የአልሆነ ግንኙነት ወይም የለየለት ጥላቻ፣ [ሌላ] በመሆናቸው ብቻ በ እሚፈበርክባቸው የተዛባ የደፈረሰ ሪያልቲ፣ የሌለ የመጠቃት የመበደል ስሜት እና እምአይጨበጥ ስጋት ላይ የተመሠረተ የቡድን ዐዕምሮ መታወክ ነው።

የ ናርሲሲስቲክ ቡድን ዳይናሚክስ፤ በተለይም በቡድኑ ዉስጥ የተከፋፈለ የስልጣን ስብጥር ፈተና ሲገጥመው እና አክራሪዎች ወይም ሕዝብኧኛ ፖለቲከኞች የልብ-ልብ ሲሰማቸው – በእራስ የቡድን-ጥቅም ላይ ተከሰተ እሚሉትን የትንኮሳ የስጋት ስሜትአቸውን ከማቅለል ከማርገብ ይልቅ፤ ማራገብን ማቀጣጠልን ይመርጣሉ። እነእርሱ ትንኮሳ ስጋት አድርገው ለእሚቆጠሩት ዉሃ-እምአይቋጥር ጉዳይ ሁሉ፤ አግባብ የለሽ የተራገበ የተጋነነ አፀፋ ምላሽ መስጠትንም ይመርጣሉ።

የቡድን ናርሲሲዝም ከብሔርዓዊ ስሜት ጋር ሲቆራኝ፤ ለሃገር የአለን ፔትሪየቲዝም ከፍ ያደርጋል። ምንአልባት ከውጪ ሃገርዐት ጋር ለእሚፈጠር ችግር ምክንያት ሊሆን ይችል እደሆነ ነው እንጂ፤ ከእዚያ አልፎ ተርፎ በእራስ ሃገር ዉስጥ ችግር ሲፈጥር ግና አይታይም። በአንፃርኡ፤ የቡድን ናርሲሲዝም ከጎሣ ከሃይማኖት ወይም ከሁለቱም ጋር የተቆራኘ ሆኖ ከተገኘ፤ አስከፊ ጉዳቶችን ያስከትላል። በሙያው የአሉ ሰዎች፤ ሂትለር'ን እና የ ናዚ'ን ቡድን/ፓርቲ እንደ ጥሩ ማሳያ ይጠቅሱ አለ።

ስለ አንድ የእራስ ለሆነ ጎሣ ወይም ሃይማኖት ጥሩ ነገር መመኘት እና ቀና ዕምነትን ማዳበር ክፋት እንደአለው ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ክፋት እሚኖረው – አንድ ጎሣ ወይም ሃይማኖት፤ "ወደር-የለሽ" እንደ ሆነ ማማን እና ያ-እንን ተጓዳኝ አድርጎ – የመረረ ውሸትን ሴራን እና ጥርጣሬን መሠረት በማድረግ፤ "ሌላ" ጎሣ ወይም ሌላ ሃይማኖት ላይ በእሚፈበረከው የተዛባ የደፈረሰ ሪያልቲ'ን ተመርኩዞ፤ ሌላኛው ጎሣ ወይም ሃይማኖት ጠላት እንደሆነ አድርጎ መቁጠር፣ ወደር-የለሽ እሚለውን የ'ናርሲሲስቲክ ቡድንን ስሁት ዕምነት በግድ ተቀባይዕነት እንዲያገኝ ለማድረግ መጣር — እንዲሁም፤ በማህበረሰብዓዊ ግንኙነቶች ዉስጥ የበለጠ ተቀባይዕነት የበለጠ ድርሻ እንዲያገኝ እና ልዩ-ጥቅም ሊሰጠው እንደ እሚገባ መነዝነዝ፤ የቡድን ናርሲሲዝም ዓይነተኛ መገለጫ ናቸው — ጥላቻን፣ ፀብ-አጫሪዕነትን ብቀላን ማቀነቅን መተግበርን እና ወደ የለየለት ዕብደት መቀየርን ጨምሮ!

ጎበዝ፤ በግለሰብም ሆነ በቡድን ናርሲሲዝም ዙሪያ የወጡ አርቲክል'ዖችን ብትአነቡ፤ በእጅግኡ ትገረማላችሁ። ጥናትዖቹ ኢትዮጵያን የተመለከቱ እንድአልሆኑ እየአወቃችሁ — በ እምታነቡቡት ጊዜ በዓይነ-ኅሊናችሁ እሚቀረፀው ትዕይንት ግና፤ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ዉስጥ እንደተደረጉ አድርጋችሁ እንደትቆጥሩአቸው ይቃጣችኋል።

የቡድን ናርሲሲዝም ብዙውን ጊዜ በ አክራሪዎች በ ፅንፈኞች እና በመሳሰሉት እሚዘወተሩ ሲሆን፤ ሕዝብኛ ፖለቲከኞች ፓርቲዎች እና የፖሊሲ ጥያቄዎች ከ እሚያገኙት የሕዝብ ድምፅ በስተጀርባም ስለ እማይጠፉ – የቡድን ናርሲሲዝም ምንዕነትን እና ማንዕነትን በ እሚገባ ማወቁ መገንዘቡ እጅጉን ጠቃሚ ነው።

*በአጭሩ – የ ቡድን ናርሲሲዝም፤ ለ የእራስ ቡድን እሚፈበረክ የገነነ ፍቅር እና "ሌላ" ለተባለ ቡድን የአለዕዳው እንዲሸከመው እሚገደድ የእምአያባራ ጥላቻ ማለት ነው።*

የ ምርምር ውጤትዖች እንደ እምይአያሳዩት፤ የ ቡድን ናርሲሲስቶች ጥማትአቸው ፍትህ ወይም ዕኩልዕነት ሳይሆን፤ ልዩ-ጥቅም ነው። እናም፤ የ ቡድን ናርሲሲዝም፤ ችግሬ ብሎ ለ እምይገምተው ጉዳይ፤ በ ሰላምዓዊ መንገድ መፍትሄ ለማግኘት ከመጣር ይልቅ – ጥላቻ ብቀላ ጠብ-አጫሪዕነት እና ጥቃት መሰንዘር ይቀናዋል። የ ቡድን ማንዕነትኡን እምይጋፋ እሚመስለው የአደጋ ስጋትን ሲያስብ – በቅፅበት ነው ጭራ እሚያበቅለው።

የቡድን ናርሲሲት'ዖች፤ በ ቡድንአቸው ላይ ከሌላ ወገን ጥቃት እንደሚሰነዘርባቸው የአላቸውን ስጋት ከፉኛ ማጋነን ያበዛሉ፤

ከሌሎች በተሠነዘረ ጥቃት እየተጐዳ የአለውም፤ የ እነ እርሱ ቡድን ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ቡድንአቸው መቼም ቢሆን እሚገባውን አግኝቶ እማያውቅ መሆኑን እና ለ እሚከሰቱ ችግርዖች ሁሉ ብቸኛው እና ተገቢው መውጫው መንገድ ጥላቻን ሃይልን እንደ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም እንደሆነ በመዉሰድ፤ ለትንሽ ለትልቁ ስጋት ሳያመነቱ ወደ የተጋነነ ጥላቻ እና በቀል ማምራት ምርጫቸው አድርገው ይወስዳሉ።

ሌላው.......፤ የቡድን ናርሲሲስቶች – ሴራ መፈልፈያ፣ ሴራ ማጉያ መሣሪያ ከቢሮአቸው አይጠፋም። እነእርሱ ላይ ስጋት እምያሳድር ነገር ጆሮአቸው ከደረሰ፤ ትክክል ነው አይደለም ብሎ ለማረጋገጥ ጊዜ መስጠት እሚባል ነገር አያዉቁም። ይህ በ ቋፍዕነትአቸውም፤ ከ ቡድንአቸው ውጪ እየመጣ ነው ብለው ለእሚገምቱት ስጋት ብቻ ሳይሆን፤ በዉስጥአቸው ሊከሰት ለእሚችል ማንአቸውም የአፈንጋጭዕነት ጭምጭምታ ጭምርም ነው። አባሎችአቸውን በጠበቀ ተዐማኝዕነት እሚመለከቱበት ልዩ መነፅር አላቸው። ተዐማኝ እሚሉአቸውን ሲያቀርቡ፤ ትንሽም ጥርጣሬ የአሳደረባቸው ላይ ዕርምጃ ለመውሰድ አያመነቱም።

እምይገርመው፤ የቡድን ናርሲሲስት'ዖች – የቡድንአቸውን ታላቅዕነትን ከማራገብ በስተቀር፤ ለቡድንአቸው አባልዐት ደህናዕነት ብዙም ሲጨነቁ አይታዩም – በ የቡድኑ አባልዕነትአቸው ሳቢያ በሚያገኙት ስም እና ዝና የእራስአቸውን የግል ተፈላጊዕነት ያረኩበታል፣ የአላቸውን ፍራጃይል የእራስ-መተማመን ይንከባከቡበታል እንጂ።

ጎበዝ፤ ስለ ቡድን ናርሲሲዝም የአለንን ቅንብር ከመቋጨትአችን በፊት፤ [ምን ማድረግ ይቻላል] ይሆን በእሚል ሃሣብ ዙሪያ ምርምምር የአደረጉ፤ በመስኩ የአሉ ሰዎች ከእሚጠቃቅሷቸው እንዱን የመፍትሄ ሃሣብ ተየህ ቀጥለን እንድናካትት ፈቃዳችሁ ይሁን።

አዎን፤ እንዲህ ይሉ አለ። [የቡድን ናርሲሲዝም] እና [ጤናማ በእራስ ቡድን መተማመን] በ አንድ ቡድን ዳይናሚክስ ዉስጥ አብረው ሊገኙ ይችላሉ። ይ-ህ [የቡድን ናርሲሲዝም] እና [የጤናማ በእራስ ቡድን መተማመን] አብሮ መገኘትም፤ የቡድን ናርሲሲዝም ቡድን-ኤክስ በ ቡድን-ዋይ ላይ ከእሚያቀነቅነው የጥላቻ አዙሪት ይወጣ ዘንድ፤ እንደምያግዝ ይገመታል። አወንታዊዕነት ወደአላቸው የቡድን እሴቶች እና ወደ ቀና የቡድን መገለጫዎች በማመዘን እና ጤናማ በእራስ መተማመንን በማሳደግ በማጐልበት።

እናም – ጤናማ በእራስ ቡድን መተማመን፤ በ ግለሰብ የእራስ መተማመን እና በ የቡድን ናርሲሲዝም መሃከል ሊኖር እሚችለውን አወንታዊ ትስስር ያሳልጣል — ጤናማው በእራስ ቡድን መተማመን፤ ሊያመዝን ይችል የነበረውን የቡድን ናርሲሲዝም በእጅጉ በማደብዘዝ፤ ህብርዕነትን አንድዕነትን ቀናዕነትን አወንታዊ በሆነ መልኩ እሚያስተናግድ አወንታዊ ማህበረሰብዓዊ ትስስርን በመፍጠር በኩል – ግዙፍ ሚና ይጫወታል የእሚል ዕምነት አለ።

በአንፃሩ — የቡድን ናርሲሲዝም የበለጠ ትኩረትን እሚስበው፤ ናርሲሲዝም የቡድኑ ገላጭ እሴት ተደረጎ ከተወሰደ እና አወንታዊው ጤናማው በእራስ ቡድን መተማን ገሸሽ የተደረገ እንደሆነ ነው። ለምሣሌ፤ የስልጣን ጥቅለላ፣ ማህበረሰብን እምይአራርቁ ነገሮችን ማጉላት፣ የህብርዕነትን የአንድዕነትን ጥንካሬ ማጣጣል፣ ከማህበረሰብ መራቅ እና የመሳሰሉ ነገሮችን ተግባርዓዊ ማድረግ — ቀድሞውንም በእራስ የመተማመን ጥርጣሬ የአለባቸውን የ'ናርሲሲስቲክ ቡድን አባልዐት፤ ምንአልባትም የጥላቻ ፊታቸውን ወደ "ሌሎች" ቡድኖች ላይ እንድያዞሩ የበለጠ ሊገፋፋቸው ይችላል። የ በእራስ የመተማመንአቸውን ቁመና እሚያጎለብትላቸው፤ ተሳታፊ የሆኑበት ቡድን እንደሆነ ያምናሉ — በእራስ የመተማመን ስሜትአቸውን እምይጠብቅላቸውን "ቡድን" ደሞ በተራቸው ይጠብቁት ዘንድ የግድ መሆኑንም ይቀባላሉ።

ይህ-እን ማድረግአቸውን እሚያስመሰክሩትም – ከሁሉም አባልዐት የጐላ ስራ መስራትአቸውን እርግጠኞች ለመሆን፡ ከሁሉም አባልዐት የበለጠ የገዘፈ ዕኩይ ስራ መስራትአቸውን እርግጠኞች በመሆን ነው።

አንዴ እንድገመው። የ ቡድን ናርሲሲዝም እና ጤናማ በእራስ ቡድን መተማመን አብረው መገኘት – የቡድን ናርሲሲዝምን፤ ስነልቦናዊ ጠቀሜታ ከአላቸው አወንታዊ ማህብረሰብዓዊ እሴቶች ጋር እንዲቆራኝ ያደርጉታል። ከ ማህበረሰብ ጋር ቀና-ትስስር መፍጠርን፣ ህብርዕነትን አንድዕነትን ደስተኛዕነትን እና የመሳሰሉትን በጎ ስብዕናን አጎልባች ከሆኑ እሴቶች ጋር እንዲዛመድ ይረዱታል።

የእዚህ ዳይናሚክስ ውጤትም፤ የ ቡድን ናርሲሲዝም ተሸክሞት እሚጓዘውን አሉታዊ ጎጂ የጥላቻ ስሜቶችን እና ዕኩይ ዝንባሌዎች እጅጉን ማደብዘዝ ነው እሚሆነው። የቡድን ናርሲሲዝምን — ከ በጎ የግለሰብ-ትስስር ስነልቦና፣ ሕዝብን በቅንዕነት ከእሚያስተሳስሩ እሴቶች ጋር ማዛመድ እና ለእራስ ከ እሚሠጥ የገነነ ትኩረት ይልቅ፤ እጅጉን የላቀ የሞራል-ልዕልናን በማጐናፀፍ – [ሰዉ]ም [ፈጣሪ]ም ከእሚወደው ቀና ማህበረሰብዓዊ ህይወት ጋር ያዛምደዋል እሚል ሙያዊ ዕምነት አለ።

በአጠቃላይ – በ አንድ ናርሲሲስቲክ ቡድን ዉስጥ፤ አወንታዊ የ መንፈስ ጥንካሬን እሚያጎለብቱ እሴቶችን ማጉላት፣ ቀና ስሜትን መፍጠር መቻልን እና የሁነቶች አወንታዊ ገፅታዎች ላይ የማተኮር ዝንባሌዎችን ማጎልበት — የ ቡድን ናርሲሲዝም፤ ቡድን-ኤክስ በ ቡድን-ዋይ ላይ እምይፈጥረውን የጥላቻ እና የጠላትዕነት መንፈስ ለማስወገድ ይረዳል።

እኛ አዳራሽያንስ ለ ውድ የ ኢትዮጵያ ልጆች ዕምንዕለው አንድ ተጨማሪ ነገር አለ። ስሙን እማ — የሰዎችን የናረ ስሜትዓዊዕነት የመግታት ችሎታን እምያዳብሩ ተሞክሮዎችን በማህበረሰቡ ዉስጥ በማስረፅ እና በማጎልበት፤ ህብርዕነትን እና አንድዕነትን የማዳበር ተሞክሮን በማጉላት እሚገኙ ልምዶችን በማስፋፋት፤ በ አንድ ናርሲሲስት ግለሰብም ሆነ በ አንድ ናርሲሲስቲክ ቡድን መንስኤዕንት፤ ቡድን-ኤክስ በ ቡድን-ዋይ ላይ እሚፈጥጠረውን ጥላቻ እና ጥቃት ለማርገብ — በተጓዳኝም፤ ሊከተል እሚችለውን የ ብቀላ እርምጃ ለመከላከል እና ሰላም እና መረጋጋትን ለማስፈን እምያስችል ስልጡን ማህበረሰብዓዊ ኢንቫይሮንመንት'ን መፍጠር፤ እንደ እማይቻል

ተደርጐ ሊቆጠር አይገባም እና — ፈርጀ-ብዙ በሆነ መልኩ፤ በ ግራንድ-ስኬል በቀናዕነት እንሞክረው!

ምርጫ ቢሱ ምርጫ

በ ወርሃ ነሃሴ 2012 ዓ.ም ሊደረግ ታቅዶ የነበረው 6-ኛው ሃገርዓዊ ምርጫ፡ እስከ ዛሬም ድረስ በተለየ መልኩ አወዛጋቢ ሆኖ እንዳለ-አለ። ለ ሁለት ጊዜ ያህልም ምርጫ ይደረጋል በ እሚል የተቆረጡት ቀንዐት እንዲራዘሙም ተደርገዋል። በሂደቱም፤ በ የመንግሥትዕነት ቦታው ላይ የአለው፤ ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ ለ ውሳኔዎቹ ምክንያቶቼ እየ አለ ለ ሕዝብ የ አካፈለአቸው ሃሣቦች ሁሉ፤ ቅን መሆን የአልተፈጠረበት መሆኑን እምይአረጋግጡ ውሸቶች እንደ ነበሩ፤ ዕሙን ነው።

ለእዚያም ነበር አዳራሽ ሂደቱን እንደ ቲያትር ትቆጥረው የነበረው። ምክንያቶቹ የለየለት ዲስኢንጀኒወስዕነትን እሚያንፀባርቁ ነበሩ እና! የሚያዝያው 2012 ዓ.ም ቲያትር [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ 1]፣ የመስከረም 2013 ዓ.ም ቲያትር [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ 2] እንደ “ስኼሌ” እና ምናልባትም፤ ይህ-እኛው የግንቦት 2013 ዓ.ም ቲያትር [ሴቪንግ የጎሣ–ፖለቲካ 3] ሪሊዝ “ፊናሌ” መሆኑ ነው እንግዲህ። ገዥው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ — ነገ ምን እንደ እሚል ባይታወቅም።

ጠቅለል አድርገን ስንወስደው፤ ምርጫው እንዲራዘምም ሆነ እንዲካሄድ ለማድረግ ይሰጡ የነበሩት ሰበቦች፤ በ ኮቪድ–19 ዓለም-አቀፍ ስርጭት [የስጋት መጨመርም ሆነ የስጋት መቀነስ] ሂደት ላይ የሙጥኝ ያሉ እንደነበር መርሳት አይቻልም – በቅርቡ የቅድመ ምርጫው ሂደት ምርጫ-ቦርድ እንደአቀደው ስለአልሄደለት እሚለውን ሸንገላ ጨምሮ። እንጂ እማ ዕውነትኛ ምክንያቶቹ [ከሞላ ጐደል] እሚከተሉት እንደ ነበሩ ዕንዐምን አለን።

- *ሚያዝያ 2012 ላይ ምርጫው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲራዘም – የሰላም እና መረጋጋት እጦት፣ የመሠረትዓዊ ቅድመ-ሁኔታዎች አለመሙዋላት፣ የተፎካካሪ ድርጅቶች ፈርጠም ብሎ መታየት እና ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ እሚያሸንፍ መስሎ ስለአልታየው፣*
- *መስከረም 2013 ላይ ምርጫው እንዲደረግ ሲወሰን፤ ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ የ ህገ-መንግሥታዊ ቅቡልዕነት ጥያቄ እንቅልፍ ስለነሳው እና አንድ-አንድ ተፎካካሪ ድርጅቶችን ኢምፖተንት በማድረግ በኩል የተሳካለት ስለመሰለው፣*
- *ግንቦት 2013 መጀመሪያ ላይ ምርጫው እንደገና እንዲራዘም ሲደረግ – የሰላም እና መረጋጋት ችግር እየባሰበት ስለመጣ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ብሶት መጉረፍ እና ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ፤ የ ውጪ ሃገራት የፈጠሩትን አሉታዊ ጫና ማስተናገድ ስላልቻለ፤ ትንሽ ፋታ ለማግኘት በማሰብ እና*
- *ብዙም ሳይቆይ በ ግንቦት 2013 መጨረሻ፤ ምርጫው ሰኔ አጋማሽ ላይ እንዲደረግ ሲወሰን – የተፈጠረ አንዳችም በጐ ነገር ኖሮ ሳይሆን፤ ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ፡ በዉጪም በ ዉስጥም ተሰንቆ ስለተያዘ፣ የ ህገ-መንግሥትዓዊ ቅቡልዕነት ጉዳይ ሆዱን እየቆረጠው ስለተቸገረው፣ አንድ ሁለት የ ኦሮሞ ድርጅቶች በምርጫው ተሳታፊ በአለመሆናቸው፤ ብልፅግና ምርጫውን እንደምንም ብዬ ማሸነፌ አይቀርም ብሎ ስለተማመነ፤ የተሻለ ነው ብሎ እምይአምነው ሌላ አማራጭ ስለሌለው እና ዙሪያው ገደል ስለሆነበት የ-ተስፋ መቁረጥ እና የ ይለይለት መንፈስ የገፋፋው ውሳኔ፤*

መሆንአቸው አያጠራጥርም።

በነገርአችን ላይ – ብልሁ የኦሮሞ ሕዝብ፤ ድርጅቶቹ በምርጫው እንዳይሳተፉ ተደርገውበት እየአየ እየሰማ፤ የአመኔታ የድምፅ ካርዱን — ለብልፅግና ይሰጣል ብለን ዐንዐምንም።

ሌላው — ምርጫን በተመለከተ፤ የመሠረትዓዊ ቅድመ-ሁኔታዎች አለመሟላት፡ በተለይም የሰላም እና መረጋጋት አለመኖር እና ኢትዮጵያዊ ተቋማት አለመኖራቸውን በማገናዘብ፤ ዛሬ ልንአደርገአቸው እሚገቡን ነገሮች ቢኖሩ — <u>ምርጫ ማድረግን ሳይሆን</u>፤ ነፃ-አውጪ ነን ባይ ሽብርተኞችን እምአያካትት፡ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ መጥራት፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማዋቀር፣ አዲስ [ንፁህ] ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመስረትን ብቻ ናቸው — በ መሠረትዓዊዕነት!

ትክክል። ምርጫው መሠረትዓዊ ችግሮቻችንን አያቃልልም – ፍትህዓዊም ነፃም ህግዓዊም አይደለም። ዲሚክረሲን ያዋልዳል እሚባለውም፤ የደናቁርት ቧልት ነው። እንደ እምትአዩት፤ ምርጫው ምርጫ አይመስልም። ሕዝብ በምርጫው ደስተኛ አለመሆኑን በተለያየ መልኩ ግልፅ አድርጓል። ተፎካካሪ ተብዬዎች — አንዳንዶቹ ለማስመሰል ያህል ብቻ ቢሆንም፤ የመረረ ብሶት በማሰማት ላይ ናቸው። ምርጫ ቦርድ ከህግ በላይ ነኝ እየአለ ነው። የውጪ ሃገርዐት ሳይቀሩ፤ በምርጫው ላይ ዕምነት እንደሌላቸው በግልፅ እየተናገሩ ነው። ከእዚያም አልፈው፤ ማዕቀብ በመጣል እና ተጨማሪ ማስፈራሪያዎችን በመሰንዘር – ለእዚህ መንግሥት አንዳችም ዕምነት እንደሌላቸው እየአስታወቁ ነው። ታዲያ፤ ስለ የምን ምርጫ ነው እሚወራው?! ከየት ለእሚመጣ ሌጅትመሲ ነው እሚቋመጠው?!

ትክክል፡ ምርጫው ገና ከ ሂደትኡ ከሽፏል። ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ ሊያሸንፍ እንደሚችል መገመት ከባድ ባይሆንም፤ እየቋመጠለት ያለው ሌጅትመሲ እንዳማረው መቅረቱ ግና ምንም ጥርጥር የለውም! አሁንም አልረፈደም። መንግሥት ተብዬው ምርጫውን ሊሠርዝ ይገባል ብቻ ሳይሆን ተፎካካሪ ተብብዬዎችም ቦይካት ማድረግ አለባቸው። መራጩ ሕዝብ በምርጫው እንዲሳተፍ ከተገደደ ግና፤ አደራ – ድምፅ መስጠት ላይ የመሳተፍአችን ተልዕኮ፤ ብልፅግና እሚባለውን የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ፤ ከፖለቲካው ማማ አዉርዶ፡ ከ አራት-ኪሎ ማባረር ብቻ መሆኑን መዘንጋት አይገባም!

ወቅትዓዊ ዕውነትዐዎች

ከእዚህ ቀደምም እንደነገርንአችሁ፤ ከ ህወሓት ጋር እየተደረገ የአለው ጦርዕነት ዛሬም ድረስ አልተጠናቀቀም። በፍጥነት ሊጠናቀቅ ይገባል። በእየገደሉ እሚሮጡ አሁንም አሉ። አፈ-ቀላጤዎችአቸውም ከ ኢትዮጵያ በዘረፉት ገንዘብ እየተረዱ የ’ዲፕሎማሲውን መድረክ እየአጣበቡት ነው። ይ-ህ ጦርዕነት ከተጀመረ በኋላ፤ የሃገር አፍራሽዋ ህወሓት ቡችላዎች – ዛሬም ድረስ ዕትብትአቸው እንድአልተቆረጠ እና ለ’ኢትዮጵያ የአላቸው አመለካከት ዛሬም ቢሆን ያ-ው ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው

የ ህወሓት የደደቢት ማኒፌስቶ እንደሆነ ግልፅ እየአደረጉልን ነው።

ህወሓት ላይ እየተወሰደ የአለው እርምጃ፤ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ከ ህወሓት እና ከ ኦነግ ጋር [ዛሬ] ድርድር እሚባል ነገር ሊታሰብ አይገባም። ኢትዮጵያዊ መንግሥት ከመሠረትን በኋላ እንጠራቸዋለን — እስከዚያ ድረስ ነፍሣቸው ከቆየች። ህወሓት በአሁንዋ ሰዐት [ዲካፒቴትድ ቺከን] ማለት ነች። የተደረገው ጦርዕነት በመሆኑ፤ ትግራይ ዉስጥ ችግር መኖሩ አይካድም እና ንዋሪው ሕዝብ እንድአይጎዳ ጥንቃቄ አይጉደል። የህወሓት ተከታዮች ለእምያሰሙአቸው የ መረረ የውሸት ክምሮች ጆሮ መስጠት አያስፈልግም። የ ዐማራ ልዩ ሃይል ትግራይ ዉስጥ መኖሩን እርግጠኞች አይደለንም። የ ኤርትራ ሠራዊት ግና፤ ዛሬውኑ መውጣት ይኖርበታል። የ ሴቶች መደፈር ጉዳይ፤ ትኩረትን ይሻል። ህወሓት መቀሌን ከመልቀቅዋ በፊት [ከጦርዕነቱ በፊት]፤ የሴቶች መደፈር ችግር የከፋ ደረጃ መድረሱን እሚጠቁሙ ዜናዎች ከወደ መቀሌ ይሰሙ እንደነበር እንአስታውሳለን — ያገባናል የአሉ ሴቶች የተቃዉሞ ሰልፍ ሊያደርጉ ሲሉም፤ በዋናዎቹ የህወሓት ባለስልጣንዐት በይፋ መከልከላቸውንም ጭምር። ለመሆኑ፤ ከጦርነቱ በፊት ትግራይ ዉስጥ ይደርስ የነበርውን የጎላ የሴቶች መደፈር፤ ማን ነበር እምያደርሰዉ?

በ የአለፉት 30-ዓመትዐትም ሆነ የሰሞኑ ጦርዕነት ከተጀመረ በኋላም ቢሆን፤ በ ህወሓት ከደረሰበት የማንዕነት ቅሚያ፣ ሰቆቃ እና ጀኖሳይድ ጋር ሲነፃፀር — የ ዐማራ ሕዝብ የአሳየው ሁለዕንተንዓዊ ቻይዕነትን ጨዋዕነትን እና [ሰው]ዓዊዕነትን፤ መስካሪዎቹ የህወሓት ቡችሎች ሳይሆኑ፤ ጤናማ የሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ እና ፈጣሪ ብቻ ናቸው። ዛሬ-ዛሬ የ ህወሓት ርዝራዦች፤ የ ዐማራውን ሕዝብ ስም እና ቅዱስ ተግባርዐት ለማጠልሸት እና በእነርሱ አገላለፅ ["አያኗኑረንም"] እሚልኡትን ጥጋብ፣ ዕብሪት እና ድንቁርና የተጠናወተው ዛቻ አይሉት ድንፋታ፤ ነፍስአቸውን ለማትረፍ ከተሸሸጉበት፤ ተራ በተራ ብቅ እየአሉ ሲያላዝኑብን ይደመጣሉ። ይልቁን እስ፤ ሰውን-ከሰው፣ ሕዝብን-ከሕዝብ ሊያስተሳስሩ ሊያቀራርቡ ሊያፗኑሩ እሚችሉ በጎ ቀና ማህበረሰብዓዊ እሴቶችን ማጎልበት ማስፋፋት ላይ ብትሰሩ አይሻላችሁም?!

እዚህ ላይም፤ የ ህወሓት ቡችሎች አንድ የአልገባቸውን ነገር እንዲገባቸው እንፈልግ አለን። ህወሓት እና ዓምላኪዎቿዋ፤ እንደ ጐረቤት ከ ዐማራው እና ዛሬ-ዛሬ ከ ኤርትራ ሕዝብ ጋር ብቻ ሳይሆን፤ ከ መላው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር — እንደ አንድ ሃገር ሕዝብ [አብሮ መኗኗር] እሚባል ነገር የ አቆሙት፤ ህወሓት ደደቢት ከገባችበት ያ-ች የተረገመች ቀን ጀምሮ ነው። አይደለም እንዴ? እና፤ ዛሬ መውጫ መግቢያው ሲጠፋችሁ፤ ስለ የትኛው አብሮ መኗኗር ነው እምታላዝኑት። ማንስ ህወሓትን ያምናታል እና ነው ስለ ስትራቴጂክ አላያንስ እምትዘላብዱት? ህወሓቶች የእራስአቸውን ወንድሞች ነበር እኮ፤ ለስብሰባ/ለድርድር ብለው ጠርተው፤ ሲጨልም አዳርአቸው ላይ የአረዷቸው። አይደለም እንዴ?

[በ ወልቃይት ጠገዴ ራያ] አካባቢዎች፤ ህወሓት — የ ማይካድራን ጀኖሳይድ ጨምሮ፤ ለ 27-ዓመትዐት ገደማ የ አደረሰችውን የማንዕነት ንጥቂያ እና ገና የአልተነገረለት ጀኖሳይድ፤ በ ኢትዮጵያ ልጆች የተጠና እና የተቀናጀ ሪፖርት ለ ዓለም ሕዝብ ይፋ ሊደረግ ይገባል። በ መላው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የ አደረሰችውንም ሰቆቃ እና ዕልቂት ጭምር!

እንደ ማጠቃለያ

ዕውነት ነው። ኢትዮጵያን እየገዛ የአለው መሪ ተብዬም ሆነ እሚከተለው አይዲዮሎጂ አሮሙማ፤ ጤናማ አይደሉም። እናም፤ በዙሪያው የአላችሁ ጤናማ ሰዎች፤ ወገንዓዊ ምክርአችንን እንድእትሰሙ አጥብቀን እንጠይቅ አለን። እንደ 21ኛው ክፍለ-ዘመን [ሰዉ] ልትሰሩ እምትችሉት ስልጡን ነገር አለ። ሳይኪያትሪስቶችንም ሆነ ሳይኮሎጂስቶችን አማክሩ። ዝም ብሎ መመልከቱም ትልቅ ስህተት ነው እና — ይብቃ!

ኢትዮጵያ፤ የዉስጥ ፖለቲካዋን ፈር ማስያዝ ከቻለች፤ የውጭ ሃገርዐት ጣልቃ-ገብዕነትን አደብ ማስገዛት አያቅታትም ብለን በፅኑ እንደእምንዐምን – ሕዝብ እሚላችሁን ከአልሰማችሁ ግና የጊዜ ጉዳይ ከአልሆነ በስተቀር፤ ሃገርንም ሕዝብንም እራስአችሁንም ይዛችሁ አሁን የተዘፈቃችሁበት ጨለማ ዉስጥ፤ እንደእምትሰምጡ – ለ 3-ዓመታት ያህል የአለመሰልቸት በተደጋጋሚ ነግረንአችኋል።

በኢትዮጵያ ግዛትዖች ሁሉ ተንሰራፍቶ የአለው የሰላም እና መረጋጋት እጦት፣ በ ዐማራ እና በ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኚያን ላየ እየተፈፀመ የአለው ጀኖሳይድ ዛሬም አልቆመም። የወደሙ ከተማዎች ሊገነቡ፤ ህይወትአቸው የተመሰቃቃለ የተፈናቀሉ ወገኖችአችን ሊቋቋሙ ይገባል። እየአሰለጠናችሁ እምታሰማሩት የ ኦንግ መንጋ፤ የ [ሰው] ልጆችን መጨፍጨፍ እንዲያቆም ይገደድ እና ለፍርድ ይቅረብ!

ብታዳምጡን ይበጅአችኋል! እናንተ እንደእምትሉት፤ የ ኢትዮጵያ የህልውና ጠላትዖች የውጪ ሃገራት አይደሉም። ለ ኢትዮጵያ ህልውና ወሳኝ የሆኑ ወቅትዓዊ ተግባራትም፤ ምርጫው ወይም ግድብኡ ናቸው ብለን ዐንዐምንም። ምርጫውን ዕኮ ህወሓትም ስልጣን ላይ ብትሆን ኖሮ፤ ታካሂደው ነበር – ያውም ለ ስድስትኛ ጊዜ እና ምን አልባትም ከእናንተ በተሻለ መንገድ። የግድብኡ መሠራትን በተመለከተም፤ ዐፄ ኃይለሥላሴ – በሃሣብ ማንሸራሸር ደረጃም ቢሆን አሻራቸው አለበት። ስለ አረመኔው መንግሥቱ የሰማነው ብአይኖርም፤ በይበልጥ ግና ከሃዲው ሃገር አፍራሹ መለስ ጊዜው የፈቀደለትን ያህል ሰርቷል። በምርጫው ወይም በግድብኡ ዙሪያ — የብልፅግና አስተዋፅዖ ለመሆኑ ምንድነው?! ችግሮችን ከማባባስ እና ከማመሰቃቀል በስተቀር።

አዎን፤ የኢትዮጵያ የህልውና ጠላትዖች፡ ገዢው የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ [ብልፅግና] እና እሚመራበት አይዲዮሎጂ [አሮሙማ] ናቸው። ለ ኢትዮጵያ ህልውና ወሳኝ የሆኑ ወቅትዓዊ ተግባራትም፤ ሽብርተኞችን እምአያካትት፡ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ መጥራት፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማዋቀር፣ አዲስ [ንፁህ] ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመስረት ናቸው።

ሕዝብ እምይነገርአችሁን፤ በቀናዕነት ወስድአችሁ ተገቢውን ለውጥ ለማካሄድ ፈቃደኛ ከአልሆንአችሁ፡ ዛሬ ከእምትገኙበት መቀመቅ የባሰ — በቅርቡ፤ እራስአችሁን ልትተነፍሱ ከእማትችሉበት ቦታ እንደምታገኙት፤ አንጠራጠርም። ደጋግመን ይህ-እንን የ እምንነግርአችሁ ለእንአንተ አዝነን እንድአይመስልአችሁ። ለ ኢትዮጵያ እና ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ስንል እንጂ! እግረመንገዱን እሚጠቅማችሁ ከሆነም፤ ቅር አይለንም። እኛ እንደ እንአንተ አይደለንም። በ[ሰዉ] ልጅ ላይ በእሚደርስ ችግር ሰቆቃ እና ዕልቂት — አንደሰትም!

ውድ የ ኢትዮጵያ ልጆች፤

ነገሮች ሁሉ እየመረሩ ነው። መንግሥት ተብዬው፤ ከውጪም ከዉስጥም መፈናፈኛ አጥቶ እየተደናበረ ነው። በ እንዲህ የአለ ጊዜ፤ ምን ሊከሰት እንደ እሚችል ማወቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል እና ለከፋም ለደጉም፤ በአግባቡ ተደራጅቶ ተዘጋጅቶ እና ነቅቶ መጠበቅ፤ ብልህዕነት ነው።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ – ምርጫው፤ ምርጫ ቢስ ነው። ለ ምርጫው ሊቀርቡ የነበሩ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን እና አንድ-አንድ ፖለቲከኞችን በ እየምክንያቱ በማባረር – ምርጫው [ፍትህዓዊ] እንድአልሆነ ተረጋግጧል። በ ኦሮሞ ክልል – ተስማምተዉም ሆነ ተገድደው – ሌሎች የኦሮሞ ድርጅቶች እንዲሁም ሌላ ማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ሊወዳደሩ አለመቻልላቸው እና በሌሎች በዛ የአሉ ግዛቶችም፤ በሰበብ አስባቡ ምርጫ ስለማይደረግ – ምርጫው [ነፃ] እንድአልሆነ ተረጋግጧል። ምርጫ ቦርድ ከህግ በላይ ነኝ በማለቱ እና ለምርጫ ሊቀርቡ ፍርድቤት የፈቀደላቸውን ዜጎች አልመዘግብም በማለቱ፤ ምርጫው [ህግዓዊ] እንዳልሆነ ተረጋግጧል። ብልፅግና በመንግሥት ሃብት ንብረት እሚጠቀም መሆኑ እና የቅደመ ምርጫው ሂደት በብልፅግና እሚስተናገድ በመሆኑ – ምርጫው [ዲሚክረሲን ሊይአዋልድ] እንደ እማይችል ተረጋግጧል።

እናም፤ መንግሥት ተብዬው ምርጫውን ከመሠረዝ፣ ተፎካካሪ ተብዬዎችም ቦይካት ከማድረግ ሌላ አማራጭ የላቸውም። አዎን፡ “ህይወት” [የ እኛም ህይወት ህይወት ከተባለ፤] መቀጠሉ ስለእማይቀር – በምርጫው መሳተፍ ግድ ከሆነ – ድምፅ የመስጠት ተልዕኮው፤ ብልፅግናን ከፖለቲካው ማማ አዉርዶ፤ ከ አራት-ኪሎ ሲባረር ማየት ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ህልውና ቀንደኛ አደጋ እርሱ እራሱ ብልፅግና ነው እና! ዕውነት ነው፤ የጠቀስነው ተልዕኮ በእዚህኛው ምርጫ ላይሳካ ይችል ይሆናል። የምርጫው ውጤት፤ የእሚሆንኧውን ቢሆንም፤ በድምፅ አሰጣጡ ላይ መሳተፍአችን፤ በዋናዕነት – እንደ [የ ቀጣዩ] ሕዝብዓዊ ንቅናቄ አንዱ አካል ተደርጎ ነው ሊቆጠር እሚገባው።

ብልፅግናን እና እሚመራበትን መሠሪ አይዲዮሎጂ ኦሮሙማን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንድአልተቀበለው፤ የአመኔታ ድምፅአችንን ነፍገን፤ ለ ዓለም-ሕዝብ እምንሰደው የ ፍትህ ጥማት ሲግናል – ትርጉሙ ረቂቅ እና ኃያል ነው። እናም፤ የ 14-ሰኔ ቀጠሮአችን፤ ድምፅአችን ሲታፈን ድምፅ የሆኑልንን፣ ስንሰቃይ አይዞአችሁ የአሉንን፣ ስንገፋ ከጎናችን የቆሙትን የደገፉንን እና ስንጨፈጨፍ አብረውን የጮሁትን ለመምረጥ ይሁን — አደራ!

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

### አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንገናኝ –

# በ ዕንቅርት ላይ ጆሮ-ደግፍ

ሃምሌ ፪ሺ፲፫ ዓ.ም || ጁላይ 2021

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

ምርጫ ተብዬው በከፊል የተካሄደ መሆኑ እና መንግሥት ተብዬው ኢ-ራቲክ በሆነ መልኩ ትግራይን ለቅቆ መውጣቱ፤ ሁለት ቀልብ የሳቡ ጉዳዮች ሆነው መሰነነባበታቸውን ሰበብ አድርገን፤ ዕምንዕለውን ለማለት በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበን አለ።

እናም፡ "አብረን እንቆይ" – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

ወደ ሁለቱ ሰሞነኛ ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት፤ ለ ኢትዮጵያ [ትናንትም ዛሬም ሆነ ነገ] መሠረታዊ ናቸው እምንላቸውን ነጥቦች ጠቅሰን ማለፍ ግዴታችን እንዲሆን መርጠን አለ።

<u>መሠረትዓዊ ችግሮቻችአችን</u>

ለ 30-ዓመትዐት ተግባርዓዊ እየተደረገ የአለው፡ ህወሓትዓዊ ኦነግዓዊ እና ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ብልፅግናዊ ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ የጎሣ-ፖለቲካ እና በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሰረተው ፌደራሊዝም ናቸው።

<u>መሠረትዓዊ የ መፍትሄ ሃሣቦች</u>

ሀ) ኢትዮጵያዊ ሀገርዓዊ ጉባኤ ማካሄድ። ተልዕኮው፤ ለ የ ኢትዮጵያ የፖለቲካ በሽታ ፈውስ መፈለግ። ስያሜ ላይ መፈላሰፉም ሆነ መነታረኩ ፋይዳ የለውም።

ለ) የ ሕዝብን፣ የ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጥምረት በማቀናጀት፤ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት ማዋቀር። የሽግግር መንግሥቱ ተልዕኮ፤ በዋናዕነት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ማስከበር፣ የህዝቧን ሰላም እና መረጋጋት ማስፈን፣ የ ሁሉንም ተቋምአት ተግባር በሃላፊዕነት መምራት፣ እሚቀጥለውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበት'ን ምርጫ – ፍትሀዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ እሚያስፈልጉትን ተቋምዓዊ ለውጦች ተግባርዓዊ ማድረግ። አሁንም – ስያሜ ላይ መፈላሰፉም ሆነ መነታረኩ ፋይዳ የለውም።

ሐ) ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ኢትዮጵያዊ ህገመንግስት መቅረፅ። ተልዕኮው፤ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን መታደግ። እንደ አዲስ በእሚቀረፀው ህገመንግስት ውስጥ — አለመረሳቱን ብቻ ሳይሆን፤ ጎልቶ መታየቱንም ጭምር እርግጠኛ ልንሆን ከእሚገባቸው ክሪቲካል ጉዳይዖች መሃከል፤ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ መገደብ፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ ማፍረስ እና በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ማካተት ።

መ) ሰው በሰውዕነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት።

እነእኚህን በቀናዕነት ተግባራዊ ማድረግ፡ ዕሙኑን፤ ከ ግለሰብ እና ከ ድርጅት በላይ የሆነ ማይንድሴት'ን የግድ እሚል — የ ኢትዮጵያ እና የ ኢትዮጵያዊዕነት የህልውና ጉዳይ ነው!

የ ምርጫው ጉዳይ

ምርጫው፤ [ይሄም ምርጫ ከተባለ] ደንበር ገተር እየአለም ቢሆን ወደ መጠናቀቁ ገደማ እየተቃረበ ነው። በ 14-ሰኔ የመጀመሪያው ዙር ተከናውኗል። እሚቀጥለው፤ ለ ጳጉሜን ቀጠሮ ተይዞለታል። ተዚያ የተረፉት ምርጫ ያልተደረገባቸው ግዛቶችን ዕጣ-ፈንታ ጊዜ ይነግረናል ብለን እንጠብቅ።

የ ቅድመ ምርጫው ሂደት፤ ፍትህዓዊ'ም ነፃ'ም ህግዓዊ' ከ አለመሆኑም በአሻገር፤ ዲሚክረሲን ሊያዋልድ እንደ እማይችል'ም ግልፅ ነበር – አንድ። ምርጫ-ቦርድ በአግባቡ በአለመዘጋጀቱ እና የገዥው ፓርቲ የለየለት የምርጫ ድምፅ ዘረፋ ስለአካሄደ፤ የ ድምጥፅ አሰጣጡ ስነስርዐት [ተዐማኒ-ፍትህዓዊ-ነፃ-ህግዓዊ-ዲሚክረሲዓዊ] በሆነ መልኩ ሊካሄድ እንዳልቻለ ምስክር ፍለጋ መድከም አያስፈልገንም – ሁለት። ሦስት – ድህረ-ምርጫው በ ብሶት በ የመረረ ቅሬታ እና በ አቤቱታ የተጣበቡ በ መሆናቸው፤ ምርጫው ባተቃላይ — በ ዕንቅርት ላይ ጆሮ-ደግፍ የሆነ ፊውታይል ኤክሰርሳይስ ሆኖ መቅረቱ'ን ዕንዐምን አለን። በ እዚህ መንገድ የተገኘ የድምፅ ብልጫ ላይ ተመርኩዞ እሚመሠረት መንግሥት፤ እሚኖረው ረብ ሕዝብዓዊ ቅቡልዕነት — የለም!

የሆነው ሆኖ — የ ምርጫው ውጤት ምን ሊሆን እንደ እሚችል እና ፋይዳ ቢስ ነው ብእንልም ቅሉ፤ ዛሬ ይህችን ብሏግ እየጫጫርን እያለን እንኳን፤ ውጤቱን በጉጉት ይጠብቅ የነበረን ያህል ነበር ውስጥአችንን እሚሰማን። አ-ሃ.........ለካስ እኛም [ሰው]ዖች ነን እና!

አዎን.........የ ምርጫው ውጤት ይፋ አልሆነም። ያ-ግና ቀጥለን ዕምንእለውን ከማለት ሊያግደን አይገባም ብለን ወሰንን።

ለምርጫው በዕጩዕነት ለሰታተፋችሁ ወገኖችአችን፤ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን በቀና-ልብ ሰንቃችሁ፤ ከ ፖለቲካ በሽታዋ ትፈወስ ዘንድ የተቻላችሁን ለማበርከት በምርጫው ሂደት ተሳታፊ በመሆን የ ማህበረሰብዓዊ'ው ንቅናቄ አካል ለነበራችሁ ወገኖችአችን ሁሉ — ምስጋናችን የላቀ ነው።

የምርጫው ውጤት ይፋ እሚደረገው መቼም ሆነ መቼ፡ የአሉት አማራጮቹ ሁለት ናቸው — ማሸነፍ ወይም አለማሸነፍ።

አሸንፋችሁ እንደ እየ ሃላፊዕነትአችሁ በቅርቡ ወደ ስራ እምትገቡ ሁሉ፤ ሀ) [ተልዕኮዬ፤ ኢትዮጵያን መጠበቅ እና ኢትዮጵያዊያንን በቀናዕነት ማገልገል ነው] እና ለ) [የያዝኩት ወንበር'ም የግል ንብረቴ ሳይሆን፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት መሆኑን አውቃለሁ] እሚሉ አረፍተ-ነገሮችን፤ ግንባርአችሁ ላይ እንድትነቀሱ እንፈልግ አለን!

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ነውጥ አሳስቧችሁ፤ ሃገርን እና ሕዝብን ለመታደግ፤ ዕጩ በመሆን ተወዳድራችሁ፤ ለጊዜው በቂ ቁጥር የአላገኛችሁ ወገኖችአችን — ውጤቱ መሸነፍ እንዳልሆነ እንድታውቁልን እንፈልግ አለን። የ ኢትዮጵያን የፖእልትካ ነውጥ በመረዳት የመፍትሄው አካል ለመሆን፣ ለመደራጀት እና ለመታገል በመፍቀድ ለከፈላችሁት መስዕትዕነት — እኛ አዳራሽያንስ የአለን ከበሬታ ግዙፍ መሆኑን ስንገልፅላችሁ፤ በንፁህ ወገንዓዊዕነት ነው።

በቂ ቁጥር በአለማግኘታችሁ የቀረ ነገር ቢኖር በመንግሥት መዋቅር [በ ሲስተም'ኡ] ውስጥ ሆኖ ለውጥ ለማምጣት እምትችሉበትን ኦፖርቹኒቲ አለማግኘትአችሁ ብቻ ነው — ለ አሁኑ!

እናንተ ከማንአችንም በላይ እንደ እምታውቁት፤ በ መንግሥትዓዊ መዋቅር ውስጥ ሆኖ ለውጥ ማምጣት እሚቻልበት አጋጣሚው ከአልተገኘ — ቀናው አማራጭ እና እሚቀጥለው ዕርምጃ፤ ማህበረሰብዓዊ ንቅናቄውን አጠናቅሮ በመቀጠል፤ ስኬታማዕነትን በ አንድ ምሽት ለማሳጠር በ ቁርጠኛዕነት መታገል ብቻ ነው። ለ እዚያ እሚያስፈልገንን [ፖቴንሽያል] ዕምቅ ሃይል፤ ፈጥራችሁ አለ። የ ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት፣ የሃሳብ ጥራት፣ የ ዓላማ ፅናት እና ድርጅትዓዊ መሠረት አስተማማኝ'ም በሆነ ቁመና ላይ ይገኛል። ያ-ም ትልቅ ድል ነው! የ-እዚህ ማህበረሰብዓዊ ንቅናቄ ጥንስስ አካል በመሆንአችሁ'ም ከምርጫው በፊትም - በምርጫው ቀንም - ከምርጫው በኋላም አሸናፊዎች ናችሁ እና በርቱ፤ እንበርታ!

የ መንግሥት ተብዬው ኢራቲክ ፍርጠጣ

አራት-ኪሎን አልለቅም የአለው ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ብልፅግና፤ የኢትዮጵያ ግዛት የሆነችውን ትግራይ እና ንዋሪውን ሕዝብ – አሸባሪ ተብሎ ለተሰየመ በ የለየለት ጦርዕነት ደም ለተቃባ ወንበዴ ድርጅት አጋልጦ መፈርጠጡ፤ የ እሚነገረን ዕውነታ ቢኖር — ብልፅግና፤ ምን ያህል አተርሊ ኢንኮምፒተንት የሆነ፤ ትሪዝን እየፈፀመ የአለ የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ መሆኑን ነው።

መሠረታዊው ጥያቄ፤ ይህ እንን ትሪዝን እየፈፀመ የአለ የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ የመንግሥትን ስልጣን እንዲያስረክብ ለማስገደድ፤ ምንድን ነው እሚጠበቀው –እሚል ነው።

እንደ ማጠቃለያ

ውድ የ ኢትዮጵያ ልጆች፤

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ለ ዛሬ – ምንም የመፃፍ ፍላጎት አልነበረንም፤ የለንም'ም። ሰሞነኛ ጉዳዮች ሁሉ እጅጉን አሳሳቢ ናቸው። እየአንድ አንድዋ ናኖ-ሰከንድ ወሳኝ ናት። ምን ሊፈጠር እንደ እሚችል መገመት ቀላል አይደለም። ግምትአችንን ማጋራት'ም አልመረጥንም።

ሕዝብ፣ ህወሓት፣ ብልፅግና እና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ከ ስሜትዓዊዕነት እና ከ ዕብደት በመላቀቅ፤ ኢትዮጵያን እና ኢትዮያዊዕነትን በቀናዕነት ለ መታደግ፤ የመጨረሻዋ ቅፅበት ላይ መሆንአችንን በማስገንዘብ — አበቃን!

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንገናኝ –

# አጣብቂኝ ውስጥ የገባች ሃገር

ነሃሴ ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ‖ ኦገስት 2021

**አዳራሽ** – ኢትዮጵያ እንደ ሃገር እና ኢትዮጵያዊያን እንደ ሕዝብ፤ መራር አጣብቂኝ ውስጥ ገብተናል። አሸባሪዎች በአንድ በኩል እና ኢንኮምፒተንት መንግሥት በሌላ በኩል። የከፋው ጉዳይ ደሞ፤ የውስጥ ችግሮቻችን ብቻ ሳይሆኑ፤ የውጪ ድርጅቶች እና መንግሥታት በጠላትዕነት ተሰልፈው፤ እየአጠቁን ናቸው። ደግዕነቱ፤ ለ 30-ዓመታት የተዘራው የጎሣ-ፖለቲካ ካንሰር፤ እንደእሚያጠፋን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ የገባው ደረጃ ላይ ደርሷል። ኢትዮጵያዊያን አንድ ከሆንን፤ ለምንም እንደእማንበገር ለማስመስከር፤ አድዋ — ማለት እና ንፁሁን ሰንደቅዓላማችንን ማወልብለብ ብቻ በቂ ነው። ተገቢውን የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት እና ኢትዮጵያ ሰላም ታገኝ ዘንድ፤ ሕዝብ ከምንጊዜውም በላይ አንድዕነቱን በማስመስከር ተዘጋጅቷል። ተግባራዊ መፍትሄ ለማምጣትም፤ መንግሥት ቀና እና ቆራጥ እርምጃዎችን መውሰድ የግድ ይለው አለ። መንግሥት፤ ሰንደቅ-ዓላማችንን ሊመልስን ይገባል። ፀረኢትዮጵያ የሆነውን ህገ-መንግሥት ለመገደብ እና — አዲስ ንፁህ ህገ-መንግሥት እሚቀረፅበትን ሂደት ጅማሮ ይፋ እሚያደርግ አዋጅ አውጆ በአስቸኳይ ወደ ተግባር በመግባት፤ መንግሥት የበደላትን ሃገር እና የአሰቃየውን ሕዝብ — ይካስ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

ኢትዮጵያ፤ ከምንጊዜውም በላይ የመረረ አጣብቂኝ ውስጥ ነች። በአንድ በኩል — የ ነፃዕነት ትርጉም እምአይገባቸው ነፃ-አውጭ ተብዬ ሽብርተኛ ወንበዴ ቡድኖች። በሌላ በኩል — ቢመከር ቢመከር አልሰማ የአለው፤ የ ኢትዮጵያዊዕነት ጠረን የሌለው፤ በ መንግሥትዕነት ቦታ ላይ የተቀመጠው፤ የጎሣ ድርጅቶች ስብስብ። ሁልአችንም፤ ኢትዮጵያን ከ እዚህ መራር አጣብቂኝ ውስጥ በጥንቃቄ ፈልቅቀን የማውጣት ታሪክዓዊ ሃላፊዕነት ተጥሎብናል።

ዛሬም እንግዲህ ጎበዝ፤ ተላይ በጠቀስናቸው ጉዳዮች ዙሪያ በማውጠንጠን፤ ዕምንእለውን ለማለት፤ ከፊትአችሁ ቀርበን አለ።

እናም፡ [“አብረን እንቆይ”] – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

አራት-ኪሎ መሻጊው ብልፅግና፤ የህወሓት ወንበዴዎች እየአደረሱት የአለውን ዕልቂት በአግባቡ መቋቋም አልፈለገም። ሕዝብ እየአለቀ እና ሃገር እየፈረሰም ነው።

የ ውስጥ የፖለቲካ ችግርአችን [የጎሣ-ፖለቲካ እና በ ቋንቋ እና በ ጎጥ ላይ የተመሠረተው የ ኤትኒክ ፌደራሊዝም] የፈጠረው ሁለንተናዊ ማህበረሰብዓዊ ነውጥ — እንዲሁም፤ [በሪሞት ኮንትሮል] ብሎም በ ውክልና በ እሚስተናገድ ጦርዕነት፤ ሊነዱን ሊያዙን ሊገዙን እሚፈልጉ የ ውጪ አካላት [ድርጅቶችም ሆኑ መንግሥታት] — የአለ የሌለ ጉልበታቸውን በመጠቀም — ኢትዮጵያ የገባችበትን የመረረ አጣብቂኝ የበለጠ በማጨናነቅ፤ እንደ ሕዝብም እንደ ሃገርም ጥፋትአችንን እያፈጠኑት ነው።

ኢትዮጵያ ከተሰነቀረችበት የመረረ አጣብቂኝ ትላቀቅ ዘንድ — ቀና ልጆቿ እየአደረጉት የአለው የህልውና ትንቅንቅ፤ በ ሃሣብ ጥራት እና በ ድርጅታዊ ቁመና እየጐለበተ የመጣ መሆኑን በማየትአችን በ እጅጉ ኰርተናል። ቢሆንም ቅሉ፤ ዛሬም ቢሆን ወደ ዘላቂ እና ቀጣይዕነት ወደአለው ፈውስ ሊወስደን እሚችለውን መንገድ ይዞ ለመፋለም የአለው ቁርጠኛዕነት – ገና፤ የበለጠ መጎልበት ይኖርበታል ብንል፤ ከ ዕውነታው ብዙም እምንዕርቅ አይመስለንም። መራራው ትግል ገና መጀመሩ ነው!

አዳራሽ እና ግዴታዋ

ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እና መረጋጋት ዕውን ሆነው እስከ እምንዐይ ድረስ — ለ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ነውጥ፤ ፍቱን ፈውስ እሚሆንላት ቴራፒውቲክ ሞዳሊቲ ምን ሊሆን እንደእሚገባው አለመታከት ማስገንዘብ – ለ አዳራሽ፤ የ ላይፍ-ታይም ግዴታዋ እንዲሆን ዐምነን ፈቅደን ተቀብለን አለን።

እንዲህ ነው ጉዳዩ።

የ’ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ነውጥ ዐይነተኛ ጥቅል ምክንያት፤ ዛሬ’ም እየተተገበረ የአለው [ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገመንግሥት፣ የጎሣ-ፖለቲካ እና በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ፌደራሊዝም] ነው። ፍቱን ፈውስ እሚሆንላት መሠረትዓዊው ቴራፒውቲክ ሞዳሊቲ’ም፤ አሸባሪዎችን እምአያካትት [ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሀገርዓዊ ጉባኤ ማካሄድ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የ ሽግግር መንግሥት ማዋቀር፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት] ብቻ ነው።

የዛሬ ሦስት ዓመት፤ ይህ-እንን ተግባርዓዊ በ አለማድረግአችን፤ ዛሬ የገባንበት ዐረንቋ ውስጥ ልንገኝ በቅተናል። ዛሬም መሠረትዓዊውን ቴራፒውቲክ ሞዳሊቲ፤ ተግባርዓዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ከአልሆንን — ነገ፤ እንደ ሕዝብም እንደ ሃገርም እራስአችንን ከዛሬው እጅጉን የከፋ፤ አዎ – እጅጉን የመረረ ዐረንቋ ውስጥ እንደ እምንአገኘው፤ አንጠራጠርም

ዕብሪት

የዛሬ ወር ገደማ መሆኑ ነው እንግዲህ፤ የ መንግሥትን ከ ትግራይ ፈርጥጦ መውጣት፣ ከበስተጀርባም መንግሥት ተብዬው ታንክ እና መሰል ከባድ የጦር-መሣሪያዎች፣ ቀለብ፣ ገንዘብ ለ ህወሓት በገፍ አስረክቦ መፈርጠጡን ተከትሎ፤ “ዱቄት” አድርገናታል የተባለችው ህወሓት ነፍስ ዘርታ — የ ዐማራን እና የ አፋርን “ድንበር” ጥሳ በመግባት፤ ሕዝብ በመጨረስ እና ከተማ በማውደም ላይ ተጠምዳለች። አስቤበት አቅጄ ነው ትግራይን የለቀቅሁት ሲል [መንግሥት ተብዬው] — ህወሓትን እንደገና ሪሰሲቴት አድርጎ፤ ጦርዕነቱን ከትግራይ አውጥቶ ወደ

ዐማራ ክልል እና ወደ አፋር ክልል የወሰደበትን መሠሪ የ ትሪዝን ተግባሩን፤ ገና ሳይገረፍ እየለፈለፈልን እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል። በታሪክ እሚያስጠይቀው ወንጀል ነው የፈፀመው — ዕብሪተኛው መንግሥት ተብዬ!

ሌላኛዋ የ ዕብሪተኞች መንጋ [ህወሓት] ዛሬም ትክክለኛውን የ ዕብደት ተልዕኮዋን፤ የሰለለ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ በተደጋጋሚ እየነገረችን ነው። ተልዕኮዋ፤ የ ዐማራን ሕዝብ አጥፍታ ኢትዮጵያን ማፈራረስ መሆኑን፤ በእማያወላዳ መልኩ ነግራን አለች! ከ ዐማራ ሕዝብ ጋር፤ እምንአወራርደው ሒሳብ አለን ነው ያለችው።

አልተሳክቶም ሆኖባት እንጂ፤ ከመሞከር እኮ ወደ ኋላ አላለችም — ቢያንስ ለ አርባ ዓመታት ያህል!

ትክክል፤ አልተስካላትም ስንል — ጥፋት አላደረሰችም ከፍተኛ ወንጀል አልፈፀመችም ማለት አይደለም።

ህወሓት፤ ኤርትራን አስገንጥላለች፣ የባህር በሮችአችንን አሳልፋ ሰጥታለች፣ ወንድማማች እህትእማማች ኢትዮጵያዊውን በጎሣ በቋንቋ ከፋፍላ ኢትዮጵያዊ ማንዕነትአችንን አጉድፋለች፣ የወልቃይት ጠገዴን እና የ ራያን ሕዝብ ማንዕነት ቀምታለች፣ በ ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ቁጥር-ስፍር የሌለው ጄኖሳይድ ፈፅማለች፣ ከ ቀሪው የኢትዮጵያ ግዛቶች ንብረት ዘርፋ [የዳቦ መጋገሪያ መሺን እና የ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ጀኔሬተር ሳይቀር] ከተተከሉበት ቦት እየነቀለች ወደ ትግራይ አግዛለች፣ በ ትሪሊየን እሚቆጠር ዳለር ሰርቃ እራስዋን እና ቡችሎችዋን አበልፅጋለች — ኢትዮጵያን መቀመቅ ውስጥ ከትታለች።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ለ ሕዝብአችን ሲባል እና ለወደፊትዋ ኢትዮጵያ ቀና ከመመኘት አኳያ፤ ሒሳብ ማወራረድ እሚባል የዕብሪት የዕብደት ተልዕኰ ባይያዝ በመረጥን ነበር። ታልሆነ ግና፣ ተተገደድን ግና፤ ሒሳብ ማወራረድ እሚባል ነገር ከመጣ ግና — የ ዐማራ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው፤ ከ ዕብሪተኛዋ ህወሓት ጋር ሒሳብ እሚያወራርደው።

አ፤ የረሳን እዳይመስላችሁ። ህወሓት፤ እምንአወራርደው "ሒሳብ" አለን ያለችው፤ የ ዐማራን ሕዝብ እንጨርሳለን ማለቷ ነው። አዎ፤ ለ እሱም ቢሆን፤ በአንችው ብሶ አንቺው ካመጣሽው እማ፤ ዐማራው እንዳመጣጥሽ ሊያስተናግድሽ፤ ከ እምትገምችው በላይ ተዘጋጅቶልሻል። ለፈጣሪ፣ ለ የኢትዮጵያ ዓምላክ ክብር ምስጋና ይግባው እና፤ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብም፤ እንዲሁ!

የ ድል ቀን፡ መዘግየት

በቅርብ ትውስታችን ምህዳር ውስጥ የአሉ የኢትዮጵያ ገዥዎች፤ [ዐፄ ኃይለሥላሴ – ከ ኤርትራ፣ ፕሬዝደንት መንግሥቱ ከ ኤርትራም ሆነ ከ ትግራይ] ነፃ አውጪ ተብዬዎች ጋር የነበራቸውን ፍልሚያ፤ በ አሸናፊዕነት መወጣት ያልቻሉት [አቅም አንሷቸው ሳይሆን] – እጅጉን በአመዛኙ፤ በ ግማሽ-ልብ ይዋጉ ስለነበረ እና ከ ሰርጎ-ገቦች ከከሃዲዎች እራስአቸውን ማጥራት ስላቃታቸው ነበር ብለን ዕንዐምን አለን። የ ዓለም-አቀፍ የፖለቲካው ምህዳር መለዋወጥ እና ሌሎች ጉልህ የሆኑ ምክንያቶች መኖራቸው እንደ የተጠበቀ ሆኖ።

የ ዛሬው ለየት የአለ ነው። አራት-ኪሎ መሻጊው ገዢው ፓርቲ፤ ከ ህወሓት ጋር እያደረግሁት ነው እሚለንን "ፍልሚያ" ማሸነፍ የተሳነው፤ እንደ በፊቶቹ ገዥዎች ሁሉ — አቅም አንሶት ሳይሆን፤ እሱ እራሱ ኢትዮጵያዊዕነቱ የአልለየለት በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ መፍረስ ስለማያሳስበው እና በ ኩርማን-ልብ ስለሚዋጋም ጭምር ነው ብለን ዕንዐምን አለን። ።

ጉበዝ፤

ጦርዕነቱን በፍጥነት ለመቋጨት በእሚል — ለ አሸባሪ ድርጅቶች፤ ምንም ዐይነት የድርድር በር-እም ሆነ የመሣሪያ ማስገቢያ እና የመፈርጠጫ ኮሪዶር ይሰጣቸው ዘንድ፤ እንደ አልቲሜተም ለ እሚቀርቡ ሃሣቦች፤ ኢትዮጵያ ሸብረክ ልትል አይገባም ባዮች ነን፤ በፍፁም። ጠያቂው አካል ህወሓትም ሆነች አጋሮቿ!

ህወሓት ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ኢትዮጵያዊዕነት የሆነ እማይለወጥ አቋም የአላት የዕብድ ፖለቲከኞች ስብስብ ናት። የ ህወሓት የ ዕሩቅ-ጊዜ ተልዕኮዋ፤ ነፃ እምትለውን የ የግልዋን ሃገር መመሥረት ነው። በ ኢትዮጵያ ምድር ላይ! ከሞኝ-ደጅ ሞፈር ይቆረጣል እንዲል የሃገራችን ሰው። ህወሓት፤ እንወክለውአለን የእምትለው የትግራይ ሕዝብ ተወካይ አልነበረችም፣ እይደለችምም። ህወሓት፤ ጄኖሳይድ የፈፀመች እየፈፀመች የአለች፣ ሃገር የአፈረሰች እና በ ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጦርዕነት እየአካሄደች የአለች፤ በየትኛውም መመዘኛ ከምድረ-ገፅ ልትጠፉ እሚገባት ሃጢያተኛ ወንጀለኛ ድርጅት ናት።

የ ድልን ቀን — ቀረብ ለማድረግ፤ የፌደራል መንግሥቱ፤ በ ሙሉ-ልብ፣ በቀናዕነት እና በከፍተኛ ቆራጥዕነት፤ በሁለት ዳይሜንሽን'ስ ፍልሚያውን እጅጉን የበለጠ አጠናክሮ ተግባርዓዊ ሊያደርግ የግድ ነው። ዳይሜንሽን አንድ — የ ስነልቦና። ዳይሜንሽን ሁለት — የ ውትድርና።

ዳይሜንሽን አንድ፤

የ ስነልቦናውን ፍልሚያም ሆነ ግጥሚያ ለማሳለጥ፤ ዕልቂቱን ጉልህ በሆነ መልኩ እሚቀንሱ ብቻ ሳይሆን — ምንአልባትም ሊያቆሙት ይችላሉ እምንላቸው፤ አንድ ሁለት መሠረትዓዊ ጥያቄዎች የግድ መልስ ማግኘት ይኖርባቸው አለ።

<u>መሠረትዓዊ ጥያቄ አንድ፡-</u> የመከላከያ ሠራዊቱም ሆነ አጋዥ ኃይላት፤ በ ጦር ግንባር እሚያውለበልቡት ሰንደቅ-ዓላማችን — የ ህወሓት ኮከብ የሌለበት፤ ታሪክዓዊው [አረንጓዴ ቢጫ ቀይ] የ ኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዓላማ ይሁን።

ያ-ብቻውን የ ህወሓት ቅስም በቅፅበት ይሰበር ዘንድ በቂ ጉልበት አለው።

<u>መሠረትዓዊ ጥያቄ ሁለት፡-</u> አሸባሪዎችን እምአያካትት ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ጉባኤ ለማካሄድ፤ ብሎም ወደ [ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ምሥረታ ለማምራት፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ህገ-መንግሥት ለመቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ለመመሥረት] እሚያስችል ሂደት መጀመሩን እሚያበስር አዋጅ ይፅደቅ — ሳይውል ሳያድርም ወደ ተግባር እንግባ።

መሠረትዓዊ ጥያቄ አንድ እና መሠረትዓዊ ጥያቄ ሁለት፤ ፈጣን መልስ ከአገኙ — ህወሓት ጨርቋን ጥላ እንድታብድ እና አጋሮቿ የውጪ ሃገራት ድርጅቶችም ሆኑ መንግሥታት፤ ለቀብር ቪዛ ለመጠየቅ ድፍረቱ ባይኖራቸውም፤ በ እየአሉበት ሃዘን መቀመጣቸው ግና — አይቀሬ ነው።

ዳይሜንሽን ሁለት፤

የ ውትድርናውን ፍልሚያ እና ግጥሚያ፤ በሙሉ-ልብ እንዲተገበር ማድረግ እና የውስጥ ሰርጎ-ገቦችን በማጥራት፤ የመከላከያ ሠራዊቱንም ሆነ አጋዥ ኃይላትን በማቀናጀት ንፁህ ኢትዮጵያዊ የመከላከያ ሠራዊት መፍጠር የግድ ነው። ዛሬ ያ — አለ ብሎ ማሰብ፤ ትልቅ ስህተት ነው። አሁንም ቢሆን ዕርማት ሊደረግባቸው እሚያስፈልጉ፤ “ስህተት” በእሚል ሽፋን እሚድበሰበሱ የጦር ወንጀሎች፤ በአስቸኳይ ለፍርድ ሊቀርቡ ይገባል።

አዎን፤ ጦርዕነቱ መካሄድ የአለበት በ ሃገሪቷ መከላከያ ሠራዊት እንጂ፤ በ ክልል ልዩ ኃይልም ሆነ ሚሊሽያ መሆን የለበትም። ይ-ህ እንዲሆን መፍቀድም ሆነ እንዲቀጥል ማድረግ፤ ቶሎ መታረም የአለበት ጉዳይ ነው። በ ፌደራል መንግሥት በኩል እሚሰለፈው ሠራዊት፤ ድጋፍ ወይም አጠናካሪ ኃይል ከፈለገ፤ ግልፅ በሆነ አዋጅ እና መመሪያ ከመላዋ ኢትዮጵያ የተውጣጣ ማጠናከሪያ አጋዥ ኃይል ሊቀርብለት ይገባል።

ወደ ዘጠኝ አስር ወራት ገደማ እየአስቆጠረ የአለው ጦርዕነት፤ እንደ እኛ ቢሆን ኖሮ፤ ሊደረግ እሚገባው ነበረምም ነውምም ብለን ዐንዐምንም። ይ-ህ አባባል ግና ከምንም በላይ — [ክሊሼ] ሆኖ እየተሰማን ነው።

ኦፍ-ኮርስ፤ ማን ጦርዕነትን ይፈልጋል! ገፍቶ ከመጣ እና የግድ ከሆነ ግና፤ እንዳመጣጡ ማስተናገድ ላይ – እንደገና ዕንዳይከሰት መደረጉ ላይ፤ አንዳችም ስህተት ሊፈጠር አይገባም!

ያ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ እንዲህ ለመራዘሙ እና ላስከተለው የህይወትም፣ የንብረትም ሆነ የታሪክ ጥፋት — አንዳችም አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ፤ መቻል አለበት ብለን ዐንዐምንም።

የ ተስፋችን ተስፋዎች

እንደ ሕዝብም እንደ ሃገርም፤ ብዙ አላስፈላጊ ገጠመኞችን እያስተናገድን በመሆኑ፤ ተስፋችን አልፎ አልፎ እንከን እየገጠመው ቢመጣ ሊፈረድብን አይገባም። ያ-ም ሆኖ ግና፤ ጨርሰን — አ-ይ የራሱ ጉዳይ ለማለት የቃጣን ጊዜ ኖሮ አያውቅም፤ ይኖራል ብለንም ዐንዐምንም።

ህወሓት፤ “ዱቄት” ሆነች ከተባለ በኋላ፤ [ምክንያቱን (ጊዜ) እንዲነግረን ትተን] ትግራይ ተለቆላት፣ የ ዐማራ እና የ አፋር ክልሎችን ዘልቃ በመግባት፤ ሕዝብ ላይ ዕልቂት ለማካሄድ እሚያሳችላት ቁመና ተጎናፅፋ ስንአያት የመቆጣታችንን ያህል፤ ጀግናው የ ዐማራ እና የ አፋር ሕዝብ እንደአመጣጥዋ እያስተናገድዋት መሆኑን በመረዳታችን — ኩራትአችን ከምንጊዜውም በላይ ገዝፏል፤ ተስፋችን ለምልሟል!

ጦርዕነቱ — በ ዐማራ፣ በ አፋር ሕዝብ እና በ ትግራይ ሕዝብ መካከል እሚደረግ እንዲሆን በመደረጉ፤ ከበስተጀርባው ከባድ ሴራ ይኖር ይሆን ብለን በመጠርጠር፤ የተናደድነውን ያህል — የኦሮሞ፣ የሲዳማ እና የሶማሌ ልጆች [የ አልሰማንአቸው ሌሎች ወገኖችአችን እንዳሉም በፍፁም አንጠራጠርም] ኢትዮጵያዊዕነትን አስቀድመው አክብረው ፈቅደው፤ ከ ዐማራ እና ከ አፋር ወገናቸው ጎን በመቆም፤ የ 27-ዓመታት ሰቆቃዋን ልትአራዝምብን ከአልሆነላትም፤ ኢትዮጵያን ልታፈርስብን ለመጣች ህወሓት ለእምትባል አጋንንት አንንበረከክም ብለው አንድዕነትአቸውን ለማሳየት መዝመትአቸው — ልባችንን አሙቆታል! [ኤ ፍሬንድ ኢን ኒድ — ኢዝ ኤ ፍሬንድ ኢን ዲድ] ይላሉ እዚህ እኛ አካባቢ የአሉ ሰዎች።

አዎን፤ የነገሮችን በጎ ጎን ማጉላት ሳይሻል አይቀርም ብለን ነው እንጂ — የ እኛ ምርጫ፤ ጦርዕነቱ በ የክልል ልዩ ኃይሎች ሳይሆን፤ በ ተቀናጀ አንድ የ ኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት እንዲመራ ነው።

ሁለንተናዊ ጥቃት እየደረሰ የአለባት ኢትዮጵያ እና አላልቅ የአለ ሰቆቃን እየተቀበለ የአለው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የ ውጪ ሃገራት ድርጅቶች እና መንግሥታት በጠላትነት ለመቆም ፈልገው እና መርጠው ሲዶልቱብን እና ሲያጠቁን መስማት ማየቱ ሳያንሰን — በተደጋጋሚ የበሉበትን ወጪት ሰባሪ ሰርጎ ገብ መሠሪዎች እሚፈፅሙብንን ወንጀሎች እየአሰብን፤ በ ቁጭት ብንእንገበገብም ቅሉ፤ የ ዖሎምፒክ ጀግናችን፤ በ ዓለም-አቀፍ መድረክ ላይ አሸናፊ በመሆን፤ ቀጥ ብለን እንድንራመድ ጉልበት ሲሆነን ማየት — ተስፋችንን አግዝፎታል! እንኳን ደስ ያለህ፤ እንኳን ደስ ያለን ብለናል።

እንደ ማጠቃለያ

የ ፖለቲካው ነውጥ መልክ እየያዘ መጥቷል። ህወሓት በገዛ ወንጀልዋ ከኢትዮጵያ የ ፖለቲካ አውድ እራሷን ታሪክ አድርጋ፤ ሜዳውን በቃሬዛ ላይ ሆና እየለቀቀች ነው። መውጫዋ ላይ፤

የአልታሰበ አደጋ ልታደርስ ትችል ይሆናል እና — መጠንቀቅ ግና፤ የግድ ነው።

ህወሓት የፈፀመችአቸውም ሆነ እየፈፀመችአቸው የአሉት ወንጀሎች፤ ኢትዮጵያን የማፈራረስ የዕሩቅ ጊዜ ተልዕኰዋን ዕውን ለማድረግ ይሁን እንጂ — ትኩረትዋ ሁሉ፤ መረማመጃዋ ልታደርገው የተማማለችበት — የ ዐማራ ሕዝብ ላይ መሆኑ፤ ሳይታለም የተፈታ ነው።

እናም — ዐማራ ሆይ! እስከዛሬ እራስህን አለማዘጋጀትህ፤ ከፉኛ ለመጎዳትህ ምክንያት መሆኑ ዕሙን ነው። ሆኖም — ዛሬ የአለህበት ደረጃ ግና አኩሪ እና ተስፋ ሰጪ ነው። ትግሉ ረዥም እና ፈታኝ መሆኑን አትዘንጋ። ዛሬ የተፈጠሩትን ሁለንተናዊ አግባብ-ነገሮች በአሚገባ አጋናዝበህ፤ ህልውናህን ለመታደግ እሚያስችል፤ ፍትህ አጎናፃፊ ኃይል የመፍጠር ታሪካዊ ግዴታ ተጥሎብሃል እና ነቅተህ ተደራጅተህ በቆራጥዕነት ታገል። ቀን እስከእሚያልፍ ድረስ፤ ከ እራስህ በስተቀር — ሌላ ማንንም አትመን። ማንንም! ማዮፒክ በሆነ አመለካከት ላለመዘናጋትም ሆነ ላለመሸነፍ ተዘጋጅ። ቀዳሚ ሃላፊዕነትህ የ ዐማራን ሕዝብ መታደግ ነው። ነገሮች አመቺ ሆነው ሲገኙ፤ ኢትዮጵያን ለመታደግ ሊኖርህ እሚችለው አስተዋፅዖ ግዙፍ ነው እና — ከሌላ ኢትዮጵያዊ ወገንህ ጋር አብረህ በመሆን፤ ኢትዮጵያን ለመታደግ ተዘጋጅ።

ትክክል። ህወሓት አረመኔ ድርጅት ናት። ከምድረ-ገፅ እንድትጠፋ [አይዲዮሎጂክሊ ማለትአችን ነው] እሚደረገው ርብርቦሽ'ም — ፍትህዓዊ ነው። ያ-ግና፤ የ ህወሓትን ኮከብ እያውለበለብን እና አንቀጥፅ 39-ኝን'ም ሆነ መሰል አንቀፆችን የአካተተውን ህገ-መንግሥት ተብዬን እና የጎሣ-ፌደራሊዝምን ተግባራዊ እያደረግን ሊሆን አይችልም — በፍፁም! እናም፤ ታሪካዓዊው ሰንደቅ-ዓላማችን ይመለስልን። ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት ይኖረን ዘንድ፤ ሂደቱ በአስቸኳይ ይጀመር። በ እየ ክልሉ "ልዩ ኃይል" በ እሚል ስያሜ የተፈጠሩት አደረጃጀቶች — ሙሉ በሙሉ ታጥፈው እንዲጠፉ ይደረግ። አግባብ በአለው መልኩ ከመደበኛው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር [መርጅ] እሚደረጉበት ስርዐት ይቀመር። ለ እሚቀሩት፤ የስራ መስክ ይፈጠርላቸው።

የዛሬ ሦስት ዓመት፤ ይህ-እንን ተግባርዓዊ በ አለማድረግአችን፤ ዛሬ የገባንበት ዐረንቋ ውስጥ ልንዘፈቅ በቅተን አለ። ልብ እንበል ጎበዝ — ዛሬም መሠረትዓዊ ቴራፒውቲክ ሞዳሊቲ የአልነውን ተግባርዓዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ከአልሆንን — ነገ፤ እንደ ሕዝብም እንደ ሃገርም እራስአችንን ከዛሬው እጅጉን የከፋ፤ አዎ – እጅጉን የመረረ ዐረንቋ ውስጥ እንደ እምንአገኘው፤ አንጠራጠርም!

የ ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ጉባኤውን ሂደት ለመጀመር አሁን በ ስልጣን ላይ የአለው የመንግሥት አካል ተነሳሽዕነቱን ይውሰድ — በ ቅንዕነት እና በ ቆራጥዕነት። የጉባኤው ተሳታፊዎች፤ በ ኢትዮጵያ ሉዐላዊዕነት እና በ ታሪካዓዊ ሰንደቅ-ዓላማችን፤ በምንም መልኩ ድርድር እሚባል ነገር እንደማይፈቀድ ዐምነው እና ፈቅደው እሚካተቱ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ይሁኑ። በሽብርተኛዕነት የተፈረጁትን ማካተት የለበትም።

ይህ ከሆነ በኋላ፤ ተሳታፊ የእሚሆኑትን [ስቴክሆልደር'ስ] ግለሰቦችንም ሆኑ ድርጅቶችን ዝርዝር ኮምፓይል እሚያደርግ፤ አንድ አድሃክ ከሚቲ ይዋቀር። ተሳታፊዎች ትራንስፓረንት በሆነ መልኩ ከተመረጡ በኋላ፤ ጉባኤው ይጠራ ይጀመር። ጉባኤው ሲጀመር አድሃክ ከሚቲው ዲዞልቭ ይደረግ።

ጉባኤው ስብሰባውን ሲጀምር፤ ተሳታፊዎች — በመሠረትዓዊው ጉዳይ ላይ አምነው ፈቅደው የተሰባሰቡ አካልዐት በመሆናቸው፤ ቀዳሚ ስራቸው [የአለምንም እንቅፋት] በጉባኤው እሚስተናገዱ አጀንዳ አይተምስ እና የ አካሄድ ስነምብግባር ላይ ያተኮረ ይሁን። እሚመረጡ አስተባባሪ ከሚቲዎች ይኖራሉ። ከእዚያ በኋላ በተከተታይ ተፈፃሚ እሚሆኑት ስራዎች ሁሉ፤ በጋራ በስምምነት እና ትራንስፓረንት በሆነ መልኩ ይስተናገዱ። ውጤቱም፤ [ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት] በማዋቀር ይጠናቀቅ። እሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት — ሃገር የመምራት ሃላፊዕነትን ከመወጣት ጎን ለጎን፤ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት በመቅረፅ፣ ትራንስፓረንት የሆነ የ ሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ በማድረግ [ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት] በመመሥረት እራሱን ያክስም። ሽብርተኞች፤ ከ እሚመሠረተው የ ኢትዮጵያ ሕዝብዓዊ መንግሥት ጋር እንዲነጋገሩ፤ ሁኔታዎች ይመቻቹላቸው።

በመጨረሻም — አዳራሽ፤ በ ውጪ ሃገራት ሰዎች እሚቦካ እሚጋገር የ "መንግሥት አካል" ተፈጥሮ፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ እንዲጫንበት አትፈልግም። ናት ኧጌን!

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንገናኝ –

# ዕንቁ....ጣጣሽ!

መስከረም ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ‖ ሴፕቴምበር 2021

**አዳራሽ** – *የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክርቤት፤ የ ኢትዮጵያን የወቅትኡ ሁለዕንተንዓዊ ነውጥ በተመለከተ: በቅርቡ መሰብሰቡ መነጋገሩ ይታወቃል። የተሰሙት ንግግሮች፤ በአንድ በኩል – አንድ አንድ ሃገራት፤ ራስአቸውን በጠላትዕነት የፈርጁበት እና በማጣጣር ላይ ለአለችው ህወሓት ጉልበት ይሆናት ዘንድ: ከዕውነት የራቁ መሆንአቸውን ለዓለም ፍንትው አድርገው የአሳዩበት ዲስኩሮቻቸውን አስደምጠውናል። በሌላ በኩል – ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን፤ ለኢትዮጵያ ሉዐልዓዊዕነት፣ ለ ጀግናው የ ኢትዮጵያ ሕዝብ የአላቸውን ፍቅር እና ለታሪክዓዊው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ-ዓላማችን የአላቸውን ግዙፍ ከበሬታ: ልብአቸውን ከፍተው የቀረቡን ሃገራት: ጉዳዩን በቀናዕነት እና በ ዕውነትኛዕነት አስተናግደው: አስፈላጊውን ድጋፍ እና ትብብር ለማድረግ ከኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን እንደእሚቆሙ በንግግሮችአቸው አረጋግጠውልናል። ኢትዮጵያም – ሉዐልዓዊዕነትዋን እና የ ሕዝብዋን አንድዕነት ለማስከበር፤ ሌሎች "ነፃ-አውጪ" ተብዬ ወንበዴዎችም ጭምር ትምህርት ሊሆንአቸው በእሚችል መልኩ: ዕብሪትኛዋን ህወሓት እንደ አመጣጥዋ ለማስተናገድ እና ኢትዮጵያ ለአንድዕነትዋም የአላትን ቁርጠኛ አቋዋም: ፈርጠም ብላ አስገንዝባለች። ስብሰባው በኢትዮጵያ አሸናፊዕነት እንደተጠናቀቀም መገመት አያዳግትም። ልብ ዕንበል ጎበዝ: አዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ፤ ይህዕንን የአሸናፊዕነት መንፈስ: በቅርቡ በተደረገው ምርጫ መሰል ነገር "በአገኘው" ፎው-ሌጂትመሲ ሳቢያ፤ ለእርሱ የተሰጠ [ቮት ኦፍ ካንፊደንስ] አድርጐ በመውሰድ: እንደ-መመፃደቅ እንዳይቃጣው በጥብቅ ማስገንዘብ እንወድ አለን። ከጐንአችን ለመቆም የወሰኑት ሃገራትም ቢሆኑ፤ ህወሓት መራሹ ኢህአዴግም ሆነ አዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ: ኢትዮጵያን እንዴት ወደ መቀመቅ እንደከተትዋት በእሚገባ ይረዳሉ። በፍጥነት ዕርምት ከአልተደረገም ገና የመረረ ችግር እንደእሚገጥመንም ከመጠቆም አልተቆጠቡም! እናም፤ አዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ: ለ ወዳጅ ሃገራቱ እና ይህዕንን ዓይነት አለኝታዕነትን ለማፍራት ምክንያት ለሆነው ከዘመን-ዘመን እየተሸጋገረ ለዘለቀው ንፁህ የ ኢትዮጵያዊዕነት [መለኮትዓዊ ሕዝብዓዊ] መንፈስ – በጨዋ ደንብ ተገቢውን ምስጋና ማቅረብ ይኖርበታል። ለ ኢትዮጵያዊው – እንአመሰግን አለን የእሚል [<u>የሸንገላ</u>] ቃል በመወርወር እና ለ ወዳጅ ሃገራት ደሞ – በፈረንጅኛ የ ታንክ-ዩ ኖት በመላክ ሊሆን አይገባም። አዎን፤ ምስጋናው መቅረብ የአለበት: ስልጡን በሆነ እና ትርጉም በአለው መልኩ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እና መረጋጋትን ለማስፈን ይቻል ዘንድ፤ የጎሣ-ፖለቲካን በህግ በመገደብ፣ በ ቋንቋ እና በ ጎጥ ላይ የተመሠረተውን ኤትኒክ ፌደራሊዝም በማፈራረስ እና ስር-ነቀል የፖለቲካ ለውጥ በማምጣት – ማለትአችን ነው። ማለት – የ ኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዓላማ ወደ የ ክብር ቦታው መመለስ። ገንጣይዎችን እምአያካትት፤ ግና [እስከዛሬ የመሳተፍ ዕድሉ የ አልገጠማቸውን፤ በውጪ ሃገር እሚገኙትን ሁሉ ጨምሮ] ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ጉባኤ ማካሄድ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ማዋቀር፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ህገ-መንግሥት መቅረፅ እና ትራንስፓረንት የሆነ የሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ ማካሄድ። በመጨረሻም፤ [ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት] መመስረት። እነእኚያ እና እነእኚያ <u>በቅንዕነት</u> ተግባርዐዊ ሲሆኑ ብቻ ነው: ምስጋናውም ሆነ ወዳጅዕነትአችን ፍሬዓማ እና ትርጉም የአለአቸው እሚሆኑት። ለ ኢትዮጵያ – እንደ ሉዐልዓዊት ሃገር እና ለ ኢትዮጵያዊያን – እንደ አንድ ህብር ሕዝብ፤ ለ የገባንበት የዕልቂት አዙሪት ፍቱን-መድሃኒቱ: ኤትኒክ-ፌደራሊዝሙን — ከምድረ-ገፅ ማጥፋት ብቻ ነው!*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

በ ፕላኔት ምድር ላይ ከአሉት ሃገርዐት፤ ቀደምት የሆነችው: ዕንቁ ሃገርአችን ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ አንድ ዕንቁ ህብር ሕዝብ፡ ደግኡንም ክፉውንም ለ ብዙ ሺህ ዓመታት እየአስተናገደ ዛሬ የአለበት ደርሷል። ዘመን አልፎ ዘመን መተካቱ የተፈጥሮ ህግ ስለሆነም፤ ይሄው እና እንደ ኢትዮጵያዊያን የዘመን አቆጣጠር ፪ሺ፲፫ ዓ.ም'ን ለታሪክ አስቀምጠን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም'ን — አዲስ ዓመት ብለን ለመቀበል፤ ዋዜማው ላይ ደርሰን አለ።

እናም፤ ዕብድ ፖለቲከኞች እየሰሯቸው በአሉት ወንጀሎች ሳቢያ፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተጎዱትን እና በመጎዳት ላይ የአሉትን ወገንዎችአችንን፡ አመቺ በሆኑ መንገዶች ሁሉ፡ ከልብ እየአሰብን እና እሚቻለውን ሁሉ ማድረጉን ስአንእዘነጋ — ለ ወድ የ ኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ፤ ዕንቁጣጣሽ! እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረን፡ ማለት እንወድ አለን። ቀጥለንም እንግዲህ፤ በሰሞነኛ ጉዳዮች ዙሪያ በ ማውጠንጠን፡ እንደ ወትሮአችን የ እምንዕለውን ለማለት፡ ከፊትአችሁ ቀርበናል።

*<u>መልዕክት ለ አዳራሽዓዊያን</u> — እንደአስተዋልአችሁት፣ የ አዳራሽ ጦማር እምትወጣበት ዑደት፡ ከ የተለመደው የ አውሮጳዊያን የወርዐት መጀመሪያ ቀንዐት፡ ወደ የ ኢትዮጵያዊያን የወርዐት መጀመሪያ ቀንዐት እንዲቀየር፤ አድርገን አለ።*

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

ሰሞነኛ ጉዳይዎችአችን፤ በጦርዕነት ዙሪያ ከማጠንጠን መላቀቅ አልቻሉም። እንደ-ሃገርም እንደ-ሕዝብም ቀደምትዕነትአችንን ስንአወጣ ስንአወርድ፤ ፈርጀ-ብዙ በሆኑ መስከዎች የመሪዕነትኡን ቦታ ይዘን መገኘት ሲገባን፡ በአንፃሩ እርስ-በ-እርስአችን እንደ አውሬ እየተባላን በመገኘትአችን — እጅጉን አዝነን አለ፣ አፍረን አለ፣ ተንገብግበን አለ።

ወደ ዓመት ገደማ እየሆነው የመጣው ጦርዕነት፤ ከቀን ወደ ቀን መያዥያ መጨበጫያ እየአጣ ነው። አዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ፡ ትግራይን ለወንበዴ አስረክቦ በመፈርጠጥ ጦርዕነትኡን ወደ ዐማራ እና አፋር ክልሎች ከ አዛመተ በኋላ — "ደጀን" ብሎ የጠራውን [የሸነገለውን ማለት ነው ትክክል እሚሆንኸው] ንፁህ የ ዐማራ እና የ አፋር ሕዝብ፤ በ ህወሓት ታንክ እና መድፍ የአለማቋረጥ እየአስደበደበ ነው። "ስልትዓዊ ማፈግፈግ" በ እሚል መሠሪ ቧልት፤ የ ዐማራ እና የአፋር ከተማዎችን መንደሮችን አኬልዳማ አድርጓቸዋል። የ ዐማራ እና የ አፋር ተወላጆች ታርደዋል ተጨፍጭፈዋል ተዘርፈዋል ተደፍረዋል ተሰደዋል፤ የ እርሻ ወቅትዐቸው በጦርዕነት ተስተጓጉሏል። አዎን፤ የ ዐማራ እና የ አፋር ሕዝብ፡ መቆሚያ መቀመጫ አጥቶ አለ። አራት-ኪሎ መሻጊው አዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ፤ "ደጀን" የአለውን የ ዐማራ ሕዝብ፡

እንድአይደራጅ እንቅፋት ሆኖ እና መሣሪያ እንድአይታጠቅ ከልክሎ፡ [ባዶ እጁን] – እስከ አፍንጫው ለታጠቀ የ ህወሓት ወንበዴ አሳልፎ በመስጠት ሆነ ብሎ አስበልቶታል፡ እየአስበላውም ነው!

እንዲያው ቢቸግርኝን ትኩረትአችንን ወደ ህወሓት አዞርን እንጂ፤ የኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ጠላትዖች — ህወሓትም፣ ኦነግም፣ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ የጎሣ ድርጅቶች ስብስብም እና ሌሎች ወንበዴዎችም ጭምር መሆንአቸውን አልአጣነውም። ሁሉም፤ በዕምነትዖችአቸው፣ በዕቅድዖችአቸው እና በግብዖችአቸው፡ አይለያዩም። በተለይ ህወሓት ኦነግ እና ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ የጎሣ ድርጅቶች ስብስብን በግልፅ እሚያቢቅሳቸው ጉዳይ ቢኖር፤ የ አራት-ኪሎ ቤተመንግሥት ብቻ ነው። አዎን፤ ሁሉም ስግብግብ የስልጣን ጥማትኞች ናቸው። የ ዐማራ መጥፋት ግብአቸው ነው። ሁሉም ስልጣን እስከአልያዙ ድረስ ኢትዮጵያ ብትፈራርስ፤ ደንታ የላቸውም። ሁሉም ለ[ሰው] ህይወት ከበሬታ የላቸውም። ሁሉም በነውጥ እና በዕልቂት እሚፈነድቁ፤ አውሬዎች ናቸው።

እንደ ኢትዮጵያዊያን፤ ለ እንደእዚያ የአለ መራር ዕውነታ የተጋለጥን በመሆንአችን ነው፡ እሚመጥን ርብርቦሽ በማድረግ ህልውናችንን እንእታደግ ዘንድ የግድ መሆኑን፡ አበክረን ደጋግመን ማስገንዘብ የእምንመርጠው። ከአብዛኛዎችአችሁ የተሰወረ ነው ብለን ሳይሆን፤ ፈርጠም የአለ ስራ እየሰራን፡ አልመስልአችሁ ስለ አለን!

እየተካሄደ ያለው ሁለዕንተንዓዊ ነውጥ እና እየተካሄደ ያለው ጦርዕነት፤ በቅርቡ ይጠናቀቃል የ እሚል ቅዠት ውስጥ እንድአንገባ እና ለፈታኝ ለረዥም ቀውስ ራስአችንን ሁለገብ በሆነ መልኩ አደራጅተን፡ ከምንጊዜውም በላይ በቆራጥዕነት ለመታገል መዘጋጀት የግድ መሆኑን መዘንጋት እንደእማይገባን አበክረን ለማስገንዘብ ብለን! አማራጩ መጥፋት ሊሆን ይችላል እና።

ፍትህ-አንኊናፃፊ ኃይል

የ ኢትዮጵያ የፖለቲካ በሽታ ፈውስ ይአገኝ ዘንድ፤ ፈርጀ-ብዙ፡ ፈርጠም የአለ ፍትህ-አንናፃፊ የ ኃይል አደረጃጀትን ይጠይቃል። ይህ-እንን ፍትህ-አጐናፃፊ ኃይል ዕውን እንዲሆን ማድረግ እሚቻልበትን መንገድ፤ የግድ ልእንአውቅበትም ይገባል። ፍትህ-አጐናፃፊ ኃይል ስዕንል፤ ሕዝብዓዊ መሠረት የአለው ኃይል ማለትአችን መሆንኡን ግልፅ እንዲሆንእም እንፈልግ አለን፡ አዎን – ለ አይቀሬው ሕዝብዓዊ ንቅናቄ፤ አስተማማኝ፣ አለኝታ እና ደጀን እምይሆን ኃይል!

ትክክል። አንድ ድርጅት ብቻ ሳይሆን፤ እንደ እየ አግባብ ነገሩ፡ በ መናበብ እና በ ቅንጅት መሥራት እሚችሉ ሕዝብዓዊ መሠረት የአላቸው፡ ፈርጠም የአሉ ኃይላት ሊኖሩን ይገባ አለ – እየአልን ነው።

አዎን፤ [ፍትህ] እምንዕለውም – በ ማንዕነትአቸው ምክንያት በእየ–ዕለቱ ለእሚጨፈጨፉ ንፁሃን ኢትዮጵያዊያን፣ በ ማንዕነትአቸው ምክንያት [መጤ] እየተባሉ በመንግሥት አካላት ጠንሳሽዕነት ተባባሪዕነት አቀነባባሪዕነት ተግባሪዕነት፤ በገዛ ቀዬአቸው በ ሠላም መኖር እንድአይችሉ፡ አዳጋች ለሆኑ ችግሮች እንድይጋለጡ በመደረግአቸው መቆሚያ መቀመጫ ለአጡ፣ የ ዐማራ ተወላጅዖች እና ለ ኢትዮጵያዊ የኅሊና የሐሣብ እና የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ነው።

ችግሩ እየገዘፈ በመጣባቸው አካባቢዎች፤ የ እዚህ ሕዝብዓዊ ኃይል ጥንሥስ መሆን እሚችሉ እንቅስቃሴዎች መጀመርአቸውን እየሰማን መሆኑ ይበል እምይአሰኝ ነው። ሊታቀፉ ሊደገፉ ሊበረታቱ ይገባል። ይህ-እንን አጋጣሚ በመጠቀምም፤ የሕዝብዓዊ ኃይል የምሥረታ ፍንጮችን ሲሰሙ፡ ብርክ እምይይዛቸውን የ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ ባለሥልጣንዐት ሽፋን-ሰጪ ሆዳም ፖለቲከኞች — አርፈው እንዲቀመጡ፣ አፍአቸውን እንዲዘጉ፣ በተለይም ከ ዐማራው ሕዝብ ጫንቃ ላይ እንዲወርዱ፣ እንዲያውም ዐማራው አጠገብ እንድአይደርሱ አምርረን ልእንመክርአቸው እንወዳለን።

ፍልሚያው

በ ፖለቲካችን ዲስኮርስ፡ [ካንሰር] የ እሚል ቃል መጠቀም ከጀምርን ከራርመናል። ትክክል። የ ኢትዮጵያ የፖለቲካ በሽታ፡ ካንሰር ነው [ሜታፎሪክሊ]። በጋራ የዘነጋንኸው ጉዳይ ቢኖር ግና፤ ይህ ካንሰር፡ ሎካሊ ከንፋይንድ የሆነ ሳይሆን፡ ሜታስታሳይዝ የአደረገ መሆኑን ነው። ማለት — አንድ መንደር ወይም አንድ ግዛት አካባቢ ብቻ የአለ ችግር ሳይሆን፡ በሠፊው በሃገሪትዋ ግዛትዖች ሁሉ ሲስተሚክሊ የተሰራጨ ነው፡ ማለት ነው። ማለት — እንዲህ ለአለ ሜታስታሳይዝ ለአደረገ "ካንሰር"፤ ሎካላይዝድ በሆነ ህክምና ብቻ ማዳን እንደእማይቻል በጋራ ልእንገነዘብ ይገባል። ያውም ሎካላይዝድ የሆነውንም "ህክምና" እንኳን በቅጡ ሳይሰጥ ይቅር እና! እንደገና ለማለት — ሜታስታሳይዝ የአደረጉትን ካንሰር ሴልስ ለማጥፋት እና ፈውስን በተቻለ መልኩ ዕውን ለማድረግ፤ በ አግባቡ የተቀመረ ፈርጀ-ብዙ የ ሜታስታቲክ ካንሰር ትሪትመንት ሞዳሊቲ፡ ተግባርዓዊ ሊደረገ የግድ — አዎን፡ የግድ ነው።

ትክክል። የእኛ የፖለቲካ በሽታ፤ የ ጎሣ-ፖለቲካ እና በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩዩ የ ኤትኒክ ፌደራሊዝም ነው። ህወሓት ቀዳማይ ላዕላይ የ በሽታው መንስኤ ጠንሳሽ ተግባሪ እና አዛማች ትሁን እንጂ፤ ሌሎች ግብዋን ሊአሳልጡላት እሚችሉ፡ መሠል ወንበዴዎችን አደራጅታ አጎልብታ፡ በ ኢትዮጵያ ግዛቶች ሁሉ ማሰራጨትዋ፡ ምንም ጥርጥር የለውም። ኦነግን እና ቤንሻንጉልም ሆነ ሌሎች ግዛቶችም ውስጥ እሚንቀሳቀሱትን፤ ነፃ-አውጪ ተብዬ፡ ደናቁርቶችን ማለትአችን ነው። እናም፤ የፖለቲካ በሽታችንን ለማከምም፡ ሁሉንም ወንበዴዎች ከንከረንትሊ ታርጌት ማድረግ የግድ ነ..........ው፡ ማለትአችን ነው።

የዐማራው ጄኖሳይድ በኦሮሚያ እና በቤንሻንጉል ክልሎች ብቻ ሳይሆን፤ የዐማራ ክልል ውስጥም፡ የ አለምንም ሃይ-ባይ እየተተገበረ እየተስፋፋ ነው። ይህ አውሬዕነት እንድይአከትም ሳይእደረግ፤ ከህወሓት ጋር እሚደረገው ፍልሚያ ብቻውን እምይአመጣው ረብ ይኖራል ማለት – ቧልት ነው።

አዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ፤ ለሦስት ዓመታት ያህል የ አለማሳለስ እየአሰለጠነ እምይአሰማራቸው፡ ደምወዝአቸውን ባንክ ዘርፈው እንዲወስዱ የፈቀደላቸው የኦነግ ጨፍጫፊዎች፡ በተለይ በዐማራው እና በኦርቶዶክስ አማኒያን ላይ እየፈፀሙት የአለው ጀኖሳይድ ብቻውን፡ እሚመለከታቸውን የመንግሥት አካልዐት ሲያል እምይአስገባቸው ነውር ሃጢያት እና ወንጀል መሆኑን፤ አምርረን ማስገንዘብ ዕንወድ አለን — ሰሚ ከአለ።

ለመሆኑ፤ የአዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ ባለሥልጣንዐት፡ ኦነግ እየፈፀማቸው የአሉትን ወንጀልዖች እና ዕልቂትዖች እየአዩ እያሰሙ እንዴት እህል ውሃ ይዋጥላቸዋል? እንዴትስ ዕንቅልፍ ይወስዳቸዋል? መቼስ ነው የአዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ ባለሥልጣንዐት በ እዚህ ወንጀልአቸው ተጠያቂ እምይሆኑት? ማንእስ ነው ይህእንን ጨክኖ ሊሆን እንዲችል እሚያስደርገው?!

ትኩረትአችን

አንድ ዕሙን ነገር አለ። ህወሓት ራስዋ በፈጠረችአቸው በተግባር በፈፀመችአቸው ቁጥር-ስፍር የሌላቸው ኢ-ሰውዓዊ፣ ፀረ-ሃይማኖት እና ሃገር አፍራሽ ነውርዖች፣ ሃጥያትዖች እና ወንጀልዖች ሳቢያ፡ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ዐውድ፡ እስከወዲያኛው ተሰናብታ አለች። ደጋግመን ደጋግመን ደጋግመን ማስገንዘብ ዕምንእገደደው ጉዳይ ግና፤ ህወሓት ላይ ብቻ የአጠነጠነ ትግል፡ የኢትዮጵያን ጠማማ ፖለቲካ፡ ማረቅ እምአይችል መሆኑን ነው።

ከ ህወሓት ጋር እየተደረገ የአለው ጦርዕነት መጠናቀቅ የአለበትም፡ በ [ድርድር] መሆን የለበትም። በፍፁም! የሸአቢያ እና የደርግ-መንግሥት ጦርዕነት የተጠናቀቀው በድርድር አይኮነን። የ ህወሓት መርአሹ ኢህአዴግ እና የደርግ-መንግሥት ጦርዕነት የተጠናቀቀው በድርድር አይኮነን። በአንዱ ወገን አሸናፊዕነት እንጂ! ዛሬ ልዩዕነትኡ፤ አሸናፊው ሌላኛው ወገን የመሆኑ ዕውነታ ብቻ ነው። እየአንድ-አንድዋን ስኴር-ሚትር የኢትዮጵያ ግዛት [ትግራይን ጭምር ማለትአችን ነው] ከ ዕብሪትኧኛ ነፃ-አውጪ ተብዬዎች፤ ፈልቅቀን በማውጣት፤ ሕዝቡ ወደ ሰላምዓዊ ህይወት እንድይመለስ ማስቻል፡ መንግሥት ተብዬው፡ ከምንም በላይ [የ ሙዝ ፎቶ ፌስቡክ ላይ ከመለጠፍም በላይ ማለትአችን ነው] ፕራዮሪቲ ሊሠጠው እሚገባ ግዴታው መሆኑን ሊረዳው ይገባል። እስከዛሬ ያ-እየተደረገ አለመሆኑን ለማሳየት፤ ምስክር ፍለጋ መዳከር እንደእማያስፈልገን፡ ቢያንስ እየአለቀ የአለው የትግራይ የዐማራ እና የአፋር ወገንአችን፤ ማስረጃችን ነው።

ከ ህወሓት ጋር እየተደረገ የአለው ጦርዕነት በአስቸኳይ ይጠናቀቅ ዘንድ — ህወሓት፤ ትዕቢትዋን እና ጦር መስበቋን አቁማ፣ ትጥቅ ፈትታ፣ በህግ እሚፈለጉ [ነውርኧኛ ሃጥያትኧኛ ወንጀልኧኛ] መሪዎችዋ እጅአቸውን ለ ህግ አካልዐት ሰጥተው፣ ቀሪ የ ህወሓት ጀሌዎች እና ቡችሎች፤ ዳግመኛ ብረት አጠገብ እንደእማይደርሱ፣ ሃገር አፍራሽ በሆነ ማንአቸውም ተግባር እንደእማይሰማሩ እና ከፋም ለማም በ ኢትዮጵያዊዕነት ምህዳር ስር በአንድዕነት ለመኖር ቃለ-መሃላ ፈፅመው፤ ወደ ሰላምዓዊ ህይወት እሚመለሱበት አመቺ ሁኔታዎች ሊፈጠሩላቸው ይገባል። ያ-ከሆነ በኋላ፤ የትግራይ ሕዝብ የማንም ጫና ሳይኖርበት፡ ተወካይዖቹን አግባብ በአለው መልኩ በማዘጋጀት፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዐውድ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ በመያዝ፡ ሰላምዓዊ ህይወት መኖር መቻል አለበት።

ጎበዝ፤ ዛሬ እያስተናገድንአቸው የ አሉት ማህበረሰብዓዊ ነውጥዖች እና ቀውስዖች ብቻ ሳይሆኑ፡ ወንድማማች እህትማማች ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ — የነገው የ ከነገወዲያው ህይወትም ጭምር እጅጉን ሊያሳስበው ይገባል። የ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣዋ እጅጉን ሊያሳስበው እና እንቅልፍ ሊነሳውም ይገባል።

ያ-እንን ማድረግ ብዙ ርቀት ሊጓዝ እሚችል ጠቀሜታ እንደአለው ዕምነትአችን ግዙፍ ነው። እኛ፤ በ የትእኛውም ግዛት የአለው የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በ በሽተኛ ፖለቲከኞች ቆስቋሽዕነት በተፈጠሩ ነውጥዖች ሳቢያ ተኮራርፎ [ቁርሾ ፈጥሮ በሉት ከፈለጋችሁ] እንደ ወትሮው ወደ አብሮዕነት፣ ወደ ሰላምዓዊ ህይወት ለመመለስ ችግር ይኖርበታል ብለን አንዐምንም። ይልቁን እስ፤ እኛን እሚያስጨንቀን — በሽተኛ ፖለቲከኞች ተመሳሳይ ከፋፋይ አጥፊ አፍራሽ ሁኔታዎችን እሚፈጥሩበት አጋጣሚ ዳግመኛ እንድአያገኙ፡ ጥብቅ ክትትል እና እርምጃ መውሰድ እንደእሚገባን ዐምንኧን መቀበልአችን ላይ ነው። አዎን፤ በህግ የተደነገገ ዜሮ ቶለራንስ ሊኖረን ይገባናል እየአልን ነው።

ዘለቂታዊ መፍትሄ ይሆናል ብልኧን እምንዐምንኧው፤ የ ጎሣ-ፖለቲካን፣ በቋንቋ እና ጎጥ ላይ የተመሠረተውን ኤትኒክ ፌደራሊዝምን እና በእዚያ ሳቢያ የተፈጠሩ ክልልዖችን፤ ማፍረስን እና በህግ መገደብን ነው። ዕመኑን፤ ሌላ አማራጭ የለም! ተገንጣይዖችን እምአያካት፡ <u>ሁሉን አቀፍ</u> ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ጉባኤ ማካሄድን፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ማዋቀርን፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ህገ-መንግሥት መቅረፅን እና ትራንስፓረንት የሆነ የ ሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ ማካሄድን፣ በመጨረሻም [ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት] መመስረትን ተግባርዓዊ አለማድረግ፤ እስከዛሬ ገጠሙን እምንልአቸውን መራራ ችግሮች፡ አጅጉን የበለጠ አባብሰን ልእንአስቀጥል —መርጠናል ማለት ነው። ያ-ም ጤናማዕነት አይደለም።

ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ጉባኤ ማካሄድን በተመለከተ አንድ ነገር እንደነገርንአችሁ እርግጠኞች መሆን እንፈልግ አለን። ህወሓት መራሹ ኢህአዴግም ሞክሮት አልተሳካለትም። በቀናዕነት ስለ አልአደረገው። እናም፤ መንግሥት ተብዬው ሆይ! “ሁሉን አቀፍ” ሲባል፤ [እስከዛሬ የመሳተፍ ዕድሉ የ አልገጠማቸውን እና በውጪ ሃገር እሚገኙትን ሁሉ ጨምሮ] ማለት ነው። ያ ከአልሆነ – ዕመንኧን፤ አንድአችም የእምትአቃልለው ችግር አይኖርም።

እንደ ማጠቃለያ

አዳራሽ፤ ምንጊዜም ቢሆን እንደ እምትዕለው — ለ የውስጥ ችግርዖችአችንን መፍትሄ ከአገኘንእላቸው፡ የውጪ ባላጋራዎችአችንን አደብ ማስገዛት አያቅትኧንም ብላ ትዐምን አለች። በቅርቡም፤ ያ ዕምነት በመጠኑም ቢሆን ጎልቶ የታየበትን ገጠመኝ አስተውለናል።

ማለት፤ በህዳሴ ግድብም ሆነ እየተካሄደ በአለው የውስጥአችን ጦርዕነት ሳቢያ፡ የውጪ ጫናው የውጪ ጣልቃ ገብዕነቱ ፈርጠም ብሎ መከራረሙ እንደ የተጠበቀ ሆኖ፤ ግድቡ የማንንም ይሁንታ እምአንጠይቅበት ተፈጥሮዓዊ መብታችን በመሆኑ እና የውስጥአችን ጦርዕነትም ፍትህዓዊ ጦርዕነት በመሆኑ፤ አርቆ አስተዋይኡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ጥርሱን ነክሶ፣ የሆዱን በሆዱ ይዞ፣ እጅ ለ እጅ ተያይዞ በአንድዕነት መቆሙ፤ የውጪ ጣልቃ-ገብነትኡን ምን ያህል አደብ እንደአስገዛልን እና የውጪ ጫናውንም ከትከሻችን ላይ በመጠኑም ቢሆን እንደአቀለለልን፡ አስተውለናል ማለትአችን ነው።

ኀበዝ፤ እንዲያ በማለትአችን፡ ብኹርታ ውስጥ መግባት አይኖርብንም። መሠረትዓዊ የውስጥ ችግርዖችአችን አሁንም አልተቀረፉም አልተነኩም። እንዲያውም ብሶባቸዋል። የውስጥ ችግርዖችአችንን ዛሬውኑ መቅረፍ ከአልቻልን፤ ያ የታየው የሕዝብ አንድዕነት ከመቅፅበት ተንኖ እንደእሚጠፋ ልእንጠራጠር አይገባም።

ያ-ኔ የመንግሥትን አካል አያድርገን! አዎን ያ-ኔ፤ ሕዝብ ከምን ጊዜውም በላይ በመንግሥት ላይ ይነሳል። ትንሽም ቢሆን ሽብረክ የአሉ የመሰሉት የውጪ ባላጋራዎችአችንም፤ አሁን የአደፈጡ ከመሰሉበት አጋጣሚ እንደገና በማንሰራራት ከምንጊዜውም በላይ በተቀናጀ በተደራጀ መልኩ፡ [ከ ሕዝብ ጎን የቆሙ መስለው] በስልጣን ላይ የአለውን የመንግሥት አካል እንዳይሆን እንዳይሆን እንደእሚያደርጉት ዕሙን ነው። የሰሞኑን የ ውጪ ባላጋራዎችአችንን ሽብረክ ማለት አትዩ። ቂመኞች ናቸው። የዛሬ “መሸነፍአቸውን” መቼም ቢሆን አይረሱትም። ሁኔታዎች የተመቻቹላቸው የመሰልአቸው ቀን፤ ከመበቀል ወደኋላ አይሉም። አዎን፤ ያ-ኔ የመንግሥትን አካል አያድርገን!

በሉ እንግዲህ፤ እንደ ያገባናል ባይ ወገን፡ እምንዕለውን በድጋሜ ብለን እንአብቃ። አንድ ቀን፤ ሰሚ [ልብ] እንአገኝ ይሆናል — በ እሚል!

እስከ ዛሬ የ አልሰማ ከአለ ይስማ፤ የ አልገባው ከአለም ይግባው። የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ መሠረትዓዊ ችግርዖችአችን፤ ህወሓትዓዊ ኦነግዓዊ እና ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግዓዊ፤ ፀረ-ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት፣ የጎሣ-ፖለቲካ እና ዕኩይኡ ፌደራሊዝም — በተጓዳኝም አልአባራ የአለው ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ፣ ጄኖሳይድ፣ ሃገርን የመውረር የማስወረር የመበዝበር፣ ሃገርን የማፍረስ የማስፈረስ፣ ከተማዎችአችንን ቅርስዖችአችንን የማውደም እና ኦሮሙማን የማንሰራፋት ዘመቻዎች ናቸው።

ህወሓት የፈጠረችው እና እየፈጠረች የአለችው አስአፋሪ ዘግናኝ [ሜስ] ለዘመንዐት እሚዘልቅ ነው። አዎን፤ ህወሓት እንደዛተችው፡ በዐማራ ንፁሃን ላይ በተደጋጋሚ ጄኖሳይድ ፈፅማለች። ከተማዎችን አፈራርሳለች። እንሥሳትን ሳይቀር ጨፍጭፋለች። ኦነግ እየአደረሰ የአለው ተመሳሳይ ዘግናኝ ጄኖሳይድም እየተሸፋፈነለት ነው – በመንግሥት አካላት!

ይህ ሁሉ ሆኖም ቢሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በሽተኛ ፖለቲከኞች የፈጠሩበትን ቁስል በፍጥነት አድርቆ፡ ወደ ቀድሞው የጋራ ህይወት መመለስ ይቸግረዋል ብለን አንሰጋም። በእዚህ በ አለፉት ሦስት-ዓመትዐት፤ ከ የኤሪትሪያ ወገንዖችአችን ጋር፡ እንደ አንድ ሕዝብ የ አሳየነው የቤተሰብዕነት ስሜት ተሃድሶ፡ ምስክርአችን ነው። ትክክል። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ የመኖር ችግር የለበትም። እየበጠበጡን የአሉት እና ችግር እየፈጠሩብን የአሉት — በሽተኛ ፖለቲከኞች ናቸው!

በተሻለ መልኩ፤ ወደ የቀድሞው ዓይነት፡ የ ኢትዮጵያዊዕነት የቤተሰብዕነት ስሜት ተሃድሶ በፍጥነት እና በዘላቂዕነት ለመመለስ ይቻለን ዘንድ፡ የ ጎሣ-ፖለቲካን እና ኤትኒክ ፌደራሊዝምን ማጥፋት፣ ከተገንጣዮች በስተቀር ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ መጥራት፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት ሌላ ምንም ሳይሆን፤ እንደ ሃገርም እንደ ሕዝብም ህልውናችንን ለመታደግ እምይአስችለን፡ ብቸኛው መድሃኒት እና ብቸኛው ፈውስ መሆኑን፤ ፅኑ ወገንዓዊ ዕምነትአችን ነው። በቅጥፈት፣ በሸንገላ እና በሸፍጥ — መገዛትአችን ያብቃ።

ኢትዮጵያ – ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እስከ እምንገናኝ –

# ጦርዕነት እና ሞራልቲ

ጥቅምት ፪ሺ፻፲ ዓ.ም ‖ ኦክቶበር 2021

**አዳራሽ** – ኢትዮጵያ፤ በቅርብሎ "ሃገርዓዊ" ምርጫ መሰል ነገር አካሂዳ አለች። ምርጫው፤ ፍትህዓዊ'ም ነፃ'ም ዲሚክረሲዓዊ'ም አልነበረም። ሆኖም፤ በ ምርጫ ቦርድ በኩል፡ አብላጫ በርጩማዎችን አሸንፏል የተባለለት ፓርቲ፡ እራስኡን በመንግሥትዕነት ሰይሞ፡ ለ 5-ዓመት ይዘልቃል ብሎ የአመነውን አዲስ የሥራ ዘመን ጀምሯል። የ እሚተዳደርበት ህገ-መንግሥት እና የ ኤትኒክ የፌደራል ስርዐቱ፤ ያ-ው ለ 30-ዓመትዐት ገደማ ህወሓት ትጠቀምበት የነበረው ነው። ምንም የተለወጠ ነገር የለም። ሁለት-ሦስት "ተፎካካሪ" ተብዬ ፖለቲከኞችን፤ ኢሴንሻሊ የ ሽፋን-ሰጪዕነት ሥራ እንዲሰሩለት እና ድርጅትዖችአቸውን ኢምፖተንት ለማድረግ ሲል ወደ ካቢኔው በመቀላቀል፡ መድብለ ፓርቲን ተግብሬ አለሁ ለማለት'ም እየቃጣው ነው። ስለ ሰላም እና መረጋጋት ዕጦት፣ ህወሓት እና ኦነግ በሃገሪትዋ ውስጥ እየአካሄዱት ስለአለው ኤትኒክ ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና ጀኖሳይድ የተነፈሰው ነገር የለም። ፓርላማው — አሁንም፤ ፀረ-ኢትዮጵያ፣ ዋሾ፣ ባለጌ እና ህወሓት'ን ናፋቂ በሆኑ ተመራጭ ተብዬዎች የተሞላ መሆንኡን፡ ገና በመጀመሪያ ቀን ስብሰባው ግልፅ አድርጎልን አለ። ይህ ዕውነትዐ እሚነግረን ነገር ቢኖር፤ ኢትዮጵያ ከመሠረትዓዊ ችግርዖችዋ እንደ እማትላቀቅ እና የ ዛሬ አንድ-ዓመት'ም ሆነ የዛሬ አምስት-ዓመት፡ እራስአችንን የከፋ መከራ ውስጥ እንደእምንአገኝ ነው። የውጪ ጣልቃ ገብዕነቱም ሆነ ጫናው፡ ተጠናክሮ መቀጠሉን'ም እየአየን እየሰማን ነው። ለ [ሰው]ዕንትአችን፣ ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ እና ለ ኢትዮጵያ ስዕንል፡ የውጪ ጣልቃ ገብዕነቱንም ሆነ ጫናውን፡ አጥብቀን እንአወግዝ አለን። ኢትዮጵያ ሉዐልዓዊት ሃገር ናት፣ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ'ም አኩሪ ታሪክ የአለው ትሁት እንግዳ-ተቀባይ አትንኩኝ-ባይ ቆራጥ ኩሩ ጀግና ሕዝብ ነው። በተፈጠረው የውጪ ጣልቃ ገብዕነትም ሆነ ጫና፡ ብዙም ይጨነቃል ብለን አንሰጋም — እንደእየአመጣጡ ያስተናግደዋል እንጂ! ሆኖም ግና፤ ኢትዮጵያ በ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብዓዊ የጋራ ህይወት ውስጥ የአላትን ሃላፊዕነትም ሆነ ግዴታ፡ በ አግባብኡ መወጣትዋን እርግጠኛ በመሆን፡ ሙሉ መብትዋን ለማስከበር ወደኋላ እንደእማትል ፈርጠም በአለ መልኩ ግልፅ ልታደርግ ይገባል። ጠላት አለማብዛት፡ ይረዳል። ለውሳኔዎችአችን ሁሉ፤ ዕውነትኛ ተጨባጭ እና በቂ ማስረጃ እስከያዝን ድረስ እና ነቅተን እስከጠበቅን ድረስ፡ አንድአችም አስጊ ጉዳይ ሊኖር አይችልም። አንድ ነገር ዕሙን መሆኑን ደግመን እንነገርአችሁ። የውስጥ ችግርዖቻችንን እስከአልፈታን ድረስ፤ የውጭ ጣልቃ ገብዕነቱም ሆነ ጫናው አይቆምም። እንዲያውም እየገዘፈ መሄዱ አይቀሬ ነው። እናም፤ መዐከልዓዊው መንግሥት፡ አገኘሁ በእሚለው ፎው-ሌጂትመሲ መመፃደቅ እንድአይቃጣው እና ስልጡን በሆነ እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ፡ እንደ [በሁሉም መስክ ስኬትአማ የአልሆነ የፖለቲካ ድርጅት] እራስኡን እንድይአከስም፡ አበክረን እንጠይቅ አለን። ልመና አይደለም፤ ግዴታ መሆኑን እየነገርንአችሁ ነው! የ ኢትዮጵያ ሕዝብም፤ ከገባበት ሰመመን ነቅቶ፡ ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ እና ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ — ሃገርን እና ሕዝብን ከጥፋት መታደግ፤ ግዴታው መሆኑን ማስገንዘብ እንወድ አለን። ማለት፤ የ ጎሣ-ፖለቲካን እና ኤትኒክ ፌደራሊዝምን በ ማጥፋት፣ ከተገንጣዮች በስተቀር ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ በ ማካሄድ [ጀግናዎቹ፤ የ ያ-ትውልድ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ክቡር መስዋዕትዕነት የከፈሉለት'ን] ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት በ ማቋቋም፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት በ መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት በ መመሥረት፡ ማለትአችን ነው። ትክክል፤ በቅጥፈት፣ በሸንገላ፣ በሸፍጥ፣ በዕብሪት እና በኢትዮጵያ ጠላትዖች መዝትአችን — ያብቃ!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

ጦርዕነትን እና ሞራልቲ'ን አጣምረው እሚዳስሱ መጣጥፍዖችን ብትእመለከቱ፤ [ጀስት ዋር ቲየሪ] የ እሚባል እሳቤ እንደ አለ፡ ሳትአስተዉሉ አትቀሩም ብለን ዕንአምን አለን።

*አዎን፤ በ አጠቃላይ — ጦርዕነትን እሚደግፍ ጤናማ ኀሊና የአለው ሰው ፈልጋችሁ አትአገኙም። አዳራሽ'ም፤ አይደለም በ የ እራስአችን ሰውዖች መሃከል ይቅር እና በ የትኛውም የ ዓለምአችን ክፍል እሚደረጉ ጦርዕነትዖችን አምርራ ትፀየፍ አለች።*

የቸገረው ነገር ግና፤ እንደ አለመታደል ሆኖ፡ የ[ሰው] ልጅ ቅራኔዎችን ለመፍታት በእሚል፡ ጉልበትን ኃይልን እና እንደ እየ ክፍለ-ዘመኑ የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀሙ — የአለ እና ምንአልባትም ወደፊትም እሚቀጥል፡ አስአፋሪ አፍራሽ ዘግናኝ እና አጥፊ፡ የ ህይወት ገፅታው አካል ነው።

ጀስት ዋር ቲየሪ፤ አሁን ከፍ ብለን የጠቀስነውን ዕውነትዐ በመጋራት ይመስላል፡ ጦርዕነት እንድአይደረግ እሚቻለውን ሁሉ ለመሞከር እና ስኬትአማ ሆነን ጦርዕነትን ማስቀረት እስከአልቻልን ዘንድ፡ በጦርዕነት ወቅት ክፋት'ን እና ጭካኔ'ን ለመቀነስ እና ጦርዕነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ'ም ወደ ሰላምዓዊ ህይወት ለመመለስ ሊደረጉ የእሚገባቸውን ሞራልዓዊ ፍትህዓዊ ተግባርዐትን ለመጠቆም በ እሚል፡ በ ሦስት ዋና-ዋና ክፍልዖች በተመደበ መሠረትዓዊ ማዕቀፍ የትአነፀ ንድፈ-ሃሣብ ነው። ሦስቱ ክፍልዖች'ም፤ [Jus ad bellum, Jus in bello, እና Jus post bellum] በ እሚል ይጠራሉ — በ ላቲን'ኛ።

*በ አማርኛ ደም፤ የ ጦርዕነት ተገቢዕነት፣ በ ጦርዕነት ወቅት ጠቀሜታ ላይ እሚዉሉ ስልትዖች ተገቢዕነት እና ከ ጦርዕነት በኋላ ተገቢዕነት ሊኖርአቸው ስለእሚገቡ ክንውኖች፡ እንደ ማለት ነው — በግርድፉ!*

ዛሬ እንግዲህ፤ በኦሮሚያ እና በመተከል፡ በኦነግ ጨፍጫፊዎች፡ <u>አላባራ ያለውን ጀኖሳይድ አስምረንበት በማለፍ፡</u> በሃገርአችን እየተካሄደ ስለአለው ጦርዕነት ከ [ጀስት ዋር ቲየሪ] ንድፈ-ሃሣብ አኳያ ሲማተር፡ ምን ሊመስል እንደ እሚችል፡ ላይ-ላይኡንም ቢሆን፡ ምልከታችንን ልእንአጋራችሁ፡ ከፊትአችሁ ቀርበናል።

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

አገርቤት እየተደረገ በአለው ጦርዕነት፤ እየደረሰ የአለው ዘግናኝ ሰቆቃ እና ዕልቂት፡ ምንአልባት በጣት ከሚቆጠሩ በሽተኛ የስልጣን ጥማትኧኛ ፖለቲከኞች እና የጦር አበጋዞች ውጪ፡ በ የትኛውም ጎራ ለእሚመደበው ወንድእማማች እህትእማማች አንድ ህብር ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ፡ ከ አቅም በላይ የሆነ ቅስም ሰባሪ ክስተት እንደሆነበት መገመት አያዳግትም። እንደ ወገን፤ ያ-እንን ማሰቡ ብቻ — ፅኑ ህመም ነው!

ትክክል። ይአገባን አለ እሚለው ወገን፤ በ አጠቃላይ — የ ጦርዕነት አጥፊዕነት እና አፍራሽዕነት ላይ ልዩዕነት አለው

የእሚል ዕምነት የለንም። ሆኖም ግና፤ እየተደረገ ስለ አለው ጦርዕነት የተያዘው አቋም፤ በ አራት ጎራ የተከፈለ መሆኑን እየአስተዋልን ነው። ሀ) ጭፍን የ ህወሓት ደጋፊዎች ለ) ጭፍን የ መዐከልዓዊው መንግሥት ደጋፊዎች ሐ) ሁለቱንም ጦርኧኞች እንደ እየአመጣጥአቸው እምይአስትናግዱ እና መ) አስመሳይዖች እና መሠሪዎች።

ጭፍን የ ህወሓት ደጋፊዎች፤ ህወሓት ወደ ስልጣን እንድእትመለስ እምይአልሙ፣ ስለ ኢትዮጵያ ግድ የሌላቸው [ኢትዮጵያን የ እሚጠሉ ብልአችሁ አንብቡት ከፈለጋችሁ] እና ዐማራ'ን ለማጥፋት የተለሙ፡ በ ጦርዕነቱ ህወሓት የበላይዕነቱን ስትወስድ "በሎ" እያሉ እምይአቀጣጥሉ፣ ህወሓት የተሸነፈች ሲመስላቸው ጦርዕነትን እምይአወግዙ እና አፍቃሬ-ድርድር ሆነው የ ውጪ ኃይልዐት ወታደር ልከው ነፃ ትግራይን እንደእሚመሰርቱእላቸው እየአሰቡ ሳልቬት ሲያደርጉ እምይታዩት ናቸው።

ጭፍን የ መዐከልዓዊው መንግሥት ደጋፊዎች፤ ፖለቲካን በተመለከተ፡ ከ ህወሓት ጋር ምንም ልዩዕነት የሌለውን አካል ከጎኑ በመቆም፡ ከርካሳ ቮክስዋገን ውስጥ አፈናጥጦ ወደ እንጦሮጦስ እየወሰዳቸው እየአለ፡ ዛሬ ጨረቃ ላይ ወጥተን እንመለስ አለን ሲልአቸው፤ በፍንደቃ — ስንት ሰዐት ላይ እንደርስ አለን ብለው እምይጠይቁ፡ እምይገርሙ ፍጡራን ናቸው። ደግዕነቱ፤ ህወሓት በጦርዕነት ተሸንፋ ከፖለቲካው ምህዳር እንድትጠፋ የቻሉትን ሁሉ ሲያደርጉ ይታያል። አብዛኛዎቹ፤ ለ ኢትዮጵያ እና ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ የአላቸውን ቀና ፍቅር ጥያቄ ውስጥ ማስገባት'ም አንፈልግም። የውጪ ጣልቃ ገብዕነትንእም ይቃወሙ አለ። ድርድርን'ም ቢሆን መዐከልዓዊው መንግሥት እሚወስደውን አቋም ከመደገፍ እምአይቆጠቡ ቢሆን'ም ቅሉ፡ ህወሓት የበላይዕነትኡን ይዛ ወደ ድርድር እንድትመጣ ፍላጎት አላቸው ብለን ማመን አንፈልግም።

ሁለቱንም ጦርኧኞች እንደ እየአመጣጥአቸው እምይአስትናግዱ ወገኖች፤ ኢትዮጵያ'ን እና የ ኢትዮጵያ'ን ሕዝብ እምይአስቀድሙ፣ የውጪ ጣልቃ ገብዕነትን እምይቃወሙ፣ የ ህወሓት ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም እምይአማቸው፣ ህወሓት ከ የ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር መጥፋት እንደአለባት እምይአምኑ፣ ጦርዕነቱ በአስቸኳይ እንዲቆም እምይወተዉቱ፣ ድርርድር ለ ኢትዮጵያ እሚያመች ከሆነ/ሲሆን ብቻ እንድይደረግ እምይፈልጉ፣ የ ህወሓትን አሸናፊዕነት ማየት እምአይፈልጉ ሆነው፤ በአንፃሩ'ም የ መዐከልዓዊው መንግሥት፡ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልክኡ፡ እራሱን ማከሰም እንደአለበት እና የ ኤትኒክ-ፌደራሊዝሙ ፈርሶ — ስር-ነቀል ለውጥን ለማየት የአለመታከት እምይጎተጉቱ'ም እምይታገሉ'ም ናቸው።

አስመሳይዖች እና መሠሪዎቹ፤ በአመዛኙ የ ህወሓት ቡችሎች እና እወደድ ባይ ርዝራዦች ናቸው። ስለ ህወሓት ዕውነታውን መናገር አይቃጣቸውም። ህወሓት እምትአራምዳቸውን ፀረ-ኢትዮጵያ አቋሞች እና በፖለቲካውም በጦርዕነቱም የበላይዕነቱን ቦታ እንደያዘች፡ ሰበብ እየፈለጉ ሲይአርአግቡ ይስተዋሉ አለ። ኢትዮጵያ እንደ እምትፈርስ፡ ህወሓትም ነፃ ትግራይ'ን እንደ እምትመሠርት፡ ነጋ-ጠባ በመደስኮር የ ሕዝብን ስነልቦና ለመረበሽ እና የመፍረስንም የ ነፃ-ሃገርን'ም እሳቤ ለማለማመድ፡ በማር የተሸፈነ መርዝአቸውን ሲረጩ ይደመጡ አለ። ይህ-እንን ሁሉ እምያደርጉት፤ ለ ኢትዮጵያ አዛኝ ሆነው በመቅረብ፣ ህወሓት'ን አንደግፍም እየአሉ እየቀጠፉ እና ሰንደቅ-ዓላማ'ችንን እየአውለበለቡ ነው።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ከ እነእኚህ አስመሳይዖች እና መሠሪዎች ይልቅ፡ ጭፍን የ ህወሓት ደጋፊዎች ይሻላሉ። እናም፤ ኢትዮጵያ'ን እምትል ኢትዮጵያን እምትዪ ሁላ፡ እነእኚህ አስመሳይዖችን እና መሠሪዎችን በጥንቃቄ ልትይዟቸው ይገባል — አደገኛ ናቸው እና!

ጎበዝ፤ ወደ የ ዛሬ'ው ዋና ነጥብአችን ስእንመለስ፤

ጀስት ዋር ቲየሪ የታነፀባቸውን፤ የ እየ እራስአቸው መመዘኛ መሠረትዓዊ ደንቦች የ አሏቸውን፡ ሦስትኡን ዋና ዋና ክፍልዖች፡ ተራ በተራ እንዕመለከት አለን እና — የ[ሰው] ልጅ ቅራኔዎችን ለ መፍታት በ እሚል፡ ጉልበትን ኃይልን እና እንደ እየ ክፍለ-ዘመኑ የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን መጠቀሙ — የአለ እና ምንአልባትም ወደፊትም እሚቀጥል፡ አስአፋሪ አፍራሽ ዘግናኝ እና አጥፊ፡ የ ህይወት ገፅታው አካል መሆኑን በመገንዘብ፡ ተፋላሚ ጎራዎች በጋራ ስምምዕነት ሊደረሱባቸው እሚችልኡ የ ፍልሚያ ህግጋት በ እሚል ሊወሰዱ እንዲችል፡ በ ጦርዕነት ዙሪያ የተቀመሩ የ ሞራል መመሪያዎች ወይም ደንብዖች መሆንአቸውን፡ ኋላ ኪስአችሁ ውስጥ አስቀምጣችሁ፡ ተከተሉን።

ዋና ክፍል ፩ — ዩስ አድ ቤሉም

የ ዋና ክፍል ፩ ትኩረት፤ ወደ ጦርዕነት የ መግባት/አለመግባት ውሳኔ ከመወሰኑ እና'ም ጦርዕነት ከ መጀመሩ በፊት፡ ጦርዕነት የመጀመርኡን እሳቤ [ሞራል ካምፐስ] ተገቢዕነት በጥንቃቄ መመዘን እንደእሚገባ መጠቆም ላይ ነው። ያ-እንንም ተግባር እምይአሳልጡ፤ የተወሰኑ ደንብዖች'ን ይአሰፍር አለ። አከርአካሪዕነትአቸውን ለ አንባቢያን እንደ የቤት ስራ በመተው'ም፡ የ ሃገርአችንን ጦርዕነት አስመልክተን የተወሰኑ ነጥብዖችን እንጠቃቅስ አለን።

- <u>ጦርዕነቱ ፍትህዓዊ ምክንያት ሊኖረው ይገባል</u>

ህወሓት እና የመንግሥት አካል፤ ሆድ እና ጀርባ ሆነዋል — የሥልጣን ጉዳይ! ለ ህወሓት፤ ታሪክዓዊ ውንብድና፣ ዕብሪት እና አጓጉል ይገባኛል ባይዕነት፡ ስንቅዋ ነው። የ መንግሥት አካል'ም፤ ተረኛዕነትን፣ ድብቅዕነትን እና አልሸነፍም ባይዕነት'ን ሰንቆ፡ ጥርሱን ነክሶ ዓይንኡን ጠበብ አድርጎ ያማትራል። የህወሓት ዕምነትዋ አቋሟ ሁሉ፡ መንግሥትን ገልብጦ፡ የ መዐከልዓዊውን መንግሥት ስልጣን እንደገና መያዝ፡ አልያም ሃገር አፈራርሶ ትግራይን እንደ አንድ ሉዐልዓዊት ሃገር መመሥረት ነው። የ ሁለትኡም ጎራዎች ባህሪይ፤ ነገሮች እምአይበርዱበት ሁኔታዎች ላይ ተንጠልጥለው ለ 3-ዓመት ያህል እንድይአዘግሙ አስገድደውአቸው ቆይተው አለ። እራስዋ እንደአመነችው፤ ህወሓት መብረቅዓዊ እርምጃ በመውሰድ ጦርዕነትኡን ጀምራ አለች — እናም ጥፋትኧኛ ናት። ያ-ም የ መዐከልዓዊው መንግሥት የወሰደውን አፀፋዊ እርምጃ እንደ

እራስን የመከላከል እርምጃ ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ፡ ፍትህዓዊ ምክንያት የአለው መሆኑን ይበይንዕለት አለ።

- <u>የ ጦርዕነቱ ዐላማ እና ግብ፡ አግባብዕነት የአላቸው ሊሆኑ ይገባል</u>

ህወሓት ሕዝብዓዊ ፍትህዓዊ ዐላማ'ም ሆነ ግብ የላትም። ህወሓት የትግራይን ሕዝብ አትወክልም፤ ትጠቀምበታለች እንጂ! ህወሓትን በተመለከተ፤ የ ጦርዕነቱ ዐላማ እና ግብ፤ መዐከልዓዊውን መንግሥት ገልብጣ፡ ስልጣኑን መልሳ መያዝ አልያም ኢትዮጵያን አፍርሳ፡ ትግራይን እንደሃገር መመስረት ነው። ያ-ም አግባብዕነት የአለው ዐላማ እና ግብ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። እስከ እነ ድክመቱ፤ መዐከልዓዊው የመንግሥት አካል፤ ህወሓትን እንደ አመጣጥዋ በማስተናገድ፤ ልክዋን እንድታውቅ እና ጤናማ ኢትዮጵያዊ ፀባይ እስከአልገዛች ድረስ፡ የ[ጦርዕነት አስከፊዕነት ሳይዘነጋ] ከፖለቲካው ዐውድ እንድትወገድ ማድረጉ፡ አግባብዕነት የአለው ስልት እንደሆነ ነው ሊወሰድ እሚገባው።

- <u>ጦርዕነት እንድይጀመር የመጨረሻውን ውሳኔ እምይሰጠው፤ አግባብነት የአለው ኃላፊ ወይም አካል ሊሆን ይገባል</u>

ይህ ቴክኒካል ጥያቄ እና ብዙ ውስጥ አዋቂዕነትን እሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ህወሓት የመጀመሪያዋን ቃታ እንዲሳብ የወሰነችው፡ በመሪዎችዋ በኩል መሆኑ ዕሙን ቢሆንም፤ ብዙ ጥያቄዎችን ማስተናገድ እምይአስችሉ ክፍተቶች ሊኖሩ እንደእምይችሉ መገመት ስህተት አይሆንም — ለምሳሌ፤ የ ውጪ ኃይልዐት። በ መዐከልዓዊው መንግሥት አካልም በኩል እንዲሁ! ግራም ነፈሰ ቀኝ፤ ሃላፊዕነት ቦታ የአሉ ፖለቲከኞች ውሳኔ መሆንኡን/አለመሆንኡን በመጠየቅ፡ ጊዜ ማጥፋት ፋይዳ አለው ብለን ዐንአምንም።

- <u>የ ጦርዕነቱ አዋጪዕነት</u>

ህወሓት፤ መንግሥት ሊወስድ እሚችለውን እርምጃ አጓጉል አቃልላ የተመለከተችው ይመስላል። አልሸነፍም እሚል ዕብሪት እነደአለባት ማየት'ም አይከብድም። የ ጦርኧኛዕነት ታሪክዋ፣ የ 30-ዓመት ስውር የጦር ኃይል ግንባታዋ፣ የውጪ ሃገራት ድጋፍ እንደ አላት ማመንዋ እና በአለፉት 3-ዓመታት ሌት-ተቀን መዘጋጀትዋ የልብ-ልብ እንዲሰማት አድርጓታል። ከ ወቅቱ ሁለዕነተንዓዊ ፖለቲካ ጋር ተመሰቃቅሎ፡ መዐከልዓዊው መንግሥት ጦርዕነቱን የአስኬደበት መንገድ [ልብ-አቁሳይ] ቢሆንም፤ አሁን አሁን፡ ህወሓት እጅጉን እንደተሳሳተች እንድትረዳው ሳይአስገድዳት አልቀረም። የ እኛ ነገር፤ እልህኧኞች አይደለን — ጦርዕነቱን በፍጥነት ማስቆም አልተቻለም። በእስተመጨረሻ ግና፤ ህወሓት ከፖለቲካው ዐውድ በዝረራ ወጥታ፤ ኢትዮጵያ የ አለ ህወሓት እንደእምትቀጥል፡ ፅኑ ዕምነትአችን ነው።

- <u>ጦርዕነት የመጨረሻው አማራጭ ሊሆን ይገባል</u>

ህወሓት ከ ጦርዕነት ሌላ ብዙ አማራጭ ነበርዐት። ልትጠቀምበት አልፈቀደችም። መዐከልዓዊው መንግሥትም ቢሆን እንዲሁ! የመጀመሪያዋ ጥይት ከተተኮሰች በኋላ ግና፤ መዐከልዓዊው መንግሥት እየወሰደ የአለው እርምጃ የመጨረሻው አማራጭ እንዲሆን እሚያስገድደው፡ ብዙ ጉዳዮችን መጥቀስ፡ ከባድ ሊሆን አይችልም።

*እናም፤ ወደ ጦርዕነት የመግባት/የአለመግባት ውሳኔ ከመወሰኑ፡ ማለትም — ጦርዕነት ከመጀመሩ በፊት፡ የ ጦርዕነትኡን ዞሪያገጠም ተገቢዕነት በጥንቃቄ መመዘንን በተመለከተ — ህወሓት የቀመሰችውን በመቅመስዋ፤ ልትአማርር እምትችልበት ምክንያት እንድአይኖርዐት አድርጓት አለ።*

ዋና ክፍል ፪ — ዩስ ኢን ቤሎ

የ ዋና ክፍል ፪ ትኩረት፤ ጦርዕነትን እምይአካሂዱ ጎራዎች – በጦርዕነቱ ወቅት የ እሚከተሉአቸውን ስልትዖች የ [ሞራል ካምፐስ] ተገቢዕነት'ን በጥንቃቄ መመዘን እንደ እሚገባ መጠቆም ላይ ነው። ያ-እንንም ተግባር እምይአሳልጡ የተወሰኑ ደንብዖች'ን አስፍሮ አለ። እዚህ ላይም፤ አከርአካሪዕነትአቸውን ለ አንባቢያን እንደ የቤት ስራ በመተው፡ የ ሃገርአችንን ጦርዕነት አስመልክተን የተወሰኑ ነጥብዖችን እንጠቃቅስ አለን።

- <u>ጦርኧኞች የ እምይአጠቁአቸውን ኢላማዎች ተገቢዕነት</u>

እየአነበባችሁት የአለው ጦማር፡ የ ጦር ሜዳ ዘገባ እንዳልሆነ ልብ በሉልን። አንድ አንድ ለፍርድ እምይአዳግቱ ድርጊትዖች መኖራቸው እንደ የ ተጠበቀ ሆኖ፤ ይህ ደንብ – ሰላምዓዊውን ንዋሪ ሕዝብ፣ የ ሃይማኖት ቦታዎችን፣ ቅርሳ-ቅርስዖችን፣ የ ጤና ሙያተኛውን እና የመሳሰሉትን የማህበረሰብ ክፍልዖች፡ መ'ነካት እንደሌለባቸው ይጠቁማል። የ መዐከልዓዊው መንግሥት፤ ይህ-እንን በተመለከተ፡ ትኩረትን የሳበ ግድፈት እንደ አለበት ማሳየት ያስቸግር አለ። ህወሓት ግና፤ በ ማንፌስቶዋ ላይ አስፍራ፡ እንደ ዕቅድ እና እንደ ግብ ወስዳ፡ ይህ-እንን ደንብ በተደጋጋሚ እንደጣሰች — የ ማይካድራን ጀኖሳይድ ጨምሮ፡ በ ዐማራ እና በ አፋር ክልሎች ንፁሃን ላይ እየአደረሰቻቸው የአሉት አሳፋሪ እና ዘግናኝ የጦርሜዳ ወንጀልዖች፣ የ አጎደፈቻቸው ቅርሳቅርሶች፣ የ አወደመቻቸው ቤተ ዕምነትዖች እና መንደርዖች፡ ለ ዘመንዐት እሚዘልቅ ጠባሳን ትተው እንደእምይአልፉ ምንም ጥርጥር የለውም። ለመሆኑ፤ የ ዐማራ እና የ አፋር ንፁህ ሕዝብ ምን አጠፋ?! ምንስ በደለ?!

- <u>የ ኃይል አጠቃቀምን በተመለከተ፡ ተመጣጣኝዕነት እና ተገቢዕነት</u>

ይህ አዳጋች ደንብ ነው። ህወሓትም ሆነች የ መዐከልዓዊው መንግሥት፤ ለመጠፋፋት ነው የተሰለፉት። ሁለቱም ጎራ የአላቸውን የጦር መሣሪያ ክምችት ሁሉ ተጠቅመዋል — ከ አየር ኃይሉ [ድሮንዖችን ጨምሮ] በስተቀር፤ የቀሩትን የጦር መሣሪያዎች፡ እየተዋዋሱ እሚጠቀሙባቸው እስኪመስል ድረስ! የ መዐከልዓዊው መንግሥት እየወሰደ የአለው እርምጃ ተመጣጣኝዕነት ህወሓት እየአስከተለች ከአለችው አደጋ ጋር ሲነፃፀር፡ ተገቢዕነቱ ሊይአከራክር አይገባም። ህወሓት የ ዐማራን ሕዝብ ለማጥፋት እና ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ነው ቆርጣ የተነሳችው። ህወሓት ሊጋ ወጣትዖችን ማሰለፍዋ እና

ንፁሃን የማህበረሰብኡ አባልዐትን በመማገድ [ተደጋጋሚ ጄኖሳይድ] እየፈፀመች የአለች መሆንዋ'ም፡ ዘግናኝ ገፅታዋ ሆኖ ለታሪክም ለፍርድም እየተመዘገበ ነው።

- <u>ኢ-ሞራል የሆነ ኃይል የመጠቀም ጉዳይ</u>

ይህም አዳጋች ደንብ ነው። ሁለቱም ጦርኧኛ ጎራዎች፤ የጦር ምርኮኞችን አያያዝ እና ኢ-[ሰው]ዓዊ የሆኑ ስልትዖችን መጠቀምን እንደእሚኮንኑ ሲደሰኩሩ ይደመጡ አለ። ጦርዕነት ኢንኸረንትሊ ኢ-ሞራል መሆኑ ብቻም ሳይሆን፡ ህወሓትንም ሆነ መዐከልዓዊውን መንግሥት፤ ተገቢውን ሁሉ ለማድረግ ይጥሩ አለ ብሎ ማመን፡ ይአስቸግር አለ።

- <u>ታዝገፔ ነው እሚባል ነገር ሊኖር እንደ እማይገባ</u>

ጦርዕነት እየተካሄደ እየአለ፤ በ ውጊያው ተሳታፊ የሆነ አካል ሁሉ፡ አለቃ ምንዝር ሳይለይ፡ ለ ድርጊትዖቹ ሁሉ አግባብዕነትአቸው እየተመዘነ ከ ተጠያቂዕነት ማምለጥ እንደ እማይችል ይአስገንዝብ አለ — ታዝገፔ ነው በሚል፡ ከ ተጠያቂዕነት ማምለጥ እሚቻል ሊሆን እንደ እማይገባ አፅንዖት በመስጠት። ህወሓትንም ሆነ የ መዐከልዓዊውን መንግሥት፤ ምን ያህል በ እዚህ ደንብ እንደ እሚመሩ ማወቅ አዳጋች ነው።

ለነገሩ፤ በየትእኛው ስርዐት፡ ህግ ፊት ቀርበው በአግባቡ ሲፈተሹ፡ አይተን እንዐውቅ እና!

*እናም፤ በ ጦርዕነት ወቅት ጠቀሜታ ላይ የዋሉ ስልትዖችን እና መሣሪያዎችን በተመለከተ — ህወሓትም ሆነች መዐከልዓዊው መንግሥት፡ በህግ ፊት ቀርበው ከመጠየቅ፡ የትም እምኢያመልጡበት ቅርቃር ውስጥ እራስአቸውን ከትተው እንደ አሉ፡ በፍፁም ልእንጠራጠር ኢይገባም።*

ዋና ክፍል ፫ — ዩስ ፖስት ቤሉም

የ ዋና ክፍል ፫ ትኩረት፤ ከ ጦርዕነት በኋላ፡ ጦርዕነቱ በማሸነፍ በመሸነፍ ወይም በ የተኩስ የማቆም ስምምነት ከተጠናቀቀ በኋላ — ወደ ሰላም ለመሸጋገር ይአስችሉ ዘንድ፡ እሚተገበሩ ክንውንዖችን የ [ሞራል ካምፐስ] ተገቢዕነት መጠቆም ላይ ነው። ያ-እንንም ተግባር እምይአሳልጡ የተወሰኑ ደንብዖች'ን አስፍሮ አለ። አሁንም፤ አከርአካሪዕነትአቸውን ለ አንባቢያን እንደ የቤት ስራ በመተው፡ የ ሃገርአችንን ጦርዕነት አስመልክተን የተወሰኑ ነጥብዖችን እንጠቃቅስ አለን።

- <u>ከጦርዕነት በፊት ወደነበሩ ነባርዓዊ ሁኔታዎች መመለስ</u>

ይህ ደንብ፤ ትርጉም እሚኖረው ጦርዕነት እየተካሄደ የአለው በ ሉዐልዓዊ ሃገርዐት መሃከል ከሆነ ነው። የጋራ መብትዖች፣ ሃብት ንብረት፣ ዳር-ድንበር እና ምርኮኞችን መለዋወጥን ይአካትት አለ። ዳር ድንበርን በተመለከተ፤ የጦርዕነቱ መንስኤ ወይም የጦርዕነቱ የመቀጠል አንዱ ምክንያት በመሆኑ፡ [ወልቃይት'ን ጠገዴ'ን እና የ ራያ'ን ጉዳይ ይአጤኗል] ወደ ነበረበት መመለስ፡ እምኢይታሰብ ጉዳይ ነው። እንደ ሃገር፤ በፍጥነት ከ ኤትኒክ ፌደራሊዝሙ ለመገላገል አለመቻልአችን፡ መንግሥትን ተጠያቂ ማድረጉ የተጠበቀ ሆኖ፡ እምኢይገባትን በመጠየቅ፡ ግግም እምትለዋ ህወሓት እየአስከተለቻቸው የአሉት ዘግናኝ ወንጀሎች፡ ከ አጥፊዕነት እና ከ ተጠያቂዕነት ልትአመልጥ እምኢያስችላት ቅርቃር ውስጥ አስገብቷት አለ።

- <u>ፍትህዓዊ የአስተድደር ስርዐትን መመስረት እና ከአለቃ እስከ ምንዝር በጦርነት ወቅት ለተፈፀሙ አስከፊ ወንጀልዖች ተገቢ ዕርምጃዎችን መውሰድ</u>

ፍትህዓዊ ስርዐት መመስረትን በተመለከተ፤ የ ወቅቱ ጦርዕነት ኖረም አልኖረ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በፍጥነት ሊመለስ እሚገባው መሠረትዓዊ ጥያቄ አለ። መንግሥት ተብዬውም፤ ኤትኒክ ፌደራሊዝሙን ከማፈራረስ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ፡ የግድ ዐምኖ መቀበል ይኖርበት አለ። ሆኖም ግና፤ ህወሓት ከፋም-ለማም፡ በ መንግሥትዕነት ቦታው ላይ ለተቀመጠው አካል፡ አግባብ የአለው ዕውቅና መስጠትን ይጠይቃት አለ። አቅም በፈቀደ መጠን፤ ለተፈፀሙ አስከፊ ወንጀልዖች ተገቢ ዕርምጃዎችን መውሰድ፡ ግዙፍ ትኩረትን እሚሻ ጉዳይ ነው።

- <u>በጦርዕነቱ ወቅት ሰለባ ለሆኑ ንፁሃን፣ የ ማህበረሰብኡ አባልዐትም ሆነ ሌሎች ተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ መክፈል</u>

ይህ አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። ህወሓትም ሆነች መዐከልዓዊው መንግሥት፤ ለ እንዲህ የአለ ነገር አቅምኡ የአላቸው አይደሉም። ለነገሩ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ፡ በየትእኛው ስርዐት፡ የመንግሥት አካልዐት ህግ ፊት ቀርበው በአግባቡ ሲፈተሹ አይተን እንዐውቅ አለን ብልአችሁ ነው። ቢቀርቡስ፤ ለ ንፁሃን ወገንዖቻችን ህይወት፡ እንዴት የአለ ካሳ፡ ፍትህን እንደእሚያሰፍን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል!?

- <u>በጦርዕነቱ ተሳታፊ በሆኑት መሃከል እሚደረግ የሰላም ስምምነቶችን መቀመር እና ዕውን ማድረግ</u>

ቀደም ብለን ከጠቀስነው፤ ካሳ የመክፈል ጉዳይ ተነስተን፡ ህወሓትም ሆነች መዐከልዓዊው መንግሥት፡ አቅም ስለሌላቸው፡ ወደዱም ጠሉም ትኩረት ሊሰጡአቸው እሚገባቸው ጉዳዮች — ተግባርዓዊ ሊደረጉ እሚችሉ የህግ ተጠያቂዕነት፡ እንዲሁም ዕርቅ እና ይቅር ባይዕነት ላይ ሊሆን ይገባል፡ ብለን ዕንአምን አለ።

*እናም፤ ከ ጦርዕነት በኋላ፤ ወደ ሰላም ለመሸጋገር ይአስችሉ ዘንድ፡ እሚተገበሩ ክንውንዖችን የ [ሞራል ካምፐስ] ተገቢዕነት በጥንቃቄ መመዘን'ን በተመለከተ — ህወሓት ብዙ ልትሸከምአቸው እማትችልአቸው [ሜስ] ፈጥራለች፡ እየፈጠረችም ነው። የሆነው ሆኖ፤ በንፁሃን ላይ ቅጣት እንድኢይፈፀም ጥንቃቄ በማድረግ፡ ሰላምዓዊ ቤተሰብዓዊ ህይወት በፍጥነት መጀመር እሚያስችል፡ የተሃድሶ ዕቅድ ሊኖረን ይገባን አለ።*

እንደ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ — ዝቅተኛ ማህበረሰብዓዊ ህይወትዋ'ም ሆነ በሽተኛ ፖለቲካዋ፡ መከራዋን እየአሳየት መሆኑ ዕሙን ነው። የእዚህ ዕውነትዐ መገለጫ'ም፡ በወንድእማማች እና በእህትእማማች መሃከል እምይደረገው ጦርዕነት፡ አንዱ ነው። ጦርዕነት፤ በፍፁማዊዕነት ሊወገድ እሚገባው ክስተት መሆኑን ቢታመንበትም ቅሉ፤ ከጥንትዓዊው ጥንት ጀምሮ የአለ እና የ ሆነ ሚረክል ከአልተፈጠረ በስተቀር፡ ወደፊትም ሊያጋጥመን

እሚችል፡ አፍራሽ አጥፊ ዘግናኝ የሆነ የ[ሰው] ልጅዖች የህይወት ገፅታ አካል መሆኑም፡ እንዲሁ!

ሃገርአችን እሚገጥሟት ጦርዕነትዖች፤ ከ ጥቂት የውጪ ባላጋራ ሃገርዐት ጋር ከተደረጉት ሌላ — በአመዛኙ፡ አሁን የአለችውን ኢትዮጵያ ለመፍጠር እና የ ውስጥአችን ማህበረሰብዓዊ እና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን በአግባቡ ማስተናገድ በ አለመቻልአችን ሳቢያ የተከሰቱ ናቸው። አንጀት አቁሳይ የሆነው ጉዳይ፤ ዛሬም ቢሆን መሠረትዓዊ ችግርዖችአችንን እንአቃልል ዘንድ፡ በ ስልጡን መንግሥት እና መንግሥትዓዊ የአስተዳደር ስርዐት መተካት ሲገባን፡ ሞሮኒክ በሆነ፡ ኤትኒክ ፌደራሊዝምን በ እሚተገብር ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ- ኢትዮጵያዊያን በሆነ ህገ-መንግሥት ለመመራት "አውቀን" ፈቅደን አለ። አዎን፤ የማስተካከል ዕድሉ ነበረን ለማለት ነው! ለማስተካከል ቁርጠን መታገል ሲገባን፤ ቁርጠኛዕነት ጎድሎን አለ ለማለት ነው!

በ አለንበት እየረገጥን ነው። አሁንም ቢሆን፤ ለ መሠረትዓዊ ችግርዖችአችን መፍትሄው፡ የ ጎሣ-ፖለቲካን እና ኤትኒክ ፌደራሊዝምን ማጥፋት፣ ከተገንጣዮች በስተቀር ሁሉን አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ መጥራት፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት ነው — አብረን መኖር የአለብን ወንድእማማች እህትእማማች፡ አንድ ቤተሰብ፡ አንድ ህብር ሕዝብ ነን እና!

በመጨረሻም፤ የ እሚቀጥሉትን 5-ዓመትዐት እመራአለሁ በእሚል፤ ስራውን ሰሞኑን የ ጀመረው መዐከልዓዊው መንግሥት፡ እራስኡ የ ኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ችግርዖች ውስጥ አንዱ አካል ስለሆነ፡ እርሱ እራስኡ መወገድ የአለበት ለመሆኑ ልእንጠራጠር አይገባም። እናም፤ በስልጡን እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ እራስኡን እንድያከስም፡ እንጠይቅ አለን። ያ-እስከእሚሆን ድረስ፤ ኦሮሚያ እና መተከል ውስጥ፡ በ ኦነግ ዘግናኝ ጭፍጨፋ፡ እየአለቀ ለአለው ዐማራ — ድረሱዕለት!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንገናኝ –

# ኢትዮጵያን አደራ!

ህዳር ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ‖ ኖቬምበር 2021

**አዳራሽ** – ፕላኔት ምድር፤ በ ሃይማኖትዓዊ ቀመር፡ ከ ስድስት እስከ አስር ሺህ ዓመትዐት ስትአስቆጥር: ሞት-አይፈሬው ሳይንስ ደሞ፡ ወደ አምስት ቢልየን ዓመትዐት ገደማ እንደእሚለጥጠው፡ መዛግብት ይነግሩናል። ግምት መሆንአቸው የተጠበቀ ሆኖ፤ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ፤ የ[ሰው] ልጅ ህይወት እጅጉን ገራሚ፣ ሁለዕንተንዓዊ እና ዘርፈብዙ ለውጥዖችን፣ ውልጠትዖችን እና ነውጥዖችን እየአስተናገደ ይገኛል። ለውጥ ለውጥን እየፈጠረ፣ ውልጠት ውልጠትን እየወለደ እና ነውጥ ነውጥን እየአስተናገደ – በ የ[ሰው] ልጆች ህይወት ውስጥ እምይመጡ፣ እምይሄዱ እና እምይመላለሱ፡ ክስተቶች፣ የፈጠራ ውጤትዖች እና የምርምር ግኝትዖች የትየለሌ ናቸው። ይሄው እና፤ ከ የ ደመነፍስ የ ዘፈቀደ ህይወት ተነስተን፡ ምድር ሰማዩን አስሰን እና አዳርሰን፡ አርቲፊሻል ኢንተልጀንስ ፈጠራ ላይ ደርሰናል። እግረመንገድአችንንም፤ የ[ሰው] ዘር በቁጥር እየጨመረ በመሄድ፡ ዛሬ [ስምንት ቢልየን] ለመድፈን እየተጣደፍን እንእገኝአለን።  በ ፕላኔት ምድር ላይ ወደ 195 እምይጠጉ ሃገርዐት [ኔሽን'ስ] አሉ። የ ማህበረሰብዓዊ ህይወት መግዘፍ መፍጠን መዛመድ መቆራኘት መወሳሰብ መዘበራረቅ ሁሉ ተነባብረው ተሰባጥረው፤ ህይወት ጉራማይሌ እንድይሆን አስገድደውት ይገኛሉ። ከ ጉራማይሌ የ ህይወት መገለጫዎቻችን  ውስጥ፤ [ፖለቲካ] ግዙፍ ቦታ ይዘው ከእምይገኙት ክስተቶች ውስጥ አንዱ ነው። እየአንድ-አንዱ ሃገር፤ የ ራሱ የሆነ የመንግሥት አካል አለው። መንግሥታት፤ ከ እየ ጐረቤት ሃገርዐት፣ በ እየ አህጉርኡ እና በ ዓለም-አቀፍ ደረጃም ጭምር፤ ትብብርዖችን ትስሥርዖችን ድርጅትዖችን ተቋማትን በመፍጠር፡ የጋራ የሆነውን ህይወት ፈር ለማስያዝ እና የ ዕለት-ተ-ዕለት ህይወትን ለማሳለጥ ሲጠቀሙባቸው እየታየ ነው። እንደ ዓይነትኛ መሳሪያ እንድይአገለግሉ በ እሚልም፤ ወደ 70-ሺህ እምይጠጉ፡ ዓለም-አቀፍ ድርጅትዖች ተቋቁመው እንደአሉ ይገመታል — ሃምሳ-ሰባት ፐርሰንት እምይሆኑት እምይታይ ስራ እየሰሩ የ አሉ። ከ እነእዚያ ውስጥ'ም፤ የተባበሩት መንግስትዐት [ዩ ኤን] እና የ ኢንተርናሽናል ማኒተሪ ፈንድ [አይ ኤም ኤፍ] የዛሬው ትኩረትአችን ናቸው። መንግሥትዐት እና ዓለም-አቀፍ ድርጅትዖች፤ በ ዕቅድ በ ስርዐት እምይመራ ማህበረሰብ ለመፍጠር እና አወንታዊ በሆኑ አትሪቢዩት'ስ የዳበረ ህይወት መምራት እንደእምይያአስችሉ ዕሙን ቢሆንም ቅሉ – ማህበረሰብአችን፤ አሉታዊ [አፍራሽ ጨቋኝ ኢ-[ሰው]ዓዊ] ከሆኑ አትሪቢዩት'ስ፡ ነፃ ሊሆን እንደአልተቻለው'ም ግልፅ ነው። በአመዛኙ፤ ለ በጐ ሲባል የተፈጠሩ መንግሥትዐት እና ዓለም-አቀፍ ድርጅትዖች፡ የ እነዚህ የ አሉታዊ አትሪቢዩትስ መተግበሪያ መሣሪያዎች በመሆን እንደእምይአገለግሉ ማየት'ም ከባድ ሊሆን አይችልም። አምባገነንዕነትን፣ ቅኝ-ገዥዕነትን፣ የ እጅ-አዙር ቅኝ-ገዥዕነት ይአጤኗል! ዛሬ በ ሃገርአችን እየታየ የአለውም ምስቅልቅል፤ የእዚህ ዕውነታ ነፀብራቅ ነው። አንድ-አንድ "ኃያልዐን" ሃገራት እና ታዛዥ ዓለም-አቀፍ ድርጅትዖች፡ በ ፖለቲካችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት እና ጫና በማስአደር፡ የ እጅ-አዙር ቅኝ-ገዥዕነትን ተግባርዓዊ ይአደርጉ ዘንድ እሚረዳቸውን  አሻንጉሊት [ህወሓት'ን] መልሰው በ ኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ላይ ሊጭኑ ደፋ ቀና ሲሉ ይታይ አለ – "ድርድር"ን እንደ ዓይነትኛ መሣሪያ አድርጐ በመጠቀም። የ ውጪዎቹ እየፈጠሩት ከአለው ወጀብ ራስአችንን በመከላከል እምንወስደው ጊዜ፣ እምንአጠፋው ሃብት እና እምንከፍለው የህይወት መስዋዕትዕነት ሳይአንሰን፤ ኢ-ፍትህዓዊ ጣልቃ-ገቢ እና ጫና ፈጣሪ "ኃያልዐን" ሃገርዐት እና ዓለም-አቀፍ ድርጅትዖች፡ ጉልበትኡም ሃብትኡም እና ዕርዳታ የመስጠትም ሆነ የመከልከል ችሎታው ወደ እነእርሱ የአመዘነ ስለሆነ እና ሊጎዱን'ም ስለእሚችሉ ብቻ፡ በ አፋጣኝ ወደ እማይበጀን "ድርድር" ግቡ እሚልኹውን ጉትጐታ፡ ዝም ብለን ልእንቀበል አይገባም። በፍፁም! እንድይአውም እንጠይቅአለን። የ ዝም-ብልአችሁ "ተደራደሩ" ጉትጐታ፤ አገር-በቀል አምባገነን መንግሥትዐት፡ [ባንኩንም ታንኩንም] ስለእምይይዙ እና ሕዝብን'ም ሊጎዱ ስለ እሚችሉ፤ ዝም ብለን እንገዛላቸው ከማለት እና [ቅኝ-ተገዥዕነት'ን ባሪያዕነት'ን ኢ-[ሰው]ዓዊ ዕነት'ን] ዝም ብልአችሁ ተቀበሉ ከ እሚል ውዳቂ ዕይታ — በምንኡ ይለይ አለ??!! ወይ የ ኢትዮጵያዊዕነት'ን ምንዕነት አ-ለ-ማ-ወ-ቅ!

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

ስለ ወቅትዓዊ ሁኔታወች አለማውራት መቼም አልተቻለም። ቁርጠኛዕነት እና ቅንዕነት የጐደለው፤ ኢንኮምፐተንስ የ እምአይገልፀው መንግሥት ተብዬ፡ ሃገር እየአፈረሰ እየአስፈረሰ እና ሕዝብ እየጨረሰ እየአስጨረሰ ነው።

ዛሬ'ም እንግድኢህ፤ በእዚህኡ ጉዳይ ዙርያ በማውጠንጠን፡ የይድረስ-የይድረስ የ አዘጋጀንአትን መጣጥፍ ይዘን፡ ከፊትአችሁ ቀርበን አለ።

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

ኢትዮጵያ ግዙፍ አደጋ ላይ ነች – በ ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ፣ በ ኦነግ እና በ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ (ብልፅግና) ምክንያት። እነእኙህ ቡድኖች፤ በ ፀረ-ኢትዮጵያ እና በ ፀረ-ኢትዮጵያዊዕነት አቋምአቸው እና በ አረመኔዕነትአቸው፡ አንድ ናቸው። ምንም ልዩዕነት የላቸውም። እምይአጣላቸው፤ የስልጣን ጉዳይ ብቻ ነው! አንድአቸውም፤ የሕዝብ እና የሃገር ጉዳይ እምይአስጨንቅአቸው አንጀት፣ ልብ'ም ሆነ ኅሊና የላቸውም። አልተፈጠረባቸውም!

አልያ እማ፤ ህወሓት'ም፣ ኦነግ'ም ሆነ ብልፅግና – ኢትዮጵያ'ን እምትአክል ታላቅ ሃገር እና ኢትዮጵያዊያንን እምይአክል፡ አኩሪ ታሪክ የአለው፣ ትሁት፣ እንግዳ-ተቀባይ፣ ቻይ፣ አትንኩኝ-ባይ፣ ቆራጥ፣ ኩሩ እና ጀግና ሕዝብ እንድይአስተዳድሩ፡ ይአውም ለ 30-ዓመትዐት ያህል ዕድሉን ያለተቀናቃኝ አግኝተው አልነበር እን??!! ዕዩአቸው እስቲ የፈጠሩትን [ሜስ]።

ከ የ ገባንበት የሰቆቃ የዕልቂት አዙሪት ለመገላገል፤ መውጫው መንገድ ግልፅ ነው። መጀመሪያ፤ ጦርዕነትኡ በአስቸኳይ መቆም ይኖርበት አለ። ያ-ም ዕውን እንዲሆን፤ ህወሓት እና ኦነግ፡ ትጥቅ ፈትተው እና ከ እምአይገባቸው ግዛትዖች ለቅቀው በመውጣት፡ መክሰም ይኖርባቸው አለ። ጥፋትኧኛ እንደእየአግባብኡ፤ ህግ ፊት ቀርቦ እንዲበየንበት በማድረግ፡ ቀሪው ጀሌ፡ ወደ ሰላምዓዊ ህይወት እሚቀላቀልበትን መንገድ በማስተካከል።

ብልፅግና፤ የ መንግሥትዕነት ቦታው ላይ ስለ አለ፤ ራስኡን በሰላም እምይአከስምበት የተሻለ ዕድል ቢኖርኧው አይከፋም። ለሃገር እና ለ ሕዝብ ሲባል። ይህ እንንም ስእንዕል፤ በ ስልጡን፣ በ ሃላፊዕነት እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ፡ ሁሉን-አቀፍ

ሃገርዓዊ ጉባኤ ተጠርቶ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የማድረግን ሂደት ሳይአደንአቅፍ፡ ማለትአችን መሆንኡን ግልፅ ማድረግ እንፈልግ አለን። አሁንም፤ የ ብልፅግና ጥፋትኧኛ አባልዐት እንደእየአግባብኡ ህግ ፊት እንድይቀርቡ በማድረግ እና ቀሪው ጀሌ ወደ ሰላምዓዊ ህይወት እንድይቀላቀል በማድረግ።

ጦርዕነትኡ

ኢትዮጵያ ውስጥ እየተደረገ የአለው ጦርዕነት የተነሳው፡ ጥቅምት 24/2013 ዓ.ም. ትግራይ ውስጥ በተተኮሰች ጥይት ምክንያት ብቻ አልይደለም። የ ጦርዕነቱ ምክንያት — የ ጎሣ-ፖለቲካ፣ ኤትኒክ ፌደራሊዝም እና በቋንቋ እና በ ጎጥ ላይ የተመሰረተው የአስተዳረር ክልሎች ፈጠራ ሳቢያ ነው። እናም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ የአለው ሰቆቃ እና ዕልቂት ሊቆም ይችል ዘንድ፡ ህወሓትን ማሸነፍ ብቻ በቂ አይሆንም። ኦነግን እና መሠል ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጅቶችን በማጥፋት እና መሠረትዓዊ ስርነቀል ለውጥ በማድረግ ጭምርም እንጂ!

ወጣም ወረደ፤ ደጋግመን እንደ አልነው፡ ጦርዕነትኡ በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት እንዲጠናቀቅ ሆኖ መካሄድ ነበረበት። አሁን እም፤ የ እኛ አቋም ያ-ው ነው። ያ-እንን ተግባርዓዊ ለማድረግ ግና፤ በ ቁርጠኛዕነት እና በ ቅንዕነት፡ ፍልሚያውን እምይመራ ኢትዮጵያዊ የ መንግሥት አካል እንድይኖረን የግድ ይላል። ዛሬ እየአየን የአለነው ያ-እንን አይደለም። የ ኢትዮጵያ የ መከላከያ ሠራዊት፤ የ ህወሓት'ን የ ኦነግ'ን ወንበዴ መንጋ ማሸነፍ ሊያቅተው አይገባም ነበር።

በ ቅርብኡ፤ ብልፅግና፡ መንግሥቱ ኃይለማሪያም ፈጥሮት የነበረውን [ደርግ] እሚመስል ስብስብ ይዞ፡ ወደ ባህርዳር ሄዶ ነበር። ለ ዐማራ ሕዝብ የአስተላለፈው መልዕክት'ም [ህወሓት'ን ማሸነፍ አልቻልኩም፣ ከ እንግዲህ ወዲህም ከጐናችሁ ቆሜ ልዋጋ አልችልም፡ እምይል ነበር።] እኛ ያ-እንን ስእንሰማ፤ አ-ይ ግልግል፡ እንግዲህ ሪዛይን ሊያደርግ ነው ብለን ነበር። ምክንያቱም፤ አንድ የ መንግሥት አካል፡ የ ሃገርን ድንበር እና የ ሕዝብን ሰላም እና መረጋጋት መጠበቅ ከ አልቻለ – ምን ሊሠራ አራት-ኪሎ ቤተመንግሥት ይቀመጣል??!! አንድ የመንግሥት አካል፤ በ ስልጣኑ ላይ እንዲቆይ የ እሚፈቀድዕለት፤ ሃላፊዕነትኡን እና ግዴታውን እስከተወጣ ድረስ ብቻ እና ቤተ-መንግሥትኡ'ም የግል የ መኖሪያ ቤትኡ አለመሆንኡ፤ እንዴት እስ ብልፅግና ውስጥ ለ አሉ ፍጡራን አልገባቸው አለ??!!

ከ እዚህ ጋር በተያያዘ'ም፤ የ ጦር ኃይልዖች ዋናው ጄንራል፡ ከ ወደ አራት ሳምንት በፊት በሰጠው የ 01:34:18 ርዝመት የአለው ቃለመጠይቅ ላይ፡ በ 01:20:00[± 00:02:00] ላይ የተናገረውን አድምጡ። ለ ዐማራ'ውም ንገሩት። ድንገት የአልቆረጠ ዐማራ እንደ አለ፤ እንድይለይዕለት!! ትክክል። ሰውየው፤ ህወሓትን ከ ዐማራ ክልል የማስወጣት አላማ የለንም ነው የአለው። መከላከያው፤ ማፈግፈግን [ቁርስ ምሳ ራትኡ] የአደረገውም፤ ለ እዚያ መሆንኡን በ እምይአረጋግጥ መንፈስ።

በ እንዲህ ዓይነት የ ከሃዲ የ ሴረኛ ማይንድሴት፤ ጦርዕነትኡ በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት ይጠናቀቅ አለ ብሎ መጠበቅ፡ ሞኚዕነት ነው። ለ እዚያም ነው፤ ከ ኲሃ ማለፍ እማይገባት ህወሓት፡ ይሄው እና ዛሬ ወሎ'ን አልፋ፣ ሰሜን ሸዋ'ን ተሻግራ፣ አዲስ አበባ ዙሪያ ደርሳ፡ ከ ኦነግ ጋር ግንባር ፈጥራ በጋራ እየተዋጋች አለች እሚባለው። አይደለም እንዴ!? ዕውነታው ያ ስለ ሆነ፤ ብልፅግና [ደምስሰናታል ጨርሰንአታል አውድመንአታል] አሸንፈን አለ ሲል – ጆሮዬን ይዛ ከ አራት-ኪሎ አላስወጣችኝም ማለትኡ ብቻ እንደሆነ ተደርጐ ነው ሊወሰድ እሚገባው። ማሸነፍ እና መሸነፍ እሚልኡት ሁለት የ አማርኛ ቃልዐት፤ አራት-ኪሎ ሲደርስኡ ትርጉም ይለዋወጣሉ፡ ከ አልአችሁን በስተቀር።

ለመሆኑ፤ ገዳፋ የሆነብንን፡ የ ህወሓትን ኮከብ የአለበት ሰንደቅ-ዓላማ ጦር ሜዳ ላይ እየአውለበለብኡ፡ ከ ህወሓት ጋር ጦርዕነት መግጠም ማለት፡ ምን ማለት ነው??!! ፀረ-ኢትዮጵያ በሆነው የ ህወሓት ህገ-መንግሥት እየተዳደርኡ እና የ ህወሓት'ን የ ጎሣ-ፌደራሊዝም እየተገበርኡ — ኢትዮጵያዊያንን ለ ዕልቂት መዳረግ እስ፡ ምን እሚሉት ስልጡን ማህበረሰብዓዊ አስተደዳር፣ ምን እሚሉት ስልጡን ፖለቲካ ነው??!!

በ እስተመጨረሻ፤ ጦርዕነትኡ እምይጠንአቀቀው በ ኢትዮጵያ እና በ ኢትዮጵያዊያን አሸናፊዕነት መሆንኡን እኛ በፍፁም አንእጠርአጠርእም። ብልፅግና፤ ከ ኢትዮጵያ እና ከ ኢትዮጵያዊያን ጐን በ ቁርጠኚዕነት እና በቅንዕነት ቢሰለፍ ይመረጥ አለ። አከሳሰሙንም እንድያሳምር ይአግዘዋል ብለን እንዐምን አለን። አሻፈረኝ በ እሚለው የ አሁንኡ አቋም መቀጠል ከፈለገ ግና፤ ኢትዮጵያዊያን የፍልሚያውን ፊትአውራሪዕነት ቦታ በ እጅአቸው በማስገባት፡ ጦርዕነትኡን በ በአሸናፊዕነት እንድይጠናቀቅ ማድረግአቸው፡ አይቀሬ ነው።

ድርድር

ድርድርን በተመለከተ፤ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው፡ እኛ ዛሬም ቢሆን ድርድር አግባብዕነት አለው ብለን አንዐምንንም። በአመዛኙ፤ ኢትዮጵያን ወክሎ የ እሚደራደር አካል አለ ብለን ስለ እማንዐምን። የ ችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነው ኢትዮጵያዊም፤ ትኲረትኡም ሆነ ምርጫው፡ ድርድር ላይ ሳይሆን፡ በ ቆራጥዕነት ታግሎ፡ ኢትዮጵያን አጠናክሮ ማስቀጠል እና ህልውናውን ማስጠበቅ ላይ ነው፡ ብለን ስለ እምንዐምን። ውሳኔ ሰጭ ስለ አይደለን ግና፡ ብልፅግና ድርድር ማድረግ ከፈለገ፡ ልእንአስቆመው እንደ እማንችል እንእረዳ አለን። ድርድር መሰል ነገር ለረጅም ጊዜ እየተካሄደ እንደ አለ'ም እየሰማን'ም እየአየን'ም ነው።

የ ሰሞንኡ ድርድር'ን በተመለከተ፤ የ ልዑካንኡ ቡድን፡ ፕሬዝደንትዋን እና ጠቅላይ ሚንስትርኡን ማንአገሩ፡ እምይጠበቅ ቢሆንም — ለምን እና እንዴት የ ኦሮሚያውን ሰውዬ ብቻ ለማናገር እንደፈለገ ስንአስብ፡ በ እዚህ በ ኦዴፓ-ኦነግ መራሽኡ ብልፅግና ላይ የአለንን ጥርጣሬ እና ስጋት የበለጠ አግዝፎት አለ።

የሆነው ሆኖ፤ ድርድር እሚባለው ነገር ከቀጠለ፡ ሊደርሱ እምይችልኡ ሁለት ግዙፍ ስህተትዖች ይታይኡን አለ። ስህተት አንድ – ህወሓት'ን እና ኦነግ'ን ወደ የ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር ውስጥ መቀላቀል ወይም የመንግሥትዕነት ስልጣን እንድይጋሩ ማድረግ እና ስህተት ሁለት – ወልቃይት፣ ጠገዴ

እና ራያ ከ አማራው እጅ እንድይነጠቁ ማድረግ። ድርድሩ፤ ከእነዚህ ስህተትዖች አንዱን እንኳን ከፈፀመ – ጦርዕነትኡን ማስቆም እምአይቻልበት ውጥንቅጥ ውስጥ እንደ እምንዘፈቅ እና በ ኢትዮጵያችን ሰላም እሚባል ነገር ለማየት፡ ገና ለ ብዙ ዘመንዐት መፋለም እንደ እሚኖርብን ልእንእጠርአጠር አይገባም።

ጦርዕነትኡ በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት በፍጥነት እንድይጠናቀቅ ለማድረግ፤ ብልፅግና፡ በ ቁርጠኛዕነት እና በ ቅንዕነት መፋለም ታሪክዓዊ መንግሥትዓዊ ግዴታው መሆንኡን በተደጋጋሚ ሊነገረው ይገባል። ብልፅግና፤ ሕዝብ እሚፈለገውን ያህል ጥረት አልአደረገም፣ ተገቢውን ድጋፍ አልሰጠንም በእሚል፡ ሰበብ እየፈለገ ማማረሩን ማቆም አለበት። እስቲ ፈጣሪ ይአሳይአችሁ – በተለይ በተለይ፡ የ ዐማራ እና የ አፋር ሕዝብ፡ ከ እዚህ በላይ ምን እንድይአደረግ ነው እምይጠበቀው?! የአለችው አንድ ህይወት ናት። እርሷን እም፤ የ አለመሰሰት፡ ኢትዮጵያን እየአለ፡ መስዋዕት እየሆነ ነው። ከ እዚህ በላይ ምን ዓይነት ጥረት፣ ምን ዓይነት ድጋፍ እንድይሰጥ ነው እምይጠበቀው። ያውም፤ ብልፅግና፡ በተለይም ዐማራ'ውን፡ አንዴ አትደራጅ አትታጠቅ፣ ሌላ ጊዜ፡ ተደራጅ ታጠቅ፡ እንደገና ተመልሶ፡ አትደራጅ አትጣጠቅ እየአለ፡ ግራ እየአጋባው!

ብልፅግና፤ ከ ሕዝብ ጋር የ መናበብ ችግር እንደአለበት ግልፅ ነው። ይህ እም፤ ችግርኡ የ ሕዝብ ሳይሆን፡ የ ራስኡ የ ብልፅግና ችግር መሆንኡን ሊያውቀው ይገባል። የ ሕዝብ'ን መስዋዕትዕነት ሪከግናይዝ አለማድረግ፤ ቢያንስ ንፉግዕነት፡ ከፍ ሲልም – ክህደት ነው።

ብልፅግና ምክርአችንን ቢይአድአምጥ ይበጀው አለ። አከሳሰሙን ለማስአመር ከፈለገ፤ በ ፍፁም ቁርጠኛዕነት እና ቅንዕነት፡ ኢትዮጵያዊ ነኝ የ እሚለውን ሕዝብ፡ በተለይም ዐማራውን በ ጠላትዕነት እና በጥርጣሬ ዐይን ማየት ማቆም አለበት። ኢትዮጵያዊውን፤ በተለይም ዐማራውን በ ቁርጠኛዕነት እና በ ቅንዕነት ከጎኑ ከአሰለፈ'ም፡ ጦርዕነቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ በአሸናፊዕነት ማጠናቀቅ እንደ እሚቻል፡ ምንም ጥርጥር የለውም።

ትክክል። ብልፅግና፤ ለ ዐማራ ሕዝብ ተገቢውን ትጥቅ ስንቅ እና ትክክለኛ መረጃ ሊይአቀርብዕለት፡ ግዴትአው ነው። ቢያንስ ቢያንስ፤ ዐማራው ኅልውናውን በ እምይአመቸው መንገድ እንድይታደግ፡ ብልፅግና እንቅፋት መሆንኡን ሊይአቆም የግድ ነው – ዐማራ ኢትዮጵያን እና ኅልውናዬን አልአስነካም ስለ አለ ብቻ እየተሰቃየ ነው እና! እገረመንገድአችንንም፤ ብልፅግና፡ ዐማራ'ን ሆነ ብሎ እየአስበላው መሆኑ፡ እንኳን ዐማራ፡ ፈጣሪ ይቅር እማይለው ነውር ሃጥያት እና ሃገርዓዊ ወንጀል መሆንኡን'ም ማስገንዘብ፡ እንወድ አለን።

ተጓዳኝ ጉዳይ

በ ህዳር ወር ገደማ፤ የሆነ የ ሁሉን-አቀፍ ሃገርዓዊ ጉባኤ የማካሄድ፡ "ፍላጎትኡ" እንደ አለ ሰምተን አለ። እኛ እንድይደረግ እምንፈልገው፤ ሁሉን-አቀፍ ሃገርዓዊ ጉባኤ፡ የ ህወሓት እና የ ኦነግ ጉዳይ ሆኖ ሊቀርብ ይገባል ብለን አንዐምንም። እነ እርሱ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለው፤ ጦር መዝዘው እየወጉን ነው። እነ እርሱን ከጎንአችን አስቀምጠን፤ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ መወያየት መደራደር፤ የሞትም ሞት ነው።

ዕውነት ለመናገር ከሆነ፤ ሃገርዓዊ ጉባኤ'ው የ ብልፅግናም ጉዳይ መሆን የለበትም። ህወሓት'ም ኦነግ'ም ብልፅግና'ም ተመሳሳይ ሃገርዓዊ ክህደት እና ሃገርዓዊ ወንጀልዖችን የፈፀሙ፡ ከ ኢትዮጵያ የ ፖለቲካ ዐውድ ሊወገዱ እምይገባቸው ድርጅቶች ናቸው። ይልቅኡን እስ፤ ሃገርዓዊ ጉባኤ'ው፡ ለሰቆቃ ለዕልቂት እና ለ ሃገር መፈራረስ የዳረገውን በሽተኛ ፖለቲካ ማረቅ ይቻለው ዘንድ፡ የ መፍትሄ አፈላላጊ ጉባኤ ይሆን ዘንድ እንድይተገበር የግድ እሚል፡ የ [120 ሚልየን] ህብር ኢትዮጵያዊ ጉዳይ እንጂ!

እዚህ ጉባኤ ላይ፤ ዐማራው ኦሮሞው ትግሬው አፋሩ ጉራጌው ሶማሌው፡ ምን አለፋችሁ ሁሉም ኢትዮጵያዊ፡ ይወክለኛል እሚለውን ድርጅትም ሆነ ግለሰብ በመላክ ሊሳተፍበት ይገባል ብለን ነው፡ እኛ የ እምንዐምነው።

ይህ ጉባኤ፤ በተግባር ሊተረጎሙ እምአይችሉ፣ በሽተኛ ፖለቲካችንን በፍጥነት ማረቅ እምአይአስችሉ ጉዳዮች ላይ ጊዜ እንድይባክን ማድረግ፡ ግዙፍ ስህተት ነው እሚሆንኧው። ትክክል። ይህ ጉባኤ፤ [አክደሚክ ኤክሰርሳይስ] እንድይሆን ማድረግ፡ ግዙፍ ስህተት ነው እምይሆንኧው። ለ እዚያ ለ እዚያ፤ የሆነ ዩኒቨርስቲ መስርታችሁ፡ ብእትአስተምሩ ይቀልአችሁ አለ። ይህ ጉባኤ፤ እምይፈለገውን ፍሬ እንድይአፈራ ለማድረግ፡ ትኩረቱ ሊያደርግኧው ይገባ አለ ብለን እምንዐምንኧው ጉዳይ፡ በጥቅልኡ፡ በሽተኛ ፖለቲካችንን በፍጥነት ለ ማረቅ ይቻል ዘንድ፡ [በ አግባብኡ፡ ሃላፊዕነት እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ የተቀመረ፡ የ ዕውነት አፈላላጊ እና የ ዕርቅ መንገድን እምይአመችአች፡ ኢትዮጵያዊ ስርዐት'ን የያዘ ጉባኤ ማካሄድአችንን እርግጠኛ መሆንን ነው]።

የ እዚህ ጉባኤ ውጤትም፤ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት መመሥረት፣ ኢትዮጵያዊ ንፁህ ህገ-መንግሥት መቅረፅ እና ግልፅ የሆነ የ ሕዝብ ቆጠራ ተደርጐ፣ ፍትህዓዊ እና ነፃ የ ሕዝብ ምርጫ ተደርጐ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት ብቻ ነው፡ ሊሆን እምይገባው።

ለ እዚህ ሁሉ፤ የ ብልፅግና'ን ቁርጠኛዕነትን እና ቅንዕነትን ቢይአገኝ ይመረጥ አለ። ብልፅግና ይህ-እንን ቁርጠኛዕነትን እና ቅንዕነትን እምይገልፀው'ም፤ ተላይ የጠቆምንኧውን ጦርዕነትኡን በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት ማጠናቀቅ እምይአስችሉ ተግባርዐትን በማከንአወን፣ ለወገን ኃይልዐት [በተለይም ለ ዐማራ እና ለ አፋር ሕዝብዓዊ ኃይልዐት] ትጥቅ ስንቅ መረጃ መስጠት፣ በ ጦርዕነትኡ ሳቢያ ህይወትአቸው ለተመሰቃቀለ ወገንዖችአችን አስፈላጊውን ድጋፍ በፍጥነት ማቅረብ፣ ኦነግ ኦሮሚያ ውስጥ ዐማራ ላይ እየአካሄደ የአለውን ጄኖሳይድ ዛሬውንኡ እንድያቁም ማድረግ እና የ አለምንም ምክንያት ድርደራ፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እስረኛዎችን፡ የአለምንም ቅድመ ሁኔታ እና ፊርማ፡ ዛሬውእንኡ እንድይፈትኡ በማድረግ፡ ሊሆን የግድ ይል አለ።

እንደ ማጠቃለያ

እንደ አለመታደል ሆኖ፤ በ ፕላኔት ምድር ላይ፡ እንደ ሃገር – ኢትዮጵያ'ን፡ እንደ ሕዝብ ደሞ – ኢትዮጵያዊ'ን፡ እንደመሆን ከባድ ነገር የለም። ብዙ ብዙ ማለት ይቻል አለ። የ ዛሬ 30-ዓመትዐት ገደማ፤ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ አረዳድ እና በ ፖለቲካ የአለው ተሳትፎ፡ ዛሬ የአለበት ደረጃ ላይ ቢሆን ኖሮ – ኤርትራ'ም አትገነጠልም፣ የባህር በርዖቻችአችንንም አንአጣም ነበር። እናም ዛሬ፤ [የከፋ አደጋ] ላይ ብእንሆንም ቅሉ፡ የኢትዮጵያ እጣፈንታዋ፡ ጭራሽእንኡ መፍረስ ይሆን አለ ብለን አንሰጋም። በፍፁም! በ የከፋ አደጋ'ው ሳቢያ፤ በ ሰው ህይወት፣ በንብረት፣ በስነልቦና፣ በታሪክ፣ በቅርስዖችአችን እና በጊዜ ላይ እምይአደርሰውን ውድመት፤ ለመቀልበስ እና ለማቅለል ይቻል ዘንድ፡ ኢትዮጵያን እሚል ሁሉ፡ በ እሚመጥን መልኩ መደራጀትን መታጠቅን መመካከርን መፋለምን ሊያውቅበት የግድ ነው። በተለይ ዐማራ፤ ለነገ እንዲቆይ የእምይደረግ የጎልውና ጉዳይ ሊኖርህ እንደእማይገባ፡ አምነህ ልእትቀበል የግድ ነው! ትክክል። የ ኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከገባበት ሰመመን ነቅቶ፡ ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ እና ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ — ሃገርን እና ሕዝብን ከጥፋት መታደግ፤ ግዴታው መሆኑን ዐምኖ መቀበል ይኖርበት አለ።

ጦርዕነትኡ የ ጎሣ-ፖለቲካ ውጤት ነው። እናም፤ የ ጎሣ-ፖለቲካን እና ኤትኒክ ፌደራሊዝምን በ ማጥፋት፣ ከተገንጣዮች በስተቀር ሁሉን-አቀፍ ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ጉባኤ በ ማካሄድ፡ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት በ ማቋቋም፣ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገመንግሥት በ መቅረፅ እና ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት በ መመሥረት፡ ህልውናችንን ከአደጋ ቅርቃር ውስጥ ፈልቀቀን ለማውጣት እና፤ አስተማማኝ ጤናማ ህይወት ማጣጣም እምንእችልበትን ኢንቫይሮንመንት መፍጠሩን ልእንአውቅበት የግድ ነው። ብልፅግና፤ የ ስልጣን ቦታውን እስኪያዘ ድረስ፡ ከ አንድ የ መንግሥት አካል እሚጠበቅበትን ስልጡን ሃላፊዕነትዖች እና ግዴታዖች ሁሉ በአግባቡ መፈፀም፡ በአግባቡ መተግበር ይኖርበት አለ። የሃገርን ዳር-ድንበር መጠበቅ እና የ ሕዝብን ሰላም እና መረጋጋት ማስፈን፤ ቀዳሚ እና ዋና ተግባርዖቹ መሆንአቸውን በፍፁም መዘንጋት አይኖርበትም። በቅጥፈት፣ በሽንገላ፣ በሸፍጥ፣ በዕብሪት እና በኢትዮጵያ ጠላትዖች መገዛትአችን — ያብቃ! እንደ አለመታደል ሆኖ፤ ለ ህወሓት መራሽኡ ኢህአዴግም ሆነ ለ ኦዴፓ-ኦነግ መራሹ ኢህአዴግ ይህ ሊገባቸው አልቻለም። ለ 30-ዓመትዐት ያህል ይ-እንን ማድረግ በ አለመቻልአቸውም፤ ከባድ ሃገርዓዊ ግፍዖች እና ወንጀልዖችን እንዲፈፅምኡ ዳርጐአቸው አለ። እናም – ዛሬም፤ ህወሓት ኦነግ እና ብልፅግና፡ ከ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳረ ራስአቸውን እንድይአገልሉ እና ራስአቸውን እንድይአከስምኡ፡ አበክረን ስእንእጠይቅ፡ ልመና ሳይሆን፡ ግዴታ መሆኑን እየአስገነዘብንአቸው'ም ጭምር ነው!

በመጨረሻም

ትርጉም የ አለው ለውጥ ዐይተን፤ ሀገራችንን ከመፍረስ እና ሕዝብአችንን ከሰቆቃ እና ከዕልቂት ለማዳን፡ መፍትሄው ግልፅ ነው። ጦርዕነትኡ በ አስቸኳይ በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት እንድይጠናቀቅ ይደረግ። ይ-ህ እማየቻልበት አንድአችም አስአማኝ ምክንያት ሊኖር አይችልም! በመቀጠልም፤ ብልፅግና [በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ] የ ሕዝብን ስልጣን ለ ሕዝብ ይአስረክብ። ይህ-እንን ስእንዕል፤ በባህር-ማዶ ሰውዖች የተለቃቀሙ ግለሰብዖችን፡ የሽግግር መንግስት ብሎ ሰይሞ፡ ከ ዲሲ አራት-ኪሎ፡ ከ ካርቶን በተሰራ አውሮፕላን ጭኖ፡ ጫንቃችን ላይ ለመጫን እሚደረጉትን ተደጋጋሚ ጥረትዖች፡ እንደእምንአወግዝ ደግመን ግልፅ በማድረግ ነው።

እኛ የ እምንፈልገው፤ [ሁልአችንንም] የ እየ እንድ-አንድኡን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ተወካይዖችን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን የ አካተተ፡ ሃገርዓዊ የ ዕውነት አፈላላጊ እና የ ዕርቅ ሂደትን በመተግበር፡ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት እንድይመሰረት ነው። ስልጡን ሰላምዓዊ በሆነ እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ፤ ተግባርዓዊ እምይሆን፡ በሽተኛ ፖለቲካችንን እምንአርቅበት ሂደት ተግባርዓዊ እንድይደረግ ነው፡ እኛ እምንፈልገው።

የሽግግር መንግስቱ፤ በዋናዕነት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ያስከብር፣ የሕዝብዋን ሰላም እና መረጋጋት ያስፍን፣ የ ሁሉንም ተቋምአት ተግባር በሃላፊዕነት ይምራ፣ እምይቀጥልኸውን የ ኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበት'ን ምርጫ – ፍትህዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ እምይአስፈልጉትን ተቋምዓዊ ለውጦች ተግባርዓዊ ይአድርግ። ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ኢትዮጵያዊ ህገመንግስት ይቅረፅ። እንደ አዲስ በእሚቀረፀው ህገመንግስት ውስጥ — አለመረሳቱን ብቻ ሳይሆን፤ ጎልቶ መታየቱንም ጭምር እርግጠኛ ልንሆን ከእሚገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳይዖች መሃከል፤ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ ተገድበው፤ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ይደረግ። በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እሚያስችል ድልዳል ይካተት። ሰው በሰውእነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እሚያገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግስት ይመስረት።

ብልፅግና፤ በ እዚህ ሂደት ውስጥ እንድይካፈል ዕድል ቢሰጠው አንእቃወምም — በ የ መንግሥትዕነት ቦታው ላይ በመሆንኡ።

ነገር ግን፤ ብልፅግና፡ ይህ እንን ምክረሃሣብ በ ቅንዕነት ወስዶ፡ ተግባርዓዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ከአልሆነ — የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ኢትዮጵያን እና ሰውዓዊ ህልውናውን ለመጠበቅ ይአስችለው ዘንድ፡ እስከዛሬ ለ ብልፅግና ይሰጠው የነበረውን ድጋፍ አቁሞ፡ ሌላ አማራጭ መንገድ ሊከተል ይገባ አለ። ለ ኢትዮጵያ-ያለ ይስማ።

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እስከ እምንገናኝ –

# የ ብዕር-ስም፤ አርማ እና አከአሄድአችን

ታኅሣሥ ፪ሺ፻፲፬ ዓ.ም ‖ ዲሴምበር 2021

***ርዕስ-አንቀፅ***:- *ትርጓሜ ላይ ልዩዕነት መኖሩ የተጠበቀ ሆኖ፤ ስለ [ኢኮሲስተም] በተነሳ ቁጥር፡ በ ዮኒቨርስ ውስጥ [ህይወት የሌላቸውም ሆኑ ህይወት ያላቸው] ፍጥረትዐት፡ ለ እየራስአቸው ትርጉም/አመቺዕነት ባለው መልኩ፡ ከ እየ አከአባቢአቸው ጋር [ከምዩንኬት] እንደ እምይአደርጉ: ይገመትም ይትአወቅም አለ። ለዛሬ፤ ህይወት የሌላቸውን ትተን፣ ህይወት ካላቸው ውስጥም ዕፅዋትን ትተን፣ ከእንስሣትም የ[ሰው] ልጅ ላይ ብቻ ስናተኩር – ከምዩንኬት ማድረግ [በ እኛ ሂሣብ "መንአበብ" እንበልኸው ለዛሬ] በ ህይወትአችን ውስጥ፡ ግዙፍ ቦታ ይዞ እንአገኘዋለን። እንደ እምታውቁት፤ የ መንአበብያ መንገድዖች፡ በሁለት ጎራ ሊመደቡ ይቻላል። <u>ጎራ አንድ</u> – ቃልን እና የ ቃልዐት አገባብ ስርዐትን በመጠቀም በአለመጠቀም እምይተገበርኸው መንአበብ ሲሆን፡ <u>ጎራ ሁለት</u> ደሞ – ቃል አልባ የ[ሰው]ዕነት መገለጫዎችን በመጠቀም በአለመጠቀም፡ እምይፈጠረውን መንአበብ ያካትታል። ጎራ አንድ፤ በንግግር በፅሁፍ በምስል — ጎራ ሁለት ደሞ፡ በ አካልዓዊ-ጥቆማ የፊት-ገፅታ የድምፅ-ቃና እና የመሳሰሉትን በመጠቀም ይቀርባል። ጎበዝ፤ የዛሬው ትኩረትአችን እምይሆነው ፅሁፍ ላይ ሆኖ – ከ ፅሁፍም ስለ ጸሓፊው/ደራሲው የ ስም አጠቃቀም — በተለይም ስለ [የ ብዕር-ስም] አጠቃቀም ላይ ነው። ፅሁፍ፤ ፊደልዐትን ብቻ ሳይሆን [አርማን ምስልን ጨምሮ] ተጨባጭ ሁኔታዎችን እና ክስተቶችን ቁልጭ-አድርጎ እምይአሳይ እምይአሰማ እምይተገብር፡ የ ራሱ የሆነ እስትንፋስ እና ኀሊና የአለው፡ የ ህያውዕነት ያክል አቅም የአለው፡ የበለፀገ የ መልዕክት መለዋወጫ፡ የ መንአበብያ መሣሪያ ነው። ፅሁፍ ሲነበብ እምይፈጠሩ ብዙ ዓይነት ስሜቶች፣ እምይተላለፉ መልዕክቶች እና በ ዓይነ-ኅሊና ውስጥ እምይቀረፁ ሪል-ላይፍ ተውኔቶች አሉ። ፅሁፍ፤ በ አጋጣሚ በመንገድ ላይ እንደ እምይታይ ክስተት፣ የመድረክ ቅንብር ወይም ሲኒማ – ስሜትን በመቀስቀስ፡ ጥልቅ መንአበብን ሊፈጥር ይችላል። ፅሁፍ ሲነበብ፤ መልዕክቱን እንደወረደ ከመረዳት ባሻገር፡ [ምን ለምን እንድየት ማን መቼ] እሚሉ ጥያቄዎችን በመጫር እና <u>የክስተቱን መንፈስ</u> በመፈተሽ፡ ክሪቲካል-ቲንከር እንድእንሆን ያግዘናል። ታድያ፤ ለምን ይሆን ጸሓፊዎች/ደራሲዎች ይህ-እንን ግሩም/ድንቅ/መለኮትዓዊ/ጥልቅ/ውብ ስራ፡ መደበኛ ስማቸውን ተጠቅመው ከማሳተም ከማጋራት ይልቅ፡ አልፎ-ልፎም ቢሆን የ ብዕር-ስም መጠቀምን እምይመርጡት?? [ዌ....ል] – የብዕር-ስምን መጠቀም ከተጀመረ፤ ዘመንዐት ተቆጥረዋል። አዲስ ነገር አይደለም። ብዙ ተዐዋቂ ጸሓፊዎች/ደራሲዎች፤ የብዕር-ስም(ዖች) በመጠቀም አንድ-አንድ ስራዎችአቸውን ያጋራሉ። በብዕር-ስም መጠቀም፤ ህግ መጣስ አይደለም – ህግዓዊ መዛግብት ላይ በ ብዕር-ስምአችን እንፈርም ካላልን በስተቀር! እኛ፤ እንዲያው የ አጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ፡ የ አዳራሽ ዩኒቨርስ ፈጣሪ አድራጊ ስለሆንን፡ አዳራሽዓዊያን እንደ እምትአውቁት፡ ብሏግአችንን እምንፈርመው፡ [አዳራሽ እና አኪዬ] እሚሉትን የብዕር-ስምዖችአችን በመጠቀም ነው። ትክክል። ከ አንድ-በላይ የ ብዕር-ስምዖችን መጠቀምም የተለመደ ተግባር ነው። ስለ የ ብዕር-ስም ጠቀሜታ ሲነሳ — ከ አንድ-በላይ ገፀ-ባህሪይን ለማንፀባረቅ፣ ወጣ የአሉ የፅሁፍ ስራዎችአችንን ከ መደበኛ/ፕሮፌሽናል ህይወትአችን ለመለየት፣ በ ሙሉ-የነፃዕነት-ስሜት ለመፃፍ፣ ወድቆ ለመነሳት፣ ከ አንድ-በላይ የሆኑ ጸሓፊዎች የጋራ ስራቸውን በ አንድ ስም ለማጋራት እና ፅሁፍአችንንም ሆነ ራስአችንን በ መደበኛ ህይወትአችን ሳቢያ ሊፈጠሩ ከ እሚችሉ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ የ መንአበብ ዝንባሌዎች [ባያስ] ለመጠበቅ ሲባል – ተግባር ላይ እንደሚውል መጠቃቃሱ በቂ ነው። አዎን፤ የብዕር-ስም መጠቀምም ሆነ አለመጠቀም – የግል ምርጫ፡ የግል ውሳኔ ነው። ከ ፅሁፍ ስራዎችአችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ ሊገኙ እምይችሉ ጥቅማጥቅሞችን ሊያሳጣን መቻሉ የተጠበቀ ሆኖ በምንም መልኩም ቢሆን፡ ከ የብዕር-ስም ጀርባ በመደበቅ፡ ነውር ወንጀልም ሆነ ሃጥያት መስራትን አምርረን ልንፀየፍ ይገባናል። ግለሰብዖች ላይ ሳይሆን፤ [<u>የ ክስተትዖች መንፈስ</u>] ላይ በማተኮር፡ እንደ አስፈላጊዕነቱ እየታየ፡ ጠንከር [አልፎ አልፎ በጣም ጠጠር] የአሉ ገላጭ ቃልዐትን መጠቀም፣ ጠንከር ጠጠር የአሉ የአገላለፅ ሀረግዖችን መጠቀም እና በ ጨዋ ደንብ ምሬትን ግሥጻን ማንፀባረቅ ግና – ክፋት አለው ብለን አንዐምንም። አንባቢያን፤ ትኩረትአችንን ከ የ ጸሓፊው ማንዕነት ይልቅ፡ በ ፅሁፉ ላይ ብእንአነብር – በ ማንበብ እሚገኘው ደስታ፣ ዕርካታ፣ እምይዳብረው ዕውቀት እና እምይተረፈው ጊዜ፡ በምንም ያህል ንዋይ እምአይገዛ [ጸጋ] ነው ብለን ነው፡ እኛ የ እምንዐምነው። የ ትውልድዐችን የ ዲጂታል-ቴክኖሎጂ ውጤትዖች፤ የብዕር-ስም አጠቃቀምን እና አነንምቲ'ን፡ እንደማንአቸውም የእየ ናኖ-ሰከንድ'ዋ ስራዎችአችን፡ ተጠያቂ ሊያደርጉን እንደእሚችሉ፣ የሞራል የኀሊና ጉዳይም ሊይአስነሱ እንደእሚችሉ እና [በ ፅሁፍ መንአበብን] የመሰለ ውብ ተሰጥዖ፡ [አዋኪ አፍራሽ አጥፊ] ለሆኑ ዕኩይ ስራዎች ጠቀሜታ ላይ እንድይውል ሲደረግም ሳትአስተውሉ አትቀሩም ብለንም እንዐምን አለን። ያ-እንን ከአልን እንግዲህ – እናንተን፤ ከቤተሰብ ከጓደኛ እና ከ ወዳጅ-ዘመድ ጋር፡ በ ርዕስ-አንቀፅአችን ላይ ፊሎሶፊካል ውይይት ታደርጉ ዘንድ እያበረታታን፡ ወደ እምይቀጥሉት ርዕስዖችአችን እንእሻገር።*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

የሃገርዐችንን ዉሎ እና አዳር፤ 24/7/365 ስለ እምንእከታተል፡ እንዴት ናችሁ ስንል፡ እንደ የ ራስ-ሰው እንደ ወገን፡ በከበደ ስሜት ውስጥ ተውጠን — አይዞን! ማለትአችንም ጭምር ነው። በ ሕዝብአችን ጥረት እና በፈጣሪ ዕገዛ፤ ይህ ክፉ ቀን እንደእምይአልፍም እርግጠኛ መሆናችንን ገላጭ በሆነ ፍፁማዊ መንፈስ።

ያ-እንን ምኞትአችንን፤ በ አንድ ንጋት ለማፍጠን እንእችል ዘንድ ግና፡ በበለጠ መልኩ መቁረጥን መደራጀትን መትአጠቅን መመካከርን እና መፍአለምን፡ ልንአውቅበት የግድ ነው እና – እጅጉን እንእበርታ! ብዙ ብዙ በአግባቡ መስመር ሊይዙ እምይገባቸው ግፍዖች ተፈጽመዋል እና፤ ዝግጅታችን መረር ረዘም ያለ ጊዜን እሳቤ በማድረግ ሊሆን እንደሚገባው መጠራጠር የለብንም።

እንደ የተለመደውም፤ በሰሞነኛ ሁኔታዎች ላይ በ ማውጠንጠን፡ በ ማንአቸውም የኢትዮጵያ ጉዳይ [ያ-ገ-ባ-ና-ል] በ እሚል ንፁህ የ ወገንዓዊዕንት አቲትውድ፡ የ አዘጋጀንአትን መጣጥፍ ይዘን፡ በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበናል። የሌለ ጊዜአችሁን አጠጋግታችሁ፡ ስለ እምታነቧትም ምስጋናችን የላቀ ነው።

እናም፤ [አብረን እንቁይ] – የምንጊዜም ግብግቦችን ነው።

ባለፉት አንድ-ሁለት ወርዐት፤ ሃገርቤትም ሆነ ባህር-ማዶ ያለው፡ ከልብ ኢትዮጵያን እምይል ወገን ነው ብለን የወሰድነው የሕዝብ ማዕበል – ያሳየው ህብረትም ሆነ አንድዕነት፡ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያን እምይበጅ ውጤት የአመጣ እንደሆነ ሆኖ ተሰምቶናል።

አዎን፤ ቢያንስ የውጭ ጣልቃ-ገብዕነቱ እና ጫናው፡ ለ ጊዜውም እንኳን ቢሆን፡ [ግራ እንዲጋባ] እና አደብ የመግዛት አዝማምያ እንድይአሳይ አስገድዶታል ብለን እንአስባለን። ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለንም እንዐምን አለን።

የውጭ ጣልቃ ገብዕነቱ እና ጫናው፤ ቀለል የማለቱ አዝማምያ፡ ሁሉ ነገር አልጋ-በአልጋ ሆኗል እሚል ድምዳሜ ላይ እንድአይአደርሠን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የተፈጠረውን ፖቴንሻል፤ ከ ግለሰብ ዐምላኪዕነት ግግርት ተላቅቀን፡ ሁለዕንተንዓዊ መሠረትዓዊ ችግርዖችአችንን፡ ከ ስርአቸው መንግለን፡ ዳግም እንድአያንሰራሩ አድርገን ለማጥፋት፡ ለ ኢትዮጵያ አና ለ ኢትዮጵያዊያን የጋራ ጠቀሜታ ብቻ እንአውለው ዘንድ፡ የትውልድአችን አደራ መሆኑን፡ እንደ [ስልጡን] ሕዝብ በትክክል መገንዘብ ይጠበቅብናል።

ያለንባቸው መራራ ኹነቶች — ጭልጥ የአለ ቅጥፈት ላይ የተመሠረተ የጎሣ-ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ አደረጃጀት፣ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጐጥ ላይ የተመሠረተው ዕኩዩ ኤትኒክ-ፌደራሊዝም፣ ተቋዋምዐት ሁሉ በገዥው-ቡድን ግለሰቦች ስለእሚነዱ እና አነእኝህን ሁሉ ተከትሎ ለ 30–ዓመትዐት ያህል ያለማቋረጥ እየተከሠተ ያለው – ማንዕነት ላይ መሠረት የአደረገ ጄኖሳይድ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፣ “መጤ” በመባል ለመፈናቀል ለበሽታ ለረሃብ ለአሉታዊ የስነልቦና ጫና መጋለጥ፣ ኢትዮጵያን በሁለዕንተንዓዊ መልኩ የማሣቃየት የተቀናጀ ዘመቻ እና ገዥው-ቡድን በቀዳሚዕነት መጠቀስ የ አለበት የችግሯ ሁሉ ቀፍቃፊ አድራጊ ፈጣሪ የመሆኑ ዕውነታን ሁሉ ያካትታሉ። በ ዕንቅርት ላይ ጆሮ-ደግፍ እንዲል የ ሃገርአችን ሰው፤ የለየለት ጦርዕነት ላይ መሆንአችን፡ ችግርዖችአችንን የበለጠ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑም አስገድዷቸዋል።

ጎበዝ፤ አንድ ልንዘነጋው እምአይገባን ቁምነገር አለ። የውስጥ ችግርዖችአችንን ማቃለል ካልቻልን፤ እየረገበ የመጣ የመሰለን የውጭ ጣልቃ-ገብዕነት እና ጫና — እንደ እምይአገረሽበት። እናም፤ ለዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት ጉልበት ይሆነን ዘንድ፡ ወደ ተግባር ተለውጠው ማየት ከ እምይገቡን ክሪቲካል ስኬትዖች ውስጥ፡ የ እየ አንድ-አንዱን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ተወካይዖችን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን የ አካተተ፡ ሃገርዓዊ የ ዕውነት አፈላላጊ እና የ ዕርቅ ሂደትን መተግበርአችንን፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት መመሥረትአችንን፣ አዲስ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት መቅረፅአችንን እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ የ ኤትኒክ-ፊደራሊዝሙን እንዲሁም በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረቱትን ግርግሞች በጥንቃቄ ማፍረስአችንን ሁሉ — በጋራ እርግጠኞች ሆነን መገኘት ይኖርብናል።

አርማ

ከፍ ብለን በ ርዕስ-አንቀፅአችን ላይ ጠቀስ እንደ አደረግነው – አርማ፤ ልክ እንደ ፅሁፍ፡ ተጨባጭ ሁኔታዎችን እና ክስተትዖችን ቁልጭ-አድርጎ እምይአሳይ እምይአሰማ እምይተገብር፡ የ ራሱ የሆነ እስትንፋስ እና ኅሊና የአለው፡ የበለፀገ የ መልዕክት መለዋወጫ፡ የ መንአበብያ መሣሪያ ነው። ይህ-እንን እምንዕለውም፤ በቅርቡ፡ ከ 25 በላይ በሆኑ በ ዓለም-ዙርያ በ እምይገኙ ከተማዎች ውስጥ የተደረጉ እና አሁንም በመደረግ ላይ የአሉ፡ ለረዥም ጊዜ ተጎድቶ የቆየውን ስሜትአችንን ቀና የአደረጉ የቀሰቀሱ፡ የ [ኢትዮጵያን አትንኩ] መንፈስ አንፀባራቂ፡ ደማቅ ሕዝብዓዊ ሰልፍዖችን እና እንደ ምንጊዜውም ያለመሰልቸት አብሮ በ ሰልፍዖቹ ላይ የተገኘውን፡ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለምዐትን እምይአከአትተው ንፁሁን የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዓላማችንን፡ በ ዓይነ-ኅሊናችን ውስጥ ቀርፀን ነው። አርማችንን!

ሰንደቅ-ዓላማችን፤ የሃገር እና የሕዝብ ማንዕነትን፣ ታሪክን፣ ዕምነትን እና ራዕይን አንፀባራቂ፡ የወል ቋንቋችን እና የጋራ መገለጫችን ነው። ለ እዚያም ነው፤ በጦር ሜዳ፣ በባህር ላይ ጉዞ፣ በ አየር ላይ በረራ፣ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ በ ትምህርት ቤቶች እና በ ሌሎች ተቅዋምዐትም ጭምር፡ በክብር በኩራት በፍቅር እንድይውለበለብ እምይደረገው። ሰንደቅ-ዓላማችን፤ በውስጡ ከያዛቸው መሠረትዓዊ ቁምነገሮች አኳያ፡ በ ቅን ኢትዮጵያዊያን ስነልቦና ውስጥ፡ እምይፈጥረው ስሜትዓዊ ማህተም፡ ታይቶ እምአይጠገብ፣ ተነብቦ እምአያልቅ፣ ትውልድ ተሻጋሪ፡ ድርብ ድርብርብ የጀግናዕነት የነፃዕነት የኩሩዕነት የ አልገዛምባይዕነት ትርጉዋሜን የተላበሰ፡ ለ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን፡ ለአፍሪቃዊያን በሙሉ ኩራት የሆነ፡ ሲገጥሙለት ሲያዜሙለት ሲዋቡበት ሲያነግቡት ሲያውለበልቡት፡ ኢትዮጵያዊ [ሰው] ነኝ የ እሚልን ሁሉ በፍቅር [ኢሞሽናል] እምይአደርግ፡ የ አያት ቅድመ-አያቶቻችን ጥልቅ ስራ ሆኖ ነው — ለ እኛ እምይታየን።

አዎን፤ አሁንም [በ ህገ-መንግሥት ተብየውም እንኳን ቢሆን] የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔርዓዊ ሰንደቅ-ዓላማ፤ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለምዐትን ብቻ የተላበሰው ነው። መንግሥትዐት በተቀያየሩ ቁጥር፤ ሰንደቅ-ዓላማችን መሃል ላይ እምይለጠፉት ማህተም መሰል ነገሮች፡ የሕዝብ አይደሉም። መሃል ላይ ተለጥፈው የ እምንአይአቸው ነገሮች፤ በጊዜው የ መንግሥትዕነት ቦታው ላይ ለተቀመጡ ሰዎች፡ የባለስልጣንዕነት ማህተምአቸው ወይም እንደ [የሃገር የ መከልአከያ ሠርዐዊት] የአሉ ታላላቅ ሃገርዓዊ ተቅዋምዐት ዐርማዎች ብቻ ናቸው። እነ-እዚህ መሃል ላይ እምይታዩት ምልክትዖች፤ ከቤተመንሥት ውጭ ወይም ከ ተቅዋምዐቱ ግልጋሎት ውጭ፡ ሊታዩም ሆነ፡ በምንም መልኩ ሌላ ጠቀሜታ ላይ ሊዉሉ እሚገባቸው አይደሉም። በፍፁም!

አዎን፤ የኢትዮጵያ ልጆች፡ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ-ዓላማችንን እየአውለበለቡ ለ ሕዝብዓዊ ሰልፍ በወጡ ቁጥር፡ ለእኛ እምይሰሙን ድምፅዖች፡ ሰልፈኛው እምያሰማቸው መፈክሮች ብቻ ሳይሆኑ – ከሥስቱ ህብረቀለምዐት ውስጥ ፈንቅሎ እምይወጣው፡ በተደጋጋሚ [ኢትዮጵያን አትንኩ] እሚል “ህያው” መለኮትዓዊ ኃይል የተጎናፀፈ ድምፀ-ነጎድጓድ — ከአድማስ እስከ አድማስ ሲይአስተጋባም ጭምር ነው።

አከአሄድአችን

አከአሄድን ማስተካከል፤ ከ መውደቅ ያድናል። ደንበር-ገተር እየአለ እሚራመድ ሰው፤ ሲወድቅ-ሲነሳ፣ ሲላላጥ ሲያነካክስ፣ ሲሰበር-ሲጠገን፡ ወቅትዐት ተፈራቀው ዘመናት ይቆጠራሉ። ጊዜው ደርሶ፤ የከፋ ነገር አጋጥሞት፡ እስከ ወዲያዕኛው እሲኪሰንአበት ድረስ።

ሃገርአችንን ለመጠበቅ እና የ ሕዝብአችንን ማህበረሰብዓዊ ህይወት ስልጡን በሆነ መልኩ ለመምራት እምንእከተለው መንገድ እና አከአሄድአችን ሁሉ የተስተካከሉ አይደሉም። ደንበር-ገተር እምይለውም አንኳን አይገልፅአቸውም። አዎን፤ በ በሽተኛ ፖለቲካችን ሳቢያ፡ እጅግኡን የመረረ ህይወት እያስተናገድን በተደጋጋሚ ስንወድቅ-ስንነሳ፣ ስንላላጥ ስናነካክስ፣ ስንሰበር-ስንጠገን፡ ወቅትዐት እየተፈራቁ ዘመናት እየተቆጠሩ ነው።

እየተደረገ ያለው የለየለት ጦርዕነት፤ እንዳይጀመር መደረግ ነበረበት። ያ-አልሆነም። ከተጀመረ በሁዋላም፤ ሰላምዓዊ የማህበረሰብአችን አካል እንዳይጎዳ፡ ጥንቃቄ መደረግ ነበረበት። አልተደረገም። እንድይአውም፤ ሆነ ተብሎ፡ ፖለቲካ ምኑም ያልሆነው ሰላምዓዊ ማህበረሰብአችንን ለመጉዳት ለማማረር ሆነ ተብለው የተሠሩ፣ እየተሰሩ የአሉም ግፍዖች አሉ — በ ተገንጣይ ወንበዴዎች ብቻ ሳይሆን፡ በ መንግሥት አካልዐትም ጭምር! ትክክል። በተወሰነ ቦታ ተገድቦ በአጭር ጊዜ ውስጥ፤ መጠናቀቅ የነበረበት ጦርዕነት፡ ወደ ተጎራባች ክፍለሃገርዐት እንድይዛመት ተደርጎ፡ በ ተዋጊዕነት ሊሳተፍ እምአይገባው የ ማህበረሰብአችን አካል ተገድዶ እንድይሳተፍበት ተደርጎ – በየትኛውም አገዛዝ ዘመን ቢሆን፡ ከ ፖለቲካ ፍጭቶች አንዲት ቤሳ-ሳንቲም አግኝቶ እምአያውቀው ንፁሁ ዜጋ፡ የአለ ዕዳው አበሳውን እያየ፡ እያለቀ ነው።

የ ሃገር መከላከያው፤ አጥፊ አፍራሽ ለሆነ ወንበዴ ከተማዎችን እየለቀቀ መፈርጠጡን — ሽንፈት ማለታችሁን ትታችሁ፣ ክህደት ማለታችሁን ትታችሁ፣ ሽፍጥ ማለታችሁን ትታችሁ፡ እንደ ተመራጭ የውትድርና ስልት አድርጋችሁ ውሰዱት ሲል ይደመጣል። ለምን?? እ--ኮ ለምን??!!

እየሆነ የአለው እኮ የ ቪዲዮ ጌም አይደለም!!!! መከላከያው አንድ መንደር ለወንበዴ አስረክቦ በፈረጠጠ ቁጥር፤ ክቡር የ[ሰው] ልጅ ነው እንደ ቅጠል እምይረግፈው – ለ ሰቆቃ ለመፈንአቀል ለመሰደድ ለመርዐብ ለመጠምዐት ለመትዐረዝ እና ለህመም እምይጋለጠው። ሃብት-ንብረቱ እንስሳቱ ሳይቀር እምይወድመው። ህይወቱ እምይመሰቃቀለው።

አዎን፤ መከላከያው አንድን [ደጀን የተባለለት] መንደር ለወንበዴ አስረክቦ በፈረጠጠ ቁጥር፡ በ 30-ዓመትዐት ሳይሆን በ ብዙ እጥፍ ድርብ ዓመትዐት፣ በ ቢልየን ሳይሆን በ ትሪልየን እምይቆጠር የሃብት የንብረት የ ተቁዋምዐት ወድመት ነው በ ህወሓት ወንበዴዎች እንዲፈፀምበት የተደረገው። መከላከያው አንድን መንደር ለህወሓት አስረክቦ በፈረጠጠ ቁጥር፤ ታሪክ እየቆሸሸ፡ የአሁኑን የእኛን ትውልድ ድርሻ ብቻ ሳይሆን፡ ህወሓት ገና ከ እምይመጣው ሁለት ሦስት ትውልድ — ህይወት ሰርቃ ነው፡ ድራሹን ያጠፋችው፡ ያወደመችው።

ይህ ሁሉ መሆኑን እየሰማን እየዐየን፡ መከላከያ የሰራውን ሃገርዓዊ ክህደት እና ሽፍጥ — እንዴት እንዴት [ከ ሚሊተሪ ሳይንስ ጀርባ ተደብቃችሁ፤ በ ስልታዊ ማፈግፈግ ስም] እንደ ዋዛ ቁጠሩት ትላላችሁ??!!

ያ በ እንዲያ እየ አለ፤ በቅርቡ፡ የ ሃገር መከላከያው የ አከአሄድ ለውጥ በማድረግ [ከመከላከል ከማፈግፈግ] ይልቅ፡ የ ማጥቃት ዕርምጃዎችን እየወሠደ እንደ አለ እምይጠቁሙ እንቅስቃሴዎችን እየሰማን እየአየን እየአለን፤ ገና ምኑም ሳይያዝ — በቃ ምዕራፍ አንድን በአሸናፊዕነት አጠናቀናል ተብሎ፤ ሌላ ግራ የገባው ወሳኔ ላይ መደረሱን ሰማን። ለ ምዕራፍ ሁለት እንመለሳለን እሚል ነገርም ጨምረውበታል፡ ወሬአቸው ውስጥ። ምዕራፍ አንድ ምን እንደነበረም ሆነ ምዕራፍ ሁለት ምን እንደእሚሆን እሚያውቀው፤ ሁሌም አይናችሁን ተጨፈኑ እና ልግዛችሁ እምይለው፡ በ ገዥው-ቡድን እምይመራው መንግሥት ተብዬ ብቻ ነው።

እዚህ እኛ አካባቢ ያሉ ሰዎች አንድ አባባል አላቸው። [ኢፍ ዩ ዶንት ላይክ ዘ ሩልስ ዶንት ፕሌይ ዘ ጌም] እምይል። እናም እኛ፤ ስለ ገዥው-ቡድን ምዕራፍ አንድም ሆነ ምዕራፍ ሁለት፡ ደንታ የለንም። እንደ እዚያ የአለ ጨዋታ መጫወትም አንፈልግም። እኛ ሃገርዓዊ ፍልሚያው በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት መጠናቀቁን እምንመዝንበት የራስአችን መስፈርት አለን።

እኛ ኢትዮጵያ አሸነፈች እምንዕለው – ህወሓትን ኦነግን እና መሠል ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጅቶችን ከሃገርአችን የፖለቲካ ዐውድ አስወግደን እንድይከስሙ ስናስገድዳቸው፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ኤትኒክ-ፌደራሊዝም እንድይፈርስ ስናደርግ፣ የእየ አንድ-አንዱን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ተወካይዖችን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ያካተተ፡ ሃገርዓዊ የዕውነት አፈላላጊ እና የዕርቅ ሂደት ስንተገብር፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት ስንመሠረት፣ ተገንጣዮች እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ ተገድበው አዲስ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት ስንቀረፅ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ ኤትኒክ-ፊደራሊዝሙ እንዲሁም በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረቱት ግርግሞች በጥንቃቄ መፍረሳቸውን በጋራ እርግጠኞች ስንሆን ብቻ ነው።

በ እኛ ዕምነት፤ መንግሥት ተብዬው፡ በስልጣን ላይ አስካለ ድረስ፡ ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ አስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅቶች እና ዕርምጃዎች ተግባራዊ እንድያደርግ ታሪክዓዊ ግዴታው ነው። ይ-ህ ዕምነትአችን ዕውን ይሆን ዘንድ ግና፤ መንግሥት ተብዬው፡ መሠረትዓዊ ችግሮችአችንን ለማቃለል ስርነቀል ለውጥ ማስፈለጉን በቁርጠኝዕነት አምኖ መቀበል እና ውስጡን ማፅዳት ብቻ ሳይሆን፡ ዙሪያ-ገጠም መሠረትዓዊ ጉዳዮችን በ ቅንዕነት ማስተናገድንም ጭምር ይጠይቀዋል። እስከዛሬ ረብ ያለው ስኬት ያላየንበት ምክንያትም፤ ገዥው-ቡድን 1) ቁርጠኝዕነት ስለሚጎድለው 2) ውስጡን ማጥራት ባለመቻሉ እና 3) ቅንዕነት ስለእምይጎድለው ጭምርም ነው።

*<u>ቁርጠኝዕነት ስንል፡-</u> መሠረትዓዊ የ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር የጎሣ-ፖለቲካ እና የ ኤትኒክ-ፌደራሊዝሙ መሆኑን፤ እናም መቀየር እንዳለባቸው፣ ህወሓት ኦነግ እና ሌሎች ተገንጣይ ድርጅቶች ከፖለቲካው ምህዳር በህግ መገደብ እንዳለባቸው እና መክሰም እንደእሚኖርባቸው፣ ሃገርዓዊ የዕውነት አፈላላጊ*

*እና የዕርቅ ሂደት መተግበሩን፣ ኢትዮጵያዊ የሽግግር መንግሥት መመስረቱን፣ አዲስ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግሥት መቀረፁን እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ ኤትኒክ-ፊደራሊዝሙ እንዲሁም በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረቱት ግርግሞች በጥንቃቄ መፍረሳቸውን በጋራ እርግጠኞች መሆን እንደሚገባን አምኖ መቀበልን እና ለተግባርዓዊዕነትአቸውም እንቅፋት አለመሆንን ማለትአችን ነው። መደጋገማችን፤ ነሆለል ጭፍን የ ገዥው-ግንባር ደጋፊዎችን ቢያነቃልን ብለን ነው እና — ቻሉት!*

ገዥው-ቡድን በተደጋጋሚ የዘረዘርናቸውን የቁርጠኝዕነት መመዘኛዎች እምአያምንባቸው መሆኑን (ለአንድ ክልል ስንል ህገ-መንግስቱን አንቀይርም ያለውን ያጤኗል) እና እስካሁንም እንቅፋት እየሆነ አንዳለ ግልፅ ነው። ገዥው-ቡድን ስር-ነቀል መሠረትዓዊ ለውጥ እንዲመጣ ስለማይፈልግም፤ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ፡ ኢትዮጵያ በምንም መልኩ አሸናፊ ልትሆን እምትችልባቸው ስኬትዖች ዕውን ሆነው ልናይ አንችልም።

ያ-ም ሆኖ ታዲያ፡ ገዥው-ቡድን ጦርዕነቱን በተመለከተ [አካሄዱ ልብ አቁሳይ ቢሆንም ቅሉ] ለኢትዮጵያ እምይበጅ አቋም የያዘ ይመስላል። ምንም እንኳን ለ ራሱ ስልጣን ሲል ቢሆንም፤ ዛሬ የለየለት ጦርዕነት ላይ መገኘቱ አንድ ነገር ነው። [ከ መከላከል ከማፈግፈግ] ወደ ማጥቃት የመሸጋገር አዝማምያውን፡ እኛ ከቁርጠኝዕነት ጋር አጎዳኝተነው በ አወንታዊዕነት አስተናገድነዋል – ተጠናቅሮ እንድይቀጥል መደረግ የአለበት መሆኑን አፅንዖት በመስጠት። የ ባለስልጣናቱ ወደ ግምባር መሄድም ሆነ ወደ አራት-ኪሎ መመለስ ብዙም ትርጉም አለው ብለን አንዐምንም። ዋናው ነገር ህወሓት ከ እየ አንድ-አንዷ ስኴር-ሚትር የኢትዮጵያ ግዛት (ትግራይን ጨምሮ) መጥፋቷን እና ከ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ዐውድ ውጪ እንደትሆን መገደድዋን እርግጠኞች መሆናችን ላይ ነው። ልብ እንበል ጎበዝ፤ ህወሓትን ወንዝ አሻግሮ፡ ጉሮወሸባዬ እንዳይባል በጥብቅ እናስጠነቅቃለን። ኢትዮጵያን አደጋ ላይ መጣል እና ጦርዕነቱን ሰቆቃውን ዕልቂቱን ለዘመናት ቀጣይ እንዲሆን የማድረግ ውሳኔ ማስተላለፍ ማለት ያህል ነው እና!

*<u>ውስጡን ማጥራት ስንል፡-</u> ገዥው-ቡድን ከ ህወሓት በተለይም ከ ኦነግ ሰርጎ ገቦች የጠራ ሊሆን ካልቻለ፤ ኢትዮጵያ አሸናፊ ልትሆን እምትችልባቸው ስኬቶች ዕውን ሆነው ልናይ አንችልም። ችግሩ፤ ገዥው-ቡድን ራሱን ከ ህወሓት ሙሉ በሙሉ ማፅዳት ይቻልዋል ለማለት ብንፈቅድ እንኳ፡ ከ ኦነግ ራሱን ያፀዳል ማለት ግና — ዘበት ነው። ገዥው-ቡድን ማለት ኦዴፓ-ኦነግ ማለት ነውና!*

ገዥው-ቡድን ውስጡን ለማጥራት ቁርጠኝዕነትን እሚጠይቁ ተግባራትን መፈፀም ይኖርበታል። ያ-ኔ ከ ኢትዮጵያዊያን እምያገኘው ድጋፍ በ እጥፍ ድርብ ይገዝፋል። ኢትዮጵያ ታሸንፋለች ሲልም ዕውነታን መሠረት አድርጎ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳይለታል። ያ-ን ዕውን እስከእምያደርግ ድረስ ግና፤ ኢትዮጵያ በምንም መልኩ አሸናፊ ልትሆን እምትችልባቸው ስኬትዖች ዕውን ሆነው ልናይ አንችልም። ይ-ህ መራራ ሃቅ ለሁላችንም ግልፅ ሊሆንልን የግድ ነው። ገዥው-ቡድን "ኢትዮጵያ አሸንፋለች" ሲል፤ ዕውነታው ህወሓትን ከ አራት-ኪሎ ወደላይ ፈቀቅ አድርገናታል ማለቱ እንደሆነ እና ኢትዮጵያን ኢትዮጵያዊያንን እያጃጃለ እንደሆነ ግልፅ ሊሆንልን ይገባል።

*<u>ቅንዕነት ስንል፡-</u> ገዥው-ቡድን፤ የ[ቅንዕነት] ችግር አለበት። ከተፈጠረባት የዛሬ 3-ዓመት ተኩል ገደማ ጀምሮ፡ አንጀት እምይአቆስሉ ድብቅ ስውር ዕኩይ ስራዎቹን እያስተዋልን አለን። ዛሬም፤ ኦነግን እየአጎለበተ፣ ከ ዐማራው ጫንቃ ላይ አልወርድ እያለ፣ ኢትዮጵያን እሚሉ ጋዜጠኞችን እያሳደደ እያሰረ፡ የ ኢትዮጵያ እና የ ኢትዮጵያዊያን ቀኝ-እጅ የሆነውን ቆፍጣናውን ጀግናውን የ አባቱ ልጅ [ፋኖ]ን ዕረፍት እየነሳ የአለው የገዥው-ቡድን — ኢትዮጵያዊዕነት በብዛት እሚጎድለው፡ በፍጥነት መወገድ የአለበት መሠሪ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን ነው እያረጋገጠልን ያለው፡ ማለትአችን ነው።*

ይ-ህ የ ቅንዕነት ችግር፤ መሠረትዓዊ ግድፈት መሆኑንም ነው የ እምንዐምነው። ገዥው-ቡድን፤ ከ እዚህ የ ቅንዕነት ችግር ራሱን ሳያላቅቅ፡ ኢትዮጵያ ታሸንፋለች እምይለውን መፈክር መጠቀም ብቻ፡ ሕዝብን ለማነሁለል ሲል እምይጠቀምበት የ ሞኝ ዘዴ መሆኑን – ከ ልብአችን ኢትዮጵያን ለ እምንል ሁሉ ግልፅ ይሆንልን ዘንድ፡ የግድ ነው።

ጎበዝ፤ የ ቁርጠኝዕነት አዝማምያ እና ውስጥን ማጥራት፡ ዙሪያ-ገጠም ቅንዕነት እና ቀጣይዕነት ካልታከለበት፡ በ ህወሓት ላይ ተገኘ ብለን የገመትነው ድል፡ ሾርት-ሊቭድ እንዲሆን፣ ተረኛው ኦሮሙማ እንዲንሰራፋ እና እንደሃገርም እንደ ሕዝብም ለ ከፋ ለ መረረ ጥፋት እንደእምንዳረግ አንጠራጠርም።

እንደ ማጠቃለያ

የ እኛ ዕምነት፤ ከ ህወሓት ጋር እየተደረገ የአለው ጦርዕነት እምይጠናቀቀው፡ በ ኢትዮጵያ እና በ ኢትዮጵያዊያን አሸንአፊዕነት እንደ እምይሆን ነው። ይ-ህ ዕምነትአችን ዕውን ይሆን ዘንድ ግና፤ ገዥው-ቡድን፡ ፍልምያውን በቁርጠኝዕነት ማካሄዱን እና ውስጡን ማፅዳቱን ብቻ ሳይሆን፡ የ ስር-ነቀል ለውጥ የግድ መሆኑን በማመን፡ በቅንዕነት ሊተገብረው እሚገባ ታሪካዓዊ ሀላፊዕነቱም ግዴታውም መሆኑን አስረግጠን መናገር ግዴታችን እንድይሆንም ወስነናል። አልያ፤ ኢትዮጵያዊያን በፍጥነት የፊታውራሪዕነቱን ቦታ በመረከብ፡ የ ኢትዮጵያን አሸናፊዕነት ዕውን ማድረጉን ልናውቅበት የግድ ነው።

አሁን ያለንበት ዕውነታ እንደ እሚነግረን ከሆነ፤ ህወሓት እንደዛተችው፡ በ ገዥው-ቡድን የስንቅ የትጥቅ እና የመረጃ ዕገዛ፡ ዐማራን በመውረር፡ በዛ የአለ የጄኖሳይድ ተግባራትን መፈፀምዋን፣ መንደሮችን ከተማዎችን እና ተቋማትን ማውደሟን ተረድተናል። ዐማራ እንደወተወተው፤ ተሳክቶለት ተደራጅቶ ታጥቆ መክሮ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ባልተፈጠረ ነበር። እናም፤ ዐማራ እንዳይደራጅ እንዳይታጠቅ እንዳይመክር አስተዋፅዖ የአደረጉ የመንግሥት አካላትም ሆኑ — ሕዝብን በግልፅ መሳደብ የጀመሩት [መድረክ አሟቂ ምላሶች] በአንዱም ሆነ በሌላው መልኩ ከተጠያቂዕነት እንደማያመልጡ ልንነግራቸው እንወዳለን።

*ህወሓት ይህ-እንን ሁሉ ነውር ሃጥያት እና ወንጀል ስትፈፅም፤ ብድር-መላሽ ዐማራዊ ትውልድ የለም ወይም አይመጣም ብላ ዐምና ከሆነ፡ ምን ያህል ስሁት የሆነ ዕምነት የያዘች መሆንዋን በተግባር ልታምን እንደምትደረግ ነግረናት ማለፍ እንወዳለን — የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው!*

ሌላ ህወሓት ላይ ያየነው ዕውነታ፤ አንድ ሀገርን ለ 27-ዓመትዐት ያህል የመምራት አጋጣሚው የተፈጠረለት አካል፡ እምያስተዳድረውን ሕዝብ ለማጥፋት፡ ለ 30-ዓመትዐት ያህል የቀበረችውን የጦር መሣሪያ ክምችት እና ሊቆረጥ እማይችል ለውጊያ ለጥፋት ያላትን መሰሪ ጥማት ስንአስብ፡ ህወሓት ምን ያህል [ቆሻሻ-ልብ] የአላቸው ፍጡራን የተሰገሰጉባት አረመኔ

ድርጅት መሆኗን ነው። እናም፤ በራሷ አፈጣጠር እና በራሷ ስራዎች ምክንያት፡ በምንም መልኩ ከምድረ-ገፅ እንድትጠፋ ብትደረግ፡ ልታማርር እምትችልበት አንዳችም ሰውዓዊ ምክንያት የሌላት መሆኑን ነው እምንዐምነው።

በተጓዳኝም፤ ገዥው-ቡድን የፖለቲካ ሽግግር ሂደቱ ስለ እሚጠናከርበት ሁኔታ መምከሩን እና አካታች ሀገራዊ ምክክር አስፈላጊ መሆኑንም አምኖበት፡ ሀገር በቀል የሆነ፡ በመሠረትዓዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያግዝ፡ ከሕዝባችን ባህልና ዕሴት ጋር የሚጣጣም፡ የሀገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በዘላቂነት ለማስከበር የሚረዳ፡ በ የ ሚኒስትሮች ምክር ቤቱ የቀረበ የ ኢትዮጵያ ሃገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ለመምከር የሆነ ፕሮሰስ ላይ እንዳለም ጭምር ሰምተናል አንብበናል።

ገዥው-ቡድን ኮሚሽን ማቋቋም እሚልን ሃሳብ፤ ሕዝብ ጆሮ እንዲደርስ ሲያደርግ፡ እኛ [ሂር ዊ ጎ ኧጌን!] ነበር ያልነው። ምክንያትአችንም፤ የ ዛሬ 3-ዓመት ተኩል ገደማ የተቋቋሙትን እና የ ውሃ ሽታ ሆነው የቀሩትን "ኮሚሽን" ተብዬዎች ዕውነታ ላይ የተመረኮዘ ነው። አሁንም፤ ገዥው-ቡድን ሕዝብን ለማነሁለል እና ጊዜ ለመግዛት ሲል ከሆነ ይህ-እንን ያደረገው፡ ሳይውል ሳያድር ዕርማት ሊያደርግ እና በ ቁርጠኝዕነት እና በ ቅንዕነት መሠረትዓዊ ለውጥን ማምጣት እምያስችል ዕርምጃዎችን መውሰድ እንዳለበት አስረግጠን መንገር እንገደዳለን። ማለትም፤ ገዥው-ቡድን ራሱን ከስልጣን መንበሩ ማውረድ እና ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ዐውድ እራሱን ማክሰም የአለበት መሆኑን አምኖ እንዲቀበል እና ቀጣይ ፍትህ አጎናፂ ተግባራትን ዕውን ሆነው እንድይታዩ፡ መሰናክል ከመሆን ተቆጥቦ፡ ወይ ኢኔብለር መሆን አልያም እጅ እግሩን መሰብሰብ ያለበት መሆኑን ማካተት አለበት፡ ማለትአችን ነው።

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንእገንአኝ –

# እንድይከስሙ ይገደዱ

ጥር ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ‖ ጄንወሪ 2022

***ርዕሰ-አንቀፅ***:- *ዛሬ የተነሳነው በተለየ የተስፋ መንፈስ ነው። ሰሞኑን በ ፈረንጅኛ 2022 ብለን መቁጠር መጀመርአችንን ምክንያት በማድረግ፤ አንዲት ጥያቄ መጠየቅም ወደድን። ጥያቄዋ – ሞራልቲ እና የ መንግሥት-አካልዐት በፈቃድአቸው ከ ስልጣን መልቀቅ፤ ቀረቤታቸው ምን ያህል ይሆን፡ ትላለች። ሞራልቲ፤ ክስተትዖች፡ [ጥሩ] ወይም [መጥፎ] ተብለው እምይፈረጁበት መሠረትዓዊ ምክንያትዖች በአግባቡ እምይስተናገዱበት ኅሊናዊ ተቋም ነው። በ ሞራልቲ ዙሪያ፤ አሻሚ ሊሆኑ እምይችሉትን ጨምሮ – የተለያዩ ምልከታዎች አሉ። ከ እነርሱም ውስጥ አንዱ፤ [ስኮላስቲሲዝም] ይባላል። የ ስኮላስቲሲዝም ፈላስፋዎች፤ የ ሞራልቲን ጭብጥ ሲያስረዱ – ሞራልቲ፤ በ የሰው ልጅ ሁለዕንተንዓዊ ተፈጥሮ ላይ ተመርኩዞ፡ ዙሪያ-ገጠም ህይወት እና መሠረትዓዊ የህይወት መገለጫዎች [ከ ሌሎች ሰዎች - ከ ዩኒቨርስ - ከ ፈጣሪ ጋር] ያላቸውን ግንኙዕነት እና ቁርኝት፡ በ ሚዛንዓዊ ሰውዓዊ ግምት ውስጥ እምይአስገባ ልብያና መሆኑን ሳይጠቁሙ አይአልፉም። አዎ፤ ለ ሰው ልጅ፡ ጥሩ እና መጥፎን ለመለየት እምይረዳው ክህሎት፡ [ፅንሰ-ሃሳብን ተግባርን እና የማገናዘብ የመለየት መለኮትዓዊ ሃይልን የአካተተ] የ ቀረቤታ ምክንያትዓዊ አፈጣጠሩ ላይ የተመሠረተ ነው። ትክክል። ኢ-አምአንያን መኖርአቸው የተጠበቀ ሆኖ፤ የ ሞራልቲ ጥያቄ እምይስተናገደው፡ በአመዛኙ ፈጣሪን በ ጠባቂዕነት ዐምኖ በመቀበል ላይ ተመሥርቶ ነውም ይላሉ። ስለ ሞራልቲ እንደመንደርደሪያ ያንን ከአልን፤ ወደ የ ተነሳንበት የ ሞራልቲ እና የ መንግሥት-አካልዐት በፈቃድአቸው ከ ስልጣን መልቀቅን በተመለከተ፡ ትንሽ ዕንበል። የ መንግሥት ስልጣንን በ ፈቃደኝነት መልቀቅ፤ ተመራጮችም ሆኑ ተሿሚዎች፡ ለ ሞራልቲ የ አላቸውን ተገዥዕነት እምይገልፁበት አንዱ መንገድ ነው። የ መንግሥትን ስልጣን በፈቃደኛዕነት መልቀቅ – ታማኝዕነትን ያንፀባርቃል፣ ሃላፊዕነትን በአግባቡ የ መወጣትን ቁርጠኛዕነትን ያጎለብታል፣ ተጠያቂዕነትን ያፀናል – እናም እንደ እየ አግባቡ፡ አሳቻ የ አልሆነ ቀይ መስመርን ያነብራል። በ ሙያው የአሉ ሰዎች እንደ እሚሉት፤ ከ የመንግሥትን ስልጣን በፈቃደኛዕነት መልቀቅ ጋር የተዛመዱት ሞራልዓዊ አመክንዮዎች፡ ከ ሦስት የተቀራረቡ የ ተዐማኒዕነት ገፅታዎች እንደ እሚመነጩ ይጠቁማሉ። ዕውነት ነው። ተመራጮች ወይም ሹመኞች፤ ከባድ ሃላፊዕነት ቦታ ላይ የአለው የሕዝብ ወንበር እምይጠይቃቸውን ግዴታዎች በሙሉ እንደእሚፈፅሙ ያለማወላወል ቃል-ይገባሉ። ቃል-መግባት ብቻም ሳይሆን፤ ቃልዐቸውን ለመጠበቅም ጭምር (ሀ) <u>አቅም</u> (ለ) <u>ብቃት</u> ብቻ ሳይሆን (ሐ) ስኬትዐማ የመሆን <u>ችሎታውም</u> ጭምር እንደአላቸው በ ፍፁም እርግጠኛዕነት ይናገራሉ። [ይባስ ብለው፤ አንድ-አንዶቹ ከ "ላይ" የተላክን ነን ሲሉም ሰምተን የለ!]። ለማንኛውም፤ [ሆነ ብሎ መሠሪ ተልዕኮውን ተግባርዓዊ ለማድረግ፡ የሃገር ክህደትን እምይፈፅመውን እና በ ሕዝብ ላይ ዘግናኝ ኢ-ሰውዓዊ ተግባርዐትን በግልፅ እሚተገብረውን ወንጀለኛ ለዛሬ ወደ ጎን አስቀምጠን] አንድ የመንግሥት ተመራጭም ሆነ ሹመኛ፡ የያዘው የሕዝብ ወንበር እምይጠይቃቸውን ሃላፊዕነትዖች እና ግዴታዎች የመወጣት [አቅምኡም ብቃትኡም ችሎታውም] እንደሌለው ግልፅ ሆኖ ሲገኝ፡ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላው መልኩ፡ የመንግሥትን ስልጣን በፈቃደኛዕነት መልቀቅ የግድ መሆኑን እምይጠቁም፡ ጠንካራ የሞራል ምክንያቶች ተሟልተው መገኘትዐቸውን፡ ይበይናል። የ ስልጡን መንግሥት፤ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ ተግባር፣ ሃላፊዕነት እና ግዴታ፡ የ ሃገር ሉዐልዓዊዕነትን መጠበቅ እና የ ሕዝብን ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን ነው። ይ-ህ እንን፤ መንግሥት እሚባል ነገር የመፈጠሩ፡ መሠረትዓዊ [ፐርፐዝ]፡ በ ስኬትዐማዕነት ተግብሮ ማሳየት ያልቻለ ወይም ያልፈለገ፡ ተመራጭ ወይም ሹመኛ፡ የገባውን [ቃል] ማክበር አልቻለም ወይም አልፈለገም ማለት ነው። ይህ ሆኖ ሲገኝ፤ የመንግሥት-አካልዐት ከስልጣን መልቀቅን እና ሞራልዓዊ ግዴታን፡ በ ፍፁምዓዊዕነት ያቆራኛቸዋል — አራት ነጥብ*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

ለ ኢትዮጵያ፤ ለ ንፁህ ሰንደቅ-ዓላማዋ፣ ለ ሉዐልዓዊዕነትዋ፣ ለ ሰላምዋ፣ ለ ታሪክዋ፣ ለ ቅርስዖችዋ፣ ለ ሃይማኖትዋ፣ ለ ግፉአን ልጆችዋ እና ለ አንድ ህብር ሕዝብዋ – ዋስ ጠበቃ በመሆናችሁ ብቻ፡ በ ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ ፊትአውራሪዎች ቂም የተያዘባችሁ፡ የ ኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች፡ ከትናንት-በስቲያ ከ እስር በ መውጣትአችሁ፡ እንኳን ደስ አላችሁ – እንኳን ደስ አለን፡ ማለት እንወድ አለን።

ያ-ው ዛሬም እንግዲህ፤ በ ወቅትዓዊ ኹነትዖች ዙሪያ በ ማውጠንጠን፡ የ አዘጋጅንአትን መጣጥፍ ይዘን፡ በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበናል።

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የምንጊዜም ግብዣችን ነው።

ስለ ወቅትዓዊ ኹነትዖች በጋራ ስንአስብ፤ ጎላ ብሎ ፊትአችን ላይ ድቅን እምይለው <u>ጥቅል ኹነት</u>፡ ሌላ ምንም ሳይሆን – [ህወሓት እና ኦነግ እየአካሄዱት ያለውን ፀረ-ኢትዮጵያ ጦርዕነት፣ በሰሜን በምዕራብ እንዲሁም በደቡብ የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ እየተፈፀመ የአለውን ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና የጄኖሳይድ አስከፊ መራር ገፅታዎችን፣ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን፡ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካን ተግባርዓዊ የአደረገውን ህገ-መንግሥት፡ ብሎም ነ-ም ፖለቲከኞች ነ-ም ኤሊት-ተብዬዎች፡ አንሶላ እምይጋፈፉበትን የግልአቸውን በብል] ያካተተ ነው።

በተደጋጋሚ ለማስገንዘብ እንደሞከርነው፤ ከገባንበት የሰቆቃ የዕልቂት አዙሪት ለመገላገል፡ መውጫው መንገድ ፈታኝ እና መራራ ሊሆን ቢችልም ቅሉ፡ ዱኸብል መሆኑን ግና ልንጠራጠር አይገባንም። አዎ፤ አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝምን ተግባርዓዊ የአደረገውን፡ የ ህወሓት-መርአሹን ኢህአዴግ እና የ ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹን ኢህአዴግ የመንግሥት ስርዐት፡ <u>እንድይከስም</u> ማድረግን፡ ማለትአችን ነው። ከ ንጉሥዓዊው መንግሥት እና ከ ወታደርዓዊው መንግሥት [መክሰም] ጋር በተያያዘ፤ ዕድሜ ያስተማረንን ዕውነታዎች ደገፍ ብለን፡ ዛሬ ኢትዮጵያን እያናወጣት ያለውን አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝም [መክሰም] ተተግብሮ ማየት ይቻል ዘንድ፡ የመወያያ ሃሳብዖች አድርገን ዕምንቆጥራቸውን መሠረትዓዊ ነጥብዖችን፡ ሁለት-ገፅታዎችን በተላበሰ [ቲ'ስስ] መልኩ፡ ቀጥለን አስፍረናቸዋል።

<u>ገፅታ አንድ</u>፤ የዛሬውን አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝም፡ ከ ንጉሥዓዊው መንግሥት እና ከ ወታደርዓዊው መንግሥት

እምይለየው መሠረትዓዊ ጉዳይ፡ የዛሬው አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝም ስርዐት ተዋንያን [ህወሓት ኦነግ ብልፅግና] የ እየግልአቸው አማፂ ወንበዴ የ ጦርሠራዊት ያላቸው የመሆኑ ጉዳይ ነው። እናም፤ አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝምን ተግባርዓዊ ያደረገው የመንግሥት ስርዐት [ይከስም] ዘንድ፡ ተዛማጅ ጦርዕነትዖች ሁሉ በአስቸኳይ እንድይጠናቀቁ ማድረግ፡ የግድ ነው። ያ-ም ዕውን እንዲሆን፤ ቀናው እና ተገቢ-ም/የግድም ነው ብለን ዕምንዐምነው መንገድ – የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ፡ [በመንግሥት ቦታው ላይ ስለአለ ብቻ፤ ለጊዜው ብልፅግናን በዕርጋታ በማስተናገድ] በቀዳሚዕነት ግና፡ ህወሓት እና ኦነግ፡ ትጥቅ ፈትተው እንድይከስሙ ማስገደድ የጠበቅበታል።

ገፅታ ሁለት፤ ጦርዕነቱን በአሸናፊዕነት ለማጠናቀቅ ከ እምይጠይቀው ፍልምያ ጎን-ለጎን [አልያም ጦርዕነቱ ከተጠናቀቀ በኋላም ቢሆን አይከፋንም] አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝምን [መከሰም] እምያስችሉ፡ ተቋምዓዊ እና መዋቅርዓዊ መሠረትዓዊ ስር-ነቀል ለውጥዖችን በቁርጠኛዕነት እና በቅንዕነት ተግባርዓዊ ማድረግን ሊይአካትቱ እምይገባቸው ግዙፍ ክሪቲካል ተግባርዐት አሉ። ማለት፤ ሃላፊዕነት እና ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ፡ ሁሉን-አቀፍ ሃገርዓዊ ስልጡን ጉባኤ ተጠርቶ – የ ዕውነት አፈላላጊ የ ፍትህዓዊዕነት እና የ ዕርቅ ሂደትን ተግባርዓዊ ማድረግ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣ ኢትዮጵያዊ ንፁህ ህገ-መንግሥት መቅረፅ፣ ግልፅ የሆነ የ ሕዝብ ቆጠራ ማድረግ፣ ፍትህዓዊ እና ነፃ የሕዝብ ምርጫ ማድረግ እና – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመስረት፡ ማለትአችን ነው።

መንግሥት ተብዬው፤ ህወሓትን እና ኦነግን አዝሎ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን ህገ-መንግስት እና አክራሪ የጎሣ ፖሊቲካውን አንጠልጥሎ፡ እሸሩሩ እምይልበት አካሄድን፡ እንደ [አንቲ'ተሰስ] ነው፡ እኛ እምንቆጥረው። ወደ ትግራይ ዘልቀን አንገባም እምይለው የሰሞኑን ሴንስለስ ውሳኔም ሆነ፤ የ ህወሓት መሪዎችን "ክስ-ማቋረጥ" በእምይል ከእስር መልቀቅን፡ የእዚሁ የአንቲ'ተሰስ አካል ናቸው ብለን ነው፡ የ ዕምንዐምነው። እናም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በጋራ ይነሳ ዘንድ፡ የግድ ነው።

የ አከሳሰም ነገር

የ ንጉሥዓዊው [ሞናርኪ] የአስተዳደር ስርዐት። በዘመኑ የነበረው የ ማህበረሰብዓዊ ህይወት ዳይናሚክስ በፈጠረው ዉስብስብ ፖለቲካ አማካኝዕነት፤ ስር-ነቀል ለውጥ ተተግብሮ፡ የንጉሥዓዊው የአስተዳደር ስርዐት ይከስም ዘንድ ሊገደድ በቅቷል። የነበረው ሞናርኪ "ከሰመ" ስንል፤ የ ንጉሥዓዊ የአስተደደር ስርዐት ውስጥ ጉልህ ሚና የነበራቸው ግለሰቦች በሙሉ [በተፈጥሮ የዕድሜ ጉዳይ ከአልሆነ በስተቀር] ተንነው እንድይጠፉ ተደርገዋል ማለትአችን አይደለም። ከእዚያም ባሻገር፤ እስከ ዛሬም እንኳን ቢሆን፡ የ ንጉሥዓዊው የአስተዳደር ስርዐትን እምይመርጡ እምይአቀነቅኑ ግለሰብዖችም ሆኑ፡ ምንአልባትም ድርጅት(ዖች) ጭምር፡ የሉም ወይም አይኖሩም ማለትአችንም አይደለም።

እናም፤ የነበረው ሞናርኪ "ከሰመ" ስንል፤ በ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሚዛን ደፊ የሆነ ሚና እሚጫወትበት ደረጃ ላይ አለመሆኑን ለመጠቆም እና ለማናቸውም [ይቅር እና ለሃገር ሉዐልዓዊዕነት ወይም ለ የኢትዮጵያ ሕዝብ – ለ ማናቸዉም ፖለቲከኛ ወይም የፖለቲካ ተቋም] አደጋ/ስጋት ሆኖ እምይታይበት ቁመና እንዳይኖረው ተደርጓል ማለትአችን ነው። ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች/ምክንያቶች ያሉት ቢሆንም ቅሉ፤ የ ወታደርዓዊው መንግሥት፡ የንጉሥዓዊውን የአስተዳደር ስርዐት እንድይከስም የአደረገው፡ ስር-ነቀል ለውጥ በማድረግ ነበር። ማለትም፤ በጊዜው እንደ አዲስ ገዥ ለመሆን የበቃውን ስርዐት ተግባርዓዊ ለማድረግ እሚያስችሉ ስር-ነቀል ለውጦችን፡ በዋናዕነት አግባብዕነት አለው ብሎ ያመነበትን አዲስ ህገ-መንግሥት ቀርፆ ተግባርዓዊ በማድረግ፡ ማለትአችን ነው።

የ ወታደርዓዊው መንግሥት፤ የ ሶሻሊስት መርህዖችን የተቀበለ የ ዲሟክረቲክ ሪፐብሊክ ስርዐትን የተከተለ ነበር። በ እዚያ ክፉ ዘመን የነበረው የማህበረሰብዓዊ ህይወት ዳይናሚክስ በፈጠረው ዉስብስብ ፖለቲካ አማካኝዕነት፡ ሌላ ስር-ነቀል ለውጥ ተተግብሮ፡ በተራው የወታደርዓዊው የአስተዳደር ስርዐት ይከስም ዘንድ ሊገደድ በቅቷል።

የ ወታደርዓዊው የአስተደደር ስርዐት "ከሰመ" ስንል፤ የ ሶሻሊስት መርህዖችን የተቀበለው የ ዲሟክረቲክ ሪፐብሊክ የአስተደደር ስርዐት ውስጥ፡ ጉልህ ሚና የነበራቸው ግለሰቦች በሙሉ [በተፈጥሮ የዕድሜ መርዘም ካልሆነ በስተቀር] ተንነው እንድይጠፉ ተደርገዋል ማለትአችን አይደለም። ከእዚያም ባሻገር፤ እስከ ዛሬ'ም እንኳን ቢሆን፡ የወታደርዓዊው መንግሥትን ወይም የሶሻሊስት መርህዖችን የተቀበሉ የ ዲሟክረቲክ ሪፐብሊክ የአስተዳደር ስርዐትን እምይመርጡ እምይአቀነቅኑ ግለሰብዖችም ሆኑ፡ ምንአልባትም ድርጅት(ዖች) ጭምር የሉም ወይም አይኖሩም ማለትአችንም አይደለም።

እኛ፤ የነበረው የሶሻሊስት መርህዖችን የተቀበለው/የተገበረው ወታደርዓዊው የዲሟክረቲክ ሪፐብሊክ ስርዐት "ከሰመ" ስንል፤ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ፤ ሚዛን ደፊ የሆነ ሚና እሚጫወትምበት ደረጃ ላይ አለመሆኑን ለመጠቆም እና ለ ማናቸውም [ይቅር እና ለሃገር ሉዐላዊዕነት ወይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ – ለ ማናቸዉም ፖለቲከኛ ወይም የፖለቲካ ተቋም] አደጋ/ስጋት ሆኖ እምይታይበት ቁመና እንዳይኖረው ተደርጓል ማለትአችን ነው። አሁንም፤ ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች/ምክንያቶች ያሉት መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ፡ አክራሪ የጎሣ-ፖለትካን ተግባርዓዊ የአደረገው የ ኢትኒክ-ፌደራሊዝም ስርዐት፡ የ ወታደርዓዊውን የአስተዳደር ስርዐት እንድይከስም ያደረገው፡ ስር-ነቀል ለውጥ በማድረግ ነበር። ማለትም፤ በጊዜው እንደ አዲስ ገዥ ለመሆን የበቃውን የ ኤትኒክ-ፈደራሊዝም ስርዐት ተግባርዓዊ ለማድረግ እሚያስችሉ ስር-ነቀል ለውጦችን፡ በዋናዕነት በ ጎሣኞቹ ዘንድ አግባብ የአለውን አዲስ ፀረ-ኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት ቀርፆ ተግባርዓዊ በማድረግ፡ ማለትአችን ነው።

ትክክል። በዋናዕነት፤ የ "ኢህአዴግ" መንግሥት [ህወሓት-መርአሹን ኢህአዴግ እና ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹን ኢህአዴግ ጭምር] የ አክራሪ ኤትኒክ-ፌደራሊዝም"ን የተገበረ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ኢትዮጵያዊ፡ በተለይም ፀረ-ዐማራ የሆነ፡ መሠሪ አምባገነን የአስተዳደር ስርዐት ነው። ባለፉት 31-ዓመትዐት ገደማ እየገዘፈ እየተወሳሰበ የመጣው የማህበረሰብዓዊ ህይወት ዳይናሚክስ በፈጠረው ዉስብስብ

ፖለቲካ አማካኝዕነት፤ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን እንደ ሃገር እና እንደ አንድ ህብር ሕዝብ፡ የከፋ የጎልውና አደጋ ውስጥ ተዘፍቀዋል። እናም፤ እንደ የንጉሥዓዊው እና የወታደርዓዊው ስርዐትዖች፡ ይ-ህ የ "ኢህአዴግ" መንግሥት፡ ማለትም – ህወሓትን ኦነግን ብልፅግናን እና መሠል ፀረ-ኢትዮጵያ አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች መሪ ተዋንያን የሆኑበትን የጎሣ-ፊደራሊዝም የተገበረ የአስተዳደር ስርዐት፡ ከሃገርአችን የፖለቲካ ምህዳር እንድይከስም ሊገደድ እምይገባበት ጊዜ ላይ ከደረስን ዓመትዐት ማስቆጠርአችንን፡ ደጋግመን ማስገንዘብ እንወዳለን።

እናም፤ ጎበዝ — የ "ኢህአዴግ" የአስተዳደር ስርዐት ከሃገርአችን የፖለቲካ ዐውድ <u>ይከስም</u> ዘንድ ሊገደድ ይገባል ስንል፣ [ህወሓት-መርአሹ ኢህአዴግ እና ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ] ውስጥ ጉልህ ሚና የነበራቸው/የአላቸው ግለሰቦች በሙሉ ተንነው እንድይጠፉ ይደረጉ ማለትአችን አይደለም። ልክ እንደ የ በፊተኞቹ መንግሥታት፤ የ ህወሓት-መርአሹ ኢህአዴግ እና ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ የ አስተዳደር ስርዐት፡ ማለትም – የ ኤትኒክ-ፌደራሊዝምን መርህዖችን የተቀበሉ እንድይቀጥልም እምይመርጡ እምይአቀነቅኑ ግለሰብዖችም ሆኑ ድርጅት(ዖች) ጭምር እንዳሉም ወደፊትም ሊኖሩ እንደእሚችሉም እንአውቃለን።

እኛ፤ ህወሓትን ኦነግን እና መሠል ፀረ-ኢትዮጵያ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ ድርጅቶችን ከሃገርአችን የፖለቲካ ዐውድ አስወግደን <u>እንድይከስሙ</u> እናስገድዳቸው ስንል፤ በ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ፤ ሚዛን-ደፊ የሆነ ሚና እሚጫወቱበት ደረጃ ላይ አለመሆናቸውን እና ለማናቸውም [ይቅር እና ለሃገር ሉዐላዊዕነት ወይም ለ ኢትዮጵያ ሕዝብ – ለማናቸዉም ፖለቲከኛም ሆነ የፖለቲካ ተቅዋም] አደጋ/ስጋት ሆነው እምይታዩበት ቁመና፡ እንድአይኖራቸው ይደረጉ ማለትአችን ነው። ህወሓትን ወንዝ አሻግሮ በመልቀቅ፣ ኦነግን በማጎልበት እና በሰበብ አስባቡ ለፍርድ ሊቀርቡ እምይገባቸውን የወንበዴ መሪዎች "ክስ በማቋረጥ" በመልቀቅ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን የጎሣ-ፌደራሊዝም ስርዐትን ማክሰም፡ አይቻልም።

ክሪቲካል ስለሆነ እንድገመው። የአሁኑ የ ኤትኒክ-ፊደራሊዝም ስርዐትን ስለ ማክሰም ስንአነሳ፤ ስር-ነቀል ለውጥን ማካሄድ፡ ማለትም – የ ዕውነት አፈላላጊ የ ፍትህዓዊዕነት እና የ ዕርቅ ሂደትን ተግባርዓዊ ማድረግ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣ ኢትዮጵያዊ ንፁህ ህገ-መንግሥት መቅረፅ፣ ግልፅ የሆነ የ ሕዝብ ቆጠራ፣ ፍትህዓዊ እና ነፃ የሕዝብ ምርጫ ተደርጎ – እንደ አዲስ ገዥ ለመሆን እምይበቃ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመስረትን፡ የፍልሚያው አንዱ ዳይሜንሽን መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ [ከላይ የጠቀስነውን በአለ ሁለት-ገፅ ቲ'ስስ ያጤኗል] – የንጉሥዓዊዉን ስርዓትንም ሆነ የሶሻሊስቱን ስርዐት እንድይከስሙ ካስቻሉት መሠረትዓዊ ለውጦች ባሻገር፡ ወታደርዓዊ ተቁዋምአቸውን እንድይከስሙ ማድረግን የጨመረ፡ ከ አማፂያኑ ጋር እምይደረጉ ማናቸውንም ተዛማጅ ጦርዕነትዖች፡ በአሸናፊዕነት እንድይጠናቀቁ ማድረግም የፍልሚያው ሌላኛው ዳይሜንሽን፡ በአግባቡ ሊስተናገድ እንደእሚደባው አበክረን ማስገንዘብ እንወድ አለን።

ሃገርዓዊ ምክክር

ዛሬ-ዛሬ፤ የአለው የማህበረሰብዓዊ ህይወት ዳይናሚክስ ከአስከተላቸው "ቀና-መሰል" ውጤትዖች ውስጥ አንዱ፤ ሰሞኑን ወደ ሕዝብ ጆሮ እንድይደርስ የተደረገው "የኢትዮጵያ ሃገርዓዊ የምክክር ኮሚሽን" ተብሎ እንድይጠራ የተፈለገውን አካል ማቋቋምን ይመለከታል። በአጠቃላይ፤ ይህ ሂደት፡ የወቅትዓዊዕነቱን ጉዳይ ጨምሮ፡ እጅጉን ብዙ ክፍተቶች የአሉት መሆኑ የተጠበቀ ሆኖ – በ አዎንታዊዕነትኡ ማስተናገድን ግና፡ ልንነፍገው አልመረጥንም። ዝርዝር ጉዳዮችን፤ ለሂደቱ ቀረቤታ ላላቸው እና ለእሚኖራቸው ወገኖች ትተን፡ አንድ-አንድ በ ወፍ-በረር ጎላ ብለው የታዩንን ነጥቦች በአጭሩ ለመጠቋቆም እንሞክር።

ከ ወደ 5-ወርዐት በፊት የተካሄደው፤ "ሃገርዓዊ ምርጫ" ሂደትኡም ሆነ ውጤትኡ [አሳታፊም፣ ነፃም፣ ዲሚክረሲዓዊም ሆነ ፍትህዓዊ] አልነበሩም ብለን ስለ ዕምንዐምን፡ መንግሥት-ተብዬው አለኝ ለማለት እምይከጅለውን "ሌጂትመሲ"፡ እኛ – [ፎው-ሌጂትመሲ] እንደሆነ ነው ዕምንቆጥረው። በተያያዥም፤ ለገዥው ቡድን፡ አመኔታችንን መስጠት እንደአልፈቀድን ሁሉ፡ ለ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱም ጭምር፡ አመኔታችንን መስጠት አንፈቅድም።

የሆነው ሆኖ፤ ህይወት የ አለእኛም መፈጠር መቀጠልዋ አይቀርም እና፡ መንግሥት ተብዬው ከ እምይሰራቸው ስራዎች ውስጥ እየመራረጥን፡ በ አዎንታዊዕነታቸው ከማስተናገድ ይልቅ፡ ንፉግ መሆንን መርጠን አንአውቅም። የኢትዮጵያ ሃገርዓዊ የምክክር ኮሚሽንን በተመለከተም፡ በረቂቅ አዋጁ ላይ የተደረጉትን ማሻሻያዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን ግምት ውስጥ በማስገባት እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡ እሚጠበቅበትን <u>ታሪክዓዊ ሃገርዓዊ</u> ስልጡን ሕዝብዓዊ ሃላፊዕነት እና ግዴታውን ለመወጣት ራስኡን ዝግጁ ሊያደርግ ይገባል ብቻ ሳይሆን፡ ይችላልም እምይልኸውን [ወገንዓዊ ተስፋችንን] በመቸር፡ ለሚቋቋመው ኮሚሽን መልካም የስራ ዘመን እንድይሆንለት ከልብ እንመኛለን። ወሳኝ የሃገር እና የሕዝብ፤ የ ጎልውና ጉዳይ ነው እና!

ዋናው ቁምነገር፤ ከጅማሮ እስከ ፍፃሜ፡ ኮሚሽኑን እምይመለከቱ መሠረትዓዊ ሃገርዓዊ እና ሕዝብዓዊ ጉዳዮች ሁሉ፡ ከማናቸውም ዓይነት ከኮሚሽኑ-ውጭ ከአሉ አካልዐት [የገዥው-ቡድንም ሆነ በመንግሥትዕነት ቦታው ላይ የተቀመጡ ግለሰብዖችን እና የ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰዎችን ጨምሮ] ከማናቸውም ጣልቃገብዕነት እና ተፅዕኖ ሙሉ-በሙሉ ነፃ የመሆኑ ጉዳይ፡ እጅጉን ወሳኝ ነው። የ ኮሚሽኑ ተግባርዐት ሕዝብዓዊ ምስክርዕነትን ቅቡልዕነትን ያገኙ ዘንድ፤ ሁሉም ተግባራት [<u>ትራንስፓረንት</u>] በሆነ መልኩ መፈፀም የአለባቸው መሆኑን አፅንዖት ሰጥተን ማለፍም፡ እንወድ አለን።

ሂደትኡን ተዐማኒ ለማድረግ፤ ዕውቀት የተሟላ-መረጃ ቆራጥዕነት ቅንዕነት ፕሮፌሽናሊዝምን እና የ አመለካከት ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትን ይጠይቃል። ምክንያትኡም፤ የኮሚሽኑ ተልዕኮ፤ ኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ፡ ጎልውና የከፋ አደጋ ላይ የጣለውን፡ አክራሪ የጎሣ-ፖለቲካ በሽታ ለ መፈወስ፡ ሃኪምዋ ሆኖ ማገልገል ነው ብለን ስለ ዕምንዐምን። ውጤትን በተመለከተ፤ ኢንዳክቲቭ ከሆነ የይዘት አናሊቲክ ሜቶዶሎጂ

ይልቅ፡ ዲዳክቲቭ የይዘት አናሊቲክ ሜቶዶሎጂን መከተል ይበጃል። ምክንያትኡም፤ (ሀ) ከውስብስብ ጉዳዮች ቶሎ መላቀቅን ስለ እምይአግዝ እና ሂደትኡ የተንዛዛ ጊዜን እንድአይጠይቅ ለማስቻል (ለ) ሊዳሰሱ እምይገባቸው መሠረትዓዊ ጉዳዮች ሁሉ አዲስ ስለ አይደሉ እና በቂ ሃገር-በቀል አልያም የሌሎች ሃገርዐት ተሞክሮዎችን ማግኘት፡ አስቸጋሪ ስለ እምአይሆን (ሐ) ሕዝብ ከሂደትኡ ምን እንደ እሚጠብቅ በቀላሉ ከምዩኒኬት ማድረግ ስለሚቻል፡ ብሎም – ውዥንብርን እና ተዳዳኝ ነውጥዖችን ከሩቁ መገደብ ያስችላል ብለንም ስለ ዕምንዐምን።

*ኢንዳክቲቭ አና ዲዳክቲቭ የይዘት አናሊቲካል ሜተድስ ስንል፤ በ ሦስት [ዝግጅት ቅንብር እና ዘገባን በተመለከተ] በ ቅደም-ተከተል እምይተገበሩ፡ የ ሳይንስዓዊ ምርምር አማራጭ ዘዴዎችን ለማለት ነው። ሁለትኡም፤ ዝግጅት ላይ ልዩዕነት የላቸውም። በ ኢንዳክቲቭ የይዘት አናሊሥስ፡ ጭብጥዖች [ትሲ'ምስ] እምይቀመሩት በተዘጋጀው ዳታ ላይ ተመርኩዘው ሲሆን – በአንፃሩ፤ በ ዲዳክቲቭ የይዘት አናሊሥስ፡ ጭብጥዖች እምይቀመሩት ከተሞክሮ በተገኙ ሃገር-በቀልም ሆነ ከሌሎች ሃገራት በተገኙ ዕውቀትዖች ዙሪያ ያጠነጠኑ እንድይሆን መደረጉ ላይ ነው፡ ልዩዕነትአቸው።*

እኛ፤ ሃገርዓዊ ምክክሩ፡ ውሃ-ወቀጣ ከመሆን ይተርፍ ዘንድ፡ ወደ ተግባር እንድይለወጡ እምያቀርቧቸው ምክረ-ውሳኔዎችን መቀመር ከ እምይአስችሉ ጭብጥዖች [ትሲ'ምስ] ውስጥ፡ እምይከተሉት <u>የግድ</u> ሊካተቱ ይገባል ብለን ዕንዐምን አለን። አልያ — ኮሚሽኑ፤ እምይጠብቀው ብይን [ዴድ ኦን አራይቫል] እምይል መሆኑ፡ አይቀሬ ነው።

<u>ጭብጥ [ትሲ'ም]፤ ቁጥር (1)</u>፡ ሊጠሩ/ሊታረቁ/ሊፈርሱ እምይገባቸው ተረክዖች።

***ተዛማጅ ምክረ-ውሳኔ 1*** *— ዕውቀትን የተሟላ-መረጃን ቁራጥዕነትን ቅንዕነትን፣ ፕሮፌሽናሊዝምን፣ ስልጡንዕነትን፣ ሰውዓዊዕነትን እና የአመለካከት ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትን በመጠቀም፡ መሠረተ-ቢስ ተረክዖችን የማረቅ ስራን፡ ተቋምዓዊ ማድረግ እና በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት።*

<u>ጭብጥ [ትሲ'ም]፤ ቁጥር (2)</u>፡ የሃገር ሉዐልዓዊዕንትን እንዲሁም የ ሕዝብ ህብርን እና አንድዕነትን አደጋ ላይ የጣሉ ተቋምዓዊ ዝቅጠትዖች።

***ተዛማጅ ምክረ-ውሳኔ 2*** *— የሃገር ሉዐልዓዊዕንትን እምያፀኑ እና የሕዝብ ህብርን አንድዕነትን እምያጎለብቱ ተቋማትን መዋቅርዐትን መዘርጋትዓቸውን ዕውን እምያደርግ፤ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት መመሥረትን፣ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይን ሁሉ የአሳተፈ አዲስ ስልጡን ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግስት መቅረፅን፣ የጎሣ-ፖለቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ እምይገደቡበትን፣ በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ እምይደረግበትን እና የ ኢትዮጵያ ሕዝብዓዊ መንግሥት ምሥረታን እንድይተገበር ማድረግን፡ በጋራ እርግጠኞች መሆን።*

<u>ጭብጥ [ትሲ'ም]፤ ቁጥር (3)</u>፡ የ ህግ እና የ ፍትህ መዛባትዖች።

***ተዛማጅ ምክረ-ውሳኔ 3*** *— የኢትዮጵያን የአስተዳደር ስርዐት መሠረትዓዊ ዕምነትዖችን እና ኢትዮጵያ እንደ ሃገር፣ ከፍለሃገርዐት፣ ተቋዋምዐት እንዲሁም ዜጎች እንደየአግባቡ ስልጡን በሆነ መልኩ እምይተዳደሩበት፡ ህግዓዊ ፍትህዓዊ መአቀፍን እሚደነግግ እምያብራራ እና ሰውዓዊ በሆነ አግባብ ተግባርዓዊ እንድይደረጉ እምያስችል፡ የሃገሪቱን ከፍተኛ የህግ፡ የፍትህ ተቋም በንፁህ ኢትዮጵያዊዕነት እንድይታረቅ እንድይታነፅ ማድረግ።*

<u>ጭብጥ [ትሲ'ም]፤ ቁጥር (4)</u>፡ የ መንግሥትዓዊ የአስተዳደር ስርዐትን በትክክል እምያንፀባርቅ እምይመራ እምይተገብር፡ ኢትዮጵያዊ ተቁዋም አልባዕነት።

***ተዛማጅ ምክረ-ውሳኔ 4*** *— ሰው በሰውዕነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል – በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እምይአገኝ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት እንድይመሰረት፡ መሠረትዓዊ ዝግጅቶችን ሁሉ በግልፅ መጠቆም እና ተግባርዓዊ እንድይደረጉ እምያስችል፡ ኢትዮጵያዊ ተቋም(ዐት) እንድይገነባ(ቡ) ማድረግአችንን በጋራ እርግጠኞች መሆን።*

ሃገርዓዊ የምክክር ሂደት፡ በህወሓት-መርአሹ ኢህአዴግ ዘመንም ተሞክሮ አይተናል። በአግባቡ ስለአልተካሄደ ግና – ድካም ብቻ ሆኖ ነው የቀረው። ይህ የአሁኑም ጥረት፤ ተገቢውን መንገድ እስካልተከተለ እና በንፁህ ኢትዮጵያዊዕነት መንፈስ እስካልተተገበረ ድረስ፡ ዉሃ ወቀጣ ከመሆን እማያመልጥ መሆኑን — ከወዲሁ፡ ጮክ ብለን፡ ደግመን ደጋግመን ማስገንዘብ እንወድ አለን።

እንደ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ዛሬም ቢሆን፤ እጅጉን ፈታኝ በሆነ ህይወት ውስጥ እንዳለች አለች። ለ አምስት-ስድስት አስርተ-ዓመትዐት ያክል፤ ከእዚያ በፊትም ጭምር፡ ረዘም ላለ ጊዜ የቆየ ፈታኝ ህይወት። የ እኛ ችግር፤ የ ፈታኝ ህይወትአችንን ምክንያትዖች ምን ምን እንደሆኑ አጥርተን አለማወቅ ብቻ ሳይሆን፡ አለማወቅአችንን ማመን ያቃተን መሆኑን እና መፍትሄያቸውን ፈልገን፡ ሃገርዐችን እምይገባትን ሰላምዓዊ ስልጡን ህይወት እንድትአጣጥም የአለማስቻላችን ጉዳይዖችም ጭምር ነው። ለሃገር ረብ ያለው አንዲት ነገር ሳንሰራ፤ ግልፅ ሰቆቃ እና ዕልቂት ቀፍቃፊዎች ሆነን እየአለን፡ መድረክ በተገኘ ቁጥር፡ ሁሉን አዋቂ ሆነን ለመታየት እምናሳየው አጓጉል መንበዛበዝ — ዕውነት ለመናገር ከሆነ፡ ያቅለሸልሻል!

አዎ፤ አልሞከርንም እየአልን አይደለም። ስኬታማ ልንሆን አልተቻለንም እየአልን ነው። የኢትዮጵያ ፈታኝ ህይወት እየባሰበት፤ የሃገር እና የሕዝብ የኅልውና ጥያቄ ወደመሆን ተባባሰ እንጂ፡ ሲቃለል አላየንም እየአልን ነው። ከ ወደ 4-ዓመትዐት ገደማ የተጀመረ "ለውጥ" መሰል ድንብርብር፤ የለየለት ጄኖሳይድ እና የእርስ-በእርስ ጦርዕነትን፡ የዕለት-ተዕለት መገለጫዎችአችን አንድይሆኑ ከማድረጉ በስተቀር፡ አንዳችም በጎ ነገር ሲሰራ አላየንም፡ ማለትአችን ነው።

ከእዚህ አረንቋ ውስጥ ለመውጣት፤ በቅድሚያ፡ ህወሓት ኦነግ እና ብልፅግና ከ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ተወግደው እንድይከስሙ ይደረግ ዘንድ የግድ ነው። ብልፅግና፡ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ፡ ኢትዮጵያ በዕውነት እንድታሸንፍ አስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅቶች እና ዕርምጃዎች ተግባራዊ እንድያደርግ ግዴታው ነው። ስራው ነው። ደሞዝ እየተከፈለው ነው። ይ-ህ ዕምነትአችን ዕውን እንድይሆን፤ ብልፅግና፡ በኦነግ በህወሓት እና በራሱ በብልፅግና፡ እየተከአሄደ ያለውን፡ የለየለት ጄኖሳይድ የለየለት ወረራ እና ጦርዕነት፡ በአስቸኳይ እንድይቋጩ ያደርግ ዘንድ ታሪክዓዊ ግዴታው መሆኑን፡ በተደጋጋሚ ለማስገንዘብ እንወድ አለን። መራርኡ ሃቅ፤ ህወሓትን ወንዝ አሻግሮ ጉሮወሸባየ በማለት፣ ኦነግን በማጎልበት እና አዝሎ እሹሩሩ በማለት እንዲሁም ለፍርድ ሊቀርቡ እምይገባቸውን የወንበዴ መሪዎች በ ሲሊ ሰበባ-ሰበብ "ክስ አቋርጦ" በመልቀቅ፡ ኢትዮጵያ አሸናፊ ልትሆን አትችልም።

ዛሬም ከ እስር ያልተፈቱ ወገኖችአችን መኖርአቸው የተጠበቀ ሆኖ፤ ኢ-ፍትህዓዊ በሆነ መልኩ፡ ለ እስር ተዳርገው የነበሩትን ንፁህ የኢትዮጵያ ልጆች መለቀቅን፡ ሊደረግ ከታሰበው ሃገርዓዊ ምክክር ሂደት ጋር በርቀት አጎዳኝተነው በአዎንታዊዕነት ልናስተናገደው መርጠናል። ነገር ግን፤ ተፈቱ የተባሉትን የስም ዝርዝር ስንአነብ፡ መንግሥት ተብዬው፡ በሽታው እየፀናበት እንደሄደ፡ ሃገርን እና ሕዝብን በግልፅ እንደካደ እና ከኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በተለይም ከ ዐማራ እና ከ አፋር ሕዝብ ጋር የተቆራረጠበት አዋጅ እንደሆነ አድረግን እንድንወስደው ተገደናል። ለመሆኑ፤ ለውጭ ኃይላት ተፅዕኖ አንምበረከክም ሲባል የነበረው፡ ብሩሃሃ ሁሉ የት ገባ!?

የለም የለም። አልተገረምንም። ብልፅግና፤ በፍፁም ሊታመን እማይችል፣ ሊታመን እማይገባ፣ ኢንካምፐተንት እና እማይድን በሽተኛ ድርጅት መሆኑን ከ ታይም-ዜሮ ጀምረን እናውቃለን። መሪዎቹ፤ በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ እማይሰሩት ዕኩይ ስራ የለም። ዕመኑን፤ ለሃገርም ለሕዝብም ደንታ የላቸውም። እናም፤ ኢትዮጵያን እና ሰውዓዊ ህልውናችንን ለመጠበቅ ይአስችለን ዘንድ፡ ብልፅግና ለእሚሰራቸው ዕኩይ ስራዎች ማብራርያ መጠየቅ ማቆም አለብን። ጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ፤ መሠረትዓዊ ለውጥ ለማምጣት ዛሬውኑ ቆርጠን እንነሳ። ትኩረትአችንም ሆነ ቅድሚያችን፤ ህወሓትን አነግን እና ብልፅግናን በተዛማጅም ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን አክራሪ የጎሣ-ፌደራሊዝም ስርዐትን ማክሰም፡ ይሁን።

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንእገንአኝ –

# እንድይበቃው ሊገደድ የግድ ነው!

የካቲት ፪ሺህ፲፬ ዓ.ም ‖ ፌብሪወሪ 2022

***ርዕሰ-አንቀፅ***:- በአሳለፍንአቸው የ ታህሳስ እና የ ጥር ወርዐት፤ የልደት እና የጥምቀት በዐልዐትን ስንአስብ፡ ሃይማኖትዓዊ ስርዐትዖች [ደስታን ፍቅርን ጨዋዕነትን ተስፋን ፅናትን ዕፎይታን አስተዋይዕነትን ዕምነትን ሃይማኖትን ንፁህዕነትን ህብርዕነትን አንድዕነትን አለኝታዕነትን ጥንካሬን ታላቅዕነትን ጀግናዕነትን ውብዕነትን ኢትዮጵያዊዕነትን ሰውዓዊዕነትን] አንፀባራቂ በሆነ መልኩ፡ ሲከበሩ ሲዘከሩ በማየትአችን በመስማትአችን፡ ደስታችን አቻ አልነበረውም። በዐልዐቱ – በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛትዖች ማለት በእምይአስደፍር አግባብ፤ ደምቀው ማየት መስማት ብቻ፡ እጅጉን ልብ አሟቂ ነበር። ለረዥም ዓመትዐት፤ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመንዐን፡ የ ኤትኒክ-ፊደራሊዝም መዘዝ ከ አስከተለባቸው ሰቆቃ እና ዕልቂት የተሞላበት አሳዛኝ ህይወት-አልባዕነት፡ ትንሽ ቀዳዳ ፈልገዉ፡ ኢትዮጵያ ምን ያህል ሪዚልየንት የሆነ ህብር ማህበረሰብ የአላት ሃገር መሆንዋን፡ በኩራት በድጋሜ ማስገንዘብ ያስቻልኡበት መድረክ ሆኖ ማለፉ፡ ዕውነት ለመናገር ከሆነ፡ ቴራፒውቲክ ነበር። በሌላ በኩል፤ የልደት እና የጥምቀት በዐልዐትን፡ በነፃዕነት ማክበር ላልቻላችሁ ወገንዖችአችን – አይዞአችሁ፡ ይ-ህ ክፉ ቀን በዕርግጥ ያልፋል፡ ማለት እንወድ አለን። በተለይ፤ መንግሥት-ተብዬው አፍንጫ ስር በእምትገኝ [ፀረ-አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ-ዓላማችን፣ ፀረ-ኦርቶዶክስ እና ፀረ-ኢትዮጵያ] አቋም የያዙ፡ ዕኩይ ፍጡራን የተሰገሰጉባት አንዷት መንደር ውስጥ፡ በጥምቀት ማግሥት ዕለት፡ የአምባገነኑ የኦሮሙማ ወራሪ ኃይል ተኳሽዖች፡ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመንዐንን፡ በጥይት ደብድበው ገድለዋል፣ ብዙዎችን አቁስለዋል፣ የማንዕነትአችን መገለጫዎችንም፡ በዕብሪት በእሳት አጋይተዋል። በእንዲያ ዓይነት የድንቁርና የዕብደት የአምባገነንዕነት የወራሪዕነት የጠላትዕነት የመሠሪዕነት ወንጀሎች፤ ተጎጂ ለሆናችሁ ወገንዖችአችን ሁሉ፡ መፅናንዐቱን ዕንዕመኝ አለን። ጎበዝ፤ ለ እንዲህ የአለ፡ ተደጋጋሚ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፡ በቀዳሚዕነት ተጠያቂው፡ ኦሮሙማን እያንሰራፋ የአለው፡ መዐከልዓዊው መንግሥት-ተብዬ ነው። አንዷት ሽራፋ መንደር በስርዐት ማስተዳደር የአቃተው መንግሥት-ተብዬ፤ ስለ ፓን-አፍሪካኒዝም ሲንበዛበዝ – ለመሆኑ አፍሪቃን አንድ አድርጐ፡ የትኛውን ቤስት-ፕራክቲስ ሊተገብር ይሆን፡ ብለን መጠየቅኡ አልቀረልንም። ኤትኒክ-ፌደራሊዝምን በአፍሪቃ ውስጥ አንሰራፍቶ፡ በጎሣ እየአባላ፡ የሰቆቃ እና የዕልቂት ኰንትነንት ሊያደርጋት?! ፈጣሪ ይሰውረን። በተጓዳኝም፤ መንግሥት-ተብዬው፡ ለ 5-ዓመት ተመርጫለሁ እና አትረብሹኝ ሲልም ተደምጧል አሉ። አንድ የመንግሥት አካል፤ የሃገር ዳር-ድንበርን ለመጠበቅ እና ሰላም እና መረጋጋትን ለማስፈን፡ አቅምኡም ብቃትኡም ችሎታዉም ፍላጐትኡም የሌለው መሆኑ ግልፅ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ፡ <u>በተመረጠ በማግሥቱ</u> እንድይበቃው ሊገደድ ይችላል ብቻ ሳይሆን – የግድ ተደርጐ ሊወሰድም ይገባል። ለ 5-ዓመት ተመርጫለሁ እና 4-ዓመት ተኩል ይቀረኛል እምይባል ነገር የለም። አሁንም ቢሆን፤ ለተዘፈቅንበት ዘግናኝ እና አልአባራ የአለ [ህይወት-አልባዕነት] ምክንያትኡ፡ ለ 31-ዓመትዐት ያህል የዘለቀው አክራሪው የ ጎሣ-ፖለቲካ፣ በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረተዉ የ ኤትኒክ-ፌደራሊዝም የአስተዳደር ስርዐት እና ከ 4-ዓመትዐት ወዲህ ደሞ እየተንሰራፋ የመጣው፡ ወራሪው ኦሮሙማ ጭምርም ነዉ። ሌላው ሁሉ ዕዳው ገብስ ነው። ደግመን ደጋግመን ለማስገንዘብ እንደሞከርነው፤ መፍትሄው፡ ስር-ነቀል ለዉጥ ማካሄድ ብቻ ነው። ማለትም፤ የ ዕውነት አፈላላጊ የ ፍትህዓዊዕነት እና የ ዕርቅ ሂደትን ተግባርዓዊ ማድረግ፣ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት መመሥረት፣ ኢትዮጵያዊ ንፁህ ህገ-መንግሥት መቅረፅ፣ ግልፅ የሆነ የ ሕዝብ ቆጠራ፣ ፍትህዓዊ እና ነፃ የሕዝብ ምርጫ ማድረግ – እንደ አዲስ ገዥ ለመሆን እምይበቃ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት መመሥረት፡ ማለትአችን ነው። ይ-ህ ዕውን ሊሆን እምይችለው ደሞ፤ ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትን፡ ኰምፐስኡ በ አደረገ፡ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የፖለቲካ ፓርቲ፡ በ እምይመራ ሕዝብዓዊ ንቅናቄ ውስጥ፡ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ብቻ ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

በ ጠንካራ ሕዝብዓዊ ንቅናቄ፤ ስር-ነቀል ለውጥ ማምጣትን፡ እንደ ፍቱን ፈውስ ልንቆጥረው እንደ እምይገባ፡ በድጋሜ እየአስገነዘብን — በአመዛኙ አብረው ተቆራኝተው ተዛምደው ተዋህደው፡ እንደእየሁኔታው ሊስተናገዱ ይገባሉ በ ዕምንዕላቸው፡ ሃገርን እና ሕዝብን በ እምይመለከቱ፡ መሠረትዓዊ ኹነትዖች ዙሪያ በ ማውጠንጠን፡ የ አዘጋጅንአትን መጣጥፍ ይዘን፡ ዛሬም፡ በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበን አለ።

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የ ምንጊዜም ግብዣችን ነው።

በድጋሜ ሊከሰት እየአኰበኰበ የ አለ፤ አንድ ፈተና አለ። የ ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ፡ ከ እምይቀፈቅፋቸው ፈተናዎችአችን ውስጥ – አንድኡ። እንደእምትአስታዉሱት፤ ከ ወደ ስምንት-ወርዐት በፊት፡ በተካሄደዉ የ "ሃገርዓዊ ምርጫ" ሂደት ዉስጥ፡ የዛሬው መንግሥት-ተብዬ፡ "በምርጫው ከተሸነፍን፡ ጎንበስ ብለን ስልጣን እንአስረክብአለን" ሲል ተደምጧል። ያ-ን ይል የነበረው ለካ፤ ምርጫ-ተብዬውን [ባይ-ሁክ ኦር ባይ-ክሩክ] በዝረራ እንደ እምይአሸንፍ ዕርግጥኧኛ ስለነበረ ነው። ማረጋገጫችንም፤ ሂደትኡም ሆነ ውጤትኡ [አሳታፊም፣ ነፃም፣ ዲሚክረሲዓዊም ሆነ ፍትህዓዊ] እንድአልነበረ፡ በእምይገባ እየተከታተልን፡ መታዘብአችን እና የመዘገብንአቸው፡ በቂ አሳማኝ ማስረጃ ነጥቦች ናቸው።

የለመደች ጦጣ፤ እንድይል የሃገርአችን ሰው – ዛሬ ደሞ፡ሃገርዓዊ የምክክር ኮሚሽንን በተመለከተ፡ በ ሃገርዓዊው የ ምክክር መድረክ ላይ፡ የ መንግሥት-ተብዬው ከሥልጣን መልቀቅ፡ የ ኢትዮጵያን ችግርዖች እምይፈታ ነው ተብሎ ከታመነበት፡ ሳንአመነታ ስልጣን ለመልቀቅ ዝግጁ ነን ብሏል፡ እምይል ቧልት፡ ወደ ሰው ጆሮ እንድይደርስ እየተደረገ ነዉ።

ያ-ን እየአለ የአለዉ፤ [ልክ እንደ የ ምርጫ-ቦርድ] <u>ኮሚሽኑ</u> ባይ-ሁክ ኦር ባይ-ክሩክ፡ የ ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ፡ በስልጣኑ እንድይቀጥል እና እየተገበረው የ አለውን፡ የ ወራሪው ኦሮሙማ መሠሪ ተግባርዐትን፡ ስር እንድይሰዱ እምያስችልለትን ውሳኔ እንዲወስንለት ተደርጐ የተፈጠረ፡ የመንግሥት-ተብዬው ጉዳይ አስፈፃሚ አካል ሊሆን እንደ እሚችል፡ መጠርጠር እና እሚሠራቸውን ስራዎች ሁሉ፡ [ዝናብ ሆነ ብራ፣ ብርሃን ሆነ ጨለማ] እግር-ተ-እግር እየተከታተሉ፡ ኢትዮጵያን እና የ ኢትዮጵያን ሕዝብ እምይጐዳ ስራ እንድአይሰራ፣ ኢትዮጵያን እና የ ኢትዮጵያን ሕዝብ እምይጐዳ

ምክረ-ሃሳብ ምክረ-ውሳኔ ከመስጠት እንድይቆጠብ፡ ሃገርዓዊ ሕዝብዓዊ ታሪክዓዊ ሰውዓዊ፡ የጋራ ግዴታችን እና ሃላፊዕነትአችን አድርገን መውሰድ ይጠበቅብናል — የ ጥንትዓዊት ሃገር እና የ መቶ-ሃያ ሚልየን ጀግና ሕዝብ፡ የኅልውና ጉዳይ ነው እና!

እንደ እምይታወቀው፤ ኮሚሽንኡን የማቋቋምኡ ሂደት ተጀምሯል። በእዚህ ረገድ፤ መንግሥት-ተብዬው ኢኒሽየሽንኡን መውሰዱ፡ ከፋት አለው ብለን አንአስብም። ሆኖም-ግና፤ ረቂቁም ሆነ የፀደቀው አዋጅ፡ ኮሚሽንኡን ነፃ አካል ሆኖ እንድይመሠረት አያደርገውም – እንድይአውም፡ የመንግሥት-ተብዬው ጉዳይ አስፈፃሚ ከመሆን ሌላ አማራጭ አይኖረውም፡ እምይለው ስጋት፡ ትክክልኛ ስጋት ነው። የ-ስድስት-መቶ ምናምን ሰዎች የመጠቆም እና አርባ ገደማ የመጀመሪያውን ማጣሪያ እንድይአልፉ የተተገበረበት መንገድ፡ ግዙፍ ግድፈት የ አለበት ነው ብለንም ዕንዐምን አለን — <u>አሳታፊም ሆነ ትራንስፓረንት አልነበረም እና</u>። በ የ ኮሚሽንኡ ማህደር ላይ [ዴድ ኦን አራይቫል] እምይል ብይን ከማስፈርአችን በፊት፤ የ ሕዝብ ተወካይዖች ምክር ቤቱ፡ ይህእን የመጀመሪያውን ስቴፕ፡ አሳታፊ እና ትራንስፓረንት ይሆን ዘንድ፡ አከአሄድኡ ላይ <u>ዕርምት አድርጎ</u>፡ የ ጥቆማውም ሆነ የ መጀመሪያዎችኡ አርባ-ምናምን ዕጩዎች አመራረጥ፡ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ <u>እንደገና ሊከናወን ይገባል</u> እምይል ዕምነት እንድይኖረንም ተገድደናል።

ዕውነት፣ ዐውድ እና አሸናፊዕነት

ዕውነት ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሃገር እና ኢትዮጵያዊያን እንደ አንድ ህብር ሕዝብ፤ ግዙፍ ከናንድረም ውስጥ ተዘፍቀን አለ።

ዛሬም ቢሆን፤ ጥቅል መሠረትዓዊ ችግርአችን — የጎሣ ፖለቲካ፣ አክራሪ የጎሣ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ አሁን በስራ ላይ የአለው ፀረ–ኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሰረተው ዕኩይ ፌደራሊዝም፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት የ አለመኖር፣ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋዋምዐት የ አለመኖራቸው እና እነእኛን ሁሉ ተከትሎ፡ ለ 31-ዓመታት ያህል በተደጋጋሚ እየተከሰተ የ አለው፡ መንግሥትዓዊ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ እና ጀኖሳይድ፡ ብሎም ኢትዮጵያን የማሰቃየት የማፍረስ፡ የለየለት ወረራ፡ የ እርስ-በ-እርስ ጦርዕነት እና ኦሮሙማን የማንሰራፋት ዘመቻን — ይአካትት አለ። እናም፤ ዓይንአችንን ከ እነእርሱ እና ከ እነእርሱ ላይ፡ መንቀል አይኖርብንም።

በቅርብኡ ተደረገ የተባለለት ሃገርዓዊ ምርጫ፤ ሃገርዓዊም ዲሚክረሲዓዊም ፍትህዓዊም ነፃም ሊሆን እንደ እማይችል፣ የ ኢትዮጵያዊያንን ሃዘን ሰቆቃ እና ዕልቂት እንደ እምይአራዝም፣ አንድአችም ኢትዮጵያዊ ሃገርዓዊ ፋይዳ ሊኖረውም እንደ እማይጠበቅ በማስገንዘብ፡ የተባበረ ሁለገብ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ንቅናቄ በመፍጠር፡ አስገድደን ምርጫውን እንድይሰረዝ ማድረግ፡ አልያም ቦይካት ማድረግ፡ የግድ መሆንኡን በ ወቅትኡ፡ ድምፅአችንን ከፍ ጐላ አድርገን ማስገንዘብአችንን — ማስታወስ እንወድ አለን።

ፍላጐትአችንም፤ ኢትዮጵያ ድንበርዋን፣ ኢትዮጵያዊያን [ሰውዓዊ] መብታችንን ህብርዕነትአችንን አንድዕነትአችንን እስከእምናስከብር እና [የ ኢትዮጵያ ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ እስከ እምይአደርግ ድረስ፡ ሕዝብዓዊ ንቅናቄው ተጠናክሮ እንድይቀጥል እንድይቀጣጠል ነበር።

የሆነው ሆኖ፤ እንደ የፈለግነው ዓይነት ጠንካራ ሕዝብዓዊ ንቅናቄን መፍጠር ስለ አልተቻለ እና "ህይወት" መቀጠሉ ስለ እምአይቀር — እጅ እና እግርአችንን አጣጥፈን ከመመፃደቅ፡ አልያም ከመቆዘም ይልቅ፡ ኢትዮጵያን የ ዕምንዕል፡ ከድርጅት በላይ የሆነ የጋራ የተቀናጀ ስልጡን ቀመር በመጠቀም፡ ምርጫው ተጠናቅቆ ውጤቱ እስከ እሚታይ ድረስ — ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ፡ በሰፊ የድምፅ ብልጫ ሲሸነፍ፣ ከፖለቲካው ማማ ሲወርድ ሲባረር እና ኢትዮጵያዊዕነት ድል ሲያደርግ ማየትን፡ በምርጫው የመሳተፍአችን፡ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ ተልዕኮአችን አድርገን ልንወስደው ይገባን አለ፡ ብለንም ነበር። ተፎካካሪ ተብዬ ፓርቲዎች፤ እንድ-አንድዖችኡ፡ ተገድደው እንድአይሳተፉ ሲበየንባቸው፣ እንድ-አንድዖችኡ፡ በሙሉ ኃይልአቸው እንዳይንቀሳቀሱ መሪዎችን እስከ ማሠር የደረሰ ሳቦታጅ እና ግፍ ሲሰራባቸው፣ እንድ-አንድዖችኡ፡ በፈቃዳቸው አንሳተፍም ብለው፡ ምርጫው ምርጫ-የለሽ ሆኖ ቀርቷል። ይባስ ብሎ፤ መራጩ ዜጋ፡ ድምፅኡን፡ ለ የአሁንኡ መንግሥት-ተብዬ "በመቸር" [ግምት ነው ይሄ]፡ ዛሬ የ አለንበት [ሜስ] ውስጥ እንድእንዘፈቅ፡ ሆነን አለን።

በ ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ ላይ፤ ፍፁም ተመሳሳይ የሆነ ሃሣብ የአለን ወገንዖች፡ ምርጫውን በተመለከተ የነበረን አቋዋም፡ ቦይካት እስከማድረግ ድረስ በአለው፡ ተመሳሳይ ሆነን እየአለን – ያ ከአልተሳካ፤ በምርጫው ተሳትፈን እና ተገቢውን ጥረት አድርገን ለማሸነፍ እንታገል እምይለዉ ላይ ግና፡ መንገድአችን አንድ አልነበረም። አብረውን መቆም የ አልፈለጉ ወገንዖችአችን፤ የያዙት አቋዋም <u>ትክክል</u> ሆኖ እየአለ – አኩርፎ እጅ እና እግርን አጣጥፎ በመቀመጥ፡ እንዴት አሸናፊ መሆን እምይአስችል ዐውድ እንደ እምይፈጥርልን ግና፡ የነገሩን ነገር አልነበረም ወይም አሸናፊ መሆን እምይአስችል ሌላ ስራ፡ ሲተገበር ማየትም አልቻልንም።

ማለት፤ ትክክል የሆነ አቋዋም በመያዝ ብቻ፡ እንዴት አሸናፊ መሆን እንደእሚቻል፡ አልሰማንም አልአየንምም።

አሁን እም፤ የኢትዮጵያ ሃገርዓዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋምን በተመለከተ፡ በተመሳሳይ መልኩ – አንድ-አንድ ወገንዖችአችን፡ ኮሚሽንኡ የ መንግሥት-ተብዬውን ፍላጐት ከማምዋላት ዉጭ፡ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን መካስ እምይአስችል፡ ውጤት ማምጣት አይቻለውም የ እምይል፡ ትክክልኧኛ አቋዋም በመያዝ፡ አሁንም እጅ እና እግርአቸውን አጣጥፈው መቀመጥን፡ መምረጥአቸውን እየነገሩን ነው።

እኛ አሁንም ቢሆን፤ የኢትዮጵያ ሃገርዓዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋምን በተመለከተ፡ ሌላ እምይመረጥ ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ ንቅናቄ እየተደረገ ለመሆኑ ፍንጭ በ አለማየትአችን እና ኮሚሽንኡ ተመስርቶ የሆነ ውሳኔ ማስተላለፍኡ አይቀሬ መሆንኡን፡ ስለ ዕምነዐምን — ለተፈጠረው [ከ ቁጥጥርአችን

ዉጭ የሆነ] ዐዉድ፡ አግባብ ያለው ምላሽ በመስጠት፡ በ ሂደትኡ ዉስጥ፡ <u>በ ያገባናል ባይዕነት መንፈስ</u> [እንደምንም ኢንፊልትሬት በማድረግ] እና ተሳታፊ በመሆን፡ ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቃሚ እምይሆንኡበትን፡ አግባብ የአለው ኢንቫይሮንመንት የመፍጠር፡ ሃላፊዕነትም ግዴታም አለብን ብለን ነው፡ ዕንዐምነው። ወሳኝ የሃገር እና የሕዝብ፤ የ ኅልውና ጉዳይ ነው እና!

አልያ — እንዴት ለማሸነፍ እንደእምትአስቡ፤ እንዴት ኢትዮጵያ ድንበርዋን፣ ኢትዮጵያዊያን [ሰውዓዊ] መብታችንን ህብርዕነትአችንን አንድዕነትአችንን እንደእምናስከብር እና [የ ኢትዮጵያ ሕዝብ] – ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ እንደእምይአደረግ ንገሩን አሳዩን እና በተግባር ከጐንአችሁ እንእሰለፍ። ትክክል የሆነ አቋዋም በመያዝ ብቻ፤ አሸናፊዕነት እንደእምአይገኝ፡ ዕድሜ የ አስተማረን ዕውነታ ነው። ማለትም፤ አሸናፊ ሊይአደርግ እምይአስችል ስልት መቀመር'ም፡ የግድ ይላል፡ እየአልን ነው።

አዎን፤ አሸናፊዕነት ስእንል — በጥንቃቄ የተቀመረን ግብ፡ ዕውን ማድረግ ማለትአችን ነው። የ ሃሣብን ትክክልኛነትም ሆነ የ ሂደትን ስኬትዐማነት ብቻ ሳይሆን፤ በጥንቃቄ የተቀመረን ግብ፡ ዕዉን ሆኖ ማየትም ጭምር፡ ማለትአችን ነው። በ ፖለቲከኛ፤ አሸናፊዕነት ስእንል፡ የ ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትን ሃሣብ፣ የ ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትን ራዕይ እና የ ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነትን ዕምነት፡ በጥብቅ በ አቆራኝ አግባብ፡ እምይጠይቀዉን ፈርጀ-ብዙ ሕዝብዓዊ ንቅናቄ ለማደራጀትም ሆነ በቆራጥነት ለመምራት ይቻል ዘንድ፡ አይበገሬ ሕዝብዓዊ ኃይል ተፈጥሮ — ኢትዮጵያ፡ ዳር-ድንበርዋን ሃገርዓዊ አንድዕነትዋን እና ሉዐልዓዊዕነትዋን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሞ፡ [ሰውዓዊ] መብትኡን ህብርዕነትኡን አንድዕነትኡን፡ እንድይአስከብር እና ፍፁምዓዊ የ መንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነትኡን ቁልፍ፡ በቁጥጥርኡ እምይአደርግባትን ዕለት፡ ዕውን ሆና ማየት፡ ማለትአችን ነው።

ያ-እንን ሁሉ መንገድ የተጓዝነው፤ በተለይ፡ በንፁህ የኢትዮጵያዊዕነት መንፈስ፣ በቅንዕነት እና በፅናት፡ በፍልሚያው ዉድ መሥዋዕትዕነት በመክፈል ላይ ለአሉ፡ ወገንዖችአችን – ኢትዮጵያ፡ አሸናፊ ሆና ዕምንአይባትን ዕለት፡ ለአንዲት ናኖ-ሰከንድም ቢሆን፡ ፈጠን ለማድረግ፡ መያዥያ መጨበጫ የአጣው፡ በይነመረብ መርአሽ ወፍ-ዘራሽ ትግል፡ መሬት-ረግጦ፡ ፈር-ይዞ፡ ሕዝብዓዊ ንቅናቄው፡ ነፍስ-እንድይዘራ ፈርጠም-እንድይል እና እስከዛሬ የአልተጓዝንበት መንገድ ከአለ ለመምከር፡ ከምንጊዜውም በላይ፡ ነገ-ሳይሆን-ዛሬ፡ ከ ስልጣን/ድርጅት በላይ ሆነን፡ በ የተሻለ መልክኡ ቢጋራ ማስላት እንደእሚገባን፡ ማንአችንንም ብቸኛ ተጠያቂ ሳንአደርግ፡ ለ ማስገንዘብ ስለፈለግን ነው።

*ተጓዳኝ እርምጃችን*

የ [ሰው] ልጅ፤ በተዘራበት በበቀለበት ስፍራ እና ጊዜ ቀመር ላይ ደገፍ ብሎ፡ ከሌሎች እንስሣት በተለየ መልኩ፡ እንደ አግባብ-ነገሩ፡ እየበዛ እየተባዛ [ግዙፍ ውስብስብ ውጥንቅጥ ኳላ-ቀር ወይም ስልጡን] ማህበረሰብዓዊ ህይወት ለመምራት የቻለ፡ የ ዕምላክ መለኮትዓዊ ኃያልዕነት መገለጫ ፍጡር ነው። አለመታደልአችን፤ የእዚህ ምስቅልቅል ማህበረሰብዓዊ ህይወት አንዱ ገፅታ፡ ጦርዕነት ሆኗል። [ሥርወ ጦርዕነት] ከ የሰው ልጅ ኢንቨረንት ራስ-ወዳድ ባህሪይዕነት፣ እስከ የሰው ልጅ ማኅበረሰብዓዊ ግንኙነቶች እሚፈጥሯቸው አለመጣጣሞችን ለመቋጨት በእሚል እሚወሰድ ኃይል የተጨመረበት እርምጃዕነት፣ እስከ ሁለትኡንም በእምይአካትት መልኩ እሚቀመር፡ የ መላ-ምት ምህዳር ውስጥ፡ እምይስተናገድ ኹነት ነው።

በ ዓለምአችን የአሉ የዘመኑ ጦርዕነቶች፤ በአመዛኙ፡ የ[ሰለጠንን] ነን እያ አሉ እሚምሉ እሚገዘቱ ፖለቲከኞች፡ የሃሳብም ሆነ የአቋም ልዩዕነቶችን ስልጡን በሆነ መንገድ መፍታት እማይሆንላቸው መሆኑን፡ በ ስሁት ውሳኔዎችአቸው እና ኃይል በተሞላባቸው አሰቃቂ እርምጃዎችአቸው እሚገልፁባቸው፤ በ የለየለት ዕብደት እሚለኩሷቸው የመጥፋት እና የመጠፋፋት ["ድግስዖች"] ናቸው። ትክክል። ጦርዕነት — የሰው ልጅ፤ በ እራሱ፣ በ ሌሎች ፍጡራን እና በ ኢንቫይሮንመንት ላይ ከእሚፈፅማቸው ዘግናኝ ውድመቶች መሃከል አንዱ ነው። ጦርዕነት፤ በ ሃገርዐት መሃከል ወይም በ አንድ ሃገር ውስጥ በ የተለያዩ ቡድኖች መሃከል፡ መደኛም ሆነ መደበኛ የአልሆነ፣ የተደራጀ፣ ዘመኑ የፈቀደውን መሣሪያ የታጠቀ ቡድንን ወይም ሥርዐዊትን በመጠቀም እምይደረግ፡ የመጥፋት የመጠፋፋት: ዘግናኝ ትዕይንት ነው።

ለ የአለፉት 50-ዓመትዐት ገደማ፤ ኢትዮጵያዊያን [ከ ሶማሊያ ጋር ከተደረገው ጦርዕነት በስተቀር] ቀጥተኛ በሆነ መልኩ የውጭ ጠላት መጥቶብን ሳይሆን፤ እርስ በ እርስአችን በፈጠርናቸው ችግሮች ሳቢያ፤ ማብቂያ በሌላቸው ጦርዕነት'ዖች ውስጥ ተዘፍቀን — ለ የ[ሰው] ልጅ ህይወት ደንታ የሌለን፣ ለሃገር ሉዐልዓዊዕነት ክብር የሌለን፤ የበሽታ ቋት የሆንን፣ ሰላም የአጣን፣ ራስአችንን መመገብ እማንችል፣ በሁሉም መመዘኛዎች የ ዓለም ሃገርዐት ጭራ የሆንን፣ ከረባት አጥላቂ ማፈሪያዎች ሆነን ቀርተናል። ዛሬም፤ በ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ እጅጉን በባሰበት መልኩ እየተደረጉ የ አሉት ጦርዕነት'ዖች — [ቢብሊካል ፕሮፖርሽን] ሊባል በ እሚችል መጠን፤ የሃገር ክህደት እና ሃገር አፍራሽዕነት፣ ሽብርተኛዕነት፣ ጀኖሳይድ፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ'ን፣ ወራሪዕነትን እና የጦር ወንጀለኛዕነትን ጨምሮ፡ ዘግናኝ ሰቅጣጭ አረመኔዓዊ ዕልቂት እና ሰቆቃ በማስከተል: ኢትዮጵያን ወደ የ ምድር ገሃነምዕነት ቀይረንዐት አለን። ለመሆኑ፤ ኦሮሚያ ውስጥ አልአባራ ለአለው፡ የ ዐማራ ጀኖሳይድ፡ ተጠያቂዎችኡ ለፍርድ እምይቀርቡት መቼ ነው?

የ ጦርዕነት ነገር ሲነሳ፤ ሪል-ታይም ተሞክሮአችን እየነገረን ያለው ዕውነታ፡ በ ዐማራ እና በ አፋር ሕዝብ ላይ፡ በ ህወሓት ወንበዴዎች እየተፈፀመ የአለው [ጀኖሳይድ]፡ ደጋግመን ለማስገንዘብ እንደሞከርነው፡ ቆራጥዕነት እና ቅንዕነት የተሞላበት ዕርምጃ በመውሰድ፡ በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት መቋጨት፡ ይገባም ይቻልም ነበር። ዛሬም ቢሆን፤ ይገባልም ይቻላልም፡ ብለን ነው፡ ዕምንዐምነው።

ሆኖም፤ እንደአስፈላጊዕነትኡ፡ ንግግርም ውይይትም ሆነ ድርድር፡ እምአይቀር መሆኑን አንአጣዉም። ከ ህወሓት ጋር

እየተደረገ የአለውን ጦርዕነት፡ በጦርዕነት ማሸነፍ አይቻልም እምይሉ ፍጡራን፡ ከ[ቲር-1] የ ህወሓት ቡችሎች እና ርዝራዦች ይልቅ፡ [ቲር-2] በትውልድ ትግሬ የአልሆኑ፡ እወደድ ባይዎች እና አሽቃባጮች ናቸው። አንድ-አንዶቹ ቅጥረኛዎች እንደእምይሆኑ መገመትም፤ ከዕውነታው መራቅ ይሆናል ብለን አንሰጋም። ጦርዕነትኡ እንድይቆም ሲጠይቁም እንኳን፤ አንድም ቀን ህወሓት ዉግያ ማቆም አለባት ሲሉ ተደምጠው አይታወቅም። ይህእንን ዕውነታ ለማስተባበል ሲሞክሩ፤ የ ቮካል-ኮርድአቸው ሪዝም ሳይቀር፡ ግራ ሲጋባ እየአስተዋልን ነው። ትክክል። ሁልጊዜም ቢሆን፤ [አት ዘ ኤክስፔንስ ኦፍ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን] ነው፡ ጦርዕነቱ እንዲቋጭ እምይወተዉቱት።

*መንግሥት-ተብዬው፤* ጦርዕነቱን ስለአስተናገደባቸው አንጀት-አቁሳይ *መንገድዎች፡* ብዙ-ብዙ ስለአልን አንደግመውም። ንግግርን ውይይትን ድርድርን በተመለከተ ግና፤ ዛሬም ቢሆን ተቀዳሚ ትኩረትአችን አይደሉም። እኛ፤ ጦርዕነቱን በ ቆራጥዕነት እና በ ቅንዕነት በማካሄድ፤ ህወሓት ብቻ ሳትሆን፡ ኦነግም ጭምር እንድይከስሙ ማስገደድ ነው መፍትሄው፡ ብለን ነው ዕምንዐምነው። የ ችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነው ኢትዮጵያዊም፤ ትኩረትኡም ሆነ ምርጫው፡ ንግግር ውይይት ድርድር ላይ ሳይሆን፡ በቆራጥዕነት ታግሎ፡ ኢትዮጵያን አጠናክሮ ማስቀጠል እና ህልውናውን ማስጠበቅ ላይ ነው። ወደ ትግራይ ክልል ዘልቀን አንገባም እምይለው ሴንስለስ ውሳኔ እየአስከፈለን የአለውን ሰቆቃ እና ዕልቂት፤ እነ እንቶኔን ሳይሆን፡ የዐማራን የአፋርን ሕዝብ ጠይቁት። ይነግርአችኋል። የ መንግሥት-ተብዬው አቋም፡ ካቴጎሪከሊ ከ እኛ የተለየ ነው። ስልጣኑን አደጋ ላይ እምይጥል ኹነት እስከአልተፈጠረ ድረስ፤ ለ ሃገር ዳር-ድንበር አለመከበርም፣ ለ ሰላም እና መረጋጋት መጥፋትም ሆነ ለ አልአባራ ለአለው፡ ሰቆቃ ዕልቂት እና ለ ሕዝብ ህይወት-አልባዕነት፡ ደንታ የሌለው አካል ነው እና!

የሰሞንኡን ንግግር ውይይት ድርድር በተመለከተም፤ ሊደርሱ እምይችልኡ፡ ሦስት ግዙፍ ስህተትዖች ይታዩናል። <u>ስህተት አንድ</u> – ህወሓት እና ኦነግ፡ ትጥቅ ሳይፈቱ እና ድርጅትዖችአቸውን ሳይአከስሙ፡ ወደ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር መቀላቀል ወይም የመንግሥትዕነት ስልጣን እንድይጋሩ ማድረግ፣ <u>ስህተት ሁለት</u> – ይህ "ክልል" እምይባል ነገር እስከአለ ድረስ፡ ወልቃይት፣ ጠገዴ እና ራያ ከዐማራው እጅ እንድይነጠቁ ማድረግ እና <u>ስህተት ሦስት</u> – የሃገር የሕዝብ አለኝታ ከሆነው [ፋኖ] ጋር፡ አምባጓሮ መፍጠር። ንግግርኡ ውይይትኡ ድርድርኡ፤ ከእነዚህ ስህተትዖች አንዱን እንኳን ከፈፀመ – ጦርዕነትኡን ማስቆም እምአይቻልበት ውጥንቅጥ ውስጥ እንደ እምንዘፈቅ እና በ ኢትዮጵያችን ሰላም ለመፍጠር፡ ለዘመንዐት መፋለም እንደእሚኖርብን፡ ዕርግጠኞች ነን። በነገራችን ላይ፤ ናይሮቢ እየተካሄደ ነው በተባለለት ድርድር፡ ተሳታፊ ነበሩ የተባሉ ሰዎች [ዕውነት ከሆነ] በቅርብኡ፡ መጥፎ ዜና እንደእምንሰማ፡ አትጠራጠሩ።

እንደ ማጠቃለያ

የተደቀኑብን ፈተናዎች፤ ብዙ ናቸው። ሆኖም፤ በ አመዛኙ፡ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ ተደርጐ ሊወሰድ እምይገባው፡ ጥቅል ችግርአችን — የ ዘመንኡን ከፉ ዕውነትዐ፡ በ ቆራጥዕነት መጋፈጥ <u>ፈርተን</u>፣ የ ኦሮሙማ ዓይን-የአወጣ ወረራ በፍጥነት እየተንሰራፋ መሆኑን መገንዘብ ተስኖን፣ ፓለቲካችንን ፈር ማስያዝ እና ከ አክራሪው የ ጎሣ-ፖለቲካ ጋር የገጠምነውን ፍልሚያ፡ በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት ለመቋጨት፡ እምይመጥን ትግል ማካሄዱን፡ አልደፈርነውም። በተጓዳኝም፤ የ ሕዝብአችንን ሰቆቃ እና ዕልቂት፡ እንድያከትም ማስገደድ አለመቻልአችን ብቻም ሳይሆን፡ በ የውስጥ አፍራሽ ኃይሎች ለ ገር መፍረስ አደጋ ተጋልጠን፣ በ ጐረቤት ሃገርም ዳር-ድንበርአችን ተደፍሮ፡ ተዋርደን አለን። ለ እነእዚህ ሁሉ መሠረታዓዊ ምክንያትአቸው፤ ኢትዮጵያችን፡ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥትም ሆነ ኢትዮጵያዊ የሆነ ህገ-መንግሥት የሌላት ሃገር፡ በ መሆንዋ ነው — አራት ነጥብ

መፍትሄው ግልፅ ነው። በስልጣን ላይ የአለው፤ መዐከልዓዊ መንግሥት-ተብዬው፡ የ አዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ፡ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት አግባብ፡ የ ሕዝብን ስልጣን፡ ለ ሕዝብ እንድይአስረከብ ሊገደድ የግድ ነው። በ እዚህ መልኩ የመወገድን ወርቃማ ዕድል እምአይጠቅምበት ከሆነ፤ በ ህወሓት በ ኦነግ እና በ ራስኡ በ ብልፅግና፡ እየተፈፀመ የ አለውን፡ የ ለየለት ወረራ፣ የ እርስ-በ-እርስ ጦርዕነት፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጀስ ክሊንዚንግ፣ ጄኖሳይድ፣ ሃገርን የማፍረስ እና የኦሮሙማን ዓይን-የአወጣ የመንሰራፋት የተቀናጀ ዘመቻ — ሳይውል ሳይአድር፡ እንዲቆም እንዲቋጭ ማድረግ፡ ግዴታው መሆኑን፡ አፅንዖት በመስጠት፡ ማስጠንቀቅ እንፈልግ አለን።

ጐን-ለ-ጐንም፤ መዐከልዓዊ መንግሥት-ተብዬው፡ የ ኢትዮጵያ ሕዝብን፣ የ ኢትዮጵያ የፖለቲካ እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጥምረት በማቀናጀት፡ ኢትዮጵያዊ የ ሽግግር መንግሥት፡ እምይፈጠርበት ሂደት፡ በቁርጠኛዕነት እና በቅንዕነት ይጀመር ዘንድ፡ ዕንቅፋት ከመሆን፡ ራስኡን ያቅብ ብለንም፡ ማስገንዘብ ዕንወድአለን። ይ-ህ ልመና፣ ማመልከቻ ወይም ምልጃ እሚላክበት ጉዳይ አይደለም። መዐከልዓዊ መንግሥት-ተብዬው፤ እንደ አንድ ስልጡን አካል፡ በ የ መንግሥትዕነት ቦታው ላይ እስከአለ ድረስ፡ ኢትዮጵያ ከሽብርተኛው ኢህአዴግ፣ ከ የ ኤትኒክ-ፌደራሊዝም የአስተዳደር ስርዐት አገዛዝ፣ ከሰቆቃ እና ከዕልቂት ትልአቀቅ ዘንድ፡ የዛሬ 4-ዓመት በፓርላማው ፊት የገባውን [ቃል] እንድይፈፅም እምይአስችለው — ግዴታው አንጂ!

በጋራ ልብ እንበል ጎበዝ፤ መዐከልዓዊው መንግሥት-ተብዬ፡ ስር-ነቀል ለውጥ [ሪቮልዩሽን[ ሳይሆን፡ ጥገናዊ-ለውጥ [ሪፎርም] ነው እየአካሄድኩት የአለው እምይለው፡ ግዙፍ መንግሥትዓዊ ቅጥፈት ነው። ዕውነትዐው፤ እንደ እየ አግባበ-ነገሩ ሁለቱንም ዓይነት ለውጦች ነው እየአካሄደ የአለው። ችግርኡ፤ ስር-ነቀል ለውጥኡን እምይጠቀምበት፡ ኦሮሙማን ለማንሠራፋት እምይአግዙ፡ ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ኢትዮጵያዊ መሠሪ ለውጥዖችን ዕውን ለማድረግ ሲሆን ብቻ ነው። ይ-ህ ክሬዚነስ፤ ሪቨርስ መደረግ ይኖርበታል።

እናም፤ እምንጠብቀው የሽግግር መንግሥት፤ ዳር ድንበራችንን ያስከብር፡ ሰላም እና መረጋጋትን ያስፍን፣ የ ሁሉንም ተቋምዐት

ተግባርዐት በሃላፊዕነት ይምራ፣ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበት ምርጫ፡ ፍትህዓዊ እና ነፃ መሆኑን ለማርጋገጥ እሚያስችሉ ተቋምዓዊ ለውጦችን ተግባርዓዊ ያድርግ። ኢትዮጵያዊያንን በሙሉ የአሳተፈ፡ አዲስ ስልጡን ህገመንግሥት ይቅረፅ። የጎሣ-ፖለቲካን እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶችን በህግ ይገድብ። በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተውን ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ያድርግ። በምትኩም፤ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እምይአስችል ድልዳል ይአካትት። ሰው በሰውእነቱ ብቻ እምይከበርበትን፤ በ ዜግነት ላይ የአተኮረ እና የ ቡድን ጥያቄዎችን የአገናዘበ መርህን እምይከተል፡ በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፡ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድልኡን እምይአገኝ፡ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት ይመሥርት። እናም፤ ኢትዮጵያ ሰላም ታግኝ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንእገንአኝ –

# የ ትዉልድዕችን ፍፁምዓዊ አደራ

መጋቢት ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ‖ ማርች 2022

**ትኩረትአችን** – ኢትዮጵያን [እስከ እነጉድለትዋ] የ ዕምንወድዐት፤ የ እኛ፡ የ ሁልዐችንም ስለሆነች ነው። በ ታላቅዕነትዋ፤ በ ወል የ ዕምንኮራባትን ያህል – ለ ጉድለትዋ'ም ተጠያቂዎቹ፡ ኢትዮጵያዊ ነን ዕምንዕለው ልጆችዋ በጋራ እንጂ – ተጠያቂዎቹ፡ የ ኢትዮጵያ መልከዐምድርም ሆነ፡ የ ኢትዮጵያ ንፁህ ሰንደቅ-ዓላማ አይደሉም። ኢትዮጵያዊ ነኝ እየ አሉ፤ ኢትዮጵያን አለመውደድ – ኢትዮጵያዊ ነኝ እየ አሉ፤ አኩሪ ታሪክዋን ማጉደፍ፡ ቅርሶችዋን ደብዛ ማጥፋት – ኢትዮጵያዊ ነኝ እየአሉ፤ ንፁህ ሰንደቅ-ዓላማዋን አለማክበር፡ በፍፁም የጤና ሊሆን አይችልም። በ ፕላኔት ምድር ላይ፤ እንደአለ ማንአቸውም ሃገር'ም ሆነ ማህበረሰብ፡ እኛም፡ አጀማመርአችንም ሆነ ለዘመንዐት የተከተልነው አከአሄድአችን፡ አልጋ-በ-አልጋ ሊሆን አይጠበቅበትም። ሌሎች ሃገርዐት፤ በስልጣኔ በሰላም፡ ከ እኛ ርቀው የተጓዙት፡ [ትናንትን] እንደ ትምህርት ወስደው፡ ጥፋትዖችን በአለመድገም እና ጠንካራ ጎንዖችን የበለጠ በማጎልበት፡ [ነገን] የተሻለ ለማድረግ፡ [ዛሬ] ተግተው በጋራ ስለሰሩ ብቻ ነው። ሌላ ምንም ተዐምር የለውም። ኢትዮጵያ የ እምትባል፤ ህብር ማህበረሰብን አቅፋ የያዘችን ሃገር ፈጥሮ፡ ውድ መስዋዕትዕነት እየከፈለ የ አቆየልንን፡ [የ አባት የ እናት፣ የ አያትዖችአችን፣ የ ቅድመ አያትዖችአችን] ዘመን ተሻጋሪ [ሰለፍለስ] ብርቅዬ ትውልድ'ን፡ በ የተንሸዋረረ ዕይታችን የፈጠርንአቸውን መሠረተ-ቢስ ተረክዖችን እየደረደርን — ተሠራ ዕምዕንለውን "ስህተት" ለማረቅ፣ ለማስተካከል፣ ዕድገት እና ስልጣኔን ለማምጣት እና ስልጡን የፖለቲካ ስርዐትን ለመገንባት፡ ረብ የአለው ስራ መስራት ተስኖን፡ ዛሬም ድረስ፡ በጅምላ፡ "እገሌ የአደረሰብን በደል ነው" እየአልን ኤክስተርናላይዝ ማድረግኡን ተያይዘነው መገኘትአችን፤ እጅግኡን አሳፋሪ ነው። መቶ ሁለት-መቶ ዓመትዐት ወደኋላ እየተጓዝን፤ በአልነበረ በአልተፈጠረ በደል እና ጭቆና ተረክ አብደን፡ ራስአችንን ወደ አውሬዕነት፣ ወደ አረመኔዕነት፣ ወደ ካኒባልዕነት ለውጠናል። እንዲያው ተፈፅመዋል ቢባል ዕንኳን፤ [ጥንት] ተሰራ የ ዕምዕንልኸውን "ስህተት" እይአመነዠክን በመኖርአችን፡ ግብረ-መጥፎ ከመሆንአችንም በአሻገር፡ በሽተኞች ጭምርም ሆንኧን አለ......[ጌት አቨር ኢት!]። በ ቅርብኡ፤ (ሀ) ስድስት-ኪሎ በ እምይገኘው የ ሰማዕትዐት ሃውልት ዙሪያ – በ የካቲት-12 ዕለት፡ 85ኛው የ ሰማዕታት ቀንን፡ (ለ) ፒያሳ በ እምይገኘው የ እምዬ ምኒልክ ሃውልት ዙሪያ – በ የካቲት-23 ዕለት፡ 126ኛው የ አደዋ-ድል ዓመትዓዊ በዐልን፡ እንድይሁም፡ (ሐ) ከ ጥቁር-አንበሣ ሆስፒታል ወረድ ብሎ በ እምይገኘው፡ የ ትግልዐችን ሃውልት ዙሪያ – በ የካቲት-26 ዕለት፡ 44ኛው የ ካራማራን-ድል፡ በጋራ በደስታ በማክበር፡ ኢትዮጵያዊ ክብር እና ኩራትአችንን፡ ማደስ እና ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ እንኳን ሲይአድአግተን በማስተዋልአችን፡ እጅግኡን አዝነናል። ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እየአለ እምይደሰኩረው፤ ወራሪው መንግሥት-ተብዬ፡ በዐልዐትኡ እንድአይከበሩ መንግሥትዓዊ-ደባ ከመፈፀሙም ባሻገር፡ በ ዕለትዐትኡ፡ ከ ሃገር እና ከ ሕዝብ ተደብቆ ተሰውርዖ በመዋልኡ — ኢትዮጵያችን፡ ኢትዮጵያዊ መንግሥት የላትም የ ዕምንዕለውን ዕውነትዐ፡ አረጋግጦልናል። በወቅትኡ፤ የፋሽስት ጥልያን ወራሪ አረመኔዎች የአደረሱት ዘግናኝ ጭፍጨፋ – ለዘመን ተሻጋሪው፡ ጀግናው ህብር-ማህበረሰብአችን፡ ፈታኝ ክስተት ሆኖ ማለፍኡ አያጠራጥርም። ክስተትኡ፤ የፈጠረው – የ ኢትዮጵያን ሉዐልዓዊዕነት የመጠበቅን ክብር፣ ወራሪዎችን የመፀየፍን ታላቅዕነት እና የ ግዙፍ ጀግናዕነትን ፅንኡ መሠረት፡ በ ወገንዖችአችን ልብ ውስጥ ተክሎ ማለፉ ግና — ሌላ ሳይሆን፡ በጋራ፡ ኩሩ እና ዕድልኸኞች ሊይአደርገን ብቻ ነበር እምይገባው። የሰማዕታት ቀንን ማሰብ እና መዘከር፤ በ ሃዘን፡ ራስአችንን ለመጉዳትም ሆነ በቀልን ለመጫር ሳይሆን፡ የ ሃገር ሉዐልአዊዕነትን በማስከበር እና የ ህብር-ማህበረሰብአችንን አንድዕነት በማጎልበት፡ እንዲያ የአለ ዘግናኝ ኹነት፡ እንድአይደገም፡ በጋራ እርግጠኞዎች ለመሆን፡ ማስታወሻ እንድይሆነን ሲባል ነው። በወራሪው የ ፋሺስት ጥልያን ላይ፤ እየአደገ የመጣው ቁጭት፡ ጉልበት ሆኖት – በ ዓይነቁራኛ ይጠብቃቸው የነበረው ወገንአችን፡ የፈጠረው ታሪክዓዊ ዳራ እንደ ምክንያት ሆኖት፡ የዛሬ 126-ዓመት ጀግናዎቹ ወገንዖችአችን የተቀናጁት የአድዋ-ድል፡ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን፡ በ ጀግንነታችን፣ በ አንእገዛም፣ በ አንደፈርም ባይዕነትአችን እንድእንትታወቅ – ለአፍሪቃዊያን፣ በ ዓለም-ዙሪያ ለአለው ጥቁር ሕዝብ እና ለ ሌሎች በጭቆና ስር ለወደቁ የሰው ልጅዖች ሁሉ፡ የ[ሰውዓዊነት] ሮል-ሚድል መሆናችን፡ በፍፁም ሊካድ አይችልም። የ ካራማራንም ድል ስእንእዘክር፤ የ እዚህኡ ዘመን-ተሻጋሪ ፀጋ ውጤት መሆኑንም ጭምር እየአሰብን መሆኑ፡ የበለጠ ሊያኮራን ይገባል። ጎበዝ፤ እንዲህ የአሉ የ ጀግና የ ኩሩ ህብር-ማህበረሰብ ታሪክዖችአችንን፡ [ሳንበርዝ ሳንአደበዝዝ ሳንደልዝ ሳንከልስ ሳንአዛንፍ ሳንአጉድፍ] ለ እምይቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ የ እምንእችለው — ኢትዮጵያችን፡ በ ከሃዲዎች በ ወራሪዎች ስትእንገላታ እና ሰንደቅ-ዓላማችን ሲደፈር፡ ዝም-ብለን በማየት ሊሆን አይችልም። የ ኢትዮጵያን እና የ ኢትዮጵያዊዕነትን ኅልውና በአግባብኡ ተንከባክበን፡ ለ እምይቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ — ከ ዘመን ተሻጋሪው ቀደምት ኢትዮጵያዊ ትውልድ የተረከብነው፡ ፍፁምዓዊ አደራ ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

ሰላምታችን፤ እንዲያው ሲቪልዕነትአችን ስለእምይገዛን ብቻ፡ ዕምዕንአደርገው አይደለም። ይልቁን እስ፤ ደስታችሁ-ደስታችን፣ ሃዘንአችሁ-ሃዘንአችን፣ ህመምአችሁ-ህመምአችን መሆኑን እና ምንጊዜም እምአይዛነፍ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ወገንዓዊዕነትአችንን፡ በ ቅንዕነት ለማንፀባረቅም ጭምር እንጂ! ዛሬም እንግዲህ፤ በመሠረትዓዊ ሃገርዓዊ ሕዝብዓዊ ኹነትዖች ዙሪያ በማውጠንጠን፡ የአዘጋጀንአትን መጣጥፍ ይዘን፡ በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበን አለ።

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የ ምንጊዜም ግብዣችን ነው።

ኢትዮጵያን እምይል ሁሉ፤ በተለይም፡ ለፖለቲካው ቀረቤታ የአላችሁ ወገኖች፡ በንቃት በጥንቃቄ ሊከታተለው እና በ ይአገባኛል ባይዕነት መንፈስም፡ ፕሮአክቲቭሊ ተሳታፊ በመኾን፡ ታሪክዓዊ ግዴታውን መወጣት አለበት ብለን ዕምንዐምነው ጉዳይ፡ በሂደት ላይ ነው። አዎን፤ የሃገርዓዊ "የምክክር" ኮሚሽን የማቋቋምን ሂደት፡ ማለትአችን ነው።

የ ሃገርዓዊ የ ምክክር ኮሚሽን፤ ተቋቋመ አልተቋቋመ፡ ምንም እምይአመጣው ለውጥ የለም፡ እምይል ወገን እንደአለ ግልፅ ነው። ህወሓት መርዐሽኡ ኢህአዴግ፤ በ 1980ዎቹ መጀመሪያ ገደማ፡ አራት-ኪሎ'ን ከተቆጣጠረ በኋላ፡ ኤርትራን አስገንጥሎ ኢትዮጵያን ማፍረስ ሲጀምር፡ ቀሪው ኢትዮጵያዊ፡ እጅኡን አጣምሮ ከመመልከት በአለፈ፡ አንዲት ቃል ትንፍሽ ሲል አልተሰማም። ዛሬም፤ ኦዴፓ-ኦነግ መርዐሽኡ ኢህአዴግ፡ የቀረችውን ኢትዮጵያ ፍርክስክስ ሲይአደርጋት እየአየን እየሰማን፡ ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ፡ ዝም ብለን ከሩቅኡ

መመልከቱን የመረጥን ይመስላል። እኛ፤ ይህ ሌይድ-ባክ አትቲዩድ በፍፁም አይመችንም።

ለማንኛውም፤ (ሀ) ከ አጀማመሩ እስከ ማብቂያው ድረስ፤ ሂደትኡ፡ አሳታፊ፣ ግልፅ፣ ከማንአቸውም ተፅዕንዖ ነፃ በሆነ እና ሕዝብዓዊ ተዐማኝዕነትን በአስመሰከረ መልኩ፡ ከተከናወነ፡ (ለ) ቅድሚያ ሊሰጣቸው እምይገቡ፡ ወሳኝ ሃገርዓዊ እና ሕዝብዓዊ ጉዳይዖችን፡ በ ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነት መንፈስ መምረጥ ከተቻለ፡ (ሐ) ፈውስ በመሆን ሊያገለግሉ እምይችሉ፡ ምክረ-ሃሳብዖችን ምክረ-ውሳኔዖችን ማቅረብ ከተቻለ፡ እናም – ወደ ተግባር ተለውጠው ለማየት እምይአስችል ቁራጥዕነት እና ቅንዕነት፡ ከመንግሥት-ተብዬው በኩል ማግኘት ከተቻለ — በ እምይል [ሆፐፉል-ኦፐቲሚዝም]፡ እኛ፡ አጠቃላይ ሃሳብኡን በአወንታዊዕነትኡ፡ ማስተናገድኡን መርጠን አለ።

ሂደትኡን በተመለከተ፤ ተአጀማመርኡ፡ የ ሃገርዓዊ የ ምክክር ኮሚሽንኡን የማቋቋምኡ ስርዐት በራስኡ፡ ግዙፍ ግድፈት ነበረበት። የ 632 ተጠቆሙ የተባሉት ሰዎችን እና 42 ደሞ የመጀመሪአያውን ማጣሪያ የአለፉ በሚል ይፋ የተደረጉትን ሰውዖች በተመለከተ፤ አሳታፊም ትራንስፓረንትም ስለአልነበረ፡ ሂደትኡ – ከወዲህኡ፡ ሕዝብዓዊ-ተአማኝዕነትን እና ሕዝብዓዊ-ቅቡልዕንትን፡ ማግኘት አልቻለም። በ ጊዜው፤ ዕርምት ተደርጎ፡ ሂደትኡ እንደገና ሊጀመር ይገባ ነበር። ያ-ም አልተደረገም።

ቀጣዩ ስራ፤ ከ 42-ሰውዖች መሃከል፡ 11 ዕጩዎችን መርጦ ለ ሹመት በማቅረብ፡ በ ምክር-ቤትኡ ማስፀደቅ ነበር። የ ሕዝብ ተወካይዖች ምክርቤት ፊትአውራሪዖች፤ ቅን ቢሆኑ ኖሮ — 632'ኡን "ተጠቆሙ" የተባሉትን ሰውዖች፡ አልያም፡ 42'ኡን በመጀመሪያው ዙር አልፈዋል የተባሉትን ሰውዖች፡ ለ ምክር-ቤትኡ አባልዐት በማስተላለፍ፡ ምርጫቸውን እንድይአቀርቡ እና ቀጥሎም፡ በድምፅ ብልጫ እምያልፉትን 11-ሰውዖች እንድይምርጡ፡ ዕድሉን ቢይአገኙ፡ የተሻለ አሰራር በሆነ ነበር። ያ-ም አልተደረገም። ይባስ-ብሎ፤ 3-ሰውዖችን፡ [ከየት እንድየት ለምን] እንደመጡ በ አልታወቀ ኹኔታ፡ ለማስፀደቅ ብቻ ወደ ምክር-ቤቱ አቅርበው ተገኝተዋል። ይህ በፍፁም መደረግ አልነበረበትም።

መኾን እምአይገባቸው ሁሉ ሆነው፤ ዛሬ፡ 11-የሃገርዓዊ የ ምክክር ኮሚሽን አባልዐት ተመርጠው፡ ኮሚሽንኡ ተመስርቶ አለ። እኛ፤ ከ አንድ-ሁለትኡ በስተቀር፡ የተቀሩትን ተሿሚዎች፡ አንአውቃቸውም። ደግዕነቱ፤ ስለ ኮሚሽንኡ፡ እምንሰጥአቸው ሃሳብዖች እና አስተያየትዖች፡ ከ ግለሰቦች ጋር እምይገናኙ በ አለመሆንአቸው – ተሿሚዎችን አለማወቅአችን ፐር-ሴ፡ ብዙም አይጐረብጠንም። እኛ፤ የሂደትኡ አጀማመር እና የሂደትኡ አቅጣጫ [አሳታፊ ግልፅ ሕዝብዓዊ-ተቀባይዕነትን እና ሕዝብዓዊ-አመኔታን የአገኘ] እንድይሆን፣ መሠረትዓዊ ችግርዖችአችን እንድይካተትኡ፣ ቅን ፈጣን ፈውስ እምይሆንኡ ምክረ-ሃሣብዖች ምክረ-ውሳኔዖች መሰንዘርአቸውን እና እምይቀርብኡት ምክረ-ሃሣብዖች እና ምክረ-ውሳኔዖች፡ በ ቁርጠኝዕነት እና በ ቅንዕነት፡ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊዕነት ዋስ ጠበቃ በሆነ አግባብ፡ ሲተገበርኡ ማየትን ብቻ ነው እምንፈልገው።

እናም፤ ለ አሁንኡ፡ በ የ ኮሚሽንኡ ማህደር ላይ [ዴድ ኦን አራይቫል] እምይል ብይን ከማስፈር ይልቅ፡ ረብ የአላቸው፡ ኢትዮጵያዊ [ሀገርዓዊ እና ሕዝብዓዊ] ኹነትዖችን ሁሉ በ ጥንቃቄ በማገናዘብ፡ ኮሚሽንኡን እንደ [ኤክስትሪምሊ ፐሪተርም] ጨቅላ፡ ማለትም – ከ ተገቢው የመወለጃ ቀን ቀድሞ [28-ሳምንትዐት እንኳን ሳይአስቆጥር] የተወለደ – ወደ ስራ እንድይገባ ከመፈቀዱ በፊት፡ ለየት-የአለ ማስተካከያ ድጋፍዖች ይደረጉለት ዘንድ — ኢንቴንሲቭ ኒዮናታል ኬር ዩኒት ውስጥ መቆየት እንደአለበት ጨቅላ፡ አድርገን ነው፡ እምንወስደው። የ ኮሚሽንኡ፤ ኤክስትሪምሊ ፐሪማቹርዕነት፡ በችኮላ [የ ይድረስ የይድረስ] የተፈጠረ ኤንትቲ መሆኑን እና፡ ብዙ ግልፅ ሆነው የ እምይታወቁም ሆነ፡ ለጊዜው ግልፅ ሆነው የአልታዩ፡ ለ ጎልውናው ስጋት የሆኑ ጉድለትዖች እንደአሉበት፡ ኢንስትራክቲቭሊ ጠቋሚ ነው።

ምክንያትዖቹ ግልፅ ናቸው። (ሀ) የአለንበት፤ ሁለዕንተንዓዊ ምስቅልቅል ውጥንቅጥ በሽተኛ ፖለቲካ፡ (ለ) የ ገዢው-ፓርቲ እና በተጓዳኝም፡ የሕዝብ ተወካይዖች ምክርቤትኡ፡ የችግርዖችአችን አካል ብቻ ሳይሆንኡ – የችግርዖችአችን ፈጣሪ ቀፍቃፊም መሆንአቸውን አካትቶ፡ በ ሂደትኡ ላይ፡ ሊደረጉ ይገቡ የነበርኡ የዕርምት ሃሣብዖችን በቅንዕነት በማስተናገድ ራስአቸውን ማረቅ የአልፈለጉ አምባገነንዖች የመሆንአቸው ጉዳይ እና (ሐ) ሕዝብም ሆነ ተፎካካሪ ተብዬ ፓርቲዎች፡ [በምርጫው ጊዜ የሰሩትን ስህተት ማረም ተስኖአቸው] ዛሬም ድረስ፡ ሚዛን ደፊ [አስገዳጅ] የሆነ፡ ፕሮአክቲቭሊ አስተዋፅዖ ማድረግ እምይአስችል ቁመናን መገንባት አለመቻልአቸውንም ጭምር፡ መጠቃቀስ ይቻል አለ። እናም፤ ኮሚሽንኡ፡ ራስኡን ችሎ ወደ ስራ እንድይገባ ከመለቀቁ በፊት፡ ተገቢውን የዕርምት እርምጃ በመውሰድ፡ የ አልተራዘመ ካችአፕ-ግሮውዝ እንድይአሳይ በማድረግ፡ በ ሙሉ ጉልበትኡ ፈንክሽን ሊይአደርግ ይችል ዘንድ ማብቃት — ለ ሁልአችንም ግዴታችን መሆንኡን፡ ልእንእቀበልኸው ይገባል እምይል ዕምነት ነው የ አለን። ይህ-እንን ኤክስትሪምሊ ፐሪማቹር ኮሚሽን፤ በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት መልኩ፡ በዓይነ-ቁራኛ መጠበቅ፣ መደገፍ፣ ማስተካከል፣ ማረቅ እና መንከባከብ ከአልቻልን – ኮሚሽንኡ፡ የ እኛንም ብያኔ ሳይጠብቅ፡ በራስኡ፡ ሰርቫይቭ ማድረግ ሊሳነው እምይአበቃው ደረጃ ላይ መድረሱ አይቀሬ ነው፡ ብለንም ዕንዐምን አለን።

አንድ-አንድ ነገርዖችን እንድእንጠቃቅስ ፈቃድአችሁ ይሁን።

የ ሃገርዓዊ የ ምክክር ኮሚሽንኡ አሰያየምን ተከትሎ፤ አጓጉል አራዳዕነት በ እሚመስል መልኩ – የ ኮሚሽንኡ ስራ፡ <u>ምክረ-ሃሣብ መስጠት ብቻ ነው – ውሳኔ የመስጠት ማንዴት የለውም</u> እምይለውን አባባል፡ ወደ ሕዝብ ጆሮ እንድይደርስ መደረግኡ፡ ሌላ ሳይሆን፡ ሕዝብን መናቅ እና የለየለት አምባገነንዕነት ነው ባዮች ነን። እንደ አጋዥ ሊቆጠሩ ይገባቸው የነበሩትን፤ የ ዕርቀ-ሰላም ኮሚሽንን እና የ አስተዳደር እና የ ማንዕነት ኮሚሽንን ለማፍረስ፡ ውስጥ ውስጥኡን እየተሰራ የአለው ሁሉ፡ የ አምባገንንዕነትኡን መንገድ፡ ጨርቅ እንድይአደርግላቸው፡ ለ ራስአቸው በመመኘት መሆንኡን መገመት አይከብድም።

መንግሥት-ተብዬው፤ ምክር-ሰጪ ብቻ ከሆነ የ እምይፈልገው፡ ሃገራዊ ኮሚሽን ማቋቋም ሳይኖርበት፡ የ ፖሊሲ አማካሪዎቹን፡ የ ኮሚሽንኡን ሃላፊዕነትዖች ተረከበው፡ እንድይአማክሩት ይዘዝአቸው። ዛሬ ኢትዮጵያ የአለችበት ውጥንቅጥ ፖለቲካ፤ የ ኮሚሽን ስም አወጣጥ እና አተረጓጎም ጨዋታ እየአስተናገደ፡ ትኩረቱን፡ ከ መሠረትዓዊ ችግርዖቹ ላይ እንድይነቅል ማድረግ፡ መሠሪዕነት ነው። ለ እዚያም ነው፤ ኮሚሽንኡ፡ የኢትዮጵያን መሠረትዓዊ ችግርዖች መቅረፍ ይቻል ዘንድ፡ እምይሰጥአቸውን ምክረ-ሃሣብዖችም ሆነ ምክረ-ውሳኔዖች፡ ወደ ተግባር እምይለዉጡ፡ የመንግሥት-ተብዬውን ቁርጠኞዕነት እና ተቋምዓዊ ዝግጅትዖች ሁሉ፡ ከወዲሁ ፈር ሊይዙ፡ ሊከናወኑ እና ለ ሕዝብ ይፋ ሊደረጉ ይገባል ዕምንዕለው።

ከልብ ከ አልቀሱ፤ ዕንባ አይገድም። መሻሻል ከተፈለገ፤ አሁንም ጊዜ አለ። የ ሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት፤ ከሚሽንኡን በተመለከተ የወሰደውን ሃላፊዕነት፡ ለ ነፃ-አካል አሳልፎ ይስጥ። የ ኮሚሽነርዖች ምርጫ አዋጁን ጨምሮ፤ ተስተካክሎ እንደገና ይተግበር። የ ኮሚሽንኡ አባልዐት፤ ሹመትአቸው ከፀደቀባት ናኖ-ሰከንድ ጀምሮ፡ እምይሰሯትን እየአንዳንድዋን ስራ፡ እስከ ማብቂያው ድረስ – ማለትም፡ ሂደትኡ፡ አሳታፊ፣ ግልፅ፣ ከማንአቸውም ተፅዕንዖ ነፃ በሆነ እና ሕዝብዓዊ ተዐማኝዕነትን በአስመሰከረ መልኩ፡ እንድይከናወኑ ማድረግን፡ ተቀዳሚ ግዴታቸው አድርገው ይውሰዱ። እምይካተትኡ መሠረትዓዊ ጉዳይዖቻችንን፣ ምክረ-ሃሣብዖችን እና ምክረ-ውሳኔዎችን፡ ጨምሮ ማለትአችን ነው።

እኛ፤ ከ የ ኮሚሽንኡ ራዳር ሽፋን ውጪ ሊሆንኡ፡ በፍፁም እንደማይገባ – እንድይአውም፡ ከአልተካተትኡ፡ – ግዙፍ ታሪክዓዊ ስህተት እንደእምይሆን፡ መጠቆም ዕምንፈልግአቸው አራት [መሠረትዓዊ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ] ጉዳይዖች አሉን።

(1) ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ኢትዮጵያዊ የሆንኡ፤ መሠረተ-ቢስ ተረክዖችን የማረቅ ስራን፡ ተቋምዓዊ ማድረግ እና በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተትን፡ ተተግብረው ማየት እንፈልግ አለን።

(2) ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊዕነትን አደጋ ላይ የጣሉ ተቋምዓዊ ዝቅጠትዖች ይስተካከሉ ዘንድ፤ ተቋማት መዘርጋትዓቸውን ዕውን እምያደርግ፡ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ የሽግግር መንግሥት እንድይመሰረት፣ አዲስ ስልጡን ንፁህ ኢትዮጵያዊ ህገ-መንግስት እንድይቀረፅ እና ንፁህኡ ሰንደቅ-ዓላማችን እንድይከበርልን እንጠይቅ አለን። የጎሣ-ፖለቲካ እና አከራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ እምይገደቡበትን፣ በቋንቋ በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ-በሙሉ እንዲፈርስ እምይደረግበትን እና የ ኢትዮጵያ ሕዝብዓዊ መንግሥት ምሥረታን ዕውን ማድረግን፡ በጋራ እርግጠኞች መሆን እምንችልባቸው ተቋማትን ተመስርተው ማየት እንፈልግ አለን።

(3) የ ህግ እና የ ፍትህ መዘባትዖች ፈር ይዘው፤ የኢትዮጵያን የአስተዳደር ስርዐት መሠረትዓዊ ዕምነትዖችን እና ኢትዮጵያ እንደ ሃገር፣ ከፍለሃገርዐት፣ ተቁዋምዐት እንዲሁም ዜጎች እንደየአግባቡ ስልጡን በሆነ መልኩ እምይተዳደሩበት፡ ህግዓዊ ፍትህዓዊ መአቀፍን እሚያደነግግ እምያብራራ እና ሰውዓዊ በሆነ አግባብ ተግባርዓዊ እንድይደረጉ እምይአስችል፡ የሃገሪቱን ከፍተኛ የህግ፡ የፍትህ ተቋም በንፁህ ኢትዮጵያዊዕነት እንድይዋቀር እንድይታነፅ ሲደረግ ማየት እንፈልግ አለን።

(4) የ መንግሥትዓዊ የአስተዳደር ስርዐትን በትክክል እምያንፀባርቅ እምይመራ እምይተገብር፤ ኢትዮጵያዊ ተቋም-አልባዕነት ተስተካክሎ፡ ሰው በሰውዕነቱ ብቻ እሚከበርበትን – በዜግነት ላይ ያተኮረ መርሕን እሚከተል እና የ ቡድን ጥያቄዎችን በአግባብኡ የአገናዘበ መርህእን እምይከተል፡ በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፤ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድሉን እምይአገኘ – ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት እንድይመሰረት እምያስችል ሂደትን እምይመርኡ ተቋማትን ተመስርተው ማየት እንደ እምንፈልግ፡ ዛሬም ከወዲሁ፡ ጮክ ብለን፡ ደግመን ደጋግመን ማስገንዘብ እንወድ አለን።

ኮሚሽንኡ፤ ዕነዕኛን ተፈፃሚ ይሆንኡ ዘንድ፡ ረብ የአለው ስራ መስራት እምአይችል ከሆነ — አባልዐትኡ፡ ዛሬውንኡ ሪዛይን ሊያደርጉ፡ የግድ ነው፡ ብልኻን ዕንዐምን አለን።

ስልጣኔ — ለ ስልጡን ማህበረሰብዓዊ ህይወት

ሰው ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ፤ እስከ የ ዛሬዋ ዕለት ድረስ፡ የ[ሰው] ልጅ ማህበረሰብዓዊ ህይወት፡ ሁለዕንተንዓዊ ለውጥ እየፈጠረ እየተገበረ፡ ረዥም መንገድ ተጉዟል፡ ይጓዛልም። መሻሻል መሻሻልን እየፈጠረ፤ መጠፋፋት መጠፋፋትን እየአስከተለ፡ ይፍጨረጨር እና፡ ሲወራረድ – በአማካይ፡ መሻሻልዐችን ሚዛን ደፍቶ፡ ዛሬ እንደአለን አለን። አንድ-አንድዖቻችን፤ እሳት የላሰ ስልጣኔ ውስጥ ብእንኖርእም ቅሉ፡ ሌሎችአችን ደሞ ኋላቀርዕነቱ ፀንቶብን፡ አውሬዕነትኡን የመረጥን መሆንአችን፡ የአደባባይ ምስጢር ነው። ስለ ስልጣኔ ስንአነሳ፤ ኹነትዖች – ፈርጀ-ብዙ ውስብስብ ውጥንቅጥ መሆንአቸው የተጠበቀ ኾኖ፡ የ ኤሌክትሪክ መፈጠር፡ ለ ሁለዕንተንዓዊ ህይወት መሻሻል፡ አስተዋፅዖው እጅግኡን ግዙፍ ነው። ትክክል። ስለ ስልጣኔ ሲወራ፤ በ አንድኡም ኾነ በ ሌላው መልክኡ፡ ስለ የ ኤሌክትሪክ ኃይል፡ መነሣቱ አይቀሬ ነው።

የ ኤሌክትሪክ አቅርቦት፤ የ አንድ ማህበረሰብአዊ ህይወትን፡ የ ስልጣኔ ዕርከን፡ ከፍ ዝቅ የማድረግ አቅም አለው። በ የ አለፉት ሦስት-አራት መንግሥትዐት፤ ጊዜው የፈቀደላቸውን አስተዋፅዖ የተደረገበትን፡ የ ጥቁር ዓባይ ወንዝ ግድብ፡ በ የአለፈው-ሰሞን ተመረቀ መባልኡን ሰምተናል። እሰዬው! ምንም ክፋት-የለውም። የቀሩትን 12-ተርባይንዖች አጠናቅቆ ለማስጀመር፡ ሰበባ-ሰበብ መደርደር ሳያስፈልግ፡ ተገቢው ስራ ሁሉ – በ ንፁህ ኢትዮጵያዊዕነት መንፈስ በፍጥነት እንድይከናወን፡ ማስገንዘብ ግና፡ የግድ ይላል። የ ኤሌክትሪክ ኃይል፤ ቴክኖሎጂን በመፍጠር በማስፋፋት፡ ለ ማህበረሰብዓዊ ህይወት መሻሻል መሰልጠን፡ ቀጥተኛ ሚናው ግዙፍ ነው። በ ትምህርት፣ በ ጤና፣ በ ግብርና፣ በ ኢንደስትሪ፣ በ ኮምዩኒኬሽን፣ በ ጥናት እና ምርምር፣ በ የፈጠራ ስራዎች፡ ወዘተ ወዘተርፈ – የ ኤሌክትሪክ ኃይል፡ [ሜታፎሪክሊ] የ ዕለት-ተ-ዕለት ኑሮአችንን፡ በ ፍትህዓዊዕነት ዕምንዕመራበት፡ "እስትንፋስአችን" ነው ብዕንል፡ ፈጣሪም እምይከፋብን አይመስለንም።

አለመታደል ኾኖ፤ በ ዓለም-ዙሪያ እምእንገኝ አንድ-አንድ ማህበረሰብዖች፡ የ ኤሌክትሪክ ኃይልን፡ በቂ በሆነ መጠን፡ ለ ዜጋዎችአችን ዩኒቨርስአሊ ተደራሽ ለማድረግ፡ በ መስነፍአችን — ሁለዕነተንዓዊ [ሶሻል ኢንኢኳሊቲስ] ተጭነውን፡ ለማመን በ እምይአስቸግር ኋላቀርዕነት ውስጥ ዕንድዕንዳከር – እናም ለ ሁለዕንተንዓዊ ድሃዕነት እና ለ ማህበረሰብዓዊ ፍትህ መጓደል እንድዕንጋለጥ፡ ተገድደን አለ። እኛን — ማየት ነው!

እናም፤ ዋናው ቁምነገር – የ ዓባይ ግድብ "መመረቁ" ሳይሆን፡ [ለ ቀሪው የ ከተማ ንዋሪም ቢሆን፡ በቂ ተደራሽዕነት የሌለ መሆኑ የተጠበቀ ኾኖ] ከ 70-80 ፐርሰንት እምይጠጋው የ ገጠር ንዋሪ ኢትዮጵያዊ፡ የ ኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሲሆን እና ማህበረሰብዓዊ ህይወትኡ፡ ሁለዕንተንዓዊ መሻሻልን ሲይአጣጥም፡ ማየት ነው። ያ-መሆንኡን፤ እርግጠኛ ከሆንን በኋላ ነው፡ ሻምፔይን ዕምዕንከፍተው፡ ማለትአችን ነው። አዎን፤ ራዕይአችን – ሲቪላይዜሽን/ስልጣኔ፡ ለፖለቲከኞች ገፅታ መገንቢያ ፍጆታ እንድይውል ሳይሆን — ለ ማህበረሰብዓዊ ፍትህ እና ለ ሲቪላይዝድ ለ ስልጡን ማህበረሰብዓዊ ህይወት ፍጆታ እንድይውል ሲደረግ ነው፡ እኛ ማየት እምንጠይቀው።

መዐከልዓዊ መንግሥት-ተብዬው፤ የ ዛሬ 4-ዓመት ገደማ፡ የመጀመሪያውን ካቢኔ ሲይአዋቅር፡ ወደ 50 ፐርሰንት እምይጥጋ ብዛት የአላቸው፡ ሴትዖች በመሆንአቸው፡ ፖለቲከኞችአችን፡ ተዐምር የተፈጠረ ያህል ሲይአራግብኡት እንደነበር፡ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። አራትኡን ዓመትዐት፤ ዞር ብለን ስዕንዕመለከት ግና፤ ወደ ሃያ እምይጠጉ፡ የ ዩኒቨርሲቲ ሴቶች ልጆችአችን፡ በ ኦነግ ወንበዴዎች ታፍነው፡ እስከዛሬ መዳረሻቸው የአልታወቀ መኾንኡን፣ ህወሓት እና ኦነግ እየአካሄዱት የአለው ኤትኒክ-ክሊንዚንግ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ እና ጄኖሳይድ፡ በ ሁሉም የ ዕድሜ ክልል ውስጥ የአሉ – ንፁህዐን ሴት አያትዖችአችን እናትዖችአችን፡ አክስትዖቻችን እህትዖችአችን እና፡ ሮጠው የ አልጠገቡ ሴት ህፃናት፡ የ አለዕዳቸው በ ዕብሪትኞቹ የ ህወሓት እና የ ኦነግ ወንበዴዎች፡ የ ሰቆቃ እና የ ዕልቂት ተጠቂ ሲሆኑ፣ ሲደፈሩ — አንዷት ትንፋሽ የ አልተነፈሱ [ሴትዖች] የ ካቢኔ፣ የ ፓርላማ አባልዐት እና ሌሎች ሴት ባለስልጣንዐት – የ እዚህ ኢንኮምፒተንት መንግሥት-ተብዬ፡ ሱፐርፊሽያልዕነት ዓይነትኛ መገለጫዎችኡ ናቸው። አሁንም ቢሆን፤ የ ዐባይ መገደብ ሊይአመነጨው ይችል አለ እምይባለውን የኤሌክትሪክ ኃይል፡ ለ ሽያጭ ከማሰብ እና ጉራ ከመቸርቸር የፖለቲካ ፍጆታ ይልቅ፡ በቅድሚያ — ለ ማህበረሰብዓዊ ፍትህ፣ ለ ግፉዐን ወገንዖችአችን፡ ሁለዕንተንዓዊ ህይወት መሻሻል ሊውል እንደ እምይገባ፡ አፅንዖት በመስጠት ማስገንዘብም፡ እንወድ አለን።

*ስለ ሴቶች፤ ከፍ ብለን፡ የአልነውን የአልነው – በቅርብኡ ታስቦ የዋለውን፡ የ ዓለም-አቀፍ የሴቶች ቀንን ሰበብ አድረገን፡ ትንሽ ጐንተል እንአድርጋችሁ ብለን ነው እንጂ – ሴትዖችአችን የተለየ ጥፋት እየሰሩ ነው ዕምይል ዕምነት ኖሮን እንድአልሆነ፡ መጥቀስአችንን ዕርግጠኞች መሆን ዕንፈልግ አለን። የ ጥፋት ነገር ከተነሳ፤ የ ወንድዖቹን ለመዘርዘር፡ ሰማይን ወደ ብራና፡ ውቅያኖስን ወደ የ ብዕር-ቀለም፡ መለወጥ ሊኖርብን ስለሆነም ጭምር — ለጤናችን!*

እንደ ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረትዓዊ የኅልውና ጥያቄዎች፤ ዛሬም ድረስ አልተመለሱም። ሕዝብአችንን፤ ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ ስር ያደርግ ዘንድ፤ እምይመጥን ተቋዋም እና የአስተዳደር ስርዐት መፍጠር ስለ ሰነፍን። ዛሬ ላይ ሆነን ስእንዐየው፤ የቀዳሚዎች ሁሉ ቀዳሚ፡ ጥቅል ችግርአችን – ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት የሌለን የመሆኑ ጉዳይ ነው። የ ሕዝብአችንን ሰቆቃ እና ዕልቂት፤ እንድያከትም ማስገደድ ተስኖን፣ በ የውስጥ አፍራሽ ኃይሎች፡ ለ ሃገር መፍረስ አደጋ ተጋልጠን፣ በ ጐረቤት ሃገርም ዳር-ድንበርአችን ተደፍሮ፡ ተዋርደን፣ ፓለቲካችንን ፈር ማስያዝ እና ከ አክራሪው የ ጎሣ-ፖለቲካ ጋር የገጠምነውን ፍልሚያ — በ ኢትዮጵያ አሸናፊዕነት ለመቋጨት፡ እምይመጥን ትግል ማካሄድን፡ አልኸመድፈርአችን ሁሉ፡ ጥቅል ችግርአችን ውስጥ፡ በ ዋና-ዋናዕነት ሊይካተትኡ እምይገባቸው ናቸው።

እስቲ አስቡት ጎበዝ — በ ፕላኔት ምድር ላይ፤ በ እዚህ፡ በ 21ኛው ክፍለ-ዘመን፡ ፀረ-ሃገር ህገ-መንግሥት ቀርፆ፣ የጎሣ-ፖለቲካን እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶችን ለማንሠራፋት ህግዓዊ መደላድል ፈጥሮ፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተ የአስተዳደር ግርግሞችን መስርቶ፣ በ ፌደራሊዝም ስም እየአጭበረበረ፡ ሃገሬ አይደለችም እምይልዐትን ሃገር እየመራ የአለ መንግሥት-ተብዬ፡ እምይገኝባት ሃገር፡ ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ይ-ህ፤ 31-ዓመትዐትን የአስቆጠረ ዕውነታ ነው እንግዲህ። የ ዛሬ 4-ዓመት ገደማ፡ የተገላገልነው የመሠለን፡ ካንሰረስ የፖለቲካ ስርዐት፡ የመሪዕነትኡን ቁልፍ፡ እንደአዲስ ከ የ ተረከቡት ፍጡራን – የትግሬዎች ተወካይ ነን ከ እምይሉ ወደ የ ኦሮሞዎች ተወካይ ነን እምይሉ፡ በሽተኛ ፖለቲከኞች ከመቀየሩ ሌላ፡ የ ሃገር እና የ ሕዝብ ችግሮች ኤክስፖኔንሽሊ ገዝፈው፡ እንደ ሃገር እና እንደ አንድ ጥንትዓዊ ህብር ማህበረሰብ፡ ዛሬም፡ የኅልውና አደጋ ውስጥ ተዘፍቀን እንገኝ አለን። የመዐከልዓዊ-መንግሥትዕነትኡ ቦታ ላይ የ አለው አካል፤ የለየለት ወረራ፣ የ እርስ-በ-እርስ ጦርዕነት፣ ኤትኒክ-ክሊንዚንግ፣ ኤትኖ-ሪሊጆስ ክሊንዚንግ፣ ጄኖሳይድ፣ ሃገርን የማፍረስ እና የኦሮሙማን ዓይን-የአወጣ የመንሰራፋት እና ኢትዮጵያን የማፍረስ — የተቀናጀ ዘመቻ፡ እየአካሄደ የአለ አካል ነው።

ትክክል። ዛሬ የመንግሥትዕነት ቦታውን የያዘው ገዥው-ፓርቲ፤ ኢትዮጵያዊ-ታሪክዖቻችንን እና ኢትዮጵያዊ-ቅርስዖቻችንን ደብዛ ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ፣ ሰንደቅ-ዓላማችንን እምይፀየፍ፣ ኦሮሙማን ማንሠራፋትን ግብኡ አድርጐ እምይንቀሳቀስ፡ ከሃዲ ወራሪ ቡድን ነው። በ ቅርብኡ (ሀ) ሕዝብ በ ርሃብ እየተጠቃ ነው፡ ተብሎ ሲነገረው – ለምን ቅዳሜ እና ዕሁድ ወጣ እየአለ፡ ቁርጥ አይበላም እምይል፡ (ለ) አንድ ሳምንት ሳይቆይ ደሞ፡ የንሮ ውድዕነት ሕዝብን እየአማረረ ነው ተብሎ ሲነገረው – የሆነ ቅጠል እየአሳየ፡ በውሃ ብቻ ቀቅላችሁ ብሉ እምይል፡ (ሐ) ኢትዮጵያን እምይሉ ጋዜጠኞችን እየአሳደደ እምይአስር፣ ለምን የ አድዋ-ድልን በተገቢው ክብር ዘከራችሁ፣ ለምን የ ኢትዮጵያችንን ሰንደቅ-ዓላማ በክብር አነገባችሁ አውለበላባችሁ፣ ለምን የ ካራማራን-ድል ዘከራችሁ በ እምይል፡ ኢትዮጵያዊያንን እየአሳደደ እምይአስር እምይገድል፡ (መ) ህወሓትን እና ኦነግን አዝሎ እሹሩሩ እየአለ፡ [ነፍሱን እና ስልጣንኡን የታደገለትን]፡ ሃገሬን ሕዝቤን አላስደፍርም እየአለ በመዋደቅ ላይ የአለውን [ፋኖ] ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳውን፡

አሳፋሪ፡ መንግሥት-ተብዬ ወራሪ ኃይል፡ ሕዝብ ቆሞ ሊመለከተው አይገባም። በፍፁም!

ዛሬም ቢሆን፤ መፍትሄው ግልፅ ነው። በስልጣን ላይ የአለው፤ መዐከልዓዊ መንግሥት-ተብዬው፡ ወራሪው የ ኦዴፓ-ኦነግ መርአሹ ኢህአዴግ – በጥንቃቄ እና ሃላፊዕነት በተሞላበት አግባብ፡ የ ሕዝብን ስልጣን፡ ለ ሕዝብ እንድይአስረከብ ሊገደድ የግድ ነው። አንድ ነገር ዕሙን ነው። እምይመጥን ትግል አድርገን፤ የሕዝብ ስልጣን በሕዝብ ቁጥጥር ስር እንድይውል ማድረግአችንን በጋራ እርግጠኞች መሆን እስከአልቻልን ድረስ፡ እንደ ሃገር'ም እንደ ሕዝብ'ም፡ ከ የገባንበት አደጋ ማምለጥ አንችልም። ደጋግመን እንደዕምንዕለው፤ ከ ወፍ-ዘራሽ ትግል ርቀን፡ ፈርጠም የአለ፡ መሬት የያዘ፡ አታጋይ ድርጅት አመቻችተን፡ ሃገርን እና ሕዝብን ለመታደግ፡ በቁርጠኛዕነት መታገል፡ የግድ ነው።

ከ የቅርብኡ ሃገርዓዊ ምርጫ ልእንማር እምይገባን ቁምነገርዖች አሉ። በተናጠል እምይደረጉ ጥረትዖች፡ ስኬትዐማ ሊይአደርጉን እምይችሉበት ፕሮባቢሊቲ፡ [ዚሮ] መሆኑ፡ አንዱ እና ዋነኛው ትምህርት ነው። ለ ሃገር እና ለ ሕዝብ ሲባል፤ የ እየግል ኢጎ'አችሁን ዋጥ አድርጋችሁ፡ ፈርጠም የአለ፡ አታጋይ ተቋም ፍጠሩ። በተለይ፤ ምርጫ በመጣ ቁጥር፡ ያዙን-ልቀቁን እምትሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፡ እየታየ የአለውን ሕዝብዓዊ ንቅናቄ ተቀላቀሉ፣ ለአምባገነኑ መንግሥት እንድአታመቹ ሆንአችሁ፡ ሕዝብዓዊ ንቅናቄውን፡ በጋራ አቀጣጥሉ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

አዳራሽ

– እንደገና እሰከ እምንእገንአኝ –

# የ ቃልዐት አበሣ

ሚያዝያ ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ‖ ኤፕሪል 2022

**ትኩረትአችን** — *የዛሬው መጣጥፍዐችን ርዕስ፤ አንድ-አንድ ቃልዐት ላይ በማተኮር፡ የኾነ-ነገር ማለት እንደፈለግን፡ ሹክ እያለ መሆኑ፡ ግልፅ ነው። ትክክል። በቅድሚያ፤ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ – መጀመሪያ፤ የ "ተማሪዎች ንቅናቄ"ን በተመለከተ፡ አልፎ-አልፎ እየደረሰበት የአለውን የጅምላ-ፍረጃ ሰበብ አድርገን፡ ትንሽ ዕምንዕለውን እንዕልአለን፣ የሃገርዐችን ሰሞነኛ ፖሊቲካ-ነክ ኹነትዖችን በተመለከተም፡ በእዚህ በ የአሳለፍነው ወር፡ ምርጫ-ቦርድ የአስተላለፈውን መመሪያ ተመርኩዘው፡ የተወሰኑ የፖሊቲካ ድርጅቶች፡ ጉባኤአቸውን ማከአሄድአቸውን በተመለከተ፡ ትኩረትአችንን በሳብኡ፡ ሁለት-ሦስት ድርጅቶች ላይ፡ በየፈርጅዐቸው፡ ክሪቲካል አተያይዐችንን እንአከአፍልዐችሁ አለን – በመቀጠልም፡ [ፅንፍ፣ ብሄር፡ ሲሉ — ፅንፍ፣ ብሄር፡ ስንል] በእምይል ንዑስ-ርዕስ ስር፡ በ ቃልዐትዑ ዙሪያ በማውጠንጠን፡ የአጠቃቀም ግድፈትዖችን በተመለከተ ዕምንዕለውን ዕንዕል አለን። በመጨረሻም፤ ለ ማጠቃለል ያህል፡ የ ኢትዮጵያ መሠረትዓዊ ጥቅል ፖሊቲካዊ ችግርዐችን፡ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት'ም ሆነ ኢትዮጵያዊ የሆነ ህገ-መንግሥት የሌለን መሆንኡን፡ መፍትሄውም፡ ሕዝብዐችንን ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ በቁጥጥሩ ስር ያደርግ ዘንድ፡ በቆራጥዕነት መታገል ብቻ መሆንኡን ጠቁመን – እኛ የ ዕምዕንፈልገው — የሽግግር መንግሥት እንድይመሠረት፣ የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቆጠራ እና ተከትሎ መደረግ የአለበት ምርጫ፡ ፍትህዓዊ እና ነፃ በሆነ አግባብ ተግባርዓዊ እንድይሆን፣ ኢትዮጵያዊያንን በሙሉ [ሁልዐችንንም] በአግባብኡ ያሳተፈ፡ አዲስ ስልጡን ህገመንግሥት እንድይቀረፅ፣ የጎሣ-ፖሊቲካ እና አክራሪ የጎሣ-ድርጅቶች በህግ እንድይገደብኡ፣ በቋንቋ እና በጎጥ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ እና በምትኩም፡ ሕዝብ እሚመርጠውን የአስተዳደር ስርዐት እንዲዘረጋ እምይአስችል ድልዳል እንድይአካተት፣ ሰው በሰውዕነትኡ ብቻ እምይከበርበትን፣ በ ዜጋዕነት ላይ የአተኮረ እና የ ቡድን ጥያቄዎችን በ አግባብኡ የአገናዘበ መርህን እምይከተል፡ በ ፍትህዓዊ እና ነፃ ምርጫ፡ ሃገርን የመጠበቅ እና ሕዝብን የማገልገል ዕድልኡን እምይአገኝ፡ ኢትዮጵያዊ ሕዝብዓዊ መንግሥት የመመሥረት ራዕይዐችን፡ ዕውን ኾኖ ማየት እንደኾነ — መጥቀስ እንደፈለግን፡ ጠቆም አድርገን፡ እንአበቃ አለን። መልካም ንባብ።*

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች – እንዴት ናችሁ?!

["ዕንቅልፍ ነስቶናል"፤] እምይለው ሃረግ — ክሊሼ እየሆነ መምጣቱ፡ ዕውነት መሆኑን፡ ተገንዝበናል። የህይወት ፈታኝዕነት፤ በእኛ የተጀመረ፡ በእኛ እምይአበቃ ባይሆንም ቅሉ፡ የ እኛ ፈተናዎች ግና፡ ከልክ የአለፉ፡ ለሰሚው ለተመልካቹ ማመን እምያስቸግሩ – ዕንቅልፍ እምይነሱ ፈተናዎች በመሆንአቸው፡ ሕዝብዐችን፡ ፍፁምዓዊ የመንግሥት ስልጣን የበላይ ባለቤትዕነቱን ቁልፍ፡ በቁጥጥሩ ስር እስክይአደርግ ድረስ፡ ቀበቶን/መቀነትን ጠበቅ አድርገን፡ በጋራ እየታገልን ለመቀጠል፡ በድጋሜ ቃል እንገባለን። ዛሬም እንግዲህ፤ ኢትዮጵያችንን በተመለከተ፡ በ ይአገባናል ባይዕነት መንፈስ፡ የጫጫርንዐትን መጣጥፍ ይዘን፡ በአክብሮት ከፊትአችሁ ቀርበን አለ።

እናም፤ [አብረን እንቆይ] – የ ምንጊዜም ግብዣችን ነው።

በ 1960ዎቹ የተደረገዉን "የተማሪዎች ንቅናቄ" በተመለከተ፤ ጐላ-ጐላ ያሉ [የጅምላ-ፍረጃ ፉት-ፕሪንት] የአላቸው ሃሣብዖች፡ አልፎ-አልፎም ቢሆን፡ ሲንፀባረቁ አስተዉለናል። የፍረጃ ሃሣብዖቹ፤ ለ 31-ዓመትዐት፡ የ ኢትዮጵያን እና የ ኢትዮጵያዊዕነትን ኅልዉና፡ አደጋ ዉስጥ ለዘፈቀዉ፡ ዕኩዩ አክራሪዉ የጎሣ-ፖለቲካ – "የተማሪዎች ንቅናቄ"ን ተጠያቂ የማድረግ አዝማምያ ይታይባቸዋል። ሞቅ ያለ ውዝግብ ሲፈጥር እምዕንመለከተው ጉዳይም፤ በ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለአሉት "ናሽናሊቲስ" በጊዜው ተነስቶ ለነበረው ጥያቄ፡ የ መፍትሄ-ሃሣብ ይሆን ዘንድ ለውይይት በቀረበች፡ አንዲት አርቲክል ዙሪያ ያውጠነጥናል። በ የቀረበችው አርቲክል ውስጥ የተንፀባረቁት ሃሣብዖች፤ ሃገር-ቤት በነበረው የተማሪዎች ንቅናቄ አማካይዕነት ይሰራጩ እንጂ፡ ባህር-ማዶ የነበሩት የትግሉ አካልዐት፡ ቀደም ብለው የተወያዩባቸው ጉዳይዖች እንደሆኑ እምይጠቁሙ መጣጥፎች አሉ።

በ-60ዎቹ ስለነበረው ፖሊቲካ ስንአነሳ፤ የ ሃሣብአችንን ምህዳር፡ እንደ ጋሪ-ፈረስ [ከ 1960 እስከ 1969] ብቻ ውሱን ስንአደርገው ይስተዋላል። ይህ ስህተት ነው። በ-60ዎቹ የነበረው ፖሊቲካ፤ ከ 1960 በፊት ጀምሮ ሲንከባለሉ የመጡ የ ህብር-ማህበረሰብዐችን ጥያቄዎችን ጭምር ያካትታል። ከ 1969 በኋላም በአለው ፖለቲካ ውስጥ፡ አሻራውም ኾነ ፍሬዎቹ መንፀባረቃቸውም የግድ ነው። ዕውነት ለመናገር ከኾነ፤ ከ እነእዚህ ጊዜዐት ውስጥ፡ "የተማሪዎች ንቅናቄ" ሚዛን-ደፊ ኾኖ፡ <u>ለብቻው</u> ጐላ ብሎ ይታይ የነበረው – ለተወሰኑ፡ ምን አልባትም፡ ለ ሦስት-አራት ዓመትዐት ብቻ ነው። የ-60ዎቹ እየአሉ ጅምላ-ፍረጃ ለመስጠት፡ ለራስዐቸዉ መብት እምይሰጡ ፍጡራን፡ እነእኛን ሦስት-አራት ዓመትዐት ነው፡ አሾልቀው ማየት እምይመርጡት።

በ-60ዎቹ የነበረው ፖሊቲካ፤ የተፀነሰዉ፡ ከ "የተማሪዎች ንቅናቄ" በፊት ነበር። በኤርትራ፣ በባሌ፣ በጎጃም፡ የነበሩትን እንቅስቃሴዎች ማየት ነው። ከ 1964 እስከ 1969 ዓ.ም. የነበረው የ-60ዎቹ እምይባለው ፖሊቲካም፤ አንድ-ሁለት ዘመንዓዊ የፖለቲካ ድርጅቶች እየተፈጠሩ መጥተው፡ እንደ እየገጠመኙ፡ በ እየጐራው አክቲቭሊ ተካፋይ የነበረው ትውልድ – በ ኢትዮጵያ ውስጥ የአለው የህብር-ማህበረሰብዑ ነፀብራቅ ነበር። የ [ተማሪው ወታደሩ ላብ-አደሩ አርሶ-አደሩ ምሁርዑ ሴትዋ ወንዱ ወጣት-ጐልማሳው አረጋዊያን ዐማራው ትግሬው ኦሮሞው ጉራጌው ሶማሌው፡ ወዘተ ወዘተርፈ፡ አንድ-ላይ] ነበር እንጂ፡ የ ወቅቱ "ተማሪዎች" ብቻ እንደነበሩ አድርጎ መቁጠር፡ ዕውነትዐን አያመለክትም።

